

የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን

ይህ ኒሻን ከፊት ለፊቱ የሚቀጥለው ፅሁፍ አለበት

"የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ አግዚአብሔርን መፍራት ነው"

በጀርባው

"ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ"



ደጃዝማች ካሳ ሀይሉ

"በስመ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሀዱ አምላክ፡
የአግዚአብሔር ፍጥረት፡ ባርያው ቴዎድሮስ..."

ከአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ መግቢያ

ሀገራቸውንና ህዝብን በቅንነት ለማገልገል ለተሰለፉና ላለፉ ዜጎች
መታሰቢያ

መቅደላ

የቴዎድሮስ ዕጣ

ኩማሲና መቅደላ
በሔንሪ ሞርተን ስታንሊ

የመቅደላ ትርጉም
ዶ/ር ገበየሁ ተፈሪ

መቅደላ! የቴዎድሮስ ዕጣ

በእንግሊዝኛ "ኮማሲና መቅደላ፣ ሁለት የእንግሊዞች ዘመቻዎች በአፍሪቃ" ተብሎ በአሜሪካዊው የኒውዮርክ ሔራልድ ጋዜጠኛ በሄንሪ ሞርተን ስታንሊ አአአ 1874 ከፃፈው መፅሐፍ የተተረጎመ::

Coomassie and Magdala
The Story of Two British Campaigns in Africa (1874)
Henry Morton Stanley
Translation of the Magdala part

ከመፅሐፉ፣ የሁለተኛው ክፍል፣ የመቅደላ ትርጉም
የመጀመሪያ ህትመት (2010)
First edition 2017

የግርጌ ማስታወሻዎችና ተጨማሪ ምስሎች በገበየሁ ተፈሪ
የሽፋን ዲዛይን በገበየሁ ተፈሪ

የተርጓሚው ቀደምት ሥራ
የተደበቀው ማስታወሻ
በገበየሁ ተፈሪና ደሳለኝ አለሙ

ሙሉ መብት የተጠበቀ፣ ያለ ፈቃድ ማባዛትም ሆነ ማሳተም ወይም በተለያዩ መገናኛዎች መፅሐፉን ማካፈል ሆነ መተረክ ከልክል ነው::
ገበየሁ ተፈሪ

Copy right © 2017 by Gebeyehu Teferi
All rights reserved including the right to reproduce this book or portions thereof in any form whatsoever

ISBN 9780692922033

Printed in the USA
Signature Book Printing. www.sbpbooks.com



ይህን ሥራ አንድሠራ ላበረታቱኝ በሙሉ ከልብ ምስጋና አቀርባለሁ።

ተጨማሪ ፎቶዎችን ወይም ምስሎችን በአሜሪካ ላይብረሪ አፍ ኮንግሬስ የሥራ ቦታቸው በማዘጋጀት ለረዱኝ ለላይብራሪ አፍ ኮንግሬስ ባልደረባ ለአቶ ፋንታሁን ጥሩነህ ጥልቅ ምስጋና አቀርባለሁ።

ርዕስ ማውጫ

መግቢያ i

ምዕራፍ አንድ 1

የአንግሊዞች ካምፕ፣በአለም ምርጥ ሰው፣ ለትልቅ ስው የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ መግቢያ

የምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች 33

ምዕራፍ ሁለት 57

አነስሊ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርቄዘር

የምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች 79

ምዕራፍ ሶስት 81

አስገራሚ የማታ ጉዞ፣ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ የተወላጆች ዲስኩር

ምዕራፍ አራት 86

የአለት አምባ፣ እንግዳ የሆነ ተፈጥሮ፣ ስመልፈንገስ በፎቃዳ፣ የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያንና የቀብር ስነ ሥርአት

ምዕራፍ አምስት 104

የናፒየር አዋጅ፣ ዲፕሎማሲ፣ ሜጀር ግራንት፣ የናፒየርና የመስፍኑ ካሳ ግንኙነት፣ የወዳጅነት ዕይታዎች

የምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች 119

ምዕራፍ ስድስት 122

አንጣሎ - የገበያ አይነት

ምዕራፍ ሰባት 149

ስመልፈንገስና እኔ ተለያዬን፣ የእንግሊዝ ጋዜጦች፣ ሃላፊነት የጎደለው ትንበያቸው፣ የእንግሊዝና ህንድ ሠራዊት መከፋት፣ የተከፉት ቴዎድሮስ፣ አሳዛኝ ምርኮኞች፣ የፖለቲካ መረጃ ሥራዎች፣ የስር ሮበርት አመራርና የዲፕሎማሲ ችሎታ፣ ስለ እንቅስቃሴው ማዝግም ማብራሪያ፣ የአሰያ ዝሆኖች በአቢሲኒያ፣ የማጓጓጉው መስመር

የምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች 174

ምዕራፍ ስምንት 178

የአቢሲኒያ ዕይታዎች፣ በተራሮች የታቀፈው የአሸንጌ ሀይቅ፣ የአልኮል መጠጣችን እንዲቀር መደረጉ

ምዕራፍ ዘጠኝ 209

የፖለቲካ መረጃ ሥራ፣ መቅደላ - የድራማው የፍፃሜ ትዕይንት፣ ቴዎድሮስ ተኩስ ከፈቱ፣ የአቢሲኒያኖች ማጥቃት፣ የኮሎኔል ፔን የመጨረሻ ስላምታ፣ ጅቦች ተኩላዎችና ሥራቸው

ምዕራፍ አስር 239

በውጊያው የተጎዱ ሰዎች፣ ጥሩ የለበሰ ምርኮኛ፣ የቴዎድሮስ ተስፋ መቁረጥ፣ ራሳም፣ ያልተጠበቀው እስረኞችን መቀበል፣ የመጨረሻው የእጅ ስጥ ጥሪ

የምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች 254

ምዕራፍ አስራ አንድ 256

ሰፍፃሜው ዝግጅት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ 30ሺ ተፋላሚዎች፣ ከባድ መሳሪያ ድብደባ፣ መቅደላ መግቢያ በር ላይ፣ መቅደላ ላይ የንጉስ ነገሥቱ ራሳቸውን ማጥፋት

የምዕራፍ 11 ማስታወሻዎች 277

ምዕራፍ አስራ ሁለት 278

የንጉስ ነገሥቱ ቤት ዘረፋ፣ ጥቁር ኮት ለባሾች፣ ሟቹ ገዥ

የምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች 290

ምዕራፍ አስራ ሶስት 295

የቴዎድሮስ ቀብር፣ ባላንጣ ንግሥቶች፣ የመቅደላ ስንብት፣ የጀኔራል ናፒየር ትዛዝ፣ የተዘረፉ ዕቃዎች ጨረታ፣ ኦፊሻል ሪፖርት

የምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች 318

ምዕራፍ አስራ አራት 320

ወደ መጣንበት - ወደ ተከዜ ጉዞ፣ የሉተናንት ሞርጋን ሞትና ቀብር፣ የቄሶች የምስጋና ቅዳሴ፣ ከመቅደላ ስደተኞች ጋር መለያየት፣ የንግሥት ቪክቶርያ ለክሩሴዱ ጦር እንኳን ደስ ያላችሁ መልክት፣ የእቴጌዋ ሞትና ቀብር፣ ልዑል አለማየሁ፣ የካሳ ሽልማትና ከናፒየር ጋር ስንብት፣ በሶሮ ማለፊያ ትልቅ ጎርፍ

የምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች 345

ዋቢ መፃሕፍት 347

መቅደላ! 348

መዝጊያ 349

የምሥል ማውጫ

የዙላ ወደብ ዕይታ 2
የዙላ ካምፕ በከፊል 3
የጥንታዊው የአዱሊስ ከተማ ፈርስራሽ በዙላ አጠገብ 5
የአርምስተሮንግ መድፎች ሲጫኑ 9
የተራራ ከባድ መሳሪያዎች ሲጫኑ 9
ሎርድ ጆን ራስል 19
ባሻ ፈለቀ ከናፒየር ጋር(በቀኝ በኩል በጥግ የሚታየው ግዙፍ ስው) 25
የአውሮፓ አስረኞች 25
ሆርሙዝ ራሳም 26
ፀሀፊው ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ 32
በዙላ የውሀ ማጠጫ ገንዳዎች 60
ኮሎኔል መርዌዘር 62
የባቡር ሀዲድ በቁማይሌ 66
ውሀ ማጠጫ በቁማይሌ 67
የሶሮ ማለፊያ (የዲያብሎስ ደረጃ) 72
በቁማይሌ ማለፊያ ፣ አንደል ዌልስ 74
ጉና ጉና በማይ ሙና ሸለቆ 83
በማይ ዋሂዝና በአዳ አባጋ መካከል የሚገኝ ግምብ ቤት 93
የአንግሊዞች ካምፕ በአዲግራት 95
የደጃዝማች ካሳ መልክተኛና ተከታዮች 107
የአንግሊዞች ካምፕ በአድ አባጋ 109
የደጃች ካሳና የሮበርት ናፒየር ግንኙነት 111
ደጃዝማች ካሳ ምርጫ 113
ሌፍተናንት ጀኔራል ሮበርት ናፒየር 115
ደጃች ካሳ የሮኬቶች ተኩስ ልምምድ ሲመለከቱ 118
የአንጣሎ ገበያ 124
በአንጣሎ የሚገኝ መንደር 125
የበሎቺዎች ሬጅመንት 133
ማርያ ተሪዛ፣ (ማር ተሪዛ)ጠገራ ብር 141
የእስረኞቹ ጎጆዎች በመቅደላ 155
የእስረኞቹ መኖሪያ በመቅደላ (ካርታ) ራሳም፤ 155
ሴባስቶፖል ወደ መቅደላ ሲጎተት! 159
ሚር አከበር አሊ 162

የአፃሎ ካምፕ 167
አምባላጌ (የወልደየሱስ አምባ) 169
የአቢሲኒያ መልከተኞች በእንግሊዞች ካምፕ 173
በአሸንጌ ሀይቅ አጠገብ ጉዞ 180
የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች በተከዜ ሸለቆ ሲጓዙ 189
ሜጀር ጀኔራል ቻርለስ ስታሽለ 198
ካፒቴን ሰፒዲ (ባሻ ፈለቀ) 200
የከባድ መሳሪያ ጉዞ መስመር 207
ወደ መቅደላ የሚወስድው መንገድ 211
ከደላንታ አፋፍ፣ የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ 212
ፑንጃቦቹ ላንጃ ወድረው አቢሲኒያውያንን ሲያጠቁ 231
የእንግሊዞች ሮኬት ተኳሾች ብርጌድ 234
የአሮጌ ውጊያ 236
የተለቀቁት አስረኞች ከቤተሰብና ሠራተኞቻቸው ጋር 251
የአፄ ቴዎድሮስ ቀሪ ሠራዊት ከመቅደላ ሲወጣ 260
የእንግሊዝ ጦር እንቅስቃሴ ወደ መቅደላ 261
የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ጥሶ ሲገባ 270
የአፄ ቴዎድሮስ ፍፃሜ 272
ኮኪት በር በእንግሊዝ ወታደሮች ሲጠበቅ 274
ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር 280
የአፄ ቴዎድሮስ ማህተም 283
በመቅደላ የንጉሥ ቤት ዕይታ 284
የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ 285
ከወርቅ የተሠራው የአቡኑ ዘውድ 285
የአፄ ቴዎድሮስ መስቀል 294
ንግሥት መስታውት ከልጇ ጋር 298
የመቅደላ ቃጠሎ 300
ቁሶች ለሮበርት ናፒየር ሲያሸበሽቡ 323
የአቴጌ ጥሩ ወርቅ የቀብር ሥነ ሥርአት 329
ወላጅ አልባ የቀረው ልዑል አለማየሁ 330
የንግሥቷን ልደት በማክበር በሰናፌ የተደረገ ሠልፍ 333

መግቢያ

ስለ አፄ ቴዎድሮስ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ፀሀፊዎች ሥራዎች ታትመው የቀረቡ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ሥራ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው፣ የአፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዎቹ ቀናትና ሰአታት አንዴት አንደነበሩ በዝርዝር ስለሚያቀርብ ነው። ፀሐፊው ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ፣ የአሜሪካው የኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጣ ዘጋቢ ነበር። ከእንግሊዝ ጦር ጋር ከዙላ ተነስቶ መቅደላ ድረስ በመጓዝ ያየውንና የሰማውን በዝርዝር ዘግቧል። አንባቢያን እንደሚረዱት፣ በመቅደላ የእንግሊዞች ዘመቻና በተያያዙ ነገሮች ብዙ የምናውቃቸውን ድርጊቶች በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን፣ ሌሎችም በብዛት የማይታወቁ ሁኔታዎችን ዘግቧል። በሰውዬው ፅሁፍ ላይ መተኮር የሚገባው ራሱ በአካል ተገኝቶ ያየውንና የሰማውን የዘገበውን ከፍል ነው። ስለ አፄ ቴዎድሮስ የሚያትተው የሰውየው ፅሁፍ፣ ምናልባትም ከሚታወቀው ትንሽ ስየት ያለ ቢመስልም የሰውየን ፅሁፍ አንዳለ አስቀምጫለሁ። ሆኖም ፀሐፊው ስለ ካሳ ወይም አፄ ቴዎድሮስ በመጠኑም ቢሆን የፃፉቸው አረፍተ ነገሮችንም ሆነ አንቀፆችን የበለጠ ማብራሪያና ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶዋስሁ።

ይህ መፅሐፍ መኖሩን ያወቅሁት፣ ከዚህ ቀደም፣ "የተደበቀው ማስታወሻ" በሚል ርዕስ ለአንባቢ የቀረበ የትርጉም ሥራ በምሠራበት ጊዜ ነበር። ያም በ2007 አ.ም ነበር። በኢጋጣሚ ነበር። ከዚህ በፊት እንዳደረግሁት ሁሉ፣ መተርጎም ብቻ ሳይሆን፣ ፀሐፊው ያተታቸው ከስተቶችን ለማመሳከር ሌሎች አያሌ መፅሐፍትን ማገላበጥ ነበረብኝ። ፀሐፊው፣ ጋዜጠኛም እንደመሆኑ፣ በተጨማሪም አሜሪካዊ በመሆኑ፣ ከእንግሊዞቹ ፀሐፊዎች ተለይቶ ወገናዊነት የጎደለው ይሆናል የሚል ተስፋም ነበረኝ፤ እናም፣ ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር፣ በርግጥም ሚዛናዊ ስመሆን ሞከሯል። ከሁሉም በላይ ግን፣ በቦታው የነበረ የአይን ምስክር በመሆኑ፣ ታሪኩን የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርገዋል።

ከዚህ ቀደም በርከት ያሉ ፀሀፊዎች ስለ አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ያካፈሉ ስለሆነ ታሪኩን ለመድገም ሳይሆን፣ አንባቢያን፣ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ስለ ንጉሡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ስለ አፄ ቴዎድሮስ የሚታወቁና የማይታወቁ ተጨማሪ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻዎች አካፍያለሁ። በዚህ ሥራ ብዙ ፅሁፎችን በመመልከት፣ በተለይም ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በቅርብ፣ በአካልም ያዩዋቸውና የተመሰከቷቸው ያነጋገሯቸውን ፀሀፊዎችን ሥራዎች

በመመርመር ስለ ንጉሡ ምኞት፣ ባሕሪ፣ ቁመናና ሌሎችም ሁኔታዎች ለእንባቢያን አቅርቤያለሁ።

ለግርጌ ማስታወሻዎች ዋቢ የሆኑ ሥራዎችን በየማስታወሻው መግለፁ በጣም ተደራራቢ ስለሆነ፣ ሁሉም በመፅሐፉ መጨረሻ ገፅ በዝርዝር ተቀምጠዋል። በእንግሊዝኛው ፅሁፍ የተጠቀመጡትን ቀናት እንዳሰ በመጠበቅ፣ ካልተጠቀሰ በስተቀር ቀናቶች በሙሉ አንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው። በተጨማሪም፣ የግርጌ ማስታወሻዎች ሰፋ ያሉና ብዛትም ያሳቸው ሰሰሆኑ፣ በየገፁ ከማስቀመጥ ይልቅ በየምዕራፎች መጨረሻ ጠቅለል አድርጎ ማቅረቡ ለንባብ ይረዳል በሚል ግምት በዚህ መልከ ተቀምጠዋል።

በትርጉም ሥራው፣ ፀሐፈው፣ ጥንታዊ የሆኑ የእንግሊዝኛ ቃላትና ምሳሌዎችን ስለተጠቀመ፣ አሰቸጋሪና አድካሚ፣ ጊዜም የሚወሰድ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ብርታት የሠጠኝ ነገር ቢኖር፣ ይህንን ታሪክ ለሌሎች አንባብያን ማቅረብ የዜግነት ግዴታ አድርጌ ስለወሰድኩ ነበር። ሌላው አምነቴ ደግሞ፣ ዛሬን የምንተረጉመው ትናንትናን ተመርኩዘን ከሆነ፤ ትናንትና ምን እንደነበር፣ ከፉውም ደጉም ሙሉ በሙሉ መገሰፅ አሰበት የሚል አምነት ሰላለኝ ነው። ፀሀፈዎች፣ ምናልባትም በበጎ መንፈስ፣ አንዳንዱን ታሪክ ሰህዝብ ባይነገር ይሻላል በሚል አመለካከት ነጥሰው ሊተዉት ይችላሉ። በኔ እሰተያየት ግን፣ ህዝቡ ራሱ በየዘመኑ ብዙ ፈተናዎችን ያየና ራሱም ምሰከር ስለሆነ፣ ያለፈ ታሪከን በትክክል ማወቁ ይጠቅመዋል አንጂ አይጎዳውም። የነገሮችን አመጣጥ በመግንዘብ ከታሪከ መጥፎው እንዳይደገም ይጥራል ባይ ነኝ። ታሪከ ሙሉ በሙሉ ካልተነገረ፣ በሚፈጠረው ከፍተት በአብዛኛው በጎ ላልሆኑ ሀሳቦች መንደርደሪያ ሊሆን ስሰሚችል፣ በተቻለ መጠን፣ የሆነው፣ የተደረገው ሁሉ አንዳለ ይቅረብ በሚል መንፈስ፣ አነሆ ይህንን ፅሁፍ ለአንባብያን ለማቅረብ በመቻሌ ሰፈጣሪ ምሥጋና አቀርባለሁ።

ይህንንም ሳቀርብ ታሪኩ ሊጎረብጣቸው የሚችሉ ሰዎች ይኖሩ ይሆን ብዬ ማሰቤን አልከድም። ነገር ግን መልሼ ደግሞ፣ ሰምንሰ ይሆን ሰዎች በታሪከ ቅር ሊሰኙ የሚችሉት በማለት ራሴን መልሼ ጠየቅሁ። ለአንባቢም ተመሳሳይ ጥያቄ ለማቅረብ አወዳሰሁ። ያለፈውን ወደኋላ ተመልሶ መሚገት ለምንሰ ይበጃል? ካለፈው ሰመማር ካልሆነ በስተቀር፤ በተለይም አሁን ሌላ ታሪከ መሥራት በሚቻልበት ወቅት። ሰዎች አዲሰ ታሪከ መሥራት ከፈለጉ ደግሞ ወደኋላ ሄደው አንደዚህ ሰሰነበረ ነው ማሰት አያሰፈልጋቸውም። ወደኋላ ከተመለሱ ግን፣ ከታሪከ፣ ከመህል ምዕራፍ ብቻ ተነስተውም መሆን የሰበትም። በተጨማሪም፣ በዚያን ጊዜ ለተፈፀመው ድርጊት፣ በጊዜው ወይም በዘመኑ ከነበረው ሁኔታ ጋር ነው መታየት የሚኖርበት። አዚህ ላይ፣ የካቶሊኩ ርዕሰ ጳጳስ ፍራንሲስ፣ ለአሜሪካ ምክር ቤት ተወካዮች ካደረጉት

ንግግር ሰመጥቀስ፣ "አሁን ባሰ መመዘኛ ያሰፈውን መዳኘት ከባድ ነው።" ብሰው ነበር። በአርግጥ፣ ታሪከ እየተነጠሰና እየተመረጠ እየተነገራቸው ያደጉ ትውልዶች ካሉ፣ በነሱ ላይ መፍረድ አሰቸጋሪ ይሆናል።

ወደ መፅሐፉ ሰመሰስ፣ ለኔ፣ ደጋግሞ በአእምሮዬ የሚመላለሰው ትልቁ ጥያቄ፣ አንዴት? ወይም ለምን? የሚለው ነበር።

በቅን መንፈስ፣ በህዝቡ ላይ የነበረውን የመሳፍንት ዘመን ቀንበር ያስወገዱ ጎልማሳ፤ ለራሳቸው ምቾት ሳይፈልጉ በየድንኳኑ ሲንከራተቱ የኖሩ ሰው፤ ለህዝቡም ቢሆን፣ አንዳይበደል፣ ወደፊት ተሰፋ እንዲኖረው ያሰቡ ሰው፤ በሀያሳን መሳፍንቶች በየቦታው ተቆራርሳ፣ ዙሪያዋን ሊቀራመቷት ከተዘጋጁ ጠላቶች መንጋጋ ያዳኑ ሰው፤ በተቻላቸው መጠን ዘመናዊ ሥርአትን ሊመሰርቱ የታገሉ ሰው፤ እንዴት ሆኖ ነው ወይስ በምን ምከንያት፣ ህዝቡ ወይም ገበሬው የራሱን ጥቅም እሳልፎ በየቦታው አልመች ያሰና ግፋ ሊል ንጉሡን ሊወጋ የነበረው። ከሁሉም በላይ የአፄ ቴዎድሮሰን መራራ ሰሜት የፈጠረው፣ ይህ ደግ ያሰቡሰት ህዝብ ቅን አሰመሆን ነበር። አዚህ ላይ መስተዋል ያለበት፣ ነገሩን የሚጭሩትና፣ አንድ ጠቅሰል ያሰ ህገር መኖሩም ያልታያቸው፣ በየቦታው የነበሩት ባላባቶችና መሳፍንቶች ነበሩ። ገበሬው፣ በመሳፍንቱ ወይም በባላባቱ ሰር የተሻለ ኑሮ እግኝቶ እልነበረም የሚያምፁ ወይም የሚሸፍቱ ባላባቶችን ተከትሎ ሲሄድ የነበረው። ቴዎድሮስ ደግ ላደረጉሰትና ደግ ላሰቡለት ህዝብ መሸፌት ምከንያት በየቦታው የነበሩ በትውልድ ከነሱ ጋር የተሳሰሩ ሰዎቻቸው ነበሩ። እነዚህ ባላባቶቻቸው ያሰቡት ሰራሳቸው አንደነበር ግልፅ ነው። አፄ ቴዎድሮሰን፣ የንግሥና ዘር የሰውም፤ እናቱ ኮሰ ሻጭ ነች እያሉ፣ ዝቅ ዝቅ ማድረግና ማከፋቱም የመጣው ከነዚህ ተሰፈኛ ባላባቶች ነበር። ባላባቶቹ የሥርአት ለውጥ ፈላጊዎች አልነበሩም። የታገሉት፣ ለነበረው በተለይም እነሱ ተጠቃሚ የሆኑበት ሥርአት አንዲቆይ ነበር። ያንን ሰማሰፈፀም ግን ተከታዮችን በዘር፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በአካባቢ፣ በባላባትነት ትውልድ ማሰሰፍ ነበረባቸው።

ሌላው ለአፄ ቴዎድሮስ ዕንቅፋት የነበሩት ደግሞ ካህናቱና መነኮሳቱ ነበሩ። ንጉሡ አምነታቸውን ከድተውም አልነበረም ከካህናቱና መነኮሳቱ ጋር ጠብ የመጣው። በሀይማኖት ከመጣ፣ ቴዎድሮስ፣ ራሳቸውን "የከርሰቶስ ባሪያ" ብሰው የሚጠሩ ሰው ነበሩ። ፈሪሀ እግዚአብሔር እንደነበራቸውም የተሰያዩ ማሰረጃዎች ይጠቁማሉ። ሰሸልማት ያሠሩት ኒሻናቸው ላይ ያሰቀረፁት ፅሁፍ ራሱ ምሰከር ይሆናል። በዚያን ጊዜ፣ ከግዛቱ እንድ ሶሰተኛው መሬት የቤተከርሰቲያኗ ነበር። ሰለዚህ ንጉሡ፣ ገበሬውን ከብዝበዛ ሰማዳን፣ ቅጥ ያጣውን አንዳንዴም አሰነዋሪ የሆነ የካህናቱን ኑሮ በልከ እንዲሆን በሥርአት አደሩ ሰላሉ ነው ጠብ የተፈጠረው። የጥቅም ጉዳይ

ነበር። ቤተክርስቲያኗ ከያዘችው መሬት የተወሰነው ለመንግሥት እንዲሆንና ወታደሮቻቸው ገበሬውን እየዘረፉ ላይሆን በደሞዝ እንዲተዳደሩ ሰሞከሩት ንጉሥ፤ ከካህናቱ የመጣው መልስ፣ የንጉሡ ወታደሮች በደሞዝ ሳይሆን ከቦታ ቦታ እየተዟዟሩ ገበሬውን እየዘረፉ እንዲበሉ ነበር። እዚህ ላይ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ "እኔ ብቻዬን ስሆንልሽ እንደ አፄ ኢዮአስ በሻሽ እንቀሽ ልትገድይኝ፣" በማለት ከወታደሮቻቸው ጋራ ሲጎትራቱቱ ነው የኖሩት። አንግዲህ፣ ይችው የተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ በታሪክ፣ በተለይም በጣልያን ወረራ ጊዜ ቀና ብላ ብትታይም፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንክስ እያለች፣ በግልፅም ለዕድገት እንቅፋት ነበረች። ይህ ደግሞ፣ በውስጧ፣ ፈጣሪን ለማገልገል፣ ምዕመናኑን ከፈጣሪ ጋራ ለማገናኘት፣ በራሳቸው አነሳሽነት ተምረው ቤተ መቅደሱን በሚረግጡ ካህናት አማካኝነት ነበር። እነሱስ ቢሆን ሥጋ ለባሽ አይደሉምን? ለቴዎድሮስ፣ የተበተነ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ በትርጉም የተነሣ የተከፋፈለ ሀይማኖትም ነበር ያጋጠማቸው።

ቴዎድሮስ፣ ምንም እንኳን የብልጭልጭ ኑሮ የማይወዱና ኑሯቸው የተራ ወታደር ቢሆንም፣ የሀገሪቱ ንጉሠ ነገሥት እንደመሆናቸው መጠን፣ በሀገራቸው ሰዎችም ሆነ በውጭ ሰዎች በኩል ምንም አይነት ከብር የጎደሰው ነገር የማይቀበሉ ሰው ነበሩ። በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ የንጉሡን ግንፍል ያለ ቁጣ የሚያስነሳው ይህ ነበር። ለዚህ እንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፣ ቴዎድሮስ ጋፋትን ጎብኝተው ሲመለሱ፣ እንድ ለማኝ ቀርቦ፣ የእውሮፓ ጌቶቼ ይረዱኛል፣ እርስዎም ይርዱኝ ብሎ በመለመኑ የበገኑት ቴዎድሮስ፣ ከእኔ ውጭ ደግሞ ማን ሌላ ጌታ አለህና ነው ጌቶቼ የምትለው በማለት ሰውየው በዱላ እንዲደበደብ እዘው፣ ወደ እውሮፓውያኑ ዞር ብለው፣ አናንተ ደግሞ ማን ሆናችሁና ነው ራሳችሁን ጌቶች የምትሉት በማለት ተሳድበዋል። የነጮቹ ንቀት ቴዎድሮስን በጣም ያበሳጫቸው እንደነበር ግልፅ ነበር። ንቀት ከመስላቸውም እርምጃ ይወስዳሉ። በላቸው ግዛት፣ ቆንስላ ካልሆነ በስተቀር፣ ሌላው ነጭ በሙሉ ከዜጎቻቸው ጋር እኩል ነው የሚታየው የሚዳኘውም። ይህ ኩራት ግን የኋላ ኋላ የውጭ ዜጎችን በማስራቸው ያስከተለውን ጣጣ ነው ይህ መፅሐፍ የሚዘግበው።

ከዙላ እስከ መቅደላ፣ ከእንግሊዝ ሠራዊት ጋር የተጓዘው ይህ ሰው፣ ለእንግሊዝ ሠራዊት መቅደላ አፋፍ ድረስ መውጣት፣ የጦር መደራጀት ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ብዙ የተሠሩ የፖለቲካ ሥራዎችን ያካፍሰናል። በዘመኑ ወድ የተባለውን የመቅደላን ዘመቻ፣ እንግሊዞቹ በታላቅ ጥንቃቄና ዝግጅት ነበር ያደረጉት። ለነሱ፣ በዚያን ጊዜ አንደ እውነቱ ከሆነ፣ በየአህጉሩ ቅኝ ግዛት ስለነበራቸው፣ የታላቋ ብሪታንያ ዜጎችን ማሰርና የንግሥቷን መንግሥት መድፈር፣ ለሌሎች ቅኝ ግዛቶች አርአያ እንዳይሆንም ነበር።

ስለ እፄ ቴዎድሮስ ባህሪ የበለጠ ለማወቅ፣ ከዛም በግርጌ ማስታወሻዎች ለእንባብያን ለማጋራት ብዙ ፅሁፎች መመልከት ነበረብኝ። እብዛኞች ፀሀፊዎች፣ በተለይም በእስር የነበሩት ንጉሡን በማከፋት የዘገቡ መሆኑ ብዙም አይገርምም። ከሌሎች አውሮፓውያን በተለየ ሁኔታ፣ እፄ ቴዎድሮስን በበጎ ባህሪ የሚያስታውሳቸው ሄንሪ ዱፍተን የተባለ እንግሊዛዊ ነው። ከዱፍተን ሌላ፣ ከንጉሡ ጋራ ሰረዥም ጊዜ እብረው የነበሩ ሰዎች፣ እንደ ፐላውደን፣ ጆን ቤል፣ ሆርሙዝ ራሳምን ጨምሮ፣ ሌሎቹ እንዳደረጉት ንጉሡን በከፋነት አይሰሏቸውም። ነገር ግን፣ በብዛት የሚታወቀው ስራ፣ ቴዎድሮስን እከፍቶ የተፃፈው ነው። ሆኖም፣ እንባቢ ከዚህ ፅሁፍ በቂ ግንዛቤዎች በማግኘት የራሱን እስተያየት መስጠት እንደሚችል ተስፋ አለኝ።

በነዚህ የተለያዩ ፅሁፎች፣ በእብዛኛው የሰውየው ባህሪ እገላለጥ አንደፀሀፊዎቹ ሆኖ ነው ያገኘሁት። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እንዱን እንብቤ ሌላውን እስከማነሳ ድረስ፣ በፅሁፉ አገላለጥ የተነሳ፣ ቴዎድሮስ እንደዚህ አይነት ሰው ነበሩ ወይ ብዬም የጠየቅሁበት ጊዜ አለ። ነገር ግን፣ በተቻለ መጠን የተለያዩ ፀሐፊዎችን ሥራ ለማየት በመቻሌ፣ በተለይም ከንጉሡ ጋር ቅርበት የነበራቸውን፣ ወይም በዘመኑ የነበሩ ፀሐፊዎች የፃፉትን ስመለከት፣ አከብሮቴ ጨመረ እንጂ አላነሰም። ያም ሆኖ ቴዎድሮስ ያላዩትን ባህሪ ለመሸሸግ ወይም ለማሳመር አልሞከርኩም። ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹም በዘመኑ የነበሩ ጉልህ ሰዎች ያደረጉትን እንዳለ ነው ያስቀመጥኩት።

ዋናው ነገር፣ ቴዎድሮስም ሆነ ሌሎች መሪዎች ላይ ፍርድ መሠጠት የሚገባው፣ ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ነው። ያም፣ በኔ እስተያየት፣ በሁለት መንገድ መታየት አለበት። አንደኛ፣ በንፁህ ልባቸው፣ ለሀገሩ፣ ለህዝቡ ከጥዋቱ ምን እስበው ነበር? ምንስ ለማድረግ ፈልገው ነበር? ሁለተኛ ደግሞ፣ ያው ግልፅ እንደሆነው፣ ምን ትተውልን አለፉ? የሚለው ነው። ይህ ደግሞ በዘመኑ በነበሩ ሁኔታዎች ነው መታየት ያሰበት። እንደምንረዳው፣ ቴዎድሮስ ወደፊት ሲያስቡ ባላባቱና ህዝቡ ደግሞ እንቅፋት ሆነው እንደነበሩ ነው። የባላባቱ እንኳን አያስደንቅም። ቴዎድሮስ አዲስ አገር አልፈጠሩም፤ የተበተነች ሀገር ነው የሰበሰቡት። ይህንንም ሲያደርጉ በዘመኑ የነበረው አማራጭ መንገድ ግልፅ ነበር።

እፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት፣ ህዝቡ ተመችቶት የሚኖር አልነበረም። ተማሮና ተቸግሮ ስለነበር፣ እንደ ቴዎድሮስ እይነት ሰው እንዲመጣ በናፍቆት ሲጠብቅ ነበረ። የኋላ የኋላ፣ ይህ በናፍቆት የጠበቃቸው ህዝብ፣ ሰውየው ያስቡሰትን የተረዳ አልመሰለም። በየቦታው፣ በተወላጅ ባላባቶቹ ስበካ ልቡን መልሶ ነፍጓቸዋል። ጨካኝ ወይም እምባ ገነን ስለሆኑ ነው? አምባገነኑ እንኳን በቀላሉ ተቀባይነት አይኖረውም። ምፅአተ

ቴዎድሮስ በጉጉት ይጠበቅ ነበር። ቴዎድሮስ፣ ካሳ ይሁን ወይም ሌላ ስው፣ ብቻ የነበረውን አሰከፊ ጊዜ የሚያስወግድ ስው ነበር የተጠበቀው። በዚያን ጊዜም፣ ህዝቡ ለሰውየው በነበረው ፍቅርና አድናቆት፣ የውነት የዲሞክራሲ ምርጫ ቢኖር ኖሮ ባሸነፉ ነበር። በዚያን ጊዜስ ቢሆን የትኛው የአውሮፓ አገር ነው በዲሞክራሲ የሚመራ የነበረው? በርግጥ ጭካኔ ነበር፣ ነገር ግን የጭካኔ አሰራሩ ቴዎድሮስን ቀድሞ የነበረና ከዚህ በተጨማሪ በዘመኑ የነበረው የአገሪቱ ህግ ወይም የፍትህ ነገሥቱ ቅጣት ራሱ በጣም ጨካኝ ነበር። ከቴዎድሮስ በፊት የነበሩ ባላባቶችና መሳፍንቶችም ብዙ የጭካኔ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር። በተጨማሪም፣ ካሳ፣ ከሽፍትነት ጀምሮ ሥነ ሥርአት አጥባቂ ሰው ሰለነበሩ፣ የሥነ ሥርአት አርምጃው ወታደሮቻቸው ላይ አንኳን የከረረ ነበር። ያም ቢሆን ወታደሮች ገበሬ ሲበድሉ በመገኛታቸው ነበር። የቴዎድሮስን ቅጣት ለየት የሚያደረገው ዘመናቸውን በሙሉ በውጊያና በዘመቻ ስላሳለፉት በሞት የሚቀጣው ሰው ቁጥር የተበራከተ መሆኑ ነው። ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው አብይ ነገር፣ አፄ ቴዎድሮስ ላሳቡት አላማ አንቅፋት የሆነ በሙሉ፣ ዘርና ሀይማኖት ሳይሰይ በትራቸውን ቀምሷል። ያሰርህራሄ ከተደመሰሱ ወገኖች አንዱ፣ የወንድማቸው ልጅ የጋረድ ከንፉ ሰዎች ነበሩ።

በመጀመሪያዎቹ ድሎቻቸው፣ የቆሰሉ ባላባቶችን ምረውና ተንከባከበው፣ አንዳንዴም ሾመው ሲሄዱ በጀርባቸው አየከዱ ማስቸገሩ፣ ንጉሡን መረር ያስ ቆራጥ ርምጃ አንዲወስዱ አድርጓቸዋል። በየትኛውም አለም ቢሆን ህገርንና ንጉሥን መከዳት የሚያስከትለው ቅጣት ከፍ ያለ ነበር።

የቴዎድሮስን መራራ በትር የቀመስ ከፍል አስሌ ከአከሌ ሳይባል ሁሉም ነበር። በርግጥ፣ ብዙ ጉዳት የደረሰበት ከፍል በየጊዜው አየሸፈተ ያሰቸገረው መሆኑ ግልፅ ነበር። ታዲያ፣ የቴዎድሮስ ሀይል ካረፊባቸው ከፍሎች፣ የንጉሡን መራራ ቅጣት ወደ ጎን አድርጎ፣ ይልቁንም ሰውየው የታገሉለትን በማስታወስ አንደ ጀግና የሚያወድሰና የሚዘክር ወገን ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ምን ሲባል የቴዎድሮስ ለም ይነሳል የሚል ወገን ብቅ አያለ ነው። ይህ በርግጥ በፅሞና ማነጋገር የሚገባ ነገር መሆን አለበት። የሞተው በዚያም በዚህ ሆኖ አያለ፣ ሥልጣኑን የተቀማው ባላባት ሁሉም ሆኖ እያለ፣ ያንዱ ወገን ቁስል ብቻ አልሽር የሚልበት ምክንያት ለምን ይሆን? ቴዎድሮስ ያወረዷቸው ባላባቶች ራሳቸው፣ የአብዛኞቹ፣ በዚያን ጊዜ ይዘውት የነበረው ሥልጣን በሀይል ያገኙት ነበር። ባጠቃላይ ሲታይ፣ በዚች ህገር ታሪክ፣ መጠኑ ይብዛ ይነስ አንጂ ያልቆሰለና ያላቆሰስ የለም።

አፄ ቴዎድሮስ ያስቡት፣ ሁሉንም በአንድ ሥርአት አስገብቶ ወደፊት ስመራመድ ነበር። በተቃራኒው በጣም የሚያሳዝነው፣ ህዝብ ወደፊት መሄድ

ፈልጎ መሪ ወደኋላ ሲጎትት ማየት ነው። የቴዎድሮስ ሁኔታ ያ አልነበረም። አውሮፓውያኑ የመሰከሩላቸው ነገር ቢኖር፣ ከህገራቸው ስዎች ተለይተው አርቀው ሀሳቢና ወደፊት መራመድ የሚፈልጉም አንደነበሩ ነው።

በዚያን ጊዜ፣ ሁሉም ጉልበት ያለው ባላባት ስመንገሥ ያስብና ይዘጋጅም ነበር። ጉልበት አለን የሚሉት ደግሞ በየግላቸው ከአውሮፓ ሀያላን ጋር በግል ይፃፃፉ ነበር። አንዳንዶቹም የህገሪቱን መሬት በሥጦታም ሆነ በሽያጭ ለውጭ ሀይሎች ስመሰጠት ሞክረዋል። ባላባቶቹ ሲፃፃፉም ራሳቸውን ንጉሥ አያሉም ነበር። ለጊዜው ጉልበት ላለው አየገበሩ፣ ውስጥ ውስጡን ግን የራሳቸውን ቀን ይቆጥሩ አንደነበር ግልፅ ነበር። የግል አላማቸውን ስማስፈፀም ከውጭ ሀይሎች ጋር ከመተባበር አይመለሱም። በዚህ በኩል ደግሞ አከሌ ከአከሌ ሳይባል ሁሉም የሚያደርጉት ነገር ነው የነበረው። በተሰይም ታላላቆቹ።

መሳፍንቶቹ ያለማሰለስ በየጊዜው ሀይላቸውን ሲፈታተሹ በመሀከላቸው የተደረጉት የርስ በርስ ጦርነቶች ምስክር ናቸው። በዚህ የርስ በርስ ጦርነት ደግሞ፣ የሚፈሩትን ስማጥቃት ሁለት ወገኖች ጎሳ ሳይለዩ ግንባር አየፈጠሩ፣ አንደገናም አርስ በርሳቸው አየተዋጉ ነበር የኖሩት። ካሳ ሲነሱ፣ ህዝቡ በጦርነት ተዳክሞ ሰላም የሚፈልግበት ጊዜ ነው የነበረው። ባላባቱ አንዱ ላንዱ ባይተኛም፣ የዚያን ጊዜውን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው፣ አያንዳንዱ አፈንግጦ መውጣት ሳይሆን በሀይል ጠቅሎ ለመያዝ ሰስሚፈልግ ነው የሚል የታሪክ ባለሙያተኞች አስተያዬት አስ። አውነታም ሊኖረው ይችላል፤ ሆኖም ካሳ ባይነሱና በጉልበት ባያዋህዱ ኖሮ፣ ሁሉም በየቦታው የራሱን ግዛት ሊያሰፋ ስለነበር የተዋህደች ህገር ለመፈጠሩ ዋስትና አልነበረም። ከካሳ በፊት መሳፍንቶቹ ጠቅልለው ስመግዛት ሳይሞክሩ ቀርተውም አልነበረም። ነገር ግን፣ በዚያን ጊዜ ለውጥ ስማምጣት የካሳን አይነት የተሰየ ባህሪ የነበረው ሰው አሰፈላጊ የነበረ ይመስላል። ሰስዚህ ካሳ ባይነሱ፣ ምናልባትም አሁን የምናውቃት ኢትዮጵያ ልትኖር አትችልም ይሆናል። የዚህ የርስ በርስ ሁኔታ፣ በተቃራኒው፣ ደንበራቸውን ጠንከረው መያዝ የሚችሉ ጉልበታም ባላባቶች በለላው ሲሞቱ፣ በደንበሩ በኩል ያለው ሀይል ሲደከም ነው የሚታየው። ስዚህም አንድ ትልቅ ምስክር፣ ከተከዜ አሰከ ቀይ ባህር ሲገዙ የነበሩት ሀይለኛው የአንደርታው ባላባት የራስ ወልደ ስላሴ ቤት፣ ከዚያም የተከተላቸውና መዲናውን ወደ አዲግራት ያዞረው የሰባጋዲስ ጦር በራስ ማርዬ ጦር ሲመታ፣ የራስ ማርዬ ጦር ተመልሶ ወደ መጣበት ሄደ አንጂ ደንበሩን ለማስጠበቅ አልሞከረም።

ይህ ሥራ፣ ርአሱ መቅደላ ቢሆንም፣ የቴዎድሮስን ማንነትና አላማ ለአንባቢ ስማስገንዘብ የጣረ ፅሁፍ በመሆኑ፣ አንባቢ ስፋ ያስ ግንዛቤ

እንደሚያገኝ ተሰፋ አለኝ። ሌላው ምኞቴ ደግሞ፣ ይህ ፅሁፍ መወቃቀሻ ላይሆን፣ ንጉሡ የደከሙበትን፣ ከዚያም በተከታዮቻቸው ተጠናክሮና ተሰፋፍቶ የተረከብነው ሀገር ውሰጥ እብሮ መኖር እንዲቻል መመካከሪያም እንዲሆን ነው። ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው ሀገር ደንበር፣ በባለሙያተኞች መልካም ፈቃድ የተሳለ እይደለም፤ የብዙ ወገኖቻችን፣ ንጉሥንም ጨምሮ፣ ደም የፈሰሰበትና እጥንት የተከሰከሰበት አጥር ነው። አሁን መህል እገር የሚባለው ክፍል፣ ደንበሩ በመሰዋትነት ተጠብቆ ሰለቆየ እንጂ፣ ራሱ መህሉ ዳር ከመሆን የሚያለጥለው ነገር አልነበረም። በዚች እገር ታሪክ፣ በተለይ በቁጥራቸው ታላላቅ የሚባሉ ብሔረሰቦች፣ በስማቸው በየተራ ሥልጣን ይዘዋል። እንዱ ብቻ በዳይ ሆኖ ሌላው ተበዳይ ከመሆን በለተቀር ምንም አይነት ሚና እንዳልነበረው ተደርጎ የሚቀርበው ከእውነታ የራቀ ነው። ይልቁንኑ፣ የየራሱን ባለባት ሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲል በእንድነት መጓዝ የሚቻልበትን መንገድ እዳከሞታል። ደጋግሞም የሚታየው በአንድ ወገን ሰም ጉልበት ያለው ሥልጣን ቢይዝም፣ የዚያ ወገን ለሆነው ለተራው ህዝብ ግን ከኑሮው የሚያሻሽለው ምንም ነገር አልነበረም። ግብሩም እይቀንለለትም፤ እንዲያውም እዲሰ ለመጣው፣ የኔ ነው ለሚለው ባላባት መከፈሉን አያቆምም ነበር። በሁሉም ወገን ለደህው ጠብ የሚልለት ነገር አልነበረም። በዚህ መፅሐፍ ውሰጥም፣ ከቴዎድሮስ ያፈነገጡ፣ ነገር ግን እዲሰ ለተተካው ለዋግሹም አልገብርም ያሉ በጦር ሲቀጡ ይታያል።

እዚህ ላይ ግን፣ ተራው ህዝብ የሚባለውስ ሀላፊነት አልነበረበትም? ወይስ የለበትም ወይ? ቴዎድሮስ ተራውን ህዝብ ክፉ ነው ብለው ነው የሚወቅሱት። ለራሱ የሚመቸውንና የሚሆነውን መንገድ አለማሰቡና ከውሰጡ በሚፈጠሩ ጥቂት መሪዎች በመነዳት እንድ ላይ ሆኖ ለሚበጀው ሥርአት አለመታገሉ፣ ንጉሡ እንዳሉት ክፉ ነው ወይ?

እዬ ቴዎድሮስ ራሳቸው የጭካኔ ሥራ እንደለሩ የሚያውቁ ይመስላሉ። እብዛኛውን የጭካኔ ሥራ ከባላንጣዎቻቸው ወይም ከሽፍቶች እንደተማሩ ይገለጣል። በተለይም፣ በንጉሡ ወታደሮች ላይ ይደረግ የነበረውን የጭካኔ ሥራ፣ ንጉሡ መልለው ሌሎቹ ላይ አድርገውታል። እንደታየው ከሆነ፣ በወሰዱት ርምጃ ተዝናንተው የሚቧርቁም አልነበሩም። በተለያዩ ጊዜያት እንደተፀፀቱ የሚገልፁ ዘገባዎች አሉ። ተራውን ሰውና ባላባቱንም ይቅርታ የጠየቁበት ጊዜ አለ። እውሮፓውያኑንም ላይቀር ይቅርታ የጠየቁበት ጊዜም አለ። እንደ ቴዎድሮለ ኩራት፣ ራሰን ዝቅ እድርጎ ይቅርታ መጠየቅ የይለሙላ እይመስልም። መቅደላም ላይ ቢሆን፣ ሰዎች ከተገደሉ በኋላ በመፀፀት እቡኑን ለምን አልገዘቱኝም ነበር በማለት የጠየቁበት ጊዜ አለ። ባንድ በኩል ግን፣ ንጉሡ፣ ከፉ ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች ለመቅጣት ሥልጣናቸው ከፈጣሪ

እንደሆነ አድርገው የተቀበሉት። ያም ሆነ ይህ፣ የብሰጭታቸው መነሻ የሆነው፣ የሰዎች በየቦታው ከህደትና መሸፈት፣ የእውሮፓውያኑ ንቀትና ከውጭ ጠላቶቻቸው ጋር ሲተባበሩ ማየት፤ እየጨመረ እንጂ እያነሰ ሰላልሄደ ብሰጭቱም ቀጠለ እንጂ እላባራም ነበር። ብዙዎች ምስከርነት እንደለጡበት፣ ሰውየው ከጥዋቱ ከፉ ሰው እልነበሩም። ይህም በመፅሐፉ በተለያዩ ከፍሎች ይጠቀሳል። እዚህ ላይም ሌላው ዋናው ነገር፣ የሰውየው ባህሪ ተቀየረ ነው። ይህን ደግሞ የውሰጥም ሆነ የውጭ ታሪክ ፀሐፊዎች በሙሉ የሚሰማሙበት ነገር ነው።

እዬ ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ ሲገሰግሱ ፍፃሜያቸውን በግልፅ ያውቁ ነበር። በመቅደላ እንደሚሞቱም ያውቁ ነበር። ለእንግሊዙ መልከተኛ፣ ለራሳም፣ ሲሞቱ እሰከሬናቸው እጠገብ ቆሞ ሊዘበትባቸው እንደሚቸል እሰቀድመው ነግረውታል። እኔ ራሴን ለፈጣሪ እሰጣለሁ እንጂ ለማንም እልሠጥም ነው ያሉት። በዚያን ጊዜ፣ ያለጅቸውን ነጮች ለመግደል ምንም የሚያግዳቸው ነገርም አልነበርም። በምክር ሲወለን፣ ቴዎድሮስ ነው የተቃወሙት፤ ለሀገሬ ለው ጠንቅ ጥዬ አልሄድም ነበረ መልሳቸው። ቢዚያ ባለቀና በጨለመ ሁኔታም ቢሆን እርቆ ማሰቡ አልጠፋም። እንዳንዴ፣ እንዲህ ቢሆን ኖሮስ የሚል ጥያቄ ማንሳት የማይመስልና የማይመች ቢሆንም፣ በህሳብ ለመሚገት፣ ቴዎድሮስ ባይነሱ ኖሮስ? ብሎ መጠየቅ እንግዳ እይሆንም። ለዚህ ጥያቄ መልስ ግን፣ ቴዎድሮስ ሲነሱ እገሪቷ በምን ሁኔታ እንደነበረች መረዳትን ይጠይቃል። ባጭሩ፣ ለመቶ እመታት በእርለ በርስ ጦርነት የደከመች እገር ነው የነበረችው።

መለስ ብለን ካየነው፣ በዚች ሀገር ውሰጥ ጥሩ ነገር ለመሰራት እንኳን ከባድ የነበር ይመሰላል። ይህ ጉዳይ፣ በእዬ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆን፣ አዬ ኃይለ ሥላሴም ቢሆን በመጀመሪያው የንግሥናቸው ዘመናቶች ብዙ ለመለወጥ ሞክረው ላይላካላቸው ተሰፋ ቆርጠው የተውት ይመስላል። ያም ሆኖ፣ እዬ ቴዎድሮስ የጀመሩት የማዕከላዊ መንግሥት ምስረታ ሙሉ በሙሉ ሥር የያዘው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው።

ቴዎድሮለ፣ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ ቤተክርስቲያኗ እንድ እንድትሆን ሞክረው ነበር። የቤተክርስቲያኗ ሲቃውንቶችና ካህናቱ፣ ሁለት ልደትና ሶስት ልደት በሚባሉ ወገኖች ተከፋፍለው ነበር። ከዳጃች ውቤ ጋር የነበሩት፣ የግብፁ አንድርያስ፣ በጳላም አቡነ ሰላማ፣ ደጃች ውቤ በራስ አሊ ሲሸነፉ፣ ከራስ አሊ ጋራ ቆይተው ነበር። ሆኖም፣ የአዘዞና የሸዋ ካህናት፣ በዚሁ በትርጉም የተነሳ፣ እንድ ላይ በመሆን እብረው፣ ለራስ አሊና ለእናታቸው ለወይዘሮ መነን ብር በመሰጠትና በመወትወት አቡኑን ወደ መጡበት ወደ ደጃች ውቤ እንዲመለሱ አድርገዋቸዋል። ሶስት ልደቶቹ፣ የአዘዞና የሸዋ

ካህናት የአቡነ ስላማን ወገኖች ዘርፈውና ገፈው ሰደዷቸው ይላሉ ደብተራ ዘነብ። በዚያን ጊዜ፣ አቡኑም ቢሆን አዝነው ስቴዎድሮስ መምጣት ፀልየዋል። አፄ ቴዎድሮስ ከነገሱ በኋላ፣ ከንጉሡ ጋራ የተመለሱት አቡነ ሰላማ ቂማቸውን ሳይረሱ፣ ቴዎድሮስ በሌሉበት ጊዜ አግራቸውን አየጠበቁ ብድራቸውን መልሰዋል። ቴዎድሮስ ህይማኖቱን ወደ አንድ ሰማምጣት ቢጥሩም፣ አፄ የሐንስ አራተኛ ናቸው ሊቃውንቱን ቦሩ ሜዳ አከራከረው አንድ ያደረጉት። ከዚያ በኋላ ተዋህዶዎች ወይም ሁሰት ልደት የሚባሉት ክርክሩን አሸንፈው ቤተክርስቲያኗ በተዋህዶ አንደፀናች ይታወቃል። የተረቱት ሶስት ልደቶች ግን ተደበቁ አንጂ ጭራሽ ለመጥፋታቸው ማረጋገጫ የለም።

በየትኛውም የአለም ክፍል፣ በስላማዊ መንገድ የተመሠረተ አገር ያለ አይመስልም። ህገር ቀርቶ፣ ታላላቅ ህይማኖቶች የሚባሉት እንኳን፣ በውስጥ ታሪካቸው ጥፋትና የሕይወት ማለፍ አብሯቸው የተፈጠረ ይመስላል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ያለፈ የርስ በርስ ጦርነት ታሪኳ ብርቅ አይደለም። ዋናው ነገር፣ አዲሱ ትውልድ የተረከበውን አገር ወደ የት ይዞ መሄድ እንደሚፈልግ ማወቅና መወሰን ይኖርበታል። አንደ አገር ጠብቆ፣ በውስጡ መብቱን አስከብሮና ተከባብሮ መኖር ይችላል ወይ? ነው ጥያቄው። በአሜሪካ አመሠራረት ላይ አንድ ተደጋግሞ የሚነገር ታሪክ አለ። ይኸውም፣ የአሜሪካ መስራች አባቶች የሚባሉት ተወካዮች ስብሰባ ጨርሰው ሲወጡ፣ ከተወካዮች አንዱ የሆነውን ቤንጃሚን ፍራንክሊንን፣ በቦታው የነበሩ ሰዎች ቀርበው፣ ምን አይነት መንግሥት ፈጠራቸሁልን ብለው ይጠይቁታል። የሰውየው አጭር መልስ ደግሞ፣ "ጠብቃችሁ መያዝ ከቻላችሁ፣ ሪፓብሊክ ነው።" የሚል ነበር። በዚህ መፅሐፍ፣ ራሳቸው ባያዩትም፣ ይችን ህገር መልሰው ስብስብ አድርገው የሠጡንን ስው ታሪክና ፍፃሜ ነው የምንከታተለው። የቴዎድሮስ የመጨረሻው ስአት አንደዚህ በዝርዝር ተገልጦ አያውቅም። በሌሎች፣ ስለ ቴዎድሮስ በሚጠቅሱ ሰዎችም፣ በመቅደላ ላይ ስለሆነው ሁኔታ በዝርዝር አፃፃፉ የሚጠቀሰው ይህ የስታንሊ ስራ ነው።

ገበየሁ ተፈሪ ዶ/ር
2009 (አኤአ 2017)

ምዕራፍ አንድ

የአንግሊዞች ካምፕ፣በአለም ምርጥ ሰው፣ ለትልቅ ሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ መግቢያ

የዙላ ወደብ ሳርፍ፣ በጣም አስገራሚና አዲስ የሆነ ትዕይንት ነው ያጋጠመኝ። በሺዎች የሚቆጠሩ ከወገብ በላይ ራቁት የሆኑ ሰዎች፣ በማያባራው የአፍሪቃ ሞቃት ፀሐይ ሥር፣ እየጮሁና አየዘመሩ ሥራቸውን ያከናውናሉ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ዩኒፎርም የለበሱ አሠሪዎች፣ መግረፊያ አለንጋቸውን ይዘው፣ በምድባቸው ያሉ ሠራተኞችን በማስገደድ ያሠራሉ። በመቶዎች የሚቆጠሩ የሚያናፉ አህዮች፣ የሚያስካኩ ፈረሶችና በቅሎዎች፣ በዝቅተኛ ድምፅ የሚያጓሩት ውሀ የተጠሙ የቀንድ ከብቶች፣ የሚሰቀጥጥ ድምፅ ያላቸው ሁለት ያልተለመዱ ሎኮሞቲቮች፣ ወዲያና ወዲህ የሚመላለሱ ጩኸት ያላቸው ተሸከርካሪዎች ተደማምሮ፣ መጀመሪያ ለተመለከተ ሰው፣ የህገሩ ሰው ሁሉ በስደት መጥቶ በአነስሊ[1] ወሽመጥ ዳርቻ ትልቅ ከተማ ሊመሠርት ያለበ ይመስላል። በሸራ የተሸፈኑ የጋራ ከምር የመስሉ የቁሳቁስ ቁልሎች፣ ረዣዥም ለጦርነት መገልገያ በሆኑ ቁሳቁሶች የተሞሉ የእንጨት ጣራ ያላቸው መካዝኖች፣ በወደቡም፣ ሞገስ ያላቸው የባሕር ማማለሻ መርከቦች፣ ወታደሮች፣ የተለያዩ የባሕር ማመላለሻ ቀላልና ከበድ ያሉ ጀልባዎች፣ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው፣ ከሞካ፣ ሶአኪም፣ ጀዳና ምፅዋ የመጡ የቱርክ ጀልባዎች፣ እንደ ክንፍ ከተዘረጋው በነፋስ የሚገፋው ሸራቸው ጋር ወደቡን ሲርመሰመሱበት የተፈጠረውን ህልማዊ ትዕይንት አባብሰውታል።

ከአንግሊዞች ሠራዊት የማውቀው ሰው ስላልነበረ፣ ይህንን የአንግሊዞች የጦር ካምፕ ኑሮ የሚያስተዋውቀኝ ሰው የግድ ማግኘት ነበረብኝ። ሳስታውስ፣ በአንድ ሻለቃ (ሜጀር ኤስ)፣ ከአንድ የአንግሊዝ ጦር የትጥቅና ስንቅ መኮንን ጋር አንድተዋወቅበት የተሠጠኝ ደብዳቤ በአጀ አንዳለ ተገነዘብኩ። አገልጋዬን አሊን፣ አስከመስስ ድረስ ከአንድ ትልቅ መካዘን አጠገብ አንዲጠብቀኝ ትዛዝ ሠጥቼ ተሰናበትኩት። በፍጥነትም፣ በአንጨት

[1] የዙላ ወይም የአራፋሊ ሠርጥ ተብሎም ይታወቃል። የቀይ ባህር ደንበር ነው።

ከተሠራ ቤት አጠገብ የተተከሉ የተንጣለሉ ድንኳኖች ወዳሉበት ሥፍራ አመራሁ። ቁጥራቸው በርከት ያለ ነጭ እጀጠባብ የለበሱና ራሳቸው ላይ ጥምጣም ያደረጉ ህንዶች በፍጥነት ይሯሯጣሉ። ሰፋ ካለውና ምቾት በተመላበት ሁኔታ በተንጣለለው ድንኳን አጠገብ ዘብ የቆመውን ወታደር ጠየቅሁት። "የካፒቴን ዚ ድንኳን የትኛው ነው?" ወታደሩም፣ ብዙም ራቅ ሳይል የተተከለ፣ ተለቅ ወዳለ ድንኳን አቅጣጫ አመላከተኝ። ድንኳኑ፣ ዙሪያውን ችፍግ ባሉ ተከሎች ተከቧል፤ ከሌሎች ድንኳኖች መለያ ምልክት መሆኑ ነው። ከተጠቀሰው ድንኳን እንደደረሰኩም፣ በውሰጡ ላለው ሰው ጎብኝ መምጣቱን ለማሳወቅ የድንኳኑን ሸራ ጫር ጫር አደረኩት። ወድያውኑ፣ የህንዶች ረጅም ጀለብያና ሰፋ ያሉ ሱሪዎች (ፒጃማ ይባላሉ) ለብሶ በሙሉ ሰውነቱ ሶፋ ላይ በተጋደመ ሰው ወደ ውስጥ እንደገባ ተጋበዝኩ።

"የኮሚሳሪያቱን ካፒቴን ዚን[2] ለማየት ነው የመጣሁት፣ ሰር፣"፤ በእንግዳ ፊት ምንም ሰሜት ያልተሰማው ሰው መሆኑን በማየትና በመገረም፣ "አርሰዎ ነዎት ወይ ሰውየው?" ብዬ ጠየቅሁ።

ቅንድቦቹን በመጠኑ ወደላይ ሰብሰብ በማድረግ፣ "እዎ፣ ሰውየው እኔ ነኝ።" ብሎ መለሰልኝ። በማሰከተለም፣ "እንተ ማነህ? ምንሰ ትፈልጋለህ?" አለ።

"ከሜጀር ኤሰ የተላከ፣ ከርሰዎ ጋር እንድተዋወቅ የተፃፈ ደብዳቤ ይዤ መጥቻለሁ።" በማለት ደብዳቤውን ለመሰጠት ወደፊት ራመድ ብዬ ጎንበሰ እልኩኝ።

"ህም፣ አሃ! ከሜጀር ኤሰ በርግጥ፣ አው! እሰኪ ልመልከተው፤ ቁጭ እትልም አንዴ? ሰለግድየለሽነቴ ይቅርታ ፣ ይህ ህገር ሙቀቱ የሰው መቅኔ ያቀልጣል!"

ይቅርታ ሲጠይቅ ከተቀመጠበት ግማሽ እንደመነሳት ብሎ ነበር። ወድያውኑ ግን፣ ወደ ነበረበት የሰውነት እቀማመጥ ጥልቅ የእፎይታ ትንፋሽ በመተንፈሰ ተመለሰ። ደብዳቤውን ከማንበቡ በፊት አሳዛኝ በሆነ አመለካከት ተመለከተኝ። ከተጋደመበት ለመነሳት ምን ያህል እንደተሠቃየም በቂ ምልክት ነበር። ሶዳ ውሀና ብራንዲ እንዲመጣ በሰውየው ታዘዘ፣ ጠቆር ባለ የህገሩ ተወላጅ ቀረበልን። ለሁሊታችንም ርካታ ሠጥቶናል። እኔም፣ ድንኳንና ሌሎች ራሽኖች እንዲሠጡኝ ጠየቅሁኝ።

---

[2] ፀሀፊው የሰዎችን ስም የመጀመሪያ ፊደል ብቻ ስላሰቀመጠ፣ ሙሉ ስም መጥቀስ አልተቻለም። ይህ ሁኔታ ወደ ፊት በሌሎች ስሞችም ላይ ይታያል።



የጥንታዊው የአዱሊስ ከተማ ፈርስራሽ በዙላ አጠገብ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

"አ፣ አዎ፣" በማለት ካፒቴኑ መልስ ሠጠ። "ቀላል ነው፤ ዝርዝሩን ፃፍ፤ የለም፤ አንዲህ ይሁን። መጀመሪያ፣ ወደ ሜጀር ኤክስ ትሄድና ለድንኳንና ለራሽን ትዛዝ ማግኘት አለብህ። ከዚያ በኋላ ችግርም አይኖርብህም።"

ሜጀር ኤክስ፣ የዙላ ሠራዊት አዛዥ እንደሆነም ነገረኝና፣ በመቀጠልም "በጣም ጥሩ የተከበረ ሰው ነው፤ ምለጉን፣ አንደኛ ደረጃ፣ የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠብም።" ለኔ መሆኑ ነው። አኔም እንደዚህ የተመሰገነውን መኮንን ለማየትና ጉዳዬን ለመፈፀም፣ ካፒቴኑን ወደፊት እንደምንገናኝ ምኞቴን በመግለፅ፣ ደህና አርፍድ ብዬ ተለናበትኩት።

ካፒቴኑ ድምፅ ሲያሰማ ከድንኳኑ አየወጣሁ ነበር። "እኔ የምለው፣ ከኛ ጋር በምግብ ሥፍራችን መመገብ ትችላለህ። በዚህ ካምፕ ውስጥ እሰካለህ ድረስም ራሰህን የከብር እንግዳችን አድርገህ መቁጠር ትችላለህ? የተከበሩ መልካም ለዎችም ታገኛለህ። የኮሚላሪያቱ ኤ፣ ቢ፣ ሽማግሌው መርከበኛ፣ አሁን የማረፈያው ወደብ ሀላፊ፣ ከሶስተኛው ቀላል ፈረሰኞች ደግሞ፣ ሲ አለ። ከዝሆኖች አዝ በኩል ደግሞ ዲ፣ በመጨረሻም፣ ከቦምቤይ ከፍል ኢ አለ። ባከህ ና፤ ትመጣለህ? ርግጠኛ ሁን! አራት፣ ከምሽቱ ሰስት ሰአት፤ ታ-ታ[3]፣ ጓደኛ"

"በርግጠኛነት፣ ውድ ካፒቴን፣ በደለታ ነው የምቀበለው። አርቧር። ታ-ታ ጓደኛ፣" በማለት የዚያን ምለጉን ሜጀር ካምፕ ቦታ ለማግኘት ወጣሁ።

የሜጀሩ ድንኳን፣ ከካፒቴኑ ድንኳን የአንድ ሙሉ ማይል[4] ርቀት አለው። ወደ ሰፍራው ለሄድም፣ በአለቸጋሪ ሁኔታ፣ በሙቀት የጋለው አሸዋ ጫማዬን እያቃጠለው፣ ነፋሱ ከሙቀቱ ጋራ ፊቴን ሲገርፈው፣ የትሮፒካል ወይም የበረሀ ኑሮ ችግርን ምን አንደሚመስል ተገነዘብኩ። ከበረሀው ሙቀት ሥቃይ ለመተንፈስ ቀዝቃዛ መጠጦችን በየጊዜው ለሚጎነጨው ለዚያ ጀግና ካፒቴንም አዘንኩኝ።

ወደ ሜጀሩ ድንኳን ለገባ፣ መምጣቴን ለማስታወቅ ሳል ጀመርኩ። ይህም፣ ፊቱ በፂም የተሞላውን ሰው አይን ሳበልኝ። ወደኔ እየመጣም፣ ሌንሱ ወፈር ያለ የአይን መነፀር አይኑ ላይ እያስተካክለ፣ በጥያቄ መልክ ተመለከተኝ። ለዚህ ድምፅ አልባ ጥያቄ ለመመለስም፣ ማን አንደሆንኩ ራሴን አስተዋውቄ፣ የመጣሁበትን ጉዳይም በመግለፅ፣ የያዝኩትን፣ ተቀበሎ በጥንቃቄ የተመለከተውን ደብዳቤ አሳረከብኩኝ። ደብዳቤውን በርካታ ከተመለከተ በኋላም፣ ከፊቱ ላይ በሚነበብ ውጥረት በመላበት አጠያየቅ ምን

[3] የአነጋገር ዘይቤ

[4] አንድ ማይል 1.61 ኪሎ ሜትር ነው

እንደምፈልግ ጠየቀኝ። "ብራንዲና ሶዳ፣ ቸሪ ብራንዲ፣ ፖርት ወይን፣ የሎሚ ጭማቂ?" እነዚህን የመሰሉ ርካታ የሚሠጡ መጠጦች፣ በአንግዳ ተቀባዩ ለሰለስ ባለ አንደበት ሲጠሩ መሰማት ብቻ፣ በሙቀት ብዛት አአምሮውን የሳተ መንገደኛን መልሶ ያነቃል።

ሥልጡኖቹ አገልጋዮቹ፣ ገና የለውየውን ድምፅ ከመሰማታቸው፣ የተጠሩትን መጠጦች በማቅረቢያ ሰህን ይዘው ወደ ውስጥ መጡ። ሜጀሩ፣ አሜሪካዊነቴን በመገንዘብ ግማሽ ብርጭቆ የሚሆን ብራንዲ ወደኔ መጠጫ ሁዳልኝና ላዩ ላይ ቀዝቃዛ ሶዳ ውሀ ሞላበት። ከሜጀሩ ጋርም ለጤና ተባብለን መጠጫችን አጋጨን። ቀጥሎም፣ መተኪያ የሌለውን የአይን መነፀሩን በጥንቃቄ ቀኝ አይኑ ላይ እያስተካከለ ስለ አሜሪካ ሁኔታ ይጠይቀኝ ጀመረ። "መልካም ነው። እኔ እንኳን ፈኒጋን[5] ነበርኩ ነገር ግን ቴዎድሮስን ለማገልገል አዚህ ድረስ መጥቻለሁ።" በማለት፣ በታቸለኝ አቅም በቀልድ መልክ መለለኩለት። ሜጀር ኤክስ፣ ባህሪው ፈጠን ያለ ቢሆንም ከአይን መነፀሩ በስተቀር አንክን የሌለው ትልቅ ሰው ነው። በህንድ አገር ታዋቂ ነው። "ኑሮ በጫካ" የተባለው ሰዕሉ የተዋጣለት የሥነ ጥበብ ሥራ ነው።

ከሰአት በኋላ፣ የኔ ድንኳን ከካፔቴን ዚ ድንኳን አጠገብ ተተከለ። አገልጋዬ አሊም ለአምስት ቀናት የሚሆን ራሽን አንዲያመጣ ተላከ። በነጋታውና ጥዋት፣ ወደ ግንባር ለመሄድ አስቤያለሁ። የጓዝ በቅሎ ከኮርቻ ጋር ተሠጠኝ። በዚህም ምክንያት ጉዞዬ ምቾት ያለው ይሆናል ብዬ ተሰፋ አደረኩኝ።

አሜሪካ ብሆን ኖሮ፣ ወይም አውሮፓ ያለ ሠራዊት የምከተል ብሆን ኖሮ፣ ሁኔታው የተሻለ ይሆን ነበር። አፍሪቃ ውስጥ ግን የተለየ ነው። ከለህተቴ የነቃሁት፣ ከአንግሊዝ ወታደሮች ጋር ዘመቻ ለመሄድ መወለኔና ለዚህ ቦታ የሚመች ልብስ አለማወቄን የተገነዘብኩ ጊዜ ነው።

"አኔ የምልህ፣ ሰውየው!" ካፒቴን ዚ ነበር ወደኔ የተጣራው። "ነገ መንገድ ልትጀምር ነው?፤ አንዴት ነው ፈረስና አገልጋዮች የሉህም አንዴ?"

"መልካም፣ ውድ ካፒቴን፣ ራሴን በደንብ አላዘጋጀሁም። አዚህ ከመድረሴ በፊት የሚያሰፈልገኝን ነገር አላወቅሁም ነበር። አሁን አንደማየው ግን የሁሉም ነገር አጥረት አለብኝ።"

"በፈጣሪ፣ ያማ የሚሆን አይደለም፤ ታውቃለህ። አዋቂ ሰው የአስፈላጊ ነገሮች አጥረት ሊኖረው አይገባም። ለንት አገልጋዮች አሉህ?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አንድ ብቻ ነው ያለኝ።" በማለት በህፍረት መለስኩ።

[5] የአየርላንድ ተወላጅ ነኝ ለማለት ይሆን?

"የፈጣሪ ያለህ! አንድ ብቻ፣ ለንትለ ፈረሶች አሉህ?"

"አንድ ፈረስና አንድ በቅሎ፤"

"ፐ ፐ፣ ያ አንኳን የሚያዋጣ አይደለም። የሚያስፈልግህ ነገር፣ ወጥ ሠሪ፣ ፀጉር አስተካካይ፣ (ኩቻ ዋላ)አስተናጋጅ፣ (ፓኒ ዋላ)ውሀ ተሸካሚ፣ በተጨማሪም የግል ጓዝህን የሚሸከም እንድ ፈረስ፣ የምግብ ማብሰያ ዕቃዎችህን የሚሸከም እንድ ፈረስ፣ ድንኳንህን የሚሸከም ሌላ ፈረስ፣ እና አንተ የምትጋልባቸው ሁለት ፈረሶች ያስፈልጉሃል። እነዚህ ሳይኖሩህ አዚህ ሀገር መኖር ያስቸግራል። በተጨማሪም ሰዎች ዝቅ አድርገው ነው የሚመለከቱህ፤ ታውቃለህ አይደል?" በተመሠጠ አስተያየት ተናገረኝ።

"ያም ሆነ ይህ፣" የቀረ ንግግሩን ሲጨምር፣ "መከበር ከተፈለገ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ነገሮች ሊኖሩህ ይገባል።"

"በርግጥ?" እልኩኝ፤ የግድ፣ የራሴን የመከላከያ ሀሳብ መስጠት ይኖርብኛል በሚል ስሜት፣ "ከዚህ በፊት ብዙ ጉዞዎችን ተሳትፌያለሁ፤ ብዙ የጦር ዘመቻዎችንም ተከትዬ ሄጀለሁ፤ ከነዚህ ቀደም ካሉ ጉዞ ልምዶች አንዳየሁት፣ የምፈልገውንና መያዝ የሚገባኝን ነገር ያወቅሁ መስሎኛል። ወደ አቢሲኒያ ለመምጣት ስነሳ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር አንድ ቦታ ላይ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ አልመሰለኝም፤ አንዲያውም፣ በተቻለ መጠን ዘመቻውን በፍጥነት የሚቀጥል ነው የመሰለኝ፤ በዚህ ሁኔታ ትርፍ ጓዝ መያዝ ለአንድ ሰው የሚያጓትት ነገር ነው።"

"እሃ፣ አያስፈልጉኝም የምትለው አንድ አሰራ ሁለት እገልጋዮች፣ ወደ ሰድስት የሚሆኑ ፈረሶች፣ ላንተ ብዙ ናቸው ነው ወይ?፤ አንደዚህ የምታስብ ከሆነ ለለ ሀገሩም ሆነ ለለ እንግሊዝና ህንድ ጥምር ሠራዊት እና ለለሚያስፈልጉት ነገሮች እውቀቱ የለህም።"

የኋለኛው ንግግር አንኳን ማታ ራት ላይ የተለዋወጥነው ነበር። ቀን፣ ካምፑ ውስጥ አንዳስተዋልኩት ከሆነ፣ በርካታ አገልጋዮች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ። አንደ አንግሊዞቹ የህንድ አኗኗር ከሆነ፣ አነዚህ እገልጋዮች በጣም አለፈላጊ መሆናቸውን አንድ ሰው መረዳት ይችላል። ለእገልጋዮቹ ቁጥር መበርከት ሌላው ምክንያት ደግሞ፣ የህንድ አገልጋይ ሲቀጠር፣ ለአንድ አይነት ሙያ ብቻ ይሆንና፣ ሠራተኛውም ያችኑ ሥራውን ብቻ ስለሚሠራ ነው። ለምሳሌ፣ የፈረሶች ባልደረባ፣ የግልቢያ ፈረሶችን መንከባከብና ማዘጋጀት ነው ሥራው። ሁሉም አንደ አቀጣጠራቸው፣ ውሀ አቅራቢው ውሀ ማቅረብና መሸከም፣ ፀጉር ቆራጩ ቢበዛ ሣር ቢያጭድ ነው። አነዚህ ሠራተኞች እያንዳንዳቸው፣ አንዱ ያልተቀጠረበትን የሌላውን ሥራ ቢሠራ አንደ ነውር ነው የሚቆጥሩት።



የአርምስትሮንግ መድፎች ሲጫኑ



የተራራ ከባድ መሳሪያዎች ሲጫኑ

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ 16)



እንግዲህ ለነዚህ የአንግሊዝ ወታደሮች በዚህ በዙላ አሸዋ ላይ መስብሰብ ምክንያት የሆኑ ነገሮችና ሁኔታዎችን መግለፅ ከርዕሰ ውጭ አይሆንም።

በአቢሲኒያ ለብዙ አመታት ከትውልድ ትውልድ እየተቀባበለ የሚነገር ትንቢት ነበር፤ ይህም ትንቢት እየጠነከረ በመምጣቱ፣ የህገሩ ተወላጆች ወቅቱና ጊዜው ደርሷል በሚል አምነት የተነገረለት አዳኝ ሰው መምጫው አሁን ነው በማለት መጠበቅ ጀመሩ[6]። ይህን ትንቢት፣ ካሳ የተባለ ልቡ ትልቅ የሆነ ወጣት፤ ባሏ የሞተባት፣ ከደምቢያ ወደ ምዕራብ በኩል ቋራ በሚባል ቦታ የምትኖር፣ ኮሶ ሻጭ ሴት አንድ ወንድ ልጅ መስማት ጀመረ። ይህ ትንቢት በየቀኑና በየወሩ በጆሮው ይወርድ ጀመር። በህልሙ ሆነ በገሀድ፣ ይህ ትንቢት ይከነክነውና ያሳድደው ጀመር። በመጨረሻም፣ ኢየሩሳሌምን ከሙስሊሞች ለማዳን የተመረጠው ለው አሱ ራሱ ነው የሚል አምነት አደረበት።

ትንቢቱም እንደዚህ ነበር።

“በኢትዮጵያ የስለሞን ሀረግ ወይም ትውልድ ያለው ንጉሥ ይነግሣል። በምድር ላይም ታላቅነቱ ይታወቃል። ሀይሉም በኢትዮጵያና በግብፅ ላይ ይንሰራፋል። አረመኔዎችን ከፍልስጥኤም ጠርጎ ያወጣል፤ ኢየሩሳሌምንም ከደፈሯት ሰዎች ያነፃታል፤ ሰሙም ቴዎድሮስ ይባላል!”[8]

ካሳ፣ የደምቢያው ገዥ የደጃች ከንፉ ቤተሰብ ስለሆነ ትምህርት እንዲማር ይደረጋል። ዝምድና ባይኖረው ኖሮ ምንም ማዕረግ ለሌለው ለዚህ ወጣት ይህ አይነት ዕድል ባላጋጠመው ነበር። ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ[9]፣ በዚያ ጊዜ በማንበብና መፃፍ የተወሰነ ብቻ ነበር[10]፤ በደጃች ከንፉ ጦር ሥር ለማገልገል ይመለመላል። ይህም በፍጥነት ዕድገትና ማዕረግ እንደሚያስገኝለት ቃል ስለተገባለት ነው። ወዲያውኑ፣ ትልቅ ችሎታ አንዳለው ግልፅ መሆን

[6] ህዝቡ ይህን አይነት ትንቢት የተቀበለበት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[7] አፄ ቴዎድሮስ፣ ባባታቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[8] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[9] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[10] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ጀመረ። የጦር ችሎታው፣ የደጃች ከንፉን የጋለ አድናቆትን አተረፈለት። ከንፉም የሻምበልነት ማዕረግ በመሥጠት፤ የሚተማመኑበትና የሚያምኑት ተከታያቸው አድርገው ወሰዱት[11]። ጀግንነት፣ በጠንምድርና በአካባቢው ግዛቶች በተደረጉ ከባድ ፍልሚያ ቢታየባቸው ዘመቻዎች፣ በፍጥነት የጦር ሜዳ ሠይም የውጊያ አሰላለፍ የመገንዘብ ችሎታው ዕድገቱን በጣም አፋጠነለት። ይህ ችሎታውም የነበረውን ገዥ[12] ከብር ስላለገኘለት፤ ገዥው ሴት ልጁን በመዳር የወረዳ ገዥነት ማዕረግ ሠጠው።

በጥንቃቄና በታማኝነት ካገለገለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፤ ካሳ በድንገት ከገዥው ጋር በመጣላት ጦርነት ያውጃል።

በደጃዝማች የሚመራ ጦር አመፀኛው ካሳ ላይ ይዘምታል። ሆኖም፣ ከሀይለኛ ውጊያ በኋላ ጦራቸው ተሸነፎ ብዙ ሰዎች ያልቃሉ፤ ራሳቸው ደጃዝማቹም በካሳ እጅ ሕይወታቸው ያልፋል። ካሳም፣ ከዛ በኋላ እንዳንድ መንገደኛ ፀሐፊዎች እንደሚጠቅሱት፣ ወደ ስልሳ ሺ የሚሆኑ ተከታዮችን ይዞ ወደ ጎንደር ይገሰግሳል። የከተማው ኗሪዎችም ያለ ምንም ደም መፋሰስ ለአዲሱ ባለጉልበት ከተማውን ያስረክባሉ። ከዚህ ድል በኋላም የጎንደር ገዥነቱን አስታውቆ፤ ያሠለጠናቸውን ወታደሮቹን በማዝመት የአካባቢ ግዛቶችን አንድ በአንድ በማንበርከክ በተሸነፉት ገዥዎች ምትክ የራሱን ታማኝ ሰዎች፣ የጦር መኮንኖቹን መሾም ጀመረ።

በጦርነት ላይ ባሳየው ጀግንነትና[13] ድንቅ በተባለ ፍጥነቱ፤ በዘመኑ በእንዳንዶች፣ ከፈጣሪ አንደተሠጠ ችሎታ በመቆጠሩ፤ ካሳ በገዥነቱ ወንበር ላይ ራሱን አደላደለ። ከአንድ ሙሉ አመት ሰላም በኋላ፤ ካሳ ተከታዮቹን በውትድርና ካሠለጠነና ለጦርነት እንዲዘጋጁ ካደረገ በኋላ፤ ከበጌምድሩ ገዥ ጋራ የሚጣላበት ሰበብ ያገኛል። ወደፊትም ጦሩን ያዘምትና በዚህ ተራራማ በሆነ ግዛት ተደጋጋሚ ድል ይቀዳጃል። በገዥው ስር የነበሩ የበጌምድር ወታደሮችም ድል ተመተው በካሳ ሰይፍ እጅ ይወድቃሉ። ገዥው ግን በካሳ ትዛዝ ለአስር ይዳረጋል[14]። የዚህ ድል ወሬ በየቦታው ሲናፈስ፤ የአጎራባች ገዥዎች ካሳን የጋራ ጠላት ያደርጋሉ።

እነዚህ ቁጥራቸው የላቀ ጠላቶቹን ከመግጠሙ በፊት፣ የራሱን ጦር በሚገባ ያጠናከራል። ከንጉሥ ሰለሞን የዘር ሀረግ በመጥቀስ ራሱን

[11] ከንፉ፣ ካሳን የልጆቻቸው ጣውንት አደርገው ነበር የሚቆጥሩት። አዋቂ ሲጠየቅ የሚወርሰው ካሳ ነው እንጂ ልጆችህ አይደሉም ብሎ ነግሯቸዋል ይባላል።

[12] ትንሹ ራስ አሊ (ተዋበችን የሰጡት አያትየዋ ወይዘሮ መነን ናቸው)

[13] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[14] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ቴዎድሮስ፣ በተወላጆቹ አጠራር ቴድሮስ[15]፣ ብሎ በመስየም ትንቢቱ የተነገረለት የመሐመዳን መንግሥቶችን ጠርጎ የሚያጠፋው አዳኝ አሱ አንደሆነ ያስነግራል::

ይህ አዋጅ ግን አሱ ካሰበው በላይ ትልቅና ሰፊ ተፅዕኖ ፈጥሯል:: ተዋጊዎች፣ በየአካባባዊ የነበሩበትን ጦር አየከዱ፣ ወደፊት የሚመጣውን የቴዎድሮስን ድል በማለብ፣ በሱ ስር ለመዋጋት በገፍ መቀላቀል ጀመሩ:: ይህ ትልቅ ሀላብ በቴዎድሮስ ሲነገር ሲሰሙ፣ ጠላቶች የሆኑት ገዥዎች በመሳቅ አንደፌዝ ይቆጥሩት ጀመር:: ነገር ግን አየከዳቸው በሚሄደው የራሳቸው ሠራዊት ምክንያት ርቃናቸውን መቅረታቸውን ሲረዱና በስላዮቻቸው አማካኝነት በሚያገኙት መረጃ ምኞቶ ሩቁ ጠላታቸው ሀይሉ አየተጠናከረ መምጣቱን ሲገነዘቡ ሹፈቱን ቀየሩ:: አንዳንዶቹ መሳሪያቸውን አውርደው በስላም ገባሪነታቸውን አሰታወቁ፤ አንዳንዶች ደግሞ፣ ፊት ለፊት መጋጠም የወለኑት፣ ተራ በተራ ድል አየተመቱ በሕይወት የተረፉት የቁም መቃብር በሆነው በጌምድር ተራራ እሰር ቤት ከበጌምድሩ ገዥ ጋር ተደረቡ:: አንድ ባንድ አያንዳንዱ በአቢሲኒያ የሚገኝ ግዛት ከትግራይ[16] በስተቀር ለቴዎድሮስ ተገዥ ሆነ:: ከዚህ ድል በኋላ ራሳቸውን ዳግማዊ ቴዎድሮስ ስዩመ አግዚአብሔር በማለት አወጁ[17]:: ይህ የሆነው አንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1853 ነው::[18]

ራሳቸውን የድፍን አቢሲኒያ ገዥ ሲያደርጉ የለላሳ አምስት አመት ጎልማሳ ነበሩ:: በዚህ ዕድሜ፣ ጠንካራ ሰውነት[19]፣ አንደ ግሥላ ፈጣን፣ አንደ አንበሳ ደፋር፣ የተወደዱና፣ በሁሉም ተዋጊ ወታደሮች ዘንድ በፍቅር የሚታዩ ሰው ነበሩ::[20]

በታሪከና በልምድ ስላለፉት መንግሥታት የተማሩትን፣ ራሳቸውም በልምድ የደረሱበትን የኢትዮጵያ ነገሥታትን የውስጥ ሽርና አደጋ በማጤን የጎንደር ቤተመንግሥትን ኑሮን መጥላት ጀመሩ:: ለራሳቸውም "መናገሻ ከተማ አይኖረኝም፤ ራሴ መንግሥት ይሆናል፤ ድንኳኔም መናገሻ ይሆናል::" ብለው ወለኑ::

[15] ስለ ንግሥና ስማቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[16] ቴዎድሮስ ትግራይ ላይ ያልዘመቱት፣ የሰሜኑን ገዥ ደጃች ውቤን ድል በማድረጋቸው ፣ በውቤ ስር የነበረው ትግራይ በእጃቸው ስለወደቀ ነው::

[17] ከዚህ በኃላ እንደአግባቡ አርሳቸው ማለት ተገቢ ነው::

[18] ሰኔ ሀያ ሶስት፣ 1845 (አአ)(በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[19] ስለ ሰውነታቸው ጥንካሬ ሲነሳ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[20] ቴዎድሮስን ተወዳጅ ሊያደርጓቸው የቻሉ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ያላቸው የተፈጥሮ ብልህነትና የወታደራዊ ችሎታቸው በየጊዜው ሃተኝሥትን አመፆች ፀጥ ማድረግ አስችሏቸዋል:: የአሮሞ አመፀኞች[21] በየጊዜው ድል ተመተዋል፤ ነገር ግን በአንድ ቦታ ሰከነው የማይቀመጡ ስለሆነ፤ የተቀዳጇቸውን ድሎች ውጤት አላሳመሯቸውም:: ስማቸው ግን የጣፈራ ሆነ:: በስማቸው ብቻም ስላም የመፍጠር ችሎታ እንዲኖረው ተጠቀሙበት::

ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ተጋበዙ፤ የአጅ ባለሙያተኞች ደግሞ እንዲበረታቱ ተደረገ:: [22]የአውሮፓ ባለሙያተኞች ስለዚህ ዕደገት ፈላጊ ሰው ሲለሙ ወደ ጎንደር ይጎርፉ ጀመር፤ በጎንደርም ቅጥር ሥራ(ባለሟልነት)፤ ሥረቤታና ሀብትም ይሠጣቸው ጀመር:: የጦር ሙያተኞች ከሆኑ ደግሞ የተለየ እንክብካቤ ይደረግላቸው ነበር:: ብዙዎቹም ሀገሪቷ ውስጥ እንዲኖሩ የተጋበዙ መንገደኞች ነበሩ::

ቆንስል ፕላውደን[23]፣ የቅርብ ወዳጅ ስለነበር ከቴዎድሮስ ጋር ለአምስት አመታት አብሮ ኖሯል፤ በዚህ ጊዜ፣ ንጉሡ በተቻላቸው አቅምና በሚቻለው መንገድ ሁሉ ሀይላቸውን ያጠናከሩበትና መንግሥትን ያደራጁበት ጊዜ ነበር:: ምንም እንኳን በጊዜው ከራሳቸው ለዎች የላቁ ዘመናዊ ወታደር ቢሆኑም፣ ባገኟቸው ድሎች ተጠቅመው የሀገሩን ተወላጆች ፍላጎት[24] ማሟላቱን አላወቁበትም ነበር:: አንዱን ግዛት ሲያሰገብሩ ሌላው አያመፀ፤ በማያባራ ጦረነት ተወጠሩ፤ ይህም ቀስ በቀስ የነበራቸው ባህሪ አንዲለወጥ አስገድዷቸዋል:: በሙሉ ልብ፣ ያለማሰለስ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ጥረትና ድካም ከምንም ያልቆጠሩት ምስጋና ቢስ ሰዎቻቸው ላይ የመረረ ስሜት ፈጠረባቸው::[25]

ጥቂት ሞስኮቦችና የጀርመን መሐንዲሶችም ወደ ሀገሪቱ በመግባት ባለሟልነት ጠየቁ:: መስራት የሚችሏቸውን ትልልቅ መድፎችና መተኮሻዎች በነገሯቸው ጊዜም፣ በአእምሯቸው የሚያስቡትን የግብፅ፣ የፍልስጥኤምና የአረብ አገሮችን ማሸነፍ የሚችሉበት ጊዜ አየተቃረበ መጥቷል በሚል አምነት በሀሲናቸው አንዲስሉ አደረጓቸው:: በሌላ አነጋጋር፣ አኒህ ድንቅና ሩቅ አላሚ

[21] አመፅ ከተነሳ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[22] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[23] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[24] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[25] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ንጉሥ እነዚህን አስደናቂ መሣሪያዎች ካገኙ ምኞታቸው እንደሚሳካ በማመን ወዲያውኑ ከመሐንዲሶቹ ጋር ተስማሙ::

ትልልቅ የባሩድ ማምረቻ ቦታዎች ተገነቡ:: የግሪክ ነጋዴዎች ለንጉሡ ጠመንጃ ገዥ እንዲሆኑ ተደረገ፤ የመድፍ መሥሪያ የሚሆኑ ማቅለጫዎች[26] ተሠሩ፤ ሁሉም ነገር ስላቸው ብልፅግናና ተስፋ በሚሠጥ መንገድ ተዋቀረ::

ቴዎድሮስ፣ የግብፁን ገዥ እንደ ዋነኛ ጠላታቸው አድርገው ነው ያዩት[27]:: ወራሪነትና ጠብ አጫሪነት በግብፆች በኩል ተደጋግሞ ነበር የሚፈፀመው:: ግብፆች የግረኳቸውን ኢትዮጵያውያኖች ደግሞ ወደ ናይል በመውሰድ በካይሮና በእስክላንድርያ ለሚኖሩ ፓሻዎች በባርነት ይሸጡ ነበር:: የቀሩትንም በመርከብ ወደ ሩቅ ወንድሞቻቸው ወደ ኮንሰታንቲኖፕል ይልኳቸው ነበር:: በግብፆች የተፈፀሙት በደሎች እነዚህ ብቻ እልነበሩም:: ይህንንም፣ ቆንስሉ ፕላውደን፣ በታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤት እንዲታወቅ አድርጓል::

ፕላውደን ለቆንስላነት ሲሾም በግልፅ መታወቅ ያለበት ነገር ሹመቱ ሰእቢሲኒያ ነው የነበረው፤ ስሰዚህም አቋሙ ከግሸው ንጉሥ ጋር ነው የነበረው:: ገዥው ንጉሥም አፄ ቴዎድሮስ ሆኑ:: በነበረው በጎ ሀላብና፣ በእንግሊዝ መንግሥትና በቴዎድሮስ መካከል ግንኙነትና ወዳጅነት ለመመስረት ብርቱ ፍላጎት፣ የቴዎድሮስን ፍቅርና መልካም አስተያዬት ሊያገኝ ችሏል:: በመሀል ኢትዮጵያ፣ የሱ ስራ የነበረው ከውጭ የሚመጣውን ሸቀና ተንከል መክታተልና ማከሸፍ፤ የባሪያ ንግድን ማስቆምና በተቻለው መጠን ንግድ እንዲስፋፋ ማድረግ ነበር:: ክእነዚህ ግቦቹ ሰመድረስ ቴዎድሮስን ወደ እንግሊዝ አገር አምባሳደር አንዲልኩ ይወተውት ነበር:: በዚህም ልዑካኑ በሁለት አገሮች መሀከል የንግድ ግንኙነት መፍጠሩ ሲኖረው የሚችሰውን ጥቅም በቀጥታ እንዲያዩ አስቦ ነው:: እዬው ግን በማያባራ ጦርነት ስስተጠመዱ የዚህን ጉዳይ ራሱ ፕላውደን ተክታትሎ እንዲያስፈፅም ሀላፊነት ሰጡት::

ቆንስል ፕላውደን ግን እንደ እውሮፓ አቆጣጠር በ1860 ወደ ምፅዋ በሚጓዝበት ጊዜ በሽፍቶች ተገደለ[28]:: ቴዎድሮስ መሪር ሀዘን ተሰምቷቸው የቆንስላውን ገዳዮች በቅጣት ተበቀሉ:: ለቆንስላው ባሳዩት ደግነት፤ የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ የተለያዩ ሥጦታዎችን የላክች ስትሆን፤

[26] ቴዎድሮስ ማቅለጫዎቹን ሲነበኙ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[27] ቴዎድሮስ፣ ቱርኮችንም ሆነ ግብፆችን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[28] ቆንስላው የተገደለው በጋረድ ክንፉ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ከስጦታዎች አንዱ ሽጉጥ ነበር:: በሽጉጡም ላይ እንዲህ የሚል ፅሁፍ ተቀርፆበት ነበር:: "ለእቢሲኒያ ንጉሥ ለአፄ ቴዎድሮስ፣ ለእግልጋዩዋ ሰነላውደን ለተደረገለት ደግነት፣ ከቪክቶርያ፣ የእንግሊዝና የእየርላንድ ንግሥት የተሠጠ፣ 1861" ይህ ሥጦታ የተላከው በፕላውደን ተከታይ በካፒቴን ካመሬሩን አማካኝነት ነበር:: ካሜሩን የተከበረ ስውና ከዚህ ቀደም በንግስቲቱ ሥር በካፒቴን ማዕረግ በህንድ ሲያገለግል የነበረ ነው::

ቴዎድሮስ መድፍ የመስራት እላማቸውን[29] በመከተላቸው፤ እንድ በእነድ እያሉ መድፎቹ ከማቅለጫው እየተስሩ ይወጡ ጀመር፤ በሚፈተሹበትም ጊዜ የቴዎድሮስን ያልተገደበ ደስታ በሚያስገኝ ሁኔታ እስፈሪ የሆኑ የውጊያ መሳሪያዎች ለመሆናቸው በሚያስሙት ድምፅና ክሰፈው እፈሙዛቸው በሚወረወሩት ትልቅ እሩሮች ተረጋገጠ:: በርግጥም በነዚህ ዮኮረገሙ ግብፆች ላይ ጦርነት የሚከፈትበት ቀን እየቀረበ መጣ::[30]

ግብፅ በአባስ ፓሻ ስር እያሰች በጣም ድሃና ስርእት ያጣች ሀገር ነበረች:: ሰያድ ፓሻ ወደ ዙፋኑ በወጣበት ጊዜ ግን ሁኔታዎች ሁሉ ተሻሽለው በጊዜው ዘያለኛ ሀገር ለመሆን በቅታለች::

በየካቲት 9፣ 1862 እኤአ፣ እዲሱ ቆንስል ካፒቴን ካሜሩን ወደ እቢሲኒያ በመምጣት ከንጉሡ ፊት ቀርቦ የተሾመበትን ደብዳቤ አቀረበ፤ የተሻለም የሆነው ይዞ የመጣቸውን ሥጦታ ሲያበረከት ነበር:: ቴዎድሮስ ንጉሣዊ ልብስ እነደለበሱ፣ ከተሰያዩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ነበር የተቀበሉት::

ለፕላውደን አንደተደረገው፣ ተመላላይ ቀረቤታና ወዳጅነት ለካሜሩንም ተሠጥቶት ሁሉም ነገር ስጊዜው በስላም ቀጠለ:: ወድያውኑም፣ ሚሲዮናውያኑ ቄሶቹ፣ ሚስተር ስተርንና ሚስተር ሮዘንታልም ተከትሰው ሰመጡ፣ ተመሳሳይ አቀባበልና እቀራረብ ተደረገላቸው:: ሌሎች ሚሰዮናውያንም ቀስ በቀስ መግባት ጀመሩ፤ እነዚህም ክስክትላንድ ሚሲዮን እና ክርስትናን በአይሁዳውያን ከሚያስፋፉ ማህበራት አባሎች ነበሩበት:: እነሱንም ቢሆን፣ ንጉሡ በመልካም ሁኔታ ነበር የተቀበሏቸው::

በዚህ ጊዜ ግን የንጉሡ ጭካኔ እየጨመረ መጣ:: በየግዛቱ የሚነሳው አመፅ ህይወታቸውን መሪር እንዲሆን ሲያደርገው፤ መላ ተፈጥሯቸውን ወደ ጭካኔና ሀይለኝነት እንዲቀየር አደረገው:: ትዕግስት ማጠርና ግንፍልነተኝነት ዛና ባህሪ እየሆኑ መጡ:: በዚህም ምክንያት የቅጣቱ አይነትም ክረር እያለ

[29] አፄ ቴዎድሮስ በተፈጥሯቸው ፈጠራም የሚወዱ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[30] ቴዎድሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመዝመት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

መጣ። የከዱ ለዎች ግንባራቸው ላይ ምልክት ይደረግባቸው ጀመር፤ ሌሎቹንም በአደባባይ መሬት ላይ አለተኝቶ በጦር መውጋት ተጀመረ።

እገር ወይም መሪዎችን የሚከዱን ሰዎች ክፍተኛ አሰቃቂ ቅጣት መቅጣት[31] በታሪክ በሠለጠነ በሚባለው የአለም ክፍልም የተለመደ ነው፤ የቴዎድሮስን የተለየ የሚያደርገው፣ ቅጣቱ፣ ንፁህን ለዎችንም ስለሚጨመር ነው። ቅጣቱ እየከፋ በመምጣቱ በጅራፍ የሚገረፈው፣ በጥይት የሚደበደው ሰው ቁጥር እየጨመረ መጣ፤ በዚህ ምክንያትም ሰማቸው በዜጎቹ ዘንድ መጠላት ጀመረ።

የእንግሊዝ ቆንስላ ወደ እቢሲኒያ ከመምጣቱ ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ ሎርድ ራለል[32] በኢየሩሳሌም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ገዳማት የነበረውን የእንግሊዝ ጠባቂነት አነሳ[33]። እንግዲህ በዚህ ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ወጭ እያወጣ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር ወዳጅነት ለመመሰረት ልዑካን በሚልክበት ጊዜ ራለል ግን ተቃራኒውን ነበር ያደረገው።

አዲሱ ቆንስላ ካሜሩንም የቀደሙን ቆንስላ ዱካ በመከተል፣ በሁለቱ እገሮች፣ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መንግሥት የወዳጅነት ውል ወይም ለምምነት እንዲፈጠር፤ በተጨማሪም ወደ እንግሊዝ ንግሥት እምባሳደር እንዲላክ ንጉሡን ይገፋፋ ነበር።

በመጨረሻም ቴዎድሮስ ለጉዳዩ ግንዛቤ መለጠት ጀመሩ። ለንግሥት ቪክቶርያም ደብዳቤ ላኩ። በደብዳቤውም የተለመደው የኢትዮጵያ ነገሥታት መግቢያ ፅሁፍ በኋላ፤ ቱርኮችን(ግብፆችን) ለማጥቃት ያላቸውን ሃሳብ ግልፅ እደረጉ። ይህም፣ እነዚህ ጠላቶቻቸው ያለምንም ለበብ ኢትዮጵያውያን ላይ፣ ቦሳ የሚባል ቦታ ጥቃት በመፈፀማቸው፤ ምክንያት የሌላቸውና ህጋዊ ያልሆኑ በተደጋጋሚ[34] የሚያደርጓቸው ወረራና ጥፋቶች፤ ሌሎችም ተጨማሪ ጥቃቶችን በማካተት ነው። በዚሁ ደብዳቤም፤ ተስፋው ለሁለቱም እገሮች ጥቅምና ዝና በሚፈጥር ሁኔታ፣ በሁለቱ እገሮች መካከል ዘላቂ የሆነ ወዳጅነት እንዲኖር ምኞታቸው እንደሆነ በመግለፅ፤ ንግሥቷ የላቸው እምባላደሮች ወደ እንግሊዝ አገር የሚመጡበትን ሁኔታ እንዲዘጋጅ እንድታደርግ በመጠየቅ፤ በተቻለ ፍጥነት ትውውቅ ለማድረግ ሁሉም ነገር ዝግጁ እንደሆነ፤ ልዑካኑም ወደ ባህር ወደብ እንደሚላኩ ነው።

[31] ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[32] ሎርድ ራለል የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒሰትር (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[33] በዚህ ምክንያት በኢየሩሳሌም ገዳማት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[34] የባርካ ነዋሪዎች(በግብፅ ስር) (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ቆንስል ካሜሩን ይህን ደብዳቤ እንደያዘ ወደ ምፅዋ በሚሄድበት ጊዜ በእንሄድ ሽፍታ መሪ ቢያዝም በስውር በሀገሩ ተወላጆች በኩል የንጉሡን ደብዳቤ ማሳለፍ ችሏል።

ደብዳቤውም፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የካቲት 1863 በስላም ሎንደን ይደርሳል። ደበዳበቤውን የተቀበለው ራለል፣ ክፍቶ ካነበበ በኋላ ጠረጴዛ ላይ ወረወሮ በመተዉ ምክንያት ደብዳቤው ፋይዳ ሳይሰጠው ያልሆነ ቦታ ተቀምጦ ቀረ።[35]

ቆንስል ካሜሮን ከእጭር ጊዜ እሰር በኋላ በሽፍቶቹ ተለቀቀ። ከዚያ ይኋላም የባሪያ ንግድ እንዳይኖር ወይም እንዲቆም ለፓሻዎች የእግር እሾህ እሰከሆነ ድረስ መታገሉን ቀጠለ። በዚህም ምክንያት መልክተኞችና ሰሞታ ከፓሻዎች፤ ወደ ራለል ይላኩ ጀመር። ለተሰማው ችግር፣ ለይድ ፓሻ፣ እጉዳሰናና ተደርጎ፤ ቆንስል ካሜሩን በቀጥታ ወደ ምፅዋ እንዲሄድና እዛ ሆኖ የቆንስላ ጉዳዮቹን ብቻ እንዲመለክት ይታዘዛል።

ብዙም ሳይቆይ በእሜሪካ የሚደረገው ጦርነት እንግሊዞችን እያሰባቸው ሰስመጣ፤ አዲሰ የጥጥ እርሻ በጉጉት የሚፈለግበት ጊዜ በመሆኑ፣ የውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤቱ ካሜሩን ወደ ሱዳን ሄዶ ሀገሩ ለጥጥ ምርት ያለውን ችስታና እመቺነት እንዲያጠና ትዛዝ ያሰተላልፋል።

የካሜሩን ወደ ግብፅ[36] ግዛት መሄድ በቴዎድሮስ በኩል የተለየ ትርጉም ነው የተሠጠው። በሚመለሰበት ጊዜም፤ አፄ ቴዎድሮስ በማፋጠጥ መልክ ካሜሩን የት እንደከረመ ይጠይቃሉ። ካሜሩንም ወደ ሱዳን ተልኮ የጥጥ እርሻና ንግድ ሁኔታ እንዲያጠና እንደተጠየቀ ምላሽ ይሰጣል። ቴዎድሮስም ከእነሂ እመት በፊት ለንግሥቲቱ ለላኩት ደብዳቤ ምላሽ ይዞ መጥቶ እንደሆን ይጠይቃሉ። ካሜሩን በእሱታዊ ሲመልስ ቴዎድሮስ በጣም ተናደዱ፤ እሃ! ንግስቲቱ ጠላቶች ወደሆኑት ወደ ቱርኮች ስትልክህ ምናልባትም በላቸው ላይ ሴራ እስባ ቢሆን ነው እንጂ እንዴት ለመሪ የሚገባውን ህጋዊ ደብዳቤ እትሰፍም፤ ስለዚህ የደብዳቤው መልስ እስኪመጣ ድረስ ካሜሩን መንቀሳቀስ እያችልም። በዚህ ምክንያት፣ በሐምሌ 1863 ካሜሩን እስረኛ ሆነ። ብዙ ሳያቆይ፣ ከፊረንሳይ መንግሥት መልስ መጣ።

[35] ይህ ሁኔታ የንቀት ብቻ ሳይሆን፣ እንግሊዞቹ በዚያን ጊዜ በሩስያ በኩል የነበረውን ፉክክርና ጉማሄ መሰፋፋት ለማስቆም የቱርክን እርዳታ ይፈልጉ ነበር። ስለዚህ ከቱርክ ጋር መጋጨት አልፈለጉም። ቴዎድሮስ የቱርኮች ጠላት ነበሩ።

[36] ሱዳን በግብፅ ፓሻዎች ስር ስትዳደር ነበር

የደብዳቤው ይዘት የሚያረካ ሰላልነበር የፈረንሳዮ ቆንሰላ መንሲንጀር[37] በአሰቸኳይ ከአቢሲኒያ አንዲወጣ ተደረገ። ከሶስት ወራት እሰራት በኋላ፣ ካሜሩን ከሎሮድ ራስል መልሰ ተላከለት።

ነገር ግን፣ በዕድሜ ገፋ ያለው ባለሥልጣን የረላው ትልቅ ነጥብ ነበር። በደብዳቤው ቴዎድሮስን ለለመጠየቅ የተገለፀ ነገር የለም፤ አንዲያውም የቴዎድሮለን ሰም የሚጠቅለ አንድ ቃል እንኳን አልነበረበትም። በጉዳዩ የበገኑት ቴዎድሮሰ የካሜሩን አገልጋይ እንዲደበደብ ትዛዝ ይለጣሉ። በዚህ ጊዜም የሚሲዮናዊው ሁለት አገልጋዮችም በከፉ ሁኔታ ስለተደበደቡ ማምሻውኑ ህይወታቸው አለፈ። በዚህ የተደናገጠው [38]ሚሲዮናዊ ሰተርን አፉን በአጁ ሲሸፍን ያዩት ቴዎድሮሰ የድፍረት ሰለመሳለቸው፣ "ይህን ለው መሬት ላይ ወርውራችሁ አንደ ውሻ ደብድቡልኝ" ብለው ትዛዝ ከመሰጠታቸው ወታደሮቹ ራሱን አሰኪሰት ድረሰ ደበደቡት። ከዚህ ከጥቅምት ወር፣ የሰተርን የረጅም ጊዜ አሰራቱ ይጀምራል።

የቴዎድሮስ ባለሟል የሆነ ባርደል[39] የሚባል ፈረንላዊ ነበር። ለአንግሲዞቹ ያለው ጥላቻ ከፍ ያለ ስለነበር የነዚህ ለዎች ወደ ህገር የመጡበትን አውነተኛ ጉዳይ ለማወቅ ሳጥኖቻቸውና ደብዳቤዎቻቸው እንዲፈተሹ ለቴዎድሮሰ ሃሳብ ይለግሳል።

ቴዎድሮሰ፣ ሁሉንም በአቢሲኒያ የሚኖር አውሮፓዊ፣ በተለይም አንግሲዞችን በጥርጣሬ ነበር የሚያዩት። የንግሥት ቪክቶርያ ለደብዳቤያቸው ምላሽ አለመሰጠት በነሰተርን ውከልና ምከንያት ነው፤ የፈረንላዩ አፄ ናፖሊዮን የምን ግዴ አፃፃፍ ደብዳቤም የአውሮፓ ሸር ነው፤ በማለት ነበር ቴዎድሮስ ሀላባቸውን የደመደሙት። አንደውነቱ ከሆነ አንደዚህ ለማለብ በቂ ምከንያት ነበር።[40]

በምፅዋ፣ የቆንስል ካሜሩን ምከትል ካፒቴን ቻርለሰ ሰፒዲ የሚባል ቁመቱ ስድሰት ጫማ ከሰድሰት ኢንች የሆነ ግዙፍ ሰው ነበር። ለአንድ አመት የሚሆን የቆንሰላ ሰራ ከሰራ በኋላ አርግፍ አድርጎ ትቶ፣ ዝሆን አዳኝ ለመሆን ወደ መህል አቢሲኒያ ይዘልቃል። ከሱም ጋር በትውልዱ አየርላንዳዊ የሆነ፣ የዘመዱ ልጅ፣ ከረንስ የሚባል ወጣት እብሮት ነበር። ሁለቱም በአዳኝነቱ

[37] የአፄ ናፖሊዮን ወይም የፈረንሳዮቹ ፍላጎት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[38] ሚሲዮናዊው ስተርን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[39] የባርደል ሸር በተክለፃዲቅ መኩሪያ "ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ተዘግቧል።

[40] አፄ ቴዎድሮስ ምኞታቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

በጣም የቀናቸው ይመስላል፤ በዚህም ምክንያት ይህ ቴላሞኒያን አጃክስ[41]፣ በስውነቱ ግዙፍና ጠንካራ ሰው፣ ዝነኛና ሰሙ የገነነ ነበር። የካሜሩንን መታሰር ሲሰማ፣ የአፄ ቴዎድሮሰ ችሎት ድረሰ ከተፍ ይላል። የሰውነቱ ግዙፍነትና ጠንካራነት የቴዎድሮስን አድናቆት አትርፎለታል፤ ቴዎድሮስም ጦሩ ውሰጥ አንዲያገለግል ይጋብዛሉ። ሰፒዲ የቴዎድሮሰን ወዳጀነት ቢያገኝም፣ ከዚህ ቀደም ከፐላውደን ጋር የነበረውን አያህልም ነበር።



ሎሮድ ጆን ራስል

አፄ ቴዎድሮለ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን የሚታወቁበትን የስውመውደድና ደግነት[42] ባህሪያቸውን አጥተዋል። በውጊያ፣ አንግሊዛዊው ጦረኛ ባሳየው ድፍረት፣ ጀግንነትና ጥንካሬ ቴዎድሮሰ የአንድ ሺ ጦር አለቃ አድርገው በመሾም "የባሻነት"[43] ማዕረግ ለጡት፤ ከዚያ ወዲህ ባሻ ፈለቀ ተብሎ ይጠራ

[41] በግሪክ ታሪክ፣ የሳላሚሱ ንጉስ የቴላሞን ልጅ አጃክስን ለመጥቀስ ነው።

[42] ስለ አፄ ቴዎድሮስ ደግነት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[43] የወታደራዊ ማዕረግ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ሎር.ዮ ጆን ራስል

ጀመር። የስፒዲ ምኞትና ፍላጎት ግን እየጨመረ መጣ፤ ይህ ቤቴዎድሮስ ሚኒስትሮች በኩል የተስተዋሰም የታሰበም ነው፤ ስለዚህ ይህንን፣ ነጭ የንጉሡን ወዳጅ ለማባረር ብዙ ተንኮልና ሸር ይሸረብ ጀመረ። ባሻ ፈሰቀ፣ ከህንድ ገሹር(መህራጃ) የተሠጠው የቱርክ ጎራዴ ነበረው። በዚህ ጎራዴ በጎችን ከጭንቅላት እስከ ጅራታቸው በአንድ ስንዝር ከሁስት በመከፈል ቴዎድሮስን ያስደንቅ ነበር፤ ይህ ግን አቢሲኒያውያኑ ማድረግ የሚችሉት ነገር እልነበረም። በዚህ ሙያና ችሎታው ለረዥም ጊዜ ከቴዎድሮስ ጎን መቆየት ችሏል።

ለእስራ ስምንት ወራት ያህል ከእፄ ቴዎድሮስ ጋር እብሮ ከከረመ በኋላ፣ ስፒዲ ወደ ጎንደር ይሳካል። በመንገዱ፣ እስራ ሁለት ከሚሆኑ የፈታውራሪ ገብርዬ ሰዎች ጋር ይገናኛል። ገብርዬ፣ ቅናትም ይሆናል ስፒዲን ይጠላው ነበር። የያዘውን መሳሪያ እንዲያስረከብና ቴዎድሮስ ወዳሉበት ወደ ደብረ ታቦር እንዲመለስ ያዙታል። ስፒዲም በመገረም፣ ገብርዬን፣ ራሱ መጥቶ መሳሪያውን ከእጁ እንዲወስድ ግን ከተጠጋው ደግሞ በያዘው ጎራዴ በጎቹን ከሁለት እንደሚጎምዳቸው ሁሉ ገብርዬን ከሁስት እንደሚከፍለው ያስጠነቅቃል። ገብርዬም ጠብ እንዲነሳ እንደማይፈልግ ያስታውቃል። ስፒዲም፣ "እንግዳውስ፣ ወደ ጌታህ ተመለስና የጎንደር ጉዳዬን ስጨርስ እንደምመለስ ንገር" ይላል። ስፒዲም መንገዱን ቀጠለ። ገብርዬም ወደ ንጉሡ ካምፕ በመመለሰ ስፒዲ ሰላደረገው ነገርና ስስ እምቢተኛነቱ ጨመርመር በማድረግ ከስፒዲ ጋር ስለተደረገው ግንኙነትና የቃላት ልውውጥ በዝርዝር ለእፄ ቴዎድሮስ ያቀርባል። እንደ ገብርዬ እቀራረብም፣ ስፒዲ የንጉሡን ትዛዝ እላከበረም።

በዚህ መህል፣ በጎንደር የነበረውን ሥራ ለራሱም ሆነ ለንጉሡ በሚያረካ መንገድ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ስፒዲ፣ ንጉሡ ወዳሉበት ወደ ደብረታቦር ይመለሳል። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ልውውጦች በሁለቱ መህከል የሆነ ነው ይባላል።

ስፒዲ፣ "ይቸው ተመልሻለሁ።"

ቴዎድሮስ፣ "እንደተመለስከ እይቻለሁ፤ ግን እንደትመለስ ሰው ስልኩብህ ስምንድን ነው ያልመጣኸው?"

ስፒዲ፣ "ምክንያቱም፣ ታማኝ እገልግሎቴን በቅጣት ይሸልሙኛል ብዬ ስላላመንኩ ነው።"

ቴዎድሮስ፣ "ምን?፣ ገብርዬ እኔ እንደምቀጣህ ነገረህ ወይ?"

ስፒዲ፣ "እዎ! ነግሮኛል"

ቴዎድሮስ፣ "እንግዲያማ እኔ ከማውቀው በላይ ነው የነገረህ"

ስፒዲ፣ "እሱ ውነት ሊሆን ይችላል፤ በጎንደር ያዘዙኝን ሥራ በሚገባና በታማኝነት ጨርሼ መጥቻስሁ። እሁን የምጠይቀው፣ ከፍያዬ እንዲሰጠኝና ከሥራም እንድሰናበት ነው።"

ቴዎድሮስ፣ "አይሆንም፤ ያማ ሊሆን አይችልም፤ በሠራዊቴ ውስጥ ካለ ምርጥ ወታደር ጋርማ መለያዬት እልችልም።"

ስፒዲ፣ "ግርማዊነትዎ! ትልቅ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ፤ ልብዎ የሚያስበው ምክንያትም ይኖርዎታል፤ እኔ ንጉሥ ባልሆንም የራሴ ልቦናና ምክንያት ደግሞ አሰኝ። መጀመሪያ ወደዚህ ስመጣ፣ ለእግልግሎቴ ጥሩ ከፍያና ጉርሻም እንደማገኝ ቃል ገብተውልኝ ነበር። እርስዎን ለማገልገል ተስማማሁ፤ እርስዎንም በታማኝነት እገለገልኩ። በጦር ሜዳ ውያስሁ፤ ራስዎ በአይንዎ እንዴት እንደተዋጋሁ ተመልከተዋል፤ በዚህም በዚያም ዕደገት ሰጥተውኛል፤ ነገር ግን እርስዎን ማገልገል ከጀመርኩ ጀምሮ ገንዘብ የሚባል ተከፍሎኝ እያውቅም። የምበላውን ዳቦና ጨው በገንዘቤ ገዝቼ ነው፤ ስእገሊጋዮቼም ከራሴ ገንዘብ እየከፈልኩ ነው። የርስዎን ትዛዝ ስመፈፀም መንገድ በወጣሁ ጊዜ፤ ርስዎ የህስት ወሬ፣ እነ ፊታውራሪ ገብርዬ የሚያወሩትን፣ በጆሮዎ በመስማት እኔን መልስው የሚያመጡ ሰዎች ልከውብኛል፤ በምን ምክንያት እንደሆነ ርስዎ የበለጠ ያውቃሉ። ገንዘቤ ተከፍሎኝ ከሥራ እንደስናበት እጠይቃስሁ።"

ቴዎድሮስ፣ "እናስ ወደየት ትሄዳለህ?"

ስፒዲ፣ "ወዳገሬ ነው የምሄደው"

ቴዎድሮስ "ምናልባትም ሀገሩን እንዳትስቅ ምርጫዬ ቢሆንስ?

ስፒዲ፣ "እንደዘ ከሆነ ስው ይሞታል፤ ልጅ እንዳልሆንኩ ያውቃሉ፤ ስለዚህ እጄን ዝም ብዬ እልሠጥም።"

ቴዎድሮስ፣ "ከኔ ጋር እንድትቆይ የሚያደርግህ ምንም ማድረግ የምንችለው ነገር የለም?"

ስፒዲ፣ "ምንም! በኔ ዙርያ የሚሸረበውን ተንኮልና ሸር ማየት በቅዶኛል።"

ንጉሡ፣ ስፒዲን ጥሎ ከመሄድ የሚያስቀረው ነገር እስመኖሩን ሲረዱ፣ የሚገባውን ሁሉን ገንዘቡን በመከፈል፣ ፈረስ፣ ጋሻና ጦር በመሸለም በፍቅር ተሰናበቱት[44]።

ባሻ ፈለቀ፣ ካፒቴን ስፒዲ፣ ዘመዱን ከረንስን ይዞ ወደ ምፅዋ ሄደ። ወጣቱ ከረንስም፣ የቆንስል ካሜሩንን ደብዳቤ ይዞ ወደ ሎንደን ሄደ። ዕረፍት

---

[44] አጼ ቴዎድሮስ ለሌሎች አውሮፓውያን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

የሰሹ ሰፒዲም ሌላ ሥራ በመፈስግ ወደ ኒውዚላንደ ሄደ፡፡ በኒውዚላንድም የሚሊሻ ካፒቴን በመሆን በማኦሪ[45] ጦርነት ጊዜ ዕውቅናን ሊያገኝ ችሏል፡፡ ወደፊት ስለሱ እንስማለን፡፡

ከረንስ፣ ክውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤት ለካሜሩን የሚሠጥ ደብዳቤ በመያዝ ወደ እቢሲኒያ እንዲመለስ ተላክ፡፡ እቢሲኒያ የደረሰውም በህዳር 1863 ነበር፡፡ ደብዳቤው ከእፄ ቴዎድሮስ ስለተላከው መልክት ምንም አይጠቅስም፡፡ እንደዚህ እይነቱ ለረዥም ጊዜ መልስ እለመሠጠቱ፤ በእፄ ቴዎድሮስ በኩል እንደስድብና ከብራቸውን እንደመናቅ ተደርጎ በመቆጠሩ ከፍተኛ ጥላቻ ነው ያሳደረባቸው፡፡ ይህ የሎርድ ራስል የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤት ደግሞ ቆንስል ካሜሩን፣ ሚሲዮናውያኑን እና ሠራተኞቻቸውን በእግር ብረት እንዲታሰሩ ነው ያደረገው፡፡

ከረንስም ቢሆን ዕድለኛ እልነበረም፡፡ ስሥጦታ ያመጣው ምንጣፍ ላይ ጁለስ ጌራርድ የተባለ አንግሊዛዊ[46] ሰው የአረብ ልብስ እንደሰበሰ አንበሳ ሊገድል ሲል ተስሎበታል፡፡ ይህን በማየት ክስድብ ስሰቆጠሩት ቴዎድሮስ በቁጣ ይገነፍላሉ፡፡ በቴዎድሮስ እመለካከት፣ ጁለስ ጌራርድ የሚገሰው እንበሳ፣ የይሁዳን እንበሳ ሆኖ በግብፆች(የአረብ ልብስ) እንደሚሸነፍ አድርገው ነው የወሰዱት፡፡ ከረንስም ያለርህራሄ ተገርፎ እንደሌሎቹ በእግር ብረት ታሠረ፡፡

ግብረ ሠናይ ባላቸው በእንዳንድ የእንግሊዝ ሰዎች፣ እስረኞቹን ስማሰፈታት ጥረት ተደርጎ ነበር፡፡ ወይዘሮ ስተርን የባሏን መታሰር ስትሰማ፣ ንግሥቲቷ የተፈረመ ደብደቤ ስቴዎድሮስ እንድትልክ ተማፅና ነበር፡፡ ሎርድ ሻፍትስበሪ የተባለ ሰውም በደግነት ሰዎችን ወክሎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ደብዳቤ እቅርቦ ነበር፡፡ የተሠጠው መልስ ግን "ንግሥቲቷ ስአቢሲኒያ ንጉሥ ደብዳቤ አንድትፅፍ ማድረጉ በኔ በኩል ጥሩ ምክር እይደለም፡፡" ነበር፡፡ አንዲህ አይነቱ የከፋ ፖሊሲ፣ ፖሲሲ ከተባለ፣ ያስክተሰው ነገር ቢኖር በምርኮ በእስር ቤት ላሉት ሰዎች ቅጣትና ስቃይ ነው ያበዛባቸው፡፡ ቴዎድሮስ እያደረ ህዘናቸው እየጨመረ፤ ጨካኝም አየሆኑ መጡ፡፡

በተለይም ንጉሥነታቸውን የሚያዋርድና እንደ ስድብም የሚቆጠር ነገር በሴት[47] በኩል መደረጉ በጣም ነው ያበሳጫቸው፡፡ ስለዚህ በቀላቸውን

[45] ከ1845 -1872 እኤአ በተወላጆቹ በማኦሪዎችና በኒውዚላንድ መንግሥት ተከታታይ ጦርነቶች ተካሄደዋል፡፡ ሰውየው ቅጥረኛ ወታደርም ነበር፡፡

[46] ፈረንሳዊ ሆኖም ይጠቀሳል፡፡ የሚታወቀውም በአዳኝነቱ ነበር፡፡ ሄንሪ ዱፍተን ከአቢሲኒያ ሲመለስ፣ ከረንስን ምፅዋ ላይ አግኝቶት ይህን ገደ ቢስ ምንጣፍ እንዳሳየው ዘግቧል፡፡ ቴዎድሮስ ግን ምንጣፉን የላከው ባሻ ፈለቀ ነው የሚሉት፡፡

[47] ንግሥት ቪክቶርያን በመጥቀስ፡፡

በእስረኞቹ ላይ ይወጡ ጀመር፡፡ እስረኞቹ በእስራት አያሉ ያላለፉት መክራ የሚነገር ታሪክ ነው የሆነው፡፡

ገንዘብ ካስ በአቢሲኒያ ውስጥ መደረግ የማይቻል ነገር እልነበረም፡፡ ከቴዎድሮስ ጋር ወዳጅነት የነበረው፣ ካሜሩን ከመታሰሩ በፊት እቢሲኒያ ሲወጣና ሲገባ ሲክተሰው የነበረ አቶ ላሙኤል የሚባል ሰው ጉቦ የሚደልሰው ሰው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በገንዘብ፣ አቶ ላሙኤል[48] ደብዳቤዎችን ምፅዋ ድረስ ይወስድ ነበር፤ ራሱ ካልሆነም በሱ ታማኞች በኩል ደብዳቤዎች በምስጢር እንዲወጡ ያደርግ ነበር፡፡ ከነዚህ ደብዳቤዎች፣ በአንዱ፣ ካሜሩን የእስራቱን ምክንያትና የደረሰበትን ችግር በሰፊው እትቶ "ለጃንሆይ (ቴዎድሮስ) መልስ ደብዳቤ ካልተላክ በሰተቀር የኔ መፈታት ተስፋ የለውም፡፡" ብሎ ፅፏል፡፡

ይህ የካሜሩን ደብዳቤ ታይምስ ወደ ተባለ ጋዜጣ ይደርሳል፤ ጉዳዩም በአንግሲዘ ጋዜጦች በመጥፎ ሁኔታ ነው የታየው፡፡ ታይምስ የተባለው ጋዜጣም መንግሥት ባደረገው የጅል ስራ ቁጣና ጥላቻውን ሲያወርድ፤ ሌሎች ጋዜጦችም ያስተጋባሉ፡፡ በዚህ የቁጣ ማዕበል ምክንያትም ሚኒስትሩ ሀሳቡን ቀይሮ ንግሥቲቱ ደብዳቤውን እንድትፅፍ ይመክራል፡፡ ደብዳቤው ተፅፎ ይላካል፡፡

ሚስተር ላያርድ የሚባል የፓርላማ እባል፣ ከዚህ ቀደም በጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ ጥንታዊ ቁሳቁሶችን በሚፈልግበት ጊዜ ስሠራተኞቹ ደሞዝ ከፋይ ሆኖ የሚሠራ አንድ ፀሐፊ ነበረው፡፡ ይህ ፀሐፊ ደግሞ አርመናዊው ሆርመዝ ጄ ራሳም ነበር፡፡

"ኒነቭህ" የተባለው ፅሁፍ ደራሲው ሚስተር ላያርድ ፣ እንግሲዝ አገር በሚመስስበት ጊዜ፣ የሠራተኞቹ ደሞዝ ከፋይ የነበረውን ፀሐፊውን አልረሳም፡፡ ራሳም፣ በጊዜው በኤደን የፖለቲካ ወኪል ስነበረው ስኮሎኔል መርዌዘር ተቀጥሮ ይሠራ ነበር፤ ይህም የእንግሊዝ ሚኒስቴር በቴዎድሮስ ላይ የነበረው ፖሊሲ በአንግሲዝ ጋዜጦች ከተወገዘ በኋላ ነበር፡፡ ራሳም በመተማመን፣ ለላያርድ ደብዳቤ በመፃፍ የንግሥቷን መልስ ስቴዎድሮስ ለመውሰድ ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል፡፡

አመስጋኙ ጥንታዊ ቁሶች ሰብላቢው፣ ራሳም መልክተኛ ሆኖ አንዲሾም ጥረት ያደርጋል፡፡ ስስተሳካስትም፣ መልስ ለመስጠት ይህን ያህል ረዥም ጊዜ የወሰደውን ደብዳቤ ለማድረስ የተላክው ራሳም ነበር፡፡ ክራሳም ጋር ሁለት የእንግሲዝ መኮንኖች፣ ሉተናንት ፕሪዶና ስርጀን ሄንሪ ብላንከ የሚባሉ ነበሩ፡፡

[48] አቶ ሳሙኤል የአፄ ቴዎድሮስ አስተርጓሚ ነበረ፡፡ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

የራሳም ሹመት፣ ለአንድ ፀሐፊና ደሞዝ ክፋይ ለነበረ ለው ከሚገባው በላይ፣ "ልዩ ከፍተኛ መልከተኛ" የሚል ነበር።

ራሳም ካይሮ ሲደርስ፣ የካቲት 1865 መሆኑ ነው፤ አንድ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ከመልከተኞቹ ጋር አብሮ አለመላኩ ይታወቃል። ይህም የንግሥቷ የቀለበት ማህተም ነበር። መልከተኛው እንዲመለስ ይደረጋል። ዶሴው ከተሟላ በኋላ እንደ አዲሰ ወደ አቢሲኒያ ጉዞ ይጀመራል። ለደብዳቤው መዘግየት ለእንግሊዝ መንግሥት በሚሰማማ ሁኔታ ዝርዝር ምክንያት እንዲያቀርብም ታዟል።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም መልከተኛው ራሳም ምፅዋ ይደርሳል። ሆኖም ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ አንድ ሙሉ አመት በምፅዋ ይቆያል።[49]

በነዚህ ረዥም ጊዜያቶች መህከልም አሰረኞቹ ይለቃያሉ። ለነሱ ሁኔታዎች እየከፉ ነው የሄዱት። ዳቦና ውሃ ብቻ እየተሠጣቸው፤ በሠንሰለት ከግድግዳ ጋር እንደታሰሩ ይደበደቡ ነበር። ካሜሩን ተሠቃየ፤ እንደሱ አባባል "ህያ የሚሆኑ እቢሰኒያውያን እጅና እግሮቼን በገመድ ወጥረው ራሴን እስክስት ድርስ ይጎትቱኝ ነበር። የትክሻ መጋፊያ አጥንቶቼ እስኪጋጠሙ ድረስ ወደኋላ አወጠር ነበር። ጭንቅላቴ ጭኖቼ ውስጥ እስከሚቀበር ድረስ ኩርምት አንድል ተደርጌ ጀርባዬ ከጉማሬ ቆዳ በተሠራ አለንጋ ይገረፍ ነበር፤ ጀርባዬም ሰምበር ያወጣና ደምም ይደማ ነበር፤ እንደዚህ ሲሆን ደግሞ እሸዋ ላይ እንድንከባለል ይደረጋል።"

ይህ ሆኖ፣ ራሳም ግን ምፅዋ ይከርማል። በፓርላማው ወስጥ በተደረገው ከርክር ምክንያት ሚስጥር ወደ ውጭ ሲወጣ፣ ለሎርድ ላያርድ ደቀመዝሙር የሚሰማማ ሁኔታ አልነበርም። ሎርድ ራስልም አማራጭ ስላልነበረው፤ የታወቀውን መንገደኛ ሚስተር ፓልግሪቭን ወደ አቢሲኒያ ዘልቆ አሰረኞቹን አንዲያስፈታ ጥረት እንዲያደርግ ሾመው፤ ራሳም ደግሞ አንዲመለስ ተጠየቀ። ተመላሹ ራሳም አዲሱን መልከተኛ ምፅዋ ላይ አገኘው። ራሳም ወዲያውኑ ወደ ሱዌዝ በማምራት፣ አለከሳንድርያ (አስክንድርያ) ላለው ፅሕፈት ቤት ካሜሩን ተለቋል የሚል የቴሌግራም መልክት ላከ[50]።

ይህ የምስራች መልክት በኢንግላንድ በፍጥነት በዜና ሲሰራጭ በሁሉም በኩል በሙሉ ልብና በደሰታ ስሜት ነበር የተደመጠው። ፓልግሪቭ ካይሮ ቢደርሰም በዚህ ምክንያት የሱ ተልኮ አለቀለት። የያዘውን ሥጦታም ለራሳም አሰረከበ።

---

[49] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[50] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ባሻ ፈለቀ ከናፒየር ጋር(በቀኝ በኩል በጥግ የሚታየው ግዙፍ ሰው)



የአውሮፓ አሰሪኞች

(ከግራ ወደቀኝ፣ ካረንስ፣ ሪሳም፣ ሰተርን፣ ሉተናንት ጉዱዶ፣ ወይዘሮ ሮዘንታልና ልጇ፣ ሮዘንታል፣ ዶክተር ብላንክ፣ ፒየትሮ፣ ካሜሮን ናቸው)



ሆርሙዝ ራሳም

ራሳም ስጦታውን አንደያዘ ወዲያውኑ ወደ ምፅዋ ተመለሰ፤ ምናልባትም፣ ሥጦታውን የተፈታውን ካሜሩንን ኣጅበው እስክ ምፅዋ ድረስ ለሚመጡ ሹሞች ለመሥጠት ነበር።

መልክተኛው ራሳም፣ ከአጃቢዎቹ ከብላንከና ፕሩዶ ጋር ክምፅዋ ተነስቶ፣ መንገድ ላይ ሳያቆም በጥር 28፣ 1866 ደብረ ታቦር ገባ።[51] "ገናናው ንጉሥ ሆይ! ለዘላለም ያኑርዎ!" የሚል ስላምታ ነበረ ክአቢሲኒያውን ንጉሥ ክአፄ ቴዎድሮስ ፊት የቀረበው የአንግሊዝ መልክተኛ ያቀረበው። ክንግስቷ የተላክው ደብዳቤ ግን የተጠበቀውን ያህል አልነበረም፤ የሚገባውን ክብርም ለቴዎድሮስ ባለመሰጠቱ ካሜሩንም አልተለቀቀም፣ አንዲያውም ራሳም፣ ፕሪዶ እና ብላንክ ቴዎድሮስ ካሰሯቸው አሰረኞች ጋር ተደረቡ። ራሳም በነበረው ብልጣ ብልጥነት[52] ዲፕሎማሲ ምክንያት አልተደበደበም፤ ክንግስቷ በኩል የጎደለውን እክብሮት፣ አራሱ በመልካም ፈቃዱ ጨማምሮ አቀረበ። የቴዎድሮስ ጭካኔም ቢሆን እንዲህ ያለውን አክብሮት በመልካም ሁኔታ

[51] ሶስቱ መልክተኞች፤ ሀኪሙ ብላንክ፣ ወታደሩ ፕሩዶ እና ዲፕሎማቱ ራሳም ይበቃሉ ተብሎ የተወሰነው ክብሪታንያ ነው። ፕሩዶን የመረጠው መርዌዘር ነበር።

[52] ቴዎድሮስ ራሳምን በጣም ይወዱት ነበር፤ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ሰለተቀበለው ለአሰረኛ የሚገባውን ደግነትና አንክብካቤ ለመልክተኛው ራሳም እንዲደረግለት ሆኗል። በራሳም ተፅኖ የካሜሩን ሁኔታም ተሻሽሎ ነበር።[53]

መልክተኞቹ ከታሰሩ ከሶስት ወር በኋላ፣ ሚስተር ፍላድ አለከሳንድርያ ያደርሰና የመልክተኞችን ዕጣ ዜና ያሰማል። ሆኖም እሱ ራሱ ወደ አቢሲኒያ ሰ.መለስ ክአሰረኞቹ ጋር ይደመራል።

ቴዎድሮስ፣ የነበራቸው ሥልጣን በአርግጥ ክአጃቸው እየወጣ አንደሆነ ተሰምቷቸዋል። ክዚህ ቀደም የነበራቸው ጥንካሬና ችሎታ፣ የነበራቸው ጀግንነት፣ ማዕረግና ክብሩ፣ ወይም ጭካኔያቸው የነበሩትን ግዛቶች በሥራቸው ማቆየት አላስቻላቸውም። አሮሞዎቹ ህይላቸውን አስባስበው ክኋላቸው ያወጓቸው ጀመር። ለተወሰነ ጊዜ፣ ቴዎድሮስ በጀግንነት ተቋቋሙት፤ ሆኖም የመለሱት አየፈረስ ሲሄድ መንዳታቸውን ያዩ ጠላቶቻቸው የልብ ልብ ያሰማቸው ጀመር። የቴዎድሮስ ሞራልም እየተዳከመ መጣ። ነገር ግን የትም ቢሆን ቢሆን፣ የቴዎድሮስ ካምፕ፣ በነበሯቸው መድፎች ምክንያት የማይጣስ ሀያል ነው የሆነው። የአውሮፓውያን ሠራተኞቻቸው ሀያ የሚሆኑ መድፎች አምርተውላቸዋል፤ ከነዚህ አንዳንዶቹ በጣም ግዙፍ ነበሩ።

መድፎቹን አየወደዷቸው ነው የሄዱት። አስራ ሁለትና አስራ አምስት ኢንች አሩሮቹ ነብሳቸውን ነው የሚያስደስታቸው[54]። የመድፎቹ ጩኸት ብቻ ጠላቶቻቸውን እንዲሚያሸብራቸው ነው ያሰቡት። የነዚህ መድፎች ዝና በድሩን ሀገሩ በተወራ ጊዜ፣ ደፍሮ የቴዎድሮስን ካምፕ የሚያጠቃ አልነበረም። ነገር ግን ሁሉም በያሉበት ይሸፍታሉ፣ ቴዎድሮስም ፍፁም የማያወላውል ቆራጥ የሥነ ሥርአት አርምጃ[55] ስለሚወሰዱ፣ በሚደረገው ግጭነኔ የተመላበት ቅጣት ምክንያት በመቶ በመቶ የሚቆጠሩ ወታደሮቻቸው እየጣሏቸው ይሸሹ ጀመር።

እሁን፣ ጦርነት አንዲታወጅ ወደ ሆኑት ምክንያቶች እየመጣን ነው። ሰበበ በግልፅ ተቀምጧል። የአንግሊዝ አሰረኞች በቁጥጥር ስር አንዳሉ

[53] የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን፣ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[54] ሥድፋና የጦር መሳሪያዎችን በጣም በመውደዳቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[55] ቴዎድሮስ ሥነስርአት የሚወዱ ሰው ነበሩ። ሥርአቱን መተላለፍ ከባድ ነው። ወደ ሸዋ ሲዘምቱ ወታደሮቻቸው ገበሬውን ዘርፈው አንዳይበሉ ጥብቅ ትዛዝ ሠጥተው ነበር፤ ነገር ግን ትዛዙን የተላለፉ ስላሳ ሰባት ወታደሮች በሞት አንዲቀጡ አድርገዋል።

ናቸው። እነሱን ለማስፈታት የተደረገው ተልኮ ውጤት አልባ ሆነ። የዚህ ሁሉ መጨረሻ ምን ይሆን? አስኪ እንመልከት።

በ1866፣ በእንግሊዝ አገር፣ የወግ አጥባቂው ፓርቲ ሥልጣኑን ያዘ፤ የደርቢው መስፍን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን፤ ልጅየው ሎርድ ስታንሲ ደግሞ በውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤት ሀላፊ በመሆን ወንበሩን ያዘ። ከረረ ወዳለ ደረጃ ከመሻገራቸው በፊት፤ ሚኒስትሮቹ፣ የታሰሩትን ለማስለቀቅ ስቴዎድሮስ አጅ መንሻ ስመስጠት ሀሳብ አቀረቡ። ያም አልተሳካም።

ቴዎድሮስ፣ እንግሊዞቹ ዜጎቻቸውን ስማስለቀቅ ሲጨነቁና ሲጠበቡ ሲያዩ፤ እንግሊዞች (ህዝቡ) ዜጎቻቸው በአስር ከሚከርሙባቸው የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ብለው ገመቱ። በእንድ በኩል የቴዎድሮስ ጥርጣሬ ትክክል ነበር፤ እዎ የእንግሊዝ ህዝብ ለዜጎቻቸው ሲሉ ያማያደርጉት ነገር አልነበርም፤ ጦርነትም ቢሆን። ነገር ግን ቴዎድሮስ ራሳቸው ባዋረዱት ዙፋን ላይ እንዲቆዩ በጭራሽ መርዳት አልፈለጉም። ሰለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት ጦርነት አወጀ።

የሚገርመው ነገር ግን፣ ጦርነቱ ሲታወጅ፣ የእንግሊዝ ህዝብ ምንም አይነት የድጋፍ ወይም የተቀባይነት ስሜት አላሳየም ነበር። የጦርነቱ ዕቅድ በርጋታና በፅሞና ነበር ውይይት የተደረገበት። በህዝቡ ዘንድ የተቀባይነት ስሜት ባለመፍጠሩ ምክንያት፣ እደጋ፣ መጥፎ ንግርትና ምልክቶችን የሚጠቅሱ ደብዳቤዎች እየተላኩ ቢጋዜጣ አዘጋጆች ይወጡ ጀመር። ሁሉም የራሱን ትንቢት መናገር ጀመረ።

እንድ ራሱን "እውነተኛው ጆን ቡል" ብሎ የሚጠራ ዘጋቢ፣ በራሱ አመለካከት እንደፃፈው ከሆነ፣ አንድም ሠራዊት ከዚያ አገር ተመልሶ እንደማይመጣ ገለፀ[56]። የእንግሊዝ ታክስ ከፋይ ህዝብም ቢሆን ራዕይ ነው የታየው፤ በጊዜው በህርትፎርድሸር የነበረ ሩቅ አላሚ፣ እያንዳንዱን ወታደር ዝናብ ጠርጎ ወደ ባህር ይወስደዋል ብሎ ተነበየ። ጆሊ ብሪቶን፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በምንም አይነት ቴዎድሮስን መማረክ እይችሉም አለ። ራሱን የካምብሪጅ ተማሪ ነኝ የሚል፣ በአለምሮው ውስጥ የግሪክና የትሮይን ጦርነት ስሎ፣ የአቢሲኒያን ሽለቆዎች የሚያሻግር ድልድይ እንዴት እንደሚሠራ ጠየቀ፤ አቢሲኒያ ግሪክ ካልሆነች፣ እራት ሺ ጫማ ጥልቀት ባለው ሽለቆ ላይ ያለ ድልድይ እንዴት መሻገር እንደሚቻል በአእምሮው ሊመጣለት አልቻለም። ይህ አዋቂ ሰው ደግሞ፣ የእንግሊዝ ጂኒራሎች ከትሮይ እንደሚበልጡ

[56] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

እርግጠኛ ነው፤ እንደዚያም ሆኖ፣ የትሮይን ታክቲክ በመጠቀም የአቢሲኒያን ሰፋፊ ሽለቆዎች መሻገር መቻሉ ተሰፋ የሌለው ነገር ነው ይላል።

በአጠቃላይ፣ በዘማቾቹ ላይ ይደርሳል ተብሎ ያልተተነበየ አደጋ፣ እስከፊ ነዠና በሽታ አልነበረም። መርዛማ እና አደገኛ የእባብ ዝርያዎች[57] የወታደሮቹ ልብሰና ብርድ ልብስ ላይ እንደሚተራመሱ ተገለፀ። ሀኪሞችም ቢሆኑ ሠራዊቶችን፣ ጭንቅላቱ የሮዝ ቀለም ካለው ትንሽ ዝንብ እንዲጠነቀቁ፣ ሰመንገድ ዳር የሚያገኙትን ማር እንዳይነኩ፣ የኖረ የጉድጓድ ውሀ እንዳይጠጡ፣ ከአይን በሽታ እንዲጠነቀቁ፣ ድንገት ተቅማጥ[58] ከያዛቸው ቶሎ ወሰኑታት የሚችሉት ቀበቶ እንዲታጠቁ፣ በቶሎም መድሃኒት እንዲጀምሩ፣ እነሬቱን ከሞላው የጅብ መንጋና ከጉማሬ ለመከላከል የሚቻላቸውን እንዲያደርጉ በማሰት አስጠነቀቁ። የእንግሊዝ ወታደሮችን ክላይ አስክታች ያረስ የተቅማጥ በሽታ እንደሚያውካቸውም ተነገረ።

ከዚህ ቀደም ወደ ሌሎች አገሮች ተጉዘው የሚያውቁ ሰዎች፣ ብዛት ያላቸው የማይመስሉ ምክሮችን ሰገሱ፤ ከሎንደን ቲያትር ቤቶች ውጭ ወጣ ብለው ተጉዘው የማያውቁ ሰዎችም ቢሆን፣ ከልምዳቸው በመነሳት፣ ለውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ምክር በነፃ ይለግሱ ጀመር። ታማኝ የሆኑ የእንግሊዝ ዜጎች ደግሞ ያለምንም ርዳታ በራሳቸው እስረኞቹን ማስፈታት እንደሚችሉና ለመሰሰፍም ዝግጁ መሆናቸውን አስታወቁ[59]። በራሳቸውም ሰለሚተማመኑ፣ ጎዳጁን ያለምንም አደጋ ሳይቸገሩ መወጣት እንደሚችሉ ነው፤ ይህንንም የሚያደርጉት ራሳቸውን ለማዝናናት ሲሉ ነው።

ሌሎች ደግሞ፣ የውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ሊከሽፍ የማይችል ዕቅዳቸውን እንደሚቀበል ተሰፋ አደረጉ፤ ዕቅዱም፣ የፈረሰኞች ካምፓኒ ጦር ይዞ ከአቢሲኒያው ንጉሥ ካምፕ ውስጥ ጥሶ በመግባት በሀይል መማረክ ነው። ታይምስ የተባለ ጋዜጣ ልዮ ዘጋቢም ቢሆን ከተፈጠረው ውዥምብር ነፃ አልወጣም። እንደሌሎቹ ሁሉ ሀሳብ ሲሰጥ፤ ኮሎኔል መርዌዘር የፈረሰኞች ስኳደርን ይዞ ቢሄድ፣ ሁሉም ነገር አንድ ወር ባላነሰ ጊዜ ይጠናቀቃል በማለት የራሱን እምነት በርግጠኝነት አቀረበ።

ካፒቴን ስመልፈንስ፣ ለታይምስና ለሎርድ ስታንሲ በላከው ፅሁፍ፣ ያለ ሀውሳዎች እርዳታ የእንግሊዝ ወታደሮች በአቢሲኒያ መንቀሳቀስም እይችሉም፤

[57] ከሀሉት አይኖቹ በላይ ቀንድ ያለው ሰራሰተስ የሚባል አባብ ፣ ጀርባው ላይ ጥቁር ብጠማዝማዛ ቀለም ያለው አደገኛ መርዛማ እባብ

[58] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[59] የታሠሩ ቤተሰቦችን በመወከል የመጣው ዶክተር ቤክ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ሀውሳዎች መደበኛውን ጦር ለመርዳት አገሩን በማለስ፣ ከጦሩ ፊት ፈት አንደ ቃፊር አየሆኑ በመላከ ማገልገል እንደሚችሉ ገለጠ። በጦሩ ውስጥም በኮሎኔሌነት ማዕረግ ተመድቦ መርዳት አንደሚችል አሰታወቀ። ሀውሳዎች በናይጀሪያ፣ በሌነለ ብቻ ሰለሚኖሩ አንዴት አድርገው በአቢሲኒያው ውስጥ አንደሚመለመሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ሊታየው አልቻለም። ለምን ግን የማይሆነውና የማይመለለውን ነገር መከተል ያስፈልጋል። ሁሉም ነገር የአቢሲኒያ ብሉ ቡከ[60] በሚባል ማህደር አልተመዘገበም ወይ? ጦር ከየት ነው የሚመጣው? የተወለነው፣ ጦሩ አንዳለ የህንድ ጦር አንዲሆን፣ በቦምቤይና በኢንግላንድ የሚገኘው የአውሮፓና የሰፖይ ጦር ስንቅና የመጫኛ ኢጋሠሎችን ብቻ እንዲሠጥ ተወለነ። ለለዚህ፣ የቦምቤዩ አገረ ገዥ፣ ሰር ሲሞር ፊትዝጀራልድና የቦምቤይ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሰር ሮበርት ናፒየር በውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ከተነገራቸው በኋላ ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ። ጦሩ አስራ ሁለት ሺ ወታደሮች አንዲኖረው፣ ሁለት ሺ ሰዎች ለባህር ዳርቻ ዙላ ወደብና በአቢሲኒያው ደጋማ መሬት በሰናፈ የሚመደቡ፣ ሁለት ሺ በዙላና በመቅደላ ግማሽ መንገድ እንጣሎ ላይ የሚመደቡ፣ ሁለት ሺ ደግሞ በጦሩ መሀከል ያለውን ግንኙነት እንዳይቆረጥ የሚያደርጉ፣ የተረፉት ስድስት ሺ ወታደሮች ግን ቀጥታ ዘማቾች አንዲሆኑ ነበር።

መኮንኖች፣ ከብትና እጋስስ ለመግዛት ወደ ስፔይን፣ ግብፅና ሶሪያ ተላኩ። መድፎችን፣ ኮርቻ፣ ስንስለትና ልጓሞችን፣ ድንኳኖችና ሥንቅ ማቅረብ የአንግሊዞች ወሳኝ የጦር ዝግጅታቸው ነው። ለሆስፒታል እገልገሎት የሚሆኑ መርከቦች ወደ እነስሊ ወሽመጥ ተላኩ፤ እነሱም የታመመሱትን ለመቀበልና ዙላን የሚጠብቁ ሰዎችን ለመንከባከብ ነበር።

በታላቅ ጥንቃቄና ግልፅ ባለ ሁኔታ የዘመቻው ዕቅድ በሰር ሮበርት ናፒየር ቀረበ። አንዴ ቴዎድሮስ ያለበት ቦታ ከታወቀ፣ ዘመቻው በምንም አይነት መንገድ መከሸፍ አይጠበቅበትም። የተዋጊውን ከፍል ራሱ ናፒየር ነው የመረጠው። ሌሎቹ፣ የማዳራስና የቤንጋል አዛጉች መጠነኛ የሆነ የራሳቸውን ድርሻ ለመለጠት ቢጓጉም፣ ጀኔራል ናፒየር በጦሩ ውስጥ ስምምነትና መዋህድ እንዲኖር ከአንድ ከፍል ብቻ ቢመጣ ይሻላል ብሎ ነው ያሰበው።

ጦሩ ከባህር የሚወርድበት ቦታ በሌፍተናንት ኮሎኔል መርዌዘር አንዲመረጥ ነው የተወለነው። ኮሎኔሉ፣ በኤድን ተቀማጭ የነበረ የፖለቲካ ሀላፊ፣ ጀግና ደፋርና ብልህ መኮንን ነው። የአቢሲኒያን የባህር ደንበር ከላይ አለከታች እጥንቷል። እነለሊ ወሽመጥ ምንም እንኳን ከመቅደላ ቢርቅም፣

[60] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ለሠራዊነት በመመቸቱ፣ ለተራሮች የቀረበ በመሆኑና ባለው በቂ የውሀ መጠን ሦግነያት ተመረጠ።

በታጁራ ሠርጥና በመቅደላ መህከል የመቶ ሃምሳ ማይሎች ርቀት አለ። ከለሃምፊላ ሠርጥ ከሆነ፣ ሁለት መቶ ሃምሳ ማይሎች፣ ከሆዋኪል ሶስት መቶ ሀያ አምስት፣ ከአነስሊ ወሽመጥ ደግሞ ለትንሽ ከአራት መቶ ማይሎች በታች የሚሆን ርቀት ነበር።

የሚቀጥለው ርምጃ፣ ሁለቱንም፣ እንግሊዝኛና የአቢሲኒያ ቋንቋ መናገር የሚችሉ አስተርጓሚዎች መፈለግ ነበር። ቄስ ሉዊስ ሲ ከራፕ የተባለ ከዚህ ቀደም በአቢሲኒያ መንገደኛ የነበረ ሰው ተመረጠ። ሆኖም በእድሜ ገፋ ያለ በመሆኑ ለዘመቻው የሚሆን አልነበረም። ሚስተር ሄንሪ ዱፍተን፣ ሌላው መነነደኛ፣ ስለ ቋንቋው የማውቀው ነገር አለ ሰላለ በመረጃ ሱብሳቢው ከፍል ተመደቦ ኮሚሳሪያቱንና የስንቅና ትጥቅ ሀላፊውን፣ በሚናገራቸው ጥቂት ቃላት እንዲረዳ ተደረገ። የተሠጠው ሥራ መደበኛ የሆነ እልነበረም። በመጨረሻ ግን፣ ሎርድ ሲታንሊ ለዚህ ሥራ ትከከለኛ ነው ከሚባለው ሰው ጋር ተሞገቱ። ይህም ሰው በኒውዚላንድ ሚሲሻ አያገለገለ ያለ ከዚህ ቀደም ዮቴዎድሮስ ሠራዊት አባል የነበረው ካፒቴን ስፒዲ ወይም ባሻ ፈለቀ ነበር። ባሻም፣ ከቦምቤይ በተላከለት ቴሌግራም ለሰር ሮበርት ናፒየር ሪፖርት እንዲያደርግ ተነገረው። ባሻ ፈለቀ ለእንግሊዝ ሠራዊት ያደረገው ታላቅ እስተዋፅኦ በግልፅና በዝርዝር በሚቀጥሉት ከፍሎች ይገኛል።

በ1867 በህዳር ወር ቀዳሚው የአቢሲኒያ ዘማች ጦር ዙላ ወደብ ያርፋል።

አንባቢዎች፣ አሁን፣ ለዚህ ዘመናዊ ከሩሌድ ጦርነት መከሰት ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በየተራ ከተመለከትን በኋላ፣ የተሳሳተ ዲፕሎማሲ ያለከተለውን ውጤት ከመረመርን በኋላ፣ በመጠኑም ቢሆን የዘመቻውን ዋና ዝግጅት ካካፈልኩ በኋላ፣ ቀዳሚው ጦር አነስሊ ባህር ዳርቻ መድረሱን ካሰታወቅሁ በኋላ፣ ወደዚህ ዝነኛ አገር አብረን እንድንጓዝ እየጠየቅሁ፣ የወታደሮቹንና የጀግናው ሽማግሌ መሪያቸውን አስገራሚ ጉዞ በመከተል እንዲት መቅደላ እፋፍ ላይ ስንደቅ አላማቸውን እንደተከሉ እንመልከት።



ፀሀፊው ሄንሪ ምርተን ሰታንሊ

የምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች

ቁጥር 6፣ ህዝቡ ይህን ኣይነት ትንቢት የተቀበለበት ምክንያት በዘመኑ የነበረውን ከፋ ሥራ በማየቱ ነው። ደብተራ ዘነብ፣ የቴዎድሮስ ታሪክ ብለው በዘገቡት ፅሁፍ ሥሚከተለው ይገኝበታል። "የዚህ ዘመን ካህናት ሰለ ምድራዊ ንብረታቸው ነው። የነሱስ ሥራቸው፣ ምንዝር፣ አለማት፣ ሰካር፣ የዚህን ዓለም ክብር፣ ጌጥና ኩራት፣ ሥግኔት ዘፈን፣ ለሰው ለመታየት፤ ብርሃን ለማግኘት ነው። ቀን ቀን የሰውን ሰራ ይሰራሉ፣ የየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይተረጉማሉ፤ የሚሰማቸውም የለም። ሌሊት፣ ዚጎለምታ ያድራሉና። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንዳለው። ለሰው ጥኑ፤ ብነም አሰራችሁ በጫንቃው ላይ ትጭኑበታላችሁ። አናንተ ባንድ ጻንታችሁ አንኳ ኣትነኩትም አንዳለ። ደግሞም አትሰረቁ ትላለህ፤ አንተ ትሠርቃለህ አንዳለ። ይህንን ሁሉ ከፋት ባየ ጊዜ አግዚአብሔር በህበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አሰነሳ። ምንዝር ሥሚይወድ፣ ገንዘብ፣ ሐሰት፣ ሥርቆት የሚይወድ። ሸፍጥንም ሁሉ የሚይወድ። እግዚአብሔርን የሚፈራ። ኢሮግ የሚሰጥ፤ አንግዳ የወደደ፣ ለታመመ የሚያዝን፤ ለአንድ ሴት የቆረበ" ደብተራ ዘነበ የጠቀሷቸውን ባህሪያትን ቴዎድሮስ ያሳዩና ያስመሰከሩበት ጊዜ ነበር።

ቴዎድሮስ ራሳቸውን፣ "የክርስቶስ ባሪያ" ብለው ነበር የሚጠሩት። ሀይላቸው ከፈጣሪ አንደሆነ አድርገው መቀበላቸውን በተለያዩ ጊዜያቶች ከተናገሯቸው ንግግሮች መረዳት ይቻላል። ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን የገለፁበት ሁኔታ በዚህ መልክ ነበር። ካሰ፣ ወታደራቸው ሲፎክር፣ በሰሜት የያዙትን ብርሌ ይወረውራሉ፤ የወረወሩበት ዝኒታ በብዙ ቦታዎች ሲሰባበር፣ ብርሌው ሳይለበር ይቀራል። በዚህ ጊዜ ፎከረው በመነሳት፣ "አኔ የክርስቶስ ባርያ፣ ክርስቶስን ከያዝኩ ከፊቴ ማን ይቆማል" ብለው፣ በብርሌዋ ጠጅ ከቀረበላቸው በኋላ አግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ማዳን ይቻልሃል ጌታዬ ሥሚለበረውን አዳንክ ብለው ወደ መሬት ወድቀው ሰገዱ። ይላሉ ደብተራ ዘነብ።

በሌላ አጋጣሚ፣ በወሎ፣ አምባ ማርያም የሚባል ቦታ ሠፍረው አያለ፣ ሠራዊቶቻቸው ካልዘረፍን ብለው አሰቸገሯቸው፤ ንጉሡ ተበሳጭተው የሚቀጥለውን ተናገሩ። "የመቅደላ ሰዎች አሰቲ ምክሩኝ፤ ይህንን መንግሥት ትቼ ለመሄድ ሃከረኩ። ደግሞም ፈጣሪዬን ፈራሁት፤ ግዘ፣ ንዳ ብዬ ብሠጥህ አምቢ አልክ ብሎ ይጣላናል ብዬ።" ቴዎድሮስ ቅጣቱን ቢሆን በፈጣሪ ፈቃድ እንደሆነ አድረገው ነበር ሃተቀበሉት። ከመልከተኖው ራሳም ጋር ሲጨዋወቱ፣ "በጊዜዬ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ገድያለሁ፤ ነገር ግን ለሞታቸው ፀፀት ተሰምቶኝ አያውቅም ምክንያቱም ፈጣሪን ፊቃድ አየፈፀምኩ ሰለሆነ የሚገባቸውን ነው ያደረግሁት...።" ብለዋል።

ከሰቸው ውጭ፣ ሌሎችም ቢሆን በዚህ ነገር አምነት ነበራቸው። ቴዎድሮስ ሠኖ ወሎ ሲዘምቱ፣ ወረሂመኑ የሚባል ቦታ የሚኖር፣ ሼህ ያሲን የሚባል ቃልቻ ነበር፣ ይህን ንጉሥ አላስመጣውም (ወሎ አንዳይገባ) ብሎ ወዳጃ ያዘ። በሶስተኛው

ቀን ግን፣ ሼህ ያሲን፣ በህልሜ፣ መልአክ ከምድር አሰክ ሰማይ የሚሆን ጦር ይዞ፣ ለሁሉም መቅጫ ያወረደውን ግደልልኝ አልክ፣ አሁን ከመሬት ጋር በሰፋሁህ ብሎ አሰፈራራኝ፤ ብሎ ተናገረ:: ወደ መቅደላም ሄዶ፣ ንግሥት ወርቂትን አንቺም ሸሺ፣ አኔ አልሆነልኝም፤ ይህ ሰው ከአላህ የተላከ ነውና ዛሬ ሌሊት ሞቼ ነበር በማለት አርሱ ራሱ ግን ለቴዎድሮስ የሚመጀን መሆኑን በመግለጥ ማለ:: ቃልቻውም ሸሽ፤ ወርቂት በዛን ጊዜ ከጨጨሆ አሰክ ሸዋ ደንበር ትገዛ ነበር፤ አሷም ሸሸች::

ንጉሡ ከእግዚአብሔር የተላኩ ናቸው በማለት ሊዋጓቸው የተሰለፉ ኦሮሞዎች እንኳን ቴዎድሮስን ካዩ ይሸሹ ነበር:: ቴዎድሮስ የገበሬ ልብሰ ለብሰው፣ ተሰውረውም ቢገቡ ሰለሚያውቋቸው ይሸሹ ነበር:: ቴዎድሮስ በሌሉበት ጦር ከተላከ ግን ጦሩን ገትረው ይዋጉ ነበር:: ይህን ሁኔታም ምርጫ ወርቄ ነገረኝ ብሎ ከለመንት መርካም ዘግቦታል:: ሁኔታውም፣ መቶ የሚሆኑ የኦሮሞ ፈረሰኞች ታይተዋል ተብሎ ለንጉሡ ሲነገር፣ ማንንም ሳያስከትሉ፣ ብቻቸውን እየጋለቡ ወደ ሰዎቹ ሲገሰግሱ አይተው ሰዎቹ ሳይዋጉ ሸሹ:: ያን ጊዜ ምርጫ ወርቄ ከንጉሡ ጋር አብሮ እየተጓዘ ነበር::

ቁጥር 7፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ ባባታቸው በሀይሉ ወልደ ጊዮርጊስ በኩል ከአፄ ፋሲል ሀረግ የነጋሲ ዘር አላቸው:: በዝርዝር ሲታይ፣ የትውልድ ሀረጉ እንደዚህ ነው:: አፄ ፋሲል→ ልዕልት ሰብለ ወንጌልን → እንስት→ እንቁዋል→ ክንፈ ሩፋኤል→ ወይዘሮ ወለተ ገብሬ→ ደጃዝማች አልፍዮስ ህላዌ ነው:: ደጃዝማች አልፍዮስ፣ የቋራና የደምቢያ ገዥ የነበሩትን ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስን ይወልዳሉ:: ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስ የቋራውን ገዥ ደጃዝማች ሀይሉ ወልደ ጊዮርጊስን ይወልዳሉ:: ደጃዝማች ሀይሉ ከመጀመሪያ ሚስታቸው ከወይዘሮ ወለተ ተከሌ ስመ ጥሩውን ገዥ ደጃማች ከንፉን ሀይሉን፣ ደጃዝማች ገብሩ ሀይሉን፣ ደጃዝማች አንዳዋ ሀይሉን ይወልዳሉ:: ከወይዘሮ አትጠገብ ደግሞ ልጅ ካሳ ሀይሉን (አፄ ቴዎድሮስን) ይወልዳሉ:: ደጀዝማች ሀይሉ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበራቸው:: አንደኛዋ ወይዘሮ ወለተ ወርቅ ሌላኛዋ ደግሞ ወይዘሮ ዮሴፋ ነበሩ:: ወይዘሮ ወለተ ወርቅን፣ አፄ ቴዎድሮስ ከፈረንሳዩ መልከተኛ ከመሴ ሌዣን ጋራ አጋብተዋት ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ፣ እንግሊዛዊው ሄንሪ ዱፍተን፣ የደጃች ካሳ (አፄ ዮሐንስ) መልከተኛ፣ ምርጫ ወርቄ፣ ቴዎድሮስ የነጋሲ ዘር አላቸው ብሎ ነግሮኛል ይላል::

ቁጥር 8፣ ይህ ትንቢት ቀላል ግምት የሚሠጠው አልነበረም፣ አኤአ በ1830 አንድ ሰው፣ በጎንደር፣ ቀሀ የሚባል ወንዝ አጠገብ ጥሩምባ ነፍቶ፣ ቴዎድሮስ የሚባለው ንጉሥ አኔ ነኝ ብሎ አስነገረ፤ ተከታዮችም አግኝቶ ነበር:: ወዲያውኑ ግን በሥልጣን ላይ የነበረው ንጉሥ አሰፈልጎ ካገኘው በኋላ፣ በጎንደር በአደባባይ በሰቅላት አንዲቀጣ አድርጎታል:: ህዝቡ ነፃ የሚያወጣው ሰው ይጠብቅ ነበር:: ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ እንኳን፣ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት፣ ምን ያህል አውነት እንደሆነ ባይታወቅም፣ ቴዎድሮስ ነኝ ብሎ ጭፍራ ያስከተለ ሰው አንደወጣ፣ ሲታይ ግን፣ የሩሲያ ተወላጅ ሆኖ ሰለተገኝ፣ ምኒልክ ገንዘብ ሠጥተው ወደ ሀገሩ መለሱት የሚል ፅሁፍ አለ::

ቁጥር 9፣ ካሳ ሀይሉ፣ ቸንከር ገዳም እየተማሩ እያለ የደምቢያው ደጃማች ማሩ ሲሸፍቱ፣ በዚያን ጊዜ የበጌምድር ገዥ የነበሩት የራስ ይማም ጦር ገዳሙን ሰብሮ በመግባት አብረው የሚማሩትን አርባ ሰምንት ልጆች ሰልቦ ካሳን ትቷቸው ሄደ:: የካሳ መትረፍ ከእግዚአብሔር ነው በማለት ደብተራ ዘነብ ዘግበዋል:: ከዚህ በኋላ፣ በተለያዩ ባላባቶች ቤት ባለሟል በመሆን አገልግለዋል፣ ያደጉት ግን በታላቅ ወንድማቸው በደጃች ከንፉ ቤት ነበር:: ከንፉ ሲሞቱ በልጆቻቸው፣ በይልማና በመኮንን መሀከል በተደረገው ውጊያ፣ ካሳ የወገኑት ከመኮነን ጋር ነበርና፣ መኮንን ድል ሲሆን ካሳም ተማረኩ:: አብሮ አደግ በመሆናቸው ምሯቸው ያውም ዝነኛ፣ ጋማው ረዥም ፈረሳቸውን መልሶ ሰጣቸው(ታጠቅ የሚባለው ፈረሳቸው ይህ ይሆን?):: ከዚያ በኋላ አቶ ቢተዋ ከሚባሉ የቋራ ገዥ ቤት ነበሩ:: በዚሁ በፈረሳቸው ሆነው ባንድ ቀን ሁለት ዝሆን ገደሉ፤ ይህ ግን ቢተዋን ሰላስቆጣ፣ ቢተዋን ጥለው ሸሽተው በየቦታውና በሸፍትነት ኖረዋል:: ካሳ በሸፍትነት ዘመናቸው የሚታወቁት፣ የዘረፉትን መልሰው ለደሃ በማከፋፈል ነበር:: ባህሩ ዘውዴ፣ "የአቢሲኒያው ሮቢን ሁድ" ይሏቸዋል::

ቁጥር 10፣ ትምህርቱን ያገኙት በናታቸው በኩል ገዳም ተልከው ነው:: እናታቸው ኮሶ ሻጭ ናቸው ተብሎ ቢወራም፣ በሌላ በኩል ንብረት የነበራቸው ሌት እንደሆኑ ይነገራል:: የኮሶው ታሪክ አመጣጥ፣ ሴትዮዋ፣ በጎንደር ኮሶዬ የሚባል ቦታ የነበራቸውን መሬት አስፈርደው ሲመለሱ፣ አብራቸው የነበረች ሠራተኛ የኮሶ ፍሬ ሸምጥጣ ወደ ጎንደር ይዛ ስትሄድ ያዩ ሰዎች ናቸው ይህን ወሬ የጀመሩት ይባላል:: ወይዘሮ አትጠገብ ከዳሞቱ ደጃዝማች ወንድ በወሰንና የንጉሥ ዘር አለባቸው ከሚባሉት ከእናታቸው ከወይዘሮ ትሳል በዳሞት ነው የተወለዱት:: አፄ ቴዎድሮስ በኮሶ የተነሳ የተበቀሉት፣ ከአቴጌ መነን የተላከ ቀኛዝማች ወንድይራድ የሚባል ሰው ነው:: ወንድይራድ ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ ይገፍ አመጣለሁ ብሎ ፎክሮ ነበር፤ ሆኖም ሲማረከ፣ ካሳ ፉከራውን ሰምተው ስለነበር፣ እግዚአብሔርን አመሰግነው፣ ለወታደሮቻቸው፤ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛል ብለው ብዙ ኮሶ አሰበሰቡ:: ለቀኛዝማች ወንድይራድም፣ እናቴ ከገበያው ኮሶ ሳይሸጥላት ቀረ፤ አህል ታጣና ይህንን ኮሶ ተመገብ ብለው ለቀኛዝማቹ ሰጡ:: ይህን ሲያደርጉ ጦራቸውን ጭናቸው ላይ እንደያዙ ነበር:: ሰውየው ግማሹን እንደጠጣም አሰመለሰው (አስተፋው)::

ቁጥር 13፣ የልጅ ካሳ የመጀመሪያ ድል የሚባለው፣ በሸፍትነታቸው ጊዜ፣ ከሌሎች ሸፍቶች ጋር፣ እኔም ባገኝ እናንተም ብታገኙ ባንድነት እንድንበላ ብለው ተማምለው ነበር:: ሆኖም በቁጥራቸው በርከት ያሉት ሌሎቹ ሸፍቶች፣ ወንደሞቹ ሲገዙን የነበረው ላይበቃ አሱም የሌባ አለቃ ልሁን አለ ብለው ከካሳ ጋር የነበራቸውን መሀላ አፍርሰው ፍሪዳ አርደው መብላታቸውን የሰሙት ካሳ፣ ከአሰራ ሁለት ሰዎች ጋር ሆነው ገሰግሰው፣ ለምንድነው የከዳችሁ ብለው ሸፍቶቹን ሲጠይቁ፣ ሸፍቶቹ፣ እንተም የራስህን አኛም የራሳችን እንበላለን ባሉ ጊዜ፣ ካሳ ጎራዴ መዘው በለው ባሉ ጊዜ ሰባ ጋሻ(ሰባ ሰው) ሲሸሽ፣ ሰባቱ ተያዙና ተቀጡ:: አስራ ሁለት ሆነው ሰባውን

ሰው በእግዚአብሔር ሀይል አሸነፉ ተብሎ ተዘግቧል፡፡ ሰባቱ የከዱት ሰዎች፣ ከጉልበት በታች ነው የተቆረጡት፡፡ ይህ ደግሞ፣ ካሳ፣ ከልጅነት ጀምሮም ቢሆን ከህደት በጣም የሚጠሉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

ቁጥር 14፣ ለይስሙላ ንጉሥ የነበሩት ሣልሳዊ ዮሐንስን (ፃዲቁ፣ አንዳንዴም ጅሉ ዮሐንስን የሚባሉትን ለመጥቀስ ነው)፡፡ የራስ አሊ እናት፣ መነን፣ የአቴጌነት ማዕረግ ለማግኘት ሲሉ ሰውየውን አንደባል አድርገው ቢይዙም ሥልጣኑ ግን በሴትዮዋና በልጃቸው ነበር፡፡ ሰውየው መጀመሪያ ሳር አምባ፣ ከዚያም መቅደላ በአስር ኖረዋል፡፡ መነንና ልጃቸው ራስ አሊ የአሮሞ ባላባቶች ናቸው፡፡ ከነራስ ጉግሳ ጀምሮ ሀገሪቱን ቢያሰተዳድሩም፣ በሥርአቱ መሰረት የግድ ንጉሥ መኖር ስለነበረበት የጎንደር ነገሥታትን ለይሰሙላ አያስቀመጡ ሥልጣኑን ይዘው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ በህዝቡ ተቀባይነት ለማግኝት፣ ሀይማኖታቸውን ከአስልምና ወደ ክርስትና ይቀይሩ ነበር፡፡ በዚህ በተለይ በጣም የሚታወቁት ራስ ጉግሣ ነበሩ፡፡

አዚህ ላይ፣ በዘመኑ ሀይለኛ መሳፍንቶች ሰለነበሩት ሰለነራስ ጉግሣ ሥልጣን አመሰራረት መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ አፄ ተክለጊዮርጊስ የሚባሉ ንጉሥን ለመጀመሪያ ጊዜ፣ የየጁ ተወላጅ የሆነ፣ ራስ አሊ (ትልቁ) በአፈረዋናት ውትሜራ የሚባል ቦታ መታቸው፡፡ ከዚያም ሥልጣኑን በመረከብ ለአራት አመታት በጌምድርን ሁሉ ገዛ፡፡ አሱ ሊሞት ወንድምየው አሊ ጋዝ አምሰት ዓመት ገዝቶ ሞተ፡፡ ከዚያም የላስታ ሰዎች የሆኑ ራስ አሥራትና ራስ ወልደ ገብርኤል ሰባት አመት ገዝተው አርስ በርስ ሲጣሉ፣ ራስ ወልደ ገብርኤል ተሰደው ወደ መቅደላ በሸሹ ጊዜ፣ የመቅደላው ገዥ አመዴ፣ ጉግሣንና አሉላን ራስ ወልደገብርኤልን አንዲረዱ ላካቸው፡፡ ጉግሣ ግራዝማች ተብለው ፎገራ ተሠጣቸው፡፡ ጦርነቱም ወገራ ላይ ነበር፤ የራስ አሥራት ረዳቶች ደግሞ፣ ከጎጃም ራስ መርድ፣ ከሰሜን ራስ ገብሬ ነበሩ፡፡ በዚህ ጦርነት፣ ራስ ወልደ ገብርኤል፣ ራስ አሥራትና፣ ራስ መርድ ሞቱ፡፡ የተረፉት፣ የሰሜኑ ራስ ገብሬ ሸሹ፡፡ ድል የራስ ወልደ ገብርኤል ሰለነበር ልጃቸው ወንበሩን ያዝ ቢባል በአባቱ ሞት አያለቀሰ አምቢ አለ፡፡ አልጋው ከፍት በመሆኑ፣ አሉላ፣ ጉግሣን ባልጋው ተቀመጥበት ብሎ ሲመከር፣ ጉግሣ ደግሞ፣ ማን ሠጠን ብለን ነው በሰው አልጋ የምንቀመጥ ብሎ ሲጠይቅ፣ አሉላም፣ "ረቢ ሰጠን ብለን" ብሎ መከረ፡፡ ከዚህ በኋላ፣ አሉላ አንዲህ የሚል አዋጅ አስነገረ፤ "የሞትንም እኛ፣ ያለንም እኛ፣ ለጉግሣ ያልታጠቀ፣ ወንዱ ብልቱን፣ ሴቱ ደግሞ ጡቱ ይቆረጥ፡፡" ብሎ አስነገረ፡፡ ይህንን አዋጅና አፈፃፀም፣ ሌሎች የዘገቡት፣ ጉግሣ ወንበሩ ላይ ለመቀመጥ የግድ ክርስትናን ተቀብሎ መጠመቅ ሰለነበረበት፣ አንጠመቅም ያሉ የራሱ ዘመዶችን ብልትና ጡት አስቆርጧል ብለው ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ የየጁው ጉግሣ፣ በጌምድርን፣ ጎጃምን፣ ወሎን ሁሉ ለሃያ ሰባት አመታት ገዝተዋል፡፡ በራስ አሥራት በኩል የተሰለፉት ባላባቶች፣ ራስ መርድ የደጃች ተድላ ጓሉ አያት ሲሆኑ፣ ራስ ገብሬ ደግሞ የሰሜኑ ገዥ የደጃች ውቤ ኃይለ ማርያም አያት ናቸው፡፡

ይህን የምጠቅሰው ልጅ ካሳ ድረስ ለማምጣት ነው፡፡ ጉግሣ በሞቱ ጊዜ፣ ልጃቸው ይማም ተተከተው ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ገዙ፡፡ የዚህ የራስ ይማም ጦር ነው ካሳ ይማሩበት በነበረው የቸንከር ገዳም ገብቶ ካሳ ሲያመልጡ ሌሎቹን ተማሪዎች የሰለበው፡፡ ራስ ይማም ሲሞቱ፣ ወንድምየው ራስ ማርዬ በቦታው ተተኩ፡፡ ራስ ማርዬ ከትግራዩ ገዥ ከስባጋዲስ ጋር ደብረ ዓባይ ላይ ሲዋጉ፣ በስባጋዲስ ልጅ በሀጎስ ተገደሉ፡፡ ሆኖም ድሉ የራስ ማርዬ ወገን ሰለነበር፣ የራስ ማርዬ ሰዎች ስባጋዲስን ገደሉ፡፡ ከራስ ማርዬ ቀጥሎ ወንድማቸው ራስ ዶሪ ለሶስት ወር ከገዙ በኋላ ሲሞቱ፣ በምትኩ፣ የጉግሣ ልጅ፣ የዶሪ፣ የይማም፣ የማርዬ ወንድም አሉላ ሥልጣኑን ያዙ፡፡ አሉላ ለሀያ ሁለት አመታት ገዝተዋል፡፡

አሉላ ከመነን ራስ አሊን ወለዱ(ትንሹ ራስ አሊ)፡፡ አነዚህ መሳፍንቶች ሲገዙ፣ ነገሲታቱን በስም አያስቀመጡ ሥልጣኑን በጃቸው ይዘው ነበር፡፡ አሉላ ሲሞቱ ልጃቸው ራስ አሊ በናታቸው በመነን ሞግዚትነት ሥልጣኑን ያዙ፡፡ መነን ደግሞ ለአቴጌነት ማዕረግ ሲሉ፣ ለምስል የተቀመጡትን፣ የጎንደር ሰው ፃዲቁ ዮሐንስ አያለ የሚጠራቸውን ንጉሥ (ሳልሳዊ ዮሐንስን) አገቡ፡፡ በዚህ ዘመን ግን አንደ ደብተራ ዘነበ አገላለጥ ብዙ ነውር ነገር ይፈፀም ነበር፡፡ "ምንዝርና ከፍቶ ወንዶች በወንዶች ነውር ያደርጋሉ፤ ዘመዶቻቸው፣ ደሃን፣ የአበሻ ሰዎችን ሁሉ ይበድላሉ፤ መልካም መሰራትን፣ እግዚአብሔርን መፍራትን ትተው፣ በስም ክርስቲያን ተብለው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ፋንታ አስማት፣ ምንዝር፣ ስካር፣ ቧልት ባደረጉ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አምላክ ቀናኢ ነውና፣ ሁሉን የሚቀጣ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡" ይላሉ፡፡ አንግዲህ ቴዎድሮሰ የነበራቸው ጀግንነትና ብልህነት ሳይጎድል በዚህ መሀል ብቅ ማለታቸው ለነበራቸው ተከታይ መብዛት ምክንያትም ነበር፡፡ "ያባቶቼን አገር አረከሱት" የሚሉት አባባላቸውም በዚህ ምክንያት መሆን አለበት፡፡

ቁጥር 15፣ ሰለ ንግሥና ስማቸው ለወታደሮቻቸው የተናገሩት ደጃች ውቤን ሊወጉ ስሜን በዘመቱ ጊዜ ነበር፤ ሊቀመኳስ ቤል በሩቅ መነፀር የደጃዝማች ውቤን ካምፕ አይቶ አንደዲነግራቸው ከጠየቁ በኋላ፣ ካምፑ መኖሩን ሲነግራቸው፣ "አያሳድረኝ አላሳድረውም" ብለው፣ ወታደሮቻቸውን ሲያነሳሱ፣ "አንኳን ይህን ቁርጥማታም፣ ወሎን መትቼ የሸዋውን ንጉሥ አይዘዋለሁ፤ ስሜን ስሜን አነግራሃለሁ ያልኩህ ወታደር፣ ስሜ ቴዎድሮስ ነው፡፡" አሉ፡፡ ከዚህ በፊት አስቀድመው ወታደሩን በንጉሥ አምላክ በል፤ ስሜን ሰሜን አነግርሃለሁ ብለው ነበር፡፡

ቁጥር 18፣ ሰኔ ሀያ ሶስት፣ 1845(አኢአ) ራስ አሊ ያላቸውን ሀይል በሙሉ፣ የሰሜን፣ የደምቢያንና የበጌምድርን ጦር ይዘው ከካሳ ጋር አይሻል የሚባል ቦታ ውጊያ ገጠሙ፣ ብዙ ሰው አልቆ "ደሙ አንደጎርፍ ወረደ፤ ሬሳውም አንደ ካብ ሆነ፡፡"፣ ራስ አሊም ተሸንፈው ሸሹ፡፡ ድሉም የደጃች ካሳ ሰለሆነ፣ ደብተራ ዘነበ፣ "ንጉሥ በጠፋ በሰባ አንድ አመት፣ አግዚአብሔር ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡ የኦሮሞዎች ግዛት፣ በበጌምድር፣ በጎጃም፣ በላስታ፣ በየጁ፣ በወሎ በዚህ ነው ያለቀው፡፡" ይላሉ፡፡ አንግዲህ የተራ ጉዳይ ሆኖ ነው አንጂ፣ ራስ ማርዬም ቢሆን፣ የትግራዩን ባላባት፣ ከተከዜ እስከ ቀይ

ባህር ድረስ የነበረውን ግዛት ባንድ ጦርነት እንዳከተሙት ተገልጧል። ቴዎድሮስ የነሱት ደቻዝማች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በየካቲት አምስት ቀን ነበር።

ቁጥር 19፤ ስለ ስውነታቸው ጥንካሬ ሲነሳ፣ የብሪታኒያው መልከተኛ ራሳም፣ የወንዝ ዳርቻ ሲሻገር እንሽራቶት ሊወድቅ ሲል ቴዎድሮስ በፍጥነት በእጃቸው ይዘው እንዳወጡትና በአረብኛ አይዞህ በርታ ብለው መናገራቸውን ገልጧል። የንጉሡን የስውነት ጥንካሬ በእጃቸው አያያዝ ምስክርነት ይሰጣል። ራሳም ሲጨምርም፣ ንጉሡ ከድንጋይ ወደ ድንጋይ በባዶ እግራቸው በፍጥነት እየዘለሉ ሲንቀሳቀሱ በማየቱ የተገረመ መሆኑን ይገልጣል። በሌላ አጋጣሚ፣ ሄንሪ ዱፍተን የሚባል እንግሊዛዊ ያየውን ሲመሰክር፣ ቴዎድሮስ የኮርቻውን አርካብ ሳይረግጡ ዘለው ፈረሱ ላይ በመውጣት በፍጥነት አይጋለቡ ሲሄዱ አይቶ "ፈጣንና ንቁ" ናቸው ብሎ መስክሯል። ራሳም፣ ቴዎድሮስ ጉግሥ ሲጫወቱ፣ ከዚያም የውጊያ ትርኢት ሲያደርጉ አይቶ፣ ፍጥነትና የጦር እያያዛቸው የተለየ ነው ይላል። የሚገርመው፣ ይህንን ትርኢት ካሳዩ በኋላ፣ ወደ ራሳም ሄደው፣ "ሚስተር ራሳም፣ ራሳችን ለማዘናናት ባደረግነው በዚህ ኋላ ቀር ነገር መቼም አትስቅብን። የናንተን የውጊያ አይነት ለማየት በጉጉት አጠብቃለሁ።" ብለውታል።

ቁጥር 20፤ ቴዎድሮስን በመጀመሪያው የሥልጣን ዘመናቸው ተወዳጅ ሊያደርጓቸው የቻሉ በሳቸው በኩል የተወሰዱ ርምጃዎችን መጥቀስ ተገቢ ነው። ይህን የምጠቅሰው ደግሞ፣ ከእንግሊዛዊ ፀሀፊ፣ ከሄንሪ ዱፍተን፣ ያገኘሁትን ነው። ከብዙዎች የውጭ ፀሐፊዎች፣ ቴዎድሮስን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የገለጠ ቢናር ዱፍተን ነው። ይህ ምስክርነት ሰፋ ያለ ስለሆነ ያንባቢዎችን ትግስት በፅሞና እጠይቃለሁ። ዱፍትን በመጀመሪያ ስለቴዎድሮስ ገፅታ ሲገልፅ፣ "ጠየም ያሉ ሆነው ግን በምንም አይነት የኔግሮ ገፅታ አይታይባቸውም ይላል። ሲቀጥልም፣ ግንባራቸው ከፍ ብሎ ጎላ ወይም ወጣ ያለ ነው፤ መላ ገፅታቸው አውሮፓዊ ነው የሚመስሉት፣ ጠጉራቸው በወፍራሙ ተጎንጉኖ ባንገታቸው ጀርባ ይወርዳል። አይኖቻቸው ጥቁር ሲሆኑ፣ አሳት የለበሱ ይመስላሉ፣ ፈጣንና በስተው የሚገባ ዕይታ አለባቸው። አፍንጫቸው እንደ ሮማዊ አፍንጫ ሰልከክ ብሎ ጫፉ ላይ ሾል ብሎ ግን ለአመል ያህል ሰበር ይላል። አፋቸው በትክክል የተሠራ ሆኖ፣ ፈገግ ሲሉ ደግሞ በጣም ተሰማሚና፣ አስደናቂ ነው ይላል። መላ ባህሪያቸው፣ ሰው አክባሪ፣ አስደሳችና ሊጋስኑት ይታይበታል። ጠቅላላ ሁኔታቸው፣ እርፈው ተቀምጠው ቢሆን የብልህነትና የበጎ ስሜትን ያሳያል።" ይላል።

ቴዎድሮስ በተከታታይ ያወጧቸው አዋጆች እንደሚከተሉት ነበሩ። የመጀመሪያው፣ "ሁሉም ሰው ወደ ነበረበት ሙያ እንዲመለስ፤ ነጋዴው ወደ ንግዱ፣ ገበሬው ደግሞ ወደ እርሻው፤ በዚህ ለዋጅ፣ በእርስ በርስ ጦርነት ታምሶ የነበረው ህገር ወደ ሰላምና ብልፅግና እንዲመለስ ታስቦ ነው። ይህንን ህግ ለሚጠናከር፣ ወታደሮቻቸው ምግብ እየገዙ እንዲበሉ አንጂ፣ ገበሬውን እንዳይዘርፉ አደረጉ። ከዚያም መደበኛ የወታደር ሥርአት መሰረተው ደሞዝ እየተከፈለው እንዲተዳደር ለማድረግ አሰቡ። ይህ መደበኛ ወታደር ደግሞ ጠመንጃ የታጠቀ እንዲሆን ወሰኑ።

ነፃ የወጣውን ጦርና ጎራዴ ግን፣ ወደ ማረሻ፣ መቆፈሪያና የርሻ መሳሪያ እንዲቀየር ፉላንታቸው መሆኑን ገለጡ። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ገበሬው በየመንደሩ፣ በራሱ ዳኛ እንዲዳኝ እንጂ እየዘረፈ በማበላ ወታደር እንዳይዳኝ ወሰኑ። (የመጨረሻው፣ ከነጎላውደን ሪፖርት ነው) በጦርነት ምክንያት ተዘግተው የነበሩ የንግድ መንገዶች እንዲከፈቱ፤ የቀረጥና የግብር ሁኔታም ቀለል ያለ እንዲሆን አደረጉ። ለሥራ ከመጡት ሰዎች ጋር በመሆን መደበኛ መንገድ መስራት እንዲጀመር፣ መንገዶቹም ከሮብረታበር ወደ ጎንደር፣ ወደ ጎጃምና ወደ ዋናው ምሽጋቸው ወደ መቅደላ ሚወስዱ እንዲሆኑ ነበር። እንግዲህ አቢሲኒያን በመሰለ ሀብታም ህገር እንደዚህ ሊሪነት መደበኛ መንገድ ተሠርቶ አያውቅም ነበር። በሀገሪቱም የድንጋይ ከሰልና ሶብረት ማዕድን ያለባቸው ቦታዎች እንዲታሰሱ ፈልገው ነበር። በተጨማሪም ጉቋ የሆኑ የአቢሲኒያ ልጆች ወደ ውጭ ህገር፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ አገር ተልከው የእጅ ሙያ ተምረው እንዲመለሱ፤ የእጅ ባለሙያተኛ የሆኑ የውጭ ሰዎችም ወደ ህገሩ ሠሞተው ኗሪ እንዲሆኑ ለመሳብ ሞክሩ።

ምፅዋ በቱርኮች ቁጥጥር ስር ስለነበር፣ በቂ የጦር መሳሪያ ወደ መሀል አቢሲኒያ እንዲገባ ስለማይፈቅዱ፣ ቴዎድሮስ፣ መሳሪያዎች በመሀል ህገር መሰራት እንዳለባቸው ሠስነዋል። በጉበ የባለገውና ሥርአት ያጣው የዳኝነት ሥርአት እንዲታደስ ያደረጉ ሲሆን፣ ለዚህም ድጋፍ ለመስጠት፣ በሄዱበትና ባረፉበት ቦታ ሁሉ የይግባኝ ሰሚ ፉርድ ቤት በማቋቋም የተበደሉ ሰዎችን ከርከር ራሳቸው መስማትና መብየን ጀመሩ። (ይህንን ይግሰኝ ሰሚነት እውሮፓውያኑ ሲያናንቁት ይታያል)

ለድሆች የተለየ እንክብካቤ በማድረግ፣ ችግራቸውን ማዳመጥና፣ ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊትም ምፅዋት ይሰጡ ነበር። በሰብአዊ ርህራሄ ሰሜትና እንደ አሱተዳደራቸው ፖሊሲ በመቁጠር በዘመቱበት ቦታ ሁሉ ለድሆች ገንዘብ ይበትኑ ነበር። በዶከተር ከረፐ ሚሲዮናዊ ጥናት ውስጥ የተገኘ መረጃ እንደሚጠቁመው፣ ቴዎድሮስ፣ "እኔ ራሴ ድሃ ነበርኩ፤ ድሆችን ባልረዳ፣ ለፈጣሪ ስሞታ ያቀርባሉ" ይሉ ነበር። ለናፒየር በፃፉት በመጨረሻው ደብዳቤ፣ "ራሴ የምጦራቸው ሰዎች" ብሣለት፣ የሚያስተዳድሯቸው ባልቴቶች፣ ሴቶችና ህፃናት እንደነበሩ ይጠቅሳሉ። በተለያዩ ጊዜያት የሚሠጡት ፍርድም በስው መወደድንና መደነቅን አትርፎላቸው ነበር። ሁለት ምሳሌዎች ለመጥቀስ፣ ሁለት ሰዎች ተካሰው ንጉሥ ፊት ቀረቡ፣ እንደኛው ላንዱ ፈረስ በትውስት ሠጥቶት ናሮ፣ ተቀባዩ ግን ይክዳል። ሠጭው ለተቸዋለሁ ብሎ ሲምል፣ ተቀባዩ አግዚአብሔርን በመፍራት መቀበሉን ያምናል። ይህን የሰሙ ቴዎድሮስ፣ ስውየው በነበረው ፈሪሀ አግዚአብሔር ምክንያት፣ አዳውን አኔ አክፍልሃለሁ በማለት ለከሳሹ ፈረስና ብር ሠጥተዋል።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ፣ ቢጋይንት አያሉ፣ የቴዎድሮስ ወታደር ባላገር ይገድላል። ዘመዱ የሞተበት ሰው ንጉሥ ፊት ቀርቦ ጮኸ፤ ቴዎድሮስ ወታደሮቻቸውን ቢጠይቁ (በአፈርሳታ)፣ ወታደሮቹ አላደረግንም አሉ። ንጉሡም ተጨንቀው ነበርና አስበው እንዲህ አሉ፤ "ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ፤ ብዬ ያዘዝኩ እኔ ስለሆንኩ፣ ደመኛህ እኔ

ነኝ፣ አኔን ግደለኝ::" ብለው ገበሬው ነገሩት:: ባለ ደሙ (ዘመዱ የሞተበት ሰው)፣ እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም አለ:: ንጉሡም ብዙ ብር ሠጥተው ሰደዱት::

በሀይማኖታቸው፣ ያባቶቻቸውን ሀይማኖት የሚጠብቁ ቢሆኑም፣ በገዳም ሲማሩ(ቸንከር) ያስተዋሉትን በመገንዘብ፣ ቤተክርስቲያኗም ሆነ የመንግስት ሥርዐት ለውጥ ማድረግ አንደሚገባቸው ወስነዋል:: ቁጥራቸው የላቀ ቄሶችና ደብተራዎች፣ የግዛታቸውን ጠቅላላ መሪት አንድ ሶስተኛውን ይቆጣጠሩ ነበር:: ይህ ለቤተክርስቲያን ሲሶ ወይም አንድ ሶስተኛ መወሰን አመጣጥ፣ በዛጉዌ ሥርወ መንግስትና በሰሎሞን ሥርወ መንግሠት መሀከል በመነኩሴው በተከለሀይማኖት አማካኝነት ከተደረገው ስምምነት ነው:: ካህናቱ ይህንን መሬት ለገበሬዎች በኪራይ እያሳረሉ፣ የተንደላቀቀ ኑሮና፣ አልፎ አልፎም ስካርና የረከሰ ባህሪ ያሳዩ ነበር:: ቴዎድሮስ፣ ከደብሮች አካባቢ የተወሰኑ መሬቶች በሰተቀር፣ ሌላው ወደ መንግሥት እንዲመለስ አደረጉ:: ይህ ውሳኔያቸው ከካህናቱና መነኮሳቱ የመረረ ጥላቻ ቢያመጣባቸውም፣ ቴዎድሮስ ለድሆች በሚያሳዩት ደግነት፣ ከሀይማኖት ጋር ጠብ እንደሌላቸው ምስከር ሆነ:: ከዚህ ከተወረሰ መሬት የሚገኘው ገቢ ደግሞ ለወታደሮቻቸው ደሞዝና ለሌላው ለሀገሪቱ ዕድገት ለሚያስቡት ዕቅድ የሚውል ሆነ:: ራሳቸው ግን፣ እንደ ተራ ሰው እንጂ ንጉሣዊ ያልሆነ ኑሮ ይኖሩ ነበር:: ይህ አኗኗር፣ ከመጨረሻ ሚስታቸው ከአቴጌ ጥሩ ወርቅ ጋር የግጭት መንስኤ ነበር:: አቴጌዋ፣ ንጉሡ አንደ ንጉሥ እንዲኖሩ ትመኝ ነበር::

ቴዎድሮስ፣ የተበተነ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ በራሷ በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ውስጥ ከባድ የተከፋፈለ ወገን ነበር ያጋጠማቸው:: ይህ ከፍፍል ደግሞ ከጠብ አልፎ ለውጊያና ለእርስ በርስ ግጭት የዳረገ ነበር:: ከፍፍሉ የመጣው በከርሰቶስ ባህሪ ትርጉም፣ በአንድ ወገን ፀጋ፣ በሌለው ወገን ቅባት እንዲሁም ካራ እየተባሉ በሚጠሩ በቤተክርስቲያኗ ሊቃውንቶች መሀከል ነው:: ቴዎድሮስ በሀይላቸው የተበነውን ሀገር ሲያገናኙ፣ አብረዋቸው የነበሩት፣ አቡነ ሰላማ ደግሞ ሀይማኖቱን አንድ ለማድረግ ጥረው ነበር:: በዚህ በኩል ቴዎድሮስ የሞከሩት ሳይሳካ ቀርቶ፣ በኋላ አፄ ዮሐንስ (አራተኛ)፣ ሊቃውንቱን ቦሩ ሜዳ ላይ አከራከረው ነው አንድነት የተፈጠረው:: ይህንን የነበረ፣ በትርጉም የተነሳ ከፍፍል፣ የኦሁኑ ዘመን የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች አምብዛም አያውቁም:: አሁን ያለቸው ቤተክርስቲያን በትርጉም ሳይሆን በሌላ መንገድ ተከፋፍላ ትታያለች:: ቤተክርስቲያኗ፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ ጉልህ የሆነ የሀገር ወዳድነት ስሜት ያንፀባረቀችበት ጊዜ ቢሆንም፣ በሌሎች ታሪኮች ግን የራሷን ጥቅም ለመጠበቅ ስትል ለዕደገት እንቅፋት እንደነበረች ግልፅ ነበር:: የቤተክርስትያን መሪዎችን የመረረ ጥላቻ የተቀበለ መሪ አንደ ቴዎድሮስ ያለ የለም:: በተገኘው አጋጣሚ ንጉሡን በአደባባይ ይዘልፉም ነበር:: በዚህ እንድ የሚጠቀስ ነገር ቢኖር፣ ንጉሡ፣ ከደብረታቦር ተነስተው መቅደላ በመከራ በደረሱበት ጊዜ፤ ሁለት ካህናት፣ ንጉሡን፣ እርስዎ ሀይማኖትዎን ከደዋል፤ ፆሙን አላከበሩም፤ ወታደሮችዎም ሥጋ እንዲበሉ አድርገዋል፤ ብለው ሲኮንኗቸው፤ አፄ ቴዎድሮስ ግን፣ በተለመደው ስድባቸው፣ "አህዮች" በማለት፣ መቅደላ ላይ መልሼ ባያችሁ፣ በጅራፍ ነው

የማስገርፋችሁ በማለት፣ ሰዎቹ ከነህይወታቸው ከመቅደላ እንዲወጡ አድርገዋል:: ካህናቱ ቴዎድሮስን በሀይማኖት ስማቸውን እንደሚያጠፉ፣ ንጉሡ ይህንንም እንደሚያውቁ፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ ለናፒየር በፃፉት የመጨረሻ ደብዳቤያቸው ገልጠውታል::

ሌላው አዋጅ፣ ትዳር በአንድ ወንድና ሴት መሀል እንዲሆን አንጂ ብዙ ሴቶች ማግባትን የሚከለከል ነው:: በርግጥ ይህ ህግ የነበረ ቢሆንም፣ ብዙ ሰዎች ህጉን ይተላለፉ ስለነበር ህጉን የሚያስከበር አዋጅ ነው የወጣው:: ከአዋጁ በተጨማሪ፣ አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው፣ ለቸገራቸው ሰዎች ገንዘብ አየሠጡም ያጋቡ ነበር::

ሌላው ተጨማሪ ህግ፣ በግዛታቸው ውስጥ የባሪያ ንግድ እንዲቆም ማድረጋቸው ነበር:: በዚያን ጊዜ፣ እንደ ዱፈተን ገለጣ፣ የባሪያን ንግዱን የሚያካሂዱት ሞስሊሞች ሲሆኑ፣ በባሪያነት የሚጋዙት ደግሞ በደቡብ በኩል የሚገኙ ተወላጆች ነበሩ:: ጎጃም ውስጥ ባሶ የሚባል የገበያ ቦታ ዋና መናህሪያ ሲሆን፣ ከዚህ ተነስቶ በምፅዋ ሆነ በመተማ በኩል ንግዱ ወድ ውጭ ድረስ ይሄድ ነበር:: በቴዎድሮስ፣ የራሱን ወገን ክርስቲያን የሆነን ዜጋ የሚሸጥ ከተገኘ የሞት ቅጣት ይፈረድበት ነበር:: ሆኖም የተጠለፉ ክርስቲያኖች በግድ ወደ ሙስሊምነት እንዲቀየሩ ቀደርገው በቱርክ ግዛቶች በሙሉ ይሸጡ ነበር:: ሰዎቹም፣ አንድ ቀን ሁሉ ወደ ሀገራችን እንመለሳለን በማለት ለሚያምኗቸው ሰዎች ክርስቲያን እንደነበሩ ይናገሩ ነበር:: አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው ባሶ ገበያ ድረስ ሄደው፣ ለሽያጭ የቀረቡትን ባሮች ከወሰዱ በኋላ፣ በበጌምድር፣ ጉና የሚባል ቦታ በመውሰድ ነፃ ለቀው፣ "የወደድካትን ሥረጥ" በማለት አርስ በራሳቸው ተመራርጠው እንዲጋቡ ፈቅደው አጋብተዋል::

ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ያዩትን ግፍና በደል ለማስወገድ ነበር ከቋራ ጀምረው የተነሉት:: ሌሎችም እሰከ እለተ ሞታቸው ድረስ አብረው የወደቁ ይህንን የቴዎድሮስን አላማ የሚደግፉ ሰዎች ነበሩ:: እንደ ዱፍተን አገላለጥ፣ አንደ ቴዎድሮስ ያለ ሀገር ወዳድ ንጉሥ በዚያች ሀገር ተፈጥሮ አያውቅም:: ቴዎድሮስ የጠፋውን የአባቶቼን ሀገር እመልሳለሁ በማለት የተለያዩ ግዛቶችን በጉልበት በማዋሀድ ኢትዮጵያን እንደገና መሰረቱ:: አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከቀድሞዋ ኢትዮጵያ በስፋት ያነሰች መሆኗን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ቱርኮች የምፅዋን ወደብ እኤአ 1570 ጀምሮ ለብዙ አመታት ይቆጣጠሩ ነበር፤ ግብፆችም በምዕራቡ ድንበር የታቻላቸውን ያህል መሬት እየወሰዱም ነበር:: ለዚህም ይሆናል፣ ቴዎድሮስ ለራሻው ዛር ኒኮላስ የወዳጅነት ስሜት የነበራቸው:: ከቱርኮች ጋራ በከሬሚያ ስለሚዋጋ:: ለኒኮላስ፣ ሶርያን አብረን እንውጋ በማለት ደብዳቤ ልከው እንደነበር ይነገራል:: ያባቶቼን ሀገር አረከሱ የሚሏቸውን የውስጥ መሳፍንቶች አንበርከከው፣ ረዥሙ ዕቅዳቸው ቱርኮችን ከግዛታቸው አስለቅቀው ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት ነበር:: አዚህ ላይ አንባቢ ነገሩን ወደ አስላምና ክርስቲያን እንዳይቀይር መጠንቀቅ አለበት:: ቴዎድሮስ የሀገራቸው ጠላት ከሆነ፣ አስላም ሆነ ክርስቲያን አይለዩም:: ገና በሽፍትነት ዘመናቸው፣ ኢድሪስ የተባለ ሻንቅላ ተወላጅ ወዳጃቸውና አጋራቸው እንደነበረ መታወስ አለበት:: ከዚህ በተጨማሪ፣ ቴዎድሮስ፣ በሉዳን ለነፃነታቸው የሚታገሉ

በግብፅ ላይ የተነሱ አማፅያንን ይረዱ ነበር፤ የአመፁ መሪ የነበረው ወድ መከ ነምሪ፣ በቴዎድሮስ ግዛት ሥር መጠለል ብቻ ላይሆን፣ በቴዎድሮስ ሰም ሱዳን እየዘለቀ ግብር ይሰበሰብ ነበር:: ለዚህ ደግሞ ሌላ የሚጠቀስ ሁኔታ ቢኖር፣ ቴዎድሮስ በጣም ያሰቸገራቸውና አልጨበጥ ያላቸውን አመፀኛ አመዴ በሽርን ሲያሳድዱ፣ አንድ መሰሊም፣ ሰው ገድሎ ፊታቸው ይቀርባል:: ንጉሡም ሰውየውን፣ ምን ብለህ ገደልከው ብለው ይጠይቃሉ፤ ገዳዩ ሲመልሰ፣ ወንድሜን ሰለገደለ ነው ይላል:: ቴዎድሮስም፣ ወንድምህን እሱ እንደገደለው በምን አወቅህ ብለው ሲጠይቁት፣ ሰውዬው ሲመልሰ፣ ካፊርና(ክርስቲያን) አሰላም፣ ከነቢዩ ጀምሮ አሰከ ግራኝ፣ ከግራኝ አሰካሁን ደመኞች ነን ይላል:: ቴዎድሮስ ሰውየውን ከቀጡ በኋላ፣ "ከአመዴ በሽር ጋር የተጣላነው ባገር ነው ብዬ ነበር የውነት ደም ነን" ብለዋል:: ደመኞች ነን ማለት፣ አንዱ አንዱን ለመግደል ቀድሞ የወሰነ ወይም በሞት የሚፈላለግ ማለት ነው:: እንደሳቸው አባበል፣ ውጊያው የአገር ጉዳይ ነው የነበረው::

በሀገራቸው፣ ሌላ አይነት የክርስትና እምነት እንዲሰበክ እንዳልፈቀዱ ይታወቃል:: አይሁዳውያንን ወደ ክርስትና እምነት ለመቀየር ከአወሮፓ ተነሰተው የመጡ ሚሰዮናውያን፣ ሰዎቹን ወደክርስትና እምነት ቢቀይሩም ወደ ኦርቶዶክሰ ሀይማኖት እንጂ ወደ ሌላ እንዳይሆን ቴዎድሮስ አግደው ነበር:: በክርስትና ሀይማኖት ሰም፣ በተዋህዶና በካቶሊክ፣ እንዲሁም በራሷ በተዋህዶ ውስጥ የነበረው ክፍፍል ብዙ ብጥብጥ ያስከተለና ለህይወት ማለፍ ምክንያት እንደነበረ ንጉሡ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር:: ንጉሡ ፀሎት አሰልሰው አያውቁም ነበር፤ ቤተክርስቲያን መድረስ ካልቻሉ፣ ከሰዎቻቸው ዞር ብለው ወደ ጫካም ቢሆን ገባ ብለው ይፀልዩ ነበር:: ይህን ሁኔታ ያስተዋለው ራሳም በመፅሐፉ ዘግቦታል::

ይህን ሁሉ ዕቅድ ያወጡት፣ ለድሃ ህዝብና፣ ለተበደለው፣ ለተማረረው መልስ የሰጡ ንጉስ በየቦታው አመፅና ሽፍትነት ሲጀመር በጣም መናደዳቸው የሚገርም አይሆንም:: ከዚህ በተጨማሪ የአጋራቸው፣ የባለቤታቸው፣ ኦሮሞዋ አቴጌ ተዋበች ሞትና፤ የወዳጀቻቸው የሊቀ መኳስ ዮሐንስ(ጆን ቤል) እንዲሁም የቆንስል ፕላውደን ሞት በጣም እንደቀየራቸው ይታወቃል:: ሊቀ መኳስ ዮሐንስ (ጆን ቤል)፣ ለአፄ ቴዎድሮስ የሼክስፔርን ሥራዎች ያነብላቸው እንደነበርና አሳቸውም የሼክስፔርን ፅሁፎች፣ "የዮሐንስ መፅሐፍ ቅዱስ" ይሉ ነበር:: አፄ ቴዎድሮስ ለተዋበች የነበራቸው ፍቅር የተለየ እንደነበር በሁሉም ታሪክ ዘጋቢዎች ይጠቀሳል:: ቴዎድሮስና ተዋበች አንድ ላይ ሲሆኑ መፅሐፍ ቅዱስ አብረው ያነቡ ነበር:: አቴጌዋ ሲሞቱ፣ ቅኔ ይችላሉ የሚባሉት ቴዎድሮስ የገጠሙትን ማስታወሰ፣ ንጉሡ ለባለቤታቸው የነበራቸውን ሰሜት ይገልፃል:: ግጥሙም፣ "አስኪ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ፣ አቴጌ ተዋበች ሚሰት ናት ገረድ" የሚል ነበር:: አቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ፣ አንድ ጊዜ፣ በእርካብ ምክንያት እግራቸው ቆስሎ አልድን ሲል ያዩ ተከታዮቻቸው፣ "አይ፣ ምሽቱ ነበረች እንጂ ሀብቱም ንብረቱም፣ እሷ ከሌለችማ ምን ዋጋ አለው::" ሲሉ ተሰምተዋል:: አሳቸውን በጣም ያበሳጫቸው የሚመስለው ግን፣ ራሳቸው የተራ ሰው እየኖሩ ሲረዷቸውና ኑሯቸው እንዲሻሻል ቀን ከሌሊት የሚጥሩላቸው የሀገሪቱ ዜጎች፣ ንጉሡን በሚፃረር

መንገድ ሲሰለፉ በማየታቸው ነው:: ለዚህ ደግሞ ይህ የቴዎድሮስ አባባል ዋቢ መሆን ይችላል:: "እኔ ያሰብኩት" ይላሉ ቴዎድሮስ፣ "ፈጣሪ ያስነሳኝ ለህዝቡ በረከት እንድሆን ነበር፤ ነገር ግን፣ እንዳየሁት ከሆነ ተሳሰቻለሁ፤ ለዚህ ነው መድፌ ላይ፣ "ቴዎድሮስ የርጉማኖች መቅሰፍት የሚል ፅሁፍ ያሰቀረፅኩበት" (የመጨረሻው፣ ከሌጃን መፅሀፍ የተወሰደ)

★ጥር 21፣ በአመፅ ከተነሳ፣ የመጀመሪያው የነበረው፣ ራሳቸው ጎጃም ላይ የሾሟቸው፣ ተድላ ጓሉ መሸፈት ነበር:: ከዚያም ደግሞ ዘመቻ በወጡበት ጊዜ ከፍተቱን በመጠቀም፣ የወንድማቸው ልጅ፣ ጋረድ ከንፉ፣ በመሸፈት ጎንደርንና የሰሜን ከፍሉ መበዝበዝ ጀመረ:: ይኸው የወንድማቸው ልጅ ነው እንግዲህ ለሁለቱ እንግሊዛውያን ወዳጆቻቸው፣ ለፕላውደንና ለጆን ቤል ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው::

የኦሮሞ አመፅ ከተነሳ፣ ቴዎድሮስን በጣም ያወካቸው አመዴ በሽር የሚባል ሰው ነው:: ሰውየው፣ ንጉሡ በዘመቱበት ቁጥር ሰለሚሸሽ በእጃቸው ሲገባ አልቻለም:: በሱ ጦስ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል፤ የብዙ ሰዎች ሕይወትም አልፏል:: በሱ ምክንያት ንጉሡ ወሎን ሰባት ጊዜ ነው የተመላለሱበት:: ቴዎድሮስ አገሩን አስገብረው ሲሄዱ ወይም ወደ ሸዋ ሲሻገሩ ከጀርባቸው በሚሸፍተው ሰው ላይ ከባድ ቅጣት ነበር የሚያደርሱት:: በተረጋጋ ጊዜ ትዛዝ ተላልፍው የገበሬ የቁም ከብት አርደው የበሉ የራሳቸውን ወታደሮች እንኳን ይቀጡም ይገሉም ነበር:: በአመዴ በሽር የተነሳ፣ የራሳቸው በቅርብ የሚተማመኑባቸው የመቅደላ አዛዥ የነበሩት ግራዝማች አለሜ ከድተው ነበር(በኋላ ደጃዝማች):: ይህም የሆነው ከአመዴ በሽር ጋር ተላልከሀል ተበለው ንጉሡ ይገድልሃል ብሎ የራሳቸው ሎሌ ሰለነገራቸው ነው:: በሸዋም ቢሆን፣ ቴዎድሮስ የሾሟቸው መርዕድ አዝማች ሀይሌን፣ ስራህ ብዙ የሚባል ሰው የአመዴ በሽርን መልከተኛ በሚስጥር ተቀብለህ አልብሰህ ሰደሃል ብሎ በቴዎድሮስ ፊት ከሰሳቸው:: መርድ አዝማቹ፣ መልከተኛው መጥቷል ግን አይሆንም ብዬ መልሼ ሰደድኩት ብለው አመኑ:: ቴዎድሮስም መርድ አዝማቹን አሰረው፣ ስራህ ብዙን፣ ሸዋ ላይ ማንን ልሹምበት ብለው ቢጠይቁ፣ ስራህ ብዙ፣ አቶ ዳርጌን ቢሾሙ ሸዋ ደስ ይለዋል ሰላሉ፣ የንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ልጅ አቶ (አቤቶ) ዳርጌ ተሾሙ:: በሰሰተኛው ቀን ግን፣ ጃራ የሚባል ሰው፣ ራሱን ስራህ ብዙን ከዳርጌ ጋር ውሥጥ ለውሥጥ ተማምሏል ገንዘብም ከፍሏል ብሎ ቴዎድሮስ ፊት ከሰሰው:: ነገሩ ሲጣራ ውነት ሆኖ ስለተገኝ፣ አቶ ዳርጌም ታሰሩ፣ ስራህ ብዙም በንጉሡ ተወረፈ:: በተጨማሪም፣ የለገ ጎራና የወረ ኢሉ ገዥዎች ከአመዴ በሽር ጋር ተነጋግረሃል ተባብለው እርሰ በርሰ ተካሰው ሁሉቱም ቴዎድሮስ ፊት አመኑ:: ሁለቱም ሰላመኑ፣ ቴዎድሮስ ቅጣቱ ወደ እሰር ብቻ እንዲቀየር አደረጉ:: እንግዲህ መቅደላ ላይ የተሰበሰቡ የአቢሲኒያ አስረኞች፣ በተለይ የባላባቶቹ አመጣጥ በአብዛኛው በዚህ ምክንያት ነው የነበረው:: እስረኞቹ፣ አውሮፓውያኑ እንደሚያሰወሩት ሁሉም ከጥፋት ንፁህ የነበሩ ሰዎች አልነበሩም:: የተወሰኑ የራሳቸውን ሰዎች በፍራቻና በጥርጣሬ አስረዋል:: አቤቶ ዳርጌም መቅደላ ነበሩ:: ቴዎድሮስ ከእሰራት ይልቅ በሞት መቅጣት ይችሉም ነበር:: ዳርጌ የአፄ ምኒልክ አጎት ናቸው:: ቢያሰሯቸውም፣

ቴዎድሮስ፣ ዳርጌን፣ "ዳሩ" ብለው ይጠሯቸው ነበር፡፡ የመርድ አዝማች ማዕረግ ከተነሣ፣ የሸዋ ገዥዎች በሳህለ ሥላሴና በሀይለ መለኮት ጊዜ ራሳቸውን ንጉሥ እያሉ እንደሚጠሩ ግልፅ ነበር፡፡ ሆኖም አፄ ቴዎድሮስ፣ ሸዋን ካስገበሩ በኋላ ነው ንጉሥ የሚባል ማዕረግ እንዳይጠቀሙ በመከልከል የመርድ አዝማች ማዕረግ የተጀመረው፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ከኦሮሞዎች ጋራ ብዙ ጦርነቶች ቢያካሂዱም ኦሮሞና አማራ አንድ ለማድረግ አስበው የማሉበትን ታሪክ መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ ንጉሡ በወሎ ከተለያዩ የኦሮሞ ባላባቶች ጋር ተዋግተዋል፡፡ በዘመቻቸው በአንዱ፣ ጊምባ የተባለ ቦታ ሲሄዱ አሮሞ አንድነት ሆኖ ከበባቸው፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስም በትንቢት ፈከሩ፣ አንዲህ ብለው፣ "አሮሞና አማራን ባንድ ሰደቃ(ማዕድ) ያላበላሁ አንደ ሆነ አኔ የከርስቶስ ባሪያ፣ የቅዱስ ዮሐንስ ለት፡፡ ከርስቲያን አትበሉኝ፡፡" አሉ፡፡ በጳጉሜ፣ ኦሮሞ ሁሉ ከበበ፣ ጊምባ ላይ፤ ንጉሥ ቴዎድሮስም ከፊተኛው ሰልፍ ቁመው፡፡ ከኋለኛው ሰልፍ ብዙ ፈረሰኛ አዙረው ሰደዱበት ይሉና፣ ደብተራ ዘነብ ሲቀጥሉ፣ ከጦርነቱ በኋላ፣ የዘመን መለወጫ ዕለት፣ ኦሮሞ ሁሉ ከተት ብሎ ገባ (ለአፄ ቴዎድሮስ)፡፡ አንደ ንጉሡም ትንቢት ሆነ፤ ሠራዊታቸው ሁሉ ተደነቀ፡፡ ባንድ ሰደቃ አበሉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፣ ቴዎድሮስ የሚወዷት ሴት፣ ወይዘሮ (አንዳንዶች አቴጌ ይሏታል) የተመኙ የየጁ አሮሞ ነበርች፡፡ አንግዲህ አቴጌ ተዋበችንም ሳንዘነጋ ነው፡፡ ሀይሉ የሚባለው አንደኛው ልጃቸው የተወለደው ከሌላ የኦሮሞ ሴት ነበር፡፡

ቁጥር 22፣ አፄ ቴዎድሮስ በራሳቸው አነሳሺነት ባለሙያተኞች አንዲያመጣላቸው ደብዳቤ የላኩለት ስው ሳሙኤል ጎባት ይባላል፡፡ አቡን ነበር፡፡ በደብዳቤያቸው፣ ቄሶች እንደማይፈልጉ ገልፀው፤ "አሳት የሚተፋ፣ ለርሻ የሚሆን ተሸከርካሪ መኖሩን ሰምቻለሁ"፤ በማለት ጥበበኞች አንደሚፈልጉ ገልጠውለታል፡፡ ሆኖም ሳሙኤል ጎባት ግን በጥበበኞች ፋንታ ኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰባኪ ሚሲዮናውያንን በመቀስቀስ፣ ወንጌላቸውን በኢትዮጵያ የሚሰብኩበት ጊዜ ደርሷል በማለት ሚሲዮናውያኑ ጥበበኛ መስለው አንዲገቡ በመምከር ወደ ኢትዮጵያ አንዲሚጡ አደርጓል፡፡ ንጉሡ የፈለጉትን አላገኙም፡፡

ቁጥር 23፣ አንግሊዛዊ ቆንስል ፕላውደን (በቴዎድሮስ አጠራር፣ ቡላዲን) የንጉሡ አማካሪ ነበር፡፡ ፕላውደን መጀመሪያ ከራስ አሊ ጋራ ስምምነት ፈርሞ ነበር፡፡ ፕላውደን፣ ከራስ አሊ ጋር በተደረገው ሰምምነት መሠረት የእንግሊዝ ባንዴራ ጎንደር ላይ አንዲውለበለብ ሲጠይቅ፣ ቴዎድሮስ በቁጣ ገንፍለው፣ "ምን? አኔ እንደ ተራው ሎሌ አሊ መሰልኩህ አንደዚህ በድፍረት የምታናግረኝ? እንደ አሊ ያለ ከሀዲ አሽከርስ ከውጭ መንግስት ጋር ውል መግባት ይችላል?" በማለት ባንዴራው አንዳይውለበለብ ከልከለዋል፡፡

ቁጥር 24፣ በዘመኑ የነበሩ ባላባቶችና ህዝቡ ከቴዎድሮስ ምኞትና አሠራር ጋር የሚጣጣሙ አልነበሩም፡፡ ይህንንም ቴዎድሮስ ከራሳም ጋራ በተለዋወጡት አነጋገር፣ በአንደበታቸው ይገለፃል፡፡ ንጉሰ ነገሥቱ እንዲህ ብለዋል፡፡ "በሰላም አንዲኖሩ

ሞከርኩ፤ አንደሠለጠነው አለም ወደሥልጣኔ እንዲሄዱ ታገልኩ፤ በሥርአት እንዲኖሩ፣ ልጆቻቸው ተስፋ አንዲኖራቸው ሞከርኩ፡፡ ነገር ግን ከፉ ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡ የራሳቸውን ሰዎች ነው፡፡ በተጨማሪ፣ ከመልከተኛው ከራሳም ጋራ ሲነጋገሩ፣ የሸፈቱ ሰዎችን ምን ላድረጋቸው ብለው ሲጠይቁት፣ ራሳም የህንድን ምሳሌ በመጥቀስ፣ ንግሥቷ በመላው ህንድ ላመፁት በሙሉ ምህረት አድርጋለች በማለት ሲነግራቸው፣ ቴዎድሮስም ፈገግ በማለት መልሰው፣ "የአቢሲኒያ ሰዎች እንደሌሎች ሰዎች ናቸው ብለህ ታሰባለህ? ከፉ ናቸው፣ ምክርም አይሰሙም፡፡ አኔ ትክክል እንደሆንኩ ለማሳየት፣ ለሁሉም ሽፍቶች የምህረት አዋጅ አሁን አስነግራለሁ፡፡ ግን ታያለህ፤ አንዱም እንኳን ቢሆን አዋጁን አይቀበሉም፡፡" አሉ፡፡ ከዛ በኋላ አዋጁ ሲነገር አንዲሰማ አንደኛውን አሰተርጓሚዬን አንድልከ ጠየቁኝ፡፡ አዋጁም ተነገረ፤ የኔ አሰተርጓሚም ምስከር ነበር፡፡ ይላል ራሳም፡፡

ቁጥር 25፣ አፄ ቴዎድሮስ የህዝቡን ባህሪ በደንብ የተገነዘቡ መሆኑን የሚያሰረዳ ከራሳም ጋር ያደረጉት ልውውጥ አለ፡፡ ራሳም በአሰተርጓሚው በደሲታ አማካኝነት እንዳንዴ በአረብኛ አንዳንዴም በትግርኛ፣ ንጉሡ የተለያዩ ርእሶችን አንስተው ስናወራ ይላል፣ ቴዎድሮስ ስለ ግብር አሠራር ጠየቁኝ ይላል፡፡ እሱም በሀገሩ አንዴት የገቢ ግብር እንደሚሰበሰብ ስነግራቸው፣ "ያገሬ ሰዎች በገንዘባቸው ነግደው ለኔ ግብር ከሚከፍሉ መሬት ውስጥ ቢቀብሩት ይመርጣሉ፡፡" አሉ፡፡ ከዚያም፣ ፈረስና የወንድ አገልጋይ ያለው ሰው ግብር አንደሚከፍል ስነግራቸው፣ "ሚሰተር ራሳም፣ ያገሬን ሰዎች አታውቃቸውም፤ ፈረሶቻቸውን፣ በቅሏቸውን ሌላም የቤት አንሰሳ ላይ ቀረጥ ባደርግ፣ አንድም ሰው በፈረስም በበቅሎ አይሄድም፤ እያንዳንዱ ሰው ደግሞ የራሱ አገልጋይ ይሆን ነበር፡፡" ብለዋል፡፡ በዚያን ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ አንደዚህ አይነት ግብሮችን ህዝቡ ላይ ለመጣል ባይጨከኑም፣ ከሳቸው በኋላ አሰከ ጣልያን ሁለተኛው ጦርነት ድረስ፣ የበጌምድር ሰዎችና ሌሎችም ከመጠን በላይ የሆነ ግብር፣ በቤት፣ በኩበትና በዶሮ ሳይቀር ይገብሩ ነበር፡፡

ቁጥር 26፣ አፄ ቴዎድሮስ በጋፋት የተሠሩትን ማቅለጫዎቹን ሲጎበኙ፣ ሄንሪ ዱፍተን በጥቂት ያርዶች ከኋላቸው ይከተል ነበር፡፡ ማቅለጫዎችን ደግፎ ለመያዝ በቀርከሀ የተሠራ ሥራ ነበር፡፡ ያጋጠመውን ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡፡ "አዳልጦኝ አንደኛው ቀርከሃ ላይ ስወድቅ፣ የቀርከሃው ሌላኛው ጫፍ ንጉሡን ጭንቅላታቸውን ከጀርባቸው በኩል ይመታቸዋል፡፡ ይህን ሁኔታ ከቴዎድሮስ ውጭ ሌላ ስው አላስተዋለም ነበር፡፡ ቴዎድሮስም በዝምታ ዞር ብለው ላንዳፍታ አዩኝ፡፡ ሁኔታው እንዴት እንደተፈጠረ ንጉሡ የተረዱ ይመስለኛል፡፡ አመለካከታቸው ደግሞ የተለየና ድግ የሆነ አጭር ዕይታ ነበር፡፡ እኔም ስተረጉመው ወዲያውኑ ይቅርታ እንደተደረገልኝ አድርጌ ነው፡፡ በጣም የከፋኝ ነገር ግን ሰዎች በብዛት ሲተራመሱ ስለነበር አጠገባቸው ቀርቤ ይቅርታ መጠየቅ ስላልቻልኩ ነበር፤ አሳቸው ግን ጉዳዩን ጠቅላላ ረስተውታል፡፡" ይላል፡፡

ቁጥር 27፤ ቴዎድሮስ፣ ቱርኮችንም ሆነ አሽከሮቻቸውን ግብፆችን አየተዋጉ ነው ምዕራቡን የኢትዮጵያ ደንበር ያስጠበቁት:: ለቴዎድሮስ፣ ግብፅና ቱርክ ልዩነት አልነበረውም:: ቴዎድሮስ፣ በደብዳቤዎቻቸውም ቱርክ አንጂ ግብፅ የሚል ቃል አይጠቀሙም:: በዚያን ጊዜ በርግጥ ግብፅ ራሷ በቱርኮች ሥር ነበረች:: ለራሳም ሲነግሩት፤ በልጅነታቸው የምዕራቡን ግዛት ከቱርኮቸ ነፃ አውጠተው አስከ ሱዳን ድረስ አንዳባረሯቸው፣ "ፈሪዎች! በመድፋቸው ጀርባ ባይደበቁ ኖሮ ድል አደርጋቸው ነበር::" በማለት ይገልጣሉ:: ይህ ቦታ ደበርኪ ይባላል:: በሌላ ዘገባ፣ ቴዎድሮስ የመድፍን ጥቅም የተገነዘቡት በዚህ ጊዜ ነበር:: ሆኖም ሱዳንን የወረሩት ግብፆች፣ እመቺ ጊዜ እየጠበቁ፣ ምዕራባዊ የኢትዮጵያን ደንበር እየጣሱ ቦታዎችን ይዘዋል:: ይህም፣ ከቴዎድሮስ በፊት፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ የተዋጉባቸው ታላቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉ ዕድሜ ልካቸውን ይዋጉት የነበረው ከቱርክ ከሚላኩ ግብፆች ጋር ነበር:: ለዚህ ነው፣ "የክንፉ ጎራዴ ብረት የነበረ፣ አየቀላ ሄደ ቱርክ አየመሰለ" የተባለላቸው:: በዚህ ጀግንነታቸው፣ ደጃዝማች ክንፉ በግብፅ አገር ታዋቂ ነበሩ:: ሆኖም ክንፉ ሲሞቱ በሁለቱ ልጆቻቸው መሀከል ውጊያ ሲካሄድ፣ ግብፆች አጋጣሚውን ጠብቀው ሲሰፋፉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ደጃዝማች ካሳ ከወይዘሮ መነንና ከልጃቸው ከራስ አሊ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ መተማ ድረስ ዘልቀው ቦታ ይዘው ነበር:: ነገር ግን፣ ደጃዝማቸ ካሳ፣ ራስ አሊን ድል ከመቱ በኋላ ተመልሰው፣ ግብፆችን ከመተማ አንዳስወጡ ተዘግቧል:: አፄ ቴዎድሮስ በምዕራቡ ደንብር፣ አይደለም መተማ፣ ቱክሪርም የኢትዮጵያ ነው የሚሉት:: በዚያን ጊዜ፣ ግብፅ የኢትየጵያ ዋና የውጭ ጠላት ነበረች:: ይህም በተለይ ቱርኮቹ አየተዳከሙ፣ ግብፆቹ ራሳቸውን ባጠናከሩበት ጊዜ ነበር:: ከግብፆች ጋር የነበረው ጦርነት በቴዎድሮስ አላቆመም:: በአፄ ዮሐንስ ጊዜም፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ ጎራዴያቸውን ያሰሉበት ታሪክ ነው::

ቁጥር 28፤ ቆንስላው የተገደለው በቴዎድሮስ ወንድም ልጅ በጋረድ ክንፉ ሀይሉ ሰዎች ነበር:: ቴዎድሮስ በተሰማቸው መሪር ሀዘን የቆንስላውን ገዳዮች አይቀጡ ቅጣት ነው የቀጡት:: ይህም በጎንደር ደባርቅ በሚባል ቦታ ነበር:: "የተሰለፈውን በሙሉ ከሴት በስተቀር አንድ ሳይቀር..." ቀጣሁ የሚሉት አባባል አለ:: ሆኖም በዚህ ውጊያ ሌላው አንግሲዛዊ ወዳጃቸው፣ ሲቀ መኳስ ቤል፣ ቴዎድሮስን መትቶ ለመጣልና ጦርነቱን ለማሸነፍ የወሰነው፣ የወንድማቸው ልጅ፣ ጋረድ ክንፉ ወደ ቴዎድሮስ ሲገሰግስ አይቶ በሽጉጥ ተኩሶ ሲገድለው፣ የጋረድ ወንድም ጆን ቤልን ይገድላል:: ጆን ቤል፣ ንጉሡን ቴዎድሮስን ለመከላከል በሰውነቱ ሲከልል ነው የተገደለው:: ቴዎድሮስ ለፕላውደን ላደረጉት አንክብካቤ፣ ከንግሥት ቪክቶርያ የሽጉጥ ስጣታ ተልኳላቸዋል:: ጋረድ ሲሞት፣ የቴዎድሮስን ዝምድና ለመጥቀስ የተገጠም ግጥም ይህ ነበር፣ "ጋረድ ሞተ ተቀበረ፤ ያንተ ወንድም ነውና አንፈራው ነበረ::"

ቁጥር 29፤ አፄ ቴዎድሮስ በተፈጥሯቸው ፈጠራም የሚወዱ ብቻ ሳይሆን የሚሞክሩ ነበሩ:: ከአውሮፓውያኑ ጋር ሲወያዩ፣ የመንሳፈፍ ሁኔታን አንስተው፣ አንድ ነገር

ጨው ባለውና በሌለው ውሃ ላይ አኩል ይንሳፈፋል ወይ ብለው በመጠየቃቸው ነጮቹ ተገርመዋል:: ይህንንም ጠይቀው፣ ጣና ሀይቅ ላይ፣ መንኮራኩር ያለበት ጀልባ አስርተው ለመቅዘፍ ሞክረው፣ ጀልባው ትንሽ አንደሄደ ሰጠመ:: አንደ ሀሳባቸው የዜሕር ሀይል ለማቋቋም ነበር:: ከዚያ በኋላ ይህን ሀሳብ ርግፍ አድርገው ትተውታል::

ገና በልጅነታቸው፣ ጣቁሳ በተባለ ቦታ፣ ከራስ አሊ ሰዎች ጋር ሲዋጉ ሲሰላለፉ፣ ደጃች ካሳ፣ አንጨት አስፈልፍለው፤ በላዩ ላይ ብረት ጠምጥመው፤ በውስጡ ባሩድ (ዮብረት አሩር) አስገብተው ካሸጉ በኋላ፣ አንደገናም ባሩድ በሽክላ በሽክላ እያደረጉ የጠላት ጦር የሚሰፍርበት ቦታ ከቀበሩ በኋላ፣ ከረጅም ቀርከሃ ጋር አያይዘው፣ ቀርከሀውን ወስጡን ባሩድ ሞልተው፣ ውስጥ ለውስጥ ምሽጋቸው ድረስ አስመጥተው ይጠባበቁ ነበር:: ጠላት ካምፕ ላይ ሲስፍር ከምሽጋቸው ሳይወጡ ለመለኮስና ለማፈንዳት ነው:: ነገር ግን ከደጃች ካሳ ወገን አንድ ሰው ተይዞ ሲያስፈራሩት ሚስጥሩን አወጣባቸው:: ሚስጥራቸው ስለወጣ በጣም ተናደው ከራስ አሊ ሰዎች ጋር አርቅ አደረጉ:: ሌላ መረጃ ካልመጣ በስተቀር፣ ደጃች ካሳ፣ የመጀመሪያውን የአቢሲኒያ ፈንጅ ነበር የሰሩት:: ይህን ታሪክ ደብተራ ዘነበ ሲዘግቡት፣ ራሳቸው ንጉሡ ይህንኑ አንስተው ለራሳም አጫውተውታል::

በሽፍትነታቸው ዘመን ደግሞ፣ ገባሮቻቸው ሻንቅሎቹ ማር ሲያመጡላቸው፣ "የማሩን ወለላ አቅልጠው ከጣሩ በኋላ፣ በፋጋ በፋጋ (ከቅል የተሠራ መጠጫ) አድርገው ምድር ቆፍረው አንዲቀዝቀዝ መሬቱ ውስጥ ቀበሩት:: ከዚያም በአዳራሽ ሰዉን ጠርተው፣ ለወታደርና ለሽማግሌ አንድ ፋጋ ለሁለት፣ ለልጅ ለልጁ ደግሞ አንድ ፋጋ ለሶስት ሰጡ:: ወታደሮችም በጠገቡ ጊዜ በካሳ ጥበብ በጣም ተደነቁ::" ይላሉ ደብተራ ዘነብ:: ታዲያ ይህ ሁሉ ችሎታም ነበር መወደድና አድናቆትን የጨመረላቸው::

አፄ ቴዎድሮስ፣ በዘመኑ ከሚገባው በላይ ብዙ ዕውቀትም ነበራቸው:: ቀልደኛም አንደሆኑ የታየበት አንድ ሁኔታ፣ በጋፋት፣ ራሳም ላይ ያደረጉት ነገር አለ:: ለራሳም ሰለ ግሪኩ ፈላስፋ ዲዮጀነስና(በአማርኛ ፅሁፍ፣ ዲዮጋን) ሰለ ገንዳው አንስተው አጫወቱትና፣ መልሰውም ፈላስፋው፣ አብድ ነው ወይስ ራሱን ወዳድ ነው ብለህ ታስባለህ ብለው ጠየቁት:: ራሳም ሲቀጥልም፣ ንጉሡ አኔ ከማውቀው በላይ ሰለ አውሮፓ ታሪክ አጫወቱኝና፣ የንግሥት ሳባና የንጉሥ ሰለሞን ትውልድ አለኝ ብለው ሲነገሩኝ፣ በዚህ ነገር ላይ አንዲያብራሩልኝ ስጠይቅ፣ ንጉሡ ግን በመቀጠል፣ አንዴት አንድ የአቢሲኒያ ልዕልት ታላቁ አስክንድርን እንደጎበኝችውና በቆይታዋም ከአስክንድር ወንድ ልጅ አንደወለደቸና ልጁም ሲያድግ የአለምን ግማሹን አንደገዛ ነገሩኝ:: ከዛም፣ በአቢሲኒያ ታሪክ ታላቁ አስክንድር በክብር የሚታይ ሰው ነው፤ ምክንያቱም በህይወት አያለ መንግሥተ ሰማይ ደርሶ የተመለስ ሰው ስለሆነ በማለት ግራ ስጋባ አይተው ታሪኩን ለማረጋገጥ፣ ከንቲባ ሀይሉን ጠርተው ከመፅሐፉ እንዲያነቡልኝ እዘዙ:: ከንቲባ ሀይሉ ይህን መፅሐፍ (ዜና አስክንድር) አንደ መፅሐፍ ቅዱስ ነው የሚያምኑትና፣ በሳሙኤል አስተርጓሚነት ተነበብልኝ፣ ወደ ሰላሳ የሚሆኑ

ስዕሎችም ነበሩበት ይላል። ባጭሩ ከንግሥት ጄሌና የተወለደው ሕፃኑ አሰከንድር መንግሥተ ሰማይ ደርሶ እንደተመለሰ ነው የሚያስረዳው። ንጉሡም፣ ታሪኩን እንዴት አንዳገኘኸው ሲጠይቁኝ፣ እኔም ሰመልሰ፣ አሰከንድር ወደ ምድር መመለሱ ሞኝ ነው፣ እኔ ብሆን አልመለሰም አልኩኝ። ይህ እባባል እንደተተረጎመላቸው፣ ንጉሡ ከተቀመጡበት ወንበር ሊፈነከሱ ትንሽ አሰኪቀራቸው ድረስ በሳቅ ፈነዱ። ከዛም፣ "እኔ በእንደዚህ አይነቱ ተራ ነገር የማምን ይመሰልሃል?" ብለው ጠየቁኝ። በዚህ ጉዳይ ከልብ የሚያምኑት ከንቲባ ሀይሉ ግን ደንግጠው ድምፅ አልባ ነበሩ። ከንቲባ ሀይሉ፣ ከዚህ በፊት የንጉድር ከተማ ከንቲባ ነበሩ፤ ሆኖም እነ ራስ አሊ የሚያደርጉትን ነገር በቅርብ ሰለሚያዩና ከርሰቲያንነታቸው የማስመሰያ መሆኑን ሰለተረዱ፣ ሰዎችን በጣም ይጠሉ ነበር። ያለዕድል ሆኖ፣ እንዲት ከንጉሡ ቤት የተባረረች ሴት ሠራተኛን ከንጉሡ ፈቃድ ውጭ አሰጠግተሃል ተብለው ተከሰው ከቴዎድሮስ ጋር ተጣልተው፣ ንጉሡ መቅደላ አሰረዋቸው ነበር። ሌላ የሚጠቀሰ ነገር ቢኖር፣ አፄ ቴዎድሮስ ጥንቁላና አሰማት ሰለማይወዱ፣ ከንቲባ ሀይሉ በዚህ ይታሙም ሰለነበር ነው። መቅደላ ላይ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ከፈቷቸው ሰዎች ከንቲባ ሀይሉ አንድ ነበሩ። ከንቲባ ሀይሉ፣ ቴዎድሮስን፣ ከአሰራ አራት አመት በኃላ አትኖርም ብለው ፊት ለፊት ነግረዋቸው ነበር ይባላል። እንደተባለውም ንጉሡ በነገሡ በአሰራ አራተኛው አመት ነው መቅደላ ላይ ራሳቸውን ያጠፉት።

ቁጥር 30፣ አፄ ቴዎድሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመዝመት የነበራቸው ሀሳብ በወታደሮቻቸውም የታወቀ ነበር። ወታደሮቻቸው ካደረጓቸው ከታወቁ ሁለት ጉርምርታዎች አንዱ በዚሁ በኢየሩሳሌም የተነሳ ነበር። ንጉሡ ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ፣ ከደብረብረሃን ወደ አንከበር ሲወርዱ ከባድ የጉም ጨለማ ነበር፤ አሳቸውም ራስ አንግዳን ለቀለብ ወደ ምሰራቅ ወደ አውራምባ ሲልኳቸው፣ ከንጉሡ ጋር የቀረው ወታደር፣ አነዚህን አሰቀድሞ የሰደደው፣ ለኛን ኢየሩሳሌም ወሰዶ ሊያሰፈጀን ነው ብሎ አንጎራጎረ። ሁለት ወታደሮች አፋፍ ላይ ሆነው፣ ለዚህ ንጉሥ ውሀ የቀዳ፣ እንጨት የሰበረ፣ የተከተለውም ውጉዝ ይሁን በማለት ውግዘቱ ከአጨጌውና (በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የከህነት ሥልጣን) ከአቡነ ሰላማ የመጣ ነው በማለት ለፈፉ። አጨጌውና አቡኑ ግን የኛ ቃል አየደለም አሉ። ንጉሡ ተበሳጭተው የመቱትና በጥይት የሳቱት ወታደር ነበር፤ ሆኖም በአቡነ ሰላማና በአጨጌው ግልግል ቴዎድሮስ በረድ ቢሉም፣ በነጋታው፣ አነዚህ ሰዎች ግዘቱን ሲደግሙ ያዬ ሰው ሄዶ ሽምቆ ይዟቸው መጣ፤ ሲጣራ ሁለቱም ሰዎቹ ቅስና የሌላቸው ወታደሮች ሆነው ተገኙ። ቴዎድሮስም በዙሪያ ያሉትን፣ ንጉሥ ላይ ያሴረ ሰው ምን ይሁን ብለው ሲጠይቁ፣ ሌሎቹ ሞት ይገባቸዋል ብለው ፈረዱ። ከወታደሮች አርባ ሰምንቱ በቦታው ተገደሉ፣ ቶራ መስከ ይባላል። ሁለቱ ገዘቾች ግን ከዳሞት የመጡ ሰለነበር፣ ንጀም ተውሰደው ተሰቀሉ። አንግዲህ በአንዲህ አይነት ሁኔታ ነው የአብዛኞቹ ሰዎች ሞት የተፈጠረው። አንደ ሲታንሊም አሰተያየት፣ በማንኛውም በሠለጠነው አለም፣ አገርና ንጉሥን የሚከዳ ከፍተኛ ቅጣት ነበር የሚደርስበት ።

የማንሳራትር ነገር ከተነሳ፤ አቴጌ ተዋበች ሲሞቱ፣ አፄ ቴዎድሮስ አሰከሬኑን ይዤ ልሂድ ብለው ሲነሱ፣ ወታደሩ በውሃ ሲያሰበላን ነው ብሎ ሰላንጎራንረ፣ ቴዎድሮስ የባለቢታቸውን አሰከሬን ለሁለት ወራት በየዘመቻው እየያዙ ሲንከራተቱ ከርመው ግሸን ወሰደው ቀበሯቸው። የእዜ ቴዎድሮስ አህት፣ ወይዘሮ ወለተ ወርቅ ይባላሉ። (አዜ ቴዎድሮስ ለፈረንሳዩ መሴ ሌዣን ድረዋቸው ነበር) ሲሞቱ፣ ንጉሡ ወደ መቅደላ በመጓዝ ላይ ሰለነበሩ፣ አሰከሬኑ እንዲሁ መንገድ ከርሞ በመጨረሻም መቅደላ ደርሶ ተቀብሯል። በዚያን ጊዜ፣ ኢትዮጵያውያን አሰከሬን በሰም አደርጎ የመገነዝ ጥበቡ ነበራቸው፤ ሰለዚህ ለብዙ ቀናት ሳይቀበር መቆየት ይችላል። ሌላኛዋ የአፄ ቴዎድሮ አህት፣ ወይዘሮ የሴፋ፣ የትግራዩን ደጃጣዝች ሰባጋዲስን አግብተው ነበር። ሌላ ነፋስ እንደተጠቀሰው ፣ ደጃች ሰባጋዲስ ከራስ ማርዬ ጋር ሲዋጉ ተይዘው በአዛዥ አሰቴ ትዛዝ ተገደለዋል።

ቁጥር 31፣ ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ አውሮፓውያን የሚያስወሩትን ንጉሡ በደንብ ያውቁ ነበር። ለዚህም ምሳሌ፣ ራሳም እንዲህ ሲል የሚገልፀው ሁኔታ አለ። ንጉሡ፣ እንድ የህየ አመት ወጣት ወንጀለኛ በሰንሰለት እንደታሰረ ወደኔ ላኩልኝ። ወጣቱ ለመዝረፍ ሲል ወላጅ እናቱን የገደለ ነበር። ወንጀለኛው ራሱ የሚናዘዘውን ነገር ራሌ ከለፉ እንድሰማና ንጉሡ ከምን አይነት ሰዎች ጋር እንደሚታገሉ እንድረዳ ነበር ኮሎሳከው። ቴዎድሮስም ሲፅፉ፣ "ይህን ሰው በህጉ መሠረት ብቀጣው፣ ላንተ ያሰረከብኩህ እንዳንድ አውሮፓውያን ነብሰ ገዳይ ይሉኛል።" የሚል ነበር። ይህ እናቱን ገዳይ፣ በአቢሲኒያ ህግ መሠረት ቢቀጣ፣ ሰውነቱ ተቆራርጦ ለቀብርም አይበቃም ነበር። ነገር ግን፣ ንጉሡ በጥይት ተገድሎ ወዲያው እንዲቀበር አዘዙ። ራሳም ሲቀጥል፣ ቴዎድሮስ ምንም ጨካኝ ቢሆኑም፣ የሳቸው ፍርድ ከፍትህ ነገሥቱ ወይም ከአቢሲኒያ ህግ ቀለል ያለ ነበር ይላል። ምንም እንኳን ሰዎችን በብዛት ቢያጠቁም፣ በጭካኔ ከመጣ ግን፣ ቴዎድሮስ ያደረጉት፣ ይጃች ውቤና ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ካደረጉት ከማሟሹም አይደርሰም። ከቴዎድሮስ በፊት፣ ለቀላል ጥፋት እንኳን ሰዎች አይናቸው ይጎለንል፣ ምላሳቸውም ይቆረጥና አግራቸውም ይቆረጥ ነበር። ይህ ደግሞ በሰውነት ላይ ከሚደርሰው ሰቆቃ በተጨማሪ ነው። ደብተራ ዘነብ የሚጠቅሱት አንድ ጎጂ የተባለ ሰው፣ የሰዎችን አይን አስነልጉሎ በእንቅብ አሰሞልቶ፣ አንድ ሰው ብቻ አይኑ እንዲተርፍ ካደረገ በኃላ አይናቸው የተነለጎሉትን ሰዎች አየመራ እንዲሄድ ያሰደርግ ነበር ይላሉ። ራሳም፣ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲደመደም፣ በሠገሬቱ ዳር አሰከ ዳር ቢጓዙ እንደዚህ አይነት አይንና ምላሰ የሚነለጉል በቴዎድሮስ ዮሉደረገ እንድም ቢሆን አይገኝም ይላል። በሌላ ዘገባ፣ በሽዋም ቢሆን ሰውነትን በመቆራረጥ ቅጣት ይፈፀም ነበር፤ ቴዎድሮስ ሽዋን ካሰገበሩ በኃላ ግን ይህን አይነት ተግባር በአዋጅ አሰቁመውታል።

ቁጥር 32፣ ሎርድ ጆን ረሰል በዘመኑ የአንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒሰትር የነበረና፣ በመሀሉም ከሥልጣን በመውረድ በተተካው ጠቅላይ ሚኒሰትር በፓልመርሰተን የነውጭ ጉዳይ ሚኒሰትር ሆኖ ተሹሞ ነበር። ፓልመርሰተን ሲሞት ተመልሶ ጠቅላይ

ሚኒሰትርነቱን ይዟል። የእንግሊዝ መንግሥት ባደረገው የእቋም ለውጥ ምክንያት፣ የግብፅ ቤተክርስቲያናት በኢየሩሳሌም የነበሩትን የኢትዮጵያን ንዳማት በጉልበት ወሰዱ። ይህ ዜናም የቴዎድሮስ ጀሮ ደረሰ። በፊት የነበረው የእንግሊዝ ቆንስል፣ ጀምስ ፊን ንዳማቱንና ኢትዮጵውያኑን ከጥቃት ይጠብቅ ነበር፤ ሆኖም አሁን የተካው ናወል ሙር ግን፣ ከላይ እስቆቹ ካልረዱኝ በሰተቀር ምንም እቅም የለኝም ብሎ ነው የተወው። ከእንግሊዝ መንግሥት በኩል ምንም አይነት ርዳታ ወይም ጣልቃ ገብነት አልተደረገም። ይህ የሆነው፣ በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት የሚፎካከረው ከሩሰያ ጋር ስለነበር፣ የሩሰያን መስፋፋት ለማሰቆም ከሩሰያ ጠላቶች፣ ከቱርኮች ጋር ማበሩን ፖሊሲ ሰላደረገ ነው። ግብፅም ቢሆን የቱርክ ቅጥያ ማለት ሰለነበር፣ በቴዎድሮሰና በእቢሲኒያ ኪሳራ፣ እንግሊዞች ግብፆቹን አልተጫኑም። ይህ የእንግሊዝ ባህሪ፣ በእዜ ዮሐንስ ጊዜም ቢሆን፣ በወቅቱ ጉልበት ነበረው ለተባለው ለጣልያን መንግሥት በማይሳት፣ እንግሊዞቹ ምፅዋ በጣልያኖች እጅ እንድትወድቅ ነው ያደረጉት። እንግሊዞቹ፣ ጣልያኖች ምፅዋን እንዲይዙ ጋብዘዋል የሚሉ ዘገባዎችም አሉ።

ቁጥር 33፣ በዚህ ምክንያት በኢየሩሳሌም ንዳማት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ቤትየለሽ ሆነው ተሰደው እንደነበር፤ በሰደታቸው ጊዜም የእርመን ቤተክርሰቲያን መነኮሳት በቀለብ ኢትዮጵያውያንን ይረዱ ነበር። ሆኖም ለመሰደዳቸው ምክንያት ዋነኖዎቹ ራሳቸው እርመኖች ነበሩ። ቴዎድሮሰን ለማባበል እነዚህ መነኮሳት ወደቦታቸው እንዲመለሱ፣ በብሪታንያና በእርመኖች መካከል ሰምምነት ተደርጎ ነበር። ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌም ደረሰ የሚፎከሩበት አንዱ ምክንያትም ይህ ሊሆን ይችላል።

ቁጥር 34፣ በጥቅምት 25 ለምሳሌ የባርክ ነዋሪዎች(በግብፅ ሰር የሚተዳደሩ) ቦሳሰን በመውረር ከርሰቲያኖችን በማጥቃት ብዙ ሴቶችና ወንዶች ከገደሉ በኋላ፣ 120 ሴትና ወንዶች ልጆችን በማጋዝ ለባርነት እንደዳረጓቸውና ከብቶቻቸውንም እንደነዱ ተዘግቧል። ይህ ደግሞ በተደጋጋሚ ይደረጉ ከነበሩ ወረራዎች አንዱ ነው። የግብፁ ገሸ ይህንን ነገር በቀላሉ ማሰቆም ይችል ነበር፤ በተለይም የባሪያ ንግድ በዚያን ጊዜ እየተከለከለ ሰለነበር ሰዎችን ለባርነት መጥለፉን ማሰቆም ይችል ነበር።

ቁጥር 37፣ የእዜ ናፖሊዮን ወይም የፈረንሳዮቹ ፍላጎት፣ እዜ ቴዎድሮሰ በክቶሊክ እምነት ተከታዮች ላይ ጫና እንዳይፈጥሩ ነው። ካቶሊኮቹ በዚያን ጊዜ ከሰሜኑ ደጃዝማች ንጥሄ ጋር በመተባበር ይሸርቡ ነበር። ሆኖም ቴዎድሮሰ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ፍጥነት በመገስገስ ደጀች ንጥሄን ድል አድርገው የካቶሊኮችን ሴራ አከሸፈዋል። ከዚህ በተጨማሪ የፈረንሳይ ጀስዊቶች፣ ማህደረቃል የሚባል የኢድዋ ተወላጅ ኢትዮጵያዊን ያለፍላጎቱ የክቶሊክ ሰራ እንዲሰራላቸው ንጉሱን ጠይቀው፣ የፈረንሳይ ንጉሰ ሰፖሰቲካ ሥራ ሰለፈለገው፣ ቅር እያለው ወደነሱ እንዲመደብ ወሰኖ ነበር። ማህደረቃል፣ የፈረንሳይ ቄሶች የፈለጉትን ነገር መሰራት ሰላልወደደ፣ ግብፅ ሲደርስ ይጠፋና ከሌላ፣ ለፈቨር ከሚባል ፊረንሳዊ፣ ጋር ይሆናል። ሆኖም፣ ለፈቨር

ሣህደረቃልን፣ ወሰጡን ሳያሰነብበው እንድ ሰነድ ላይ እንዲፈርም ይጠይቀዋል። ለትዮጵያዊው ግን አልፈርምም ካለ በኋላ፣ ከሌላ ሰው ጋር ሆኖ ሰነዱን ሲያነብ፣ ሠሉ ላይ የተፃፈው ነገር፣ ማህደረ ቃል ወደ እገሩ እቢሲኒያ ሲመለስ፣ 500 የሚሆኑ እዘሲኒያኖችን መልምሎ ወደ በርበን እንዲሄዱ እንዲያደርግ ነበር። ማህደረቃል በሥናይደና በመደናገጥ ለፈረንሳይ ቆንስል አመልከቶ ከለፈቨር ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥለት ተደርጓል። በኋላም ከነ ፍላድ ጋራ በመሆን ወደ አቢሰኒያ ተመልሰ በትውልደ ቦታው አድዋ ሆኖ ወንጌል ያስተምር ነበር። ከዛም እዜ ቴዎድሮሰ ባሰተርጓሚነት እንዲያገለግል ጠርተውት ለተወሰነ ጊዜ አብሯቸው ነበር። ሣህደረቃል ወደ ትውልድ ቦታው የተመለሰው፣ እዜ ቴዎድሮሰ ደጀማች ተድላ ጓሉን ካሸነፉ በኋላ ነው። ያን ጊዜም በቴዎድሮስ ሰር ተሰልፈው ሊዋጉ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች፣ ንጉሡ ካሡን በኋላ አልፈልጋቸውም ሰላሉ ከማህደረቃል ጋር ወደ ትውልድ ቦታቸው ተመልሰዋል።

መንዚንጀር ተባሮ ቢወጣም፣ በምፅዋ የፈረንሳይ ምክትል ቆንስል ሆኖ ይሰራ ነበር። በምፅዋ፣ ሁሉም ሰው በተለይም ቱርኮቹ፣ ለመጣ ለሄደው ሁሉ ቴዎድሮሰ ከፉ ነው እያሉ ነበር የሚያወሩት። የሚገርመው ነገር፣ መንዚንጀር ግን፣ ራሳምን፣ ዮመነመዳኑንን ወሬ አትሰማ፤ አውሮፓውያኑ ቴዎድሮሰን የሚገባቸውን ከብር ቢሰጧቸው ኖሮ ይህ ሁሉ አይፈጠርም ብሎታል። ንጉሡ በተፈጥሯቸው ከፉ አልነበሩም። ንጉሡ ለራሳም በፃፉት ደብዳቤም ይህንኑ የአውሮፓውያን ንቀትና ሲሶብ ይገልጣሉ።

የአርቄቆው(አርጊን) ናይብም ቢሆን፣ ምንም አንኳን አንዴ በቴዎድሮሰ ቢታሰርም፣ የንጉሡ ደጋፊ ነበር። ቴዎድሮሰ በተፈጥሯቸው ደግና ሩህሩህ ሰው እንደሆኑ፣ ነገር ግን ሲወለዱ ጀምሮ ደም ከጠማቸው ሰዎች ጋር ሰለሚታገሉ ነው ጨከነኛ የሆኑት ብሏል። ሰውየው በመጨመርም፣ የአውሮፓውያኑ መታሰር ዮቴዎድሮሰ ጥፋት አይደለም ነው የሚለው። በንጉሡ ግዘት ሲኖሩ አንደ ራሱ ዜጎች ነው የሚያያቸው፣ ታዲያ በግዘቱ አየኖሩ ለንጉሡ ጥላቻ የሚያሳዩ ከሆነ፣ እንደማንም ሰው መቀጣት አለባቸው ይላል። ናይቡ የታሠረው፣ በምፅዋው የቱርክ ገዢ ወደ ቴዎድሮሰ ተልኮ፣ ቴዎድሮሰ ግን ከጠበቀው በላይ እንዲዘገይ ሲያደርጉት፣ የምፅዋ ጊታዩ እንድዘገይ ፈቃድ አልሰጠኝም በማለቱ፣ ቴዎድሮሰ ቡን ብለው እንዴት ቱርክ ጊታዩ ነው ትላለህ በማለት ነበር። ተደጋግሞ እንደሚታየው፣ ቴዎድሮሰ ራሳቸው እንደወታደር ቢድንኳን እያደሩ፤ በባዶ አግራቸው እየሄዱ፤ ሥራም ለመሰራት ብዙ ጊዘ በመሪነት ራሳቸው በጀቸው እየቆፈሩና እየተሸከሙ፤ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ቢናኙም፣ የኢትዮጵያን ንጉሥ ነባሥትነታቸውን ዝቅ የሚያደርግ ወይም የሚያንጓጥጥ ሰው ከተገኘ ግን፣ ነጭ ሆነ የራሳቸው ዜጋ ከባድ ቅጣት ነበር የሚደርስበት። የዘገራቸው ሰዎች በውጭ ሰዎች ሲሰደቡ መሰማት አይፈልጉም። ከባሻ ፈለቀ(ሰፒዲ) ,ዣ ጎልቁ የጥላቻ መንስኤ፣ የእቢሲኒያን ሰዎች እህያ ናቸው ማለቱን ሰለሰሙ ነበር። እንደ ገላውደን ዘገባ ቴዎድሮሰ በሥልጣናቸው ቦጣም ይቀናሉ።

ቁጥር 38፣ ሚሲዮናዊው ስተርን፣ ከኢትዮጵያ ለመውጣት አሽከሮቹን አስከትሎ ሲሄድ መራ ላይ ከአፄ ቴዎድሮስ ካምፕ ይደርሳል። ሰላምታ ለመስጠት ጎራ ሲል ንጉሡ ወዴት አንደሚሄድ ጠየቁትና አብረው ያሉትን አሽከሮቹን ወዴት አየሄዱ ነው በማለት ሲመለከቱ፣ አንደኛው አሽከር ቤተሰቦቹን ላይ ነው ብሎ ሲመልስ ቴዎድሮስ አንዴት በድፍረት ይናገራል ብለው አሽከሮቹ አንዲደበደቡ ትዛዝ ይሰጣሉ። ይህንን ያየው ስተርን ጣቱን በጥርሱ ይነክሳል፤ ይህ ደግሞ በዘመኑ የመበቀል ምልክት ነበር፤ ይህን ያዩ ቴዎድሮስ አሉንም አንዲገረፍ ትዛዝ ሰጡ። ሰውየውም ታስሮ ተመለሰ። በጣም ከሚጠሏቸው ሰዎች አንዱ ስተርን ነበር። ቴዎድሮስ አቶ ኮከብ ነበር የሚሉት። ስተርን ማለት ሲታር ነው። ስተርን በአንድ መፅሐፉ ቴዎድሮስን "የአራዊቶች ንጉሥ" በማለት መዝለፉን ደርሰውቢታል። ራሳምን ሲነግሩት አኔን አንዲህ ብሎ የሰደበኝ ሰው፤ ቁመቱ ይኽን ነው የምታክል በማለት አጃቸውን ከምድሩ አራት ጫማ የሚሆን ከፍ አደርገው ለራሳም ነግረውታል። በአስተርጓሚያቸው በአቶ ሳሙኤል ውትወታ፣ አጃቸውን ለአመል ያህል ትንሽ ከፍ አንዳደረጉ ተዘግቧል።

ቁጥር 40፣ አፄ ቴዎድሮስ ምኞታቸው፣ የአባቴን አገር በጉልበት ይዘዋል የሚሏቸውን ቱርኮችን ከምፅዋ ለማስለቀቅ ነበር። ለዚህም የአውሮፓውያኑን አርዳታ ይፈልጉ ነበር። ሆኖም አንግሊዞችና ፈረንሳዮች ከቱርክ ጋር የተባበሩበት ጊዜ ነበር። ሶስቱም ባንድነት በከፊሚያ፣ ሩሲያን ሲቃውሙ፣ አፄ ቴዎድሮስ ግራ አንደገባቸው ይጠቀሳል። ይህ ጦርነት፣ ቴዎድሮስ በጣም የሚከታተሉት ጉዳይ ነበር። የመጣው ሰው ሁሉ ስለ ክፊሚያ ጦርነት ይጠየቅ ነበር። ከሆርመዝ ራሳም ጋር ሲወያዩ፣ ቴዎድሮስ፣ ስለ አሜሪካ አርስ በርስ ጦርነት፣ በብሪታኒያና በአሻንቲዎች ስለነበረው ውጊያ አውርተው፣ በከሪሚያ ጦርነት የተሸነፈውን፣ የሩሲያን ዛር፣ ኒኮላስን "አንግሊዞቹ አልገደሉትም ወይ?" ብለው ጠይቀዋል። ቴዎድሮስ በዚያን ጊዜ ቦሄሚያ የሚባል አገር ስለነበረው አምባገነን ጨካኝ ግዥ በደንብ ያውቁ ነበር።

ቁጥር 42፣ ስለ አፄ ቴዎድሮስ ደግነት የውጭ ፀሀፊዎች የዘገቡትን መመልከት አስፈላጊም ይሆናል። ከነዚህ አንዱ ፕላውደን ሲሆን፣ ዱፈታን፣ ራሳም፣ ቫልድማየርም ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት ያዩትን የሰውየውን ደግነት አሰፈረዋል። ከጠዋቱ፣ ቴዎድሮስ፣ ወታደሮቻቸውንና የጦር መሳሪያዎችን አንጂ ለሌላው ንብረት ደንታ የነበራቸው አይመስልም። ከሚገባው በላይ ሊጋሥ ነበሩ፣ የንቢጋባነት ባህሪ አይታይባቸውም ነበር። ቴዎድሮስ፣ አውሮፓውያኑን መልሰው ሲያስሩ የተወረሰውን ብር ቦሳቸው በኩል ምንም ሳያነድሉ አንዳለ መመለሳቸው ተዘግቧል። ቫልደማየር ሲገልፅ፣ ንጉሡ በመንዳቸው የታረዘች ድሃ ሴት አግኝተው፣ ከፈረሳቸው ወርደው የለበሱትን የራሳቸውን ሸማ አውልቀው ሴትዮዋን ሲያለብሱ አይቷል። ወላጅ አልባ የነበሩ ህፃናትን ሰብስበው ከአራሳቸው ካዝና በሚወጣ ገንዘብ ያስተዳድሯቸው አንደነበር ይታወቃል። በውጊያ ላይ ከተማረኩ ሰዎች ስለ መድሃኔ አለም ተብሎ በምህረት የሚለቀቁ ቢበዙ ነው አንጅ አያንሱም ነበር። በርግጥ በሞት የሚቀጡ አሉ፣ በመጀመሪያው አካባቢ፣ በዘመኑ የነበረው ፍትህ ነገሥት ተከፍቶ ነው ፍርድ

ሥሚሠጠው። ከተሸነፉ በኋላ፣ ደጃማች ብሩ ጎሹን ምህረት አድረገው በከብር ዘሥንጣፍ አስቀምጠው፣ አንተ ብትሆን አኔን የያዘከኝ ምን ታደርገኝ ነበር ብለው ዘ.ጠየቁት፣ አገልዎ ነበር ብሎ መመለሱ የሚዘነጋ አይደለም። በዚያን ጊዜ፣ ሳር፣ብቀሉ፣ አማዚአብሔር በጠላቶቼ አጅ አይጥለኝም ነበር ያሉት።

ሰለ ደጃች ብሩ ጎሹ በጥቂቱ፣ ብሩ ጎሹ የደጃማች ጎሹ ዘውዴ ልጅ ነው። ከአባቱ ጋር ተዋግቶ ጎጃምን ጠቅለል አድርጎ ይዞ ነበር። ያደገው በራስ አሊ ቤተ መንግሥትም ስለነበር ኩራተኛና ትቢተኛ ነው ይባላል። አንደ ቴዎድሮስ ሁሉ ሊላሦን የራስ አሊን ልጅ የውብዳርን በማግባት አማቾም ነበር። ያም ሆኖ አፄ ቴዎድሮስ በአባቱ በደጃች ጎሹ ቤት ስለኖሩ በአከብሮት ነበር የሚይዙት። ተንኮሉ ሰላለስቸገራቸው፣ ዕድሜዬ ይፍታህ ብለው መቅደላ ልከውት፣ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ነው ከመቅደላ የተለቀቀው። የተማረኩ ሰዎችን ምህረት በማድረግ፣ አንደጠላት ሳይሆን ለነሩ ወዳጅና ጓደኛ ያያሉ ብሎ ፕላውደን ለዘገበው መረጃ አንደዚህ አይነት ብዙ ምሳሌዎች አሉ።

ቁጥር 43፣ የወታደራዊ ማዕረግ ተዋረዱን የጀመሩት ቴዎድሮስ ናቸው። ሻምበል፣ ሻለቃ የመዶ አለቃ ወዘተርፈ። ለንጉሣዊ በሰላት፣ ራሶችና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ ከሀር የተሠራ ሸሚዝ ይለብሱ ነበር። የንጉሡ ወታደሮች የሚለብሱት ቀይ ሸሚዝ ቢጤም ነበር። በመቅደላ በአሮጌ ውጊያ ጊዜ የታየ ነበር። ናፒየር፣ በአ:ጌ ቁልቁል ለውጊያ የወረዱት የአቢሲኒያ ተዋጊዎች በለበሱት ቀይ ልብስ ምክንያት፣ በርቀት ላየ ሰው የእንግሊዝ ሠራዊት ይመስላሉ ብሏል።

ቁጥር 44፣ አፄ ቴዎድሮስ ለሌሎች አውሮፓውያን ሲናገሩ፣ ባሻ ፈለቀ ተመልሶ ምፅዋ ሲደርስ ኢትዮጵያውያንን "አህያ" ብሎ ተሳድቧል ሲሉ ምሬታቸውን ገልፀዋል። የዘፋው ደግሞ፣ አህያ ናቸው ብሎ የነገረው ለቱርኮቹ ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ በኩል፣ ለውሮፓውያኑን በሚገባ አስተናግደውና አስደስተው አያለ፣ በጅርባቸው ሲያሴሩ ማየቱን በጣም ነው የጠሉት። "ራሴ ላይ አድርጌያችሁ ብዞር አንኳን ሰሜን ከሥጉሮፍ አትመለሱም" ይሉ ነበር።

ቁጥር 48፣ አቶ ሳሙኤል የአፄ ቴዎድሮስ አስተርጓሚ ነበረ። ከካሜሮን ጋር ስለሚሠራ ካሜሮንን ረድኖ ይሆናል። በንጉሡ ትዛዝ ከራሳም ጋር ይሰራ ነበር። ንጉሡ፣ ምንም ያህል ራሳምን ቢወዱት፣ ቢያከብሩትና የራሳቸው ሰዎች ለንዲያከብሩት ቢያስደርጉም አያምኑትም ነበር። በአንድ ጉዳይ፣ አቶ ሳሙኤል፣ ንጉሡን የራሳምን ሀሳብ አንዲቀብሉ ሲወተውት፣ "አቶ ሳሙኤል፣ ራስህን አንደ ባሪያ ለአንግሊዞቹ ሸጥከ ወይ? አህያ ህ፤ ብቻ ምላስህን ሰብስብ..." ብለውታል። ከዚያ በ:ኋላ የአቶ ሳሙኤል ታማኝነት ቀንሶ በምትኩ ደስታ ተመደበ። ንጉሡ ራሳቸው ለራሳም፣ አንተ ሳሙኤልን አሳኝተህል ለኔ ደግሞ ደስታ ልጄ ነው ብለው በተዘዋዋሪ ነግረውታል። ሆኖም ደስታም ቢሆን፣ ያውም ለጎንደር በላት መቃጠል ምክንያት የነበነው ሰው (የጎንደር ሸፍቶች ዘርፈውት ራቁቱን መጥቶ፣ ቴዎድሮስ ከራሳቸው

ካዝና አልብሰውት ነበር) መልሶ ንጉሥን ከደኖ የራሰም ረዳት ነው የሆነው። ንጉሡ እያወቁም ሆነ ሳያውቁ፣ ራሰም ውስጥ ውስጡን በገንዘብም በታማኝነትም ሰውን አስከድቷል።

ቁጥር 49፣ ለዚህ መዘግየት ምክንያት፣ ራሰም ከአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ አለማግኘት ነው። ከንጉሡ የተላኩ ደብዳቤዎች ቢደርሱትም ማህተም ሰላልነበራቸው ራሰም ማረጋገጥ አልቻለም ነበር። አፄ ቴዎድሮስ የሚመልሱት ደብዳቤ ከሙሉ ልባቸው ካልሆነ ወይም ንቀት ካለባቸው ማህተም አያደርጉበትም ነበር። በዚያን ጊዜ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ ራሰቸው ፈቃድ ያልሠጡት ማንኛውም አውሮፓዊ ወደ ግዛታቸው አንዳይገባ አግደው ሰለነበር፣ ያለ ፈቃድ ወደ ጎንደር መሄድም አይችልም ነበር። ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ፣ በዚያን ጊዜ በየቦታው ሽፍታ ስለበረከተ፣ ራሰም ወደ ንጉሡ መሄድ ይከብደው ነበር። ከጎንደር የመጣ ነጋዴ፣ ወልደስላሴ ነበዚ፣ አንደሚለው ከሆነ፣ ቴዎድሮስ፣ ፕላውደን ላይ የደረሰውን ሁኔታም አልረሱትም።

ቁጥር 50፣ ራሰም የሚለው፣ የካሜርንን የመፈታት ወሬ የነገረው መሀመድ ሱሌይ የሚባል ሰው ነው። መሀመድ ደግሞ፣ የእርቂቆው (እርጊት) ናይብ ነው ይህን ውሸት አንድነግር የመከረኝ ይላል። ራሰም፣ መሀመድን፣ የማጭበርበር ሥራ ሰርቶብኛል ብሎ ለቴዎድሮስ ቢከስም፣ አፄ ቴዎድሮስ ጉዳዩን በደንብ ያውቁ ሰለነበር፣ መሀመድ ቢዋሽም ለበን ብሎ ያደረገው ሰለሆነ በማለት አልቀጡትም።

ቁጥር 52፣ ቴዎድሮስ ራሰምን በጣም ይወዱት ነበር፣ "አንተ ጥሩ ሰው ነህ፣ አለቆችህ ግን ጥሩ ሰዎች አይደሉም" ብለው ነግረውታል። የተቻላቸውን ሁሉ ያደረጉለት ሰው ቢኖር ራሰም ነው። የሚተኛበትን ከፍል ራሳቸው ጠርገው አቧራውን በእጃቸው አፍሰው፣ ምንጣፍ አንጥፈውለታል። ያም ቢሆን ራሰም በነበረው ብልጠት የቴዎድሮስን ባህሪ በደንብ ሰለሚያውቅ፣ በአከብሮት የሚገባቸውን ማዕረግ በመሥጠት አንጂ እንደነካሜርንና ስተርን ተዳፍሯቸው አያውቅም። ራሰም ንጉሡን በከብር ማናገር አንዳለበት፣ አስረኛው ካሜሮንን ጨምሮ ብዙ ሰዎች መክረውታል። ቴዎድሮስ በሌላ ቀን ከራሰም ጋራ ሲጫወቱ፣ ወደኋላ በመሄድ፣ የአብረሃምና የይስሐቅ ልጅ ማነው ብለው ጠይቀውት፣ አርሱም የጥያቄው አመጣጥ ሰለገባው፣ ትውልዱን አስከ ንጉሥ ሰለሞን ካደረሰ በኋላ፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ ከሰለሞን ሀረግ አላቸው ብሎ ተናገረ። ቴዎድሮስም ሲመልሱ፣ "ያውሮፓ ሰዎች ይህንን አምነው ከተቀበሉ፣ ለበደሉኝ ሁሉ ይቅርታ አደርግለቸዋለሁ" ብለዋል። ሌሎቹም አንዳሉት፣ ንጉሡ የፈለጉት አውሮፓውያኑ በአከብሮት አንዲያዩዋቸው ነበር።

ቴዎድሮስ ራሳቸው በአደባባይ ካደረጉት ንግግር መረዳት የማቻለው፣ አውሮፓውያኑ የመንግሥት ተወካዮች ከሆኑ የሚገባው ከብር ይሠጣቸው ነበር፣ ሌሎቹ ግን ከአቢሲኒያውያን አይለዩም። በንግግራቸው አንዲህ ብለው ነበር። "መቅደላ ከመስደዴ በፊት፣ ሚስተር ራሰም ወዳጀ ነበር፣ ምንም አንዲታሰር ባደርግም አሁንም ወዳጀ ነው፣ በዚህ ምክንያት አከብረዋለሁ አወደዋለሁ፣ በህይወት አስካለሁ ድረስ ጥሩ ነገር አደርግለታለሁ፣ ምንም አንኳን በአንግሊዝ ያሉ የሱ

የበላዮች ቢሳለቁብኝና በድህነቴ ቢንቁኝም። ነገር ግን፣ ሜሰር፣ ስተርን፣ ሮዘንታልና ካሚሩንን ከራሴ ከአቢሲኒያ ሰዎች የበለጠ ከብር አልሰጥም።"

ቴዎድሮስ የሚሳለቁባቸውን የውጭ ሰዎችን አስተሳሰብ የመረመሩበት አንድ ሁኔታ፣ በሳቸውና በራሳም መካከል በተደረገ የንግግር ልውውጥ መረዳት ይቻላል። ይኸውም፣ አንድ ቀን ከራሳም ጋር ሲጫወቱ፣ "ያገርህ ሰዎች ሲመጡ በጥቁርነቴ አንዮማይጠሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፣ አኔ የማምነው፣ ፈጣሪ ሁላችንም አከል አድርጎ አንዲፈጠረን ነው።" ብለዋል።

ቁጥር 53፣ አፄ ቴዎድሮስ ራሳምን በከብር ከማሰተናገዳቸው በተጨማሪ፣ የሰለሞን አርማና መስቀል ያለበት ኒሻን አንደኛ ደረጃ ሸልመውታል። የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን ሶስት ደረጃዎች ነበሩት፤ አንደኛ ደረጃው ሙሉ በሙሉ ከወርቅ የተሠራ፣ ሁለተኛ ሆረጃው፣ መስቀሉ ወርቅ ሆኖ አርማው በብር የተሠራ፣ ሶስተኛ ደረጃው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከብር የተሠራ ነበር። አንደኛ ደረጃውን ያገኙት፡ ራስ መሸሻ (የንጉሡ ሥሚጅመሪያ ልጅ)፣ ራስ አንማዳና ራሱ ራሳም ነበሩ። ሁለተኛ ደረጃውን ያገኙት ደግሞ የባለጠመንጃዎቹ ጦር አዛዥ የሆኑት ራስ ጠጋ፣ ሉተናንት ፕዩዶና ዶክተር ብለንክ ነበሩ፤ ሶስተኛ ደረጃው ግን አልተወሰነም ነበር። ይህን ኒሻን የሚሰራው ባለሙያተኛ፣ የቴዎድሮስ ባለሟል ዛንደር የሚባል ሰው ነበር።

ቁጥር 54፣ መድፍና የጦር መሳሪያዎችን በጣም በመውደዳቸው፣ የውጭ ስጦታ፣ ሙሳሪያ ካልሆነ ብዙም ግድ አይሰጣቸውም ነበር። ራሳም ያመጣላቸውን ሀር በሙሉ ዘፍተው ሳያዩ ለሴቶቹ አሳልፈው ነው የሠጡት። የጦር መሳሪያዎች ግን "ፍቅረ ካሳ" ይባሉ ነበር። የፈረንሳዩ ዜጋ ለዣን፣ ለቴዎድሮስ የሀር ጨርቅ አምጥቶ፣ ባገሬ ይህን ሥመሰለ ጨርቅ የሚሰሩ ሰላሉ የንግድ ልውውጥ አንዲጀመር በማለት ንጉሡን ሪጠይቃል፤ በዚህ የተበሳጩት አፄ ቴዎድሮስ ያሉት ነገር፣ "እነዚህ ሰዎች ምን ሊሮርጊያቸው ነው አንደ ሱቅ ሸቃጭ የሚመለከቱኝ?" በማለት ብሶታቸውን ገልዐዋል። ለዣንም ቢሆን፣ በዚህ ቢምሩትም በኋላ ባሰየው ንቀት፣ "የታባቱና፣ ያዙልኝ" በማለት አስረው አሰናብተውታል። ይህ ሰው ምፅዋ ሲደርሱ፣ ንጉሡን ሥጢአልፍ ፅሁፍ በመላኩ ቴዎድሮስ ሲናደዱ፣ ሌሎች አውሮፓውያንም ባደረገው ነገር ነቅፈውታል።

ቁጥር 56፣ ለዚህ ፍራቻ ደግሞ በቂ ምክንያት ነበር፤ በ1842 በአፍጋኒሰታን የነበረ የእንግሊዞች ሠራዊት ከከተማው ከካቡል ሲሸሽ ከወታደሮቹ ጋር ቁጥሩ ወደ 16ሺ ሰው ይጠጋ ነበር፤ ነገር ግን በተራራ ማለፊያ ጠብቀው የገደቸው የአፍጋን ተወላጆች፣ ከለንድ ሰው በስተቀር ሁሉንም እንደጨረሷቸው ይታወቃል። የተረፈው ሰው ዶክተር ነበር። አንደሚባለው ከሆነ ለወሬ ነጋሪነት ነው ያተረፉት። የብሪታንያ ሰዎች ይህን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር።

ቁጥር 58፣ በዘመኑ የአፄ ቴዎድሮስን ጦር ከጎዱት ነገሮች አንዱ ኮሌራ ነበር፣ "ንፍጠኛ ፈንገስ" ተብሎ ይጠራም ነበር። ወታደር ብቻ ሳይሆን የቴዎድሮስ ሹማምንቶችም

ህይወታቸው አልፏል። ከሚታወቁት አንዱ፣ ኢጋፊሪ ነለም ነበር። ወረርሽኙን መቋቋም የቻሉት ጦራቸውን በየቦታው ከፋፍሎ በማስፈር ነበር።

ቁጥር 59፣ *እዚህ ላይ የታሠሩ አውሮፓውያን ቤተሰቦችን እወክላለሁ በማለት በራሱ እነሳሽነት የመጣ ዶክተር ቤክ የሚባል ሰው ነበር። የመጣበት ጊዜም፣ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ለመፍታት ቃል በሠጡበት ጊዜ ሲሆን፣ የሰውየው ተልኮ በተቃራኒ፣ ቴዎድሮስ በእውሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አባብሶታል። የዶክተር ቤክን ጣልቃ ገብነት እንራሳምም አልወደዱትም ነበር። ሰውየው ወደ ትግራይ ዘልቆ ለንጉሡ መልክት ሲልክ፣ ያለኔ ፈቃድ ማን ሀገሬ ውስጥ ግባ አለህ በማለት ወደ ምፅዋ እንዲመለስ አድረገውታል። የሰውየውን ባህሪ በትክክል የሚያውቀው አቶ ሳሙኤል ሊናገር፣ ዶክተር ቤክ እንግዳ የሆነ ባህሪ አለው፤ ቢመጣ ኖሮ፣ ቴዎድሮስ በሁለተኛው ቀን እስር ቤት ያስገቡት ነበር ብሏል።*

ቁጥር 60፣ *አቢሲኒያ ብሉ ቡክ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ማንኛውንም ዘገባ ጥናት ወይም ታሪክ እየሰበሰበ የሚያስቀምጥበት ፋይል ነው። ይህ ፋይል የደብዳቤዎች ቅጅ ሳይቀር ይሰበሰብበታል። በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ሁኔታ ጠንቅቆ ማወቁ የመቅደላን ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን አድርጎለታል። የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዛውያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አውሮፓውያን የሚዘግቡትም ይሰበሰባል። በመቅደላ ዘመቻ፣ ፈረንሳዊው መንዚንጀር ከናፒየር ጦር ጋር ዘምቶ፣ ዋግ ሸም ነበዜን ማግባባት የቻለው እሱ ነበር። አውሮፓውያውያ እርስ በርስ የሚፎካከሩ ቢመሰልም በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ ግን ሲተባበሩ ነው የሚታየው።*

ምዕራፍ ሁለት

አነሰሊ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርዌዘር

አነሰሊ የባህር ወሽመጥ የተፈጠረው፣ ዲሲ[61] በሚባል ከአቢሲኒያ ድንበር ጋር በትይዩነት ለሀያ ማይሎች በተዘረጋ ደሴት ነው። በመሀሉ የሚገኘው ይህ ወሽመጥ ከአንድ አስከ አምስት ማይሎች የሚሆን የጎን ስፋት አለው።

ለዚህ አይነቱ ሥራ ከኮሎኔል መርዌዘር[62] የበለጠ ምርጫ ሊኖር አይችልም። ኮሎኔሉ፣ በህንድ በፈረለኛ መኮንንነት ሲያገለግል የነበረና አሁን ደግሞ በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነው። ይህ ሰው፣ ቀድሞ ከህሪመዝ ጄ ራላም ጋር በነበረው ትውውቅም ሲሆን ይችላል የለውየውን ሙታሰር ሲለማ ለማለልቀቅ ተነሣሣ። ለአለረኞቹ የሚሆን ገንዘብ ላከ፤ አቢሊኒያውያንን በጉቦ በመደለል ወደ መቅደላና ደብረ ታቦር መልክት መላክ ጀመረ። በሎንደን ለነበሩ ዋና ጋዜጦች የጋዜጣ አንቀፅ መፃፍ ጀመረ፤ በዕሁቃም፣ ታላቋ ብሪታኒያ በህንድ ሊደርስባት ከሚችለው ውርደት ራሷን ማዳን አለባት አለ፤ ይህ የአንግሊዝ መልከተኞች በመቅደላ በእስር መያዛቸው፣ በመህመዳኑና በሂንዱለታን ለዎች ከተለማ፣ በምለራቅ በሚገኘው የንግለቲቷ ግዛቶች አለም አቀፍ አመፅ ሊነሳ ይችላል።

መርዌዘር፣ አይነተኛ የሆነ መኮንን፤ በምለራቅ በኩል በተደረጉ የተለያዩ ጦርነቶች፣ ጎበዝ፣ ሰልት አዋቂ፣ ደፋርና ፊጣንነቱን ያለመሰከረ ሰው በመሆኑ፣ አቢሊኒያ ደንበር ላይ ለሚለፍረው ለመጀመሪያው ጦር አዛዥ አንዲሆን ተመረጠ። ከዚህም ጋር የህገሪቷን ተወላጆች በመጠየቅ ወደፊት ይከሰታሉ የሚባሉ ችግሮችን አንዲመረምርና ወደ መህል አገሪቱ መግቢያ መንገድ እንዲፈልግ ነበር። ወጣትና ሙሉ ጉልበት ያለው ለው በመሆኑ ለማረፊያ የሚሆነውን ቦታ ፈልጎ ሲያገኝ ጊዜም አልወሰደበትም። በዚህ፣ በአጄ ባደረገው መስፊሪያ ቦታም የቅዱስ ጊዮርጊስ ምሰል ያለበት መለቀል በራሱ እጅ ሰመጀመሪያ ጊዜ ተከለ።

---

[61] ደሴቱን ደጃች ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

[62] ኮሎኔል መርዌዘር፣ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

ህይወታቸው አልፏል። ከሚታወቁት አንዱ፣ ኢጋፊሪ ነለም ነበር። ወረርሽኙን መቋቋም የቻሉት ጦራቸውን በየቦታው ከፋፍሎ በማስፈር ነበር።

ቁጥር 59፣ እዚህ ላይ የታሠሩ አውሮፓውያን ቤተሰቦችን እወክላለሁ በማለት በራሱ አነሳሽነት የመጣ ዶክተር ቤክ የሚባል ሰው ነበር። የመጣበት ጊዜም፣ ቴዎድሮስ እሰረኞቹን ለመፍታት ቃል በሠጡበት ጊዜ ሲሆን፣ የሰውየው ተልኮ በተቃራኒ፣ ቴዎድሮስ በእውሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አባብሶታል። የዶክተር ቤክን ጣልቃ ገብነት አነራሳምም አልወደዱትም ነበር። ሰውየው ወደ ትግራይ ዘልቆ ለንጉሡ መልክት ሲልክ፣ ያለኔ ፈቃድ ማን ሀገሬ ውስጥ ግባ አለሀ በማለት ወደ ምፅዋ እንዲመለስ አድረገውታል። የሰውየውን ባህሪ በትክክል የሚያውቀው አቶ ሳሙኤል ሲናገር፣ ዶክተር ቤክ እንግዳ የሆነ ባህሪ አለው፤ ቢመጣ ኖሮ፣ ቴዎድሮስ በሁለተኛው ቀን አስር ቤት ያስገቡት ነበር ብሏል።

ቁጥር 60፣ አቢሲኒያ ብሎ ቡከ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ማንኛውንም ዘገባ ጥናት ወይም ታሪክ እየሰበሰበ የሚያስቀምጥበት ፋይል ነው። ይህ ፋይል የደብዳቤዎች ቅጅ ሳይቀር ይሰበሰብበታል። በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ሁኔታ ጠንቅቆ ማወቁ የመቅደላን ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን አድርጎለታል። የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዛውያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አውሮፓውያን የሚዘግቡትም ይሰበሰባል። በመቅደላ ዘመቻ፣ ፈረንሳዊው መንዚንጀር ከናፒየር ጦር ጋር ዘምቶ፣ ዋግ ሹም ነበዜን ማማበባት የቻለው እሱ ነበር። አውሮፓውያውያ እርስ በርስ የሚፎካከሩ ቢመስልም በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ ግን ሲተባበሩ ነው የሚታየው።

ምዕራፍ ሁለት

አነስሊ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርዌዘር

አነስሊ የባህር ወሽመጥ የተፈጠረው፣ ዲሲ[61] በሚባል ከአቢሲኒያ ድንበር ጋር በትይዩነት ለሀያ ማይሎች በተዘረጋ ደሴት ነው። በመሀሉ ሞጊጎነው ይህ ወሽመጥ ከአንድ እስከ አምስት ማይሎች የሚሆን የጎን ሰፋት አለው።

ለዚህ አይነቱ ሥራ ከኮሎኔል መርዌዘር[62] የበለጠ ምርጫ ሊኖር እያችልም። ኮሎኔሉ፣ በህንድ በፈረሰኛ መኮንንነት ሲያገለግል የነበረና አሁን ያሣፋ በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነው። ይህ ሰው፣ ቀድሞ ከሠራመዝ ጀ ራሳም ጋር በነበረው ትውውቅም ሊሆን ይችላል የሰውየውን ሠታሰር ሲሰማ ለማሰልቀቅ ተነሣሣ። ለአስረኞቹ የሚሆን ገንዘብ ላከ፤ አበሲኒያውያንን በጉቦ በመደለል ወደ መቅደላና ደብረ ታቦር መልከት መላከ ጀመረ። በሎንደን ለነበሩ ዋና ጋዜጦች የጋዜጣ አንቀፅ መፃፍ ጀመረ፤ በፅሁፉም፣ ታላቋ ብሪታኒያ በህንድ ሲደርስባት ከሚችለው ውርደት ራሷን ማዳን አለባት አለ፤ ይህ የአንግሊዝ መልከተኞች በመቅደላ በአሰር መያዛቸው፣ በሠሀመዳኑና በሂንዱስታን ሰዎች ከተሰማ፣ በምስራቅ በሚገኘው የንግስቲቷ ግዛቶች አለም አቀፍ አመፅ ሊነሳ ይችላል።

መርዌዘር፣ አይነተኛ የሆነ መኮንን፤ በምስራቅ በኩል በተደረጉ የተለያዩ ጦርነቶች፣ ጎበዝ፣ ሰልት አዋቂ፣ ደፋርና ፈጣንነቱን ያስመለከረ ሰው በመሆኑ፣ አበሲኒያ ደንበር ላይ ለሚሰፍረው ለመጀመሪያው ጦር አዛዥ እንዲሆን ተመረጠ። ከዚህም ጋር የህገሪቷን ተወላጆች በመጠየቅ ወደፊት ይከሰታሉ ሞጊባሉ ችግሮችን አንዲመረምርና ወደ መህል አገሪቱ መግቢያ መንገድ እንዲፈልግ ነበር። ወጣትና ሙሉ ጉልበት ያለው ሰው በመሆኑ ለማረፊያ የሚሆነውን ቦታ ፈልጎ ሲያገኝ ጊዜም አልወሰደበትም። በዚህ፣ በአጁ ባደረገው መስፈሪያ ቦታም የቅዱስ ጊዮርጊስ ምሰል ያለበት መስቀል በራሱ አጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ተከለ።

---

[61] ያሌቱን ደጃች ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

[62] ኮሎኔል መርዌዘር፣ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

ወሽመጡን የሚዋለነው የአቢሲኒያ ደንበር አሸዋማ የሆነ የባህር ዳርቻ ሲሆን፣ ከአሰራ አራት አሰከ አሰራ አምስት ማይል ሰፋት ያለው፣ በሰሜን ሀያ ማይል ርዝምት አሰከ ምፅዋ፣ በደቡብ ደግሞ አሰከ አነሰሊ ወሽመጥ የተዘረጋ ነው። በዚህ ከወሽመጡ መግቢያ ሶሰት አራተኛ ርቀት ጀምሮ፣ በደቡብ በአሸዋማው ዳርቻ፣ ከዙላ ወደብ ለመድረስ አራት ማይል ርቀት ባለው ሰፍራ፣ ሌፍተናነት ኮሎኔል መርዌዘር ጠቅላይ ፅህፈት ቤቱን መሠረተበት። ከዚህ የባሰ አሰቸጋሪ ቦታም አልተመረጠም። ነገር ግን፣ ይህ ቦታ የተመረጠበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት። አንደኛው ጥልቅ የሆነ ወሽመጥ በማዋሰኑ፣ ከባህር በኩል የጦር መሣሪያ በቀላሉ ሊራገፍበት ይችላል። ሁለተኛ፣ በሁለት ከፍተኛ ቦታዎች መሀከል ርዝመት ያለው ከፍተት ቦታ በመኖሩ፣ ወደ መህል አገር ቀላል መግቢያ ጋር ሰለሚያገናኝ ነው። የዚህ ወደ መህል ሀገር መግቢያ ከፍት ቦታ ከመርዌዘር ፅሕፈት ቤት በምዕራብ አቅጣጫ አሰራ አምስት ማይሎች ርቀት ላይ ይገኛል።

በዚህ ቦታ አንደሰፈረም፣ ኮሎኔል መርዌዘር፣ ለቦምቤዩ ገዥና በሎንደን የህንድ ፅሕፈት ቤት ለሰር ሰታፈርድ ኖርዝኮት፣ ሰላደረገው ከፍተኛ አሰሳ፣ የቦታ ፍሊጋና ሰለተገኘው ጥሩ ውጤት ደብዳቤ ይልካል። ያለ ዕድል ሆኖ፣ ሰላገኘው ቦታ ከሚገባው በላይ አጋኖ ነበር የገለፀው። አንደ አገላለፁ፣ አንጨትና ውሀ አንደልብ አንደሆነ፣ ሳር ከሚበቃ በላይ መኖሩን፣ ደኑም ቢሆን የሚያዝናና፣ ወደ መሃል አገር መተላለፊያው ቀላል መሆኑን፣ ሰፍራው ለአደን የሚሆኑ የተለያዩ አንሰሳት ሀብት አንዳለው ነበር።

የኮሎኔሉን መልከት አንደተቀበሉ፣ ሁለቱ ሰዎች፣ ከሎንደን የህንድ ፅህፈት ቤትና የቦምቤይ ባለሥልጣኖች ወደዚህ ብሩህና መንግስተሰማይ የመሰለ አገር ለመጓዝ ለመዘጋጀት መፎካከር ጀመሩ። ሌፍተናንት ጀኔራል ሰር ሮበረት ናፒየር የጦሩ አዛዥ አንዲሆን ተመረጠ። በአርሱ ትዛዝና ምክር መሠረት ለዚህ ዘመቻ መቃናት ይሆናል ያለው የሰዎች ቁጥር ተወሰነ። ከተለያዩ የጦር ከፍሎች የመጡት ሰዎች ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት በቦምቤይ አንዲሰበሰቡ ተደርጎ በየከፍል አዛጉች ግምገማና አብሮም የጋለ ማበረታቻ ንግግር ተደረገ።

ከቦምቤይ ሀላፊዎች በጣም ብዙ ሲጠበቅ ሰለነበር፣ በጉጉት፣ የጥቂት ቀናት ሰንቅ ብቻ በማሰያዝ ጦሩን ወዲያውኑ ወደ ዙላ የመላክ ምኞት ነበራቸው። ሊያዝ የታቀደው ሰንቅም ረሃብ ሊያሰከተል በሚችል ሁኔታ መጠኑ ያነሰ ነበር። ሆኖም ነገሮችን በጥሞና የመመልከት ፖሊሲ ባይኖር ኖሮና፣ በሰር ሮበርት ናፒየር ለአንደዚህ አይነቱ ትርጉም የለለው የሲቪሊያኖች አቀራረብ ጠንካራ ተቃውሞ ባይደረግ፣ ከፍተኛ የሆነ ጥፋት በተከተለ ነበር።

ሎዳሚው ብርጌድ፣ በውሰጡ የዋናው አዝ ከንፍ ሶስተኛው ቀላል ፈረሰኛ ክፍለ፣ 10ኛው የቦምቤይ የተወላጆች[63] አግረኛ ጦር፣ 3ኛና 4ተኛ ኮምፓኒ፣ እና የተወላጆች (ህንድ) ምሽግ ቆፋሪዎችና ካምፕ አዘጋጆች ያሉበት ዙላ ሠፈረ።

ይህ ከፍልም የጦር ካምፑ ዋና ጠባቂ አንዲሆንና ወደፊት ተከትሎ ለሚመጣው ጦር አሰኳል አንዲሆን ታስቦ ነው። ከዚህ ብርጌድ ጋር፣ ሁለት ዘንዘሎች፣ ከታዋቂ የአንግሊዝ መፅሔቶች ከታይምስና ከደይሊ ኒውስ ነበሩ። ከታይምስ የመጣው ዘጋቢ የደረሰበት መከራ በዚሁ መፅሔት ላይ ሰዕላዊ ዘገባ አገላለጥ በአምዶቹ ላይ ተፅፎ አልነበረምን?

ዙላ ካረፉት አንዱ ብርጌድ ወሽመጡ አንደደረሰ፣ ብዛት ያላቸው የባህር ሠመላሻዎች ያመጧቸውን በሺ የሚቆጠሩ በቅሎዎች፣ ግመሎችና የቀንድ ከብቶቹን፣ በቅሎ መሪዎችና ከብት ጠባቂዎች ሳይኖሩ አንዲሁ ለቀቋቸው። እነሰሶቹ፣ ከባህር ጉዞ በኋላ ከወደቡ ሲለቀቁ ግጦሽና ውሀ ፍለጋ ምንም ሳያገኟቸው አካባቢውን ይራወጡትበት ጀመር። ሣርና ውሀም ባለመገኘታቸው በየቁጥቋጦውና ጫካው ሲርመሰመሱ በየገደሉ እየወደቁ በሠቡዎዎች የሚቆጠሩ ይሞቱ ጀመር። ብዛት ያላቸውም ይሠረቁ ጀመር፤ ብልጣ ብልጥ የሆነ የፈረስ ደላላ ምፅዋ ላይ መርከብ ይዞ ቢጠብቅ፣ ሦሰቡትን በቅሎዎችና ግመሎች ከወረዱበት ከአቢሲኒያ ምደር ወድያውኑ እንደአመጣጣቸው በፍጥነት መልሶ ወደ ህንድ በወሰዳቸው ነበር።

ከሁሰት አሰከ ሶሰት ሺ የሚቆጠሩ አንሰሶች ሲሞቱ፣ የጦሩ አዛዥ ለዚህ ነፋት መላ መፈጠር የሚያሰፈልግ መሆኑን ተገንዘበ፤ አሱም በቀላሉ የሚሰራ ሀሣ ነው የተገኘው።[64]

በአንፋሎት የሚነዳው የውሃ ላይ ማመላለሻ በባሕሩ ወሽመጥ አንዲቆይ ተደርጎ ውሀ አያፈላ በአንፋሎት የሚወጣውን ውሀ አያቀዘቀዘ አንዲያጠራቅም ተወሰነ። ለዚህም፣ ጀልባዎች ወደ ህንድ ተልከው ለዚህ ሰራ የሚሆኑ አንፋሎት የሚያቀዘቅዙና የሚሰብስቡ በአሰራዎች የሚቆጠሩ መሳሪያዎችና ብዙት ያላቸው የአሜሪካ የኖርተን የውሀ ፓምፖች እንዲያመጡ ተደረገ።

---

[63] ተወላጆች የሚለው የህንድ ሰዎችን ነው።

[64] በመርከብ የመጡት አንሰሳት ቁጥር፤ 2,538 ፈረሶች፣ 44 ዝሆኖች፣ 17,673 በቅሎና የሻኮነት ፈረሶች፣ 5,735 ግመሎች፣ 1,759 አህዮች፣ 7,071 ድልብ በሬዎች ነበሩ። ከሀገሩ ሰዎች ደግሞ 270 በቅሎዎች፣ 1,004 በሬዎች ነበሩ። ባጠቃላይ የእንሰሳቱ ቁጠር 36094 ነበር። (Record of The Expedition to Abyssinia)



በዙላ የውሀ ማጠጫ ገንዳዎች

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

እነዚህ መሣሪያዎች እንዲመጡ ትዛዝ ከተሠጠ ከሶሰትና አራት ሳምንታት በኋላ መሣሪያዎቹ ዙላ ደረሱ፤ ከነሱም ጋር በሺ የሚቆጠሩ (coolies, ኩሊዎች[65]) የቀን ሠራተኞች እብረው መጡ፡፡ የኋለኞቹ፣ ወድያውኑ ሌሎች የሚመጡትን ከባድ ጓዞች ለመቀበል የወደብ ከፍሎችንና የውሀ መውረጃ ገንዳዎችን ሥራ እንዲጀምሩ ተደረገ፡፡ የዚህ ሥራም በሚገርም ፍጥነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ፡፡ ለአንደኛው ትልቅ ውሀ ማጣሪያ በድንጋይ ደሴት ተሠራለት፤ የተጣራውን ውሀ ለማውረድ ከደሴቱ ወደ መሬቱ የውሀ መውረጃ መለመር ከተሠራለት በኋላ፣ የተጣራውን ውሀ ከባህሩ ዳርቻ ባሉ ውሀ ማጠራቀሚያዎች በማጠራቀም ለአገልግሎት እንዲውል ተደረገ፡፡

እነዚህ፣ እዲስ፣ በመርከብ ከሰዊዝ እየተጫኑ የሚመጡት አንሰሳት ከሰፔይን፣ ከጣልያን፣ ከሶርያና ከግብፅ ነበር የተሰበሰቡት፤ ከነዚህ ጋር ደግሞ የቀርከና አረብ በቅሎ መሪዎች እብረው መጡ፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው የሚያሳዝንና ብልሃት የጎደለው ትዛዝ ነበር፡፡

ማንም፣ ከነዚህ ሰዎች ጋራ የሥራ ግንኙነት የነበረው መንገደኛ በደንብ የሚያውቀው ነገር ቢኖር፣ ቱርኮችና አረቦች በጣም አስከፊ የሆነ፣ ከሰው ጋር የማይገጥምና የሚበጠብጥ ባህሪ አንዳላቸው ነው፡፡

ወድያውኑ፣ በኮሎኔል መርዌዘር ሥር ደጋማዋን ቦታ ለመያዝ ወደፊት የሚገሰግሱት ወታደሮች፣ ጓዛቸውና ጓዙን የጫኑት እንስላት ከመሪዎቻቸው ጋር መጥፋታቸው ተነገራቸው፡፡

በጀምላ፣ የሰዎችና የከብቶቹ መጥፋት ሁኔታ በየቀኑ ይከሰት ነበር፡፡ በየከፍሉ የሚገኙ የቀዳሚው ጦር አዛዦች በየጊዜው የሚጠፋውን ንብረትና ሰው ቁጥር በተረዱ ጊዜ፣ የታጠቁና በሥነሰርአት የሚጓዙ ወታደሮች፣ ከዘመቻው በተጨማሪ ለሌላ ሥራ የሚያስፈልጉ መሆኑን በመረዳት፣ ከጓዙና ከሰዎች ጀርባ ጥቂት የታጠቁ ወታደሮች መድቦ እንዲጠብቁ ማድረግ አዋቂነት የተገባው ተግባር መሆኑን ተገነዘቡ፡፡

እንዲህ ያለው የሥራ ልምድ ከብዙ ኪሣራ በኋላ የሚገኝ ነገር ነው የሆነው፡፡ የእንግሊዝ ሠራዊት በቦምቤይና በቻታም በካምፕ ሠፍሮ ለብዙ ጊዜ ሰለኖረ ለዘመቻ የሚያስፈልጉ ብዙ የሚደረጉ ነገሮች መኖራቸውን ዘንግቷል፡፡

በዙላ፣ የወታደሮች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ነበር፡፡ ወደፊት ያለው መንገድ ወይም ማለፊያ በር ከተቃኝ በኋላ፣ ሰር ቻርልስ ሰታቨሊ የተባለው ጄኔራል፣ ማለፊያው በር መጨረሻ ላይ በከፍተኛው ቦታ የሚገኝ፣ ለናፌ

---

[65] ይህ ቃል በቻይናና በአካባቢው አፀያፊና ከስድብ የሚቆጠር ነበር፡፡ በኢትዮጵያም በተለይ በአዲስ አበባ ለተወሰነ ጊዜ ይህን ቃል ህዝቡ ሲጠቀምበት ነበር፡፡

የሚባል መንደር አንዲያዝና ወደ መቅደላ በሚደረገው ዘመቻ ሁለተኛው ዴፖ ካምፕ(ከዙላ ቀጥሎ) አንዲሆን ያዛል፡፡ በመርዌዘር የሚመራ ጦር ስናፌን ለመያዝ መንገድ ላይ ነበር፡፡ በኋላም በቀረበው ሪፖረት፣ በስናፌ በቂ ውሀ አንዳለ፣ አየሩም ጤናማ መሆኑን፣ በቂ ሳር አንዳለ፣ ገለባ፣ አጃና ገብስ ከነዋሪዎች ማግኘት የሚቻል መሆኑ ሲታወቅ፣ የጦሩ አብዛኛው ከፍል ወደ ስናፌ አንዲዛወር ተደረገ፡፡



ኮሎኔል መርዌዘር

ወደ ደጋማው ከፍል ማስፈያው ከብዙ ጉልበት ሥራ በኋላ፣ በማወዳደር ሲታይ፣ ቀለል ባለ ሁኔታ ሊጠናቀቅ ተችሏል፡፡ አንባቢዎች በደንብ አንዲረዱትና አገላስፁ ቀለል ያለ አንዲሆን፣ አኔ የምገልፀው የቁማይሌ ማለፊያ ከላይ ከባሕር ወስል በላይ 7ሺ ጫማ ከሚገኘው ስናፌ ከተለያዩ ተራራማዎች በሚወርዱ የጎርፍ ወራጆች የተፈጠረ ሸለቆ ነው፡፡ ይህ ማለፊያ[66] ወይም ሸለቆ ቁልቁል አየወረደ በከረምት ጊዜ በመሙላት ሀይለኛ ወራጅ ውሀ

[66] (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

የሚፈጥረውን ወንዝ በመከተል ከ63 ማይል ርቀት በኋላ ዙላ ወደብ ላይ ይቆማል፡፡

ሆኖም በበጋ ወራት ደረቅ ስለሆነ፣ ሙሉውን የወንዙን ርዝመት፣ መንገደኞች በእግራቸው ያልፉበት ነበር፡፡ በደረቀው ወንዝ ዱካ የነበረ ነገር ቢኖር፣ ከላይ ከከፍታማ ቦታዎች የወረዱ አለቶችና የአንጨት ቅርንጫፎችና ስብርባሪዎች ነበሩ፡፡ ለወታደሮቹ ማለፊያ፣ በጣም ከፈት ያለውን የማያስቸግር ስፍራ በመመረጥ የተሸከርካሪ መሄጃ መንገድ አንዲሆንም ተደረገ፤ ነገር ግን በአንዳንድ ጠባብና አስቸጋሪ ቦታዎች አለቱን በመቁረጥ መንገድ መሠራት ነበረበት፡፡ በነበራቸው አጭር ጊዜ ውስጥ ባወጡት ዕቅድ፣ ከዚህ የተሻለ መንገድም አይስራም ነበር፡፡ ስለዚህ የዚህ ሥራ ሃላፊ ስነበሩ መሀንዲሶች ትልቅ ምስጋና መስጠት ተገቢ ነበር፡፡ ወታደሮች፣ ጓዝ፣ አንስሳት፣ ከባድ መሳሪያው እና ተሸከርካሪዎች በተመቸ ሁኔታ ከፍ ባለ ቦታ ወደሚገኘው ወደ ስናፌ መጓዝ ቻሉ፡፡

በሁለት ወራት ውስጥ፣ ወደፊት ለሚደረገው አንቅስቃሴ ሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር፤ እናም ስር ሮበርት ናፒየር ደረስ፡፡ የተሠራውን ሁሉንም ነገር፣ የተሠሩትን መካዝኖች፣ ውሀ ማጣሪያዎች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ የወደብ ከፍሎች ከጎበኘ በኋላ፣ ቀዝቀዝ ያለ ነፋሻማ አየር ወዳለበት ወደ ስናፌ ተሻገረ፡፡

አጭር፣ ወደ አምስት ማይል ርዝመት ያለው ሀዲድ ከዙላ ወደብ አስከ ካምፑ ጠርዝ ድረስ ተዘርግቷል፡፡ ሁለት ባቡሮች ከባሀር ወርደዋል፤ አነዚህም ብዛት ያለውን ወደቡ ላይ አየተራገፈ በየቀኑ በፍጥነት የሚከማቸውን ጓዝ ወደሚመች ቦታና ወደየጦር ከፍሉ በማመላለስ ትልቅ አስተዋፅኦ ነው ያደረጉት፡፡

አቢሲኒያ በደረስኩ በማግስቱ፣ በካምፑ ውስጥ፣ ማንም ስው ገና ዝር ሳይል፣ አኔና ሠራተኛዬ አሊ በጠዋት ተነስተን ዙላን ስቀን ጉዞውን በመልካም ሁኔታ ጀምረናል፤ ሆኖም ለጉዞው የሚሆን የሚበቃንን ቁሳቁሶች አልያዝንም፡፡

በሀሳቤ የነበረው፣ የኔ፣ የአቢሲኒያና የአንግሊዞች ዘመቻ አመለካከት ያልተጠና ነበር፤ ይህም ያለ ምንም ጥርጣሬ ወደፊት በምናደርገው አንቅስቃሴ በደንብ ይገለጣል፡፡

ከዙላ አስከ ቁማይሌ የነበረው ርቀት አስራ አራት ማይሎች ነበር፡፡ የዙላን ካምፕ አንደጨረሱ መንገዱ በረሃና አሸዋማ ነው፤ አልፎ አልፎም በተለያዩ የተከል አይነቶች የተሞሉ ችፍግ ያሉ ቁጥቋጦዎች ይታዩበታል፡፡

ተወላጆቹ የሚኖሩበትን የዙላን መንደር ካለፍን በኋላ፣ ደናማ፣ ያልታረሱ፣ አጠር ባሉ ቁጥቋጦዎች የተሸፈኑ ጉብታዎች መውጣት ጀመርን፡፡ በጉብታዎቹ፣ በከረምት ወራት አንደልቡ አየጎረፈ የሚወርደው ውሀ የሸረሸራቸው ከፍተቶች አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡ አንደገናም በዝናቡ ወራት የሚያፈልቁ አሁን ግን የደረቁ ደቦልቦል ባሉ ድንጋዮች የተሞሉ የምንጭ ቦታዎችን አናያለን፤ ከዚያ ደግሞ ዳገት የግድ መውጣት ነበረብን፤ ከትንሽ ጊዜ በኋላ አንደገና አፈር ብቻ ወደሆነ ጎድጓዳ ቦታ ቁልቁል መውረድ ነበረብን፡፡ የውሀ ጠብታ የሚባል የትም አይታይም፡፡ በኋላ፣ በቁማይሌ አንደተረዳነው፣ ለመጠጥ የሚሆን ውሀ በባህሩ ዳርቻ አንደማይገኝ ነበር፡፡ ኮሎኔል መርዌዘር በቂ የሚጠጣ ውሀ አለ ብሎ ሪፖርት ሲያደረግ፣ በጣም በሰሀተት ተመርቶ ነበር፤ ምክንያቱም በዝናቡ ወራት የነበረው ውሀ አርሱ ከመድረሱ በፊት ደርቆ ነበር፡፡

አንዳንድ ቦታዎች የተቋሩ ውሀዎች አግኝቶ ነበር፤ አነሱም ቢሆን በጥቂት ቀናት ውስጥ አንዳለ ከአይን ነው የተሰወሩት፤ ምክንያቱም ቦታው አሸዋማ ስለነበር የነበረውን አርጥበት አንኳን ወደ ውስጥ ሰቦታል፡፡

በግምት፣ ከአሰቸጋሪ የአምሳት ሰአታት ጉዞ በኋላ ከተራራ ሰር ደረለን፤ ከተራራው አናት ላይም የቁማይሌ ካምፕ መታየት ጀመረ፡፡ በዚህ ቦታ ነው እንግዲህ ተራራውን ከሁለት ከፍሎ ወራሪዎችን ወደ አቢሲኒያ የሚያስገባው ማለፊያው በር ያለው፡፡

ትልቅ ሰፋ ያለ ከፍተት በጎንና በጎን በተራሮች ለንሰለት ታጅቦ ይታያል፤ ተራሮቹም በቁጥቋጦና በቁልቋል ተከሎች ተሸፍነዋል፡፡ አልፎ አልፎ የአየር ፀባዩ የተፈራረቀባቸው ግራጫ መልከ ያላቸው አለቶች ከጋራዎች ጎን ብቅ ብቅ ይላሉ፡፡ አለቶቹም ቢሆን ደመቅ ያለ አረንጓዴ ተከሎችና ከአለቶቹ ጎን በበቀሉ ተከሎች መሀል ነው ፈጠጥ ብለው የወጡት፡፡ ቀረብ ካሉት የጋራ ለንሰለቶች በላይ፣ ሌሎች፣ ተለቅና ሰፋ ያሉ ተራራዎች፣ አሻቅበው ሲመለከቷቸው አናታቸው ደመናውን የሚለሙ መስለው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ከፍ ያሉት፣ ሴሎቹን፣ አንደቲያትር ቤት አዳራሽ መድረክ አካበውና አቅፈው ሲታዩ፤ በመሀሉ፣ ማለፊያው መንገድ ጠቆርና ጨለም ብሎ ይታያል፡፡

ካምፑ ያለበት ቦታ ከብነቱ ሶስት አራተኛ በሆነ ስፍራ ላይ ነው ፡፡ ሁለት ተለቅ ያሉ ኮረብታዎች በካምፑ ዳርና ዳር አንደጠባቂ ወይም ተከላካይ ዘብ ቆመው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ትልልቅ ኮረብታዎች ደግሞ፣ ጠበብ ባለ የተራራ ሰንሰለት ከነዚያ ከትልቆቹና ሰፋፊ ተራሮች ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ አዳራሽ ወደመሰለው ቦታ ከማምራታችን በፊት፣ የመጣንበትን አካባቢ ለማየትና ባህሩንም ለመለናበት ወደ ኋላ ዞረን ተመለከትን፡፡ ማንም መገመት የማይችለው ብሩህ አይታ ነበር፡፡ ከግርጌያችን፣ አሸዋውን ከአይታ በደበቁ

ተከሎችና ቁጥቋጦዎች የተሞላ ሜዳማ ቦታ ይታያል፡፡ ደመቅ ካለ አረንጓዴያማው ቦታ አለፍ ብሎ የተንጣለለ ነጣ ያለ የሚያብረቀርቅና የሚያታጥለው አሸዋ፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ የተበታተኑ የበረዶ ከምሮች የመለሉ የካምፑ ድንኳኖች፣ ከዚያ አለፍ ብሎ ደግሞ መልሀቃቸውን የጣሉ ግርማ ሞገስ ያላቸው መርከቦች በወሽመጡ ይታያሉ፡፡ አየሩ ግልፅና ለማዩም ደመና ለላልነበረው፣ የአያንዳንዱ መርከብ ሽራና ገመዶች ተለይተው ይታያሉ፤ ከዚያም በራላቸው ተከልለው በአኩለ ቀኑ ፀሀይ ሰር የሚያንቀላፉ ይመስላሉ፡፡ አለፍ ብሎ የሚታየው ደግሞ የዲሴ ደሴት ነበር፡፡ ካለንበት ከፍታ ሆኖ አይናችን ከደሴቱ ጀርባ ለማያዊና ፀጥ ያለውን ከአድማሱ ባሻገር የተሸሸገውን የቀይ ባህርን መቃኘት ይችላል፡፡ ካለንበት በግራ በኩል ወደ ሀያ ማይሎች ርቀት፣ በአረንጓዴ ዛፎች መሀከል የተኮለኮሉ ጠፍጣፋ ጣራ ያላቸው ቤቶች ያሉበት የምፅዋ ከተማ ለአይታ ይገባል፡፡

ወደፊታችን ከትንሽ አርምጃዎች በኋላ፣ ጨለማ በሆነው ማለፊያ ውስጥ ገብተን ተሠወርን፤ በከለሉን ኮረብታዎቹ አማካኝነት ቤታችን ነው ብለን ከምናለበው፣ ከጓደኞቻችንና ከሥልጣኔ ጋራ ተለያየን፡፡

የአሜሪካ ኖርተን ፓምፖች በቁማይሌ ተአምር ነው የሠሩት፡፡ ውሀ በየቦታው ነው የሚገኘው፡፡ የደከሙት ግመሎችና በቅሎዎች ይህን ውድ መጠጥ አንደልብ ነው ያገኙት፡፡ ካምፑን ዙሪያዎን በከበቡት ከፍታዎች ምክንያት፣ በተፈጠረው ጥላና ከተራሮቹ ቁልቁል በሚነፍሰው ንፁህና ቀለል ያለ አየር ምክንያት በፍጥነት ነው ያገገሙት፡፡ ዙላ ለሳምንታት ሲቆዩ፣ ሰውነታቸው የተጎላቆለውና የደከመው ህመምተኞቹ ወታደሮችም ቢሆኑ በዚህ ስፍራ ሲሰነብተ ቶሎ ነው ያገገሙት፡፡ እንደ አውነቱ ከሆነ መላው ካምፕ ዙላ ከነበረበት ሁኔታ የተለየ ነው የሆነው፡፡

የሾሆ(ሶሆ) ጎላ አባላት የሆኑት የአካባቢው ተወላጆች፣ ፍየሎች፣ በጎችና ላሞቻቸውን ይዘው ወደ ካምፑ ይጎርፉ ጀመር፡፡ ይህ ደግሞ አካባቢውን የዘላን ገፅታ አንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ፍየሎቹ በአካባቢው ካለው ግራጫ መልከ ያለው ቋጥኝ ላይ በመውጣት ከበቀሉት ቁጥቋጦዎችና ተከሎች ጫፍ ጫፉን ይቀመቅማሉ፤ ከታች፣ በጎች በሚያሳዝን ድምፅ ይጮሃሉ፤ ላሞችም ቢሆን ድምፅ ያለማሉ፤ ጠቆር ያሉና ራቁታቸውን የሆኑ የሾሆ ልጆች ደግሞ ይጫጪሀሉ፤ አለዚያም ከሸምበቆ በተለራው ዋሽንታቸው ይጫወታሉ፡፡

በአካባቢው የሚገኘው አብዛኛው ሥፍራ የገበያ ቦታ ሆኗል፤ አንደ ሉቅ የሆኑት ደግሞ መሬቱ ላይ የተዘረጉ የለሌን ምንጣፎች ነበሩ፤ አነሱም በግራና በቀኝ ተነጥፈው በመሀሉ ለመተላለፊያ መንገድ ከፍተዋል፡፡ ህንፃዎችና በውስጣቸው ያለው ቁሳቁለ የተለየ ባይሆን ኖሮ፣ ይህ ቦታ ከተማ ውስጥ ካለ የሱቆች ጎዳና ጋር በተወዳደረ ነበር፡፡



የባቡር ሀዲደ በቀማይሌ
(Record of Expedition to Abyssinia)



ውሀ ማጠጫ በቀማይሌ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ገበያውን ስንመለከት፣ ብዛት ባላቸው ሸቀጦች የተሞላ መሆኑን አስተዋልን፡፡ ሽንኩርት፣ የትምባሆ ቅጠል፣ ከስታምቡል የሚመጣ ላታኪያ ከተባለ ቦታ የሚበቅል መዓዛ ሽታ ያለው ቡናማ ቀለም ያላቸው ሥር ከምሮች የእንጨት ጠረጴዛዎች ላይ በሚያጓጓ መልከ ተደርድረዋል፤ ቅርንጫፋቸው ላይ ያሉና በከብ ዕቃ ውስጥ የተቀመጡ የሾላ ፍሬዎች፣ ወደ እፍ ማስገቢያው በኩል ብሩህ ቀለም ያላቸው የትምባሆ ማጨሻ ቱቦዎች፣ ላያቸው ላይ የሚያምሩ ምስሎች የተቀረፁባቸው የትምባሆ ማቃጠያ መያዣዎች፣ ተራ የአንግሊዝ ከሸክላ የተሠሩ የትምባሆ ማጨሻዎች፣ ከካይሮ የመጡ የሱረት ማጨሻ ረጃጅም ቱቦዎች፣ ከፐርሽያና ከህንድ የመጡ ሁካዎች፣ ጥቁር የወይራ ፍሬ የሞሉባቸው ጠርሙሶች፣ በኪስ የሚያዙ መነፅሮች፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ኮኛክ፣ የሶዳ ውሀ፣ ሌሎችም ብዛት ያላቸው ከፓሪስና ከሎንደን የመጡ ነገሮች ነበሩ፡፡

እዚህ ቦታ የማይገኙ ነገሮች ቢኖሩ በዘመቻ ለመጡት ወታደሮች የሚጠቅሙም አልነበሩም፡፡

አንግዲህ በገፍ የነበሩ በገበያ ተፈላጊነት ያላቸው የሾላ ፍሬዎች፣ የተምር ፍሬዎች፣ ኦቾሎኔ፣ አረቄ ቢኖሩም አንደ መፅሐፍ፣ ፋኖስ፣ ጋዜጣ የፖስታ ቤት ዕቃዎች(አንዚህን አንኳን ያስፈልጋሉ ብዬም አስቤ አላውቅም) የመሳሰሉት ደግሞ አልነበሩም፡፡ ገበያው፣ በሾሆ ተወላጆችና ካምፑን አየተከተሉ በሚጓዙ ሰዎች ይዘወተራል፡፡ የእገሩ ተወላጆች የሆኑት ጠቆር ያሉት ሴቶች ደግሞ ምንም ጌጣ ጌጥ ላያደርጉ ልብስም አንኳን ላይደርቡ ይመጣሉ፤ ለቀቅ ያሉ ራቁት የሆኑ ልጆችም በደስታ ሲሯሯጡ ይታያሉ፤ ካምፑን ተከትለው የሚጓዙት ልብስ ደራርበው የለበሱ፣ ከበርበራ፣ ዳናኪል፣ ኤደን፣ ራቅ ካለው ከፐርሺያና ከህንድ ደናማ ቦታዎች የመጡት ወንዶች በዘረጓቸው ሱቆቻቸው ሰብሰብ በማለት ሳይረበሹ በነፃነት ጋደም ብለዋል፡፡

ቀዳሚውን ጦር ለመቅደም ጉዞዬን ማጣደፍ ስለነበረብኝ፣ አዲግራት በተባለ ጣቢያ የኮሚሳሪያቱን ክፍል ስላየሁ ሠራተኛዪን አሊን ድርሻዬን ራሽን እንዲቀበል ላኩት፡፡

ለአንዳፍታም ቢሆን የተመደበልንን ድርሻ አንደተቀበልን ተደርጎ መታሰብ የለበትም፡፡ የራሽን ማከፋፈያው ክፍል ሀላፊ የነበሩት ሌቦች ፋርሶች[67] ከተመደበልን ግማሹን ያስቀሩብን ነበር፡፡ ወደ መሀል እገር አየገፋን በሄድን ቁጥር፣ በተደጋጋሚ ሩዝ፣ ሻይ፣ ሰኳር፣ ቡና፣ ድንች፣ ቅጠላ ቅጠል፣

[67] Parsees (በ7ኛውና በ8ኛው ምዕተ አመት ከፋርስ (የአሁኑ ኢራን) ተሰደው ምዕራባዊ ህንድ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡

አይብ አይሰጠንም ነበር፡፡ ጭራሹን ለሁለት ወራት የሚሆን ጊዜ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሳይሰጡን የከረምንበት ጊዜ ነበር፡፡

አሊ ከኮሚሳሪያቱ ሊመለስ ፀሀይ አየገባች ነበር፡፡ ለወትሮው ላቂና ተጫዋች የነበረው ሰው ሀዝንተኛ መስሎ ተከዞ ነው የታየው፡፡ እንዲህ የከፋው ምክንያቱ ምንድነው ተብሎ ሊጠየቅ በተሰባበረ አንግሊዝኛ "በገበያው ቦታ፣ አረቦቹ፣ እንግሊዞቹ በሀበሻ ምድር ይገድሉሃል ብለው ነገሩኝ፡፡ ስለዚህ ወረቀቴ ይሰጠኝና ወደ ሱዌዝ ልመለስ፡፡" ይህን አንዳለም ሰቅ ሰቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ፡፡

ነገሩ የሚመስለው፣ በአንግሊዞች ካምፕ ውስጥ በነበረው ጥብቅ ሥርእት የማስከበር ሁኔታ ያልተመቸው ቅብጥብጥ አረብ፣ አሊን፣ አንግሊዞቹ ጨካኝ ሰለሆኑ ያላደላቸውን ሠራተኞቻቸውን አስኪሞቱ ድረስ ይገርፏቸዋል ብሎ ሰለነገረው፣ አሊ ደግሞ በዚህ በሀበሽ ምድር ሞቶ አፅሙን ጥሎ የመሄዱ ሀላብ በጣም ስላስፈራው፣ ወደ ሱዌዝ ለመመለስ እኔን ፈቃድ ለመጠየቅ ወሰኖ ነው የመጣው፡፡ እኔ አሱን ያገኘሁት ሱዌዝ ነው፡፡ ለጊዜው አፅናንቼና አረጋግቼ አንዳውም ከኔ ጋር አብረህ ሰናፌ ድረሰ ትሄዳለህ በማለት አባበልኩት፡፡

ዙላን ለቅቄ ስሄድ፣ ለራሴ የሚሆን ድንኳን ለመያዝ አልተጨነኩም፤ ምክንያቱም ሊያስፈልገኝ አገዛለሁ በማለት ነበር፡፡ በክፈል ትክክል በክፈል ደግሞ ሰህተተኛ ነበርኩ፡፡ የራሴን በቅሎ፣ ፈረስና ድንኳን ከዙላ ብይዝ ኖሮ እንደልቤ ለመንቀላቀስ ነፃ ነበርኩ፤ ነገር ግን ወደ መቅደላ በፍጥነት ልንገሰግስ ነው የሚባል ጭምጭምታ በካምፑ ውስጥ ሊወራ ስለነበር፣ በትክክል የማለብ ችሎታዬን አስቀይሮኝ የባቡር ፍጥነት ያህል ተጣድፌ ለመሄድ ወሰንኩኝ፡፡ የአየር ፀባዩ መልካም ስለነበር፣ አንድ የነበረኝን ንብረት፣ የያዝኩትን ከጎሽ ቆዳ የተሠራ ካፖርት ከብርድ ለመከላከል ስል ስለብሰው ሰለነበር ብዙም ችግር በመንገድ ላይ አልተሰማኝም፤ እንዲያውም ወድጄዋለሁ፡፡

ቀልጣፋው አሊ ያዘጋጀልኝን ቀለል ያለ አራት ከበላሁ በኃላ፣ ሲጋራ ለኮሰኩና ያንኑ የጎሽ ካፖርቴን ደርቤ ተጋደምኩ፤ በአእምሮዬ ውስጥ ብዙ ሰለነበረ ለማሰብ አንጂ ለመተኛትም አልነበረም፡፡

ጎህ እንደቀደደ፣ በጊዜ፣ ኮርቻችን ላይ ወጣንና፣ የሚያዛጋ አፉን ከፍቶ ወደሚጠብቀን ማለፊያ ዘው ብለን ገባን፡፡ ካምፑን፣ የንጋቱን ፀጥታ ከአደፈረሰው ግርግርና ጫጫታው ጋር በርቀት ወደኃላ ጥለነው ወተናል፡፡ በቋጥኞቹ መጋጠሚያዎች ዙሪያ፣ በሚሞላ ዛፎች ደኖችና ላውረል ቁጥቋጦዎች መሀል፣ ሰፋ ብሎ በተዘረጋው ቅርንጫፎቻቸው ላይ በቀለም የተሻፕጎረጎሩ ወፎች ያሉባቸውን ከፍ ያሉ የችብሃ ዛፎችን በማለፍ አየተመራን ነበር፡፡ የአለት ግድግዳ ያላቸው ቀጥ ያሉ ገደሎች ስር፣ ጠበብ ብለው ወጣ

ባሉት ፊትለፊት ባሉ ኮረብታዎች ዙሪያ፣ ጥቅጥቅ ባለ ደን መሀል አቋርጠው በሚሄዱ መንገዶች እየተዘዋወርን መንገዳችን ቀጠልን::

ቀጥሎም፣ በማለፊያ መንገዳችን ጎንና ጎን ያሉት የጋራዎች አናቶችና ዳገቶቻቸው ምትሀታዊ በመሰለ ሁኔታ እየተቀየሩ መጡ:: ድብዝዝ ካለ ግራጫ ገፅታ ወደ ብርቱካንማ ቀለም ይቀየሩና ወዲያው ደግሞ በብርማ ቀለም ይተካሉ፤ ቀስ በቀስ ብርማ ቀለሙ በምዕራብ በኩል ያሉትን ዳገቶች ይሸፍንና ወደ ምስራቅ በኩል ባሉትም መታየት ይጀምራል:: ከላይ ከሰማያዊው ሰማይ መሀል፣ የአሳት ኳስ የመሰለች ፀሀይዋ ያለምንም ርህራሄ የእሳት ፍንጣቂ የመሰሉ ጮራዎቿን አናታችን ላይ ትሰቃለች፤ አኩለ ቀን የመሆኑ ምልከት ነው:: በዚያን ጊዜም በሚሰማው ድምፅ ምክንያት የሚቀጥለው ጣቢያ ሶሮ እየተቃረብን ምምጣታችን አወቅን:: የቋጥኞቹ መጋጠሚያ ዙሪያ ወደ ቀኝ በኩል በዘጠና ዲግሪ ለንታጠፍ፣ የወታደሮቹ የካምፕ ድንኳኖች መታየት ጀመሩ::

ከፊረሴም ወረድኩና፣ ከትልቅ ዛፍ ስር፣ ጥላ ያለበት ቦታ ሳገኝ ምንጣፍ ዘርግቼ ለማረፍ ጋደም አልኩኝ:: አሊ፣ መጀመሪያ ከብቶቹን አሰማርቶ የሚያጠግብ ላር መጠን አቀረበላቸው፤ እሳት ተቀጣጥሎ፣ ውሀ የተሞላ የቡና በራድ በግ በግ የሚሉት የእሳት ነበልባሎች ላይ ሲጣድ የቤት ትዝታን ለለሚሰብ በርካታ ፈገግ አንድል አደረገኝ፤ ከዚያ ደግሞ ሲፈላ የሚያሰማው ድምፅና ደመቅ ያለው የቡናው ሽታ ከተበታተነው ሀሳቤ አነቃኝ::

ከሁለት ለአታት መዝናናት በኃላ አንደገና መንገዳችን በመቀጠል ወደሚቀጥለው ጣቢያ ወደ አንደል መግፋት ጀመርን::

በሶሮ ጎንና ጎን፣ ለሶስት ማይሎች የሚሆን ርዝመት የማለፊያው አለቸጋሪና አደገኛ ከፍሎች ይታያሉ:: ለሰድሰት ማይሎች ርዝመት ደግሞ፣ መንገደኞች በጎን በጎን አለከ 800 ሜትር ከፍታ ባላቸው ቋጥኝ ግድዳዎች መሀል ባለ ጠባብ ማለፊያ ያልፋሉ:: በነዚህ ማለቂያ የሌላቸው በሚመስሉ ግድግዳዎች መሀል፣ ድንጋዮች ላይ እየዳሀን አንወጣለን፤ የረገጥነው ድንጋይ ድንገት ተፈንቅሎ እንደማይወጣ፣ ወይም የተዘረጉት የዛፍ ቅርንጫፎች ተገንጥለው ወደ ታች ወደ ማለፊያው ገደል ይዘውን እንደማይወርዱ አርግጠኛ አልነበርንም:: ዝቅ ያለ የሰዎች ድምፅ እንደነጎድጓድ ነው የሚለማው፤ የፊረሶች ኮቴም ቢሆን ድልድይ ላይ ሲያልፍ የሚንኳኳ የመድፍ ተሸከርካሪ ድምፅ ነው የሚመስለው:: ካለንበት አለር ጫማ ከፍታ ላይ፣ በክረምት ወራት ወደ ማለፊያው ሲወረወር የነበረው የውሀ እንጥፍጣፊዎች ይታያሉ:: ሰፋ ያለው የማለፊያው መሄጃ የጎን ስፋት ሀያ አምስት ጫማ የማይበልጥ ሲሆን፣ ጠበብ ያለው ደግሞ አንደምንም አለራ አምስት ጫማ ቢሆን ነው:: አንዳንድ

ቦታዎች ላይ ወደ አገሩ ወራሪ እንዳይገባ ታይታንስ[68] ለምዕተ አመታት ቁጥጥር ሲጠርቡና ሲያመቻቹ የኖሩበት ይመስላል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ሸኑሪሮች፣ ውሀ መውረጃዎች፣ ሥንጥቆች፣ ለሃምላ ማይሎች ርዝመት ወደ ማለፊያው ወደ ሶሮ ሲወርዱ ማየት፣ በዚህ ስፍራ ላይ አንድ ትልቅ ውሀ ነበሞኑት የነበረ፣ ከዚህም ጋር ሀይለኛ አዙሪት ነበረው ብሎ መገመት ያስችላል::

በመጨረሻም፣ ከጨለማውና ድንግዝግዝ ካለው ከሶሮ ጥልቅ ሸለቆ ሠላሳን ስፋ ያለና ወደተንጣለለው የማለፊያው ከፍል ገባን:: አልፊናቸው ከመጣባናቸው ቀጥ ብለው በቆሙ ገደሎች ምትከ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመጊዝም ቅርፅ ያላቸው ኮረብታዎች፣ በመጠኑ ዳገታማ ከሆኑ ጎናቸውና በላያቸው ላይ በበቀሉ በቁልቋል፣ ኢጋም፣ በቁጥቋጦዎች፣ በጥድና በሌሎች ዛፎችም ተሸፍነው ይታያሉ:: ቀጥሎም፣ በጣም አስደናቂ በሆኑ ተራሮች ከፋፍሎች መሀል መጓዝ ጀመርን፤ የተራሮቹ አናቶች ደግሞ በትንንሽ ሾጥ ሾጥ ባሉ ደብዘዝ ያሉ አለቶች የተቆራረጡ ናቸው፤ ይህም በማለፊያው ከታች ወደኃም ሰሩ ላይ ትልልቅ ጥርብ አለቶች በአፈር አልፎ አልፎ ተሸፍነው ተንሳደመው የሚታዩበት ቦታ አለከንደርስ ነበር:: አነዚህ ጥርብ አለቶች ሆን ተብሎ ከላይ ቁልቁል የተወረወሩ ይመስላሉ:: አልፎ አልፎ ሾለከ ብሎ የሚወርደው የፀሀይ ጨረር ሲያርፈባቸው አንደ አልማዝ የሚያንፀባርቁ የነዚህ ግዙፍ ጥርብ አለቶች ከፍሎች አይን ይሠርቃሉ:: እንደገናም፣ አይን፣ ከላይ ሾል ሾል ብለው ወደቆሙት፣ የተራራው አናት ላይ የሚገኙ ከንፁህ ሰማያዊው ሰማያ ጋር የሚነፃፀሩትኝ የአለት ከፍሎች ያማትራል::

ደማቅ ፀሀይ በርቃ፣ የተራሮቹን አናቶች ብርሃን ለታፈሰበትና፣ ኮረብታዎችን የቀሰተ ደመና ህብር በመሰለ ቀለም ለትኩላቸው፣ የአንኳን ደህና መጣችሁ የካምፕ አሳት ወደ ሚታይበት አንደል ዌልስ ካምፕ ደረስን፤ ለዚያን ቀን ላደረግነው ድርብ ጉዞ ማቆሚያ ቦታችን ነበር::

ሌላ የሙሉ ቀን ረዥም ጉዞ፣ ከዚህ ቀደም አንደተገለፀት አይነት ቦታዎችን በማለፍ፣ ከትልቅ ቀጥ ብሎ ከቆመ ተራራ ስር አደረስን፤ የወታደሮቹ ሠንጋጅ፣ መጠነኛ የሆነ ዳገታማ ቦታ አለኪደርስ ድረስ በዚህ ጋራ ዙርያውን ተጠነሞጥሞ ነበር የሚሄደው:: በዚህ ዳገታማ ጋራ ለማሽሽ ማይል የሚሆን ወደላይ ሌላ ከፍተኛ ዳገት ከወጣን በኃላ፣ በመጨረሻ፣ ከባህር ወለል በላይ ስምንት ሺ ጫማ ከፍታ ላይ የሚገኝ የአቢሲኒያ ደልዳላ ቦታ ደረስን:: ይህ

---

[68] ታይታንስ (Titans) ግዙፍ ጃይንቶች ወይም ከሰው ተፈጥሮ በላይ የሆኑ



የሶሮ ማለፊያ (የዲያብሎስ ደረጃ) Record of the Expedition…

ቦታ መጠኑ ሰፋ ያለ አይታ አለው፡፡ በመጀመሪያ እይታ ብቻ፣ ትልቅ ሜዳማ የሆነ ቦታ፡ እዚህም እዚያም ገደሎች እንደ ነጠብጣብ ይታያሉ፤ ብዛት ያላቸው ዋሻዎችና ቅጥ የሌላቸው ጉድጓዶች መሬቱን በሰተውት የማር ሰፈፍ አስመስለውታል፤ ከዚህ በተጨማሪ ሰፋፊ ሰንጥቆችና በእሳተ ገሞራ አማካኝነት የተቆራረጡ የመሰሉ፣ እይን የማይሰቡ የጋራ አናቶችም ይታያሉ፡፡ ከዛ ብለው ከቆሙት፣ ከትልቁ፣ ግራጫ መልከ ያለው ቀጥ ብሎ ተኮሳትሮ የቆመ ቋጥኝ ስር ሰናፌ ይገኛል፡፡ ከደጋማው ከፍታዎች ጠርዝ አንድ ማይል ርቀት ላይ ነው ያለው፤ ይህ አንግዲህ፣ ጠቀሜታ ያለው የአቢሲኒያ መንደር ስናይ የመጀመሪያው ነው፡፡ ከመንደሩ ፊት ለፊት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ያርዶች ርቀት፣ ከትልቅ ግራጫ መልከ ባለው ቋጥኝ ጥላ ስርና ትንሽ ጉብታ ላይ፣ የቀዳሚው ጦር ካምፕ ይታያል፡፡ ከጉብታው ጀርባ፣ በመሬት የታጠረ፣ በየትም አቅጣጫ የሚመጣን ሀይል ለመቆጣጠር በሚመች ቦታ ላይ የትጥቅና ስንቅ ክፍሉ የለፈረበትና በቅሎዎች የታሠሩበት ቦታ ነው፡፡ አልፎ አልፎ በሣርማው ቦታ ላይ ማዕረግ ያላቸው ሰዎችና ዕድሉ የተሠጣቸው የጦር መኮንኖች ድንኳኖች ተተከለዋል፤ ባለ ድንኳኖቹ ደግሞ፣ አንግሊዞችን በተለይ የሚያስደለታቸውን ቀዝቃዛውንና ነፋሻውን አየር ለመቀበል የታደሉ መሆናቸው ነው፡፡

ከነጫጮቹ ድንኳኖች በቂ ርቀት፣ የፍየል መንጋና ጅራተ ሰፈ በጎች፣ ጀርባቸው ላይ የበግ ቆዳ ጣል ባደረጉ ልጆች ይጠበቃሉ፤ ልጆቹ፣ ከርቀት ቀይ ዩኒፎርም የለበሱትን የአንግሊዝ ወታደሮች፣ የሚያብረቀርቁ ጠመንጃዎችንና የሚቀነጠነጡትን የወታደሮችን ፈረሶች በአድናቆት ይመለከታሉ፡፡

እንደለማሁት ከሆነ ሰናፌ በማታ በጣም ይበርዳል፡፡ ድንኳን ለማግኘት ማመልከት እንዳለብኝ ወሰኜ፤ በዚህ መልካም ሀሳቤ ተማምኜ፤ በመሀል ካምፑ ውስጥ ወደ ተተከለው የዋናው አዛዥ የተንጣለለ ድንኳን ርምጃ ጀመርኩ፡፡ ዋናው አዛዥ፣ ጄኔራል ኤም ይባላል፡፡ ባጭሩ፣ ከሱ ጋር ያደረግሁት ቃል ልውውጥ፣ "ደህና አደር" በሚል ቃል ቢጠቃለል ይሻላል፤ በተጨማሪም የተሠጠኝ ማረጋገጫ፣ ሁለተኛ የሱ ድንኳን ውስጥ ብገኝ እርሱ ራሱ እንድመጣ ልኮብኝ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ እየጋለብኩ ከጄኔራሉ ድንኳን ርቄ ስሄድ፣ በውስጤ ለአንግሊዞች ምንም አይነት የፍቅር ስሜት እንደሌለኝ እየተሰማኝ ነበር ድንገት በሥርአት በለበሰ መኮንን፣ ሰው አየፈለግሁ አንደሆነ ስጠየቅ፡፡

"የለም፣ ማንም የምፈልገው ሰው የለም፡፡" አልኩኝ አየሳቅሁኝ፣ "ማታ የማድርበት መኝታ ቤት እየፈለግኩ ነው፡፡"



በቁማይሌ ማለፊያ ፣ አንደል ዌልስ
(ዋቢ መፅሐት ተ.ቁ. 16)

"መኝታ ቤት! የኔ ጌታ፣ ሰናፌ ውስጥ እንደልብ አይገኝም፤ ነገር ግን፣ እንተን ለማስተናገድ ደስተኛ የሚሆኑ ብዙ ደግ ሰዎች አሉ፡፡"

"አህ፣ እምንህለሁ ጌታው፤ በርግጥ፣ ግን የምታውቀው ስም ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"እንዴ፣ እዎ፣ ካፒቴን ስመልፈንገስ የሚባል አለ፡፡" (የስተርንን "ትዝታ ያለው ጉዞ" የሚባለውን ያነበቡ አንባቢዎች ይህንን ስም አይረሱም)"ትልቅ ድንኳን አለው፤ እሱ..."

"ምን!" አልኩኝ፣ "ስመ ጥሩው ካፒቴን ስመልፈንገስ እዚህ አለ? ሰስዚህ ትልቅ ሰው በየቦታው ነው የሰማሁት፡፡ መጀመሪያ በእለከሳንደሪያ፣ ከዛ በሰዊዝ፡ ዙላ፣ ቁማይሌ፣ እና አሁን ደግሞ ሰናፌ ብቅ አለ፡፡ ወደ ድንኳኑ ልታመላከተኝ ትችላለህ? በጣም የሚያሰገርም ሰው ስለሆነ፣ እሁኑኑ አጋጣሚው እያለ መተዋወቅ እፈልጋለሁ፡፡"

"አህ፣ በሚገባ፣ ትንሽዋ ዳገት ላይ ብቻውን ያለ ድንኳን ይታይሃል? ካፒቴኑን እዛው ታገኘዋለህ፡፡ እንደማይህ ከሆነ የተጣደፍከ ትመስላለህ፣ ሰላም እደር፡፡"

"ደህና እደር፣ በጣም አመሰግንሃለሁ፣" ከልቤ ነበር የመለለኩለት፡፡ ከዛም ፈረሴን ኮልኩዬ ከካፒቴኑ ድንኳን ፊት ደረስኩ፡፡

ከካምፑ አቅጣጫ በቁልቁለቱ፣ እጠር ችፍግ ያለ ፂም ያለው ሰው በፈረስ ሲመጣ አየሁ፤ ሰውዬው ቡናማ ቀለም ያለው ልብስ ለብሷል፤ ጠመንጃው ከኮርቻው ጎን ባለ አፎት ውስጥ ይታያል፤ ሁለት ያደናቸውን የወንዝ እሞራዎች ለማሳየት ይመስል በእጁ እያወዛወዘ ነው፤ እደን ለመውጣቱ መረጃም ነው፡፡ ከፈረሱ ወርዶ፣ ፈረሱንና የያዛቸውን ሁለት እሞራዎች ሊረዱት ለመጡት ሁለት እገልጋዮች ከሰጠ በኋላ ዞር ብሎ ሲመለከት እንግዳ መኖሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ይገነዘባል፡፡ ከትልቅ ፈገግታና ከይቅርታ ጥያቄ በኋላ፣ ይህ ግሩምና ታላቅ ሰው፣ በምን መንገድ ሊረዳኝ እንደሚችል ጠየቀኝ፡፡

"የመጣሁት ካፒቴን ስመልፈንገስን ፈልጌ ነው፣ ጌታው፣" አልኩኝ፤ "ባልሳሳት፣ ሰውዬው እንተ መሰልከኝ፡፡"

ወፍራሙን ፂሙን፣ ደጎስ ባሉ ጣቶቹ እያሻሽ፣ እንደገናም በሰፊ ፈገግታ ፊቱን ፈካ እድርጎ፣ "እዎ ጌታው፣ ሰውዬው እኔ ነኝ፡፡" አለ፡፡

እኔም ፂም የለሽ ፊቴን በመዳፊ እየዳሰስኩ፣ ቀደም ሲል የተሰማኝን የብሰጭት ስሜት በማለስለስ መልከ እሱ እንዳደረገው ሁሉ እገጩን እሸት እያደረግሁ፣ ሰለሱ፣ ስለችሎታው፣ የተለየ ሰው የመሳብ ችሎታውና ስለ

ተቀዳጃው ድሎቹ ብዙ የለማሁ ስለሆነ ሳላገኘውና ሳልተዋወቅ ማደሩን አልፈለግሁም ብዬ ነገርኩት።

"አሀ፣ ጌታው፣ ከሚገባው በላይ ከብር ሰጠሽኝ፤ ለመሆኑ ለመነጋገር ይህን አስደሰች አጋጣሚ ያገኘሁት ከማን ጋር ነው?"

የሚፈልገውን አሰደሳች አጋጣሚ ያለ ምንም ገደብ ነው የሰጠሁት። አሜሪካዊ መሆኔን ለናገር፣ ጆሮዎቹ ቆሙ፤ አይኖቹን ወደላይ አንከባለለ እናም ፂሙን እንደማይሆን ሊያደርገው ነበር፤ ነገር ግን ጋዜጠኛ መሆኔን ሲጠቁም፣ በርግጥም እንዲህ አይነት የተቀደሰ የመሰለ ሰሜት በፈቱ በሚታይ ምልክት ይገለፃል ብዬ አልገመትኩም፤ በሰሜት ስለተሞላም፣ ሊናገር ቃላቶች ጎሮሮው ላይ ተሰንቅረው የቀሩ ይመስል ነበር።

ሊናገርም፣ ያገሩ ልጅ እንደሆንኩ፣ ወንድሙ ማለትም እንደሆንኩ፣ በዜግነት ብቻ ሳይሆን በሙያ ጭምር መሆኑንም ገለፀ። ድንኳኑ የኔ እንደሆነ፣ ለራተኞቹም፣ ያለው ራሽንና ማብሰያ ቁሳቁሶቹ የኔም እንደሆነ አረጋገጠልኝ። እንድ ጋዜጠኛ ከዚህ በላይ ምን ይመኛል? አዚህ ቦታ፣ እንግዲህ፣ ቤት፣ ሠራተኞች፣ በቂ የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ የተትረፈረፈ ራሽን ከዚህም በላይ የተከበረ ያገሬ ልጅና ወንድም ተገኘ።

"ጓደኛ፣ አሁን ግን ወደ ውሰጥ፣ ወደ ሽራው መኖሪያዬ እንግባ። ለእንግዳም የሚበቃ፣ ለፈጣሪ የሚሆን አራት ተዘጋጅቶ እየጠበቀን፣ ለምን በዚህ ምሽት ውጭ እንቆማለን።" ምሲጋና የተሞላበት እንግዳ ተቀባይ የሆነ ንግግሩን ከጨረሰ በኃላ፣ እኔና አዲሱ ጓደኛዬ ወደ ድንኳኑ ገባን። በውኑትም የሚያጓጓ ምግብ ተዘጋጅቷል። በዚህ እንዳለን፣ የኔው ውዱ አሊ ሁለቱን እንሰሶች ይዞ ደረሰ፤ ጭነታቸው ወረደላቸውና ከካፒቴኑ የከብቶቹ ምግብ እንዲመገቡ ተደረገ።

አንድ ነገር መናገር አለብኝ በሚል፣ ያለምንም ሰሚታዊ ንግግር፣

"ይቅርታ አድርግልኝ ካፒቴን፤ ባልሳሳት፣ ከጋዜጣ ጋር ግንኙነት እንዳለህ ነካ አድርገህልኝ ነበር።" አልኩኝ።

ካፒቴን ሰመልፈንገስ፣ እንዴት ብሎ በጣም ከፍተኛ የሆነ ታዋቂ የጋዜጣ ሰው እንደሆነ አድርገው ሌሎች እንዲያዩት እንዳደረገ፤ ወይም እንዴት ብሎ በእንግሊዞች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከፍተኛ ሥራ እንደተመደበ ለመግለፅ መብቱ ወይም ፈቃድ የለኝም። ግን ከዛ ቀን ጀምሮ የሰመልፈንገስ የምግብ ጓደኛ ነው የሆንኩት።

በነገታው ጠዋት ለነሳ፣ ፀሀይዋ መሀል ሰማዩ ላይ ከፍ ብላለች። ጎበዙ ካፒቴን፣ በላዩ ላይ "ሰር X. Y." የሚል ፅሁፍ ካለበት ከአንድ ረኸም ሳጥን አጠገብ በርከክ ብሎ፣ አንድ ትልቅ ለው ሊኖረው የሚገባው በውሰጡ ያሉትን

ነገሮች ያገላብጣል። ቀጥሎም፣ በወርቅና በብር የተሰሩ ኮከቦችን፣ ሜዳሊያዎችን በጥንቃቄ ያስቀምጣል። እንደገናም፣ ከህንድ የፑቲያላ መሀራጃ ሥተሠጠውን ለየት ያለ የጩቤ ሰጦታ አላየኝ፤ በሀይደራባዱ ኒዛም የተሠጠውን ሰያሳ፣ የተለየ ያጌጠ ከዘራ፣ ከባሮዳው ጉዊኮዋር፣ ብጫማ ቀለም ያለው የእንሰት ሀብል ከቦፓል ቤገም፣ ከካምብሪጁ መስፍን የተሠጠው ጎራዴ፣ ከጆንራል ቤኔዲክ፣ ከኮኒገራትዝ ጦርነት ከሁለት ቀናት በኃላ የተሠጠው አፈ ሠገባቸው ሰፋ ያለ የዱዌል ሽጉጦች፣ ከአሜሪካው ጂኔራል ሮበርት ኢ ሊ[69] የመሰለያያ ሰጦታ ከብር የተሠራ ሪቮልቨር ኮልት ሽጉጥ፣ እና ሌሎችም ቁሣሪያቸው በርከት ያሉ ነገሮች ነበሩ።

ሣጥኑን እንደገና አየት አደረግሁና፣ "ከሰር X. Y. ጋራ ዝምድና አላችሁ?" ብዙ ጠየቅኩት።

"አዎ፣ የወንድሜ ልጅ ነው፤ በቅርብ ጊዜ ሊሞት፣ በዶረስትሻየር የሚገኝ ዋ;ነው ገሺ ፓውንድ የሚሆን ምን የመሰለ ቤት ለኔ በውርሰ ተወልኝ።"

"አሀ፣ በርግጥ! በጣም ጥሩ ንብረት ነው። እንዳንተ ያለ፣ ከብዙ ሰው ;ዛ; ተውውቅ ያለው ሰው እንዲህ አይነት ጥሩ ንብረት ይጥልለታል።"

"እዎ፣ ልከ ነው።" አለ። ቀጥሎም በአልባሌ አነጋገር፣ "ለነገሩ እንኳን ሣሣሽ ዶዘን የሚሆኑ የዚህ አይነት ትንንሽ ቤቶች በ;ለያዩ የእንግሊዘ አገር ቦ;ታዎች አሉኝ።"

እኔም፣ ወደ ጦር ግንባሩ መቼ ለመሄድ እንደወሰነ ጠየቅሁት።

"ያለ ምንም ጥርጥር፣ ዛሬ ማታ፣" ብሎ መለሰ።

"እንደሱ ከሆኔ ለኔም ይመቸኛል፤ ለፈጣን ጉዞ በአንደኛ ደረጃ ዝግጁ ነኝ።"

"እንደተዘጋጀህ አየለሁ፤" አለ በፈገግታ። "ነገር ግን፣ ብዙ ዕቃዎች ነው ያሉኝ፣ አምስት የጭነት ከብቶች ያለኝን ዕቃ በሙሉ መጫን መቻላቸውን እጠራጠራለሁ፤ ያው የተለመደ የመንገደኞች አባባል እንደሚለው መውሰድ የሚያስችሉትን ዕቃ ጥሎ መሄድ ነው።"

ካፒቴን ሰመልፈንገስ ለካምፕ የሚያለፈልጉ ማንኛውንም ቁሳቁሶች በሚገባ ይዟል። ትልቅ የአሜሪካ ድንኳን፣ አነሰ ያለ ድንኳን፣ ቁጥር ያላቸው የነሳም፣ ጀበናዎቹ፣ ሰሀኖች አሉት። ከዚህ በተጨማሪ የሚበቃ የተለያዩ የፃሙራበ አይነቶች ከአምስት ሠራተኞች ጋር አለው።

ሥኑን ሙሉ፣ ካፒቴኑ ከጓዙ ጋር ሊባትል ነው የዋለው። ያለምንም ሰሪፋት ከአንዱ ወዳንዱ ሊሯሯጥ፣ አንዴ ፈረሶቹን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ

---

[69] ጀኔራል ሮበርት ኢ ሊ(በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ ይመልከቱ)።

የሚሰናዳውን ጓዝ፣ የሚሄደውን ሲያዘጋጅ፣ የማይጠቅም የመሰለውን ሲወረውር፣ አንግዲህ እሱ ለመንገድ ሲዘጋጅ፣ ዙሪያውን አሰፍሰፈው የሚመሰከቱ የአቢሰኒያ ልጆችም አሉ፤ አነሱም መንገደኛው አይረባም ብሎ የሚጥለውን ዕቃ አፈፍ ሰማድረግ ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ፡፡

ከፀሀይ ግባት አንድ ሰአት በኃላ ነው ሁሉም ነገር ተጠናቆ መንገዳችን የጀመርነው፡፡ ከማሰፈያው ሶሮ አጠገብ ካሰ ከፍታ ላይ ሆኖ የሚታይ አሰገራሚ ዕይታ አለ ሲባል ስለሰማሁ ለማየት ወደ ተባለው ቦታ አመራሁ፡፡

በከፍታው ቦታ፣ ጫፍ ላይ ከወጣሁ በኋላ አራሴን ሰሚታየው ዕይታ አዘጋጀሁኝ፤ ወደ ምስራቅ አቅጣጫም ተመለከትኩ፣ በርግጥም ሠአሊ ሰሎት የማያውቀው አሰገራሚ ዕይታ ነበር፡፡

ይህንን ቦታ ያዩ ሰዎች ለእድሜ ልክ የሚረሱት ነገር አይደለም፡፡ በዚያ በአንድ ቅፅበት፣ አየሽሽ የሚሄደው፣ የሚበርቅ የፀሀይ ጮራ የአድዋ ተራሮች ላይ አብርቶ፣ ማቆሚያ የሌላቸው የሚመስሉትን የተራራ ሰንሰለቶች በብርሃን ባህር ያጥለቀልቃቸዋል፤ ይህም ፀሀይ አሰከትጠልቅና ሌሎች ከተራሮቹ ጀርባ ያሉትን የአሰም ከፍሎች አሰከታበራ ድረስ ነበር፡፡

የምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች

ቁጥር 61፣ *ይህን ደሴት፣ ደጃች (አገው) ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ ስለሰጣቸው ለተወሰነ ጊዜ ይዘውት ነበር፤ ሆኖም በምፅዋ የነበሩት ቱርኮች ቦታውን አንዲለቁ አድርገዋቸዋል፡፡ ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል የደጃች ውቤ የአህት ልጅ ነበር፡፡ ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን ቧሂት ላይ ድል ሲያደርጉ ደጃች ንጉሤ ቆስሎ ስለነበር፣ ቴዎድሮስ፣ ማር፣ ቅቤ፣ ፍሪዳ ስጥተው "አድኑት" ብለው ሄዱ፡፡ ንጉሤም፣ ሲድን ሸፍቶ፣ ብዙ ጭፍራ አሰከትሎ ብዙ ጉዳትም አድርሶ ነበር፡፡ ፈረንሳዮች ከሮማ ካቶሊኮች ጋር በመተባበር የንጉሤ ደጋፊዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ የፈረንሳይ መንግሥት፣ ንጉሤን የአቢሲኒያ ንጉሥ በማለት ዕውቅና ሰጥቶት ነበር፡፡ ለዚህም ነው ደሴቱን በሥጦታ የሰጠው፡፡ የቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ጋረድ ከንፉ ሲሸፍት ከንጉሤ ጋር አብሮ ነበር፡፡ አፄ ቴዎድሮስ፣ ትግራይ ድረስ በመዝለቅ፣ አከሱም አጠገብ ሳጋሞ የሚባል ቦታ ከንጉሤ ጋር ይፋጠጣሉ፡፡ የሚባለው፣ ሴሊቱን ወደ ንጉሤ ካምፕ መልክተኛ ተልኮ፣ ንጉሤን ከድቶ ለሄደ ወታደር በሙሉ ምህረት ይሠጣል የሚል መልክት ይሠራጫል፡፡ ንጉሤና ወንድሙ ተሰማ፣ በጠዋት ሲነሱ ሠራዊታቸው ከድቶ ብቻቸውን ሆነዋል፤ ከዛም ወደተንቤን ሸሽተው ነበር፡፡ ግን ከተያዙ በኋላ በፍትሀነገሥቱ መሠረት በሞት ተቀጥተዋል፡፡ የቋመጡት ፈረንሳዮችም መሬት ሳያገኙ ቀሩ፡፡ ቴዎድሮስ ንጉሤን ድል ከመቱ በኋላ፣ ትግራይ ላይ፣ ትክክለኛውን ወራሽ፣ የሰባጋዲስን ልጅ ካሳን (ካሳ ምርጫን አይደለም) ሾመው ተመልሰዋል፡፡ በዚያን ጊዜ መልክኛ የነበረቸው፣ የካሳ ሰባጋዲስ ልጅ፣ አበራሽ፣ ባሏ፣ ተሰፋጽዮን የሚባል የሐማሴኑ ገዥ የደጃች ሃይሉ ልጅ፣ በንጉሤ ተገድሎ ባል አልባ ነበረች፡፡ አቴጌ ተዋበች ከሞተኝ በኋላ ስለነበር፣ ቴዎድሮስ አበራሽን አንደ ዕቁባት ወስደዋት ነበር፡፡ በዚህም ከትግራይ ጋር የነበረው ግንኙነት ለማጠናከር ነበር፡፡ ሆኖም አበራሽም ሆነ አባቷ ካሳ ሰባጋዲስ፣ ብዙም ሳይቆዩ ሁለቱም ሞቱ፡፡*

በዚያን ጊዜ ፈረንሳዮች፣ በኢትዮጵያ ወሰን፣ ቀይ ባህር ደንበር ቅኝ ግዛት ቦታ ለመመስረት ይፈልጉ ነበር፡፡ በህዳር ወር፣ ካውንት ደ ቢሶን የሚባል የፈረንሳይ ጄኔራል ከብዙ ተከታዮች ጋር ሐማሴንን ለመያዝ መንቀሳቀሱ ሲሰማ፣ የሐማሴን ባላባቶች ሰውዬውን ለመውጋት ጦር አደራጅተው ከዚያም ለአፄ ቴዎድሮስ ስለ ፈረንሳዮች አንቅስቃሴ መልክት ልከዋል፡፡ ይህ ደግሞ፣ ቴዎድሮስ በአውሮፓውያኑ ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አጠናከሮታል፡፡ ይህ የፈረንሳይ ጄኔራል፣ ከአስራ አምስት ወራት በፊት በግብፅና በሌሎች ቦታዎች የሰበስባቸውን 40 የሚሆኑ ሰዎች ይዞ ወደሐማሴን መጥቶ ቅኝ ግዛት ለመመስረት ሞክሮ ነበር፤ ሆኖም በሐማሴን ተወላጆች ከፍተኛ ተቃውሞ ስላጋጠመው፣ ያመጣቸውን ሰዎች በትኖ ተመልሷል፡፡

ቁጥር 62፣ *ኮሎኔል መርዌዘር፣ አፄ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን መሳሪያና ቁሳቁሶች በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተዘጋጅቶ ነገር ግን በእንግሊዞቹ ፍራቻ ማለትም*

እነዚህስ ቢታሰሩሰ በማለት፤ በተጨማሪም እነስተርንና ካሜሩን ከውስጥ ሆነው በስውር በሚልኳቸው ደብደቤዎች ጉዳዩን በመቃወም ነው የቀረው፡፡ ስውየው ሊያመጣቸው የነበሩ ቁሳቁሶችና የሠራተኞች ከፍያ ተደምሮ፣ 3500 የብሪታንያ ፓውንዶች ነበር የሚያወጣው፡፡ ቴዎድሮስ ይህን ቢያገኙ ሰዎችን ይለቁ ነበርን? የኔ ጥያቄ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ፣ ራሳም ራሱ፣ 500 ጠመንጃዎች ለቴዎድሮስ በሥጦታ መልክ እንዲሰጥ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ሆኖም፣ ጉቦ ነው ብለው ቴዎድሮስ እንዳይናደዱ፣ በተጨማሪ በየመንገዱ ያሉ ሽፍቶች ወይም የቴዎድሮስ ተቃዋሚዎች ንጉሡን ረዳችሁ ብለው ይጣሉናል በማለት ሳይወሰድ እንደቀረ ያትታል፡፡ መንገድ ላይ በነበሩ ሽፍቶች ምክንያት፣ በዚያን ጊዜም እናም ቀደም ብሎም ብዙ የውጭ ሰዎች በሉዳን አልፈው፣ በምዕራብ፣ በመተማ በኩል ነበር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡት፡፡ ከመተማ ወደ መሀል ከመግባታቸው በፊት፣ በጭልጋው ገዥ በባላምባራስ ገልም በኩል ማለፍ ነበረባቸው፡፡ በዚህ በኩል ከገቡት እንዱ፣ ሄንሪ ዱፈተን፣ ሰለ መንገዱ በዝርዝር ዘግቧል፡፡ ዱፍተን የገባው ከፈረንሳዊው ሌዣን ጋር ነበረ፡፡ ቴዎድሮስ እህያ እየጋለበ መጣ ብለው ከንቀት በመቁጠር በሌዣን ቢናደዱም፣ በእህያ ጀርባ የገባው ግን ዱፍተን ነበር፡፡

ቁጥር 66፣ *እንግሊዞች፣ በዚህ ማለፊያ፣ በግራኝ መሐመድና በፖርቱጋል ወታደሮች መሀከል የተደረገውን ውጊያ አጥንተው ስለነበር፣ ማለፊያው በከረምት ሆነ በበጋ ሊታለፍ ይችላል የሚል ግምት ነበራቸው፡፡ በዚህ ሥፍራ ነበር የፖርቱጋል ወታደሮች መሪ የነበረው ከርሰቶፎር ዳጋማ የተገደለው፡፡ ፅሁፎች የሚጠቅሱት፣ ግራኝ እህመድ የሰውየውን ጭንቅላት ቆርጦ ወደ ምፅዋ በመላኩ፣ የቱርክ ወታደሮች ሳይቀር ተናደው ግራኝ ጥለው ተመልሰዋል፡፡*

ቁጥር 69፣ *ጄኔራል ሮበርት ኢ ሊ፣ በአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የደቡቡ ወይም የኮንፈደሬት ሠራዊት አዛዥ ነበር፡፡ ጄኔራሉ በኮሎኔልነት ማዕረግ እያለ፣ ታዋቂ የፀረ ባርነት እንቅስቃሴ(Abolitionist) ባለታሪኩን፣ አሜሪካዊው ጆን ብራውን፣ በቨርጂኒያ በጦር መካዝን ላይ ጥቃት ሲያደርስ የማረከ ሰው ነው፡፡ ጆን ብራውን በስቅላት ቢቀጣም፣ በደቡብና በሰሜኑ መሀከል ለተከሰተው የርስ በርስ ጦርነት መቀጣጠል እንዱና ትልቁ ምክንያት ነበር፡፡ ሰውየው ነጭ ነበር፣ በአሜሪካው ፕሬዚደንት፣ የአሜሪካ የፖስታ ቤት ሀላፊ ሆኖ ተሹሞ ነበር፡፡ ነገር ግን የባርነት ሥርአቱን ለመገርሰስ የትጥቅ ትግል ጀመረ፡፡ በመጨረሻው ዘመቻ፣ ሁለቱ ልጆቹ በግጭቱ ተገድለዋል፡፡ በዚህ ጊዜም፣ እዔ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ የሚባትሉበትና የባርነት ሥርአት እንዲጠፋ የሚታገሉበት ጊዜ ነበር፡፡ የሮበርት ኢ ሊ ሀውልት እንዳይፈርስ ለተቃውሞ በተሰለፉ አፍቃሪ ናዚና ነጭ አከራሪዎችና በነሉ ተቀዋሚዎች መሀከል በተደረገው ግጭት፣ ቻርሎተስቪል በሚባል በቨርጂኒያ ከተማ የአንድ ሰው ህይወት አልፏል፡፡ ነሐሴ 2017.*

ምዕራፍ ሶስት

አስገራሚ የማታ ጉዞ፣ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ የተወላጆች ዲስኩር

የጨስማ ጉዞ፣ ስውን የሚያጓጓ ምንም ባህሪ የስውም፡፡ መንገደኛው በዙሪያው ያስውን ፅልመት አሻግሮ ለማየትና ክፍተት ቦታ ስማግኘት ያለመታክት ይጥራል፡፡

በዚህ በመጀመሪያው ወደ አቢሲኒያ ዋና ምድር የጨለማ ጉዟችን፣ ሀሳባችንና ምኞታችን ሁሉንም ነገር ቢያካትትም ተስማሚ ግን አልነበረም፡፡ ጨስምለም ማለት ጀምሮ ነበር፤ ገና አንድ ሰአት የሚሆን መንገድ አንኳን አልተጓዝንም፣ የዱር አውሬ መንጋ እየተከተለን ነው ብለን ማሰብ ስንጀመር፡፡ የቁጣ ድምፅ የሚያስሙና፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ ቅፅበታዊ ፍጥነት አልፈውን የሚደርሱብን ነው የመስለን፡፡ ወዲያው ግን፣ ፀጥ ያስውን ጨስማ ያደፈረሰ የሚያስካካ ድምፅ በዙሪያችን እየተቀባበለ መስማት ጀመርን፡፡ ወዲያው ደግሞ ሌላ ፍፁም ፀጥታ ተከተለ፤ ነገር ግን ወዲያውኑ እስፈሪ የአውሬ ድምፅ ተከተሎ መጣ፤ ያሁኑ አንኳን ወደኛ ቀረብ ያለ ነበር፡፡ ሳናስበው በድንገት ፋጫ ጀመርን፡፡ ከዚህ ቀደም የአንበሳ፣ የነብር ወይም የእነር ድምፅ ደጋግሜ ሰምቼ አውቃስሁ፤ ግን እርግጠኛ ነኝ፤ ይህ የስማሁት ድምፅ የአንደኛቸውም አልነበረም፤ አብሮኝ ያለው ካፒቴን የመንገድ ልምድ ያስው ነው ብዬ በማሰብ ጥያቄዬን አቀረብኩለት፡፡ ካፒቴኑ፣ የአውሬውን ጩኸት ከመስማታችን በፊት ከኛ ቀደም ብሎ ነበር የሚጓዘው፤ ስተክታዮቹ ወታደሮች መንገድ አንደሚመራ ሰው፣ በአጁ ትልቅ ጦር ይዟል፤ እያያዙም ትክክስኛ የተዋጊ አይነት ነበር፤ ነገር ግን፣ ቀስ እያለ ፍጥነቱን በመቀነስ አሁን ከኔ ጎን ለጎን ይሄዳል፡፡

"ምን አይነት አውሬ ነው? ካፒቴን" ይህን አንደጠየቅሁ፣ በራሴ ድምፅ የተበረታታሁ ይመስል፣ ድንገት ወዳለሁበት ሁኔታ አአምሮየ ሰብሰብ ማስት ጀመረ፡፡

"ጅብ ነው፣" በማስት ሰውየው መልስ ስጠ፡፡

"አደገኛ አውሬ ነው ወይ ? "

"በጣም"፣ ነበር ምላሹ

"ይተናኮለን ይሆን?"

"እኛ ካልተናኮልነው በስተቀር አይነካንም፡፡"

"ግን በያዝከው ጦር ብትፈታተነውስ?"

"የለም፣ አመሰግናለሁ።።" በማለት መለሰለኝና ሲቀጥልም፣ "ለሱ ስል ጦሬን አላበላሽም። ይልቁንስ ሰአንበላ፣ ጎሬላ፣ ለጉማሬ ወይም ለዱር አሳማ ብጠቀምበት ይሻላል።።"

ከዚያ በኋላ እልጨቀጨቅኩትም። የሱ እጠገቤ መሆን ብርታት እንደሰጠኝ ያሰበ መሰለኝ፤ እናም ከአራት ሰአታት በኋላ ጉና ጉና እሰከንደርስ ድረስ ከጎኔ እልተሰየኝም።።

የጅቦቹና የተኩላዎች ድምፅ ሌሊቱን በሙሉ ከአጠገባችን አልራቀም፤ ወይ እየተከተሉን ነበር፤ እለዚያም አጠገባችን በብዛት ነበሩ ማለት ነው።።

ጉና ጉና ካምፕ አካባቢ የእውሪዎቹ ጩኸት በጣም ደመቀ፤ ሰሀገሩ እንግዳ ሰለነበርን ካፒቴኑ ለኛ በማሰብ ድንኳናችን በካምፑ መሀል እንድንወጥር አደረገን፤ ይህም ከዱር እውሪዎች ጥቃት በደንብ ይጠብቀናል።።

ከመተኛታችን በፊት ግን፣ በመሀል እቢሲኒያ አየሩ ቀዝቃዛ ስለነበር ደመቅ ብሎ በሚነድ እሳት ዙሪያ ተሰባሰብን።። ይህንን እሳት ያዩ የካምፑ ወታደሮችም፣ እዲሰ የመጣነውን መንገደኞችን በዛው ሰላምታ ለመስጠት ሲሉ ተቀላቀሉን።። ከሁሉም በላይ፣ በለበሰው ቡናማ ቀለም ያለው ልብሱ፣ ኮራ በማለቱና በማዕረጉ ምክንያት፣ የአብዛኛውን ትኩረት ያገኘው ካፒቴኑ ነበር፤ በካምፑ ውሰጥ አምስት ደቂቃዎች በማይሞላ ቆይታችን ሁሉም ሰው ከካፒቴኑ ጋር ትውውቅ አደረገ ።።

በካምፑ ውስጥ የነበረው ውካታና ድንኳናችን ቅርበት ድረስ ሲሰማ የነበረው የአራዊቱ ጩኸት በሚቀጥለው ቀን ለሚከተለው እውነታና ግዳጃችን እንድንነቃ ነው ያደረገን፤ ቀኑም ገፍቶ ነበር።። ወዲያውኑ ከሸራው ጣራችን ስር ጥሩ የሆነ የቢጋ አየርና የጋለ አድናቆታችን ወዳተረፈ ዕይታ ወጣን።።

የጉና ጉና ካምፕ ያረፈበት ቦታ በጣም የሚወደድና የሚያሰደስት ሽሰቆ ውሰጥ ነበር።። በዚህ የተፈጥሮ ውበት የተመሠጠው አንድ የሰኮትላንድ ተወላጅ ወጣት፣ ይህ ቦታ የሰኮትላንድን የገጠር ቦታ በተከሎቹና በሚገርመው ውበቱ ገልብጦታል አለ።።

የሸለቆውን ዙርያ በከበበው ገደል ወደላይ ግማሹ ላይ በአለታማው ደልዳላ ሥፍራ ላይ የሸሆ መንደር ይገኛል፣ የቦታው ሰም፣ ጉና ጉና የመጣው ከዚህ መንደር ነው።።

ወደላይ እንውጣና ለመጀመሪያ ጊዜ የእቢሲኒያ መንደር ውሰጥ እንግባ።። ምን አይነት እንግዳ የሆነ ሰፈር ነው? ክሩቅ በጣም የሚያምር የሚመስለው፣ ቀርበው ሲያዩት ግን ደሰ የማይል ሰፍራ ነው።። ተጠጋግተው የተሠሩ ጠፍጣፋ



ጕና ጕና በማይ ሙና ሸለቆ

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ጣራ ያላቸው የጭቃ ቢቶች እንግዳና ለየት ባሉና ያልተለመደ አለባበስ ባላቸው ሰዎች የተሞላ ነው። ሰዎች አሉበት በሚባለው ቦታ ሁሉ፣ ጠቆር ያሉ ራሳቸው በቅባት የራሰ ወንዶች፣ ሴቶችና የልጆች ሰብሰብ ነው የሚታየው። ወጣቶቹ በሙሉ አርቃናቸውን ናቸው፤ በዕድሜ ገፋ ያሉትም ቢሆኑ ለሰሙ ነው ጨርቅ ጣል ያደረጉት። በመንደራቸው መሀል ሰፍራ በሚገኝ አደባባይ ሰቆም፣ ሁሉም በተቻላቸው መጠን አተኩረው ነበር ያዩኝ። በዚህ አደባባይ፣ የሰፈሩ ሽማግሌ የተቀመጠበት በማ የሚባል ቦታ አለ፤ ሽማግሌው በሌሎች እለቆች፣ በሽማግሌው ምክትሎች ወይም በዕድሜ ተከታይ በሆኑ ሰዎች ተከቧል። ደንብ አስከባሪው በሰውየው ቀኝ በኩል ተቀምጧል፤ ንግግር የሚያደርገው ይኸው ሰው ነበር፤ ከሱ አጠገብ ደግሞ ከሳሽ ነው ብዬ የገመትኩት አንድ ወጣት ተቀምጧል። ፍርድ ቤት ነው ማለት ነው፤ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ አና ችሎት ተይዞ ነበር። ምንም እንኳን በጣም እንግዳ የሆንኩ ሰው ብሆንም፣ ተሟጋቾቹ፣ ሽማግሌዎቹ አና የችሎቱ ሰዎች በሙሉ በሙግቱ ሰላተኮሩ እኔን ለረዥም ጊዜ እተኩረው አላዩኝም። ትንንሾቹ ግን ዙሪያዬን ከበው፣ በነዛ ጥቋቁር አይኖቻቸው ያለማቋረጥ አፍጠው ያዩኛል። ሲጋራዬ የተለየ ትኩረት ነው የሳበው፤ ትንሽ እንኳን አይኔን ባንቀሳቅስ ወይም ጠቀሰ ባደርግ ለነዚህ አቦርጂኒዎች[70] የተለየ ሰሜት ነው የሚፈጥረው። ሳል ሰሰል፣ ሁሉም በሃሳብና በአትኩሮት ነው የተዋጡት፤ ድምፄ ደግሞ ሌላ የማይነገር ሁኔታ ነው የፈጠረው። የቆዳዬ ቀለም ደግሞ ምን እንደሆነ ሲፈቱት የሞከሩት ሌላ ነገር ነበር። የእጆቼ ሁኔታ ደግሞ ከራሳቸው ሰውነት ጋር እያወዳደሩ የተመሰጡበት ነገር ነበር። እኔ ግን ችሎቱን ረሳሁት።

ተናጋሪው ሰውዬ እጆቹን ዘርግቶ መሬቱን በእግሩ እየተመተመ ወደፊት በመፈናጠር ቃላቶችን ረግጦ እንዲናገር ያደረገው ነገር ምን ይሆን ብዬ ማሰቤ አልቀረም።

የአቢሲኒያኖችን ሸንጎ ዕድሜ ይሰጠው! ከዚያ በኋላ በሠፈሩ ሰው አንዳለ ታጅቢ የጎጆዎችን ውሰጥ ሁኔታ በቅርብ ለማየት አመራሁኝ። ጎጆዎቹ ለየብቻቸው የተሠሩ ሲሆን፣ ግድግዳዎቻቸው ከሰድሰት እሰከ አሰር ጫማ ከፍታ አላቸው፤ የተሠሩትም በቀይ ጭቃ ነው። ጣራቸው በቀርከሀ አንጨቶች የተሠሩ ሲሆን፣ ላያቸው ላይ ሳር ተደርጎበት ላዩ የማማሸ ጫማ ውፍረት ያለው አፈር ተደምድሞበታል።

---

[70] አቦርጂኒዎች በአወስትራሊያ የሚገኙ ጎሳዎች ናቸው። ፀሐፈው ለምን አቦርጂኒ እንዳሳቸው ግልፅ አይደለም፤ ከጥቁረታቸው በስተቀር። ነገር ግን፣ በፀያፍ አጠቃቀም ጥንታዊ ሰዎች ለማለትም ይሆናል።

በመጠነኛው የጎጆዎች ዙሪያ ባለው ጥላ ስር የሚታዩት በእድሜ የገፉ እያት ሴቶች ሲሆኑ፣ ጥርሳቸው ወልቆ በእድሜ ብዛት ፊታቸው የተጨማደደ ነበሩ፣ አነሱም በእድሜያቸው ክዚህ ቀደም የሚያስታወስቱን ዜማ ሲቆዝሙ ይሰማሉ፤ ዝቅ ባሉት መግቢያ በሮች ደግሞ፣ እድሜያቸው በመቶዎች አመታት የሆኑ ቅድመ አያት ወንዶች ይታያሉ፤ አነሱ ግን በርጋታ ፀጥ ያሉ ናቸው።

ከመንደሩ ሌላው አካባቢ፣ ስዎች፣ "የምስራች! አሸናፊዎች መጡ" ሲሉ በሰማንበት አቅጣጫ ቁጥር ያላቸው ህፃናትና ሴቶች መጡ፤ በአይኔ ዙሪያውን ስመለከት፣ ንቅሳት ያላቸው ጠቆር ያሉ አናቶች በኛ ዙሪያ ተቀምጠዋል። አናቶቻቸውን በማየት የተበረታቱ፤ ወደ ሃምሳ የሚሆን ከብ ዐይን ያላቸው ትንንሽ ልጆች አቧራው ላይ ይቧርቁና ይንከባለሉ ጀመር፤ አቧራውንም ቁልል ፒራሚድ ወይም ቤት የመስለ ቅርፅ ይሰሩበታል፤ ይህም የኛ ልጆች በባህር ዳርቻ ባለ አሸዋ አንደሚጫወቱት አይነት ነበር። ፣ ምንም እንኳን ብዙ ጥቅም ባይኖረውም የሚታየውን ሁሉ ነገር ካየሁ በኃላ፣ የግድ መመለስ ነበረብኛና ጋራውን ወርጄ ስጨርስ፣ ካፒቴኑ አንደገና ሰዛሬው መንገድ፣ ለጉዞ ተዘጋጅቶ ሲጠብቅ አገኘሁት።

በቾኮላ፣ አሳቢው ሠራተኛዬ አሊ ያፈላልኝን ሻይ ጠጥቼ፣ ሲጋራ ለኩሼ ፈረሴ ላይ ወጣሁና ያንን የሚያስደስት እይታ ያለውን ጉና ጉናንና ሸለቆውን ተሰናብቼ ተጓጉችን ተከተልኩ።

ምዕራፍ አራት

የአለት አምባ፣ አንግዳ የሆነ ተፈጥሮ፣ ስመልፈንገስ በፎቃዳ፣ የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያንና የቀብር ስነ ሥርአት

ካፒቴኑንና ተጓዦችን ስደርስባቸው፣ ካፒቴኑ፣ ሀሰን በሚባል ወደፊት መንገድ ስመቀጠል ፈቃደኛ ባልሆነ አገልጋይ በጣም ተበሳጭቶ ነው ያገኘሁት።

ጠቆር ያለው የሀገሩ መሬት አንደአውነቱ ከሆነ አስፈሪ ገፅታ ነው ያለው። ከደረቁ ጥቂት ችፍንች በስተቀር ተከል የሚባል ነገር ፈፅሞ የተራቆተ ነው። ድንጋያማ በሆነ መሬት ብዙ ማይሎች ርቀት የሚሆን ተጓዝን። በግራ በኩል፣ ለብዙ ማይሎች በመንገዳችን ጎን አብሮን የሚሄድ በአለቶች መሀከል የተቦረቦረ በየጊዜው ድንገት የሚታጠፍ ሸለቆ ነበር፤ በቀኛችን በኩል ደግሞ አርባ ማይል ርቀት የሚሆን ጨለም ብሰው በውል የማይለዩ የአድዋ ተራራዎች ይታያሉ።

የአራት ሰአታት ጉዞ ከአንድ ጋራ ስር አደረስን። ጋራው፤ ያቋረጥነውን ደረቅ መሬት ከመሰለ ቦታ ላይ ወደ ላይ ከፍ ብሎ አንደ ጀብራልታር የቆመ ነው። በሁሉም ጎኑ ለመከላከል አመቺ በሆነ ቀጥ ባሉ ገደሎች ነው የተከበበው፤ ዝቅተኛው ቦታ አንኳን ቢሆን ከመሬቱ ሶስት መቶ ጫማ ከፍታ አለው።

አንድ ሺ ጫማ ርቀት ከሚገኘው ሾጠጥ ብሎ ወጣ ያለ ኮረብታ በስተቀር ሌላ ጋራውን መቆጣጠር የሚቻልበት ቦታ የለም። ካለው ስፋት አንፃር ወደ አስር ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ሊያስፍር ይችላል። ለምን አንዲህ አይነቱ በተፈጥሮ የማይደፈር ቦታ በአቢሲኒያው ንጉሥ በቴዎድሮስ አንዳልተያዘ በጊዜው በሃሳቤ ጥያቄ የፈጠረ ነገር ነበር። አንጣሎ የሚባል ቦታ አስከደርስ ድረስ የሀገሪቱ ፖለቲካ በውል አልገባኝም ነበር።

በዚህ ቦታ በደቡባዊ ምሥራቅ ጠርዙ በኩል የአንድ ማይል ተኩል ርዝመት ያለው የኮረብታዎች ስንሰለት ይታያል፤ ላዩም በአጫጭር ዛፎችና የጥድ ዛፎች ተሸፍኗል። በጎንና በጎኑ በኩል ደግሞ ጠበብ ያሉ ሸለቆዎች፣ ስፌ የተባለው ቦታ አንኳን አንድ ማይል የማይሞላ ቀጥ ባሉ የ600 ጫማ ጥልቀት ያላቸው ገደሎች የተመሠረተ ነው። ሸለቆዎቹ ስፋ አያሉ ይሄዱና ዘርጋ ያለ ሜዳማ ቦታዎችና ዛፎች የሞሉበት በውስጡ ወራጅ ውሀዎች የሚፈሱበት ቦታ

ያካፈታሉ። በዚህ ሥፍራ ለአደን የሚሆኑ የተለያዩ አንስሳት ሞልተውበታል። በዘህ በሸለቆው፣ የፎቃዳ መንደርና ቤተክርስቲያን ይገኛሉ። በአጠገቡ፣ ከፍ ባለው ቦታ ላይ የፈረስኞች ካምፓኒ ድንኳኖች ተተክለው ይታያሉ። የወታደሮቹ ካምፕ መሆኑ ነው። በርከት ያሉ የጉድጓድ ውሀዎችን በመቆፍር ውሀ አንደልብ ለማግኘት ተችሏል፤ ውሃውም ስፋ ያለ ማጠራቀሚያ ላይ ተሞልቶ አንስሳቶችን በሙሉ ማጠጣት ተችሏል።

ፎቃዳ ካምፕ የደረስነው ፀሀይ ከመጥለቋ ከሁለት ስአታት በፊት ነበር። ሻዩ በበቂ መጠን ከጠጣን በኋላ፣ ከዚህም ጋር ምቾት ወዳጁ ካፒቴኑ ጓደኛዬ ያዘጋጀውን የተቀመመ ምግብና የሥጋ ጥበስ ከበላን በኋላ ያሳሰፍነውን ችግር በዛፍነት ረሳነው።

ፎቃዳ በጣም የሚስብና የሚያስደስት ቦታ ነበር። ካፒቴኑና አኔም ከረኽቦም ውይይት በኋላ፣ ለሳምንት ወይም ከዛ በላይ ምንም አይነት ወታደራዊ አንቅስቃሴ ስለማይኖር አኛም ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት በዚሁ ቦታ ለመቆየት ወሰን።

የተከበረው ጓደኛዬ፣ የመጀመሪያውን ቀን ያሳለፈው ከጉና ጉና ጉዞ በኋላ በአሳዛኝ ሁኔታ ተጠርፎ የመጣውን የራሱን ጓዝ በማውረድ ነው። በርከት ያሉ ዕርድና ሌሎች ቅመሞችን የያዙ ጠርሙሶች በመንገዱ ላይ በደረስባቸው መንገጫገጭ ተሰባብረዋል። በዚህ ምክንያት፣ የሰውየው ጎኑድጓድ የሆነ የርግማን ጩኸት ከአድሰቢሶች አሽከሮቹ ጆሮ አልፎ ተሻግሮ ወደ መቅደላ አቅጣጫ በሳይንሳዊ መንገድ ቢነጣጠርና ቢለቀቅ መቅደላን ብትንትኑን ባወጣው ነበር።

አጋጣሚ ሆኖ፣ የምግብ ባልንጀራ አስገራሚ ጓደኛዬ አደን በጣም የሚያደንቅና የሚወድ ስለነበር በፎቃዳ ቆይታችን አብዛኛውን ጊዜ በአደን አሳለፈው። ማታ ሲመሰስ፣ በአደኑ ያጋጠመው ገድል፣ አንደሱ አገላለፅ፣ ጠቀም ያለ የፅሁፍ አምድ ይሞላ ነበር። በመጀመሪያው ቀን ሁለት አነሮች፣ ቁለማም የሆነ ኩምቢው ተለቅ ያለ የወፍ ዝርያዎች፣ ሰባት አርግቦች፣ አንድ ጅቦ፣ አንደ ቀበሮ እና የዱር ጥንቸል ገድሏል። ወደ ቤት ይዟቸው ካመጣቸው መሀል፤ አኔ የምመስከረለት አንድ ኮሳሳ ጥንቸል፣ ሶስት ብጥስጥስ ያሉ አርግቦች አና አንድ ትልቅ አሞራ አሰበት። አሞራው ሲለካ፣ በጀርባው ከላባው ጫፍ አስከ ኩምቢው ጫፍ ድረስ፣ አምሰት ጫማ ርዝመት አለው። አብሮት የሄደውን አሊን ስጠይቅ ግን፣ አንደ አሱ አመላለስ ካፒቴኑ ወደ ቤት ያሏቸው ካመጣቸው ውጭ ሌላ ሲገድል አላየሁም ብሎ ነገረኝ። ምናልባትም በአለ. ደካማ የአይን ችግር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በፎቃዳ ቆይታችን በሁለተኛው ቀን፣ ከፍ ያለ ድምፅና ጩኸት ከመንደሩ አቅጣጫ ይሰማን ጀመር። ካምፑም የተሰየመው በዚሁ በመንደሩ ስም ነው። የፎቃዳ መንደር ከኛ በትንሹ ወደግራ በኩል ባለ ኮረብታ ላይ ነው የተመሰረተው። ወዳለንበት ካምፕ የሚያመራውን መታጠፊያ መንገድ መቆጣጠር የሚቻልበት ቦታ ላይ ነው ያለው። ከጋራው ግርጌ ቤተክርሰቲያን አለ። ይህ ደግሞ ከሰናፌ ወደ አንጣሎ በሚወስደው መንገድ የመጀመሪያው የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያን ነው። ቤተክርሰቲያኑ ዙሪያውን በዛፎች ታጅቦ፣ ጠበብ ያለ ከፍተት ጠርዝ ላይ ነው ያለው። ይህ ከፍተት ከቤተክርሰቲያኑ ትንሽ ያርዶች ርቀት ይጀምርና አየሰፋ በመሄድ ትልቅ ሸለቆ ይሆናል። በሸለቆውና በቤተክርሰቲያኑ መሀከል የኋሪዎቹ እነስ ያለ የመቃብር ቦታ አለ።

የኛ ድንኳን የተተከለው በካምፑና በመንደሩ መሀከል ሊጋማሽ ቦታ ነው፤ ሰለዚህ የካምፑና የመንደሩ ጥሩ ዕይታ አለን። ጩኸቱ እየንላ መጣ፤ ከዚያም በረድፍ የሚመጡ ሰዎች ወንዶችም ሆነ ሴቶች ጭንቅላቶቹ ቁልቁሰቱን ሲወርዱ ይታየን ጀመር። ሰዎቹ በዝግታ ነበር የሚጓዙት። አሁንም አሁንም፣ ቆም እያሉ የጀሮ ታምቡር የሚበሳ ጩኸትና እሳዛኝ ድምፅ ያሰማሉ። ጉዳዩ ምን እንደሆን ከጠየቅሁና የቀብር ስነ ሥርአት መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ፣ ሥርአቱን በደንብ ለማየት ከፍታ ቦታ ላይ ወጣሁ።

ትንሹም ትልቁም ተደምሮ ወደ መቶ ሃምሳ የሚሆኑ ሰዎች በጥቂት ካህናት አየተመሩ ይጓዛሉ። አነዚህ የአቢሲኒያ የቤተክህነት ሰዎች የለበሱት፣ በተሰመደው በሥርአት የሚለበስ ረጅም ከጥጥ የተሰራ ቀሚስና ከእንገታቸው ዙሪያ ጀምሮ ሙሉ ሰውነታቸው ላይ የሚወርድ ሰፋ ያለ ሻወል በማድረግ ነው። ቀባሪዎቹ ደግሞ የሚወራጩ ይመስላሉ፤ ላያቸው ላይ የለበሱትን ልብስ ይቀዳሉ፤ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፤ እጃቸውን ደረታቸው ላይ አጣምረው መግለፅ በማይቻል ሁኔታ የሀዘን ምልክት ይታይባቸዋል። በተለያዩ ምስሎችና ፅሁፎች የተሞሉ በብራና በደንብ የተጠረዙ መፅሀፍቶች በእጃቸው ይዘዋል። ፅሁፉም በእራቢክ[71] ቋንቋ ነው። መፅሐፎች አሁንም አሁንም አየተገለጡ ለሚወዷቸው ቅዱሳን ፀሎት ያደርሳሉ፤ ረዘም ያለ ፀሎቱም በጠንካራ የሳምባ አስትንፋስ፣ አፍንጫ ላይ ያዝ በሚያደርግ በሚያሰዛን ድምፅና ማነብነብ ነው የሚካሄደው። ይህ ሥርአት ለሁለት ደቂቃ የሚሆን ከተደረገ በኋላ፣ ካህናቱ እንደማንነበስ ብለው አንደገና ጉዟቸውን ይቀጥላሉ። በየተወሰኑ ርቀቶች አንደመንበርከክ ይሉና ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዜማ ያሰማሉ።

[71] ፀሐፊው ግዕዝ የሚባል ቋንቋ መኖሩን ያወቀ አይመስልም

የመቃብሩ ቦታ ሲቃረቡ፤ አስከሬኑን የተሸከሙት፣ ፀጉራቸው ላይ ሽበት የሚታይባቸው ሰዎች ወደ ጉድጓዱ ጠጋ እድርገው አወረዱት። አስከሬኑ በሕያወት እያለ ሲለበስው በነበረው ሸማ ተጠቅሏል። ከዚያ ቀጥሎ ካህናቱ በሰኑት ያሰሙ ጀመር ሲተረጎም እንደሚከተለው ነው።

"ወርቅነህ፣ የእያሱ ልጅ አሱም የተከኤ ልጅ እርፏል፤ እነሆም እመስግኑ፤ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያቆብ ጋራ ለመሆን ወደ እረፍቱ ሄዷል። በሕያወት ላሉት አንፀልይ፤ ነፍሳቸው ለተኮነነው አንፀልይ። ነፍሱ ከፍርድና ከሥላት ትድን ዘንድ አንፀልይ። ነፍሱስ ከፍዳ እንዴት ትተርፋለች? እጥበቆ በሠገለይ። በአብርሃም ጥላ ሥር አንዲሆን፣ በሙሴ ጎን በሰላም አንዲራመድ ከነብያቶችም ጋር፤ ፀልዩ፣ አሜን እሜን።"

መቃብሩም ተዘጋ፣ ላዩም ላይ የእፈር ቁልል ተከምሯል፤ ዙሪያውን ደጎላም ሞልሞል ያሉ ድንጋዮች ከተደረገ በኋላ፣ በግርጌና በራስጌው ጠፍጠፍ ያሉ ድንጋዮች አንዲቆሙ ተደረገ። ቀባሪ ተበተነ። እብዛኛው ሰው ደግሞ ሥጊያኒቃቃ ዜማ የሚያዜመውን ሰው ተከትሎ ነው የሄደው። ከዚህ ትኩስ ሠፓብር ተነስቼ ወደቤተክርስቲያኑ አመራሁ። ፀሎትና ዜማ ሲያደርሱ ከነበሩት ካህናት አንደኛው ወዲያውኑ የኔ አጃቢና አስጎብኝ እንዲሆን ተመደበልኝ።

ለጉበኝቱ፣ መጀመሪያ፣ በአዲሱ የማርትሬዛ ዶላር ከፍያ መደረግ ነበረበት። ዋጋው ሲነፃፀር በስምንት ሳንቲሞች ከአሜሪካው ዶላር በላይ ያሠኖናል።

በሁለት ትልልቅ የዋርካ ዛፎች የተሸፈነ ቅስት አልፈን ወደ ቅጥር ግቢው ገባን፤ ለከርስትና አምነት ፀሎትና ሥርአት የተከለለ ቦታ መሆኑ ነው።

እንደውነቱ ከሆነ አንዳችም የቤተክርስቲያን ምልክት፣ ማለትም ከትልቁ ካቴድራል ጀምሮ በየትኛውም የአለም ከፍል፣ ከአፍሪቃ በስተቀር፣ የሚገኝ የመስብሰቢያ ቦታ ጋር እንኳን የማይገናኝ ነው። ቁሽሽ ያለና ያልፀዳ፣ በፎቃዳ፣ በቅዱስ ሚካኤል ስም የተሠራ ነው። በበሩ በኩል አንድ ርምጃ ወደ ውስጥ ለተራመደ ሰው፣ ቃል የማይገልፀው የሚያሳዝንና የተረሳ ቦታ መሆኑን ማንም ሠረዳት ይችላል።

ፎቃዳ በመጣን በሶስተኛው ቀን፣ በጥዋት ተነስተን፣ ጓዛችን ሸክፈን፣ ካለንበት የአስር ማይሎች ይርቃል ወደተባለው፣ የሚቀጥለው ጣቢያ፣ ወደ አዲግራት መንገድ ጀመርን።

ይህን መንገድ ለጠረጉት ሰዎች ድካም በቂ ምክንያት ነበረ። ለወታደራዊ ጉዞ አንደዚህ ያለ አሰቻጋሪ ምድር ማግኘት ይከብዳል። የመንገዱ አያንዳንዱ ሣይል የተዘረጋው በጠንካራ ንጣፍ አሰት ላይ ሲሆን፤ አሰቱ ደግሞ በተሰያየ

አቅጣጫ አንደ ጥርስ ፍሩግሩግ ብለው ወደላይ ሾል ሾል ብለው ወጣ በማለት በሚታዩ የአለቱ ከፍሎች የተሞላ ነው። የድንጋይ መፍለጫ መሳሪያዎች አዚህ ቦታ በጣም ያሰፈልጉ ነበር፤ ቀለል ያሉ ቦታዎችን በዚህ የአለት ቦታ ላይ ወደ መንገድ ለመቀየር ብዙ ሰልትና ጥበብ ያስፈልግ ነበር። መንገዱም፣ በሾላ፣ በቁልቋልና በሌሎች ትልልቅ ዛፎች በኩል አልፎ ይሄዳል። ተጨርሶ ሲታይ፣ የሚያስገርም የወታደራዊ ምህንድሰና ሥራ ነው የሆነው። ወደ ጎን፣ ሰፋቱ 15 ጫማዎች ሲሆን፣ በተቻለ መጠንና የአካባቢው ሁኔታ በሚፈቀድው ላዩ ለሰለሰ ያለ እንዲሆን ለማድረግ ተሞከሯል። በሰልፍ የሚጓዙት ወታደሮች በቀላሉ ሊራመዱበትና የማጓጓዣ ጋሪዎችም ቢሆኑ ከባህሩ ደንበር ተነሰተው አዲግራት ድረስ ሊሄዱበት ይችላሉ።

ከዚህ መንደር አንድ ማይል ርቀት ካለፍን በኋላ፣ ጎድጎድ ያለ ቦታ ደረሰንና ቁልቁለቱን በዝግታ ወረድን። በዚህ ሥፍራ፣ በጉዟችን ለመጀሪያ ጊዜ አረንጓዴ በቆሎ አየን። ሰፋ ያለ ቦታ ሆኖ፣ በሥርአት በተቆፈረ መስኖ ውሀ ይጠጣ ነበር።

በዚህ ሰፋ ባለና ፈገግ በሚያሰደርግ አይታ፣ ጣራቸው ዝቅ ያሉ ቤቶች አጅብ ብለው ይታያሉ፤ እኔም ወደነሱ አቅጣጫ መራመድ ጀመርኩ። ወፎች በደሰታ ይዘምራሉ፤ ከምዕራብ አቅጣጫ በሚነፍሰው ነፋሰ፣ የበቆሎ ተከሎች ይወዛወዛሉ፤ የፀሀይ መቀቱም ቢሆን ላዩ ላይ ልከ ባህር ላይ እንደሚወዛወዝ ውሃ ጥላ፣ በአርሻው ላይ ሲርገበገብ ይታያል።

በቦታው አንደደረሰኩ፣ ጠየም ያሉ፣ ፀጉራቸው ጭንቅላታቸው ጀርባ ላይ የተጎነጎነ ሴቶች ልጆች፣ ነጣ ያልነውን ፀጉረ ልውጥ ሰዎች ለማየት ከበቡን። ልጆቹም፣ ልከ ከየትም የአሜሪካ ትምህርት ቤት የሚመለሱ ልጃገረዶች እንደሚያደርጉት በጩኸትና ፍንድቅድቅ በማለት ነበር የተሰበሰቡት። ራቂታቸውን የሆኑ ትንንሽ ልጆች ደግሞ መጡ፤ እነሱም የሰውነት አንቅስቃሰ ችሎታቸውን ለነዚህ የተለዩ እንግዶች ለማሳየት፣ እየተፈናጠሩና እየተዘሏሩ ነበር። እኔም "ሀሊብ" ወይም ወተት እንዳለ ጠየቅሁ; የተለመደውን አዲስ ገንዘብ "ግርሽ" ለመከፈል ፈቃደኛ መሆኔንም ገለፅኩ።

አንዲት ወጣት ሴት ልጅ፣ እንደ ሄብ ረጋ ባለ ሁኔታ ወተቱን ሰጠችኝ። እኔም እንደተጠማ ሰው በማጣጣም በደንብ አድርጌ ጠጣሁ።

አኩለ ቀን ሲሆን፣ የሰር ናፒየር ዋና ጽ/ቤት ያለበት አዲግራትን ማየት የምንችልበት ቦታ ደረሰን።

የተጓዝነው መንገድ አጭር ሰለነበር፣ ተጨማሪ ጉዞ ለማድረግ ወሰንና፣ ከማቆማችን በፊት በኮሎኔል ፋይሪ ከሚመራው ቀዳሚ ወገን ለመድረስ ሙከራ አደረግን። ካፒቴኑ በመንገዳችን ላይ ሁለት ደርዘን የሚሆኑ አርማቦች

በመግደል ለሰር ሮበርት ናፒየር ስጦታ ሊያቀርብ ነው፡፡ እሱ ወደካምፑ ሲሄድ፡ እኔ ደግሞ ወደ ቀኝ ታጠፍኩና የአዲግራት መንደርን ለማየት ሄድኩ፡፡

አዲግራት የተቀመጠቸው፣ በሰፊ ሜዳ መህከል ላይ ባለ እነስ ያለ ከፍታ ቦታ ላይ ነው፡፡ የቦታው ዋናው ገፅታ፣ ከጭቃ በተመረቱ ጡቦች የተሠራ ግምቡ ቤት ነው፡፡ በእንድ ጎኑ፣ ግምቡ አራት ማዕዘን የሆነ ሰቀላ ያለው ሲሆን፡ ከእናቱ ላይ እራት ወጣ ወጣ ያሉ የተገነቡ ነገሮች አሉት፡፡ በሠለጠነ አይን ላየው፣ ለመከላከያ ወይም ለጥንካሬ የተገነባ ከመምሰል ይልቅ ለምስል የቆመ ነው የሚመስለው፡፡

እኛ ቤቱን አልፈን በሄድንበት ጊዜ፣ በቴዎድሮስ ቁጥጥር ስር የሆነ ጌታ ሚስት ትኖርበታለች፡፡ ባሏ ስሌለ፣ ሴትዮዋ በሀዘን የምትፅናና አይነት አልነበረችም፤ ስለዚህ ባሏ ተመልሶ ሀዘንተኛውን ልቧን እለከሚያስደስተው ድረስ፡ ፀሀይ ሆነ ዝናብ ራሷን እንዳይነካት መሀላ ገብታ ከቤቱም አትወጣም፡፡

(ለአንባቢዎች ተጨማሪ ቃል ለመስጠት፣ የምገልፀው ነገር ቢኖር የዚህ ቤት ጌታ መቅደላ ሲያዝ የተለቀቀ ሲሆን፣ አዲግራት መጥቶ የቤቱን ግንብ ሲሆር ፀሀፊዊም በተመሳሳይ ጊዜ አዲግራት ደርሶ ነበር፡፡)

ከዚህ መከላከያ አጠገብ ቤተክርስቲያን ነበር፤ ያለምንም ጥርጥር ከጨለቆት በስተቀር በአቢሲኒያ ካየኋቸው ቤተክርስቲያናት በሙሉ የሚያምር ነው፡፡ ዙሪያውን በቁልቋል ተከሎች የተከበበ ነው፤ የቁልቋሎች ጥላ ራሱ የሚደነቅ ሲሆን፣ ላካባቢው ለላማዊ የሚያረጋጋ ስሜት ፈጥሮበታል፡፡ ቁሶቹ የተከበሩና ሸምገል ያሉ ሆነው፣ በራላቸው ላይ ቀጥ ያለ ከፍታ ያለው ከመጠን በላይ ገዘፍ ያለ ጥምጣም አድርገዋል፡፡ እነሱም መጥተው በሰላምታ ተቀበሉኝ፡፡

ቤተክርስቲያናቸውን ለማየት ባለኝ ፍላጎት የተለመደው መደለያ ተሰጥቶ፣ ለስጦታየም ምክንያቱን ለማስረዳት ባደረግሁት የሰውነት እንቅስቃሴ ተገልፆ ነው፡፡ እነዚህ በጥቅሻና በሰውነት እንቅስቃሴ መግባባቶችን አንድ ስው በቀላሉ ነው የሚማራቸው፡፡ በተጨማሪም ለትውውቅ የሚረዱ ታላቅ ነገሮች ናቸው፣ በዚህ መንገድ የህገሪቱ የምቾት ነገሮች ለምሳሌ ወተት፣ እንቁላል፤ እይብ፤ ዳቦ እና አጃ የመላሰሉትን፣ የገንዘብ ንብረት በፈቀደው መጠን እንድታገኝ ይረዳል፡፡

ቁሶቹ የስጦታዬን ምክንያት ተገንዘበዋል፤ በመግቢያው በኩል በተከሎቹ መሀል አልፈው ወደ ከፍት ገላጣው ቦታ እቅጣጫ ሲሄዱ እኔም ተከተልኳቸው፡፡ ንፁህ ገላጣውን ቦታ አልፈው፣ ወደ ውስጥ በሚያስገባው በአራት ማዕዘን በር አልፍን ሄድን፤ መራመድ ለሰውነት እንቅስቃሴ ሲሉ

የሚያደርጉት እንጂ የተፈጥሯቸው ያልሆነ ይመስል ቄሶቹ እርስ በራሳቸው እየተላለፉ ነው የሚሄዱት::

በቤቱ መግቢያ ወይም በረንዳ በኩል ካለፍን በኋላ፣ ከውስጥ በኩል በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የሚዞር ከፍት አዳራሽ ወስጥ ገባን:: የዚህ ከብ የሆነ ቤተክርስቲያን ግድግዳ የተሠራው በድንጋይ ሆኖ፣ ላዩ አንድ ኢንች ውፍረት ባለው ጭቃ ተስስኖ በተቻስ መጠን ለስላሳ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል::

በዚህ ጸሎት ቤት፣ የእቢሲኒያ ምስሎች ባልተለመዱ መሳሪያዎች ተስለዋል:: መጀመሪያ የቅድስ ጊዮርጊስ ምስል ድራጎኑን በፈረሱ እግር ርግጦ ይታያል፤ የሚያደንቁ ታላላቅ ስዎችና ሴቶች በቡድን ሆነው፣ በፊታቸው ላይ ጥልቅ የሆነ የርካታ ስሜት እያሳዩ፣ ሰው በላው ጠላት ሲገደል አያዩ ነው:: ሁለተኛው ስዕል ፀሎተ ሀሙስ ነው፣ 13 ደቀመዝሙሮች አራት ሲበሉ በሚደነቅ ሁኔታ ነው የተሳስው:: ሶስተኛው ስዕል፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲሰቀል የሚያሳይ ነው:: በዚህ በከፋ መስዋዕትነት፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ስቃይ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፣ የአቢሲኒያው ስእሲ፣ ስቃይ የደረስበትን ሰው ገፅታ ለመሳል ብዙ የደከመ መሆኑን ያሳያል:: በግድግዳው ላይ ሌሎች ስዕሎችም ነበሩ፤ እነሱም ስእምነታቸው ሲሉ መሰዋዕትነት ሲከፍሉ ነው የሚያሳየው:: ባልተባረከው አይኔ የቅዱሶችን ቅዱስ ቦታ ከማየቴ በፊት፣ ሌላ ዶላር ተጠየቅሁኝ፤ ግብሩን ከከፈልኩ በኋላ ቄሱ ወደ ውስጥ፣ በከቡ መሀል፣ ወደ መቅደሱ ወስደኝ:: በቄሱ እየተመራሁም ዙሪያውን ተራመድኩኝ::

ስአይን የሚታይ ምንም እስደናቂ ነገር እልነበረም:: ከፊት ሰፊቱ ከነሀስ የተሠራ ትልቅ መስቀል ያስበት አንደነገሩ የሆነ ጠረጴዛ እስ፤ ይህም ቄሶች በሰንበት ቀን የሚቀድሱበት ነው፤ ስንበት የሚውስውም ቅዳሜ ቅዳሜ ነው:: ትልቅ በቆዳ የተጠረዘ መፅሀፍ አስ፤ መፅሀፍ ቅዱስ ይሆናል፤ ታጥፎ አትሮኖሱ ላይ ተቀምጧል:: ወለሉ ንፁህም እልነበረም፤ እንዳንድ ቦታ ላይ ገስባ ተበትኖ ይታያል፤ አኔን የመሰለኝ፣ አንድ የማይረባ ወሮበላ እንደ መኝታ የተጠቀመበት ነበር::

ከቤተክርስቲያኑ ወደ ውጭ ወጣሁ፤ ቤተክርስቲያኑና ግምብ ቤቱ ከተሠራበት ከዚህ ከፍታ ላይ ሆኖ የአዲግራት ጠቅላላ ሜዳው ይታያል:: በመሀከሉም፣ እንደ በረዶ ቁልል፣ የእንግሲዝ ሠራዊት ንፁህ ነጭ ድንኳኖች ይታያሉ:: ወታደሮቹም እስከዚህ ድረስ በጄኔራሱ እየተመሩ የመጡት የሀገራቸውን ስዎች ለማስለቀቅ ነው::

አሁንም አሁንም፣ ስየት ያስ ሳቅ ይሰማል፤ የእንግሊዝ ሰዎች አይነት ነው፤ በጣም ጎርነን ያስ በመሆኑ፣ ከሩቅ ሲሰማ ስውነቱ ግዙፍ ከሆነ ሰው የሚመጣ የማያቋርጥ ሳቅ ይመስላል:: ቀይ ዩኒፎርም የለበሱ ወታደሮችና



በማይ ዋሂዝና በአዳ አባጋ መካከል የሚገኝ ግምብ ቤት

ዘቦች በእጃቸው የሚያብረቀርቅ ብረት ይዘው፣ በአንዳንዶቹ ዋና ጽ/ቤት ከፍሎች አካባቢ ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ ይታያሉ፤ አለዚያም ባተኮሩ አይኖቻቸው የስንቅና ጥትቅ ከፈሉን ቦታ ይመስከታሉ፤ ይህ ቦታ እንግዲህ የዘመቻው ዋናው ጅማት ቦታ ነው:: ያማረ ዩኒፎርም የለበሱ መኮንኖች፣ በጎናቸው የያዟቸውን ሾተሎች እና የፈረስ መኮልኮያቸውን እያንኳኩ፣ በፈረስ ላይ ሆነው እየተጣደፉ ሲመጡና ሲሄዱ ይታያል፤ እነሱም መልከቶችን ለተለያዩ የሬጅምንት ከፍሎች ለማድረስ ነበር:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ፈረሶችና በቅሎዎች በተርታ ታስረው በረሃብ እያናፉና አየጮሁ የሚቀርብላቸውን መጠነኛ መኖ ይጠብቃሉ:: አሁን እኩለ ቀን ሰስሆነ፣ ውሀ

የሚጠጡበትና የሚመገቡት ሰአት ነበር። በቁጥር ብዛት ያላቸው ያገሩ ተወላጆች፣ ላይናቸው እንግዳ የሆነውን ነገር በጉጉት ለማየት ሰብሰብ ሰብሰብ ብለው ቆመዋል፤ ስላዩት እንግዳ የሆነ ነገር እየተነጋገሩ ነበር ለማለት እደፍራለሁ።

ከዚህ በእቢሲኒያ ሜዳ እንግዳ የሆነና የሚያነቃቃ ዕይታ ጥቂት ማይሎች እለፍ ብሎ፣ ደፋር ተራሮች ወደ ጠርዝና ገደል የመሰለ ቦታ ይታጠፋሉ፤ ከዚያም ሆነው በወይን ጠጅ ቀለም የተጋረደ የባህር ዳር ደመና መስለው፣ በእኩለ ቀኑ ፀሀይ፣ ፀጥታ በሰፈነበት ሁኔታ ይታያሉ። ይህንን በመመልከት፣ መግለፅ የማይቻል የትዝታ መንፈስ በሰውነት ይሰርጣል። ከዚህ ባሻገር እንደገና፣ ተራ በተራ ወደላይ ደብዘዝ ያሉ ተራራዎች ይታያሉ፤ ምስጢራዊና አሰደናቂ በሆነ ከፍታቸው፣ በደናኪል ጨካኝ ጎሳዎችና በእቢሲኒያኖች መካከል በቂ የመከላከያ አጥር ሆነው ያገለግላሉ።

ይህንን ዕይታ እየተመለከትኩ እያለሁ፣ ለራሴና፣ ያለምንም ሀሳብና የሚያስብላቸውም በሌለበት ሁኔታ የሚጓዙትን ሠራተኞቼን እስታወስኩ። ምንም እንኳን ራሴን ለሰር ሮበርት ናፒየር ማስተዋወቅ ብፈለግም፣ የሚሻል ሀሳብ ነው ያልኩት፣ ቀዳሚው ብርጌደ በነጋታው ስለሚጓዝ፣ እኔ ቀደም ብልና ከኛ ቀድመው መንገዱን የተያያዙትን የቃኘውን ጦር ከፍል ብጠጋ ነው። ስለዚህ በፈረሴ ግልቢያ ጀመርኩ፤ እቧራው ሲቦን፣ እንደ አብድ የሚሯሯጡትን ልጆች ሰላስደሰታቸው፣ ፈረሱ እየተጠጋቸው ሲሄድ ከፊት ለፊቱ ይሮጣሉ። ይህ ደግሞ፣ የኛ የሠለጠኑ ልጆች ባቡር ሲመጣ እንደ አብድ ቆመው በመጠበቅ፣ ከዚያም ሲጠጋቸው፣ ለመጨፍለቅ ጥቂት ሲቀራቸው፣ እምልጠው በመሮጥ እንደሚያሳዩት ድፍረትና አይበገሬነት ጋር ተመሳሳይ ነው።

የአዲግራትን ቤተከርስቲያንና ምኑም የማያምረውን ግምብ ቤት በመጎብኘት ያሳለፍኩት የቀን ህልም ጊዜዬን ስለወሰደብኝ፣ ሠራተኞቼ ከኋላ እስከደርስባቸው ድረስ ቀድመውኝ ብዙ ማይሎች እንዲጓዙ ረድቷቸዋል። ከአዲግራት፣ መንገዱ በጥድና ሌሎችም ዛፎች፣ በቁልቋል ተከሎች ታጅቦ፣ ለአይን ደስ የሚያሰኝ መሀል ነው የሚወስደው። ቦታው፣ እንደሰማነው፣ አድፍጦ ለሚጠብቅ ቀማኛ የተመቸ ነው። ነዋሪዎቹ እንደጠቆሙን ከሆነም፣ በየቦታው የሚዘዋወሩት አሮሞዎች ምስጢራዊ በሆነ ቦታ የማይጠረጥር ሰው ድንገት እንደሚያጠቁ ነው።

ያን ቀን ባደረግነው ጉዞ እንደዛ እይነት ቀማኞችም አላጋጠመንም፤ ተጉዘንም፣ ከትልቅ ግዙፍ ከሆነ አለት ስር ባለ፣ ቅጠል የበዛበት መሸዋለኪያ ቦታ ደረስን፤ ይህም ቀጥለን ለምናደርገው ጉዞ መተላለፊያ ነበር። በዚህ ቦታ



የአንግሊዞች ካምፕ በአዲግራት
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

መሀሉ ላይ ትንሽዋን ድንኳን ተከልንና፣ የወደቀ የዛፍ ግንድ ላይ የካምፕ አሳታችን አቀጣጠልን:: ምግብ አዘጋጆች፣ መቀቀያቸውን፣ መጥበሻቸውንና ሰሀኖቻቸውን አዘጋጁ:: አሊ የውሃ መያዣ ከረጢቱን ይዞ ንፁህ ውሃ ወደሚወርደበት ትንሽ ወራጅ ውሃ ሄደ:: የጋማ ከብቶችን የሚቆጣጠረው ሰው፣ በረዥሙ በአሰትና በድንጋይ ላይ በተደረገው ጉዞ የደከመ ቢሆንም፣ ብሰጭቱን የተወጣው አግባብ ያልሆኑ ቃላትን፣ አንደልቡ፣ በራሱና በፈረሶቹ ላይ ካወረደ በኋላ ነው፤ ሆኖም በመጨረሻው፣ ፈረሶችን ውሃ ለማጠጣት ይዞ ሄደ:: አኔ ደግሞ የዚህ ካምፕ ጌታ አንደመሆኔ፣ ራሴን ሞቅ በሚያደርጉ ብርድልብሶችና ከከብት ቆዳ በተሰራ መጎናፀፊያ ተጠቅልዬ፣ በትዕግሥት የካፒቴኑን መምጣት እጠብቃለሁ:: ካፒቴኑ፣ ከኔ ምንም ተቃውሞ ሳይኖር፣ ራሱን የሁሉም አላፈ አድርጎ ነው የሾመው::

በሚገርም ሁኔታ ኮሰተር ብሰን በራሳችን ሀሳብ ተውጠን በነበረበት ወቅት፣ መሀል ላይ፣ የካፒቴኑ ቆርጠጥ ብሎ አቀማመጥ ድንገት የነበረኝን ዕይታ አቋርጦ፣ ባልተለመደ ቀልድ፣ ብሩህ አንዲሆን አደረገው::

"በሉ በሉ፣" አለ በድንገት፣ "ሰራት ምን አላችሁ? ለዘላላማዊ ሰዎች የሚሆን ያማረ አራት እናዘጋጅ፤ አኔ ምግቡን አቀቅላለሁ፣ እና አንተም አጣቢ ትሆናለህ:: ምንድን ነው የምንበላው፣ እህ?" አናም፣ ጣቶቹን ወደላይ አደርጎ፣ በአሱ አጅ ከሚገኝ ሳጥን ውስጥ ያሉ መዘጋጅት የሚችሉ ጣፋጭ ምግቦችን መቁጠር ጀመረ::

"በመጀመሪያ ይህን የመሰለ ሾርባ፣ ለዋናው ምግብ ደግሞ፣ የሚሆነንን ልመልከት፤ የጎሽ ሻኛ፣ የተቀቀለ ወርች፣ ዛሬ ከኮሚሳሪያቱ የተሠጠን አሱም ለኔ ተብሎ ነው፣ ዛሬ ካደንኳቸው የተረፈ የተቀቀለ የዳከየ ሰጋ:: አህ፣ አዎ፣ ደግሞ ሌላ አሞራ አለ:: በጆቭ፣ የአሞራው ሥጋ አለ፣ ከኮሚሳሪያቱ የተሠጠን የተቀቀለ ሥጋ፣ ሩዝ፣ ከሽንኩርት የተሠራ ማባያ አናም አልጫ፣ ሁሉም ከተበላ በኋላ በሞካ ቡና ነው የምንጨርሰው:: ማታ ከመተኛታችን በፊት፣ ከኔ የእንግዳ ጠርሙሴ፣ መጠጥ አብረን እንጠጣለን:: እህ! ምን ትላለህ ፣ አልድ ቦይ?"

"ግሩም!" አልኩኝ፣ "የአቮንን ባርድ ቃላት በመዋሰ፣ ከምግብ ፍላጎታችን ጋር ምግቡም በሰላም ይፈጭልን፣ ለሁለቱም ጤና ይሰጠን!"

"ብራቮ! አው! አው! አ ማይ!" በሎ ጮኸ:: መላጣውን አያሻሽ፣ ወደ ጎን የረዘመ ጢሙን አየጎተተ፣ ሰሜት በተመላበትና በተነቃቃ ሁኔታ መሬቱን በእግሩ ይተመትማል::

መሀመድ፣ ሀሰን፣ ሃቢቡላህ እና አሊ ወዲያውኑ ሥራ ጀመሩ:: እሳቱም ነዶ ይወለበለብና ይንጣጣ ጀመር፤ ሠራተኞችም ወዲያና ወዲህ ይሯሯጣሉ፤

ቀኑ እያዘገመ በትህትና ወደ ምሽት ሲለወጥ፣ ላያችን ላይ የተጋተረው ገደልና ብቸኛው ሜዳ ለእይታችን እየተንሰራፉ በአርንጓዴ ቁጥቋጦዎች ተሸፍነው፣ እየጠለቀች ባለችው ፀሀይ ብርሃን መልበስ ጀመሩ፣ ይህም ለአይን ደስ የሚል ነገር ነበር፣ በዚህ ጊዜ ራት መድረሱ ተነገረ::

የቀረበው ምግብ ሁሉ በጣም ጣፋጭ ነበር:: ሁለታችንም ቢሆን ጥሩ የ ምግብ ፍላጎት ስለነበረን የበላነው ጤናማ ነው የሆነልን፤ ምግብ እየተበላም ማታውን ገፋ አደርግን አመሸን፤ ካፒቴኑም ስላጋጠመው አስደናቂ ገድሎቹ አያወራን ነበር፤ የፀጉር ያህል ከፍተት ሲቀር ከአደጋ ያመለጠባቸው ሁኔታዎች፣ የፍቅር ወሬዎች፣ በጨረቃ ብርሃን በህንድ ሜዳዎች ላይ ያደረጋቸው ግልቢያዎች፣ ከኒሎቲኮች ጋር ባጋጠመው ታሪኮች፣ ፋጢማና ዙሲካ በቀላሉ ታሪካቸው ሲገለጥ፤ የዶን ሁዋን ስሟ ካልታወቀ ሴት ጋር ያደረገው መተሻሸት፤ ተስፋ የሚያስቆርጡ ታሪኮች በሲባስቶፖል፤ ያም የካፒቴኑን የመሰለ ነጭ ፊት በኢንከርማን የምሽግ ጉድባ ለሁለት ሳምንት መጋደም፤ ከነዚህ የሁለት ሳምንታት ሞት የመሰለ ሰመመን ሰዎች አንዳዳኑትና፣ ከዚያም ደግሞ ለአንድ ወር በስኩታሪ ሆስፒታል አልጋ ላይ መከረም፤ የደፋሩ አረብ፣ ወደር የሌለው የነጂድ ጎሳዎች አሚር፤ ፈረሰኛ ሆኖ በቱከሳስ ምድር ከፌደራሎቸና ከኮማንቺዎች[72] ጋር ስላደረገው ውጊያ፤ ጤናማ ባልሆኑ ረግረጎችና ጫካዎች ስላደረገው ውጊያ፤ እና ሌሎችም አስደናቂና አስደሳች የሆኑ ታሪኮችን ጨምሮ ነው:: እነዚህ ሁሉ ታዲያ በፀሀፊ መልአከ ተመዝግበው በመፅሐፍ አልተፃፉም ወይ? ያለጥርጥር፣ ከሱ ሌላስ ማን የፎኖግራፊ አዋቂ አለ፤ አስዚያ እነዚህን አስገራሚ ታሪኮቹን ለመፃፍ በርግጥ እሰቸጋሪ መሆን አለበት፤ ይህም የዚህ የውድ ወዳጄ፣ ጀግናው የምግብ ጓዴ፣ የተከበረው የካፒቴን ስመልፈንገስ ታሪክ ነው::

ከአዲግራት ወደ ማይ ዋሂዝ ርቀቱ አሰራ አራት ማይሎች ነበር:: በዚህ መንገዳችን ላይ ሰው መኖር በማይችልበት ቦታ ነው ያለፍነው:: ለሶስት ሰአታት መንገዳችን ላይ ያጋጠመን ፍርግሩግ ያለ የድንጋይ መንገድ በመሆኑ ለሰውም ሆነ ለእንስሳቱ አድካሚ ሆኖ ነው የተገኘው:: ነገር ግን፣ ማይ ዋሂዝ ለመድረስ ግማሽ መንገድ ላይ ሰንደርስ እይታው ተቀየረ:: ሌላ ሜዳማ ቦታ፣ ልክ በአዲግራት አንዳየነው ተመሳሳይ ደረቅ ያለ ቦታ አይነት ፊት ለፊታችን ተዘርግቷል፤ ድርቀቱ ጠንከር ያለበት ቦታ ላይ አልፎ አልፎ በጥቂት አርንጓዴ ችፍጎች ነፍስ ይዘራል:: በጋራው ጎንና ጎን የነበሩ የተከመሩ ድንጋዮችን ላለመነካካት ስንል ወደዚህ ቦታ ቁልቁል ስንወርድ በጥንቃቄ ነበር::

---

[72] በሰሜን አሚሪካ ከሚገኙ ተወላጆች (በተለምዶ ሬድ ኢንዲያንስ) ጎሳዎች አንዱ

ቁልቁለቱን ስንወርድ፣ ጠጠራማ የነበረው ስንጓዝበት የነበረው መንገድ ወዲያውኑ፣ በቀኝ በኩል፣ በተራው ቀጥ ያሉ ገደሎች ወዳሉበት ወጣ ገባ ቦታ ይገባል፤ አነዚህ ወጣ ገባዎችም ብዛት ባላቸው ሥንጥቆች ተከፋፍለዋል። እነዚህ ሥንጥቆችና ቁጥቋጦዎች ደግሞ ጥሩ መደበቂያ ጫካዎች ይፈጥራሉ፤ በዚህ ቦታም ብዛት ያላቸው ሥጋ በል የዱር አውሬዎች ከተደበቁበት በሌሊት ምግብ ለመፈለግ ይወጣሉ።

በጣም ደህ የሆኑ ገበሬዎች፣ እንደ ጥንታዊ ሰዎች፣ እነዚህን ገደሎችና ዋሻዎች ከጨካኝና ፍርደ ገምድል ገዥዎቻቸው ለመደበቂያ የሚሆኑ ጥሩ ቦታዎች ሆነው አግኝተዋቸዋል። ነገር ግን፣ በነፃነት ሲኖሩ ድፍረትም ስለሚሰማቸው እናም በየጊዜው አየጠነከሩና ቁጥራቸው አየጨመረ ሲሄድ፣ ገበሬዎቹ ከራሳቸው መህል አለቃ ይመርጣሉ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ራሳቸው የተጨቆኑ የነበሩት ወደ ጨቋኝነት ይቀየራሉ። በተሳኩ ዘረፋዎች ንብረት ካከበቱ በኋላ፣ ሊደረሰባቸው በማይችሉ ከፍተኛ ቦታዎች የራሳቸውን መንደሮችና መከላከያዎች ይገነባሉ፤ አልፎ አልፎ ሲወጡም ያልጠረጠረ ገበሬን በማጥቃት፣ ንብረቱን፣ ሚሰቱንና ልጆቹን ይወሰዱበታል።

በዚህ አካባቢ ላሉ ከተማዎች አሠራር ምክንያቱ ይህ ነበር። በዚህ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በድፍን አቢሲኒያ የከተማዎች አመሠራረት በዚህ መልክ ነው። የአሁኑ አቢሲኒያ ሰዎች፣ ብዙ ምእት አመታት ወደኋላ ሳይኬድ፣ የብሪታንያ ጦረኛ ባሮኖችን ነው የሚመሰሉት። ወይም፣ የደጋማው ሰዎች በሰላም በቆላው ቦታ የሚኖሩትን ሰዎች ተመላልሰው ሲያጠቁ፣ የራሂን የወንበዴ ባሮኖችና ካውንቶች ሲያደርጉት እንደነበረው ነው።

ይህንን ሀሳብ ልሰጥ የቻልኩበት ምክንያት፣ ብዙ በመከላከያ የተሠሩ መንደሮች፣ እንደ አሞራዎች፣ ብዛት ባላቸው ሾጠጥ ባሉ ጋራዎች ላይ ከታች ደልደል ካለው ሜዳማ ቦታ በሁሉም አቅጣጫ ከፍ ብለው ተመሥርተው ሰላየሁ ነው። አስፈላጊ ምግቦችን፣ እንደ አንቁላል፣ ቅቤ፣ ወተትና ዳቦ ለመግዛት ወደ አምባዎቹ ግርጌ ከተጠጋን፣ የአምባው ምልከት ነጋሪ ወይም የሚያስጠነቅቀው ሰው መናደዱን በማያሳስት ሁኔታ መግለፅ በሚቻል አነጋገር ሲጮህ አንሰማለን። በእያንዳንዱ አምባ ስር የውሃ ጉድጓድ አለ፤ በጉዟችን ላይ አነዚህ ብቻ ናቸው የመጠጥ ውሀ የሚገኝባቸው። እኛ ግን በአብዛኛው ለመጠጠ የማይሆን የተቋረ ውሃ አጠገብ ነበር ከምፓችን የምናደርገው፤ ይህም ምንም አማራጭ ስላለነበረን ነው። ጦሩ በቦታው አልፎ አስኪሄድና አቢሲኒያኞች ላይ የሚያስተማምን ነገር አስኪፈጥር ድረስ ለደህንነትም አስጊ ነው የነበረው።

ጠዋት መንገድ ስንነሳ አናቆምበታለን ያልነውን ማይ ዋሂዝን ትተን፣ መንገዳችን ቀጠልንና በቂ ውሃ እንደልብ ወዳለበት ወደ አድ አባጋ ገፋን።

አድ አባጋ የሚገኘው የሰሀን ቅርፅ በመሰለ ጎድጓዳ ቦታ ሲሆን፣ ሰፋቱ ሁለት ማይሎች ይሆናል፤ ዙሪያውን በተያያዙ ኮረብታዎች የተከበበ ሲሆን፣ በነኮረብታዎቹ ላይ መንደሮች አሉባቸው። በመንደሮቹ የሚኖሩት ሰዎች አጥቂዎችና ጠብ ወዳዶች ናቸው፤ የሚገርመው ግን፣ በአብዛኛው አንዱ ካንዱ ጋር ዮሀንስ ነው። እርስ በራሳቸው፣ በሚገርም ሁኔታ በለላማዊ መንገድ አብረው መኖር ቢችሉም ከነሱ ውጭ ከሆነው ከቀሪው አለም ጋር ግን ሞጣሀን አይደለም።

በዚህ ቦታ፣ ለአንድ ሌሊት ካምፕ አደረግንና፣ በነጋታው ከአድ አባጋ 12 ማይሎች ርቀት በሚገኘው ወደሚቀጥለው ጣቢያ ወደ ዶንሳሎ ገፋን። ይህ ሙንጎድ የሚያልፈው ልዩ ለሜት በሚሰጥ ምድር ነው። ተከትሎ ለሚመጣው ሠራዊት ሲባል መንገዱ ብዙ ጉልበት ፈሶበታል። ለመጀሪያዎች ሶስት ማይሎች ብዙ ለሜት የማይሠጥ ፈዘዝ ባለ ያገሩ ከፍል ነበር የተጓዝነው። ሣጥና ቁልቁለት አየተፈራረቁበት፣ ሾጠጥ ያሉ የጎጆ ጣሪያዎች ያሉባቸው ሙንደሮች በየጋራው አናት ላይ ሆነው ይታያሉ፤ አነዚህ ደግሞ ከታች ከሜዳው ካሉ ሰዎች በኩራት የተለዩ መሆናቸው ነው።

ከዛ ቀጥሎ፣ አጠር ካሉ የቁጥቋጦ ጫካዎች ተመንጥሮ በተሠራ መንገድ ላይ ተጓዝን። ከነዚህ ቁጥቋጦዎች በላይ የጥድና ሌላም ዛፎች ረዘም ብለው ይታያሉ። ቅርንጫፎቻቸው፣ ለኩለ ቀን ላይ፣ ከምለራቅ ባህር ከደናኪል በረሀ አልፎ በሚመጣው ንፋስ ሲወዛወዙና ሲያጎነብሱ ይታያል። ከዚያ ቀጥሎ በየቦታው፣ አንዳንዶች ትልቅ፣ ሌሎቸም አነስ ያሉ የድንጋይ ቁልሎች መገመት በማይቻልና በሚያደናብር ሁኔታ በየቦታው ተቀምጠው ይታያሉ። ወዲያውኑ ፊዜለም ባለ ሸለቆ አለፍን፤ በሸለቆው ጎንና ጎን ባሉ አናቶች ላይ፣ ጥቂት ሰዎች ብዛት ያለው ሠራዊት ማባረር የሚችሉባቸው ሥፍራዎች ናቸው። እንደገና በለጥቀጦዎች በተሞላ ደን ውስጥ፣ ቀጥሎም ትልልቅ ዛፎች ያሉበት መንገድ ላይ ተጓዝን፤ በነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው ላይ ጦጣዎች የሚራወጡባቸው፣ ወሮች የሚዘምሩባቸው፣ ቀለማም የሆነው ወፍ ከንፉን በመዘርጋት ለአገሩ እንግዳ የሆኑ ነጭ ወራሪዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል ይመስላል።

የሚያሳዝነው ግን፣ ከነዚህ ዕይታዎች በተለየ፣ ግራጫ መልከና ጠቆር ያለ ገፅታ ያለው የአለት ቋጥኝ ፈጠጥ በማለት ይታያል፤ ፀጥ ያለም ሆኖ ላዩ ላይ ወሮችም አይዘሙበትም፣ ባለ ላባ ወፎችም አይዘምሩበትም ነበር።

በነዚህ ዕይታዎች መህከል በፍጥነት አልፈን፣ በመታጠፊያው ዙሪያ ግዙፍ የሆነው የባምባ ዛፍ ይታያል፤ ቅርንጫፎቹም በአቢሲኒያ ዝንጀሮዎች ተሞልታል፤ ዝንጀሮዎችም በተጠጋን ቁጥር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ለመግለፅ ያጉረመርሙ ነበር፤ ከዛም ወደ ሚቀጥለው ጋራ ጠቅለው በመውጣት ጥላቻቸውን በሚያሰሙት ድምፅ ይገልፁ ነበር።

የባምባ ዛፉንም አልፈን መንገዳችን በተራራ ዳገት ዙሪያ ወስደን፡፡ የተራራው አናት ከፍ ያለ በመሆኑ ደመናውን የሚጠቅስ ይመስላል፤ ቀና ብሎ ለሚያይ ሰው ራስ የሚያዞር ስሜት ይፈጥራል፡፡ ዳገቱን አቀፍ አድርገን ዕይታችን ቀየርን፤ የተለያዩ ተራራውን የፈጠሩትን አለቶች ለማድነቅም ነበር፡፡ በአግድሞሽ በደረጃ የተቀመጡትን የተራራውን ከፍሎችና የተለያዩ የድንጋይ አይነቶችን አይተን፣ ትንሽ ብርቅ የሆኑ ጠጠሮች ለቅመን የዶንጎሎ አረንጓዴ ሸለቆ አስኪታየን ድረስ መንገዳችን ቀጠልን፡፡ በደንጎሎ በመሀሉ፣ ሁለት ወይም ሶሰት ድንኳኖች ልከ የተከመረ ቾከ መስለው በሚመቸው ላር ላይ ተተከለዋል፡፡

አንድ ሌሊት በዶንጎሎ ካደርን በኋላ፣ የአስር ማይሎች ርቀት በመጓዝ ወደ አጉላ ወንዝ ሄድን፡፡ ፀሀይዋ ገና በደንብ ሳትወጣ፣ ራላችን በአንድ ኩባያ ሻይ ካረጋጋን በኋላ፣ አንደገና ዳገታማ፣ ወጣ ገባ የበዛበት ኮረብታ ላይ መንገድ ቀጠልን፡፡ በሜዳዎች አቋርጠን፣ አረንጓዴ ሸለቆዎችን፣ በሽፍቶች መኖሪያና በገበሬዎቹ ዋሻዎች አድርገን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ጉዞ ቀጠልን፡፡ ፀሀይ ወጣችና የፈነጠቁት ጮራዎቿ ደግሞ ከፈት ለፈታችን የነበረውን መቀነት የመስለውን ጭጋግ በመብሳት የሚያሸበርቅ ኅብረ ቀለም ያለው አለደላች ብርሃን ፈጥረውበታል፡፡

የነበረው ጭጋግ ሲጠፋ፣ ጠቆር ያለ ጥላ ያላቸው በቁልቋል የተሸፈኑ የተራራ ስንስለቶች ከፍታቸው በሚለይ ሁኔታ ለኛ ተገለጡልን፡፡ ከዚህ ቀደም ከአንድ ለአት በፊት ያየነውን አድማስ አቋረጥን፤ ሆኖም ሌላ በደመና የታጠረ ኮረብታ፣ ጨለም ያለና አለፈሪ የሆነ ተተካብን፡፡ ይህም፣ ባህር ብቻ ላየና የኢትዮጵያን ተራራዎች ላላየ ሰው የማይታመን ነገር ነው፡፡ ከዚህ አልፎም ተለፋፍቶና ተንጣሎ፣ በርቀት፣ ሌላ ምድርና ሰው ያልረገጠው በረሃ አንደሚኖር ተገንዝበናል፡፡ ያም ሆኖ ፀሀይዋ ያለ ምህረት አናታችን ላይ ትወርዳለች፤ አንደገናም ተመሳላይ ዕይታ ደግሞ ደጋግሞ ይታያል፡፡ በትግስትና ምንም ሳያማርሩ፣ ከብቶቻችን የተረጋጋ ጉዞ ያደርጋሉ፤ ሙቀቱንም ሆነ ኩቻ ዋላዎች የሚያወርዱባቸውን ዱላዎች ቁብ የሠጡት አይመስልም፡፡

ለመልፈንገስ ከትንሽ የመንገደኞች ቡድን ፈት ለፈት ቀደም ብሎ ነው የሚሄደው፤ ያደረገው ለፋ ያለ ባርኔጣ ጭንቅላቱንና ፈቱን ሸፍኖታል፤ ምኑም አይታይም ነበር፤ ተኝቶ ይሆን እያለመመ ይሁን መገመት አልቻልኩም፤ ወይም ደግሞ አይኑን አፍጥጦ አካባቢውን አያስተዋለ፣ የነበረውን ፀጥታ አደፍርሶ፣ የሆነ ነገር ለማለጥ አይጠበቀ ይሆናል፤ የማያስደስት ፀጥታ ነው፤ አኔም ከኋላ አየተከተልኩ ነበርኩ፡፡

ፈረሴም ቢሆን፣ አኔ አንደተሰማኝና አንዳሳየሁት ሁኔታ በጣም የተከፋ ነው የመስለው፡፡ ለማያዊውን ለማይ አስተውዬ፣ አንደ ሁለት ጊዜም ቢሆን

ሀይለኛዋን ፀሀይ በአይኔ ጠቀስ አድርጌያለሁ፤ ከዚህም ጋር አድማሱን እየመላለስኩ ተመልከቻለሁ፡፡ የበቅሎዎችን ማለሪያዎች የጎደለ ነገር አንዳለ ብዬ በከንቱ ፈልጌ ነበር፤ የሠራኞችን ባህሪም በጥንቃቄ ተመለከትኩ፤ አለቃው ማን መሆኑን ለማላየት ለቅጣት የሚሆን ለበብ እየፈለግሁ ነበር፡፡ የካፒቴኑን ጀርባ አያየሁ በአአምሮዬ ብዙ ምስል አየፈጠርኩ ነበር፤ በሀሳቤም አሽንጌ ሀይት ላይ ከነትልቅ ባርኔጣው ቁጭ ብሎ ሲቀዝፍ አየሁት፤ እሱም ቢሆን ይህን አደርጋለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ነበር፡፡

ከሚያለጨንቀው አለልቺ ጉዞ አረፍ ለማለት ምን ማድረግ አችላለሁ? ጥያቄው በራሱ ተመለስ፡፡ በቀኑ በጠራራው ፀሀይ ሁለቱ አይኖቼ እንደተገለጡ፣ የቀን ህልም ጀመርኩ፤ በጣም የሚያምር፣ የምቾት፣ አዲለ ወይም አንግዳ የሆነ ነገር በመመኘት፣ የሚያነቃቃና የሚያለደስት ነገር አያስምኩ ነበር፡፡

ግራ የሆነ ሀሳብ በአአምሮዬ ብልጭ አለብኝና አኔም ሳቅሁኝ፤ በዚህ ጊዜ የኔው አሊ በትልልቅ ጥቁር አይኖቹ ዞር ብሎ አየኝ፤ በመገረምም አየተመለከተኝ፣ "አሁን በሀበሻ ምድር ምን የሚያስቅ ነገር አገኘህ? ጌታው፡፡" የሚል ይመስላል፡፡

ካፒቴኑ ሾጠጥ ያለውን ጭንቅላቱን ሲያዞር፣ ጭንቅላቱ ላይ የነበረው ባርኔጣ አንደ ሙዚቃ ማጫወቻ ሽክላ አብሮ ዞረ፡፡ በመደነቅ ሁኔታ ተመለከተኝ፤ አኔም ትንሽ አንደ ማፈር አልኩ፤ ነገር ግን፣ ከሱ አሻግሬ በርቀት ተመለከትኩኝ፡፡ ከዛም፣ "ካምፕ! ካምፕ!" አያልኩ ጮህኩኝ፡፡ የሚገርም ትንሣኤ፡፡

በቅሎዎችም አናፉ፤ ፈረሶችም አሰካኩ፤ ካፒቴኑም፣ ከሱ አፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁትን ዜማ፣ "ላ ላ ላ ቲ፣" በማለት መዘመር ጀመረ፡፡ የአረቡ ሱሩጂና የህንዲስታኑ ኩቻ ዋላዎች በአራት ጥንድ ከንፈሮቻቸው የሚያላዝን አይነት ዜማ ማጉረምረም ጀመሩ፤ ነገር ግን ለትልቅ አፎይታና ከልብ የመነጨ ምስጋናም ለመግለፅ ነበር፡፡ ይህም፣ ከካምፑ አጠገብ ወዳለው የወንዝ ዳርቻ ለንደርሰ የተደገመ ነበር፡፡ በአቢሲኒያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየነው ይህ ወንዝ ከዋርካ ጥላ ስርና ከፈረስ የቀድሞ ቤተመቅደለ አጠገብ ነበር፡፡

ካምፓችን ያደረግንበት ይህ የፈረለ ቤተ መቅደለ፣ በአለራ አንደኛው ከፍለ ዘመን አፄ ላሊበላ ቅዱስ ዶርካስ ለተባለ ለግሪክ ሰው ያሠራው ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ በዚህ ሀይማኖተኛ ንጉሥ በየቦታው ከተሠሩት ቤተ ክርስቲያናት አንዱ ነበር፡፡ የመሀመዳን ጎላ የሆኑ ሰዎች እንደርታ ድረለ በመዝለቅ ባደረጉት ወረራ ምክንያት ቀስ እያለ እየፈራረሰ ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ የአጉላ ወንዝ ይወርዳል፡፡ ለባጋዲስ ሥልጣን ሲይዝ፣ በዚህ ቦታ ብዙ

ንብረት ተቀብሯል የሚል ወሬ ስለሰማ ቦታው እንዲታሰስ ትዛዝ ሰጥቶ ነበረ። በዚህ ንብርት ፍሲጋ ምክንያት ግንቡ መፍረስ ነበረበት።

ንብረቱም ተገኘ፤ ነገር ግን፣ ይህ ጥንታዊ ቦታ፣ ንብረት ፈላጊ ሠራተኞች ሲቆፍሩ አፈርሰው ትተውት በሄዱበት ሁኔታ ይገኛል። ሁለት ምሰሶዎች ብቻ ነው ቆመው የቀሩት። በአንዳንድ ክፍሉ፣ ከአምነበረድ የተሠራው ወለል እንዳለ ይታያል። በዚህ በምንጓዝበት የሀገሪቱ ከፍል ወንዝ በጣም ሰለማይገኝ፣ ወንዝ ተብዬውም ለአከብሮት ሲባል እንደ ስሙ ወንዝ ከተባለ፣ በጣም ፈጣን ትንሽ ወራጅ ውሃ ነበር። ጥልቅ በተባለበት ቦታ የውሀው ከፍታ እስከ ቁርጭምጭሚት ብቻ ነበር፤ በጎን ግን ትንሽ ያርዶች ያከል ሰፋት ሰለነበረው እኛም ሆነ ከብቶቻችን ዘሰን ገባንበትና ሰእንድ ሰአት የሚሆንም ትንሽ ተንፈስ አልን።

በአጉላ ካምፕ፣ ኮሎኔል መርዌዘርንና የዘመቻው የተከበረ የጂአግራፊ ባለሙያውን ሚስትር ከለመንት ማርከህምን አገኘናቸው። አንደሚታወሰው፣ ኮሎኔል መርዌዘር ወደ መቅደላ የሚወስድ ምቹ መንገድ ለማግኘት መጀመሪያ አቢሲኒያ ያረፈው የቃኘ መኮንን ነው። ፊት ለፊት ከተገናኘን በኋላ፣ በኔ ዳኝነት፣ እንደሱ፣ ለተመደበበት ሥራ ትከከለኛ የሆነ ሰው ማግኘት ይከብዳል።

ፈጣን የሆነና አንቅሰቃሴ የተላበሰው ይመስላል፤ በጣም የሚገርም ነገሮችን የማስተዋል ችሎታ አለው፤ ወሳኝና ፈጣን የሆነ መንፈስ ያሳያል። የሲንዲ ሆርስ (ፈረሰኛ) የሚባለው የጦር ከፍል ኮሎኔል ነው፤ ነገር ግን ወደ አቢሲኒያ ከመምጣቱ በፊት በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነበረ። ኤደን እያለ፣ ራሳም የሱ ፀሀፊ ነበረ፤ በሚሰተር ላያርድ ግፊት ነው እንግዲህ የእርመን ተወላጁ ራሳም ወደ ቴዎድሮስ መልከተኛ ሆኖ የተሾመው። በኔ አስተያየት ያ ምርጫ ትከከል አልነበረም፤ ነገር ግን፣ መርዌዘር ሌላ የተሻለ ኢይገኝም በሚለው አምነቱ ፀንቶ ነበር።

ኮሎኔሉ ደግና ተወዳጅ ባህሪ የተላበሰ ነው፤ አንደዚህ ያለ ሰው ሲናገር፣ ምንም አይነት ስሜት የማየሳይ እና ስራም ሲያከናውን ምንም የተለየ ነገር የማያሳይ ሰው ማየት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነበር።

እጉላ በቆየንባቸው በሶስቱ ቀናት፣ ካፒቴኑ ለአደን ወጣ። እመሸሽ ላይ፣ የተለያዩ ያደናቸውን በደርዘን የሚቆጠሩ የአሞራ ዝርያዎች ይዞ ይመጣል። ሶስት ከርከሮ ገድያሰሁ ብሎ ተናግሯል፤ እኔ ግን እንድ እንኳን ማየት ብመኝም ያየሁት ምንም ነገር የለም። በአራተኛው ቀን፣ ድንኳናችን ነቅለን፣ ጓዛችን ጠቅለን፣ ከብቶቻችን ጭነን ወደ እንጣሎ ጉዞ ጀመርን።

ከአጉላ ወንዝ ወደ አንጣሎ ያደረግነው ጉዞ ምንም የሚያስደስት አልነበረም። በመጀመሪያው ቀን ማምሻውኑ ከእጉላ 19 ማይሎች ርቀት ቦታ ሦሚንኘ ዶሪሎ የሚባል ቦታ ደረስን፤ በሁለተኛው ቀን፣ 9 ማይሎች ርቀት ላይ እያኩለት ደረስን፤ በሶስተኛው ቀን ከ14 ማይሎች ጉዞ በኋላ አንጣሎ ገባን።



የግሪክ ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ በአጉላ፣ የሰታንሊ ድንኳን

ምዕራፍ አምስት

የናፒየር እዋጅ፣ ዲፕሎማሲ፣ ሜጀር ግራንት፣ የናፒየርና የመስፍኑ ካሳ ግንኙነት፣ የወዳጅነት ዕይታዎች

እኔና ሀይለኛው ካፒቴን በደስታና በተዝናና ስሜት ወደ አንጣሎ ስንጓዝ፣ ከጀርባችን ከትንሽ ርቀት በኋላ አንድ የእንግሲዝ ጄኔራልና የአቢሲኒያ መስፍን ዋና ተወናዮች የሆኑበት የሚገርም ትዕይንት እየተካሄደ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ለመግለፅ ከዚህ ምዕራፍ ውጭ በሌላ የመፅሐፉ ከፍል የተሻለ ቦታ አይገኝም፡፡

የተከበረው ሌፍተናንት ጄኔራል ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የአቢሲኒያ ዘመቻ ጠቅላይ አዛዥ፣ አቢሲኒያ እንደገባ የሚከተለውን እዋጅ[73] ለገዥዎች፣ ለአሰቆች፣ ለሀይማኖት መሪዎች እና ለአቢሲኒያ ህዝብ አስነገረ፡፡

"ሁላችሁም እንደምታውቁት፣ የአቢሲኒያ ንጉሥ ቴዎድሮስ፣ የሠለጠኑ መንግሥታትን ህግ በመጣስ የእንግሊዝ እምባሳደር ካሜሩንን፣ የእንግሊዝ መልክተኛ ራሳምንና ሌሎችንም በእስር ይዟቸዋል፡፡ በወዳጅነት በተደረጉ ግፊቶች እስረኞችን ማስለቀቅ እልተቻለም፤ የሀገሬ መንግሥት እስረኞችን ለማስለቀቅ ጦር ይገፍ እንደመጣ ትዛዝ ስጥቶኛል፡፡ ለእስረኞች ወዳጅነት ያሳየ ወይም እነሱን ነፃ ለማውጣት የተባበረ ሁሉም ሰው ሽልማት ያገኛል፡፡ ነገር ግን እነሱን የሚጎዳ ማንም ሰው፣ የእንግሊዝ ጦር ወደ ሀገራችሁ በሚገባበት ጊዜ ከባድ ቅጣት ይደርስበታል፡፡ የእቢሲኒያ ህዝብ፣ ልብ በሉ፣ የእንግሊዝ ንግሥት በናንተ ላይ ምን ከፉ ሀሳብ የላትም፤ ሀገራችሁም ሆነ ነፃነታችሁ ላይ ምንም ዕቅድ የላትም፡፡ የሀይማኖት ቤቶቻችሁ፣ ስዎቻችሁና ንብረታችሁ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡ ለወታደሮቼ የሚቀርብ ሁሉም ነገር ዋጋው ይከፈላል፡፡ ማንኛውም ሰላማዊ ኗሪ ጉዳት አይደርስበትም፡፡ ለእንግሊዝ ወታደሮች ወደ አቢሲኒያ መላክ ዋናው ተልዕኮ የግርማዊነቷን እገልጋዮች ነፃ ለማውጣትና ሌሎችም ያለአግባብ የታሰሩትን ለማስለቀቅ ነው፡፡ ይህ ተልዕኮ እንደተሳካ ጦሩ ወደመጣበት ይመለሳል፡፡"

"የአቢሲኒያን ግዛቶች በቋሚነት ለመያዝ ወይም በአገሪቱ መንግሥት ጣልቃ ለመግባት ምንም ፍላጎት የለም፡፡"[74]

ፊርማ 'R. Napier.' (እር. ናፒየር)

---

[73] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[74] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

ደጃዝማች ካሳ[75]፣ የትግሬው ራስ (በአንግሎ ሳክሶን አጠራር ጄኔራል ካሳ፣ የትግራይ ልዑል የሚል ማዕረግ በመስጠት) የዚህ በጥንቃቄ የተፃፈ ለስለስ ያለ አዋጅ ቅጂ ይደርሰዋል፡፡ ደብዳቤውን እንደተቀበለ ልዑሉ እድናቆቱን ይገልፃል፤ የደብዳቤውን ፀሐፊ፣ አለዚያም በእሱና በፀሐፊው መሀከል ግንኙነት ለመፍጠር ሥልጣን ያለው የፀሐፊውን መልከተኛ ማግኘት ይፈልጋል፡፡ የአዋጁ ፀሐፊ፣ በልዑሉ አገር አቋርጦ ወደመቅደላ ስለሚጓዝ፣ በሁለቱ መሀከል ወዳጅነት ቢፈጠር ትልቅ ፖለቲካ ጉዳይ ይሆናል፡፡ የሚቀጥለው ደብደቤ ከልዑል ካሳ ወደ ሰር ሮበርት ናፒየር የተላከ ነበር፤ እንደኔ ግምገማ፣ እንደ እንግሊዙ አዛዥ ደብዳቤ ሁሉ፣ የዚህም ቃላቶቹ በጥንቃቄ የተመረጡ ነበር...

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ፡፡

ደብዳቤ ተፃፈ ከደጃዝማች ካሳ፣ ርዕሰ መኳንንት ኢትዮጵያ፣ ይድረስ ለእንግሊዝ ወታደሮች አዛዥ፡፡ እንደምን አሉ? ደህና ነዎት ወይ?

በክርስቶስ ፈቃድ የአባቶቼን የሚካኤልን፣ የወልደ ስላሴን[76]፣ የሰባጋዲስን ዙፋን አስመልሻለሁ፡፡ ቀደም ብሎም ክቆንስል ሳልት ጀምሮ እስክቆንስል ፕላውደን ድረስ ወዳጆች ነበርን፡፡ ከአርስዎ ደብዳቤ እጠብቅ ነበረ፤ ሆኖም ሰለዘገየ አኔ ራሴ ልኬያለሁ፡፡ የመጣችሁበትን ጉዳይ አላውቅም፤ ባውቅ ደስ ይለኛል፡፡ ወዳጆች ነን፡፡ የአኔንም የአርስዎን ቋንቋ በሚያውቅ ሰው፡ በአቶ ወርቄ ልጅ፣ በምርጫ[77] በኩል ሰድጃለሁ፡፡ አኔ በልቤ ያለውን ልኬያለሁ፤ አርስዎም በልብዎ ያለውን ይላኩልኝ፡፡"

ተፃፈ 1860 አመተ ምህረት፣ ዘመነ ዮሐንስ፣ በህዳር 18፣ ረቡዕ ቀን፡፡

ፊርማ ደጃዝማች ካሳ[78]

ርዕሰ መኳኳንንት ዘኢትዮጵያ

ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ፣ እኛም እንዳመንበት፣ ልዑል ካሳ የልቡን ገልጧል፤ ሰር ሮበርት ናፒየርም በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የልቡን እንዲገልጥ በትህትና ተጠይቋል፡፡

ስፖለቲካ ሲባልም ወደፊት እንደምንመለከተው፤ የእንግሲዙ ጄኔራል ተሞጊ ብቻ ሳይሆን አንደኛ ደረጃ ዲፕሎማት ሰለሆነ፤ ሜጀር ጄምስ ግራንት፣

---

[75] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[76] ደጃዝማች ካሳ በአያታቸው በራስ ወልደ ሥላሴ በኩል ከጎንደር ነገሰታት ይወለዳሉ

[77] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[78] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

ሲ.ቢ፣ የናይል ወንዝ አሳሽና አዋቂ የሆነ ትልቅ ሰው ከብዙ አጅ መንሻ ጋር ወደ የኢትዮጵያው ርዕሰ መኳንንት ተላከ። ሜጀር ግራንት፣ አንደ አንግሊዙ አዛዥ ዋና መልከተኛነቱ መልካም አቀባበል ተደረገለት፤ በአከብሮት ተስተናግዶ በመጨረሻም በአንግሊዝና በትግራዩ አዛዦች መህከል ግንኙነት አንዲደረግ ተወሰነ።

አቶ ምርጫ፣ የትግራይ አምባላደር ሆኖ ወደ ናፒየር ተላከ። አምባሳደሩንም፣ ኮስተር ያሉት ናፒየርና ረዳቶቹ ለዝግጅቱ ተገቢ በሆነ ሥነ ሥርአት በተመላበት ሁኔታ ነው የተቀበሉት። የተወሳሰቡ የወታደራዊ ሥርአቶች፣ የሻምላ ውድድር፣ ረዥም ምንጣፍ፣ ትራምፔት አየተነፋ ታምቡርም እየተመታለት ነበር። ሥነ ሥርአት ያለው የትግሬው አምባሳደር ወደ አለቃው ተመለሰ፤ ነገር ግን ባየው ነገር በጣም ተገርሞና ተደንቆ፣ መቼም በሀሳቡ በርግጥኝነት አስከ ዛሬ ካያቸው ሰዎች አነዚህ ፈረንጆች በጣም የሚገርሙ ናቸው ማለቱ አይቀርም፤ ያ ደግሞ አውነታ አለው። ነገር ግን ይህን የወዳጅነት አዝማማሚያ ለሚጠራጠሩ ሰዎች፣ ካላን አንደ ሮማዊው ፋቢየስ ከንክታቶር[79] አድርገው ነው ያዩት። መልከተኞች እንደገና ልከ ውጤቱን በርቀት ይከታተላል። መልከተኞቹ ያገኙትን ልባዊና መልካም አቀባበል ከንክታቶሩ ካላ ከተመለከተ በኃላ፣ በመጨረሻ ሁለቱ "የቤት ወዳጆች" የሚገናኙበት ቀንና ቦታ ተወሰነ።

ሁለቱ ከሚገናኙበት ቀን ማምሻውን ቀደም ብሎ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር የሁለተኛውን ብርጌድ ጦር በመያዝ አድ አባጋ የተባለውን ጣቢያ ይይዛል። የትግሬው አዛዥ ደግሞ ሀውዜን የተባለው ቦታ ካምፕ አንደሚያደርግ ነበር የተጠበቀው፤ ነገር ግን አላደረገም፤ ተዋጊው ሰር ሮበርት ናፒየርም የግድ አድ አባጋ ላይ መዘግየት ነበረበት። አራሱን "የኢትየጵያ ርአሰ መኳንንት" ብሎ የሚጠራው ያልሠለጠነ አለቃ አሰኪመጣ ድረስ መጠበቅ ነበረበት። ለሰምንት ቀናትም ጠበቀ፤ ተሰፋ ቆርጦ ትዕግስቱ ባለቀበት ሰአት ሌላ መልከተኛ ደረሰና የሀውዜኑ ንጉሥ መምጣቱን አበሰረ።

በሚቀጥለው ቀን ሰር ሮበርት ናፒየር ከሚመቸው የአድ አባጋ ሸለቆ ካምፑ፣ 500 አማረኛ፣ 300 ፈረሰኛ፣ የተወሰኑ የሮያል ኢንጂኔርስ ሰዎች አና አራት 12-ፓውንደር የሚባሉ መድፎች አሰልፎ ወጣ። በጣም የተደራጀ አነሰተኛ ጦር፣ ነገር ግን በማሸፍም አይነት የትግሬው መሰፍን ከጠበቀው የአንግሊዝ ጦር መጠን ያነሰ ወይም የተለየ ነበር።

[79] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)



የደጃዝማች ካሳ መልከተኖና ተከታዮች
(Record of the Expedition to Abyssinia)

የሰናይደር[80] ጠመንጃዎችን ትከሻቸው ላይ አደርገው፣ ለአንድ ቀ
የሚሆን ስንቅ በኮረጆቻቸው ይዘው፣ የጦሩ ባንድ ከፊትለፊት ሙዚ
እያሰማ፣ ይህ አነስተኛ ጦር መንገዱን ቀጠለ። የሚያብረቀርቀው ጠመንጃቸው
ከለበሱት ቀይ ዩኒፎርምና ካደረጉት የፀሀይ ባርኔጣ ጋር የሚንፀባረቅና ሊ
የሚያፈዝ ነው። ብርጌዱ ጉዞ እንዲጀምር የትራምፔት ጥሪው ሲነፋ፣ ከብረት
የተሠሩት አፎቶችና የፈረስ መከልከያዎች የመንኳኳት ድምፅ ያሰሙ ነበር።

ከነሱ ቀጥሎ ጥቂት መድፈኞች ተከተሉ፤ መጠናቸው አነሰ ያለ ለለነበር
መድፎቹ ከበቅሎዎች ጀርባ ተጭነዋል። ከኋላ፣ ኩምቢያቸውን ወደ ጎንና ጎ
እያወናጨፉና እየተጎማለሉ ዝሆኖች ይከተላሉ፤ ከጀርባቸው ላይ ብዙ ሰዎች
የሚይዘው ቤት የመሰለው ኮርቻና ከዝሆኖች ማጅራት ላይ የተቀመጡት
የዝሆን መሪዎች(ነጂዎች) ይታያሉ።

የጦር አዛዡ ፈረሱ ላይ ተቀምጠ፣ ረዳቶቹ ደግሞ ባልሠለጠነው ሠራዊት
አለምሮ ላይ አድናቆትን ለመፍጠር፣ ያላቸውን ጥሩ ልብሰ በመልበስ
ከሠልፈኛው ፊት ለፊት በሰምሰማ ይሄዳሉ።

በጥሩ ሥነ ሥርአትና ሲጀምሩ እንደበረው ቅልብጭ ያለ አሰላለፍ፣
በደንብ የተደራጀው አነስተኛ ሠራዊት፣ ማይ ደብር ከተባለው የአፈሴል
ግንጉነቱ የሚደረግበት ሜዳ ይደርሳል። የሚያስደሰት ቦታ! በሁለቱ ለዎች
መሀከል ለሚደረገው የከብርና የመልካም ምኞት ልውውጥ በጣም አመቺ ቦታ
ነበር። በዘርና በሃይማኖት ያን ያህል ይለያያሉ ወይ! በዚህ ግማሽ ማይል
በማይሞላ ዙሪያ፣ አረንጓዴ የለበሱ ኮረብታዎችና ዳገቶች፣ መሐሉ ላይ ደግሞ
ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት የማይ ደብር ሸለቆ ነው።

ጠመንጃዎች መሬት ላይ ተደርድረው፣ ፈረሰኞቹ ከየፈረሶቻቸው
ወርደው፣ ወታደሮችም ከሚወርደው ንፁህ ውሀ ከጠጡ በኋላ ሜዳው ላይ
ተጋደሙ። በሚገርም ሁኔታ ምንም የሀሳብ ምልከት ሳይታይባቸው
የመስፍኑን መምጣት ይጠባበቃሉ።

ጄኔራሉና ረዳቶቹ በርጋታ ዳገቱን ወጥተው፣ የሚመጣውን አጀብ
ለማየት ከፍ ካለው ቦታ ላይ ቆመዋል።

ራቅ ብሎ፣ ሜዳማ ቦታው፣ የቁልቋል ተክሎች አልፎ አልፎ አንደ
ነጠብጣብ አየታዩበት የወይን ጠጅ ቀለም ባለው መልኩ ተንጣሎ ይታያል።
ተራራማው ደብር ደምቦ በሜፎቹ ጠቆር ያሉ ደመናዎችን በሰቶ ይታያል፤
ከሜዳዎቹ፣ ከጎድጓዳ ስፍራዎችና አነስ ካሉ ኮረብታዎች በላይ የተለያዩ
በድፍረት የቆሙ አምባዎች በተለያየ አቅጣጫ ይታያሉ።

[80] ሰናይድር ጠመንጃ



የእንግሊዞች ካምፕ በለድ አሳጋ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ወደኋላ በኩል፣ አምባ ሹኩላት ፀጉሩን እንደተላጭ ግዙፍ ጀይንት በእናቱ የደመናዎችን ስብስብ በስቶ ይታያል። መስባ ተራራ ከፊት ለፊት ነበር፤ የእርንዲን ተራራ ደግሞ በጎንና በጎኑ የደንሰሎ ግለፊያን ይታከካል፣ ከፊት ለፊታችን ቀጥታ እንደ ጦር ቅርፅ ያለው ሌላ ከፍታ ስር ነጭ የኤተር ጋዝ የሚበንበት ይመስላል። አይደለም፤ ኤተር አልነበረም፤ አፄ ቴዎድሮስ ነበር። የሚነፍስ ነፋስ አፄ ቴዎድሮስን ሲያስለቅቀውና የእንግሊዝ ቃፊር ፊረሰኛች ሲመለከቱ፣ ከማይ ደብር አጠገብ በሰሜያት ላይ እንዳሉ ኮከቦች ከምችት ብሎ የሚታየው የልዐል ካሳ ሠራዊት ነው።

"ባለህበት! ሻንጣ በጀርባ፣ ጠመንጃችሁን ያዙ፣ ተሰለፍ! ወታደር በሰነ ሥርአት! በማቻል ሁኔታ በደንብ ሁኑ!" በቅፅበት፣ ትዛዙ ተፈፀመ። በደንብ የታጠቁ፣ ደመቅ ያለ ብርቱካንማ ልብስ የለበሱ እግረኛ ወታደሮች በመስመር ተሰለፉ፤ በቀኛቸው በኩል ፈረሰኛው፣ በግራ በኩል መድፎቹና ተኳሾች በተጠንቀቅ ቆሙ። ሰልፉም በሚያምር ሁኔታ በእንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ አጠገብ ነበር።

የእንግሊዞቹ አባሻገም በፍጥነት ወደድንኳኑ በመሄድ አለባበሱን አሰተካከለ። ረዳቶቹ ድንኳኑን ሁሪያውን ከከበቡ በኋላ ምሰጥራዊ ውይይት ተካሄደ። ከዚህ በኋላ ሶስት መኮንኖች፣ ሰማያዊና ብርማ ቀለም ያለው ዩኒፎርም በለበሰ በሶስተኛው ቀላል ፈረሰኞች ታጅበው ወደ መስፍኑ አቅጣጫ ሄደው የእንግሊዙ ጀኔራል ከሱ ጋር አኩል እንቅስቃሴ እንደሚጀመር ነገሩ።

ታምቡሮችና አጠር ያሉ ትዛዞች በተቃራኒ ባለው ከፍታ ቦታ ይሰሙ ጀመር። የአቢሲኒያውያን ጦር መንቀሳቀስ ሲጀምር፣ ሰልፉ ረዘም ያለ የፈረሰኛና የእግረኛ ጦር ይህ ነው የቀረበው። ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ እጃቸው ረዘም ያለ ጠንከር ያሉ ሰዎች ፊት ለፊት እየጋለቡ ይመራሉ። ደማቅ ቀለም ያለው ድንኳን ከተተከለ በኋላ አንድ ሰው ወደ ድንኳኑ ሲገባ ታየ፣ ምናልባትም መስፍኑ ይሆናል።

ከአስር ደቂቃ ጉጉትና ትግስት የተመላበት ጥበቃ በኋላ፣ መስፍኑ፣ ደመቅ ብሎ ያጌጠ ፊረስ ላይ ወጣ፤ አንድ የእንግሊዝ መኮንንም በፍጥነት እየጋለበ ለጀኔራሉ የመስፍኑን መምጣት ተናገረ።

ጀኔራሉ ከድንኳኑ ሲወጣ፣ የአመት በአል ሪባኖች አልባሳት የተደረገበት ትልቅ ዝሆን በበሩ በኩል ቆሞ ነበር። ጀኔራሉም ዝሆኑ ላይ ተሣፈረ። በዚህ ዝሆንና ሌላም በሚከተል፣ በረዳቶቹም ተከቦና በፊረሰኞች ታጅቦ፣ ጀኔራል ናፒየር ወደ ወራጅ ውሃው አመራ።



የደጃች ካሳና የሮበርት ናፒየር ግንኙነት

(ዋቢ, *መፅሐፍ ተ.ቁ. 16*)

መስፍኑ በቁልቁለቱ ሲወርድ፣ እንደ ክንፍ፣ በግራና በቀኝ በ500 የተመረጡ ተዋጊዎች ታጅቦ ነበር። መልከኛ የሆነ ሰው የማዕረግ ጃንጥላ (ድባብ) በመስፍኑ ራስ ላይ ከትሮ ይዟል። ጃንጥላው ወይንጠጅ ቀለም ያለው ሲሆን፣ በምርጥ ከፋይ የተሠራና ኩበር በተሠሩ ጌጦች የተንቆጠቆጠ ነበር። በቀኙ በኩል፣ ጋሻና ጦሩን የያዘ ረዳት አለ። በግራ በኩል የትግራይ ታላቅ ሰው ልጅ የሆነ ጠመንጃ ያዥ አለ። የጦር አለቆቹ፣ መስፍኑን ቀድመው በእግራቸው ይራመዳሉ፤ ከነሱ ፊት ለፊት መስፍኑን ለመገናኘት የሄዱት ሁለት የእንግሊዝ መኮንኖች ይመራሉ።

በዚች በትንሽ ወራጅ ውሃ ዳርቻ፣ ናፒየር ከተባባሪው መስፍን ጋር ተገናኘ። ሁለቱም ከተሳፈሩበት ከወረዱ በኋላ፣ ወዳጅነት በሚያሳይ ሁኔታ ተቃቀፉ። ይህም የአሜሪካ ኢንዲያኖች የሰላም ኮሚሽነሮችን እንደሚያቅፉት አይነት ነበር። በዚህ አዲስ የጓደኝነት ትዕይንት፣ መስፍኑ ቁንጥንጥ ነበር፤ ናፒየር ግን ከሚገባው በላይ ረጋ በማለቱ ሞገስ ያለው ሁኔታም አላሳየም።

ሁለቱ፣ ማለትም ናፒየርና መስፍኑ ወደ ከብር እንግዳ መቀበያው ድንኳን ገቡ። ካሳን ተከትለው የመጡ አምስት አለቆች፣ ጋሻ ያዡና ማዕረጋቸው የሚፈቅድላቸው ሰዎች ደርዘን ከሚቆጠሩ የናፒየር ረዳቶች ጋራ ወደ ድንኳኑ ገቡ። በዚህ ጊዜም የክብር መድፍ ተተኮሰ፤ ይህ ሁኔታ ግን ኪጋራው ማዶ ባሉ ሰዎችና ፈረሶች ግርግርና ድምፅ ፈጠረ። በነዚህ ጠየም ያሉ ጦራቸውን ቀና አድርገው የያዙና ቀይ ዩኒፎርም የለበሱ የእንግሊዝ ወታደሮችን ቁልቁል የሚመለከቱ ሰዎች ላይ ያለመረጋጋት ምልክት ይታይ ነበር።

ከዚህ ቀደም የተጠቀሰው አምባሳደር አቶ ምርጫ፣ ሁሉም ከተቀመጡ በኋላ፣ በሁለቱ ባለሥልጣናች፣ በእንግሊዙ ጄኔራልና በልዑል ካሳ መሀከል የሚገባው ፎርማሊቲ ልውውጥ እንዲጀመር በማድረግ የነበረውን ፀጥታ ቀየረው።

በግዛቱ በኩል፣ ወደ ደቡብ አልፈንበት የምንሄድበት የትግራዩ መስፍን፣ የለበሰው የሀር ቀሚስ ሆኖ እንደ የሲፍ ልብስ በአበባ ምስሎች የተዠንረረ ነበር። እናቱም ላይ ከአንበሳ ጋማ የተሰራ ጎፈር አድርጓል፣ ከጎፈሩም ሶስት ጉንጉኖች በጀርባው በኩል ወርደው ይታያሉ። ጭንቅላቱ ደግሞ አግዚአብሔር ለአቢሲኒያኖች በርከት አድርጎ በሠጣቸው ፀጉር ተሸፍኗል። ፀጉሩ ቅባት በደንብ የጠጣ ሲሆን እንደ ሹሩባ ተጎንጉኖ በአንገቱ ላይ ወርዷል። በመስፍኑ አናት ላይ ደግሞ፤ ምንም ጠቅር ያለ ቢሆንም ከመጠን በላይ መልከኛ የሆነ ሰው ጃንጥላ ይዟል።

ካሳ ረጋ ያለና የወዳጅነት ገፅታ አለው፤ ሆኖም በሚያሳየው ቁርጠኛ ያልሆነ ባህሪ ምናልባትም "ያልተዘጋጀ ነው" ሊባል ይችላል።



ደጃዝማች ካሳ ምርጫ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ካሳ፣ "የፈረንጁን ንጉሥ በኔ ስም ሰላምታ አቅርብልኝ።" በማለት መልዕክተኛውን ምርጫን ጠየቀው፤ ምርጫም በጥያቄው መሠረት የጊታውን ቃል ትንሽ በማሳመር ለናፒየር ተናገረ።

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ቡተራው ሲመልስ፣ ካሳን በማየቱ ደስተኛ መሆኑን ገለፆ፣ የእንግሊዝ ክርስቲያን መንግሥት እንደራሱ የክርስትና ሀይማኖት እምነት የሚከተሉ ሰዎችን በአቢሲኒያ በማየቱ በጣም ደስተኛ መሆኑንም ገለፀ።

ካሳ ሲመልስም፣ በሀገሩ ፀጉረ ልውጥ ሰዎች ማየቱን እንደማይወድ፣ ነገር ግን እንግዳ መምጣት ካለበት ደግሞ ክርስቲያኖች ቢሆኑ እንደሚመርጥ ነገረ።

ይህ አባባል በርግጥ በእንግሊዞች በኩል የወዳጅነት ስሜት እንዲፈጠር አላደረገም። ምንም እንኳን በሚጀር ግራንት በኩል ዲፕሎማሲ ሥራ

በሲራም፣ የነዚህ ክሩሴደሮች[81] አላማ ላይ ብዙ ጥርጣሬ አለ። "ነገር ግን፣" አለ ሰር ሮበርት፣ "እዚህ ሀገር ብንመጣ፣ ምክንያቱ፣ መጥፎ ሰዎች ያገራችን ዜጎች እንደምርኮ በመያዛቸው ነው። ሰዎችን፣ ሁሉንም ካሰፈታን በኋላ፣ ግዛታችሁን ሳንረብሽ ወደ ሀገራችን ተመልሰን እንሄዳለን።"

"እሱስ ትክክል ነው።" ብሎ ካሳ መለሰ። "ቴዎድሮስ ክፉ ሰው ነው፣ የሚገባውን ቅጣት እንደምትሠጡት ተስፋዬ ነው።"[82]

ከዛም ጀኔራሉ፣ ካሳን ተክትለው የገቡትን ሰዎች ስም በትህትና ጠየቀ፣ አንደኛው ታላቅ ወንድም፣ ሁለቱ ደግሞ የካሳ አጎቶች መሆናቸውን አረጋገጠ። ሁሉም አለቆች ከወርቅ የተሠራ ሙሉ ከንዳቸውን የሚሸፍን አምባር የመሠለ ነገር አድርገው የአንበሳ ለምድ ደርበዋል።

ለካሳ የመጡት ስጦታዎች ቀርበው መታየት ሲጀምሩ፣ መደበቅ የማይቻል አድናቆት በሁሉም ዘንድ ይታይ ነበር። ስጦታዎችም፣ በሎንደን ፕርዲ የተሠራ አንድ ባለድርብ አፈሙዝ ነፍጥ፣ ከጠርሙስ የተሠሩ የበሄሚያ ምንቸቶች፣ ከራሱ ሰር ሮበርት ጋጣ ደግሞ አንድ የአረብ ፈረስ ነበሩበት። ሁሉንም ስጦታዎች፣ ካሳ በተትረፈረፈ ምስጋና ተረከበ።

ከዚህ በኋላ ስብሰባው ተዘጋ፤ ሁሉም አለቆችና የእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ድንኳኑን ትተው ወጡ። ድንኳን ውስጥ የቀሩት ግን፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የጦሩ ፀሐፊና አንድ ረዳት ጀኔራል ባንድ በኩል፣ ልዑል ካሳና ቤተሰቦቹ፣ ከምርጫ ጋር በሌላ ወገን ነበሩ።

ቀጥሎ የሆነውን በዝርዝር መግለፅ አይቻልም። ነገር ግን የዚህ ሚስጥራዊ ስበሰባ ውጤት የነበረው፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በግዛቱ አልፈው እንዲሄዱ ካሳ ፊቃድ መስጠት፤ ከዛ በተጨማሪ ደግሞ በተቻለው አቅም በቀለብ እንደሚረዳ ነው። በርግጥ ቀለቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በእንግሊዙ የጦር ኮሚሳሪያት የሚገዛ ነው። በመጨመር ደግሞ፣ ቴዎድሮስ ከተሸነፉ በኋላ፣ ለራሱ እርዳታ ስለሚያስፈልገው፣ ቢሰጠው ምኞቱ መሆኑን ገለፀ። ለዚህ፣ ሰር ሮበርት ቃል የገባው ሁሉንም ነገር ሲሆን፤ ነገር ግን፣ የመስፍኑ ተባባሪ ለመሆንና፣ መስፍኑን ሥልጣን ላይ የማውጣት ጉዳይ ላይ ግን የኢንግላንድን ንግሥት ትዛዝ የሚከተል መሆኑን፣ ማለትም ሰዎቹን ካስፈታ በኋላ ሀገሩን እንዳገኘው መልሶ እንደሚተውና የካሳን ምኞት ለሚሟላት ቃል እንደማይገባ ገለፀ።

---

[81] ግብፃዊው የምፅዋው ገዥም ቢሆን፣ እንግሊዞቹ አገራቱን የመውረር ሀሳብ አላቸው ብሎ መልክት ልኮ ሰለነበር ለጥርጣሬው በቂ ምክንያቶች ነበሩት።

[82] (በምዕራፍ አምስት ማብራሻዎች)



ሌፍተናንት ጀኔራል ሮበርት ናፒየር
የአቢሲኒያው ጦር ጠቅላይ አዛዥ by John Watkins (1860s)

በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ካሳም የግድ ሀሳቡን መቀበል ነበረበት። የእንግሊዞችን እርዳታ እሱ ማግኘት ካልቻለ፣ ሌላ ራስ ወይም ሥልጣን ፈላጊ ስለማያገኝ በዘዴ ረከቷል።

ሠልካም ምኞትና የወዳጅነት መግባባት በሁለቱም ወገን አለቆች በኩል ከተፈጠረ በኋላ፣ ወይንና ሌሎች መጠጦችም ማሳለፍ ተጀምሮ ሁለቱም ወገኖች አርስ በርስ በመጨዋወት እንደ ሳከሶኖች "ዋስ ሄል[83]" የተባለ የባህል አጠባበቅ በኋላ ስብሰባው ተዘጋ።

ወታደሮችም ለልዑሉና ለወታደሮቹ ታይታ ሰልፍ ማሳየት ጀመሩ። የብሪታንያ ወታደሮች በሰልፍ በመዓዝ ወደፊትና ወደኋላ ይመላለሳሉ፣ ወደ ግራም ወደቀኝም ይንቀሳቀሳሉ፣ ኮምፓኒ በረድፍ በታምቡርና በዋሽንት (ጣሊጥ)ና በሌላም ወታደራዊ ሙዚቃዎች በመመራት፣ ይህንን ትዕይንት አዘጋጅ የሚመለከተው እንግዳ በተመስጦ እሲያደንቅ ድረስ ትርኢት ያሳዩ ነበር።

---

[83] 'Waes Hael'

ናፒየርም በተራው ከመሰፍኑ ጋር በመሆን ወንዙን ተሻግሮ የአቢሲኒያ ወታደሮችን ለማየት ሄደ።

ወታደሮቹ ደህና ሰውነት ያላቸው ሆኖ፣ በደንብ የተዘጋጁና የእትሌቲክ እቋም ያላቸው ናቸው፤ በርግጥ መደበኛ ላልሆነ ጦርነት ሁነኛ የሆኑ ናቸው። ከእምስት መቶ እለከ ሰድስት መቶ የሆኑት የተለያዩ ነፍጦች ይዘዋል፤ ጥንድ አፈሙዝ ያለው ነፍጥ፣ የሚለኮስ ነፍጥ[84]፣ የፖርቱጋል ፉሲሎችና የተለያዩ ሀገራት ነፍጦች ይዘዋል። ሌሎች እግረኞች ደግሞ እንደ እቅማቸው መጠን፣ ጦር፣ ጋሻና ጎራዴ ይዘዋል። በተራራማ ሀገር ወይም ቦታ፣ እነዚህ ሰዎች ከሌላ የሠለጠነ ወታደር ጋር አደገኛ ፍልሚያ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ ጥሩ እሰላለፍ ቢኖራቸውም፣ ከእፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች ፊት መቆም አይችሉም፤ አድርገውትም አያውቁም ነበር።

ወታደሮቹን ካስነበቦ በኋላ፣ መሰፍኑ፣ የእንግሊዙን ጀኔራል ወደ ሚያምረው ድንኳኑ እንዲገባ ጋበዘ። በድንኳኑም ውስጥ፣ ሁሉም ለው መሬቱ ላይ በተነጠፈ ሲጋጃ ላይ ተቀምጧል። ዳቦ፣ ጠጅ፣ እረቄና እህል ቀረበ፤ ሁሉም ተጋበዙ። ከመሄዱ በፊት፣ ካሳ፣ ጀኔራል ናፒየርን ታላቅ ጀኔራልና ታላቅ ሰው ነው በማለት ተናገረ። ከዚያም የራሱን ለምድ እውርዶ፣ የጫካውን ንጉሥ፣ የእንበሳውን ቆዳ የጀኔራሉ ትከሻ ላይ እስቀመጠ። የራሱን ጋሻና ጦርም ለጦታ አቀረበለት። ጋሻው፣ በጎንደር ጥበበኛ የተሰራ ድንቅ ሥራ ነው። የጋሻው ወጣ ያለው መሀል ከፍሉ በወርቅ የተለበደ ነበር፤ የጋሻው ጠርዝ ደግሞ ቁጭ ቁጭ ባሉ ብዛት ባላቸው በወርቅና በብር በተሠሩ ጌጦች ተንቆጥቁጧል። ከመሀሉ ላይ የእንበሳ ጋማ ተንጠልጥሎበታል።

ስለ እንግሊዝ ወታደሮች፣ የአቢሲኒያ ወታደር የሚያስበው፣ ግልጥ ሜዳ ላይ ከሆነ የእንግሊዝ ወታደሮችን ማጥቃት አይቻልም፤ ተራራማ ቦታ ላይ ከሆነ ግን ምንም ማድረግ አይችሉም ነው። በካምፓቸው ውስጥ ሲወራ እንደለሙት ላይሆን መድፎቹ አነስ ያሉ ናቸው። ከዚህ ሌላ ደግሞ የሰሙት፣ የእንግሊዝ ጦር፣ እያቋጨ የሚወረወር እሳት የሚተፋ መሳሪያ እንዳላቸውና፣ የሚወረወረው እሳት ደግሞ ሁለት ሶሰት ማይል ርቀት ተወንጭፎ ቤት የሚያቃጥል መሆኑን ነው። እነዚህ መሳሪያዎች(ሮኬቶቹ) እንግሊዞች የሚተማመኑባቸው የመጨረሻ መሳሪያዎች ናቸው። እንግሊዞች የዚህ አይነቱን መሳሪያ በብዙ ቦታዎች ተጠቅመውበታል። እንደ ንጉሡ ትልቅ መድፎች ባይኖራቸውም፣ በውጊያ ማሸነፍ ላይችሉ ሊቀሩ ወደነዚህ መሳሪያዎች ያዞራሉ፤ መሳሪያዎቹንም ማከሸፍ ወይም መከላከል ሰለማይቻል

[84] Matchlocks ተጨማሪ ማስታዎች ምዕራፍን ይመልከቱ

ከብር መሠጠት የሚገባቸው ናቸው። ስር ሮበርት ናፒየር እነዚህን የሚጠሉ የእርምስትሮንግ ሮኬቶች እውነተኛ ሀይል ለማላየት ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ እሩሮች ብቻ ተኮሰ፤ ከዚህም ዘላቂ ጠቀሜታ ሊገኝ ይችላል። ነገር ግን ስለ ቴሥያሮስ ሀይል፣ ወይም መቅደላ ላይ ምን አይነት ምሽግ እንዳላቸው በጣም ትንሽ ዕውቀት ነው ያለው፤ ስለዚህ የእነዚህ የጦር መላሪያ ተተኳሾችን ሰነዮታ ሊል አለማባከኑን መርጧል።

መሪዎቹ ከመለያየታቸው በፊት ተቃቀፉ፤ እንደኛው የሚችለውን ያህል ሌላውን ለመርዳት ቃል ገቡ።



ደጃች ካሳ የሮኬቶች ተኩስ ልምምድ ሲመለከቱ
(ዋቢ. መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

የምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች

ቁጥር 73፤ *ይህ አዋጅ እንደተነገረ፣ ካሳ ምርጫና ዋሽም ነበዙ ለኮሎኔል መርዌዘር ደብዳቤ ልከዋል። ለእንግሊዞቹ፣ ይህ አዋጅ ከታሰበው በላይ በጣም ጥሩ ውጤት ነበር ያስገኘላቸው። ምናልባትም፣ ደጃማች ካሳም ሆነ ዋሽም ነበዙ የእንግሊዞቹን እመጣጥ በቅኝ ገዥነት ቢያዩት ይዋጉ ነበር ወይ? በርግጥ፣ ደጃዝማች ካሳ ጥቃት ያደርሳሉ ተብሎ ተፈርቶ ነበር። ደራሲውም ቢሆን ይህንን ይገልጣል። የምፅዋ ገዥ የነበረው ግብፃዊ ሁሴን ቤይ የምፅዋውን ናይብ መህመድን ደብዳቤ አሲይዞ ወደ አድዋ ልኮት ነበር። ይህ የሆነውም የእንግሊዙ ሜጀር ግራንት ከደጃች ካሳ ጋራ በተገናኙበት ወቅት ነበር። የምፅዋው ገዥ የሀገሩን ተወላጆች(አቢሲኒያኖቹን) እንግሊዞቹን እንዳይረዱ እንዲያውም እንዲዘርፉ፣ ደጃች ካሳን ቢሆን ዘመቻውን እንዲቃወሙ መክሯል ተብሎ፣ የግብፁ አድሚራል ምፅዋ ለጉቦኝት ሲመጣ፣ ሰውየውን ከሥልጣን አስነስቶታል። እንግሊዛዊው ፀሀፊ፣ ሔንሪ ሆዚየር፣ ከሥልጣን መነሳቱ ይገባዋል ይላል።*

ቁጥር 74፤ *ቴዎድሮስ፣ በታህሳስ 2 እንግሊዞች ዙላ ማረፋቸውን ሰምተዋል። በ20 ደግሞ በአማርኛ የተፃፈው ይህ የናፒየር አዋጅ በትግራይ በኩል ደርሷቸዋል። የተፈራው፣ ቴዎድሮስ ተናደው የአውሮፓ ባለሟሎቻቸውን በሙሉ ያስራሉ ተብሎ ነበር። ነግር ግን፣ ቴዎድሮስ ፈጣን ብለው ደብዳቤውን ለማንም፣ ለፀሐፊያቸው ለአለቃ እንግዳ እንኳን ሳያሳዩ እስቀምጠውታል። እኔ በሠጠኋቸው የቆርቆሮ ሣጥን ውስጥ ነው ያስቀመጡት ይላል ራሳም። የሚገርመው ይህን የናፒየር አዋጅ ለራሳም የላኩለት ዋሽም ነበዙ ነበሩ።*

ቁጥር 75፤ *ደጃች ካሳ (በኋላ አፄ ዮሐንስ) ሙሉ ስማቸው ካሳ ምርጫ (በዝብዝ ካሳ) ሲሆን፣ እንግሊዞቹ የልዑልነት (መሰፍን) ደረጃ አላቸው በሚል ልዑል የሚለውን ማዕረግ ስለሠጡ፣ ፀሐፊው፣ ልዑል ካሳይ አያለም ይጠራቸዋል።*

ቁጥር 76፤ *ይህ ደብዳቤ የንጉሣዊ ማህተም አንዳለበት ተገልጧል። መርዌዘር፣ ማህተሙን ያላየ በመምሰል ሳይጠቅስ መልሰ እንደላከ ተዘግቧል። (Record of the Expedition to Abyssinia) ይህ፣ ገና ሳይነግሱ፣ ራሳቸውን ንጉሥ አያሉ በመጥራት ማህተም ማሰራት በደጃች ካሳ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም፣ ምኒልክን ጨምሮ የሚታይ ነገር ነበር። ለዚህ ደብዳቤ ምላሽ የተሠጠው ከኮሎኔል መርዌዘር ነበር። የደብዳቤው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነበር። በታህሣስ 5 ነበር የተፃፈው።*

እንደምናሉ፤ ደህና ነዎት ወይ?

የኛት ደብዳቤ ደርሶናል፤ ከፍተኛ ደስታ ነው የሠጠን። ከዚህ ቀደም ሁለት ደብዳቤዎች ልከንልዎት ነበር፤ ነገር ግን ከርስዎ ባለመድረሳቸው በጣም እናዝናለን።

እነዚያን ሁለት ደብዳቤዎች ስንልከ፣ በመሀከላችን፣ ከራስ ሚካኤል፣ ወልደስላሴ እና ሰባጋዲስ ጀምሮ በነበረው ወዳጅነት ዕውቀት በመተማመን ነው። አሁን ወደ ሰናፌ እየተጓዝን ነው፤ ጄኔራል ሮበርት ናፒየር እስከሚመጣ በዚሁ ቦታ እንቆያለን። አሰከዚያ ድረስ ግን በመሀከላችን ያለውን ትልቅ ወዳጅነት መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የምንልከልዎትን እዋጅ በርስዎ ግዛት እንዲያለነግሩ እንለምንዎታለን።

ሌላው በጣም ትልቅ ነገር፣ የሚያስፈልጉን ነገሮች፣ ለንዴ፣ ገብስ፣ እህልና ሌሎችንም አለፈላጊ ነገሮች፣ እንዲሁም ብዛት ያላቸው በቅሎዎች ጨምሮ ነው። ለነዚህ ሁሉ ተመጣጣኝ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች ነን።

የምንጠይቅዎት ነገር፤ በመልካምነት እስዎ ይህንን ጉዳይ ለአለቆችና ለገበሬዎች እንዲታውቅ እንዲያደርጉና ሰዎችም የተባሉትን ነገሮች ለኛ እንዲያቀርቡ ነው።

ልጅ ምርጫ ከኛ ጋር ቢሆን ደስታችን ነው። በመሀከላችን ላለው ግንኙነት ጠቃሚ ለለሚሆን ፈቃድ እንዲሠጡት እንጠይቃለን።

ቁጥር 77፣ ምርጫ ወርቄ በሀንድ እገር በቦምቤይ የተማረ ሰው ነበር። ሄንሪ ዱፍተን፣ ምርጫን ከለረንሰ ጋር ምፅዋ በእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት እንዳገኛቸው ገልጦ፣ ቆንስላው ካሜሮን፣ ወደ ሱዳን ለሰራ በጄደቡት ጊዜ ሁለቱም ተወካይ ሆነው ይሰሩ ነበር ብሏል። የደጀዝማች ካሳ መልከተኛ ሆኖ ወደ እንግሊዞች ካምፕ የሄደው ይህ ራሱ ምርጫ ነው። የሰውየው ቦምቤይ መማርም በእንግሊዞቹ የዘመቻ ዘገባቸው ተገልጧል። ራሳምም፣ ይህንን በማረጋገጥ፣ ምርጫ ወርቄ ቦምቤይ እንደተማረና በምፅዋም በእንግሊዝ ቆንስላ ተቀጥሮ ይሠራ እንደነበር ይገልፃል። ራሳም፣ ምፅዋ ሲደርስ ምርጫ ወርቄን አብሮት እንዲሠራ ልኮበት ነበር፤ ሆኖም ምርጫ ቴዎድሮስን ፍራቻ ፈቃደኛ አልነበረም።

ቁጥር 79፣ ፋቢየሰ ከንክታቶር በ1880 ከከርሰቶስ ልደት በፊት የነበረ የታወቀ የሮማ ፖለቲከኛና የጦር ጄኔራል ነበር። ጀኔራሉ የሽምቅ (ጎሬላ) ውጊያ መሰራች እንደሆነ ነው የሚነገረው። እንግሊዞቹ፣ ደጃች ካሳን የፈሩበት ምከንያት፣ ገና ጦራቸው ሰናፌ እያለ ቡተሊያዊ መልከተኞች በኩል፣ ካሳ 8ሺ ጦር ይዞ የእንግሊዞች ጦር ወደሀገሩ እንዳይገባ ይከላከላል የሚል ዜና ደርሷቸው ስለነበረ ነው። (Record of The Expedition to Abyssinia)። የእንግሊዙ መልከተኛ ሜጀር ግራንትም ደጃዝማች ካሳ ላይ ጥሩ አመለካከት እልነበረውም። ካሳ ምርጫ በዚያን ጊዜ የሀያ ስድስት እመት ዕድሜ ያላቸው ወጣት ነበሩና ቁርጠኛ ሀሳብ አያሳዩም በማለት ነበር። እንደ መርካም ገለፃ፣ ከእንግሊዞቹ ጋር ወዳጅነት መፍጠሩ ጠቀሚታ አለው ብለው የወሰኑት የካሳ አማካሪዎች ናቸው። አንድ ግልፅ የተደረገ ነገር ቢኖር፣ እስፈሪውን ቴዎድሮስ እንግሊዞቹ ራሳቸው ወይም ብቻቸውን እንደሚወጉ ነው። በካሳ በኩል ግን ቀለብና ከብት በማሸ እንደሚቀርብ። ከዚያም እንግሊዞቹ ሲመለሱ መሳሪያዎች እንዲሠጡት ነበር።

ቁጥር 82፣ ደጃች ካሳ ምርጫ፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የቴዎድሮስ ባለሟል ነበሩ። ቴዎድሮስ ለምን ለወንደሞቻቸው ከፍ ያለ ማዕረግ ሲሰጡ፣ ለካሳ የባለምባራስነት ማዕረግ ብቻ እንደሠጡ ግልፅ የሆነ ነገር የለም። ይህ ነገር ግን ካሳን ብቻ ሳይሆን ወንደሞቻቸውንና ዘመዶቻቸውን አስከፍቷል። በተለይም በዕድሜ ከሳቸው የሚያንሰውን ምኒልክን የደጃዝማችነት ማዕረግ በመሰጠታቸው፣ ካሳ በመሸፈት ወቅቱ ሲዘሩ ኖረዋል። የቴዎድሮስ ሌላው ባለንጣ፣ ዋግሹም ጎበዜ በኋላም አፄ ተክለጊዮርጊስ፣ ካሳን የተንቤን ገዥ አድርገው መሾም ብቻ ሳይሆን ቢጋብቻም ግንኙነታቸው እንዲጠናከር አድርገው ነበር። ሆኖም ካሳ በመሸፈት ጠቅላላ ትግራይን በመቆጣጠር ሀይላቸውን አያጠናከሩ መቆየት ብቻ ሳይሆን፣ ጳጳስ ወደ ተክለጊዮርጊስ እንዳይገባም መንገድ ዘግተው፣ ለራሳቸው ግን አስመጥተው ለንግሥናው ይዘጋጁ ነበር። እንደ ዘገባዎች ከሆነ፣ ደጃች ካሳ(አፄ ዮሐንስ አራተኛ) በዘር ሀረጋቸው የኢጋሲ ዘር ሰላለባቸው ዙፋኑን ይመኙ ነበር። አሳቸውም እንደአፄ ቴዎድሮስ "የአባቶቼን አገር" የሚሉ ቃላት ሲጠቀሙ ይታያል። ጀኔራል ናፒየርና ደጃዝማች ካሳ የተገናኙበት ወራጅ ውሀ ማይ አዲያብ ይባላል።

ቁጥር 84፣ Matchlocks በላዮቸው ላይ የሚነድ ክር ያለባቸው፣ ጥይቱም የሚተኮሰው ክሩን በመለኮስ ነው። በዚህ ምክንያት ይህ ጠመንጃ ትልቅ ታሪክ አለው። ይኸውም፣ የቴዎድሮስ ሹም የነበሩት የሸዋው ገዥ ደጃዝማች በዘብህ፣ ቴዎድሮስ ላይ ከሸፈቱ በኋላ፣ ቀደም ብሎ ለምኒልክ ቃል ያልገቡ ይመስል የሸዋን መንበር በመመኘት ንጉሥነት ፈልገው ነበር። ሆኖም ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው፣ ሀይላቸውን አጠናክረው፣ በዘብህን በጦርነት አሸንፈው ከሰገሩ በኋላ፣ በዘብህ ንጉሥን(ምኒልክን) ሊገድል ሽጉጥ ይዞ ተገኘ ተብለው የሞት ፍርድ ሲፈረድ፣ በዚህ ጠመንጃ ነበር የተደበደቡት። ባሩድና ጨርቅ የሚጠቀጠቅበት ይህ ጠመንጃ ሚቹ ልብስ ላይ አሳት አስነስቶ እንዳቃጠላቸው ይጠቀሳል። ለዚህ ነው በዘብህ ላይ፣ "እንተም ጨካኝ ነበርከ ጨካኝ እዘዘብህ፤ እንደ ገና ዳቦ አሳት ነደደብህ" ተብሎ የተገጠመው።

ምዕራፍ ስድስት

አንጣሎ - የገበያ አይነት

በአንጣሎ[85]፣ አኔና ሰመልፈንገሰ፣ በሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ ሀላፊው በሌተናል ኮሎኔል ፋይሪ የሚመራውን ቀዳሚ ጦር አገኘን። ከአሁን በኋላ እንደፈለግነው በሀገሩ ውሰጥ መንቀሳቀስ እንችልም፤ የወደፊት ጉዟችን ከጦሩ ጋር ነው የሚሆነው።

ከዙላ አሰከ አንጣሎ የጋጠመኝንና ያየሁትን በዝርዝር ገልጫለሁ። ይህም ከወታደሮቹ ተለይተን ለብቻችን ሰለምንጓዝ ነበር። ከትከሰኛው የዘመቻ አውነታ ጋር ገና አልተዋወቅንም።

ጦሩ አንጣሎ አሰከሚመጣ ድረሰ፣ በሀገሩ ውሰጥ አንደልቤ አየጋሰብኩ፣ ጅብና ተኩላ እያሳደድኩ ራሴን አስደሰቼ ነበር፤ በአካባቢው ያሉ መንደሮችን አየንበኘሁ ቅቤ፣ ዳቦ፣ ወተት፣ ዶሮ አየገዛሁ፣ ወይም አሜሪካ ሳደርግ አንደነበረው ሁሉ ምግብ ያለበት ቦታ አየዞርኩ ነበር።

በአንጣሎ፣ ዕሮብ ገበያ ሰለሚውል የአካባቢው ገበሬዎች የሚሰባሰቡበት ቀን ነው።

አሁን ባለንበት ካምፕ በደረሰን በመጀመሪያው ዕሮብ ቀን፣ ከካፒቴኑ ጋር በመሆን ይሀንን መገናኛ ቦታ ለማየት ወጣን። በዚህ ቀን የአቢሲኒያ ምርጥ ሰዎች ይገኙበታል ይባላል።

ለካምፑ እንዲሆን የተቀየሰው ሰፍራ በሚዳማው ቦታ መሀሉ ላይ ነው፤ ይህም በምዕራብ በኩል ከአንጣሎ አሰከ አፍጎል የተዘረጋ ነው፤ በምሰራቅ በኩል ወደ አሰራ እምሰት ማይሎች ርቀት ላይ ሲሆን፣ በአንጣሎና በጥንታዊና አሰገራሚ በሆነው በጨለቆት ከተማ እኩል ርቀት መሀል ላይ ነው። የጉንዳዋ ወንዝ በበጋ ጊዜ ቢደርቅም በካምፑ ምዕራባዊ ዳርቻ ይወርዳል። ይህ የሚመች አገር፣ ሳሩ ረዥም በመሆኑ፣ በዘመቻው የመጡት ከብቶች በሙሉ በቂ ግጦሽ እግኝተዋል።

ጉንዳዋን አንደተሻገርን፣ ፈረሶቻችን ኮልኩለን በፍጥነት መጋለብ ጀመርንና አንድ ለአት በፈጀ ጊዜ ከተያያዙ ተራሮች ሥር ደረሰን። ተራሮቹ፣

---

[85] አንጣሎ፣ ተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ

ወደ ላይ ከፍ ከፍ አያሉ ይሄዱና፣ አናታቸው ደግሞ፣ ልክ አንደ ዘውድ፣ በእምባ አንጣሎ ኮረብታዎች ይሸፈናሉ። ከነዚህ አንደ ጥላ ከሚከልሉ ግዙፍ ኮረብታዎቹ ሥር ነው የአምባ አንጣሎ ከተማ የተመሠረተው። ከታች ከሜዳው ወደ ላይ፣ ከፍታው ወደ 2ሺ ጫማ ይሆናል።

አንጣሎ ወዳለበት ከፍታ ሰንወጣ፣ ደልዳላው ቦታ ማለቂያ ላይ ያሉ ሁለት ከብና ወደላይ የቆሙ ህንፃዎችን ተመለከትን። አነዚህም በተከርሰቲያናት ሆነው ነው ያገኘናቸው፤ አናታቸው ላይ፣ በሰንን አንቁላሎች የተሠራ የመሰቀል ቅርፅ አለባቸው። እንደገናም፣ ቀጥ ያለ ዳገት ወጥተን ጠባብ መንገድ ውሰጥ ገባን፤ መንገዱ፣ በሰንና በሰኑ ከአሰር አሰከ አሰራ ሁለት ጫማ ከፍታ ባላቸው ከጭቃ በተሰሩ ግድግዳዎች ታጅቧል። በዚህ መንገድ እንድ መቶ አርምጃዎች ከተራመድን በኋላ የገበያ ቦታው ደረስን፤ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሆኖ፣ ዙሪያውን ከአደባባይ አይታ ለመከለል ከጭቃ በተሰራ ግድግዳ የታጠሩ የሰዎች መኖሪያ ቤቶች ተከቧል። አደባባዩ፣ በእድሜያቸው ከትንሹ አሰከ ትልቁ ድረሰ ከየአካባቢው መንደሮች ወደ ገበያው በመጡ ሰዎች ተጨናንቋል። ወንዶቹ፣ ከጥጥ በተሠራ ከፊኑ ላይ ጠቆር ያለ ቀይነት ጥለት ያለው አጀ ጠባብ ለብሰዋል፤ ሴቶቹ ደግሞ በጥጥ የተሠራ፣ ሰውነታቸው ላይ ሰፋ ብሎ የተትረፈረፈ ቀሚስ ለብሰዋል፤ የሁሉም ልብሰ ያደፈ ነው። ልጆቹ፣ ሴቶችም ሆነ ወንዶቹ ራቁታቸውን ናቸው።

ጠጋ ብሎ፣ ከሳር (ሰምበሌጥ) የተሰሩ ዕቃዎች ገበያ አለ። ከጆን ጥላ ጀምሮ፣ ቅርጫቶች፣ ትንንሽ ዕቃ መያዣዎች፣ ኩባያዎች፣ የሕፃን አልጋዎች ይታያሉ። ከዚህ ቀጥሎ የትምባሆ ገበያ ቦታ ነው፤ ትምባሆ ቅጠሉ አንደ ዳቦ እንድ ላይ ተጋግሮ በጣም አሰቃቂ ሽታ ያመነጫል። ቀጥሎ፣ የተለያዩ ዕቃዎች መደብር ነው፤ ካውያ፣ የፀጉር ወይም የሻወል ማስያዣ መርፌ ቁልፍ አይነቶች፣ በሐር የተሰሩ አንገት ላይ የሚታሰሩ ከሮች፣ ማንም ከርሰቲያን ነኝ የሚል ሰው አንገት ላይ የማይጠፉ የብረት መሰቀሎች፣ ከሰም የተሰሩ መቁጠሪያዎች፣ የሰም ቂጣ፣ ዱባ፣ በርበሬ፣ ሽንኩርት፣ ማር፣ ድንች፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ከቆዳ የተሰሩ መደረቢያዎች፣ ከፍየል ቆዳ የተሠሩ ሰልቻዎች እና ሌሎችም ብዙ ቁጥርና አይነት ያላቸው ዕቃዎች ይታያሉ።

አውሮፓዊ የሚገዛው ሁሉም ዕቃ ዋጋው በዶላር ነበር፤ ዕቃው በዋጋ የሁለት ሳንቲሞች ግምት ቢሆንም አንኳን። የአንጨት ቋጠሮ ሊሆን ይችላል ወይም ዳቦ፣ ወተት፣ አንቁላሎች ይሁኑ ብቻ ዋጋው አያንዳንዱ አንድ ዶላር ነው። አቢሲኒያኖች በጣም ብልጥ ሰዎች ናቸው። ከአሰር ሳምንታት በፊት አንጣሎ የመጣ አንድ ሰው ይህን ሁሉ ዕቃ በአንደ ዶላር ብቻ መግዛት ይችል ነበር፤ ሆኖም አንግሊዞቹ የዶላር ሳንቲሞቻቸውን በምንግዴ አይነት ሊጋሰነት በየቦታው ይበትኑ ነበር።



የአንጣሎ ገቢያ
(ዋቢ መዕሐፍ ተ.ቁ. 16)



በአንጣሎ የሚገኝ መንደር

(ዋቢ መፅሐፍ ኮ.ቁ. 16)

ከተማውን ትተን ቤተክርስቲያኖቹን ለመጎብኘት ሄድን። ከውጭ ሊመለከቷቸው በአረንጓዴ ዛፎች ተከበው በጣም ውበት ነበራቸው። እየተጠጋን ስንሄድ ግን፣ በሩቅ ያየነው ውበት አየደበዘዘ ይሄዳል። ከውጭ በኩል በረት ነበር የሚመስለው፤ ውስጥ ስንገባም የተሻለ አልነበረም። ከአጠገቡ በሚገኝ ቤት ውስጥ ቁሱ ይኖርበታል። አውሮፓውያኖች መምጣታችን ሲያይ፣ የቤተክርስቲያኑን ውስጥ ካሳየን በኋላ ወደቤቱ አንድንገባ ለመነን። ገብተን ከተቀመጥን በኋላ፣ በዋንጫ አርጎና የፍየል ወተት አቀረበልን። ከዙላ እስከ አንጣሎ ድረስ ያላየነው ነገር ስለነበረ በአንግዳ ተቀባይነቱ በጣም ተገረምን። ያም ሆነ ይህ፣ የተሠጠንን የሚጥም መጠጥ ጠጣን። ከዚያ ቀጥሎ ፅሁፎችና መፃሕፍት አመጣልንና ሊሸጥልን አንደሚፈልግ ነገረን። ከነበረን ጉጉትና ከሰብሰናቸው ዕቃዎች ለመጨመር ብዙም ስሜት ባይሰጠንም ግማሽ ደርዘን የሚሆኑትን ከጓደኛዬ ጋራ ገዛን። ለመሄድ ስንነሳ፣ ቁሱ፣ ለወተቱ መከፈል አለመፈለጋችን ጠየቀን። ለመክፈል እንኳን አላሰብንም፤ ነገር ግን፣ በመልካም ሁኔታ፣ ብንከፍል የሚቀበለው ነገር መሆኑን ጠቆም ስላደረገን፣ ለመፃሕፍቱ ሁለት ዶላር ብንከፍልም፣ ምንም ሳንቅማማ ለወተቱም ከፈለን።

ወደ ካምፕ ከመመለሳችን በፊት፣ አኔና ካፒቴኑ ጓደኛዬ ለአደን ወደ ተራራዎቹ አመራን። ጥንቸሎች በብዛት አሉ፤ ቆቅና ዥግራዎች በየቦታው ነበር የሚበሩት፤ ሚዳቋዎችም ቢሆን በአካባቢያች ሲፈናጠሩ ነበር። ጓደኛዬ ከርከሮ አይቻለሁ ብሎ ሊያሳምነኝ ሞከሮ ነበር።

ወደ ካምፕ ፊታቸን ከማዞራችን በፊት ቀኑ አየመሸ ነበር። ብዙ ቦታዎችን አካልለናል አና የሚያስደስቱ የተራራ ዕይታዎችና ገላጣ መሬቶችን አይተናል። ቀኑ አየተገባደደ፣ ምሽቱ በችኮላ አየመጣ፣ ፀሀይዋም በግርማ፣ ራቅ ባለና በስፋው መሬት ላይ አየጠለቀች፤ በሜዳማው መሬት ላይ ብጫማ ደብዘዝ ያለ ብርሀን አያበራች፣ ራቅ ያሉ ተራሮች ላይ ደግሞ ወይን ጠጅ የመሰለ ቀለም ስትቀባ፣ በተራሮቹ ሰር ያሉ ገደሎችና መንገዱ ላይ ደግሞ ጥላ አያጠላ ነበር።

ውድ ጓደኛዬ ካፒቴኑ፣ ከዚህ ቀደም ስላደረጋቸው አስደናቂ ገጠመኞቹ በማጫወት ትኩረቴን ሊስበው ሞክሯል። አንደ አወራሩ ከሆነ አውነቱን የሚናገረ ሰው ለመሆኑ መረጃ ነበር። በርግጥ፣ ለመናገር ያለው ስሜት በማንኛው ጊዜና ቦታ ይገለጥ ነበር። አንዲህ ያለ አዋቂ ሰው መኖሩን ማወቅ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን የኔ ድርሻ ነበር። ለለ ጓደኛዬ፣ በአአምሮዬ ሃሳብ ውል ሊልብኝ፣ ትልቅ ሥልጣን ያለውና ሰፊ ሀብት ያለው መሆኑን ሳስታውስ ደስ የሚል ሀሳብ ሊኖረኝ የሚገባውን ሁኔታ ያዘናጋኛል፤ ነገር ግን፣ ይህ፣ መጠነኛ አንግዳ የሆነ የአአምሮ ለውጥ ብቻ ነበር።

ከካምፓችን አምስት ማይሎች ርቀት ከልል ውስጥ ደርሰናል። አልፎ አልፎ፣ በምንጓዝበት መንገድ፣ ጉብ ያሉ ከፍታዎች ዝቅ ያሉ ቦታዎች ላይ ጥላ ከመጣሉ በስቀር፣ በሙሉ የጨረቃ ብርሃን የእግር መንገዱ ይታይ ነበር። ጀለቆ ከፊት ለፊታችን እለ፤ ጠመዝመዝ ያለውን መንገድ ያዝንና ከፍ ያለ ቋጥኝ ጥላ ያረፈበት ጉድጓድ ሳንደርስ ለማለፍ እንደ ግማሽ ኪብ መንገድ ሙሄድ ጀመርን። ቋጥኙ ቦታ እንደደረስን፣ ጎርነን ያለ የአውሬ ድምፅ መስማት ጀመርን። ለመግለፅ ያህል፣ ከዚህ ቀደም ከዘንዶ፣ ከነብር ጋር አስቃቂ ፍጥጫ ያጋጠመው ጓደኛዬ፣ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት አካባቢውን በደንብ ሙቃኘት እንዲችል በፍጥነት ፊረሱን ከኔ ጀርባ አስጠጋ።

"ምንድነው ነገሩ?" ብዬ ጠየቅሁ።

"የግሥላ ድምፅ፣ አልሰማህም እንዴ?" በማለት እኔኑ መልሶ ጠየቀኝ

"እርግጠኛ ነህ ግሥላ ለመሆኑ?"

"በጣም እርግጠኛ"

"እሀ! ያውና፣ ከፊረስህ እግር አጠገብ" አልኩኝ።

"የት ? የት?" ብሎ ጠየቅ ፊረሱን በፍጥነት ወደኋላ እየሳበ።

"ያውና፣ ቁጥቋጦው ውስጥ፣ በቀኝ በኩል ተጠግቶሃል። ጠመንጃህን፣ አስተውል፣ ካልተጠነቀቅህ እኔን ትመታኛለህ። እንዴ፣ ለውዬ፣ አይታይህም እንዴ? ሊዘልብህ ነው። አሁኑኑ ተኩሰበት፤ አለበለዚያ ትዘገያለህ።" ብዬ ጮህኩበት።

"አይታየኝም፤ አይታየኝም፣" ተስፋ በቆረጠ ድምፅ ጮኸ።

"አይታይህም ወይ? ወደ እንተ እያደባ ነው፤ በቀኝ በኩል ወደ ሀያ ያርድ ርቅት"

"አሀ፣ አዎ!"፣ "ድው!" የጠመንጃ ድምፅ፣ "ሞቷል ወይ?" ብሎ ጠየቀ።

"ወድቋል"፣ ብዬ መለስኩ።

"እሃ፣ ሃ! የሸማግሌው ቀኝ እጅ ሙያውን አልረሳም።" በመፈንደቅ ተናገረ። ቀጥሎም፣ "የኔ ልጅ፣ አንዴ ከመዘዝኩ ስቼ አላውቅም ብዬ ነግሬህ አልነበርም?"

"እዎ፣ ሁልቀን ነው አንጂ፣" የኔ መልስ ነበር። "ነገር ግን፣ እንዴት ነው አውሬው አጠገብህ አስኪደርስ ድረስ ያላየኸው? የዕይታ ችግር አለብህ ወይ?"

"አልፎ አልፎ፣ በተለይም በጣም ስሜታዊ በምሆንበት ጊዜ።"

"ታዲያ አሁን መነሳሳትክን እታምንም? በተለይም አሁን፣ ታምናለህ?"

"እሀ! እኔ መወራጨት? ውድ ጓደኛዬ፣ በሕይወቴ ተወራጭቼ አላውቅም።"

"አሃ፣ ይቅርታ አደርግልኝ፣ የተነሳሳህ መሰሎኝ ነበር፤ ሆኖም የዕይታ መደናገር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ምን አይነት አውሬ ነው ለመሆኑ የተኮሰከበት?"

"ጠመንጃየን ጥይት አሰክማጎርስ ድረስ፣ አባከህ ራሰህ ምን አንደሆን አየው።"

"አንዴት፣ ጅብ ነው።" አልኩ። የወደቀውን አውሬ ለተወሰነ ጊዜ ካስተዋልኩ በኋላ፣ በሆዴ ግን፣ አሱ ራሱ ቢያየው ተመኝቼ ነበር።

"ጅብ? ነው አንዴ? አሆ ሆ! ብዙ ጊዜ ጅቦች ከግሥላ በላይ አደገኛ ናቸው። ለምሳሌ፣ በጥርሳቸው አንዴ ከያዙ ምንም ቢሆን አይለቁም።" ይሄን አየተናገረ በመራመድ ወደ ወደቀው አውሬ ተቃረበ። ጭንቅላቱ አጠገብ ሲደርስ አውሬው ቀና ማለት ጀመረ፤ ካፒቴኑ ጠመንጃ ቢይዝም፣ በማያወላውል ሁኔታ ትንሽ ተደናግጦ ነበር። በጅቡ በኩል የጣዕረ ሞት ነበር፤ በካፒቴኑ በኩል ደግሞ የአዳኞች ጣዕር ነበር። አውሬው የመጨረሻ አስትንፋሱን ሲያቆም፣ "ቀልደኛው ሽማግሌ"፣ የአውሬውን አስከሬን፣ ጭንቅላቱን መርጦ ተኮሰበት። "ለማረጋገጥ፣ ለመጨረስ ነው፣ ታውቃለህ።" አለ።

ወደ ካምፕ ስንመለስ መሸቶ ነበር፤ ጓደኛዬ ጅብ ከመግደሉ በሰተቀር ሌላ ምንም አይነት አስገራሚ ገጠመኝም አልነበረንም።

በመጋቢት 3፣ 2ኛው ብርጌድ፣ ጀኔራል ናፒየር አና ጀኔራል ቻርለስ ሰታቨሊ አኛ ያለንበት የአንጣሎ ካምፕ ደረሱ። በጣም የሚያጓጓ ትዕይነት ነበር። የ(ትልቅ ትልቁ ጌታ) "ቡራ ቡራ ሳሂብ"፣ ከፈረንጅ ወታደሮች ጋራ መምጣቱ ወሬ ሲሰማ፣ የአንደርታን አውራጃ አንዳለ አነቃቅቶታል። አንጣሎ የአንደርታ አውራጃ ከተማ ነው። በሺዎች የሚቆጠሩ፣ አነስ ያለ ልብስ የለበሱ ተዋጊዎች፣ ገላቸው ሙሉ በሙሉ ያልበሰ ሴቶች፣ ጠያይሞች ትንንሽ ልጆች፣ በየመንገዱ ዳር ተጋድመው፣ አዛውንቱ፣ ወጣቱ፣ ወንድና ሴቱ፣ ቁሱም ሆነ ተራው ሰው፣ የማይል በሚሆን ርቀት በመንገዱ ዳርና ዳር ሆነው የትልቁን ጌታ "ሳሂብ" አና የአንግዳ ተቀባዩን መምጣት ይጠብቃሉ።

የሬጅመንቱ የሙዚቃ ባንድ ወደፊት ቀደም ብሎ፣ ለሚመጡት ጓዶቻቸው የአንኳን ደህና መጣችሁ ሙዚቃ ያሰማል።

ጀኔራል ኮሊንግስና ረዳቶቹ፣ ኮሎኔል መርዌዘርና ሌሎችም መኮንኖች፣ ሰር ሮበርት ናፒየርን ለመቀበል አየጋለቡ ወጣ ብለዋል።

በመጨረሻም፣ በጉጉት የሚጠበቀው ጀኔራልና ወታደሮቹ በሙዚቀኞች አየተመሩ መጡ። ሙዚቀኞቹ፣ አየሩን ሥርአት ባለውና በሌለው ዜማ አደናግረውታል። የመጀመሪያው ሬጅመንት መታየት ሲጀምር፣ አንጣሎ ያሉት

ወታደሮች ደስታቸውን በሰላምታና በደምፅ ገለጡ፤ ለነሱ ድምፅ ለመመለስ ደግሞ ሬጂመንቱ፣ "ሁዛ!" በማለት፣ በጩኸት ድምፅ አሰማ። ከኋላ የሚከተለው ጦርም ድምፁ በርቀት እሰኪሰማ ድረስ ጩኸቱን አሰታጋባ። ተወላጆቹ ደግሞ፣ በተራቸው፣ ወደራሳቸው አንደበት ቀይረው፣ እልልታውን አቀለጡት።

መጀመሪያ የመጣው የአየርላንዶቹ ሬጅመንት ነው፤ ወታደሮቹ፣ አንደ አነር ዒማቸውን አሳድግው፣ በሞቃታማ ቦታዎች ፀሀይ ፊታቸው ጠቆር ያለ፣ በሙያቸው ልምድ ያላቸው፣ በተለያየ የአየር ጠባይ፣ በህንድ ዘመቻዎች፣ በሂማልያ በረዶዎች፣ በሰንዲ (ፓኪስታን)፣ በወኔ የታገሉ ናቸው። በላያቸው ላይ የሚውለበለበው የሬጅመንቱ አርማ፣ በአይቤሪያን ሠርጥ ገዳይ ቦታዎች በተደጋጋሚ የተወረወረና የተውለበለበ፣ ለዚህም የዌልንግተንን አከብሮት ያገኘ ነው።

ከነሱ ቀጥሎ፣ 4ኛው ሬጅመንት "የንጉሡ" ጦር መጣ። አነሱ የያዙት አርማ፣ በከሬሚያ ዘመቻ በአሳትና በአሩር ማዕበል የተብተከተከ ነው። ከነዚህ ወታደሮች በኋላ የተወላጆቹ ጦር መጣ፤ ይህ የ27ኛው አግረኛ፣ የፑንጃብ ጦር ይባላል። ሰዎቹም ረዘም ያሉ፣ በሥርአት የተሰለፉ፣ ከህንድ፣ ፑንጃብ ከሚባል ቦታ ነው የመጡት። የቤሎቹ ሬጅመንት- ቤሎቹዎች አረንጓዴ ጥምጣምና ቀይ ልባስ ነገር ላያቸው ላይ ጠምጥመው ቀይ መለመር ያለው አርንጓዴ ዩኒፎርም ለብሰዋል። 10ኛው፣ የተወላጆቹ (ህንድ) አግረኛ በውሰጡ ከተለያየ የህንድ ጎሣዎች የተውጣጡ ቆፋሪዎች(መንገድ ሠሪዎች) ያሉበት ነው። በመጨረሻው ሬጅምንት ካሉት ሰዎች፣ እያንዳንዱ፣ በጦሩ ውሰጥ የተሰለፉ ከሰላሳ አሰከ አርባ የሚቆጠር ዘመዶች አለው።

ከነሱ በኋላ ደግሞ የፈረሰኛው ክፍል መጣ፣ የሰንዲ ፈረሰኞች፣ ደመቅ ያለ ቀይ ልብሰ ታጥፎ እንደጥምጣም አንገታቸው ላይ ተደርጓል። ሰዎቹም አረንጓዴ ዩኒፎርም የለበሱ ሲሆን ፈረሰቻቸው ደግሞ አረንጓዴ የኮርቻ አልባሳት ተደርጎባቸዋል። አያንዳንዱ ሰው አጭር ጥንድ አፈመዝ ያለው ጠመንጃና የህንድ ጎራዴ ይዟል።

መኮንኖቹ ብርማ ቀለም ያለው ባርኔጣ አድርገዋል። ከፈረሰኞቹ ኋላ፣ ሰር ሮበርት ናፒየርና ሰር ቻርልስ ሰታቨሊ ሥርአት ያለው አለባበስ በለበሱና ባማረ ሁኔታ ፈረሰ በሚጋልቡ ረዳቶቻቸው ታጅበው መጡ። ከወታደራዊ ሁኔታ ለየት የሚያደርግ ከሚገባው ወይም ከመጠን በላይ የሆነ አለባበስም ይታያል። አንድ ወጣት ጌታ ለምሳሌ፣ ነጭ ጓንትና አርንጓዴ ቬሎ ለብሷል።

የጠቅላይ ዕዝ ጽ/ቤት ሠራተኞችን፣ የ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ ኮምፓኒ ይከተላል፤ ፈረሰኞቹ የህንድ ተወላጆች ወታደራዊ ገፅታ ያላቸው ሰዎች

ናቸው፤ መኮንኖቻቸው አንዳንዶቹ ተወላጆች (ህንዶች) ሲሆኑ፣ ልከ ወደ ግርግር ቦታ ሀይለኛ ፈረስ እየጋለበ እንደሚሄድ ሰው፣ በኮርቻቸው ላይ ወደ ላይ ወደ ታች፣ ከፍና ዝቅ እያሉ ፈረሶችን ይጋለባሉ። ሱሪዎቻቸው ከሥር መጠፈሪያ ቀበቶ ስላልነበራቸው፣ ፊርጠም ያሉ ባቶቻቸውን እጋልጠው ያሳያሉ። የነዚህ ወታደሮች ዩኒፎርም እንደ ስማያዊ ግራጫ መልከ ያለው ሆኖ ነጭ የትከሻ ማንገቻዎችና ነጭ እጅጌዎች አሉበት።

ከነዚህ ኋላ፣ የከባድ መሳሪያው ከፍል ነው የመጣው። ሰድስት የእርምስትሮንግ የሚባለው ከባድ መሳሪያ ባትሪ አለበት፤ ቀጥሎም ዝሆኖችና ጓዝ ተሸካሚው ከፍል ሰባት ማይሎች በሚሆን ርቀት እየተከታተለ ይመጣል። በቅሎ መሪዎች ራሳቸው ብቻ የሠራዊት ያህል ብዛት ነበራቸው።

ከ2ኛው ብርጌድ ጋር የተመደቡ 7ሺ በቅሎዎች ነበሩ፤ ይህ የ2ኛው ብርጌድ፣ የነኛው ዲቪዚየን የሚመራው በጄኔራል ቻርልስ ስታቨሊ ነበር። ለነዚህ በቅሎዎች ደግሞ 3ሺ ሰዎች ያስፈልጉ ነበር። ከዚህ በላይ፣ የከምፕ ሠራተኞች፣ ዝሆን መሪዎች፣ ግመል ጎታቾችን ሲጨምር፣ ቁጥሩ በጠቅላላ ወደ አምስት ሺ ሰዎች ከፍ ይላል።

ከኒዘህ ሰዎች በተጨማሪ ያገሬው የአቢሲኒያ ሰዎች አሉ። እነሱም፣ ሰፋሪዎች፣ የትምባሆ፣ የዳቦ፣ ገብስ፣ አይብ ሽቃጮች፣ የኮሚሳሪያቱን ፍየሎችና ከብቶች የሚነዱ እረኞችም አሉበት። ከብዛታቸው የተነሳና በቀለምም ለየት ብለው ከመታየታቸው አንፃር ከጠቅላላው መንገደኛ ጎላ ብለው ከሚታዩት ወገን ናቸው። ሌሎች መርሳት የሌለብኝ ሰዎች ደግሞ፣ ብዛት ያላቸው ተሸካሚዎች፣ ልብስ አጣቢዎች፣ ውሀ የሚያመላልሱ፣ ከብቶችን የሚመሩ ሰዎች፣ የዘማቹን ቁጥር እንዲገዝፍ ካደረጉት መሀከል ናቸው። እንዲህ ያለ የተለያየ ገፅታ ያለው ስብጥር በዘመናዊ ጦር ውስጥ ታይቶ አይታወቅም። የዩኒፎርሞቹ ቀለም አይነት፣ የለበሱት ልብስ፣ ምንጣፉ፣ ጥምጣሙ፣ ባርኔጣዎች ደግሞ ውስብስብ ያለ የተለያየ ቀለማት የሚታዩበት ነገር ነው።

የፖላንድ ተወላጆች ከባስታረኒከ ተራራዎች፣ ፂማሞች ጠንካራ ሰዎች ከሳርማቲያን፣ እፍ ከሚያበዙት የፈረንሳይ ተወላጆችና ኮሰትር ካሉት ጀርመኖች ጋራ በደሰታ ያወራሉ። ጥምጣሙን ያደረገው የቱርክ ተወላጅ፣ ከማይለየው ሱረት ማጨሻው ጋር በመዝናናት አብሮ ይጓዛል፤ የቱርክ ተወላጆች፣ ለእንቅስቃሴ ምንም እይነት ፍላጎት ምልከትም አያሳዩም፤ ጠቆር ያለ መልከ ያላቸው አረቦችም ፍም የመስለውን ትምባሆ እየሳቡ አብረው ይገኛሉ። የወይራ ቀለም ጉንጮች ያሉት አይሁዳዊም ቢሆን ጥርት ብለው ከሚታዩት አይኖቹ ጋራ፣ በማያውቀው ሀገር፣ ከማያውቃቸው የከሩሴድ ዘማቾች ጋር በሰልፍ የሚከተሉትን በቅሎዎቹን እየመራ ይከተላል። በአእምሮው፣ እንድ ሰፍራ የደበቀው ውድ ንብረት እንዳለና ከአፍሪካ

ሲመለስም የአልማዝ ነጋዴ እንደሚሆን የቀን ህልም አያስበ ይሆናል። ሰንጋጋ ባህሪ የሚታይባቸው ፋርሶች ወይም ከፔርሽያ የመጡ ጉበሮችም እንድ ሩፒን በትርፍ ሁለት ለማድረግ አጋጣሚ ፍለጋ ላይ ሆነው በትሎቻቸውን ከሚመሩት አይሁዶች ጋር ጎን ለጎን ይጓዛሉ። በቅባት የተወለወሉት ከማህራታስ የመጡ ሲኮችም ቢሆኑ ረጋ ካሉት ከደንከን ከመጡ የቆፋሪዎች ዘቦች ጋር የሞቀ ጨዋታ ይዘዋል። ማቋረጫ ያለው ከማይመስለው ተጓዥ ጋር ደግሞ አስቸጋሪዎቹ ሶማሊዎች ከሶማሊ ላንድ፣ አስቀያሚ መልክ ያላቸው የበርበራ ሰዎች፣ ሁለት ልብ ያላቸው ቤንጋሎች፣ የአውሬ ገፅታ ያላቸው ሽሆች፣ ቀልጣፎቹ ኑብያኖች እና ደፋሮቹ ሀዞራይቶች ይገኙበታል።

በስልፍ የሚወርደው ሰው ምንም የወታደራዊ ስሜት ቢኖረውም በጣም የተደበላለቀ ገፅታ ነበረው። ነጮች ነበሩ፤ ቀይ፣ ጠየም ያሉ፣ ብጫነት ያላቸው፣ ጥቁሮች፣ ሁሉም ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ተቀላቅለው ነበር። ከሎንደን የመጡ ኮከኒዎች፣ ከአየርላንደ የመጡ ከልትስ፣ አሸዋማ ገፅታ ያለው ፀጉር ያላቸው የስኮትላንድ ሰዎች ከህንዶች ጋር ጎን ለጎን ይጓዛሉ።

የሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ በቅሎዎች፣ የከፍሉ ማረፊያ ቦታ ላይ ሲደርሱ ጭነታቸው ወረደ። የጭነት ከብቶችም የተጫኑት ጓዝ በየባለቤቶቻቸው ድንኳን አጠገብ ተራገፈ። ከዛ በኋላ፣ ከብቶቹ ገንዳዋ ወንዝ አጠገብ ወዳለው ቤረታቸው ተወሰዱ።

የመድፈኛው ከፍል በግራ በኩል በሚገኝ ጉብታ ቦታ ላይ በመስፈር፣ የብረት መድፎችና ተሸከርካሪዎችን መወልወል፣ ፈረሶችን ወህ ማጠጣት፣ ከዛም ቀለብ ወይም ምግብ ማከፋፈል ሲጀመር፣ በሌላ አገር እንደሚሆነው ሁሉ፣ ጫጫታ የበዛበትና ግርግር የበዛበት ስፋት ያለው ካምፕ በዚሁ በአፍሪካ አፈር ላይ አየተመሰረተ ነበር።

በሰንቅና ትጥቁ ካምፕ ዙሪያ ወዲያውኑ እንግዳ የሆነ ነገር መታየት ጀመረ፤ ከዚህ በፊት ጦሩ ወደ አንጣሎ ሲንቀሳቀስ ተከትዬ አብሬ ብሄድ ኖሮ በተደጋጋሚ ላየው የምችል ሁኔታ ነበር። ፓረሶች ዶላር የያዙት ከረጢቶችን ይዘው በመውጣት ከህገሩ ተወላጆች ጋራ መገበያየት ጀመሩ። እንግሊዞቹ በሊጋስነት ብዙ ብር የሚከፍሉ መሆናቸው ባገሩ ተወላጆች ስለታወቀ፣ በዚህ ግርግር መህል ትንሽም ቢሆን ሥርአት ያስፈልግ ነበር። ውድድር ነበር፤ ቀድሞ ስልቻው የያዘውን ገብስ ሚዛኑ ላይ ለመገልበጥና እነዚህን አቢሲኒያውያን በጣም የሚወዱትና ሲያዩት አንኳን አይናቸው በደስታ ወገግ የሚሉባቸውን አዳዲስ የማር ተሬዛ ብሮች በአጅ ለማድረግ ነበር። ፖሊሶች (ቹፐራዎች)፣ ቀደም ብለው በቦታው ተገኝተው በጉጉት የሚጠብቁትን አቢሲኒያውያን ሥርአት ለማስያዝ ውጤት አልባ የሆነ ጥረት አያደረጉ ነው። ተወላጆቹ፣ ገብስ፣ ዱቄት፣ አጃ፣ ሌላም አህል፣ ዳቦ፣ ማር፣ የሥር አይነቶች፣

እንጨት፣ ከብት፣ ፍየል፣ በግ፣ በቅሎ፣ አቆማዳና መጫኛዎች ይዘው ይመጣሉ።።

በረዳት ሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ፣ ለሠራዊቱ የሚሆን ምግብ ለመግዛት ወደ አሰራ ሁለት የሚሆኑ ፓረለች ተቀጥረዋል።። መደነባበር እንዳይፈጠር፣ እያንዳንዳቸው አንዱ ከሌላው በአለር አርምጃዎች ርቀት ተመድበዋል።። ስለዚህ፣ ዳቦ ዱቄቱ ላይ እንዳይወረወር፣ ዶሮና ቅቤ ከዳቦ ጋር እንዳይቀላቀል፣ እንጨቱም ቢሆን ዶሮዎች ላይ እንዳይወረወር ነበር።።

አያንዳንዱ ሰው በገበያው ሰዎች ተከበ፣ አሱና የያዘው የማርተሪዛ ከረጢት ተጋፈ ከሆነ ተመልካች አይታ ተጋርዷል።። ከልጅነታቸው ጀምሮ በማታለልና በማጭበርበር ላደጉ ሰዎች፣ ብር የያዘው ከረጢት የማይቋቋሙት ፈተና ነው የፈጠረው።። ሁኔታውን ለአንዳ አፍታ ላስተዋለ ሰው፣ በመሀል የሚላላኩ የፓረሳውያን ልጆችን ማየት ይችላል።። እነዚህ ልጆች፣ ከሚዋከበው ሰው ወይም ሻጭ ጋር ተደባልቀው ዶላሩን ይቀበሉና፣ ቀስ ብለው ከግርግሩ ወጣ ብለው፣ ከሰንቅ ከፍሉ ካምፕ አጠገብ የተወጠሩ ጠቆር ያሉ ድንኳኖች ውስጥ ሲሰወሩ ይታያሉ።። እነዚህ ድንኳኖች ደግሞ እነዚህን ልጆች የቀጠሩ ሰዎች የሚኖሩበት ነው።። በአንድ ቀን እንደነዚህ አይነቶች የመሀል ገብ ሥራዎች በብዛት ይከናወናሉ፤ ምናልባትም፣ እያንዳንዳቸው ሻጮች ከሰባ አምስት አሰከ መቶ ዶላሮች ያግበሰብሳሉ።። በጣም የሚገርመው፣ አንድም ፓረሲ በሌብነት ተከሶ ቀርቦ አያውቅም።። የሚሠሩት ሥራ ታላቅ አስተዋፅአ ስላለው፣ አነሱ ላይ ከረር ያለ አርምጃ መውሰዱ ለፖለቲካው የሚበጅም አልነበረም።። ቢሆንም ከነዚህ ጎሰኞች ጋር ያለተነካኩ ውለታ የሌለባቸው ጥቂት መኮንኖች ብቻ ነው የነበሩ።።

አነስ ያሉ የወረቀት ገንዘቦች፣ ያለነዚህ ሰዎች ርዳታ ወደ ጥሬ ገንዘብ መቀየር አይቻልም።። የወታደራዊ መኮንኖች ደግሞ ከሌላው ሰው በበለጠ ሁኔታ ገንዘባቸውን እንደልብ ለማውጣት ነፃ ስለሆኑ፣ በዚህ ዋጋ በናረበት በአቢሲኒያ፣ እንደዚህ አይነቱ ወደ ጥሬ ገንዘብ መቀየር አስፈላጊና በብዛትም የሚደረግ ነገር ነበር።። ከጦሩ ካዝና መጠቀም ያልተለመደ ሥርአት ስለሚሆን፤ መኮንኖቹ የፓረሲዎቹን ግብረገብ የጎደለው ሥራ ለማጣራት ከመንቀሳቀስ ይልቅ ለሀንድ ደላሎች ከፍ ያለ ቅናሽ መክፈሉን ይመርጣሉ።።

ከላይ እንደገለፅኩት፣ የማጓጓዣ ከብቶች ጭነታቸው ከወረደ በኋላ ወንዙ እጠገብ ወዳለው ካምፕ ተወስደዋል።። የማጓጓዣ ከፍሉን በደንብ ለመረዳት፣ በሚቀጥሉት ገፆች ቃሉ ተደጋግሞ ለለሚመጣ፣ በሚቀጥለው ሁኔታ እገልፀዋለሁ።።



የበሎቹዎች ሬጅመንት

ወደ አቢሲኒያ የሚመጣው አጠቃላዩ የማጓጓዣ መስመር በየካቲት 14፣ 1868 ከቦምቤይ ነበር የተፈጠረው። ነገር ግን፣ ይህ መለመር ከዚህ ቀደም በጥቅምት ወር ለአፍሪካ ጉዞ ተዘጋጅተው ከነበሩ ከሁለት የፑንጃብ የማጓጓዣ ክፍሎች ነው የተመሠረተው ማለት ይቻላል።

የደጋማው የማጓጓዣ መስመር የተደራጀው ለደጋማው የአቢሲኒያ ክፍል ነው፤ የዚህ ክፉሉ፣ በሰር ቻርለስ ስታቨሊ በሚመራው አሁን ወደመቅደላ በመገስገስ ላይ ላሉት የነኛው ዲቪዚዮን ነኛውና 2ኛው ብርጌዶች ጓዝና ምግብ ያጓጓዛል፤ የቆላማው የማጓጓዣ መስመር ግን በሰናፈና ዙላ መሀል አገልግሎት ለመሥጠት የተወሰነ ነበር።

የደጋው የማጓጓዣ መስመር፣ እያንዳንዳቸው 2ሺ በቅሎዎች ባሉባቸው አራት ክፍሎች የተከፈለ ነበር፤ እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ 150 ወታደሮች ሲኖሩበት፣ የክፍል መጠንና አደረጃጀት ደግሞ አንደሚከተለው ነበር።

1 ካፒቴን

3 ዝቅተኛ መኮንኖች

4 አውሮፓውያን ተቆጣጣሪዎች (ከብሪታንያ ሬጅመንት የተመረጡ)

20 ጃማዳር ወይም ሻምበል ባሻዎች

80 ዱፋዳሮች ወይም ሃምሳ አለቃዎች

667 በቅሎ መሪዎች

2 ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ናልባንዶች ወይም የፈረስ ጫማ ሰሪዎች

10 ምክትል ደረጃ ያላቸው ፈረስ ተንከባካቢዎች

1 የህንድ ተወላጅ አንጥረኛ አለቃ

10 ረዳት አንጥረኞች

10 ውሀ አመላላሽ ከብቶችን የሚቆጣጠሩ

2 ገመድ ሠሪዎች

1 የህንድ ተወላጅ የከብት ሀኪም

1 የህንድ ተወላጅ ፀሀፊ

ዘመቻው ሲጀመር፣ አንድ ሰው ሁለት በቅሎዎች ብቻ ነበር የሚቆጣጠረው፤ ሁለቱን ብቻ መንከባከብ እንጂ ሌላ ሰራም አልነበረውም። ጋጣ፣ ውሃ ማጠጣትና ሌሎች ሥራዎችም ከቤንጋል ፈረሰኛ ሬጅመንት ቀን ተቀን ሥራ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር የሚሠራው። አነዚህ በቅሎ መሪዎች ትምህርት የተሠጣቸው በመሆኑ ሰራቸውን ጠበቅ ባለ ሥነ ሥርአት በሚገባ ነበር የሚያከናውኑት። ሻምበል ባሻዎቹ፣ በነሱ ምድብ ያሰውን የወታደር ስም ዝርዝርና የሚከፈለውን ክፍያ በፋርስ ቋንቋ ነበር የሚመዘግቡት። የእያንዳንዱ

ሰው ሙሉ ዝርዝር በፋርስ ቋንቋ በፀሀፊዎች ተመዝግቧል፤ የከፍያ ሂሳብ ደግሞ፣ በእንግሊዝኛ በካርቴኑ አጅ ይቀመጣል።

የቲንጃቡን የማጓጓዣ መስመር የሚያዙት መኮንኖች ያልተገደበ ሥልጣን አላቸው፤ በዚህም ሰዎችን ስውነት ላይ ቅጣት ማስፈፀም ብቻ ሳይሆን ለሁለት አመታት የማሠር መብት አላቸው። ሁሉም በምከትል ዳይሬከተሩ ትዛዝ ስር ነው፤ ምከትል ዳይሬከተሩ የጠቅላይ ዕዝ ቢሮ አባል ሆኖ፣ ቀጥታ ለረዳት የትጥቅና ስንቅ ሀላፊው ከፍል ሪፖርት ያደርጋል። ለዚህም የስታፍ መኮንንና፣ በየቦታው እየተዘዋወረ የሚያየውን ወይም የዘገበውን ሁሉ ነገር ለሱ ሪፖርት በሚያደርግ ተቆጣጣሪ ይታገዛል። የማጓጓዣ መስመሩ በአዲግራትና በመቅደላ መሀከል ያጓጉዛል። ዋና ሥራውም፣ ጓዞችን፣ ጥይቶች፣ የሆስፒታል መገልገያዎችን አና ለጦሩ ለአንድ ወር የሚሆነውን ስንቅ ማቀበል ነው። በመህል በሚገኙ ተለቅ ያሉ ጣቢያዎች ላይ የስታፍ መኮንን በቋሚነት ተመድቦ የጓዙ ሀላፊ ከሆነው መኮንን የሚደርስውን ሪፖርት በመቀበል ለጠቅላይ ዕዙ ጽ/ቤት ያስተላልፋል። በነዚህ መህል ቦታዎች ላይ ተጠባባቂ የጭነት ከብቶች ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ፤ ይህም የታመሙ ወይም የደከሙ የጭነት ከብቶችን ለመተካት ነው። በቅሎዎቹ፣ ከሰፔይን፣ ከግብፅ፣ ከህንድ፣ ከፔርሺያ እና ከአቢሲኒያ አየተገዙ ሥራ ላይ ይውላሉ።

የስፔይን በቅሎዎች ገዘፍ ያሉ ጥሩ ዝርያ የሌላቸው ናቸው። አንዳየሁት ከሆነ፣ በተፈጥሯቸው ደከም ያሉ ሆነው ተለዋዋጭ የአየር ፀባዩን የሚቋቋሙ አልነበሩም። በብዛት የሚሰቃዩት በነበራቸው የመመገብ ፍላጎት ምክንያት ነበር፤ በተለይም ሳሩ ቢኖርም በበቂ መጠን ስለማያገኙ ነበር። የተገኘው ሳር ደግሞ የደረቀና ሸካራ በመሆኑ አልወደዱትም። ምንም እንኳን አርፈውና እንደልባቸው የሚግጡት ሳር በመህል ጣቢያዎች ቢገኝም፣ አንድ ጊዜ ከደከሙ መልሶ ለማጠንከር አስቸጋሪ ነበር። መጠነኛ የሆኑት ጥሩ ዝርያ ያላቸው የስፔይን በቅሎዎች ግን ደህና ምላሽ ያሳያሉ። የፔርሺያ፣ የህንድና የግብፅ በቅሎዎች በተቃራኒው ችግር ቻይ፣ መጠነኛ አህል የሚበቃቸው፣ ያገኙትን የሳር አይነት የሚበሉና በዛም የሚዳብሩ ነበሩ።

የአቢሲኒያ በቅሎዎች ችግር የሚቋቋሙ አልነበሩም፤ ሲገዙ በጥሩ ሁኔታ የነበሩት አንኳን፣ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ በብዛት ከአገልግሎት ውጭ ነበር የሚሆኑት። በመጋቢት 1፣ 5412 ከብቶች በደጋው የማጓጓዣ መስመር ውስጥ ነበሩ ከነዚህ መህል 1002 የሚሆኑት በሽተኞች ነበሩ።

በሚያዝያ 1፣ 6691 ከብቶች ነበሩ፤ ከነዚህ ውስጥ 1002 በሽተኞች ነበሩ። በግንቦት 1፣ ከ7960 ከብቶች መህል 1944 በሽተኞች ነበሩ። ከመጋቢት 1 ጀምሮ በደጋማው ሀገር 2720 ከብቶች ሲገዙ፣ ከቆላማው፣ 1740 የሚሆኑት ወደ ደጋማው ቦታ አንዲመጡ ተደርጓል። ከዚያ ጊዜም ጀምሮ

በመንገድ ላይ 449 ከብቶች ሲጠፉ፣ 1257 የሚሆኑት ወደ ቆላማው የማገሚያ ቦታ ወደ ቁማይሌ ተልከዋል። እነሱም እንደማይመለሱ ተሰርዘው ነው፤ 309 ከብቶች በደጋማው ማገሚያ ጣቢያ ተገድለዋል ወይም ሞተዋል። 2418 የሚሆኑት በህከምና አገግመው ተመልሰው ወደ ሥራ ተልከዋል። በቅሎዎቹም ፋታ ሳያገኙ ከመርከብ እንደወረዱ ነበር እገልግሎት ላይ የዋሉት።

ሠራዊቱን ተከትለው ከመጡ ሰዎች መህከል ጉልህ የሆነ የሥራ ባህሪ ልዩነት አሰ። ከነዚህ መህል ጦሩን ተከትለው፣ ከሀንድ፣ ራውል፣ ፒንዲ ተነሰቶ እሰከ ፐርሺያ ሰርጥ ከራቺ ድረሰ ለሸ ማይሎች መንገድ በመጓዝ ልምድ ያካበቱት ሰዎች፣ የጭነት ከብቶቻቸውን በደንብ ነበር የያዙት። በተለይም ከዶከተር ሀለን በኩል የሚመጣውን ችግርና ጭቅጭቅ ችለው ነው። ሌሎቹ ከግብፅ፣ እሰከንድርያና ካይሮ የተመረጡ ተራ ሰዎች፣ በመቶዎች ቁጥር ሆነው ለሚፈለገው እገልግሎት የመጡት፣ የሚቆጣጠሯቸውን እንሰሶች ለሚያሳዝን አደጋ ነው የዳረጓቸው። በጥባጭና ተተናኳይ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ እሰቸጋሪ ዳጎትና ተራራዎችን የመውጣት ችሎታም እልነበራቸውም። ይህም ከዚህ በፊት በነበራቸው የሰንፍና ባህሪ ምክንያት ነው።

አገልግሎት ላይ የዋሉት ኮርቻዎች የተለያዩ አይነት ነው የነበሩት። የቦምቤይ ፓድ፣ እሰቸጋሪው የቱርኮች፣ አታንና መከማሆን የሚባሉ የእንግሊዝ ኮርቻዎች ነበሩ።

የአታንው ኮርቻ፣ በኔ እሰተያየት፣ ከተሠሩት ሁሉ በጣም ጥሩው ነው። ከጠንካራ፣ ከእንግሊዝ አገር ቆዳ የተሠራ ነው። ጎንና ጎኑም ከዚሁ ከእንግሊዝ አገር ቆዳ የተሠራ ሆኖ፣ የከብቱ ጎን ላይ ከሚያርፉት ከአራት ማዕዘን ትራሶች ጋር የተሰፋ ነው። እነዚህ ደግሞ፣ በቆዳ ክተሸፈነ፣ ከከብቱ እከርካሪ ሶሰት ኢንች ከፍ ፍሎ ከሚገኝ ጎበጥ ያለ ጠንካራ የብረት ደጋን ጋር ይገናኛሉ። በሁለት ጎን ሁለት መንጠቆዎች አሉ፤ እነሱም የሚንጠለጠውን እቃ እሰረው መያዝ የሚችሉ ጠንካራ ቀበቶዎች በተለያየ ርዝመት እሉባቸው። ከብደቱ ወደ 28 ፓውንዶች ይሆናል። መከ ማሆን የሚባለው፣ ጥቅጥቅ ያለ ኮርቻ ሲሆን የ66 ፓውንድ ከብደቱ ግን ሰእግልግሎት እንዳይውል ያደርገዋል።

ሰለ እንሰሳቱ ህመምና ሞት የጠየቅሁት፣ ከኛው ዲቢዚዮን ጋር የተመደበው የከብት ህኪም፣ ለእንስሳቱ በብዛት መታመምና መሞት ዋናው ምክንያት፣ "በከፍታ ቦታ ላይ ከባድ ሥራ፤ ዕረፍት እያሰፈለጋቸው ግን ያለማቋረጥ እንዲሰሩ መደረግ፤ በቂ ምግብ እለመኖርና፣ የሳሩ አይነት ጥራት የሌለው በመሆኑ፤ ጊዜ ጠብቆ እለመመገብ፤ በመጥፎ ኮርቻ ምክንያት መቁሰል፤ የቆሰለውንም በጊዜ ማከምና ማሳረፍ እለመቻል፤ የከብት ጫኞቹ ግድየለሽ ኮርቻና ጭነት እጫጫን ነው።" በማለት ተናገረ። በቅሎ ጫኞቹ

ከፍንጃብ ከዛው አካባቢ ከተመለመሉ ወታደሮች ተከታይ ሆነው ነበር የተቀጠሩት። ከዚሁ በታ፣ ከህንድ የተቀጠሩት ሰዎች፣ አንጣሎ ሲደርሱ እረቦችንና ቱርኮችን እንዲተኩ ተደረገ። ምክንያቱም የኋለኞቹ፣ ሰነፍ፣ ስሜት የሌላቸውና በአጠቃላይ ለማስተዳደር የማይመቹ ሆነው ስለተገኙ ነው።

በጣም አዋቂ ከሆኑት በቅሎ መሪዎች መሀል ጀማዳርና ዱፋደሮች ተመለመሉ።

የጓዝ መስመሩ መኮንኖች፣ ከህንድ ሬጅመንት በወዶ ፈቃደኝነት ለዚህ ሥራ የመጡ ናቸው። በሌሎቹ፣ እነዚህ ሰዎች የሚከፍሉትን መሰዋትነት ግስተዋል ባልቻሉ ሰዎች፣ በጣም ከሚበደሉት ወገኖች ናቸው።

በቀላሉ መታየት እንደሚቻለው፣ በሥራቸው ባህሪ፣ ዙላና ሰናፌ ላይ ያየሁት አይነት ድከመት የለባቸውም። ነገር ግን ውነተኛ መኮንኖች፣ ለግዳጃቸው በሙሉ ልባቸው የተሰለፉ፣ ጥሩ ነው ብለው ላመኑበት ነገር ልባቸውንና ኑበላቸውን የሠጡ ናቸው። ሁልጊዜ ኮርቻ ላይ ሆነው ወዲያና ወዲህ ከእንዱ ቡድን ወደ ሌላው እየተመላለሱ፣ አዳዦቹን መገፋፋት፣ ግስገድድ እንዲያም ሲል በማሰፍራራት በቅሎ መሪዎቹ በየተመደቡበት እንዲገኙ ያደርጋሉ። እያንዳንዱን ምሽትም በጊዜ ሳይተኙ ያመሻሉ፤ ይህም በሀገሩ ሁኔታ ምክንያት የሚጠበቅ ነገር ነበር።

በዙላና በሰናፌ መሀከል ያለው መንገድ ተሸከርካሪ ማሳለፍ የሚችል እንዲሆን ሲደረግ፣ ወዲያውኑ የማጓጓዣው መሰመር ከቦምቤ በመጡ ወይፈኖችና ከማልታ በመጡ የበቅሎ ጋሪዎች እንዲጠናከር ሆነ። ነገር ግን ይህ ወቅታዊ የሆነ እርዳታ ቢኖርም ማለፊያው ጠበብ ያለ ነበር፤ ከቆላማው አካባቢ የበቅሎ ጭነቶች መውደቅ ጀመሩ፤ ለጊዜው በርከት ያሉት ከኤደንና ከፔርሽያ የመጡ ግመሎች እንኳን ቁጥራቸው እያነሰ መምጣት ጀመረ። የመጀመሪያ የጋሪዎች ቡድን በቁጥር ሰምንት የሚሆኑ፣ በእንድ የህንድ የወታደር ኢንሰፔክተር የሚመሩ ወደላይ ወደሰናፌ ማለፊያ በተሳካ ሁኔታ በመሻገሩ ምክንያት፣ የእንደዚህ አይነቱ ጭነት መጠን እንዲጨምር የተቻለው ሁሉ ጥረት ተደረገ። ካፒቴን ግራመ፣ ከ102ኛው እግረኛ፣ የዚህ አይነቱን ጋሪ እንዲያዘጋጅና እንዲያደራጅ ተመረጠ፤ በነበረው ጥረት ምክንያትም ውጤቱ በጣም የተሳካ ሆነለት።

ጋሪ የሚጎትቱ በቅሎዎች ቁጥር እየነጠፌ ሲሄድና በእገልገሎት ላይ የነበሩትም በከባድ ሥራ ምክንያት መሥራት ሳይችሉ ሲቀር፣ በጓዝ ክፍል ተቆጣጣሪ ፈቃድ፣ ካፒቴን ግራመ፣ የበቅሎ ጋሪዎችን በመቀየር፣ በቀንበር፣ በኩበቶች የሚጎተቱ ጋሪዎች አደረጋቸው። ይህ ደግሞ ትልቅ የተሳካ ነገር ነው የሆነው፤ ምክንያቱም ሀላፊ የነበሩ ሰዎች ጋሪውን መጎተት የሚችሉ የቀንድ

ከብቶች ከሀገሩ ተወላጆች መግዛት ስለሚችሉ ነው፤ ስለዚህ በወቅቱ ለአግለግሎት የሚውሉ ሰድስት መቶ ጋሪዎች ነበራቸው::

የከብት ህኪሞች ከፍል፣ ለጠቅላይ ዕዝ ቢሮው የጭንቀት መንሥኤ ነው የነበረው:: ከቦምቤይ ሲነሳ፣ ይህ ከፍል በሚያሳዝን ሁኔታ የተሟላ አልነበረም:: ያም ሆኖ፣ ከጣልያንና ከፈረንሳይ ከብት መሪዎች መህከል ከስምንት አሰከ አሰር የሚሆኑ፣ የከብት ህክምና የመጀመሪያ ደረጃ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ተሰበሰቡ:: ይህ በተራው ለሰርጀኖቹ ትልቅ አርዳታ ነው የሠጠው፤ አብዛኞቹ ወጣት የነበሩና በቅርቡ ወታደራዊ አገልግሎት የገቡ ነበሩ፤ ቢሆንም በነበራቸው ከፍተኛ ጉልበት እና ለመሥራት በነበራቸው ፈቃደኝነት መልካም አገልግሎት ነበር የሠጡት:: አነዚህ መኮንኖች በቀጥታ በሰርጀን ላምብ ስር ነበሩ፤ የሠርጀኑ ሀላፊነት ደግሞ ታለቅ ነበረ፤ በመጀመሪያዎቹ አካባቢ፣ ለ30ሺ አንሰሳት ሃላፊ ሊሆን አየቆየ ደግሞ ቁጥሩ ወደ 53ሺ ከፍ ብሎ ነበር:: እናም ከአሰር ሰርጀኖች ብቻ ነበር ርዳታ ማግኘት የሚችለው:: አነዚህ ሰዎች ደግሞ በነበረው ሁኔታ ነው መሥራት የሚችሉት፤ በጣም ያልተለመደ ሥራም ነበር:: ራሳቸው መድሀኒቶችን በየጊዜው መቀመም ነበረባቸው፤ ከዛም መድሀኒቶቸን መሰጠት፤ የታመሙ ከብቶች ማጠብና ቁሰላቸውን ማከም፤ ሰለዚህ ለራሳቸውም ረዳት ያሰፈልጋቸው ነበር::

ለጉዞው የሚሆኑ በቂ ቁጥር ያላቸው ከብቶችን ማቅረብ ብዙ ጉልበትና ወጭ ይጠይቃል:: በተለያዩ ቦታዎች ያሉ የአንግሊዝ ቆንስላዎች፣ ማላጋ አሊካት፣ ካዲዝ፣ ባርሰሎና፣ ጀኖአ፣ ትሪፖሊ፣ ቤይሩት፣ ኮንሰታንቲኖፕል፣ ሰሜርና፣ ጂብራልታር አና በማልታ የሚገኙ፣ በቅሎዎች እንዲያዘጋጁ ትዛዝ ተላለፈላቸው:: መኮንኖቹም ከሰርጀኑ ጋር በመሆን ተልከው፣ ወደከብት ማጎሪያው ከሚላኩት ውስጥ፣ ለሥራ የሚስማሙ የጋማ ከብቶች መመርመርና መምረጥ ነበረባቸው:: በአንግሊዝ ውስብስብ ባለው የዲፓርትመንቶች መንግሥት መሠረት፣ ከሚያሰፈልገው በላይ ቁጥራቸው በርከት ያሉ መኮንኖች ያሰፈልጉ ነበር፤ በዚህ ምክንያት ሁሉም ነገር ውድ ነው የሆነው::

በተቻለ መጠን፣ ወደፊት የሚላከውን የጓዝ መጠን ለማፋጠንና በዝቅተኛው ቦታ ያለውን የማጓጓዣ መሰመር ለማገዝ፣ ከዙላ አሰከ ቁማይሌ አጠር ያለ የባቡር ሀዲድ ተሠራ:: ይህ በተራው፣ በዙላ ባህር ዳርቻ ጋማ ከብቶች ሊቆዩ የሚችሉበትን ሁኔታ መከላከል አስችሏል፤ አለበለዚያ ቦታው ልከ አንደደረሱ ለከብቶቹ የሕየወት ማለፍ ምክንያት ነው የሆነው:: የቀንድ ከብት ጋሪዎች በሞቃታማው አሸዋ ሊጉተቱ የነበረውን ሁኔታም ቀይሮታል::

መርከቦቹ የጫኑትን ጓዝ ወደቡ ላይ አንዳራገፉ ወድያውኑ፣ ኩሊዎች የባቡር ፉርጎዎች ላይ ከጫኑ በኋላ፣ ባቡሩ፣ የአስራ ሁለት ኪሎሜትር ርቀት፣ ወደ ቁማይሌ ጣቢያ ይወሽዳል:: ሰለዚህ ቁማይሌ ሰፋት ያለው የጓዝ

መከማቻ ነው የሆነው። የነበረው አሰራር፣ ሁለት ወይም ሶስት ሙቶ ፉርጎዎች በአንድ ጊዜ አንዲጫኑ ሆኖ ነው፤ ከዚያ በኋላ ወደ ሰናፈ፣ ከዛም ወደ አዲግራት መንገዱ ጥሩ ነበር። ሀዲዱን ለመስራት የተጠቀሙባቸው ብረቶች ቀላል ነው የነበሩት፤ ማለትም 30 ፓውንድ በያርድ፣ ወይም 25 ቶን በማይል ክብር። የሚዘረጉት ሀዲድ መስመሮች ደግሞ 6 ጫማ ርዝመትና በውፍረት እንደ እራቶኛ ኪየቢከ በዳያሜትር ነበር። የነበሩት ሶስት ባቡሮች በጣም ደካማና የሚንገጫገጩ ነበሩ፤ ቢሆንም ለተመደቡበት ሥራ የተመቹ ነበሩ። በዚህ ሁኔታም፣ በአንድ ሰአት ውስጥ፣ ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት የሚሆኑ የጭነት ፉርጎዎች ከዙላ ወደ ቁማይሌ መጎተት ይችላሉ።

ለሁሉም፣ ለጀኔራል መኮንኖችና ለሌሎችም የመካዝን ተቆጣጣሪዎች ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው ቴሌግራፉ ነበር። የአንድ ነገር አጥረት ካለ፣ ቡቴሌግራፉ፣ ሰናፈ ወይም ቁማይሌ ላለው ተቆጣጣሪ መልከት ይላከና የጎደለው ነገር በሁለት ወይም በሶስት ቀናቶች ውስጥ ይላካል። እንዲሁም፣ ቁጥታ ከግንባሩ የሚገኘው ዜና፣ መልከት ለሚያመላልሰው መርከብ እነሰሊ ወደብን ከመልቀቁ በፊት ሊደርስ ይችላል።

የእቢሲኒያ ዘመቻ ሲደራጅ፣ የታለመው የቴሌግራም መስመር፣ በቀይ ባህር ዳርቻ ከሱአኪም ተነስቶ በግብፅ ደንበር አድርጎ አሰከ አነሰሊ ወሸመጥ ሕንዲዘረጋ ነው። ከሱአኪም ወደ ካይሮም መስመር መዘርጋት ይቻላል፤ ያም ከሱዌዝ፣ ካይሮና አለከሳንድሪያ መስመር ጋር ያገናኘዋል። ነገር ግን ይህንን ለመዘርጋት የሚያስፈልገው የግንባታ ሥራ ከብደት፣ የእንግሊዝን መንግሥት ሀሳቡን እንዲተው አድርጎታል።

ከአንጣሎ ወደ መቅደላ፣ እስራ ሰባት ቀናት ይወስዳል፤ ያም በቀን ሁለት ግደሎች ብቻ መጓዝ ከተቻለ ነው። ጀኔራል ናፒየር፣ በሆነ ምከንያት ብቻ፣ መቅደላ መድረስ የሚችለው በስላሳ ቀናት እንደሚሆን አምኗል። ለአስር ሺ ሰዎች፣ ከብት ጫኞችና ካምፕ ሠራተኞችን ጨምሮ፣ ለስላሳ ቀናት የሚሆን ቀለብ ለማጓጓዝ፣ እያንዳንዱ የጭነት ከብት 150 ፓውንዶች ቢሸከም፣ ባጠቃላይ 4ሺ የሚሆኑ የጭነት ከብቶች ያስፈልጋሉ። ጓዝ፣ ድንኳኖች፣ ሮኬቶች፣ የተራራ ከባድ መሳሪያዎችና ጥይቶችን ለማጓጓዝ ከዚህ ቁጥር በላይ እንስሶች ያስፈልጋሉ።

በምንም መንገድ ቢሆን ለጦሩ ቀለብ የሚሆነውን በሙሉ ከሀገሩ መሰብሰብ ይቻላል ብሎ ማመኑ ጥሩ አይሆንም። የአስራ አምስት ቀናት የሚሆን ቀለብ በእጃችን ከያዝን፣ ካለፈው ባገኘነው ልምድ በመነሳት፣ ረሃብን ማስወገድ እንችላለን። በየቦታው መቆም ተደጋጋሚ ሊሆን ስለሚችል የአስራ ሰባት ቀኑ መንገድ ወደ ሁለት ወራትም ሊራዘም ይችላል። ብልጭልጭ የሚለውን ከብር የተሰራውን ጠገራ ብር ካዩ፣ የተወሰነ መጠን ዶቄትና ዳቦ

ከሀገሩ ሰዎች ሊጠበቅ ይችላል። አንባቢ መረዳት እንደሚችለው፣ ልምድ ባለው ጀኔራል ናፒየር ብልህነት ረጋ ባለ አርቆ ማሰብ ችሎታው ያልተጠበቁ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሊጠበቅ ይችላል። በዚህ ብዙ ሁኔታዎች ባሉበት ጉዞ የሆነው ነገር በሚቀጥሉት ገፆች ይገለጣል።

የጀኔራል ናፒየር ስሌት ምን ያህል ትከከል እንደሆነ ወይም ምን ያህል እንደተሳሳተም ይገለጣል። በያዘው ወደ አንድ መቶ ሺ ዶላሮች፣ ስር ሮበርት ናፒየር ብዙ ነገሮች ማድረግ ይችላል። ለአለቆች መደለያ፣ ለመንደር ሀላፊዎች ስጦታ መስጠት አስፈላጊ ነበር፤ በዚህም አስፈላጊ የሆኑ፣ ለቀሰብ የሚሆኑ ሁሉም ነገሮችን ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ ይቻላል። የነበረን ገንዘብ ዶላሩ ብቻ ነበር።

በአቢሲኒያ የነበረው መገበያያ 8 ኢንች ርዝመት፣ አንድ ኢንች ስፋትና አንድ ኢንች ውፍረት ያለው አሞሌ ጨው ነበር። ይህ ደግሞ ሀሽድ ከሚባል ቦታ ነበር የሚቆፈረው። በ1780 ከተሠራው ከአውስትሪያው ዶላር ውጭ፣ ሌላ የመገበያያ ገንዘብ ተቀባይነት የለውም። ከዛን ጊዜ ጀምሮ፣ ዶላሩ ያገሩን የወርቅ ገንዘብ ተክቷል።

ጀኔራል ናፒየር፣ ሩፒ[86] ወይም ሽልንግን ለሀገሩ ለማስተዋወቅ በጣም ጥሮ ነበር፤ ለመስፍኑ ካሳም ደብዳቤ ፅፎለት ነበር፤ ነገር ግን ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑ ወዲያው ነው የታወቀው። በዚህ ረገድ ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ የዕቃዎች ዋጋ አሁን ከተከፈለው በግማሽ ይቀንስ ነበር።

ያገሩ ተወላጆች ለዶላሩ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ ጥንቃቄ በማድረግ ገንዘቡ ላይ ያሉት የመለያ ምልክቶች መታየት የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፤ አለዚያ ሁሉንም አይቀበሉም። ምልክቶቹ ደግሞ፣ የንግሥት ማሪያ ተሪዛ ምስል፣ ጭንቅላቷ ላያ ያሉት አንቁዎችና፣ በትከሻዋ ላይ ያለ አንቁና ገንዘቡ ላይ የታተመው S.F የሚል ፅሁፍ ናቸው። ለለዚህ ሁሉም ገንዘቦች የውኑተኛው መሆን አንዳለባቸው በጣም አስፈላጊ ነበር። ያን አይነቱ ዶላር ደግሞ በበቂ መጠን ስላልነበረ አዲስ መሠራት ነበረበት፤ ስለዚህ፣ ጊዜው ያሰፈ ይህ ገንዘብ፣ 500 ሺ የሚሆን በአውስትሪያ ቪየና በሚገኘው ኢምፔሪያል ገንዘብ መሥሪያ ቦታ ለአቢሲኒያ ዘመቻ ተብሎ በአጣዳፊ ነበር የተሠራው።

ሠራዊቱ አንጣሎ በደረሰ በመጀመሪያው ቀን ጠዋት፣ ጠቅላይ አዛዡን ማየት እንዳለብኝ ወሰንኩ፤ በሁሉም አገሮች ደንብ መሠረት፣ በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኝ ማንም ሲቪል፣ ዋና ቢሮ ድረስ በመሄድ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

---

[86] ሩፒ የህንድ መገበያያ ገንዘብ ሲሆን፣ ሽልንግ ደግሞ የእንግሊዞች ነበር



ማርያ ተሪዛ፣ (ማር ተሪዛ)ጠገራ ብር

አሰካሁን ድረስ ግን፣ ጀኔራሉ ልክ እንደ ጃፓን ሚካዶ[87] ወይም እንደቲቤት ላማ ከኔ የተሰወረ ነበር። በነበረው ከፍተኛ ሥልጣን ምክንያት በጣም የሚከበር ሰለሆነ፣ ሊጣሰ በማይቻል የወታደሮች ዘብ እጥር ተከቧል። ከነዚህ በተጨማሪ፣ የሚያንፀባርቅ የወታደር ዩኒፎርም የለበሱ ከፍተኛ ግዕረግ ያላቸው መኮንኖችም አሉ።

"ጀኔራሉን ማየት እችላለሁ?" በማለት፣ አንድ መልከመልካም ፣ ጠንከር ያለ ሰውነት ያለው የካምፑን ረዳት ካፒቴን ኤሰን ጠየቅሁ።

"የምን ጀኔራል?" መልሶ ጠየቀኝ።

"ሰር ሮበርት ናፒየርን፣ ሰር፣" ብዬ በደፈናው መለስኩኝ።

"እሃ! የተከበሩት ሰር ሮበርት ናፒየርን ማለትህ ነው?" አለ፤ በመጠኑ ቅንድቦቹን ወደላይ ከፍ አድርጎ።

"በርግጥ፣ ሰር፣" ብዬ መለስኩ፣ "አዎ፣ የተከበሩ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ሌፍተናንት ጀኔራል፣ የአቢሲኒያ ዘመቻ ሠራዊት ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ አሁን በአቢሲኒያ የሚገኙትን"

"አሁን ልታየው አትችልም" አለ፤ ፈዘዝ ያለ የፈገግታ መልክ በፊቱ ላይ እያሳየ፤ "ቁርሰ ላይ ነው።"

---

[87] የጃፓን ንጉሠ ነገሥት

ማምሻውኑ አንደገና ሞከርኩ፤ አሁን ደግሞ፣ እጅ ለመንላት ከመጡ ከተወሰኑ የአገሩ ባላባቶች ጋር ነው።

በነጋታው ጠዋት አንደገና ሞከርኩ፤ አለመታደል ሆኖ፣ ዛሬም ቁርስ ላይ ነው። ከሰአት በኋላ ስሞከር፣ እንቅልፍ ላይ ነው።

በሶስተኛው ቀን፣ ጠዋት ሶስት ሰአት ላይ እንደገና ሞከርኩ፣ ነገር ግን አዛዡ ማታ ሊሰራ ስላደረ እንቅልፍ እንደተኛ ነው።

ከሰአት በኋላ፣ ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ እንደገና ጠቅላይ ቢሮ ስሄድ፣ መከሰስ አየበላ ነው።

በአራተኛው ጠዋት፣ ከጠዋቱ አምስት ሰአት ሊሆን፣ የካፒቴን ኤስ ድንኳን ለሰባተኛ ጊዜ ቀረብኩኝ፤ ሰር ሮበርትን ለማየት ፈቃድ እንዲሠጠኝ ነበር።

"የተከበረው ሰር ሮበርት ናፒየር ሥራ ላይ ነው?" ብዬ በትህትና ጠየቅሁ።

" አሃ! ስምህን ማን ልበል?" ካፒቴኑ ጠየቀ።

" ካርዴ ይሽውና፣ ሰር!"

"ህም! አዎ፣ ሚስተር ሲታንሊ፣ የኒውዮርክ ሄራልድ ዘጋቢ። መልካም ፈቃድህ ከሆነና ብትቀመጥ፣ ሄጄ፣ ሰር ሮበርትን አነግራለሁ።"

ከተቀመጥኩ በኋላ፣ ጠቅላይ አዛዡ በምን አይነት ሁኔታ አንደሚቀበለኝ ማሰብ ጀመርኩ።

"ሰር ሮበርት ናፒየር ሊያይህ ፈቃደኛ ነው፣ ሰር!" አለ ካፒቴኑ።

ይህንን መኮንን አየተከተልኩ፣ እንደ አንግዳ መቀበያ ከፍል ወደሆነ ድንኳን ውስጥ ገባሁ። ድንኳኑ ብጫ ከጥጥ የተሠራ ከፈፍ ያለው ሲሆን፣ ወለሉ ላይ የፔርሽያ ምንጣፍ ተዘርግቶበታል፤ ይህ ከፍል፣ ከውሥጠኛው ጋር ከሀር በተሠራ መጋረጃ ተከልሏል። ጋዜጣና ዶሴዎች በተደረደሩበት ጠረጴዛ አጠገብ፣ ያልተቆለፈ ዩኒፎርም የለበሰ ሰው ተቀምጧል፤ ግራጫ ቀለም ያለው የጭንቅላት ፀጉርና ፂም ሲኖረው፣ በርጋታና በፀጥታ፣ ልከ አርሻውን ሲያይ ውሎ የሚጠበቀው ምርት ጥሩ በመሆኑ ደስተኛ የሆነ ገበሬ አይነት ነው።

"ሚስተር ሲታንሊ፣ ለር ሮበርት" በማለት ካፒቴኑ አስተዋወቀን።

በዚህ ድምፅ፣ ረጋ ብሎ የተቀመጠው ትልቅ ሰው ከመቀመጫው ተነስቶ ትውውቁን በማፅደቅ፣ ወዳጅነት በሚያሳይ ሁኔታ ጭንቅላቱን ጎንበስ በማድረግ በአጭ በማሳየት አንድቀመጥ ጋበዘኝ።

"ፍቀድልኝና፣ ሰር ሮበርት፣ ካንተ ጋር አንድተዋወቅ የያዝኳቸውን ደብዳቤዎች አንድትመለከታቸው ላላይህ።"

ደብዳቤዎቹን ካነበበ በኋላ፣ አኔን በማየቱ ደስተኛ መሆኑን ገልፆ፣ መምጣውን ተከትዬ በመምጣቴ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ተደርገውልኝ እንደሆነ ጠየቀ።

"የለም፣ ጌታዬ፣ አልተደረገም፣" አልኩኝ። "ከሆንድ የውጭ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ በቴሌግራም የሚያስፈልገኝ ሁሉ እንደሚደረግልኝ ተነግሮኝ ነበር። ነገር ግን፣ ተደርጎልኛል ብዬ መናገር አልችልም። ያለኝ ነገር ቢኖር፣ ዙላ ላይ የተሠጠኝ የጓዝ መጫኛ ኢጋስስ ነው። ዙላ ስደርስ፣ አንተ ወደ መቅደላ ከፍጥነት ገስግስህ ትሄዳለህ ብለው በነገሩኝ ሰዎች በስህተት ተመራሁ። በዚህ ምክንያት ድንኳን አያስፈልገኝም አልኩኝ፤ ነገር ግን እንደተሳሳትኩ ወዲያው ነው ያወቅሁት እናም አንድ እንዲሠጠኝ አመልክቼ ነበር ግን አልተሳካም። ድንኳንና፣ የጭነት ከብት እንዲሠጠኝ ብታስደርግልኝ፣ እንደሚለማማኝ አስባለሁ።"

"ክሰናፌ እንዴት ብለህ መጣህ?" በማለት በትህትና ጠየቀኝ።

"ከካርቴን ስመልፈንገስ ጋር። አሰና እኔ እንድ ላይ፣ በእንድ ድንኳን ውስጥ ነው የምንኖረው።"

"እንዴት! ካርቴን ስመልፈንገስ ካምፕ ውስጥ አለ?" በመደነቅ ነበር የጠየቀኝ።

"እዎ፣ ሰር፣ እሁን ትቸው መጣሁ።"

"ህምም ይህንን እንኳን አላወቅሁም ነበር። ወዳንተ ጉዳይ እንመለስና፣ በርግጥ፣ ላንተ ለብቻህ የሚሰጥ ድንኳን የማዘጋጅ አይመስለኝም፤ ይህም ወደ መቅደላ በፍጥነት ለመገስገስ ስላሰብኩ ነው። ሁሉም መኮንኖች በአንድ ድንኳን ውስጥ እንዲኖሩ ይጠበቅባቸዋል፤ ከጓደኞችህ ጋር አብርህ ለመኖር የሚመችህ ከሆነ፣ ከሁሉም የተሻለ እቅድ ይሆናል። ለማንኛውም፣ ድንኳን የግድ የሚያስፈልግህ ከሆነ ግን፣ የሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ ለሲቪል አዋቂ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር አንዲሸጥ ፈቃድ ተሠጥቶታል። ፈረለም ቢሆን፣ ከዚህ ከነዋሪዎች መግዛት ትችላለህ። ቀለብን በተመለከተ ግን፣ ኮሚሳሪያቱን ትዛዝ ልስጥ አችላለሁ እናም በየወሩ አለዚያም እነሱ ሲጠሩህ ማግኘት ትችላለህ። ለእንግሊዝ ዘጋቢዎች ከማሳየው በላይ ላንት የሚያደለ ሁኔታ ማሳየት የለብኝም። ነገር ግን ማንኛውም እነሱ የሚያገኙት ጥቅም ላንተም ይደረጋል። የምመክርህ፣ ቀለል ያለ ጓዝ አንድትይዝ ነው፤ ነገ፣ ረዳት ጀኔራሉ፣ ጓዝ ከሰባአምስት ፓውንድ በታች እንዲሆን ትዛዝ ያስተላልፋል። በዚህ ሁኔታ እንተም የሚያስፈልጉህ ነገሮች በሙሉ በሁለት ፈረሶች ብቻ እንዲሆንና ድንኳንም ብትጋራ ይሻላል።"

"አመሰግናለሁ፣ ጀኔራል:: መልካም ፈቃድህ ሆኖ ልጠይቅህ የምመኘው ነገር ደግሞ፣ ፖለቲካውን በሚመለከት የመረጃ ሥራዎችን ጠቅለል ያለ ነገር ማየት እንድችልና፣ ለሌሎች መገናኛ መላክ ይቻላል ብለህ የሚሰማማ ነው የምትለውን ነገር ማካፈል እንድችል፣ ምክንያቱም ከኒው ዮርክ ሄራልድ፣ እንተ የምትሠጠኝን ዜና ወይም አኔ የማገኘውን እንዳስተላልፍ ይጠበቅብኛል::"

"በርግጥ፣ ደስ ይለኛል፤ ረዳት ጀኔራሉ ወይም የፖለቲካ ፀሐፊው ሰሌሎቹ ዘጋቢዎች የሚሠጡትን መረጃ ማየት ትችላለህ::"

ከመለያየታችን በፊት፣ ጀኔራሉ በደግነት፣ የያዝኩት ገንዘብ ካነሰኝ፣ በድራፍት መልክ አስፈላጊ የሆነን ገንዘብ ለመሥጠት እጁን ዘረጋልኝ እናም ማምሻውን ለአራት ጋበዘኝ::

ልክ ከምሽቱ አንድ ሰአት ላይ፣ በሰር ሮበርት ናፒየር የተጋበዙ እንግዶች በሙሉ በካምፑ ውስጥ በሚገኝ ረዥም ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰብሰበዋል:: ጠረጴዛው ላይ፣ ስሀኖች፣ መጠጫዎች፣ ብርጭቆዎች፣ የወይን መያዣ ጠርሙሶች እና የማጣቀሻ ምግብ መያዣዎች ሞልተውበታል:: ስመልፈንስም የድግሱ አባል ነበር:: በሚደነቅ ሁኔታ በብዛት ከየሀገሩ የሰበሰባቸውን ሜዳሊያዎች አድርጓል:: ከመቀመጣችን በፊት፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ እለት ከለት የሚለብሰውን ጠቅር ያለ ዩኒፎርም ለብሶ መጣ:: እሱ እንደመጣ ትውውቅ ተደረገ:: የተራራ ከባድ መላሪያ ከፍሉ ኮሎኔል ፔን፣ የከፍው ሁሳሮች ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ካፒቴን ስፒዲ ከኒውዚላንድ የአንግሲዝ ሠራዊት አስተርጓሚና የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት የቀድሞ ኮማንደር፤ ከብሪታንያ ሙዚየም አርኪዮሎጂስቶች ሚስተር ሪቻርድ ሆልምስ፣ ካፒቴን ኤስ፣ ሎርድ ሲ-ኤች፣ የካምፕ ረዳት ካፒቴን ሃርደን፣ አለም አቀፋዊው ካፒቴን ስመልፈንስ እና አኔ ራሴ ጨምሮ፣ ከትውውቁ በኋላ ተቀመጠን:: ከግዙፉ ጀይንት፣ ከካፒቴን ስፒዲ አጠገብና ከሰር ሮበርት ናፒየር ፊት ለፊት የመቀመጥ ዕድሉ አጋጠመኝ::

እያንዳንዱ ሰው የራሱን መጠጫ፣ ቢላዋ፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ናፕኪን ይዞ መጥቷል:: ሰሀኖችና ሌሎች መገልገያዎች የጀኔራሉ ነበሩ:: ዋና አሳለፊው ምክትሉና ሌላውም ሠራተኛ በደንብ የሠለጠኑ ነበሩ፤ እያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ነገር ያውቃሉ፤ እናም ጠረጴዛው ዙሪያ ያለውን ጨዋታ በማያደናቅፍ መንገድ ፀጥ ባለ ሁኔታ የሚያሰፈልገውን ነገር ያቀርባሉ:: ሾርባው መጣ፤ የሚደነቅና ጠቀሜታ ያለው ምግብ ሆኖ የተገኘው፤ ከስንቅ ከፍሉ የአትክልት አይነቶች የተሠራ ነበር:: ሾርባውን በምንመገብበት ጊዜ ለአመል ያህል አንኳን ድምፅ አልተሰማም::

ሾርባው እንዳለቀ፣ ዋናው ምግብ ነጭ ልብስ በለበሱ ንፁህ በሆኑ ሥራተኞች ቀረበ፤ ሰዎቹም ወደኋላ ለጠጥ በማለት ወንበራቸው ላይ ተደገፉ፤ ለሚቀጥለው ምግብ አዲስ ጉልበት ለማግኘት አረፍ አያሉ ነበር።

በካምፑ ውስጥ የሚሠሩት ሻማዎች፣ ጠረጴዛው ዙሪያ ከድንኳኖች ብጫ ከፈፍ ጋር የሚስማማ ደብዘዝ ያለ ብርሃን ያፈልቃሉ። ከውጭ በኩል ቡም ቡም የሚለው የታምቡር ድምፅና ቀጠን ያለ ከፍሉቶች የሚወጣው ድምፅ ይሰማል። አሁንም አሁንም "ዘብ ቁም፦ ሁሉም ደህና ነው!" የሚል ድምፅ፤ ቢጂኤራሉ ድንኳን ከተዘጋጀው ተወዳጅ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር፣ ጣዕመ ዜማ የሌለው ጩኸት ይሰማል።

የህንድ፣ ሽፈን ያሉ በውስጣቸው ሌላ የምግብ አይነት የያዙ ዳቦዎች፣ ኮተሌቲ፣ ከጥጃ ሥጋ የተዘጋጁ ምግቦች ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ከፊት ለፊታችን ተደረደሩ። በመሀከላችን ምንም አይነት ቀዘቃዛ ግንኙነት ስላልነበረ፣ አንዱ ሌላውን በመርዳት ከተለያዩት የምግብ አይነቶች ያነሳ ነበር።

ንግግራችን ሞቅ ያለም አልነበረም፤ እኔ ራሴም ብሆን፣ አራት ሲበላ ብዙ መወራት አለበት ብዬ አላምንም፤ ምግቡን ያቀዘቅዘዋል፤ የምግብ ጣዕም ያሳጣል፤ እንዲያውም ዋናው ምግብ ሠሪ የሰራውን ምግብ የሚያናንቅ ይመስላል። ሁሉም በቦታው የነበሩት ሰዎች የህንድ ምግብ ወዳጆች ስለነበሩ፤ እንደ ተወላጅ ሰው የቀረበውን ታላቅ ምግብ በደንብ አትኩሮት ሰጥተውታል።

ከዛ ቀጥሎ፤ ከሥጋ ጋር የተቀቀለ አትክልት፣ የድንች ኬክ፣ ቅጠላ ቅጠልና የሥር አይነቶች፣ ኮቴሌት እና በወይን የተጠበሰ ሥጋ ቀረበ፤ ሁሉም ቢሆን የሚገባውን አትኩሮት ነው ያገኙት። ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩ የሥጋ መብሎችም ቀረቡ፤ እነዚህም ቢሆን በጣም የሚመሰገኑ ምግቦች ነበሩ።

ሌሎች ከተበሉ በኋላ፣ ለማሳረጊያ፣ ከእርድ የተሠራ ሾርባና ሩዝ ያለበት ምግብ ቀረበ፤ ይህም፣ በነበረው፣ ለስለስ ብሎ በሚያቃጥል ጣዕሙ፤ ከሚገባው በላይ ምስጋና ከባለሚማሞቹ ሰዎች በኩል እንዲያገኝ አድርጎታል። እንደኔ አስተያየት ከሆነ፣ ከእርድ የተሰራው ምግብ የተረገመ ነበር፤ ስቀምሰው የፈላ አሳት ስሜት ነው የሠጠኝ። እንደሚባለው ከሆነ ለህጢያተኞች የሚቀርብ ድርሻ ነው። ምግቡ ሲነሳም፣ በዛ የተሰበሰበውን ሰው አንደበት የከፈተው ይመስላል።

"ካፒቴን ስመልፈንገስ፣ ካንተ ጋር የአቢሲኒያ ጠጅ ለደስታ!" አለ ሰር ሮበርት ናፒየር ምንም አይነት የሰሜት ምልክት ሳያሳይ።

"ከፍ ካለ ደስታ ጋር፣ ሰር ሮበርት፣" ካፒቴኑ ለስለስ ባለ አንደበት በመመለስ፣ ቀጥሎም፣ "የጠጅ ከፍተኛ አድናቂ ነኝ አለ።"

ባንድ ጊዜ፣ ሁላችንም መጠቻችን ወደ ጀኔራሉና ወደ እርሰ በርሳችን ካነሳን በኋላ፣ እያንዳንዳችን ያገሩን መጠጥ ቀንድ ዋንጫ ሙሉ የሚሆን ፉት ብለን በእርካታ ጠጣን።

ሁሉም በዘመቻው የሚታወቁ ወደፊትም ሰንቀጥል የሚጠቀሱ ሰዎች ሰለሆኑ ሰለ እያንዳንዳቸው መጠነኛ ገለፃ ማድረግ ከርዕሰ የወጣ ነገር እንደማይሆን ተሰፋ እለኝ።

ጠቅላይ እዛዥ ጀኔራሉ፣ የሃምሳ ወይም የሃምሳ እምሰት ዕድሜ ሲኖረው ፊርጠም ያለና ጠንካራ ነው። ፊቱ፣ ደግነት የሚያሳዩ ሰማያዊ አይኖች ያሉበት ሲሆን፣ የሚያሳየው የደግነት ባህሪም በነዚህ አይኖች እማካኝነት ይበራል፤ በከንፈሮቹ ዙሪያ የሚታየው የማያባራ ፈገግታም ሌላ ነገር ነው። ለሁሉም ሰው፣ ሰር ሮበርት በጣም ዝም ያለ፣ ደግና ሰው ወዳጅ ነው። እንዳንድ ጊዜ በድምፁ መህል ሰርጎ የሚሰማ የእከብሮት አይነት እንደበት አለው፤ በዚህ ጊዜም ከሌላ ጊዜ ይልቅ ብዙ ቃላት ይናገራል።

ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ትከከለኛው የወታደራዊ መኮንን ነበር፣ ራሱን ከፍ የሚያደርግ፣ ነገር ግን ምንም ጊዜ ቢሆን ትሁት ነበር፤ የማያባራ ጥንካሬ የሚያሳይ፣ ሀቀኛ፣ መልካም ባህሪና በጣም ጤነኛ ሰው ነው።

ኮሎኔል ፔን፣ በወታደራዊ ጉዳይ ልምድ ያለው ሰው ቢሆንም በዕድሜ ግን ገና ወጣት ነው። ንፁህ፣ ሰው አከባሪነትና የማይደከም ሀይል ዋና ባህሪዮቹ ናቸው።

ካፒቴን ቻርለሰ ሰፒዲ በውነቱ ግዙፍ ሰው ነው። እጆቹና እግሮቹን ሄርኩሊሰ እንኳን ቢሆን የሚቀናባቸው እይነት ናቸው። ቁመቱ ሰድሰት ጫማ ከስድሰት ኢንች ነው። "ረዥም"፣ የሚባለው ቅፅል፣ እሱን በሚመለከት፣ የሰውየው ምኑም ላይ መለጠፍ የሚቻል ነገር ነው። ረዥም እግሮች፣ ረዥም እጆች፣ ረዥም ፂም፣ እንዲያው በሁሉም ነገር ረዥም፣ በቅርፅ፣ በሁኔታ፣ ከእርቆ ማየት መቻል በሰተቀር፣ በርግጥ በቅርብ ብቻ ማየት ሰለሚችል ሁልጊዜም ቢሆን መነፀር ማድረግ ነበረበት። ጎላ ያሉት የፊቱ ገፅታዎች፣ ከፍና ወጣ ያሉ የጉንጭ እጥንቶች፣ ዘቅዘቅ ያለ ቅንድብና፣ ቀይ የጎፈረ ፂም፣ ደግነት ያሰባቸው ሰማያዊ እይኖቹ የቆራጥነት ገፅታ ከሚያሳየው እፉ ጋር የሚነፃፀሩ ነበሩ።

ሎርድ ሲ ኤች፣ የህያ አሙት ወጣት፣ ወንዳ ወንድ ደረተ ሰፊ፣ ቁመት ያለውና ደንስ ያለ ሰው ነው።

ሚለተር ሆልመሰ፣ የብሪትሽ ወዶ ገብ ወይም ፈቃደኛ ሰው ነው፤ በተገኘው እጋጣሚ ሁሉ የብሪታንያን ከብር የሚያሰጠብቅ ነው። ወደ

አቢሲኒያ የመጣውም ፅሁፎችና ጥንታዊ የሆነ ስብሰቦችን ለብሪታንያ ሙዝየም ለመስብስብ ነው፡፡

"አህ! ጥሩ መጠጥ ነው፣" ሰፒዲ ነበር፤ በሚያሳዝን ሁኔታ እየተነፈስ፣ ጠጁን ከፂሙ አየጠረገ ነበር፤ "በጣም ጥሩ መጠጥ ነው አላለሁ፡፡"

"ሚሰተር ስፒዲ፣ የሀገሬው ሰዎች አንዴት አድርገው ነው የሚሠሩት?" ጄኔራል ናፒየር ነበር የጠየቀው፡፡

"መልካም፣ ጄኔራል፣ በዚህ ሀገር ጠጅ ለመሥራት በጣም የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ በዚህ አውራጃ፣ አንድ ኳርት የሚሆን ማር አምስት ጋሎን በሚይዝ አንስራ ውስጥ ያስቀምጡና፣ አንድ ኳርት የሚሆን ጠንካራ አረቂ ጨምረው፣ እንስራውን በውሃ ይሞሉታል፣ ከዛም ለአምስት ቀን ያስቀምጡና፣ ሁሉም ነገር ሲበስል ለመጠጥ ይደርሳል፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ጥሩ መጠጥ በመጥመቅ ታወቂ ነው፤ ነገር ግን በጠንካራ አረቂ ያጠነከረዋል፡፡"

ከምግብ በኋላ የሚቀርበው ማጣጣሚያ (ደዘርት) ከዚህ የሚያስደንቅ ወግ በኋላ ቀረበ፤ ሥለ ጣፋጭ ምግቦቹ አየተወራ አያለ፣ አዛዡ መለኛ በሆነ መንገድ ለውይይቱ የሚሆኑ ርዕሶችን ይከፍት ነበር፡፡

ከሚሰተር ሆልምስ ጋራ ስለ መንፈሳዊነት ውይይት በሰር ሮበርት በኩል ተጀመረ፤ ውይይቱ አየቀጠለ ሲሄድም ጄኔራሉ ስለዚህ ሚስጥራዊ ሳይንስ ብዙ የሚያውቅ መሆኑ ታወቀ፡፡

ቡና ሲቀርብና፣ (የሰር ሮበርት ስጦታ) ሃባናዎች[88] ሲለኮሱ፣ ጄኔራሉ ሌላ ርዕስ ከፈተ፡፡ ውይይቱን ሞኖፖላይዝ አድርጎ አንደያዘ መወሰድ የለበትም፤ በተቃራኒው ነው የነበረው፡፡ ርዕሱ በአንድ ነገር ብቻ የተወሰነ አልነበርም፤ ያቀፈው፣ ሥነ ፅሁፍ፣ ስዕል፣ የሸክላ ሥራ፣ ቅርፅ፣ የቋንቋ ጥናትንም ነበር፡፡ ከነዚህ ርዕሶች ቀስ ብለን በየደረጃው ወደ መንግሥት ጉዳዮች ተሻገርን፤ በዚህም፣ መተግበር የማይችሉ በሚደነገጉ ህጎች የሚፈፀሙ ስህተቶች በመልከአ ምድር የተያያዙ ለመሆናቸው፤ በንጉሣዊ መንግሥቶችና በሪፓብሊክ መሀከል አንፃራዊ ማበላለጥን ጨምሮ ነበር፤ ጄኔራሉም፣ ከጥንታዊ ህግጋቶችና ከዘመናዊ ድርሰቶች የተለያዩ ጥቅሶችን በማቅረብ የራሱን አመለካከት አጥብቆ ያሳያል፤ በርግጥ ለአንግሊዝ ኮንሰቱትሽናል ሞናርኪዝም የበላይነት በማድላት ነበር፡፡

---

[88] ትምባሆ ጥቅል ወይም ሲጋር

ለምዕራፍ ስድስት ተጨማሪ ማስታወሻ

ቁጥር 85፤ አንጣሎ፣ የአንደርታ አውራጃ ከተማ ስትሆን፣ የአፄ ዮሐንስ (አራተኛ) ቅድመ አያት የራስ ወልደስላሴ መዲና ነበረች። ራስ ወልደስላሴ በሚገዙበት ጊዜ፣ ግዛቱ አሰከ ቀይ ባህር ጠረፍ ድረስ ነበር። በዘያን ጊዜ ደግሞ፣ በጎንደር፣ የየጁ ተወላጅ የሆኑት፣ የትንሹ ራስ አሊ አያት ራስ ጉግሳ ነበር የሚገዙት። አንጣሎ፣ የራስ ወልደስላሴ አባት ከራስ ስዑል ሚካኤል ሲሸሹ የተደበቁበት ሥፍራ ነበር። ራስ ወልደስላሴ ሲሞቱ፣ ሰባጋዲስ ወንበሩን ሲይዝ፡ ሥልጣኑ ወደ አዲግራት ተዛወረ። ሆኖም ከየጁ ኦሮሞ ባለባቶች ጋር የነበረው ግብግብ ቀጥሎ፣ የራስ ጉግሳ ልጅ፣ ራስ ማርዬ፣ ከሰባጋዲስ ጋራ ባደረገው ጦርነት ማሸነፉን ሳያይ ሲሞት፣ የማርዬ ሰዎች ደግሞ ሰባጋዲስን ይገድላሉ። ራስ ማርዬን የገደለው የሰባጋዲስ ልጅ ሐጎስ ነበር። አሱም ወዲያው ተገደለ። ይህ ደግሞ ለሰሜኑ መሰፍን፣ ለደጃች ውቤ መጠናከረ ኢጋጣሚውን ስለፈጠረ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትግራይን ጠቅልለው ለመግዛት አስችሏቸዋል። ከለመንት መርካም ሲዘግብ፣ ራስ ወልደ ስላሴን የመስለ ጥሩ ሻሎ ታይቶም አይታወቅም ይላል። በአስተዳደራቸው በጣም የሚወደዱ ነበሩ፣ የሚታሙበት ነገር ቢኖር በስስታምነት ነው። ነገር ግን ለድሃም ሆነ ለሌላው በሚያሳዩት የደግ አስተዳደር ስስታምነቱ አንደ ቂም አልተያዘም። ዋና ከተማቸው አድዋ ቢሆንም፣ ራስ ወልደ ስላሴ ግን አንጣሎን ይወዱ ነበር። የትንሹ ራስ አሊ አጎት፣ የራስ ማርየ ጦር የነበረውን የሰባጋዲስን ሀይል ማዳከም ብቻ ሳይሆን፣ የትንሹ ራስ አሊ አናት፣ መነን፣ እንደርታና አንጣሎን ለቤልጅግ መንግሥት በ15 000 ማር ተሬዛና በ3ሺ ጠመንጃዎች ለመሸጥ ተስማምተው ነበር። (የመጨረሻው ከስቤን ሩቢ ንሰን)

ምዕራፍ ሰባት

ስመልፈንገስና እኔ ተለያዬን፣ የእንግሊዝ ጋዜጦች፣ ሃላፊነት የጎደለው ትንበያቸው፣ የእንግሊዝና ሀንድ ሠራዊት መከፋት፣ የተከፉት ቴዎድሮስ፣ አሳዛኝ ምርኮኞች፣ የፖለቲካ መሪ፯ ሥራዎች፣ የስር ሮበርት አመራርና የዲፕሎማሲ ችሎታ፣ ስለ እንቅስቃሴው ማዝግም ማብራሪያ፣ የእስያ ዝሆኖች በአቢሲኒያ፣ የማጓጓጉው መስመር

ባለፈው ምዕራፍ ከተዘገቡት ሁኔታዎች በኋላ፣ ከወድ ጓደኛዬ ከስመልፈንገስ ጋር ያለንን ግንኙነት ማቆሙ ጠቃሚ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ስለዚህም የሱን ድንኳን ገዘሁና፣ ወደ ጠቅላይ እዙ አካባቢ በመሄድ የስንቅና ትጥቅ ከፍሉ ሀላፊ በመደበኝ ስፍራ ድንኳኔን ከካፒቴን ስፒዲ ድንኳን አጠገብ ተከልኩ።

ከጠቅላይ አዛዡ ፅ/ቤት ካምፕ እራት በኋላ፣ ማለትም በሁለት ሳምንታት የጦሩ በአንጣሎ ቆይታ ጊዜ፣ ወደ ምግብ አዳሪው የሚደረግልኝ ጥሪ ወይም ግብዣ እየተደራረበ መጣ።

የእንግሊዝ ጋዘጤኞች* ቡድን በአቢሲኒያ በበቂ መጠን ነው የተወከለው። ከዘጋቢዎችም የሚደነቁ የተማሩ እዋቂ ሰዎች ነበሩ። የሚደነቁ ስልም በቅናት በማናናቅ መልከም አልነበረም፤ እያንዳንዳቸው፣ በውነት፣ በርግጥ በየራሳቸው የሚደነቁ ሰዎች ነበሩ። ምንም እንኳን በተፈጥሮ ባሕሪያቸው አልፎ አልፎ የሚያለያያቸው ነገር ቢኖርም፣ በጣም በውሱን ጊዜዎች ብቻ ነው ሲቃረኑ የሚታዩት። እንዲያውም በየድንኳኑ ውስጥ ካለው ከእያንዳንዱ የጦር ከፍል ይልቅ በጋዘጤኞቹ ድንኳን ውስጥ ስምምነትና ሰላም ነበረ። የምወዳቸውና የማከብራቸው ሰዎች ስለሆኑ በጦሩ ውሰጥ በጣም የወዳጅነት ስሜት ያላቸውና አመለ መልካም ናቸው ብዬ ባመሰግናቸው፣ እነዚህን ደጋግ ሰዎች እንደወቀስኩ እንዳይቆጠር ተስፋ አደርጋለሁ። (*የእንግሊዝ ጋዜጠኞች የተወከሉት በጓደኞቼ ደ/ር ቻርለስ እውስቲን፣ D.C.L., *Times*፣ ጆርጅ ኤ. ሄንቲ፣ Esq., *Standard*፣ ወ አወን ዋይትሳይድ፣ Esq፣ *Morning Post*፣ አሌክስ ሸፐርድ፣ Esq፣ *Daily News*, .. አዬር፣ *Daily Telegraph*.[89])

---

[89] ከጦሩ ጋር የዘለቁት ጋዜጠኞች፣ (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ምንም አንኳን የጨለማ ትንበያና ውደቀት ቢነገርበትም፣ የዘመቻው ሠረገላ በተረጋጋና በሙሉ ልብ ሁኔታ፣ በዝግታ ግን በርግጠኝነት መንቀሳቀስ ጀመረ።

በአቢሲኒያ በተነገረላቸው በየተራራው፣ በየገደሉና በየሜዳው ሞልተዋል በተባሉት የዱር አውሬዎች ሰለባ የሆኑት በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ።

አንድም ሰው ግን አሰካሁን ድረሰ በተመረዘ ማር ወይም ሌሎች ምግቦች በመብላት የሞተ የለም፤ አንድ ሰው እንኳን የጉድጓድ ውሀ በመጠጣት የተንገላታ ወይም የታመመ የለም።

አንድም ሀውሳ[90] አልተገኝም፤ ሾሆዎች፣ ኢጋሜዎች፣ ወይም የሀዞርቲት ተወላጆች ምንም የጠላትነት ሰሜት አላሳዩም፤ አንዲያውም ተቃራኒ ነው የነበረው። ሰንቅ ከፍሉ መግዛት የፈለገውን ነገር መግዛት ይችል ነበር።

ምንም ኢይነት ጉማሬ የፀሀይ ብርሃን በመከለል መንገዶችን አላጨለመውም፤ የራበው አንበሳ ሆነ፣ አቦሸማኔ በጨለማው ቦግ በሚለው አይናቸው ሰዎችን አላሰደነገጡም፤ የሚያሰፈራው አባብም ብርድልብሳቸን ላይ አልተጠቀለለም፤ የሚያሰጠሉ ብጫ ነጠብጣብ ያላቸው፣ ፒንክ ጭንቅላት ያላቸው ዝምቦችም አልታዩም።

ገዳይ ናቸው የሚባሉት ፀፀ ዝንቦች ከአይናችንም ሆነ ከአአምሮችን ውሰጥ ድራሻቸው ጠፍቷል፤ ዛልትዛልያውም[91] ቢሆን የሚርገበገቡ ከንፎቹን ዘርግቶ በፍጥነት ሾልኮ ሄዷል። ምድሩ ለአይን ውብ ነው፤ ተራራዎችም ቢሆኑ በደግነት ነበር አኖን ቁልቁል ያዩን፤ ውሀው ከኖርቶን ፓምፖች አንደልብ ነበር የሚወርደው፤ አየሩም ቢሆን እንጣሎ ከደረሰን በኋላ ጥርት ያለ ነው የነበረው።

ሆ! የሚገርም ነው! ደፍን አንግሊዝ ተደንቋል። የውሸት ነብዮቹ ከነውሸት ትንቢታቸው የማያባራውን ጩኸታቸውን ማቆም ይኖርባቸዋል።

ከሁለት ወይም ሶሰት ቀን በኋላ ወደፊት አንቅሰቃሴ አንደሚጀመር አጠቃላይ ትዛዝ ተላለፈ፤ በዚህ ትዛዝ ሁሉም ወታደሮች ጓዛቸውን ወደ ሰባ አምሰት ፓውንድ አንዲቀንሱ፣ መኮንኖችም ቢሆኑ ጓዛቸውን ወደ ሰባ አምሰት ፓውንድ አንዲቀንሱና ይዘው የሚሄዱትን ፈረሶች ቁጥር ወደ ሁለት አንዲቀንሱ ተነገረ። በተጨማሪ ትዛዝ አሰራ ሁለት ወታደሮች በአንድ ድንኳን አንዲዳበሉ፣ ሁለት መኮንኖች አንድ ድንኳን አንዲጋሩ ተወሰነ።

---

90 የፀሀፊው ሽሙጥ፤ ስመልፈንስ ለእንግሊዝ ጋዜጦች የሚፈውን ደብዳቤ በማሰታወስ

91 በመፅሐፍ ቅዱስ የሚጠቀስ የተለየ አጥቂ አሞራ

"አአ! የእንግሊዝና የህንድ መኮንኖች! የቀበጡ! መንግሰተ ሰማያት የተወለዱ! የባላባት ልጆች! እዚህ ተደረሰ? በዚህ ትዛዝ ምክንያት በጣም ተናደዱ፤ በቁጭት ተንገበገቡ። አዋቂው ሽማግሌው የጦር አዛዥ፣ ይህንን የማይመች ውሳኔ እንጣሎ አሰኪደርሱ ድረስ በሆዱ ይዞ ነበር"

"ሰባ አምስት ፓውንድ- ሰባ አምስት፣ አሰኪ አስቡት! በጣም የማይሆን ትዛዝ ነው! ይህን ለምንም የማይበቃ ለባ አምሰት ፓውንድ ይዤ ከምጓዝ ከዚህ ግዴታ ራሴን እንደማወርድ አገልጣለሁ!" በህንድ ለህያ አምሰት አመታት ያገለገሉት ለሰለሰ ያሉትና የተመቻቸው ሜጀሮችና ኮሎኔሎች ጥላቻቸውን አቃቂር ባለው ሁኔታ ነበር የገለፁት። ሰር ሮበርት ግን ፍንክች የሚል አልነበረም። ነገር ግን እነዚህ የእንግሊዝና ህንድ መኮንኖች በተራቸው ጉዳዩን አሰከመጨረሻው ድረስ ለመውሰድ ወለነዋል። ብዙዎቹ ለጦር ፅህፈት ቤቱ ለመፃፍ የዛቱ ነበሩ፤ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ዘመቻው ይጠናቀቃል።

በኮሎኔል ፋይሪ የሚመራው ቀዳሚው ወይም አሳሹ ጦር ወደፊት ተንቀሰቅሶ መንገዱን እንዲያጠራ፣ የሚያሰናክል ነገር ካለም እንዲያሰወግድና፣ ፊት ለፊት ያለውን ሁኔታ ሪፖርት እንዲያደርግ ትዛዝ ተሠጠው። ሁለት ቀናት አለፉ፤ ከኮሎኔሉ የተላከው ሪፖረት በመልከተኛ ባኩል ደረሰ። በሚደነቅ ሁኔታ ተፅፏል፤ ከበድ ያለ፣ ጠለቅ ያለ፣ ባይሆን ከሚገባው በላይ ቃላት የበዙበት ቢሆንም በአላጌ ተራራማ ቦታዎች ከአንድ ሳምንት ባነለ ጊዜ መንገድ መሠራት እንደማይቻል ይገልፃል።

"በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ነገር አይደለም።" በማለት ፋይሪ ፅፏል፤ "ከፊት ለፊታችን ያለው፣ ህገሩ፣ በወንዞችና በሸለቆዎች የተከፋፈለ፣ በተከታታይ ተራራማ ብቻ ነው። የተራራዎቹ ዳገቶች ቀጥ ያሉ ናቸው፤ ጦሩ ወደፊት ለመንቀሳቀስ ከማሰቡ በፊት ብዛት ያለቸው እርከኖች በተራሮቹ ጫፎች ላይ መሠራት አለባቸው።"

"ይህ መጥፎ ዜና ነው።" አለ ናፒየር ለስፒዲ፤ "ከዋናው መንገዳች ብዙ ማንወጣ የሚወስደን ሌላ መንገድ ይኖር ይሆን?"

ስፒዲ፣ የመጀመሪያ ማረፊያችን ወደ ሆነው ወደ እሸንጌ ሀይቅ የሚወሰድ የተሻለ መንገድ ካለ በማለት ሰላዮቹን ጠየቀ።

ሰላዮቹም፣ "እሀ፣ መንገዱማ ቀላል ነው፤ ጦሩን በቀላሉ ወደ ሀይቁ የሚያደርስ መንገድ አለ።" ብለው መለሱ። እነዚህ ተስፋ የሚሠጡ ሰዎች ከካፒቴን ኤም. ግሬሳር ጋር ተላኩ። በርግጥም ግልፅ ያለና ቀጥ ያለ መንገድ ተገኘ፤ ከታሰበው መንገድም የሚወጣ አልነበረም። ኮሎኔሉ ፋይሪ ያገሩ ተወላጆች የሚሠጡትን መረጃ ያለምንም ጥርጣሬ ተማምኖበታል።

በግልፅ እንደታየው ከሆነ ግን፣ በአቢሲኒያ እውነተኛው ነገር ተነግሮ አይታወቅም። ሁሉም አቢሲኒያውያን በጣም አሰገራሚ ውሸታሞች[92] ናቸው። ሰለ ወደፊት የሀገሩ ምድር የተነገረው በሙሉ፣ በጉዟችን እንዳየነው ውሸት ሆኖ ነው የተገኘው። በተወላጆች መረጃ ተመርኩዞ የሚቀርበው የኮሎኔል ሩይሪ ረፖርት በሙሉ፣ እንደ ሎንደኑ ትንቢት የማይታመን ሆኖ ነው የተገኘው። ስለ ሀገሪቱ ፖስቲካ፣ ወይም ቴዎድሮስ ሰላሉበት ቦታ የሚንሳፈፉ ጭምጭምታዎችም ቢሆኑ፣ በተከታዩ ቀን በሚፃፉት አፈሻል እጭር ሪፖርቶች ውድቅ ነው የሚሆኑት።

የትጥቅና ሰንቅ ሀላፊው እየተላከ፣ እካባቢውን እየቃኘ፣ መንገዱን እያጣራና መሄጃውን አሰምሮ ባይጠብቀን፣ የሚቀጥለው ቀን ሰለምንደርሰበት ጣቢያ ዕውቀቱ አልነበረንም።

አንድ ቀን፣ የአቢሲኒያ የወይን እርሻ ያለበት ቦታ ተገኝቷል የሚል መረጃ ይደርሰናል፤ የሀገሩ የቀደመ የሥልጣኔ ምልክት ተገኘ ማለት ነው፤ ሴቶቹ ደግሞ፣ በጠይም ውበታቸው፣ ኪሎፓትራና ዮዲት የመሠሉ፣ የንግሥቶች ክብር ያላቸው ናቸው። እርሻው በአይን መታየት ከሚችል ርቀት በላይ ነው። ባጭሩ ግን፣ ጦሩ የተባለው ቦታ ሲደርስ፣ ከተባለው ሁሉ የተገላቢጦሽና ተቃራኒ ሆኖ ነው የተገኘው። ይህ፣ ሁሉም ነገር የሚያሰገርም እፈታሪክና የተወሳሰበ እንቆቅልሽ ነበር!

በዚህ እሰተያየት ብቸኛ አይደለሁም። ሁሉም ዘጋቢዎች፣ ሰለዚህ የተለየ ነገር ሀሳብ ሰንዝረውበታል። የሚገርመው ነገር እንደዚህ ባለ የሚያታልል ሁኔታና ምትሃታዊ ክሰተት እንድ ሰው እንዴት አድርጎ እንድ የእውነት ቃል ደግሞ መናገር ይችላል።

“ቴዎድሮስ ሊመጣ ነው።”፤ “አይ አይመጣም።”፤ “ሥጦታ ሊልክ ነው።”፤ “ወደ ቋራ እየሸሸ ነው።”፤ “ሐይቅ እጠገብ ሊመሸግ ነው።”፤ “በሽሎን ሊሻገር ነው።”፤ “ሥጦታ እየላክና ለእርቅ እየፀለየ ነው።”፤ እናም፣ እንዱንም አያደርግም። እንዲህ አይነቱ ፍች የሌለት ሚስጥራዊ ውስብስብ፣ እንዳንዱም ቢሆን፣ ያለ ሰውየው ብልጠት የተፈጠረ አይደለም[93]።

---

92 በሰው ሀገር ጠላት መሆኑን ዘንግቶ ሁሉም አቢሲኒያዊ መንገድ እንዲመራው ይጠብቃል? ያም ሆኖ የአመባ አላጌው ጌታ ወልደ ስላሴ፣ እንግሊዞቹ በእጠገቡ እንዳያልፉ ሌላ መንገድ እንዲነገራቸው አድርጓል። ሰለዚህ ውሸት ሳይሆን፣ ሆን ተብሎም የሚደረገ ነገር ነበር።

93 ከዚህ በፊት፣ እዜ ቴዎድሮስ ምፅዋን ባይቆጣጠሩም፣ የሚመላሰሱ ነጋዴዎችም ሆነ ሌሎች ሰዎች፣ ንጉሠን ፍራቻ እንድ መጥፎ ቃል አያወሩም ነበር። ከውጭ ሰዎችም ጋር መታየት አይፈልጉም ነበር። ቴዎድሮስ ሁሉንም ነገር ይሰማሉ ወይም ያውቃሉ ይባል ነበር።

እሁን ጦሩ ወደፊት እየተንቀሳቀሰ ያለበት ሁኔታ ከደረሰን፣ እስኪ ደግሞ ወጥቂቱም ቢሆን፣ ስለ ህገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እናም የእንግሊዝ መንግሥት ሥርነት ካወጀ ቀን ጀምሮ ቴዎድሮስ ጠንክረው እንደሆነ እንመልከት።

ቴዎድሮስን መግቢያው ላይ የተውናቸው፣ ከዚህ የተረገመ ዕጣ ጋር እየታገሉ እንደነበረ ነው። ዙሪያውን የከበቧቸውን የብሪያሪን[94] እጅ ያላቸውን ጠላቶቻቸውን መልሰው እያጠቁ ነበር። ስፊው መንግሥታቸው እንደ ኢካሩስ[95] የሰም ክንፍ፣ በነበረው ጥቃትና ክዳት እየቀለጠ ነበር። በእሳት የሚቃጠሉት መንደሮችና ጎጆዎች ብርሃኑ በእኩለ ሌሊት ሰማይ ላይ እቋርጦ ይታያል። ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችና የህፃናቱ ጩኸት እየሩን ሞልቶታል፤ በጦርነት የሚሞቱ የሚያቃስቱ ተዋጊዎች ወደ ሰማይ ለበቀል ያጮሃል።

በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ ሰላሳ ሺ የሚጠጉ ሰዎች ተገድለዋል ነው የሚባለው። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ በክፉ አይን ነው የታዩት። በተሰፋ መቁረጥ ሥጌትም በመጠጥም ትክክለኛ ነገር መወሰን እልቻሉም። የቴዎድሮስ ቁጣ የቅርብ እማካሪና ጓደኞቻቸውም ላይ እላቆመም። በእውነቱ ከሆነ ጥያቄው፣ "ፈጣሪ ሊያጠፋው የፈለገውን በትክክል የማሰብ ችሎታውን ይነሳዋል" ነው ወይ። የተከፉት ቴዎድሮስ! ማንም እንደሰውየው ልቡ የተሰበረ የለም።

ምርኮኞቹ በስንሰለት ታስረዋል። በነሱ ላይ ያለው የቴዎድሮስ ጥላቻ ደግሞ እየጨመረ ነው የሄደው። ሶስት ወይም እራቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ነበር፤ ወደኋላ ግን ወደ እስራት ተቀየረላቸው። የእንግሊዝና የጀርመን[96] እስረኞቹ በሕይወት እሉ፤ ነገር ግን የተንጠለጠለው ሕይወታቸው በንጉሡ እጅ ነበር። ቴዎድሮስ በቁጥጥር ሥር አድርገው ያቆዩዋቸው፣ የራሳቸው መጨረሻ ከነሱ ደህንነት ጋራ የተያያዘ ነው የሚል እመለካከት ስለነበራቸው ነው።

ምርኮኞቹ፣ በኮሎኔል መርዌዘር ያላሳለስ ጥረት ምክንያት ገንዘብ ይላክላቸው ነበር። እስር ቤትም ቢሆን ገንዘብ ሀይል አለው፤ በዚህ ምክንያትም፣ የከፉ ሊሆን የሚችለው የእስራት ሁኔታ ገንዘብ በሚያስገኘው ምኞት የተሻለ ነበር።

---

94 በአፈ ታሪክ መቶ እጅ አለው የሚባል ጃይንት (ጭራቅ)

95 ኢካሩስ፣ በእየር ለመብረር በሰም የተሠራ ክንፍ አድርጎ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ሲል በፀሀይ ሙቀት ምክንያት ሰሙ ቀልጦ ባህር ላይ የወደቀ ሰው።

96 የጀርመን እስረኞች ቁጥር ከእንግሊዝ እስረኞች ይበልጥ ነበር።

የእንግሊዞች ዋና ቢሮ፣ አልፎ አልፎ ከቆንሰል ካሜሩን፣ ከመልከተኛው ራሳም፣ ሉተናንት ፕሩዶ፣ ከሰርጀን ብላንከ፣ ከቄሶች ከሰተርንና ከፍላድ፣ በተጨማሪም ከቫልድማየር ደብዳቤ ይደርሰው ነበር። ሁሉም ባንድ ድምፅ ሰለመከራ፣ "እየየ" የሚል መልከት ለለሚልኩ፣ የተለመደ ወይም የማያባራ ነገር ሆኗል።

ካሜሩን በደብዳቤው፣ የጭንቀት ቃላቶችን በመጠቀም፣ የነፃነት ደሰታ እንደማያይ አርግጠኛ ሆኖ ነው የሚገልፀው፤ ተሰፋ ቆርጧል፣ ሀዘንተኛም ነው። ምሰኪን ካሜሩን!

ራሳም በጭንቀት መንፈሰ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር ቴዎድሮሰ ላይ ለሰለሰ ያለ አቋም እንዲይዝ ከልቡ ይማፀናል፤ አለበሰዚያ በብቀላ ሰሜት የሞት መከራ ሊወርድባቸው ይችላል። ምስኪን ራሳም!

ሚሰተር ሰትርን ደግሞ መከራውንና ችግሩን ያሳለፈው ዘርዘር ያለ ሀገሩን የሚገልፅ ፅሁፍ አየፃፈ ነበር፤ በጣም አትኩሮት የሚሰብ፣ "Wild Boar of Ethiopia[97]"፣ የእንግሊዘ መንግሥት ላደረገው የግድየለሽነት አንቅሰቃሴ ተግሣፅ መስጠት የሚል ነበር። ደብዳቤዎቹ ግን በአውነቱ የሚያሳዝን አፃፃፍ ነው የሚታይባቸው። የከፋው ሰተርን!

መሰርሰ፣ ፍላድ፣ ፐሪዶ፣ ብላንከና ቫልደማየር የሚገርሙ ምክር የሚሠጡ ደብዳቤዎች ነው የፃፉት፤ የእንግሊዝን ህዝብ በታቻላቸው አቅም ሰለ ህዝቡ(ኢትዮጵያውያን) ባህልና አኗኗር ለማሰተማር ይሞክራሉ።

አፄ ቴዎድሮሰ የጦርነቱን አዋጅ በረጋ ሁኔታ ነው የተቀበሉት፤ ጥላቻቸውን ወይም ንቀታቸውን ለመግለፅ፣ ለጦርነቱም ሆነ፣ ሮበርት ናፒየር ለሚፅፈው ደብዳቤ ምላሽ አልሠጡም። ለተወሠነ ጊዜ፣ የሰውየው ሁኔታ ሚስጥራዊ ነበር።

ሆኖም፤ ራሳም በነበረው ግንዘብ[98] አማካኝነት፣ ለለ ንጉሡ አንቅሰቃሴና ዕቅድ፣ መረጃዎች አየሾሰኩ የአንግሊዝ ካምፕ ድረሰ ይመጡ ጀመር።

የሚቀጥሉት፣ የአንግሊዝ ጦር አንጣሎን ለቆ ወደ መቅደላ አሰከተንቀሳቀሰበት አሰከ መጋቢት 12 ድረሰ፣ ሰለቴዎድሮሰ የደረሱ መረጃዎች አጫጭር ማጠቃለያ መግለጫዎች ናቸው።

---

97 ቴዎድሮስን ለመጥቀስ ነው። ቴዎድሮስ ይህን ፅሁፍ ደርስውበት፣ ስተርን "የአራዊቶች ንጉሥ" ብሎ ሰደቦኝ ብለው ተናግረዋል። ይህ ፅሁፍ መኖሩን ሊያወቁ የቻሉት በፈረንሳዩ ባርደል አማካኝነት ነው። ስተርንን በጣም የሚጠሉበት ምክንያት በዚህ ፅሁፍ ነው።

98 (በምዕራፍ ስባት ማስታወሻዎች)



የእስረኞቹ ጎጆዎች በመቅደላ



CAPTIVES' QUARTERS AT MAGDALA.

የእስረኞቹ መኖሪያ በመቅደላ (ካርታ) ራሳም፤
በጣም ጠቅር ያለው ቦታ የራስ አንግዳ መኖሪያ፡ ከሱ ቀጥሎ ጠቅር ያለው
የፈታውራሪ ዝብርዬ ቤት ነበር።

ታህሳስ 9፣ 1867 - ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ነው ያሉት፤ ብዙ ሰዎችን አየገደሉ ነው[99]፤ ይህ የአላዋቂና የጭካኔ ሥራቸው ከሰው ጋር አያለያያቸው ነው። የሠራዊታቸውን ቁጥር ለመጨመር ሞክረው ነበር፤ ከሳቸው ጋር ለመሰለፍ የተገኘው ከፍተኛው ቁጥር ሰምንት ሺ ብቻ ነው።

ታህሳስ 15 - ከራስም የተላከ ደብዳቤ የያዘ መልከተኛ ይደርሳል፤ ደብዳቤው የሚያትተውም፣ በሸዋው ንጉሥ፣ በምኒልክ የሚመራ ብዛት ያለው ሠራዊት በመቅደላና በንጉሡ ካምፕ መሀከል ሠፍሯል፤ በምኒልክ በኩል ግልበጣ በማድረግ አስረኞቹን የማስፈታት ዕቅድ አለ። የትግራዩ ካሳ፣ ወዳጅነት ቢያስነባርም በዚህ ጭምብል ጀርባ ግን ከፉ ነገር ለማድረግ አንዳስበ አንዳንድ የሚያስስቡ መረጃዎች ደርሰዋል።

ታህሳስ 19 - ስለ ትግራዩ መስፍን የቀረበው ሪፖረት መሠረተ ቢስ ሆኖ ተገኘ። ከመስፍኑ የተላከ መልከት ካምፕ ይደረሳል፤ በመልከቱም ጥያቄው ለምን "ፈረንጆቹና አኔ ወዳጅ አንሆንም?" የሱ ጠላት የናፒየር ጠላት ነው፤ የሱ ጥቅም የእንግሊዝ ጥቅም ነው።

ታህሳስ 20 - የካሳ አምባሳደር ሰናፌ ይመጣል በተደረገለት አቀባበል ደስተኛ ነበር። ሊመለስም የአንግሊዝ አይነተኛ ወዳጅ ሆኖ ነው።

ታህሳስ 22 - ከሚስተር ፍላድ የተላከ በጣም ጠቃሚ መልክት ሰናፌ ይደርሳል። ቴዎድሮስ በቅፅበት ከደብረ ታቦር ተጉዘው በአንድ ምት ያልተዘጋጀውን የምኒልክን ጦር አሸንፈዋል። መቅደላም ደርሰው ከምርኮኞቹ ጋር ወደ ደብረ ታቦር ሊመለሱ ነው።

ታህሳስ 25 - አስተርጓሚው ዶክተር ክራፐ ከአሰሳ ሊመለስ፣ በታህሳስ 22 አሰድንጋጭ የሆነ ዜና ይዞ የመጣውን መልከተኛ መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርብለታል። ሰውየውም ነገሩ ውሸት መሆኑን ይናዘዛል፤ ይህም ደብዳቤው ላይ በተፃፈው ቀን ይረጋገጣል። እንደ ሀስት ዜና አቅራቢው ምኒልክ ላይ ጥቃት የተፈፀመው በጥቅምት ነው፤ ከሚስተር ፍላድ የተላከው የመጨረሻው ደብዳቤ የተፃፈበት ቀን ህዳር 7 ነው።

ጥር 6፣ 1868 - የተረጋጠ ዜና ከመቅደላ አስረኞች በኩል ይደርሳል፤ ምኒልክ ምንም የመንግሥት ግልበጣ ሳያደርግ ወደ ሀገሩ ወደ ሸዋ ተመልሷል። በንጉሡ ካምፕ በደብረ ታቦርና በመቅደላ መሀከል ባለው መንገድ ማንም የቴዎድሮስ ጠላት የለበትም።

---

99 ቴዎድሮስ ደብረታቦር በሳት ያቃጠሉበት ምክንያት (በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ)

ጥር 15 - ቴዎድሮስ እስር ሺ ጦራቸውንና ሀያ መድፎችን ይዘው ወደ መቅደላ እየተጓዙ እንደሆነ ዜና ይደርሳል። የሰሜኑ መስፍን ጎበዜ፣ በርቀት የቴዎድሮስን እንቅስቃሴ እየተከታተለ እየተጓዘ ነው።

ጥር 20 - ሜጀር ግራንት፣ የእባይ (ናይል) ወንዝ አሳሽ፣ ሰጦታዎችን ይዞ ወደ ትግራዩ መስፍን ተልኮውን ይጀምራል። ሜጀር ግራንት በአቢሲኒያ ጥሩ አገልግሎት ነው ያበረከተው።

ጥር 21 - ከራሳም የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፤ "ቴዎድሮስ በዝግታ ወደ መቅደላ እየተጓዙ ነው። ዋሻውም ጎበዜ ሸሽቷል። ቴዎድሮስ ለኔ በፃፉት ደብዳቤ፣ "እንደምን አለህ? ደህና ነህ ወይ? እኔ በጣም ደህና ነኝ። ምንም እትስጋ ለርዳታ ወዳንተ እየመጣሁ ነው። ራስህን ቀና እድርግ፣ በቅርቡ ከናንተ ጋር እሆናለሁ። አንድ ትልቅ መድፍና[100] ሌሎችም ረዥም መድፎች ይዣለሁ። በጣም እሸባሪ ድምፅ አላቸው፤ ነገር ግን ለማጓጓዝ ከባድ ነው የሆኑት።" ዶክተር ብላንክ በፃፈው መሠሪ መልስ፣ "እኛን ነፃ ለማውጣት ወደዚህ መምጣትዎን ስንሰማ በጣም ነው የተደሰትነው። የዚህን መጨረሻ ማንም ሰው ሊያውቅ አይችልም። ሁላችንም ቢሆን ለከፉ ቀን ተዘጋጅተናል፤ ነገር ግን ምንም ቢሆን ደግችን የሚበቀልልን መኖሩን ማወቃችን ርካታ ሞጥቶናል።"

የካቲት 2 - ካፒቴን ቻርለስ ሰፒዲ (ባሻ ፈለቀ) የእንግሊዝ ጦር አስተርጓሚ[101] ለመሆን ከኒውዚላንድ ይመጣል።

የካቲት 9 - በመኮንኖቹ የቀረበው መረጃ ጭብጥ እንደሚቀጥለው ይነበባል፤ "የፖለቲካ ክፍል ሀላፊው ኮሎኔል መርዌዘር ዛሪ ደብዳቤዎች ተረከቧል፤ ደብዳቤው የተፃፈው ከራሳምና ዶክተር ብላንክ በጥር 17 ሲሆን፣ የባልና ሚስቱ ፍላድ ተጨማሪ አለበት። ጥር 9፣ የንጉሡ ካምፕ ወደ መቅደላ እየተንቀሳቀሰ ነው። አሰካሁን ድረስ ሁሉም አሰረኞች ደህና ናቸው። መቅደላን በጥር 8 የለቀቀ የወታደሮች ቡድን ከንጉሡ ካምፕ ጋራ ተቀላቅሏል፤ ወደ አራት መቶ የሚሆኑ፣ አውሮፓውያን ያሉበት እስረኞች ከካምፑ ወደ መቅደላ እንዲወስድ ሀላፊነት ተሠጥቶታል። ለጉዞ እንዲመች እግር ብረታቸው ተፈቶ እጃቸው ግን ታስሯል። ሚስተር ሮዘንታል እብሮ እለ ይባላል። ንጉሡ መንገዱ እንዲሠራ ራሳቸው በእጃቸው ጭምር የታቸላቸውን

---

100 የትልቁ መድፍ የሴባስቶፖል የብሮንዝ ቅጂ በአዲስ አበባ ቤቴዎድሮስ አደባባይ ይገኛል።

101 ናፒየር ራሱ ሰፒዲን የመረጃ መኮንን ነው ብሎ የሚጠቅሰው። ይህ ደግሞ የሚገርም አይሆንም፤ ከእንግሊዝ ሠራዊት፣ እንደ ባሻ ፈለቀ አገሩን በደንብ የሚያውቅ ሰው አልነበረም።

እያደረጉ ነው[102]፤ ነፃ የሆኑት አውሮፓውያን (መድፍ ሠሪዎቹ) እንዲረዱ ተጠይቀዋል። መጠነኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ከጀዳ ወንዝ ስር ከሸለቆው ደርሰዋል። በራሳም ስሌት ከነጓዘቸው በየካቲት መጨረሻ መቅደላ እንደሚደርሱ ነው፤ ካልሆነም ካምፑን ጥለው ከመጡ ግን ባንድ ቀን ይደርሳሉ። የደላንታ ሰዎች ገባር ናቸው፤ ሌሎች ግን እንደገና ሸፍተዋል። ወታደሮቻቸው በምግብ አጥረትና በመንገዱም ምክንያት እየተንገላቱ ነው። በመቅደላ እንደሚነገረው ከሆነ፣ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ እንደበፊተኛው ሳይሆን በደንብ ተዘጋጅቶ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ወደ መቅደላ እያመራ ነው። በዝርዝር የተፃፈ ደብዳቤ ከእንደኛው እስረኛ በኢንግላንድ ለሚኖር ጓደኛው ተልኮ ታትሞ ይወጣል፤ ይህ ደግሞ ባልታወቀ ሁኔታ የቴዎድሮስ ካምፕ ይደርሳል፤ ደብዳቤውም በሚሰተር ባርዴል እጅ ነው ያለው። ይህ ነገር መልሶ ጉዳት ያመጣል ተብሎ ሥጋት አለ።"

የካቲት 12 - የትግራዩ መስፍን እምባስደር ይመጣል። ፣ ጠየም ላለው ጠቆር ያሉት ግርማዊነታቸው ተወካይ፣ በእንግሊዝ ጦር በኩል ደመቅ ያለ ትራምፔት የተነፋበት ሞቅ ያለ አቀባበል ይደረግለታል። የወዳጅነት ልውውጥ ይደረጋል።

የካቲት 25 - የትግራዩ መስፍን በሀውዜን በሚገኘው እንግሊዝ ካምፕ ይደርሳል፤ ራሱ፣ በእንደበቱ ኢጋር የመሆን ፍላጎት እንዳለው ያረጋግጣል።

የካቲት 27 - ሌላ መግለጫ ይወጣል፤ በመግለጫውም ዋግሹም ጎበዜና ምኒልክ ሁለቱም ከእዬ ቴዎድሮስ አጠገብ ናቸው። ካምፑም ቅርቡት ስለነበረው የዋግሹም ጎበዜ ካምፕ የሚነድ እሳት ከእዬ ቴዎድሮስ ካምፕ ሆኖ ይታያል። ዋግሹም ወደ ቴዎድሮስ መልክት ልኳል፤ ነገር ግን ከብር የጎደለውና ድፍረት መስሎ ስለታየ፣ ቴዎድሮስ መልክተኛውን በሞት ይቀጣሉ።

መጋቢት 6 - በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል መሴ መንዚንጀር፤ ጦሩን እንደ ፖለቲካ እማካሪና እንደ አስተርጓሚ በመቀላቀል፤ ዋግሹም ጎበዜ[103] የእንግሊዞች ተባባሪ እንዲሆን ለመጣር ተልዕኮ ይጀምራል።

የፖለቲካውን ሁኔታ በዚህ ጥቅጥቅ ባለ መንገድ ከተከታተልን በኋላ፣ ትንሽ አስተያየት መስጠት ቢፈቀድልኝ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር በዚህ ጉዳይ፣ ራሱን መሀል ላይ ሆኖ ያገኘው፤ ማለትም፣ በቴዎድሮስ፣ ዋግሹም ጎበዜ፣ ንጉሥ ምኒልክ እና የትግራዩ መስፍን መሀከል በሚደረገው ትዕይንት። የእስረኞች ሁኔታ እየተሻለ ስለመጣ መቅደላ እስከንመለስ ድረስ አንተዋቸው።

---

102 የአፄ ቴዎድሮስ መንደር (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

103 ጎበዜ የዋግሹም ገብረመድህን ልጅ ናቸው። (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)



ሴባስቶፖል ወደ መቅደላ ሲጎተት!

የሰር ሮበርት ናፒየር አዋቂነት የተረጋገጠው፣ በወታደራዊ ትዛዝ በዚህ በማይታወቅ ሀገር ወደ መሀል መገስገስ ብቻ ሳይሆን፣ በረቀቀ ሁኔታ ከኢትየጵያ ገዥዎች ጋር ባደረገው ዲፕሎማሲ ጭምር ነው።

እሴ ቴዎድሮስ በራሳቸው የአሰተዳደር ሁኔታ ሙሉ አቢሲኒያን መግዛት አልቻሉም። በነበራቸው ልጓም የለሽ ምኞታቸው በአንድ ጊዜ ሠፊ ከነበረው መንግሥታቸው ውስጥ፣ እያንዳንዱ መሰፍን፣ ራስ ወይም አለቃ እየራቃቸው ነው የሄደው።

ሰለዚህ ሰር ሮበርት ናፒየር ይህንን አጋጣሚ መጠቀም ነበረበት፤ ቴዎድሮስ ያጡትን የሀገሩን ተወላጆች አጋርነት ወይም ታማኝነት ለማግኘት ትልቅ ጥረት ማድረግ ነበረበት። ሚዛናዊ የሆነው የእስተሳሰብ ችሎታው በሚደነቅ ሁኔታ ለዚህ የተመቸ ነበር።

አለቆቹ ቀሰ በቀስ የሰር ሮበርት ናፒየር ታዛዦች ሆኑ፤ መጠነኛ የሆነ የራሳቸውን ፍላጎት የሚያሟላ ነገር ያደርጋሉ፤ ያም ቢሆን በናፒየር ፖሊሲ ተቀባይ እሰከሆነ ድረስ ነው። የመሰፍኑ ካሳ ሁኔታ የተረጋገጠ ነው። የሰሜኑ ሻሸ ዋግሹም ነበዜ[104] የቴዎድሮስ ጠላት ነው ተብሎ ተነግሯል። ቁጥሩ ወደ አርባ ሺ የሚሆን ሠራዊት ይዞ በማንኛውም ሰአት ቴዎድሮስን ለመውጋት

---

104 (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ተዘጋጅቷል። እሁን የእንግሊዘ ጦር በዋግሹም ሀገር አካባቢ ሰለደረሰ፣ ለሰውየው አሰፈላጊ ትኩረት መሠጠት እለበት፤ አገልግሎቱ፣ ተባባሪነቱ መልካም ፈቃዱ መረጋገጥ አለበት።

መሴ መንዚንጀር ከሰጦታና የሰላም ጥሪ ሀሳብ ጋር ወደ ዋግሹም ይላካል።

በላሰታና አንጣሎ የሚገኝበት በእንደርታ መሀከል፣ ከአንጣሎ ለላሳ ማይሎች ርቀት፣ ሌላ የጦር መሪ ቀጥ ያለ ተራራ ላይ ካምፕ አድርጓል፤ ሰሙም ወልደየሱሰ ይባላል፣ የያቆብ ልጅ፣ ኪታወቀ የጦር አዛዥ ይልቅ የሽፍታ አለቃ ይመሰላል። ለዚህ መሪም ቢሆን ናፒየርን መጥቶ እንዲጎበኘው የግብጥ ጥሪና የኢጋርነት ወይም የገሰልተኛነት ጥሪ ያለው መልከት ይልካል። ጦረኛው ወልደ ግን የሚያወላውል መልሰ ይመልሳል። ዋግሹም ጎበዜ ከመቼው በበለጠ ጉራ የመጨመር አዝማሚያ ይታይበታል፤ እርባ ሺ ወታደሮች ይዞ ማድረግ የማይችለው ነገር የለም ብሎ እሰቧል።

እንደዛም ሆኖ፣ መልሶቹ እንግሊዞችን የሚፃረሩ አልነበረም፤ ባይሆን፤ መልሱ የማያረካ ራሰን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፤ ሰላለው ሀይልና ቴዎድሮሰ ላይ ሰላለው ዕቅድ የሚገልፅ ነው።

ከኢጋርነት ይልቅ ገለልተኛነቱን የመረጠ ይመሰላል።

"ነገር ግን፣ በበቂ ሁኔታ ከተከፈላቸው፣ የሱ ሰዎች ለኛ ወታደሮች የሚያሰፈልጉትን ነገሮች አንዲሸጡልን ፈቃድ ለመሰጠት ቃል ይገባል ወይ?" ብሎ ሰር ሮበርት ጠየቀ።

"እዎ፣ ሰዎች ያሻቸውን መሸጥ ይችላሉ፤ አይከለከላቸውም። ቴዎድሮሰ የናፒየርም ሆነ የሱ ደመኛ አይደለም እንዴ?"

ሰር ሮበርት በጣም ትዕግሰተኛ ሰው ሰለሆነ በቀላሉ የሚሸበር ሰው አይደለም። የማያባሩ መልክተኞችና ከዋናው ፅህፈት ቤት የሚፃፉ የምሰጋና ደብዳቤዎች በየጊዜው ለዋግሹም ይላኩለት ነበር፤ ሰጦታዎችን ጨምሮ መልካም ምኞት መግለጫ ያላቸው ደብዳቤዎችም ነበሩበት። ማንም መሰፍን ቢሆን፣ እንደነዚህ አይነቶችን ታላቅ ሥጦታዎችና ወደፊትም ቢሆን የሚያጋጥመውን የተሻለ ዕድል ማሰብ የሚያጓጓ ነገር ሰለሆነ አሉታዊ የሚሆንበት ነገር አይደለም፤ ሰለዚህ ለተደረገለት ነገር በሙሉ ብድር መመለስ እንዳለበት ይሰማዋል። የእንግሊዙ ንጉሥ ትኩረት መሥጠትና ደግነት፤ የዋግሹምን ኩራት እቀዘቀዘው፤ ሰለዚህ፣ እሱም ቢሆን ተጠራጣሪ ተፈጥሮ ቢኖረውም ለእንግሊዞቹ ሀሳብ እጁን ሠጠ።

መልሶ በፃፈው ሊጋሰ አፃፃፍ፣ ዕቅዱን በመግለፅ ባለው ሀይሉ በሙሉ ናፒየርን እንደሚረዳና ሁኔታዎች ሲፈቅዱለት ቴዎድሮስን አንደሚወጋ አሳወቀ።

ከመቅደላ ባሻገር ባለው ሀገር፣ ከሱ ጋር ሰላም መፍጠር የሚያስፈልግ ሌላ ሰው አለ፤ ይህም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ነበር። አሱም ቢሆን ቴዎድሮስን ለማጥቃት የተዘጋጀ ወደ አርባ ሺ የሚሆን ሠራዊት አለው። ነገር ግን አንደ ጎበዜና አንደ ትግራዩ መስፍን በአንድ ቦታ የሰከነ ሳይሆን በየቦታው የሚዘዋወር ታላቅ ጎሸ ስለነበር ከሱ ጋራ ግንኙነት ማድረግ መቻሉ አጠራጣሪ ነበር።

በመቅደላ ዙሪያ ባለው አገር፣ ወደ ቴዎድሮስ ምሽግ መሄጃ በግራ በኩል፣ በየቦታው የሚታዩት አሮሞዎች በየንግሥቶቻቸው ሥር ይገኛሉ። የአዘቦ አሮሞዎች በንግሥት ወርቂት፣ የወሎ አሮሞዎች በሞግዚቷ በንግሥት ጣይቱ ሥር ናቸው። እነዚህ ሙሰሊሞች ሲሆኑ አኛ ግን ከርስቲያኖች ነበርን።

ሰር ሮበርት ግን፣ ለሁሉም አምነት ተከታዮች፣ ዘሮችና ተወላጆች ዝግጁ ነበር። አሱን ከሚከተሉት ሰዎች እንዱ፣ ጀኔራሉን ለመከተል ፈቃድ የጠየቀው መሀመዳዊው መሰፍን ሚር አከባር አሊ[105] ነበር። ይጠቅማል በሚል አምነት እንዲከተል ተፈቅዷል። ይህ ሀንዳዊ ሙስሊም፣ ከሙሰሊም ጎሹዎች ጋር መደራደር የሚችል ትከክለኛው ሰው ነበር። ጠቆር ያለው የቆዳው ቀለም፣ እምነቱ፣ መልከመልካም መሆኑና ለውድ ዕቃዎች ያለው ፍቅር የሚጠቅሙት ባህሪዎች ነበሩ፤ ለዚህ ጉዳይ ወይም ሥራ ደግሞ የተመረጠውና መንቀሳቀስ የሚችለው በአሮሞ ምድር ሰንደርስ ብቻ ነው።

ሜጀር ግራንት ከወልደየሱሰ ጋር ላደረገው ግንኙነት መመስገን አለበት፤ ተልዕኮው ሰለተሳካም፣ ወልደየሱሰ የፈረንጁን ጀኔራል ለመገናኘት ወንድሙን በመላክ ለሰላም የተደረገለትን ጥሪ ተቀበለ።

ካፒቴን ሙር የተባለ፣ በአረቢያና በፔርሽያ[106] የተጓዘ የአረብኛ አስተርጓሚ፣ ደበዳቤዎችንና ሰጦታዎችን በመያዝ ወደ አካባቢ ጎሹዎች ይላክል፤ በአንግሊዙ ጀኔራል በኩል፣ በምንም አይነት መንገድ አነሱን ለማጥቃት ምንም ዕቅድ አንደሌለ ለጎሹዎቹ ለማረጋገጥ ነበር። ጥረቱም በሙሉ የተሳካ ነበር። ጎሹዎቹ፤ በአንድ ድምፅ ተስፋቸው የአንግሊዙ ጀኔራል አሸንፎ ሀገሩን እንዲይዝ ነበር፤ ከለዎች ጋር ለመደራደር የተጠቀመበት ለቀቅ

---

105 አክበር አሊ ምድቡ ከመረጃው ክፍል ሀላፊ ከሜጀር ግራንት ጋር ነበር

106 የአሁኑ ኢራን

ያለው የጄኔራሉ ፖሲሲ፣ ቀደም ብለው አስበውት ከነበረው ከጀኔራሉ ዕቅድ ጋር የተለያዬ ነበር፤ በልባቸው፣ ነገሮች ሁልጊዜ እንደዚህ ቢሆኑ ምኞታቸው ነበር።



ሚር አክበር አሊ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ስለዚህ ሽማግሌው ሆን ብሎ የዘገየበት ምክንያት ተገልጧል። ግልፅ ከሆነው የዘመቻው ጉዞ ታክቲክ በተጨማሪ፣ በሙሉ ልብ ወደ መሀል አገር ከመዝለቁ በፊት ማከናውን የሚገባው አሳሳቢ የሆኑ የዲፕሎማሲ ሁኔታዎች ነበሩ። ምናልባትም በራሱ የሚተማመን ደፋርና ችኩል ጄኔራል፣ እንደ ሸርማን[107] አይነቱ ቢሆን፣ ከናፒየር በፊት ቀደም ቀጥታ ወደ መቅደላ ይዝሰግስ ነበር። ያማረ የመጨረሻ ውጤት የተገኘበት የዳተኛው ጄኔራል ጥረት በችኩሉ በጄኔራል ሸርማን ተቀባይ መሆኑ በጣም አጠራጣሪ ነው።

---

107 ሜጀር ጄኔራል ዊሊያም ተኩምሳ ሸርማን፣ በአሜሪካው እርስ በርስ ጦርነት በዩኒየን በኩል የነበረ ታዋቂና ደፋር ጄኔራል ነበር። ጄኔራሉ 'scortch the earth' በሚባለው ፖሊሲው ማለትም ቤቶችን በእሳት በማንደድ የሚታወቅ ነው።

የስንቅና ትጥቅ ከፍል ሀላፊው የአሳሹ ጦር ሪፖርት ሲደርስ፣ ጦሩ ካምፕ ትቅሎ ከአንጣሎ ስምንት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ሙጂ ተጓዘ።

ፊት ለፊታችን አሉ በተባሉት ታላቅ መሰናክሎች ሪፖርት የተነሳ ሁላችንም ሰለ ሀገሩ ተፈጥሮና ወደፊት በመንገዳችን ላይ ሰለሚያጋጥመን ሁኔታ ጭንቀት ነበረብን። ከአንጣሎ አምባ፣ ከላይ ሆኖ የሀገሩን አካባቢ በሰፋት ማየት ይቻል ነበር።

ከዚህ ከፍታ ሆነን ማየት ከምንችለው ሁሉ፣ አካባቢው፣ ቀጥ ያሉ የተራሮች ሰንሰለት ያሉበት ይመሰላል። ግዙፍ የሆኑ ቀላ ያሉ የተራራ ጫፎች፣ ወደ ላይ ብሩህ ሰማያዊ ቀለም ወዳለው ሰማይ የተተኮሱ ይመስላሉ፤ ግራጫ መልክ ያላቸው ግራናይት አለቶች አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርበው ይታያሉ፤ ኮረብታ በኮረብታ አየተከታተሉ አጅብ ብለው ወይም አንደ መጋዝ ጥርሰ ተደርድረው ይታያሉ። በሸለቆው መሀል፣ ከአንጣሎ ተነስቶ ወደ ጎድጓዳው ሰፍራ የሚወስደው ነጣ ያለ መንገድ ይታያል፤ መንገዱም አንደ ሰማይ ላይ እንዳለ የከዋከብት ብርሀን መስመር ተለይቶ ይታያል።

ወደዚህ መሰጊ ወደተባለው ቦታ የተደረገው ጉዞ አሰቸጋሪ ነው ተብሎ የሚጠራም አልነበረም። ካሰንበት ከአንጣሎ ካምፕ በደልዳላ ሜዳ ላይ የሚያቋርጥ ነበር። መሰጊ ከደልዳለው ሰፍራ ዳር ላይ ያለ ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን፣ መሬቱም በሁለት ንፁህ ወራጅ ውሀዎች ይታጠባል።

ከዚህ ቀደም እንደገለፅኩት፣ መኮንኖቹ መያዝ የሚቻለውን የጓዝ መጠን የሚጠቅሰውን ጥብቅ ትዛዝ መጣሰ ችለዋል። አብዛኞቹ መኮንኖች እያንዳንዳቸው፣ በአንጣሎ ከነበራቸው ስድሰት ሠራተኞች ምናልባትም ሁለቱ ብቻ ነው የቀሩት፤ ከአምስት የጭነት ከብቶች ሶስቱ ከነጂዎቻቸው ጋር አብረው ተጉዘዋል። ሰለዚህ በሁለቱ ካምፖች መሀል ያለውን ርቀት የሚሸፍን ትልቅ የተከታዮችና የከብቶች መሰመር ሠራዊቱን ተከትሎ ይጓዝ ስለነበር በፍጥነት የሚደረገውን እንቅስቃሴ አንዲያዘግም አድርጎታል።

ከሠራዊቱ ጋር መጓዝ ትግስት የሚያሳጥር ሆኖ ነው የተገኘው። ረዥም ዘገባዎችን መዘገብ ሙያችን ለሆነ ሰዎች፣ አድካሚ ሥራ፣ ካምፕ እንደደረሰን መታወቅ ጀመረ። ለአሰራ ሁለት ወይም አንደ ሁኔታው ለአሰራ አምሰት ሰአታት ኮርቻ ላይ ተጣብቆ፣ ጓዛችን ለመጠበቅና ለማጀብ ጎን ለጎን መጓዝ፤ ከዛም ካምፕ ከደረሱ በኋላ፣ ዘገባ መፃፍ ቀላል ሥራ አይደለም። በመንገድ ላይ ያጋጠሙ ነገሮችን መመዝገብ፣ የእለቱን የፖለቲካ መረጃ መሰብሰብን ይጨምራል። ከዚያ ደግሞ፣ የሰሰት ሰአታት የሚሆን ቁርጫ እንቅልፍ ሙተኛት፣ ስኳር የሌለው ሻይ መጠጣትና የደረቀ ዳቦ ጎርሶ ከጠዋቱ አሰራ

አንድ ሰአት ሲሆን የተለመደ መንገድ ለመቀጠል ኮርቻ ላይ መውጣት የሚያስደሰት ሽርሽር አይደለም። ይህ ሁሉ በቀላሉ መፍትሔ ያገኘ ነበር።

አንድ ሰው ሊረዳው አንደሚችሰው አምሰት ሺ ወታደሮች ያሉበት ሠራዊት፣ ከሚከተሉት አሰር ሺ ከሚሆኑ ከብቶች ጋር በአግር መንገድ ያውም ባንድ መሰመር መጓዝ፣ አሰር ማይል ለመጓዝ ሙሉ ቀን ይወሰድበታል፤ ያም ምንም አከል ሳይፈጠር ወይም ጓዝ ከጭነት ላይ ካልተንሸራተተ ነው። አንግዲህ፣ ይህ ያለማቋረጥ የሚጓዘው ጦርና የሚከተለው ጓዝ፣ ሙሉ ቀን ከወሰደ፣ ያለማቋረጥ ወደ ሁለት አሰከ ሶሰት መቶ የሚሆኑ በቅሎዎችን ጭነት ለማሰተካከል በየጊዜው መቆም ካሰበት፣ በቅሎዎችም በየሶሰት ርምጃዎች እየዘሰሉና መሬት አየተኙ ጭነቱን የሚያንሸራትቱትና የማይቀል ርግማን የሚያሰከትሉ ከሆነ፣ ምን ሊደረግ ነው?

በዘመቻው የሚታየው አጠቃላይ የጥበቃ ሁኔታ ከሌሎች ዘመቻዎች ጋራ ተመሳሳይ ነው። የጠዋት መቀሰቀሻው ጥሪ፣ ቀኑ ሲወጣ ተሰማ፤ ቀዳሚ ጦሩም ተንቀሳቀሰ በግማሽ ሰአት ውስጥ ከሰንቅና ትጥቅ ከፍል መኮንን ጋር በመሆን መንገድ ሲጀምር ነው። ይህ የሚንቀሳቀሰው ከፍል፣ የቃኘዎች ሀላፊ ኮሎኔል ፋይሪ ከሁለት ቀን በፊት ቀደም ብሎ ተጉዟል፤ ያም ለጣቢያ ይሆናል ብሎ የወሰነውን ቦታ ለመምረጥና ምልከት ለማድረግ ነው።

የመጓጓዣው ወይም ጭነቱ፣ በመኮንኖቹ ያላለሰ ግፊት እየተቀነሰና እየተቆነጠረ ከየሬጂመንቱ ቀድሞ ወጥቶ ነበር። ጭነቱ በበቅሎዎች ላይ ተጭኖ፣ ሰልፉ ወይም ተጓዙ አሰከሚያልፍ ድረሰ በየመንገዱ ዳርቻ መሰመር ይዞ አንዲጠብቅ ተደረገ።

ከጥዋቱ አሰራ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ ሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር። የጦር ባንድ ሙዚቃ መጫወት ጀመረ፤ አግረኛው፣ ፈረሰኛው፣ ከባድ መሳሪያ ከፍሉ፣ የባህር ሀይሉ ብርጌድ፣ ዝሆኖቹና የጓዙ መሰመር ወደፊት መንቀሳቀስ ጀመሩ።

እኩለ ቀን ሲሆን፣ የተጓዙ ቀዳሚው ከፍል አዲሱ ካምፕ ቦታ ደረሰ። ከሁለት ሰአታት በኋላም ጓዙ ደረሰ፤ ሆኖም ማታውኑ ሆነ አሰከነጋታው ጠዋት ድረሰ የሚንቀራፈፉ የጭነት ከብቶቹ አየመጡ ነበር። አንዳንድ ጊዜ፤ አንሰሶቹ ጉልበታቸው አሰኪታደሰ ድረሰ ለአንድ ቀንም ቢሆን ጉዞ አናቆማለን። አጭር የሆነ የአምሰት ወይም የሰድሰት ማይሎች መንገድ ሰንጓዝ፣ መንገዱ ቀጥ ያለ ቁልቁለት ካልሆነ በሰተቀር የጓዙ የመጨረሻው ከፍል ፀሀይ ሳትገባ ካምፕ ይደረሳል።

የየቀኑ ጉዞ ማለቂያ ሰአት ላይ፣ የአገሩ ተወላጆች፣ ከያዙት አህል፣ ሳር፣ ምግብና ዳቦ ጋር ወደካምፑ ይጎርፉ ነበር። የየመንደሩ አለቆችም አየመጡ

ይንበኙ ነበር፤ አና በዚህ ጊዜም ጠቅላይ አዛዡ፣ ሁሉም መኮንኖች እንዲገኙበት የሚጠበቅበት ግብዣ ያዘጋጃል።

መንገዱ ቀጥ ያለ ዳገት ከሆነ ደግሞ ዝሆኖቹ ከከባድ ሽከሞቻቸው ጋር ይታገላሉ። ያ ሲሆን፣ ሌሎቹ የጭነት ከብቶች አልፈዋቸው ይሄዳሉ። በሚስማማ መንገድ ሲሆን ግን አንዘህ ግዙፍ አንሰሶች 1800 ፓውንድ ከሚመዝነው ጭነታቸው ጋር ሁኔታውን በደንብ ተቆጣጥረው በበቂ ፍጥነት ጉዟቸውን ያሳካሉ። በዚህ ጊዜ፣ ላገሩ ተወላጆች የሚያሰፈሩ አለዚያም ለማየት የሚያስደሰቱ ሆነው ነው የተገኙት። ያገሬው ሰዎች ከብብ አያሉ፣ ዝሆኖቹ በሰልፍ ቁልቁለትና ዳገቱን ሲወጡ ማየት የሚታከታቸው አይመሰልም። 1500 ጫማ የሚሆን ዳገት መውጣት ለዝሆኖቹ ከባድ መሆኑ ያስታውቃል፤ የሚያሰሙት ከባድ ትንፋሽና የሚያናፉት ድምፅ የጭንቀታቸው መግለጫ ነበር። ለዘመቻው ወሳኝ ነበሩ። በየቀኑ አርባ አምሰት ፓውንድ የሚሆን ዳቦ፣ አርባ ፓውንድ የሚሆን ጭድ ወይም ያገሩን ገለባ ይመገቡ ነበር። አንዳንዶች ከታወቁት የባርነም "ሃኒባል" ከሚባሉት የሚገዘፉ ሲሆኑ፤ እብዛኞቹ ግን በአንፃሩ ወጣት ሰለነበሩ ድካሙን በዕደሜ ከገፉት የበለጠ ይቋቋሙት ነበር።

የሬጂመንቱ ወጥ ቤቶች ምግብ እያዘጋጁ አያለ፣ ወታደሮች በመጀመሪያ ካምፕ አንደደረሱ ከተፀዳዱ በኋላ ራሳቸውን በተለያዩ ስራዎች ጠመዱ። ጀምናሰቲከና ሌሎች የሰውነት አንቅሰቃሴ ይወዱ ሰለነበር፣ በካምፑ ውሰጥ የሚያጓጓና የሚያዝናና ትዕይንት ይታይ ነበር።

ፀሀይ ሰትጠልቅ፣ ከጦሩ ባንድ የብሮንዝ የሙዚቃ መሳሪያዎች ዜማ ይሰማል። ለመጀመሪያ ጊዜም፣ ዙሪያውን የከበቡት ተራሮች ይህንን የወታደራዊ ዜማ ያሰተጋባሉ። እያንዳንዱ ያገሩ ተወላጅ ደግሞ የያዘውን ጦር ተመርኩዞ፣ በፀጥታ ተሸብቦ ያለምንም መግደርደር ነብሱን የሚያረጋጉ የሚመሰሉ አነዚህን ተሰማምተው የሚወርዱ ዜማዎችን በደሰታ ያዳምጣል። ጨለማው ሲገባ ሁላቸንም አንለያያለን። ሙዚቃው በሩቅ ሲሰማ በማይገሰፅ ሁኔታ ጣፋጭ ሆኖ፣ ነፍሳችን ውሰጥ የትዝታ ሰሜት ይረጫል፤ በዚህም ምክንያት አእምሯችን በአቢሲኒያ ተራሮች ወጣ ገባ ኮረብታዎች አልፎ ሰማያዊውን ባህር ተሻግሮ፣ በርቀት ወዳለው ቤታችን በህሳባችን አንድንጓዝ አደረገን።

መጋቢት 14፣ አንጣሎን ትተን ሄድን። መሸከ ከመሰጊ ሰምንት ማይሎች ርቀት ነው ያለው። ከዚህ ከኋለኛው ካምፕ፣ መንገዱ አየተጠማዘዘ ወደላይ ከሸለቆ ጎን ለጎን ይሄዳል። ሸለቆው በጎንና ጎኑ በጣም አረንጓዴ በሆኑ ተክሎች በተሸፈኑ የኮረብታ ሰንሰለቶች ታጅቧል። በመንገዳችን ላይም ሁሉም አይነት የተፈጥሮ ዕይታ አለ። ሾጠጥ ባሉት ኮረብታዎች ላይ የከምር አሳት ይነዳል፤

ያም በጠንካራ አምባው ላይ በበረት አንደተያዘ ነብር የተቀመጠውን የአለጌ ጎሹ ሰለኛ መምጣት ለማስጠንቀቅ ነበር። ከተራራዎቹ ጫፍ ላይ የጭስ ምሰሶዎች፣ መልከ ባለው ሁኔታ ወደ ላይ ከፍ ብለው ይታያሉ፤ ይህም የስማያት አማልክትን በቀል አንዲያደርጉ ለመማፀን የሚጨስ የገፀበረከት ጭስ ነው የሚመስለው። ከየምሽጎቹ ጀርባ፣ ጠቆር ያሉ ተጠራጣሪ ሰዎች አኛን ቁልቁል ይመለከታሉ፤ ለመዝረፍና ለመግደል የጓጉ ይመስላሉ፤ ነገር ግን አንደ ብልጥ ተኩላ ያጋጠማቸውን ጥሩ ዕድል በመጠቀም ከምሽጋቸው ወርደው ከመዝረፍና ከመግደል ተቆጥበው ኢጋጣሚውን አሳለፉት።

አነስ ባሉት ኮረብታዎች በየጎጆዎች የሚኖሩት ሰዎች ግን፣ በኛ ግምት ስብስብ ብለው፤ በየዳገቱ ያልተለመደ አለባበስ ለብሰው በመገረም ቆመው ሰናይ፣ አየጎረፉ በሚሄዱት ፈታቸው ነጣ ያለ አንግዶች ምንም የጥቃት ስሜት የተሰማቸው አይመስሉም።

ካምፕ ለመድረስ ሁለት ማይሎች ርቀት ሲቀረን፣ ጠመዝማዛና ሞገደኛ የሆነ ወራጅ ውሃ በየደቂቃዎች ማቋረጥ ነበረብን። በቦታው የነበረው አነስ ያለ ሸለቆ ደግሞ እየሰፋ በመሄድ አርንጓዴ የበቆሎ ተክሎች መታየት ጀመሩ፤ በመሀሉም፣ አልፎ አልፎ ደኖችና፣ ዝቅ ያሉ ቦታዎች ላይ፣ ሜዳዎች፣ ችፍግ ባሉ ሳሮችና የተለያየ ቀለም ባላቸው በፈኩ አበቦች ተሸፍነዋል። ተራራው በሁለቱም ጎን 1500 ጫማዎች በላያችን ላይ ከፍ ብሎ ይታያል። ወጣ ገባ ያለው የተራራዎቹ ጎን፣ ብዛት ባላቸው ጥድ የመሰሉ ዛፎች ተሸፍኗል፤ በለውጡም የቁልቁልና ሌሎችም ተከሎች አሉባቸው። ትልልቅ የአለት ድንጋዮች ከዛፎቹ አናት ላይ በድፍረት ፈጠጥ ብለው ይታያሉ፤ ብዛት ያላቸው ሽንተረሮች ዳገቱን ቆራርጠውት ይታያል።

ስምንት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ፣ በረድፍ ከበቀሉ ዛፎች ዳር፣ ካምፑ በአሻጋሪ መታየት ጀመረ። የቦታው ስም መሸክ ይባላል፤ ስሙን ያገኘውም ጋራ ላይ ባለ በደንብ በመከላከያ ከተሠራ መንደር ነው። በጣም የሚያስደስት ቦታ ነበር፤ ከፍ ባሉ ተራሮች የተከበበ የመዝናኛ ፓርክ ይመስላል። ወራጅ ውሃ፣ ሜዳማ የሳር ቦታና ግዙፍ የዋርካ ዛፍ ዋና ከፍሎቹ ናቸው።

1ኛው ብርጌድ አዚህ ቦታ በ15 ነበር የደረሰው፤ 2ኛው ብርጌድ መስጊ ካረፈ በኋላ በሁለተኛው ቀን ደረሰ።

የሚቀጥለው ጉዞ ወደ አፃላ ነው፤ ያም የሸፍታው መቀመጫ አምባላጌን አልፎ ነበር። የአምባው ባለቤት ቀበሮው ወልደየሱስ አለዚያም ወልደ ያቆብ የሚባል ሰው ነው። በአጠቃላይ በዚህ መንገድ ለሚያልፉ ለዎች ሁሉ አደጋ ነው። በጋራው ላይ አንደ ንብ ቀፎ በተሠሩት መንደሮች ውስጥ፣ አሊቃው መጥራትና ማዘዝ የሚችለው አንድ ሺ፣ ጠንካራ፣ ጦር የያዙ ሰዎችና አምስት



የአፃሎ ካምፕ
(ዋቢ መፅሐፍ ፡ቁ. 16)

መዶ ጠመንጃ ያጉሾ አለው፡፡ ይህ አልፈን የምንሄድበት ቦታ የዋጂራት ክፍል ዋና ከተማ ነው፡፡ አምባው፣ ግራናይትና ላይም ሰዶን ከሚባሉ አለቶች የተፈጠረ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሆኖ፣ ካለዩ ላይ ደግሞ በብዙ መዶዎች ጫማዎች ከፍታ ያለው ሾጠጥ ያለ ኮረብታ አለበት፡፡ አምባው፣ በሁሉም ጎን ቀጥ ያለ የመዶ ጫማዎች ከፍታ ባለው ግድግዳ ከተራራው ላይ ይነሳል፡፡ የአምባው መሠረት ደግሞ ስፋቱ ወደ ሁለት መዶ ያርድ ኪዩብ ይሆናል፡፡ ወደ አምባው መውጫ ግማሹ ላይ፣ ወጣ ባለ ቦታ የተዋጊዎች መኖርያ ተሠርቶበታል፡፡ በሜዳ መነፀር ላየ ሰው፣ ብዙ ጠቆር ያሉ ፊቶች እኛን ቁልቁል ሲመለከቱ ማየት ይቻላል፡፡ እንደኔ እባባል፣ አዛዡ ራሱ ወልደ የሱስ ቢሆን ከጥሩ ቦታ ሆኖ እኛን እያየ ነው፤ የሚባለው እንኳን፣ ሰውየው ሥፍራውን ለቆ ሌላ ቦታ ሄዷል፤ ይህም፣ ናፒየር፣ በቀጥታ በሱ አምባ ሥር ለማለፍ በወሰነበት ሸር ያለበት ሁኔታ ምክንያት ነው፡፡

ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ማይሎች፣ መንገዱ በጫካዎች ጥላ ሰር ነው የሚወስደው፤ አልፎ አልፎም የሚያሰፈራ ረግረግ፣ ወራጅ ውሀዎችና በሸለቆው ውስጥ የሚታዩ የእርሻ መሬቶች ይታያሉ፡፡ በድንገት ግን ወደ ዳገትነት ተቀይሮ፣ ለሁለት ማይሎች የሚሆን ከዚህ ቀደም በተጠቀሰው አምባ ዳገቶች ላይ ይወስዳል፤ ያም፣ ከአምባው ስር የሚገኝ ኮረብታ ጫፍ ላይ ከመወጣታችን በፊት ነው፡፡ ይህ ቦታ፣ ከካምፓችን ከመሸክ 1500 ጫማዎች በላይ ነበር፡፡

ከዚህ ከፍታ ላይ ሆነን አዲሱ ካማፓችን አፃሎን ማየት አንችላለን፤ ካለንበት ቦታ 2500 ጫማዎች ዝቅ ብሎ የሚገኝ ኩብ የመሰለ ሜዳማ ቦታ ነው፡፡ በእንጨት የተከበበ አረንጓዴ ይመስላል፡፡ በማወዳደር፣ በመሀከላቸው የሚታይ ጉልህ ልዩነት ግልፅ ነበር፤ በለምለም አረንጓዴ ቦታና፣ ዙሪያውን በከበቡት ኮረብታዎች መሀል፣ ኮረብታዎቹ ላይ ቆመን ቁልቁል ስንመለከትም በአስገራሚ የተፈጥሮ ሁኔታ በጣም ተደንቀን ነበር፡፡

በፊት ለፊት፣ በተቃራኒ የሚገኘውን፣ ከአምባው ጋራ አኩል ከፍታ ያለውን ቦታ ሳንወጣ፣ በሸለቆው አልፎ መሄዱ የሚመስል ነገር አልነበረም፡፡

ሰለዚህ የነገው ጉዞ ገፅታ የሚያሰደስትም አይመስልም፡፡ ካፒቴን ጀ ሲድኒ ሪፓርት እንዳደረገው፣ ከመሸክ ወደ አፃሎ በተደረገው ጉዞ፣ ከአቢሲኒያውያን የጓዝ መስመር በኩል አንድ መዶ ሰልሳ የሚሆኑ የጋማ ከብቶች ሞተዋል፡፡

ከዚህ ሞት ከበዛበት ጉዞ በኋላ፣ የጓዝ መስመሩ እስከሚቀጥለው ጥዋት ድረስ አልደረሰም ነበር፡፡ አንድ ወይም ሁለት የሚሆኑ "የተለዩ" ሌሊቱን በኮረብታው ላይ አሳለፉት፡፡



አምባላጌ (የመልደየሱስ አምባ)
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ወልዴ፣ የያቆብ ልጅ ቸቫሊር ደ ፉሪዮሶ[108]፣ ከባህር ወለል አሰር ሺ ጫማዎች ከፍታ፣ በአምባላጌ፣ ምኞት ያላቸው ማረፊያ ከፍሎች ያሉት ሰው፣ ከብዙ ግፊት በኋላ፣ የከሩሴዶቹን እለቃ ወርዶ ለመገናኘት ተሰማማ።

እንደሚበር ሰው አየከነፈ ሳይሆን፣ ኮራ ብሎ፣ ጠቆር ባሉ ሶሰት መቶ የሚሆኑ ጠመንጃ በያዙ ሰዎች ታጅቦ ነበር። እነሱም ወደ ጠቅላይ አዛዡ ቢሮ ሊሄዱ፣ በሀሳባቸው ከአንግሊዝ ወታደር ጋራ ራሳቸውን አኩል በማድረግ ነበር። አህ፣ ያልተጠመቁ ተራ ሰዎች!

ወልዴ፣ በኩራት፣ ጌታ በመሰለ ሁኔታ ወደ ናፒየር ድንኳን ከገባ በኃላ፣ በሰፍራው በነበረው የካምፕ መቀመጫ ላይ ተኮፍሶ ተቀመጠ። ወንድሙ አብሮት ነበር። ወንድምየው ከአንድ ወላጅ የተወለደ አምሳያ ነው፤ ጎላ ያለ ቅንድብ፣ የተንጨባረረ ፀጉር፣ ቁንጥንጥና፣ ፈጠጥ ያሉ አይኖች ያሉት፣ ጎላ ያለ የጉንጭ አጥንቶች፣ ተለቅ ያሉ ጆሮዎች፣ ቀጠን ያለ ከንፈርና ሾጠጥ ያለ አገጭ ያሰው አጭበርባሪ ነው።

ወልዴ ራሱ፣ አዋቂ ሰው ይመሰላል፤ መካከለኛ ቁመት ሲኖረው፣ ደልደል ያለና ፈርጠም ያሉ ጡንቻዎች አለው። በምንም መንገድ ቢሆን መጥፎ መልከም አልነበረውም። ባህሪው ግን ይቅርታ የማይደረግለት ትዕቢት ነው ያሳየው። ልቆ መታየትና አጊጦ መታየትን መውደዱ፣ በእጆቹ ላያ ያደረጋቸው የወርቅ አምባሮች፣ አንደ ምሰሶ በቆመው አንገቱ ላይ ያደረገው ከብር የተሰሩ ሃብሎች፣ በአንበሳ ጋማ የተሸፈነው ያጌጠው ጋሻ፣ እናም ሌሎች በሱ ዙሪያ በሚታዩ ነገሮች መረዳት ይቻላል። ጠመንጃ ያዦቹ የታጠቁት የ6ኛው ከፍለ ዘመን የፖርቱጋል ፉሲሎችና ባለጥንድ አፈሙዝ ጠመንጃዎች ናቸው።

ረዥም ውይይት ቀጠለ። ወልዴ፣ የሱ ሰዎች ለአንግሊዝ ሠራዊት ቀሰብ አንዲሸጡ የሚፈቀድ ለመሆኑ ቃል ገባ፤ ጠቅላይ አዛዡም ጥንድ አፈሙዝ ያለው ጠመንጃ ከነጥይቱና መያዣው ጋር፣ ከዚህ በተጨማሪም፣ ከአዲሱ ማር ተሪዛ ዶላሮች ለሱ ሰላሳ፣ ለወንድሙ ደግሞ ሀያ ዶላር ተሰጠ። በመጨረሻ ሰለ ቴዎድሮሰ ሲጠየቅ፣ ወልዴ ሊመልሰ፣ ቴዎድሮስ የሚዋጋ አይመሰለኝም አሰ። ሰጠታውን ካገኘ በኃላ ግን ወንድምየው የተለየ ነገር መናገር ጀመረ።

አሱም አንዲህ አለ፤ "ወንድሜ ወልዴ አሁን ከተናገረው በተለየ እኔ የምመከራችሁ፣ ቴድሮሰ ይዋጋል፣ ትንፋሹ በሰውነቱ ውለጥ አሰካለ ድረስ ይዋጋል፤ አንደ ቀበሮ ብልጥ ነው፣ አንደ ጫካ ድመት(ጉልጉል ነብር) ፈጣን አይን አለው፣ አንደ አንበሳ ደፋር ነው። በድፍን ሌሊት በላያችሁ ላይ

---

108 (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ይወርዳል፡፡ ከሱ ተጠንቀቁ፣ አይኖቹን ከድኖም አያውቅም፤ ህልምም አያይም፡፡"

ናፒየር፣ "ወንድምህ ወልዴ ግን አይዋጋም ነው ያለው፡፡"

ወልዴ፣ "ይህን ያልኩት ልፈትሻችሁ ነው፡፡ ለአንግዳ ልባችን ከመስጠታችን በፊት፣ ደንባችን ነው፡፡ ወንድሜ በትከከል ነው የተናገረው፡፡ ቴድሮስ ጎበዝ ነው፣ ይገጥማችኋል፤ አይሸሽም፡፡ በሌሊት፣ ጭጋግ ከመልቀቁ በፊት ወይም ሲነጋ ከሱ ተጠንቀቁ፡፡"

ናፒየር፤ "አመስግናለሁ፤ በሉ ከኔ ጋር አንሂድና፣ ዝሆኖቻችንና ያሰንን ትልልቅ መሳሪያዎች እዩ፡፡"

አብረው ሄዱ፣ ዝሆኖችም የዝሆን መሪዎችን ትዛዝ በመቀበል፣ የተለያዩ አንቅስቃሴዎች ያሳዩ ጀመር፤ አንደ መተኛት፣ መንበርከክ፣ ድምፅ ማስማትና ግስግሶ ማጥቃት ጨምሮ ነበር፤ ይህ ደግሞ ሁለቱን አለቆች በጣም አስገርሟቸዋል፡፡ የወታደር ባንዱ ሙዚቃ አስማ፤ የ33ኛው ሬጅመንት ደግሞ የተለያዩ አንቅስቃሴዎችን አሳየ፡፡ ሁለት ፈረሶች አንዲመጡ ከተደረገ በኋላ፣ ስወንድማማቾቹ ለአያንዳንዳቸው ሥጦታ ተሠጡ፡፡ ከዚህ በኋላ፣ ወዳጅነታቸውን በማረጋገጥ ወደ አምባቸው ተመለሱ፡፡ አነሱም ቢሆን በራሳቸው ባንድ አየተመሩ ነበር፤ ከቀንድ የተሠራ ጥሩምባ አየነፉ፣ መለከትና ዋሽንት አየነፉ፣ ሶሰት ከር ያለው (ከራር) እየተጫወቱ ነበር፡፡ ለለር ሮበርት የሰጡት ስጦታ ደግሞ፣ ሁለት ጥሩ ጦሮች፣ ሁለት ጋሻዎች፣ ማር በምንቸትና ሀያ አራት በሬዎች ነበሩ፡፡

ከአፃሎ በፊት፣ 16 ማይሎች ርቀት የሚገኘው ሙካን በመጋቢት 16 በነኘው ብርጌድ ተያዘ፡፡

አምባላጌ፣ ከባህር ወለል በላይ 10ሺ ጫማዎች ከፍታ ላይ ሰለሆነ፣ አናም የአፃሎ ሽለቆ ደግሞ ከአምባላጌ ጫፍ 2500 ጫማዎች ዝቅ ብሎ የሚገኝ ከሆነ፣ በአፃሎ የሚገኘው ካምፕ፣ ከባህር ወለል በላይ 7500 ጫማዎች ከፍታ አለው ማለት ነው፡፡ ሽለቆው የሁለት ማይሎች ስፋት አለው፤ ቦታው ከደረስን በኋላ ከፍታውን ወደላይ ስንመለከት፣ በጎንና በጎኑ ዳገታቸው አስቸጋሪ በሆነው በደብረ ሙሳ ኮረብታዎች ታጥሯል፡፡ ከፍታው፣ ከአምባላጌ ይልቅ ቀጥ ያለ ነው፤ ሰለዚህ ጦሩ ዳገቱን ለመውጣት ከመሞከሩ በፊት መንገዱ ጠመዝመዛ ሆኖ መሠራት ነበረበት፡፡

ጦሩ መንገድ ከጀመረ በሁለት ሰአታት ውስጥ፣ ቀዳሚው ከፍል በተራራው ዳር መታየት ጀመረ፤ ከጦሩ በታች ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሌላ ሜዳ ነበር፣ ነገር ግን በጣም ተለቅ ያለና ከአፃሎ ጎድጓዳ ቦታ ጠለቅ ያለ ነበር፡፡

ወደታች ስንወርድ፣ ግማሹ ላይ የፒላን መንደርን አለፍን፤ ከመንደሩ በላይ በቀጥታ፣ ከዚህ በፊት ካየሁት ሁሉ በላይ በጣም የሚያምር የተፈጥሮ ስራ ይታያል። ብዙ ማዕዘን ያለው ተራራ ሲሆን፣ በሁሉም ጎኑ ቀጥ ያለ የአንድ ሺ ጫማዎች ከፍታ አለው፤ የተራራው አናት ሶስት ስኩዌር ማይል ስፋት አለው። በአገሬው ስዎች፣ አምባ ደባር ተብሎ ነው የሚጠራው። ከአምባላጌ ጋራ አኩል ከፍታ አለው። አንዲህ አይነት የማየደፈር ቦታ ለምን በቴዎድሮስ ተዘነጋ ለሚለው ጥያቄ መልሱ፣ መቅደላ የበለጠ የማይደፈር ቦታ ሰለሆነ ነው ብሎ መገመት ይቻላል።

ከደብረ ሙሳ ደቡብ በኩልና ከአምባ ደባር ግራ በኩል የሚገኘው ሜዳማ ቦታ ከደረስን በኋላ፣ ትንሽ ወራጅ ውሀ አቋረጥንና ከፍና ዝቅ የሚል ሳር ያደገበት መሬት ላይ ተጓዝን። ቀስ ብለንም ገላጣውን ሜዳ ትተን ቁጥቋጦ ባለበት መንገድ መጓዝ ጀመርን። አየደጋገመም፣ ዕይታው ይቀያየር ነበር፤ ያም የተለያዩ በተፍፅሮ ያደጉ ዛፎች፣ አበቦችና፣ ሜዳማ ቦታዎች፣ ሸንተረሮችን በሚያካትት ሁኔታ ገላጣ ፀሀያማ ሥፍራን ጨምሮ ነው። በአስራ ስድስት ማይሎች ጉዞ፣ በተፈጥሮ ባደጉ ዕፀዋት የተሞሉ የሚያዝናኑ ሸንተረሮችና ፈፋዎችን ተራ በተራ አልፈን የሙካን ካምፕ ያለበት ገላጣ ቦታ ፀሀይ ግባት ሲሆን ደረስን።



የአቢሲኒያ መልከተኞች በእንግሊዞች ካምፕ
(ዋቢ መፅሐፍ ፡ቁ. 16)

የምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች

ቁጥር 89፤ ከጦሩ ጋር የዘለቁት ጋዜጠኞች፣ ሄንሪ ስታንሲ ከ"ኒውዮርክ ሔራልድ"፣ ቪሰካውንት ኢዬር ከ"ዴይሊ ቴሌግራፍ"፣ ሲ. እወሰቲን ከ "ታይምስ"፣ ጂ.ኤ. ሄንቲ ከ"ስታንዳርድ"ና "ፓዮኒር"፣ ሉተናንተ ኤፍ.ኤ ሼፓርድ በፈቃደኝነት ከቦምቢይ የህንድ "ዴይሊ ኒውስ" ና "ታይምስ"፣ ሉተናንት ዋይትሳይድ ከ "ሞርኒነግ ፖስት"፣ ከነዚህ ውጭ የጂኦግራፊ ማህበር አባላትና የፈረንሳይ የፓለቲካ ዲፓርትሜንት ተወካይ ይገኙበታል። ከጋዜጠኞቹ በተጨማሪ፣ በብረታንያ ሳይጠየቁ፣ በራሳቸው ፍላጎት፣ በየመንግሥታቸው ተወከለው የመጡ ድምራቸው 13 የሚሆን መኮንኖች ተዘርዝረዋል። የመጡትም፣ ከጣልያን፣ ከፐሩሲያ፣ ከፊረንሳይ፣ ከኔዘርላንደስ፣ ከአውስትሪያና ከስዊይን ነበር።

ቁጥር 101፤ ይህንን ጉዳይ፣ ራሳም አራሱ፣ መቅደላ ዙሪያውን ያሉ ባላባቶችን በማባበል መልከተኞቹ አንዲወጡና አንዲገቡ የረዱት መሆኑን ይጠቅሳል። ራሳም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ቀማሹም ነበዜ በጣም እንደተባበሩት ያትታል። ቴዎድሮስ ለራሳም የሚያስዩትን ወዳጅነት ያዩ የቴዎድሮስ ሰዎች እንኳን ጫና እልፈጠሩበትም። ቴዎድሮስ መቅደላ ሲደርሱ ግን፣ ራሳም በራሳቸው ሰዎች አፍንጫ ሰር የሠራውን ተንኮል ደርሰውበት መቅደላ የነበሩ አዛዦቻቸውን ወርፈዋል። መቅደላ አሰረኞችን ሲጠብቅ የነበረውን ጦር እንዳለ አዲስ ከሳቸው ጋር በመጣ ጦር ተከተውታል። ይህም የነበረውን የውሰጥ መላላከ ለማሰቆም ነበር። ይህ ርምጃቸው ለተወሰነ ጊዜ በመቅደላ አሰረኞችና በእንግሊዝ ጦር መህከል የነበረውን ግንኙነት አቋርጦት ነበር። የሚገርመው ነገር፣ ራሳም፣ እቢሲኒያውያን ታላቸውን ከሰጡ አያጥፉም በማለት እርሱን ይረዱ የነበሩ ሰዎችን ያመሰግናል።

ቁጥር 99፤ ቴዎድሮስ፣ ደብረታቦር ላይ ሰዎችን በሳት ያቃጠሉበት ምክንያት ገለፃ ያሰፈልገዋል። ነገሩ እንዲህ ነው፤ የዳውንት ንዥ የነበሩ እቶ አዲሶ የሚባሉ፤ ከራስ ጉግሳ (ከራሰ አሊ እያት) ጀምሮ እሊቃ የነበሩ ሰው ነበሩ። ሰውየው መቶ አመት ያልፋቸዋል ተብሎ ተመዝግቧል። በምንም አይነት መንገድ ቢሆን ለቴዎድሮስ ታማኝ ነበሩ። ቴዎድሮስ ለንኳን፣ "አሳቸው" በማለት በአክብሮት ነው የሚጠሯቸው። ግብር እንደሌላው ከፍል እልተጣለባቸውም፤ ነገር ግን ለመቅደላ የሚቀርብ ቀለብ ያሰገቡ ነበር። ሽማግሌው፤ መቅደላን ለመውጋት የሚመጣ ሽፍታን በሙሉ ደራሹን ነበር የሚያጠፉት። ሆኖም፣ እንድ ሽፍታ ከሰማኒያ ሰዎች ጋር ሆኖ፣ በሌሊት የአለቃው መንደር ገብቶ፤ ቤታቸውን በእሳት ኢቃጥሎ የሚያመልጠውን ሁሉ ጨረሰ። ሽማግሌው ቀድመው ሰለወጡ አሳቸውም ተገደሱ፤ ከሳቸውም ጋር ከሰምንት እሰከ እሰር የሚሆኑ ቤተሰቦቻቸው በሳት ነደዱ። የእባቱን መሞት ያየው ልጃቸው፣ ከእምሰት መቶ ሰዎች ጋር ሆኖ፣ አባቱን ሳይቀብር፣ ከጎላቸው በመለከስ፣ ሽፍቶቹ እርፈው ብርንዶ ከሚበሱበት ቦታ በሁለት በኩል እሰከበበ ይይዛል።

ሸፍቶች አለቃ እጁን አልሰጥም በማለቱ አዛው ተገደለና፣ አስከሬኑም ወደ ዳውንት ተመልሶ፣ ሜዳ ላይ ተጣለ:: ከሱ ጋር የነበሩ ሸፍቶች አጃቸውን ቢሰጡም፣ ለፍርድ፣ ወደ ንጉሡ ወደ አፄ ቴዎድሮስ፣ ወደ ደብረታቦር ተላኩ:: የሸማግሌውን መገደል የሰሙት ቴዎድሮስ አልቅሰው አንድ ቀን ሙሉ ሰው ሳያዩ ዋሉ:: ሸፍቶቹን ግን፣ ራሳቸው ባመጡት መንገድና የዳውንቱን አዛውንት ጌታና ቤተሰቦቻቸውን በገደሉበት መንገድ፣ በጎጆ ተዘግተው በሳት አንዲቃጠሉ ተደረገ:: ይህ ዜና በምዕራባውያኑ በኩል ተጋኖ ሲነገር ይታያል:: በተቃራኒው ግን የደላንታው ገዥ፣ አርቅና፣ የራሳም ወዳጅ አንደነበርና ተላላኪዎችን ሁሉ አይደበቀ ይረዳው አንደነበር ተዘግቧል:: ራሳም፣ የደላንታውን ገዥ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር፣ ታማኞች ይላቸዋል:: ራሳም፣ ሰለ ዳውንት፣ ሰው በቤት አንዳለ መቃጠሉን ሲገልፅ፣ ሌቦቹ ያደረጉትን ነገር አንስቶ፣ "ቴዎድሮስ ሌላ ጭካኔ ተማሩ::" ይላል:: ቴዎድሮስ በአከብሮት አርሰዎ አያሉ ከሚጠሯቸው አራት ሰዎች፣ አቶ ኦዲሶ አንዱ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ፣ ጳጳሱ፣ አፄ የሐንስ ሶስተኛ አና ደጃችዝማች ብሩ ነበሩ:: ደጃዝማች ብሩ ጎሹ፣ የጎጃሙ ገዥ የደጃች ጎሹ ልጅ ናቸው፣ ቴዎድሮስ አንደባለሟል ከደጃች ጎሹ ቤት ኖረዋል:: ደጃች ጎሹ ለጦርነት ሲሰለፉ፣ ቴዎድሮስ፣ በዚያን ጊዜ፣ ካሳ፣ አባከዎ አባትና ልጅ ነን ብለው አንዳይዋጉ ለምነው ነበር:: ይህም ልመና ቀጥሎ፣ ከልጃቸው ከብሩ ጎሹ ጋር ሲሰላለፉ፣ ደጃዝማች ካሳ ብሩ ጎሹን ተው ብለው ለምነው ነበር::

ቁጥር 102፣ መንገዱን ከኋላ ደርሰው ያዩት አንግሊዞች በጣም አንደተደነቁበት ተገልጧል:: ቴዎድሮስ ራሳቸው ሠርተው የሚያሠሩ መሪ ነበሩ:: ከዚህ ቀደም አንደተጠቀሰው፣ ንጉሡ የመንገድን ጥቅም በጣም የተረዱት ይመስላል:: አንድ ጊዜ ኪጋፋት ሲመለሱ፣ በመንገዱ ላይ የድንጋይ ቁልሎች ተከምረው ዘግተውት ነበር:: የድንጋዮቹ ብዛት፣ ከቴዎድሮስ ጋር አብረው ለነበሩት አውሮፓውያን አንኳን ተስፋ አስቆራጭ ነበር:: ሆኖም፣ ንጉሡ ከፈረሳቸው ወርደው ድንጋይ ተሸክመው ወደ ዳር መጣል ሲጀምሩ፣ ይህን ያዩ ተኪታዮቻቸውና ሠራዊቱ ምሳሌውን በመከተል በአጭር ጊዜ ውሰጥ መንገዱ አንዲከፈት አደርገዋል:: በሌላ አጋጣሚም አንዲሁ፣ ሀይለኛ ዝናብ ዘንቦ የአፈር ደለል መንገዱን ዘግቶ ፈረሰኛ ማሻገር ባልቻለበት ሰአት፣ ቴዎድሮስ ማንንም ሳያዙ፣ ራሳቸው በጦራቸው ደለሉን ሲቆፍሩ ያዩ አውሮፓውያን ዘግበውታል::

ይህን አይነት ሠርቶ የማሠራት ባህሪ፣ ካሳ ገና በሸፍትነት ጊዜ ነው የጀመሩት:: ቋራ ጠፈ ሆነ(ደረቅ) የሚታረሰም በጠፋ ጊዜ፣ ካሳ ራሳቸው ጫካውን እየመነጠሩ፣ ወታደሮቻቸውም አብረው፣ ለአርሻ አዘጋጅተው አህልም ተዘርቶ አገሩ ተመልሶ ለም ሆኗል::

ቁጥር 103፣ ዋግሹም ጎበዜ፣ የዋግሹም ገብረመድህን ልጅ ናቸው:: አባትዬው ዋግሹም ገብረመድህን ከራስ አሲ በኩል ሆነው ቴዎድሮስን ሲዋጉ ቆስለው ነበር:: ቴዎድሮስ ግን፣ አይዝዎት በማለት፣ መቶ ነፍጥ ሠጥተው በሹመት ወደግዛታቸው ወደ አገው መልሰው ልከዋቸው ነበር:: ሆኖም ዋግሹም ገብረመድህን፣ ምህረት

አድረገው መልሰው በሾሚቸው በእዬ ቴዎድሮስ ላይ ይሸፍታሉ። በማንቦት ወር፣ ገረገራ የሚባል ቦታ ላይ፣ ቴዎድሮስ የዋግሹውን ጦር ወግተው መሪዎቻቸውን ማርከው፣ ቀሪዎችን ምህረት አድረገው ሲለቁ፣ በዝረው ህግ፣ በፍትህ ነገሥት እስፈርደው፣ ዋግሹም ገብረመድህንን ከሌሎች ሰምንት ሰዎች ጋር በለቅላት ይቀጣሉ። ቦታው ረጅም ግራር ይባላል። ፀሐፊው ሲደመድም የከዱትን ገብረመድህን፣ እማዚአብሔር ከንጉሥ እጅ ጣላቸው ይላል። ቴዎድሮስ ወደ ዋግሹም ገብረመድህን ከመዝመታቸው በፊት ራሳቸው የገጠሙት ግጥም፣ "ንጀምን ብንቀጣው በነፍጡ ተቀጣ፣ ወሎንም ብንቀጣው በእሳቱ ተቀጣ፣ ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለሰቆጣ።" የሚል ነበር።

ዋግ ሹሞች፣ የዋግ ግዛት ገዥዎች ነበሩ። ሥልጣኑ ከትልቁ ዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰለሞናዊው ሥርወ መንግሥት በመነኩሴው በእቡነ ተክለ ሀይማኖት እማካኝነት ሲዛወር የቀረውና የሚገዙት ግዛት ዋግ ብቻ ነበር ነበር። የየጁ ኦሮሞዎች፣ በንጉደር ቤተ መንግሥት ሆነው በጌምድር፣ ጎጃምን ሲገዙ፣ በራሰ ጉግሣ ጊዜ፣ ዋግ በዋግሹም ከንፉ ሥር ነበር፤ ከንፉ ከራሰ ጉግሣ በኩል የመጣውን ጥቃት ተከላከለው በሰላም ይኖሩ ነበር። በትግራይ፣ በዚያን ጊዜ ገዥው ራስ ወልደ ለላሴ ነበሩ። ዋግሹም ከንፉ ሲሞቱ፣ ልጃቸው ዋግ ሹም ወሰን ተተኩ። አሳቸው ሲሞቱ፣ ትከከለኛው ወራሽ ዋግ ሹም ተፈሪ ሆነው እያለ፣ ቴዎድሮስ፣ ሥልጣኑን ለዋግ ሹም ገብረ መድህን ሠጡ። ገብረ መድህን ራሳቸው በናታቸው በኩል የዋግሹም ከንፉ የልጅ ልጅ ናቸው። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው ሲሸፍቱ፣ በቴዎድሮስ ተቀጡ፣ የተወሃደሉት በመከዳት ነበር። ቴዎድሮስ ዋግ ሹም ተፈሪን በቅርብ በማድረግ ከ100ሺ ሰዎቻቸው ጋር ወደ ራሳቸው ካምፕ ነው የወሰዷቸው። ዋግ ሹም ገብረ መድህን የላስታውን ገዥ የደጃች መሸሻን እህት አግብተው፣ ነበዜና ብሩ የሚባሉ ሁለት ወንዶች ይወልዳሉ። ልጆቹ፣ የእቢታቸውን መገደል ሲያዩ አንበቀላለን በማለት ሸፍተው ከርመው ነበር። ከሁለቱ፣ ነበዜ ነበሩ ብዙ ጭፍራ የነበራቸው። የጭፍራቸውን ቁጥር የጨመረላቸው ነገር ደግሞ፣ አናታቸው፣ ከባልየው ሞት በኋላ፣ የዋድላውን ገዥ ደጃዝማች ወልደ ቂዮርቂስን እግብተው ለለነበር፣ ለወጣቱ ነበዜ ተጨማሪ ሀይል እንዲያገኝ አድርጎታል። በውሰጥ እንደሚነበው፣ አጎትየው ደጃች መሸሻ የዋግ ሹም ነበዜ ጦር መሪና ተወካይ ነበሩ።

ቁጥር 104፣ ደጃች ካሳ ምርጫ፣ መጀመሪያ በዋግሹም ነበዜ የእንደርታ ገዥ ሆነው ተሹመው ነበር። ደጃዝማች ካሳ፣ የተምቤኑ ገዥ የደጃች ምርጫ ልጅ ናቸው። እናታቸው የእንደርታው፣ የደጃዝማች ድምፁ ልጅ ነበሩ። ደጃዝማች ድምፁ ራሳቸው የራሰ ወልደ ሰላሴ የእህት ልጅ ናቸው። ሰለዚህ ካሳ ምርጫ በናትም ሆነ ባባታቸው ለሥልጣኑ ትከከለኛ ሰው ነበሩ። ዋግ ሹም ነበዜ በእንደርታ ላይ እስኪሾሟቸው ድረስ ብዙም የሚታወቅ እንቅስቃሴ እልነበራቸውም። ከእንደርታው ሹመት በኋላ፣ በመጠናከር ነበዜ ላይ ሸፍተው፣ ዋግሹም ነበዜ ከሳቸው ጋር የሸሚቸውን የኢጋሜውን ደጃች ደረሶን፣ ሀራማት በተባለ ቦታ ላይ ከፍተኛ ውጊያ በማድረግ

ደጃዝማቹን ካሸነፉ በኋላ ራሳቸውን ቻሉ:: ለትንሽ ጊዜ፣ የቴዎድሮስ ደጋፊ ሆነው ቆዩ፣ ያም ቴዎድሮስ የዋናው ጠላታቸው የጎበዜ ጠላት ስለነበሩ ነው:: ወዲያውኑ ግን፣ በእኤአ 1867 አድዋ በመገስግስ የቴዎድሮስን ሹም ደጃች ባሪያን አሸንፈው ትግራይን ጠቅልለው ያዙ:: ጎበዜ፣ በላስታ ተቀምጠው ወደ ትግራይ ተሻግረው (እንግሊዞቹ በሚመጡበት መንገድ) ካሳን ለመውጋት አስበው ነበር:: በኃላ ግን የአፄ ቴዎድሮስን እንቅስቃሴ በመከታተል ብቻ ተወሰኑ::

ዋግሹም ጎበዜ ለእንግሊዞቹ ከፍተኛ ትብብር ቢያደርጉም፣ መሠረታዊ ስምምነቱ፣ እንግሊዞቹ አስፈሪውን ቴዎድሮስ ካሸነፉ በኋላ፣ ከአቢሲኒያ እንዲሰወሩ ነበር:: መልሶም፣ የመጀመሪያው የናፒየር አዋጅ ትልቅ ሚና እንደነበረው አይካድም::

እንግሊዞችን ያስቸገረ ብቸኛ መሪ ቢኖር ወልደየሱስ ነበር:: ወልደየሱስ፣ ካሳ ምርጫን አያምንም፣ ምንም እንኳን ለእንግሊዞች ቃል ቢገባ፣ ካሳ ይወጋኛል ብሎ ይፈራል:: ወልደየሱስ፣ የራሱን ሰዎች ለእንግሊዞቹ ቀለብና ሌላም ነገር እንዳይሸጡ ከመከልከል በተጨማሪ፣ ሌሎች እንግሊዞችን የሚረዱ አቢሲኒያውያን በግዛቱ እንዲያልፉ ከልከሎ ነበር:: የእንግሊዞችን የቴሌግራፍ መስመር ለማጥቃት ሞክሮ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ሃሳቡን የካሳ ጦር አከሽፎበታል:: የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዞቹም ሆነ፣ አሜሪካዊው ፀሀፊ፣ ወልደየሱስን በከፉ ቀለም ሲቀቡትና ሲያወግዙት ነው የሚታየው:: እንደ ከለመንት መርካም አገላለጥ፣ ወልደየሱስን፣ "የወዳጅ ወራሪዎችን" ያስቸገረ ብቸኛው አቢሲኒያዊ መሪ ይለዋል:: ወንድምዬው ባሪያ ጊዮርጊስ ይባል ነበር:: ወልዴ፣ የቀዳሚው ጦር አዛዥ ኮሎኔል ፋይሪ(መርካም፣ ፈታውራሪ ፋይሪ ይለዋል) የመንገድ አቅጣጫ ሲጠይቅው፣ ቀጥተኘው በእርሱ እምባ ስር የሚያልፈው መንገድ እያለ፣ በማሳሳት ወደ ሌላ መርቶታል:: በዚህም ምክንያት፣ እንግሊዞቹ እስኪነቁ ድረስ የጦሩ ክፍል በከባድ መንገድ ሲንገላታ ከርሞ ጉዳዩ ከታወቀ በኋላ ግን ዋናው ጦር በቀጥተኛው መንገድ በአምባላጌ ስር ተጉዟል::

ቁጥር 108፣ ፀሀፊው ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ግልፅ አይደለም:: እንደ አፃፃፉ የወልዴና የወንድሙ ኩራትና ከእንግሊዞቹ ጋር የሚፈለገውን ያህል ስምምነት አለመፍጠራቸው ያናደደው ይመስላል:: ለዚህም ነው ስድብ የጨመረበት:: በዚህ ፅሁፍ እንደታየው፣ ከእንግሊዞች ጋር ያልተባበረ ሁሉ በከፉ አይን ብቻ ሳይሆን በከፉ ዘገባ ነው የተቀመጠው:: ቴዎድሮስን ለአውሮፓ አንባቢዎች አከፈተው ቢፅፉ የሚገርም አይሆንም::

ምዕራፍ ስምንት

የአቢሲኒያ ዕይታዎች፣ በተራሮች የታቀፈው የአሸንጌ ሀይቅ፣ የአልኮል መጠጣችን አንዲቀር መደረጉ

ከረኸም ጉዞ በኋላ እንደሚጠበቀው ሁሉ፣ ወታደሮች በሚቀጥለው ቀን መካን(መቃን) ላይ ማቆም ነበረባቸው።።

የአዲሱ ካምፓችን አካባቢው ብዙ ኗሪ ያለበት ነው።። ተወላጆቹ አንግዶቹን ለማየት በብዛት ይመጡ ነበር፤ ሲመጡም የተለያዩ ነገሮች ለሽያጭ ይዘው ነበር።። የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች ከትግራይና ከአዲግራት ሰዎች ቀላ ይላሉ።። አስካሁን ካየናቸው ሰዎች በሰውነት ፈርጠም ያሉና ስፋ ያሉ ናቸው።።

በመሀከላቸውም ከአሮሞ ምድር የመጡ፣ ራሳቸው ላይ ቱርባን ያደረጉ ሶስት ሙስሊሞች ረዘም ያለ ከበሬ ቀንድ የተሠራ ጥሩምባ አየነፉ ብቅ አሉ።። ሰዎቹ፣ የአሮሞው አለቃ መልከተኞች ናቸው።። አለቃው፣ በህዝቡ ሰም ለአንግሊዙ ንጉሥ፣ ስር ሮበርት ናፒየር፣ ሰላምና ወዳጅነቱ ለማሰታወቅ ነው።። ምንም መግለፅ ባይኖርብኝም፣ ይህን የአሮሞውን አለቃ መልካም ምኞት፣ ሽማግሌው በምስጋና ነው የተቀበለው፤ በአፀፋውም ቃል ለተገባው ወዳጅነት የገንዘብ ሽልማት እንዲሠጥ አደረገ።።

ሚዳቋዎች፣ ጥንቸሎችና ሌሎችም የሚታደኑ አንስሳት አንደልብ ነበሩ።። የአንግሊዝ መኮንንኖችም እንደ ጀግሪ አዳኝ በገፍ ወጡ፤ በነባር ተፈጥሮ ላይ ያደረሱት ጉዳትም ከፍተኛ ነበር።። ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ ሰው፣ በአካባቢው የነበረ የጫካ ዝሆን ተኩሶ ገድሎ፣ ሽታው ሀገሩን ዙሪያውን አስኪበጠብጥ ድረስ ግዳዩን የወደቀበት ቦታ ላይ ጥሎት ሄዷል።። አደኑ የተሳካላቸው ሁኔታ በስዕላዊ መንገድ የተነገረም አለ፤ አያንዳንዱም አንድ ወይም ሁለት ያደኑትን ይዘው ገብተዋል።።

በ18፣ በጥዋቱ ጦሩ ካምፑን ነቅሎ ወደ አሸንጌ ሀይቅ መንገድ ጀመረ።።

መሶብ ተራራ ግርጌ አስከንደርስ ድረስ፣ ለመጀመሪዎቹ ስድስት ማይሎች መንገዳችን ሽቅብና ቁልቁል ሆኖ፣ በግራና በቀኝ ከፍ ባሉ ኮረብታዎችና ጫካዎች የታጀበ ነበር።። ተራራው ግርጌ ስንደርስ፣ ወደ ላይ አየታገልን ስንወጣ፣ አርስ በራሳቸው በሚደራረቡ ኮረብታዎች ተከበናል።። ከዚህ በፊት በአግር ስጓዝ ያየሁትን የደቡባዊ ተራራማ ከፍል ይመስላል፤ ነገር ግን ይህ ትሮፒካል ውብት፣ በአቢሊኒያ ካየነው በፍፁም ተቃራኒ ነው።። ሽቅብ፣

በረኀኞችም አናናስ ዛፎች በተሸፈነ ቀጥ ባለ ዳገቶች ዙርያ በመውጣት ፍዳችን አዩን። በሁሉም አቅጣጫ ድንግል ጫካዎች ይታያሉ፤ በቀኝና በግራ ተሰፋፍተው ወደ ላይ ማቆሚያ የለለው በሚመስል ከፍታ ተዘርግተዋል፤ በላያችን ላይ ደግሞ ደሰ የሚል ቀዝቀዝ ያለ ጥላ ፈጥረዋል። በሚታየው ጥላቸው ሰር ብርቅዬ የሆነ ቀለም ያላቸው አበቦች ፈንድቀዋል።

ወደ ላይ ወደ ተራራው የሚወስደው መንገድ በጣም መጥፎ ነው፤ አንዳንድ ቦታም በጣም አደገኛ ነበር። ከአራት ማይሎች ቀጥ ያለ ዳገት በኋላ፤ ከዛፎቹ ጥላ ወጥተን፤ ስማዬን ማየት ቻልን፤ ሌላ መጠነኛ ዳገት፣ መንፈሰ በሚያረካ አረንጓዴ የተሸፈነ ቦታ ላይ ነው የቆምነው - አሱም የመሶብ ተራራ የመጨረሻው ከፍታ ነበር።

ከታች፣ ከሰራችን፣ ከሶሰት ሺ ጫማ በታች፣ የአሸንጌ ሀይቅ ዙሪያውን በከበቡት ተራራዎቹ ታፋ ላይ ያንቀላፋል።

የጦር ሠራዊት አንድ ቦታ ቆሞ የአካባቢውን ውበት ለማየት ፍላጎቱም የለውም፤ ሁላችንም መሶብ ተራራ ላይ ቆመን፣ ለሰአታት ይህን ትሮፒካዊ ውበት ያለውን ዕይታ ብንመለከት ደስ ባሰን ነበር፤ ወታደሮቹ በብዛት አየተግተለተሉ በመምጣት ዙሪያችን ወረሩት፤ ወደፊት አንድንጓዝም ግፊት ኀረና መከላከል የማንችለው የተጓዦቹ ወታደሮቹ ማዕበል አብሮ ወሰደን።

ከዚህ የተከተሉት ደግሞ፣ ከሸለቆው ሰር ጠመዝማዛ መንገዶች፣ ወጣ ያሉ ቋጥኞች፣ አንድ ላይ አጅብ ብለው የሚገኙ አለቶችና ትልልቅ ድንጋዮች ኀሩ። አለቶቹና ድንጋዮቹ ብርቅ ባለው የፀሀይ ብርሃን ደመቅ ያሉ ቀለማት ያሳያሉ፤ አለዚያም በቋጥኙ ጥላ ወይም ወጣ ብለው በተንጣለሉት የዛፎች ቅርንጫፎች ጥላ ይሸፈናሉ።

ዙሪያውን አየዞርን፣ መንገዳችንን በቋጥኝ ሸካራ የአለት ግድግዳዎች ጎን በማድረግ ወደላይ አየተጓዝን፤ ጥምዝምዝ ያለ ወራጅ ወንዝ የመሰለ መለመር ይዘን ራስ የሚያዞሩ ገደሎችን የሚያገናኙ መሻገሪያዎችን አየተጓዝን በመጨረሻ አሸንጌ ሜዳ ላይ ደረስን።

ከአስራ አራት ማይሎች ጉዞ በኋላ፤ ከሀይቁ ጠጋ ብለን፤ ከፍት ያለ ቦታ ላይ ካምፕ አደረግን። የመንገዱ የተፈጥሮ ሁኔታ፣ ጓዝ የያዘውን ከፍል በጊዜ ከመድረስ ከልከሎታል። ፀጥና ረጋ ያለው የሀይቁ ውሀ፣ ከረዥም ጉዞ በኋላ የደከመውን ሰውነታችን ለማቀዝቀዝ ውስጡ አንድንከር ገፋፍቶናል። ምንም አይነት ጉማሬ በቦታው የነበረ መሆኑን የሚገልፅ ምልክት የለም። ወይም ከሰው የባሰ ሌላ ከፉ አውሬ ለመኖሩም ምልክት የለም። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከዚህ ቀደም፣ ከፉ አውሬዎች ያጋጥሚቸዋል ተብሎ ሲወራ የነበረውን ወሬ መሠረተ ቢስ ያደርገዋል።



በአሸንጌ ሀይቅ አጠገብ ጉዞ

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

በርግጥ ሁለት ወይም ሶስት የሆኑ በተከሎች የተሞሉ የተቋሩ ውሃዎች ከሀይቁ አጠገብ ነበሩ። እነሱም ቢሆን ከትንንሽ አሳዎች በስተቀር ሌላ አይነት ሕይወት አልነበራቸውም። ሀይቁ፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የተለያዩ የእዋፍ ዘሮች አልፎ አልፎ ይታዩበታል። እነዚህም ዳከዬዎችን ጨምሮ የተለያዩ የባህር አሞራዎች ነበሩ።

በእሮሞዎች በኩል ባለው የሀይቁ ዳርቻ፣ ሰፋ ባለው ደን ውስጥ፣ ብዛት ያላቸው ሚዳቋዎች ይገኛሉ። ከእነሱም ጋር፣ ተኩላ፣ ጅቦችና ግስላዎችም አሉበት። ነገር ግን ይህ ሥፍራ ደግሞ የሙስሊም አፍሪት* ያለበት ቦታ ነው። ተወላጆቹ በጣም በጭንቀት ተውጠው ሊነግሩን የፈለጉና አንዲገባን የጣሩበት ሁኔታ ነበር፤ ሰለዚህ በዚህ ቦታ ማንም ፈረንጅ መሄድ የለበትም፤ ምክንያቱም አፍሪት ስላለ በማለት - ይቆረጣል፣(ጣቶቻቸውን ጉሮሯቸው ላይ የመቁረጥ ምልክት አያሳዩ፣ ምልክቱ ራሱ ይበቃል።)

(*የሙስልማን እፍሪት ማለት ከፋርስ አህሪማን ወይም የሰካንዲኒቪያን ሎከ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ያ ማለትም መጥፎ መንፈስ ወይም ጂኒ ማለት ነው)[109]

የሚያነቃቃ ዋናና ገላ መታጠብ ባይኖር ኖሮ፣ ምናልባትም ከነበረን ድካም የተነሳ መጥፎ መንፈስ መኖሩን ባልተከራከርንም ነበር፤ ነገር ግን፣ ጤናማ በሆነው ገላ መታጠብ ምክንያት ከነበረን ስንፍና ስለተነቃቃን የመጥፎ መንፈሱን ጉዳይ በጣም ነበር የተከራከረነው፤ እናም በተፍጥሯችን ባለን ሀሳብ ግትርነት፣ እንዲያውም በሀይቁ ዙሪያ እየጋለብን ሄድን። በእሮሞዎች በኩል ያለው የሀይቁ ዳርቻ፣ ያለምንም ጥርጥር ምስጢራዊና የሰይጣን ወይም በታሪክ የሚጠቀስ ዲያብሎስ ቤት መኖሪያ በሚያሰመስለው ሁኔታ በጣም አስፈሪና ፀጥ ያለ ነበር፤ በዚህም ምክንያትና በተጨማሪም በአእምሯችን ደግሞ ሰዎቹ ያሳዩን የአንገት መቆረጥ ምልክትም ስለነበር ወደ ውስጥ ገባ ብለን ቦታውን መመርመር ጥቅም የለውም ብለን አሰብን።

ብዛት ያላቸው የበሰበሱ እንጨቶች በምስራቅ በኩል በሚገኘው በሀይቁ ዳርቻ አሉ። በሰሜን በኩል ያለው ዳርቻ፣ ከኛ ካምፕ በትንሽ ወደ ምስራቅ በኩል ወደ አምስት ማይሎች የሚሆን ስፋት ላይ ያለው ቦታ በጣም አደገኛ ነው። በጣም ሰፈ የሆነ የሚያዘቅጥ*፣ የረጋ ረግረግ ነው። ቦታው፣ ብዛት ባላቸው ልጋግ የመሰለ ነገር በተሞሉ ፈሳሾች እንደ ወንዝ መሰመሮች ይቆራረጣል። የመሬቱን እደገኛነት ከመገንዘቤ በፊት የኔ የአረብ ፈረስ አሰከ ግማሹ ደረስ መስመጥ ጀመረ፤ ሰለዚህ፣ ካምፕ ለመድረስ ሰፋ ባለ ከብ

---

109 በአንዳንድ የወንዝ ከፍሎቹ እንደዚህ ሠይጣን አለባቸው መባል የተለመደ ነበር።

ዳርዳሩን መዞር ነበረብኝ፤ የሀይቁ ጠቅላላ ዙሪያው ወደ አሰር ማይሎች ይሆናል።

(*በተወላጆቹ የሚነገር ታሪክ አለ፤ ይህም ሶስት መቶ የሚሆኑ የእሮሞ ፈረሰኞች አቢሲኒያኖቹን ሲያሳድዱ በዚህ ቦታ ሲደርሱ አንድ ሰው ሳይተርፍ ሁሉም ወዲያውኑ በመሰመጥ ተሰውረዋል።)

የመጨረሻው የጓዝ መሰመሩ ከፍል ካምፕ ሲደርስ አኩለ ሌሊት ነበር፤ የኔ ጓዝ ወደኋላ ከነበሩት ውስጥ ሰለነበር ድንኳኔ ከመወጠሩ በፊት ለአሰር ሰኣታት መጠበቅ ነበረብኝ።

የሚቀጥለው ቀን አንሰሶቹ መጓዝ ሰላልቻሉ የግድ ማቆም ነበረብን። የነበረን ቀለብ አያለቀ ሰለነበር፤ ከመንቀሳቀሳችን በፊት አዲሰ ማግኘት ነበረብን። በዚህ ምክንያት የሚደርሰን መጠን በግማሽ ተቀነሰ።

አኩለ ሌሊት ሲሆን፣ ከትልቁ ገሸ መልከተኛ መጣ፤ ትልቁ ገሸ ወይም ኡሌማው፤ መንፈሳዊ መሪ፤ ንጉሥም ሰለሆነ፣ በአሸንጌ ዙሪያ ባሉ መንደሮች ለሚኖሩ የሙሰሊም ዘላኖች የሁሉም ነገር መሪ ነው። መልከተኛው ደግሞ የኡሌማው ወራሽ የሆነው ልጅየው ነበር። በሰውነት ቅርፅ መዳኘት የምችል ብሆን፤ መልከተኛው አይኑ የፈዘዘና አእምሮው ቢሆን የጥንቸል አይነት ነበር።

ለሰር ሮበርት ናፒየር የሚሠጥ ደብዳቤ ይዟል። በደብዳቤው፣ ባገሩ ባህል መሰረት ከሚደረገው ከተለመደው ሰላምታና መልካም ምኞት ቀጥሎ፤ ኡሌማው ከፊረንጆቹ ጋር ሰላም ለመፍጠር የሚፈልግ መሆኑን ይገልፃል። በመንፈሳዊ አመለካከቱም፤ አሪት፣ አዲሰ ኪዳንና ቁራን፣ በኛ በክርሰቲያኖቹና በሙሰሊሞች ሀይማኖት መህከል የጋራ መሆኑን ያሰረዳል፤ በፀሎቱም አንደሚያሰታውሰን ነገረን፤ አላህ አንዲጠብቀን መረቀን፤ ጠላቶቻችን ብዙና ጠንካሮች ሰለሆኑ እንድንጠነቀቅም መከረን። ባገሩ ደንብ መሠረትም ዋጋው አንድ ዶላር የሚሆን አንድ ማሰሮ ሙሉ ማር ላከልን።

ሰር ሮበርት ናፒየር፤ የእሮሞው መንፈሳዊ መሪ የላከውን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ፣ በሰውየው ሥልጣን ደረጃ የሚሆን ሰው በመልበሰ ሊያጌጥበት የሚችል የልብሰ ሰጦታ ሰመልከተኛው ሠጠ። ይህንን አይነት በወርቅ የነቆጠ የሚያምር ልብሰ ሲሰጠው፣ ሰውየው የተደሰተ መሆኑን የሚገልፁ የሰውነት ምልከቶች፤ ትንሽ ጡንቻ መንቀሳቀስ፣ ወይም አይን አርግብ ማለት፤ ወይም የፈገግታ ምልከት እንኳን ሳይታይበት፣ ስሜት የሌሰው ከሰም የተሠራ አሻንጉሊት ይመሰል ሳይነቃነቅ ቆሞ ቀረ።

ከሰአት በኋላ ደግሞ ሌላ የእሮሞ አለቃ ከተዋጊዎቹ ጋር በመሆን፤ የወዳጅነት ምልከት አንዲሆን የጦሩ ጫፍ ወይም ሰለታቸው የተቆረጠ የጦር ዘንጎች ይዘው ወደ ካምፕ መጡ። አለቃው በትከከል መልከኛ የሆነ ሰው

ክር። ይህ የማርሰ ልጅ የመሰለ ሰው ከኛ ንጉሰ ጋር ወዳጅነት እንደሚፈልግ ገለፀ፤ ሰሰዚህም ልከ ንጉሣዊ ሥልጣን ያለው ሰው የሚገባውን ከብር እይነት ተሠጠው።

ማምሻውን የተለየ ሁኔታ ታየ። ካምፕ በሚጠብቅ የሂንዱሰታን ሰው፣ እንድ አሮሞ ለስርቆት ሲያመራ ሰለታየ፣ ተይዞ በሌብነት ተከሰ ከጦር ወታደራዊ ዳኛ፣ ኮሎኔል ፍሬዝር ፊት ቀረበ። ወዲያውኑ ትልቅ ጉርምርምታ ይሰማ ጀመር። የሰውየው እገር ሰዎች ደግሞ፣ እንደ ጎሳ ባህላቸው ሰውየውን ለመጠበቅ በፍጥነት ከበቡና ለማሰለቀቅ ሞከሩ። እንድ ወጣት፣ ወንድሙ ነው የተባለ፣ ከፍ ያለ ጩኸት አሰማ። ተጠርጣሪው ኢጆቹ ወደኋላ የፈጥኝ ታሰረው፣ ታምቡር ከተመታ በኋላ የወታደራዊ ፍርድ ችሎት ተያዘ። ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ሰውየው በሰዎች እንደተያዘ ጀርባው ሰላሳ ሰድስት ጊዜ እንዲገረፍ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ካፒቴን ሰፒዲ ከነበረበት ግብጥ ተጣድፎ በመምጣት፣ ሰውየው በአገሩ ሰዎች ቢዳኝ ይሻላል ብሎ ሀሳብ አቀረበ። ፍሬዝር፣ በመቃወመ ለጦሩ ምሳሌ መሆን አለበት ብሎ ተከራከረ። ሰፒዲ ሊሚገት፣ ከአለቆቹ ጋር ሰላም ሰለተፈጠረ፣ ከመጀሪያው በከባድ ቅጣት መጀመር ነገር መጫርና ደግነትም አለማሳየት ይሆናል አለ።

"ታዲያ ምን ማድረግ እለብኝ?" ፣ ፍሬዝር ጠየቀ።

"ያገሩ ሰዎች ይዳኙት፤ አንተ ከፈለግኸው በላይ ከባድ ቅጣት ይሰጡታል።" አለ ሰፒዲ።

"መልካም፣ እንተ እንዳልከ ይሁን።" አለ ፍሬዝር። እንደተባለውም፣ የተጠርጣሪው ወገኖች ከሆኑ ሰዎች (ጁሪ) ዳኝነት የሚሰጡ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ሰዎቹ ያደረጓቸው ከርከርና ንግግሮች የኒውዮርከ ጠበቆች ሊከራከሩ ከሚችሉት በእሰር እጥፍ የሚሆን ተደጋግሞ ነበር። የሚገርም ነው፣ ያን የመሰሰ ሙግት፣ ያን የመሰለ ዘዴ፣ ያን የመሰለ ድርጊት!

ሽበቶ ጢም ያለው ሽማግሌ ያቀረበው ሙግት ፍሬ ነገሩ፣ ሰውየው ሊሰርቅ መፈለጉን ማንም መረጃ የለውም፤ በጁ ያነሳው ለማየት ብቻ ብሎ ነው። እና "ያ ወንጀል ነው ወይ?" ፣ ብሎ ጠየቀ። "ሆኖም፣" ቀጠለ፣ "መቅጣት ካለብን፣ ፊረንጁ እንዳለው፣ እሃ! እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ህገር ሰዎች አይቀጡም፤ በነሱ ላይ እምነት መጣላችን ተሳሰተናል። ሰለዚህ፣ እኔ የምዳኘው፣ በዱላ ሰድሰት ጊዜ ተመትቶ፣ ሊሰርቅ ነው የተባለውን ዕቃ ዋጋ እንድ እራተኛውን ይከፈል።" በዚህ ፍርድ መሠረት ቅጣቱ ተከናወነ። እንዳንድ የወታደራዊ ሥነ ሥርአት አሰጠባቂ የሆኑ ሰዎች ግን በሁኔታው ተበሳጭተዋል።

በ20፣ የእንግሊዝ ሠራዊት እንድ ሜዳ ያዘ። ሜዳው ከእሸንጌ ሀይቅ ዙሪያ ከሚገኘው ዝቅተኛ ቦታ ጋር የተያያዘ ነበር። ከሀይቁ ሰሜን በኩል ከሚገኘው ከኛ ካምፕ ወደ ሰባት ማይሎች ርቀት መስኒታ ከተባለ ቦታ አጠገብ ነበር። ወደዚህ ካምፕ መሄጃው በሀይቁ በምዕራብ በኩል ነበር፤ ከካምፑ በደቡብ አቅጣጫ አራት ማይሎች ርቀት መስኒታ ይገኛል።

የእንግሊዝ ጦር ከመስኒታ ተነስቶ አሰራ እንድ ማይሎች በመጓዝ ወደ ላት ሄደ።

እንዲያው የሚያደከም ድግግሞሽ ላለማድረግ፣ የዚህ መንገድ ጠባይ፣ ከዚህ ቀደም ካለፍንባቸው የብዙ ኮረብታዎች መንገድ ጋር ይመሳሰላል።

በጋማ ከብት ላይ ለሚጓዙ፣ መንገዱ በጣም መጥፎ አልነበረም። ነገር ግን፣ በጀርባቸው ሃምሳና ወይም ስልሳ ፓውንድ ተሸክመው ለሚሄዱ እግረኞች ግን መግለፅ የማይቻል ስቃይ ነበር። እንዲህ አይነቱን ነገር ማሰብ ይመች እንደሆነ እንጂ በተግባር መግለጡ የሚሆን አይደለም። ሙቀቱ ሀይለኛ ነበር፤ ማለትም በአማካይ፣ የሙቀቱ መጠን 98° ፋራናይት ነበር። ከዙላ ወደ ላት፣ በቀን የሙቀቱ መጠን ከ84° በታች ሆኖ አያውቅም። በማታ ሲሆን ግን የሙቀቱ መጠን ወርዶ ከ 30° እስከ 40° ፋራናይት ይደርሳል።

ለሶስትና አራት ሰአት ጉልበታቸውን ጨርሰው ዳገቱን ከወጡ በኋላ ተራራው እናት ላይ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያርፉ ተፈቀዶላቸው፣ የደጋውን ንፁህ አየር ሲተነፍሱ፣ ለፈረሰኞችና እግረኞች የተተረፈረፈ ካሳ ማለት ነበር፣ ።

እዚህ ያልተደሳደለ ቦታ ላይ ድንኳናችን ወጥረን፣ ከብዙ ድካም በኋላ ራሳችን ለማዝናናት በምንዘጋጅበት ሰአት አፍታም ሳይቆይ ለተረጋጋው መንፈሳችን ሴላ ቅጣት ነው የወረደው። አሱም፣ የጄኔራሉ ረዳት፣ ኮሎኔል ተሲገር የሚያሰፈራ ትዛዝ ሰለሰጠ ነበር። ያመጣናቸውን መጠጦች ጥለን መሄድ እንዳለብን በሚመለከት፣ ዋናው እሻፑ ጓዙንና ድንኳኑን እዚሁ ላት ጥሎ ለመሄድ ስሰወሰነ፣ የመጣው ትዛዝ፣ 20 ወታደሮች አንድ ድንኳን እንዲጋሩ፣ አስረ ሁለት መኮንኖች ደግሞ አንድ ላይ እንዲሆኑ ያሰገድዳል።

ይህ ትዛዝ በአንጣሎ ከተሠጠው ትዛዝ ሁለተኛው ከፍል ነበር፤ ያሁነኛው ግን በጣም ጠበቅ ያለና ድንገተኛም ነው። የመጀመሪያው ትዛዝ በህንድና-የእንግሊዝ መኮንኖች ሙሉ በሙሉ እንዳልተፈፀም ሰር ሮበርት ናፒየር ተገንዝበ ነበር። ከሁሉም በላይ፣ ምንም አይነት የጓዝ ሻንጣ ወደ ጦር ግንባሩ እንዲሄድ አልተፈቀደም። ሁሉም በቅሎዎች የሰንቅና ትጥቅ ጓዞችን እንዲያጓጉዙ ተፈልገዋል፤ ፈረስ ጫንቃ ላይ ያልሆኑ መኮንኖች እንዲይዙ የተፈቀደላቸው ካፖርት፣ ብርድልብስና ከላሰቲክ የተሠራ ምንጣፍ ነገር ነው።

የዕዙ ዕዝፈት ቤት መኮንኖችና የፈረሰኛው ኤታ ማጆሮች፣ በፈረሶቻቸው የፈቀዱትን መያዝ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሰር ሮበርት ናፒየር የሰጠው ሃሳብ፣ "ፍጥነት የሚያሰፈልገው ግዳጅ ከመጣ ግን ፈረሶቻችን ደከሙ ብለው ሰሱ አቤቱታ ማቅረብ አይችሉም።"

በዚህ ከተሰማሙ ድንኳኖቻቸውንና የጓዝ ሻንጣዎቻቸውን መውሰድ ይችላሉ። ሰኳር፣ ራም፣ ቡና፣ ሻይ፣ ድንች፣ ሽንኩርት የመሳሰሉት የቅንጦት ነገሮች ደግሞ ወደ ኋላ መቅረት አለባቸው፤ ምክንያቱም፣ መቅደላ ላይ ፈጣን አንቅስቃሴ ሊደረግ ስለታሰበ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት፣ በመጠኑ ቀለል ካለ የጓዝ መሰመር ጋርና ቁጥራቸው ያነሰ ድንኳኖችና የጓዝ ሻንጣዎች ጋር፣ ካምፑን በትነን ወደ ማርዋ መንገድ ጀመርን። እንደ ኮሎኔል ፋይሪ ስሌት አሰር ማይሎች ይርቃል፤ ኮሎኔሉ፣ ርቀቱን ለከቼዋለሁ ነው የሚለው።

በአንጣሎ የተሠጠው ትዛዝ የመኮንኖችን ሰሜት ለመገመት ሊባል ቁርጥ የሆነ አልነበርም። የአሁኑ የመጨረሻው ግን የማያወላውል፣ ጠበቅ ያለና የማይቀር ነበር። ሰለዚህ ቅሬታና፣ ውስጥ ለውሰጥም ቢሆን ጠብ የመፈጠር ሁኔታ በወታደሮች ታይቷል፤ ወታደሮች ጨመር ባለ ሁኔታ ማጉረምረም ጀምረዋል፤ በጊዜ ካልተያዘ ደግሞ ወደ አመፅ የሚያመራ ነበር።

ወደፊት የሚመጡት ረዥም ጉዞዎች ደግሞ ነገሩን ያባባሱት ይመስላል። ሰዎች መናገር ጀመሩ፤ ይህንን ደግሞ ወደ ጠቅላይ ዕዙ የሚያቀብሉ ሌሎች ሰዎች ነበሩ። ሲያጉረመርሙ ምንም አይነት መልስ ስላልተሠጠ፤ ወታደሮቹ ከየመኮንኖቻቸው ፊት ያሰምንም ፍርሃት መናገር ጀመሩ፤ የሰር ሮበርት ናፒየር ረዳቶች ፊትም ቢሆን። ኮሎኔል መከሊኦድ፣ የአዛዡ ረዳት ጀኔራል፣ በወታደሮች አጠገብ ሲያልፍ ልክ መንፈሰ እንዳለፈ አይነት፣ ያሰተዋለው ወይም ያወቀውም ሰው አልነበረም። በጣም ተናደደና፣ ሰመኮንኖች ያላቸው ክብር የት ሄደ በማለት አጥብቆ ጠየቀ። አነዚህን ውነታዎችን ለሰር ሮበርት ናፒየር ሪፖርት አደረገ።

ያን ቀን ማታ፣ አሰራ ሶሰት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ ማርዋ ላይ አቆምን። በሚቀጥለው ጥዋት ወደ ዲልዲ መንገድ ጀመርን። ተራራዎች ከፍና ከፍ እያሉ፣ አካባቢው ደግሞ ሰው አልባ አየሆነ ነበር። ወዴትና በምንሰ መንገድ ነው የዚህ ጉዞ ማብቂያው?

ቴዎድሮስ አነዚህን ሰው ሊወጣቸው የማይችሉ ኮረብታዎችን አልፈው ከሄዱ፣ መቅደላ ምን ሊመሰል ይችላል? አሁንም ቢሆን ወታደሮቹ እያጉረመረሙ ነበር፤ በተለይ የ33ኛው ወታደሮች የሚያደርጉት ጉልህ ነበር። ኮሎኔል ፋይሪ የዚህን ጉዞ ርቀት አሰር ማይል ብቻ ነው ብሎ ነበር። ነገር ግን

ከአስራ ስምንት ማይል በላይ ሆኖ ነው የተገኘው። ወታደሮች፣ ከብት ጫኞቹና አንሰሶች በቁጥር በደርዘን መውደቅ ጀመሩ፤ አንዲያውም በሃምሳዎች የሚቆጠሩም፣ ይህ ሁሉ ከፍውም ድካም የተነሳ ነበር።

ወደ ጉዞው ማለቂያ አካባቢ ሰዕላዊ የሆኑ ሽለቆዎችን ማየት ጀመርን፤ በሁሉም በውስጣቸው ወራጅ ውሀዎች ይታያሉ። የደከሙት ሰዎች በወራጅ ውሀዎቹ ዳርቻ ማረፍ ጀመሩ፤ ካምፕ ለመስራት ተስፋ የቆረጠ በሚመስል ሁኔታ ነበሩ።

ከምሽቱ አስራ አንድ ሰአት ሲሆን፣ የተወሰነ የጦሩ ክፍል ብቻ ነበር ካምፕ የደረሰው። በድካም፣ በየቡድኑ ሆነው ሲመጡ፣ ከኮረብታዎቹ ጀርባ አንድ ሺ የሚሆኑ ሰዎች ገስግሰው ቢደርሱባቸው የነበረውን ሀይል በሙሉ መደምሰስ ይችሉ ነበር። በመጨረሻ፣ ወታደሮቹ ከአዲሱ ቦታቸው ዲልዲ ሲደርሱ እኩለ ሌሊት ነበር። የጓዝ መስመሩ በረሃብና በጉዞ ደክሞ በነጋታው ጥዋት አራት ሰአት ድረስ አልደረሰም ነበር።

በዚህ በተቆራረጠ ጉዞ ምክንያት ዲልዲ ላይ አንድ ሙሉ ቀን መቆየት ነበረብን፤ አሳዛኝ ሆኖ ጦሩም ይህ አረፍት ያስፈልገው ነበር።

ጠዋቱን፣ የ33ኛው ሬጅመንት አማረኞች ማስጠንቀቂያ በሰጣቸው በሰር ሮበርት ናፒየር ፊት ተጠሩ፤ ባሳዩት ባህሪም፣ ለአቦሲኒያ ዘማች ጦር አሳፋሪዎች ናችሁ አላቸው፤ በመጨረሻው ጉዞ ላይ ሰላደረጉት ሚጉረምርም ከመኮንኖች የሰማ መሆኑን ገልፆ፣ በዚህ በማይመስል መንገድ ፀባይ ለማሳየት ደስተኛ ሰለነበሩ ቀዳሚ ጦር የመሆን ክብሩን አይስጣቸውም፤ ሰለዚህ ዝቅ በማድረግ፣ በሰር ቻርለስ ስታቨስ ስር ሆነው የኋላ ደጀን ይሆናሉ። በነሱ ምትክ 4ኛው (የንጉሥ) የነሱን ቦታ ይወስዳል። በፀጥታ፣ ያለምንም አንቅስቃሴ ቆመው፣ በተከፋ ልብና ሀዘን፣ የአዛዦቸውን ማስጠንቀቂያ ሲሰሙ ያየ ማንም ሰው ያዝንላቸው ነበር።

የ33ኛው ሬጅመንት፣ በብሪትሽ ጦር በጣም ጥሩ የሚባሉ ሰዎች ያሉበት ነው፤ አንደዚህ በቅፅበት ሲዋረዱ መታየት፣ ለነበራቸው ዝና ትልቅ ኪሳራ ነው። ከዚህ በፊት፣ የዚህ ከፍል የነበረው (የዌሊንግተኑ መስፍን) የሚባለው ጦርም በሠርጥ አካባቢ ባስየው የግድየለሽነት ባህሪ ይኸው ሬጅመንት ተቀጥቶ ነበር።

የዲልዲ ካምፕ በጣም የሚያምር ገፅታ ያለው ቦታ ነበር። ጠበብ ያለ ሽለቆ ሆኖ በደን በተሸፈኑ ኮረብታዎች የተከበበ ነበር፤ በውሰጡም ማያ የተባለ ትንሽ ወንዝ ይወርዳል። ከትናንትናው ድካም በኋላ፣ ይህ ትንሽ ወንዝ ለኛ ኤደን ማለት ነበር። ሁላችንም፣ በነፃነት፣ በልጅነታችን ስናደርገው አንደሚያስደሰትን ወንዙ ውስጥ ተነከርን። በአቢሲኒያ፣ የውነተኛ ወንዝ ስናይ

የመጀመሪያው ነበር፤ ቀስ በቀስ ስለወንዙ ባለቅኔ መሆን ጀመርን። ወንዙን የተለየ ስሜት የሚስጠው ሌላ ባህሪ ነበረው። ወንዙ ከጊዜ ብዛት መሬቱን ቦርቦሮ ጥልቀት ስለነበረው፣ በሳንና በሳን ያሉት ዳርቻዎቹ፣ ከሃምሳ አስከ ሁለት መቶ ጫማዎች የሚሆን ቀጥ ያለ ከፍታ አላቸው። አነዚህ የወንዙ ዳርቻዎች ደግሞ ብርቅየ በሆኑ ተክሎች የተሸፈኑ ነበሩ።

የቃኝዎች ጦር አዛዥ የነበረው ጀኔራል ፊልድ የኛን ወደ ዲልዲ መምጣት ለሁለት ቀናት ሲጠብቅ ነበር። እኛ ካምፑ የደረስን እለት፣ ከስንቅና ትጥቅ ከፍሉ ከኮሎኔል ፋይሪ ጋር በመሆን ወደሚቀጥሰው ማረፊያ ቦታ አመሩ። ቦታው ወንዳጅ ይባላል፤ በዚያም፣ ከነኛው ብርጌድ የአንድ ቀን መንገድ ቀድሞ ለመሄድ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ፣ መዝገር አምባ በሚባል ተራራ ዳገት ላይ ጉዞውን ቀጠለ። አቀበቱ በማያቋርጥ ሁኔታ የከፍታው ማቆሚያ የለውም ብለን አሰከናምን ድረስ፣ በዳገታማ ኮረብታዎች ወደ ላይ ይወጣል።

አኩለ ቀን ሲሆን፣ ከባህር ወለል በላይ የ10,700 ጫማዎች ከፍታ ያለው የመዝገር አምባ አናት ላይ ወጣን። በዚህ ከፍታ ላይ የአየር ፀባዩ ከበጋ ሙቀት ወደ አርክቲክ በታች ወደሆነ ቅዝቃዜ ሲለወጥ ተሰማን። ያጋጠመን፣ ቀዝቃዛ በረዶ ያለው ካፊያ፣ ዝናብና አንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ወጀብ፣ የበጋ ልብሳችን እንደለበሰን አንድንቀጠቀጥ አደረገን።

ችግር ጓደኝነትን ይወዳል ይባላል። የተሰማንን ችግር ለመጋራት ድንኳናችን ትተን፣ በዚህ ቀዝቀዛ ጭቃማ ቦታ የተረገመ ሁኔታ የሚፈጥረውን እርሰ በርሰ ወሬ ጀመርን። ዲልዲ ሸለቆ እያለን፣ አርቀው ማስብ የሚችሉ ብልሆች ለማገዶ የሚሆን አንጨት በድንኳናቸው ውስጥ አሰቀምጠው ነበር። አነሱ ባቀጣጠሉት አሳት ዙርያ ሙቀት ለማግኘት አንግዶች ይመጡ ጀመር፤ አንግዶቹም በዚህ አሳት ዙሪያ ቆመው ልባቸውን በመከፈት የአሳቱን ባለቤቶች ያደንቁ ነበር።

የኮረብታው ዳገቶች ምንም አይነት የአንጨት ምልከትም የለባቸውም። የነበሩት ተክሎች፣ አንጨት መምስል የሚቃጣቸው ቢኖሩ፣ ብዛት ያላቸው የዘንባባ ዛፍ ቅጠል የሚመስል ያላቸው ተክሎች ነበሩ። አነሱም ቢሆን ለማገዶነት አገልግሎት የሚውሉም አልነበሩም። እነሱን አንደ አንጨት ለማንደድ ከተፈለገ መጀመሪያ በእሳት መጠበስ ወይም መሞቅ ነበረባቸው። ያገሩ ተወላጆች ለኮሚሳሪያቱ የማገዶ አንጨት አንዲያቀርቡ ተጠየቁ፤ ከፀሀይ ግባት ከአንድ ሰአት በኋላ፣ የልጃገረዶች ቡድን፣ በጭንቅላታቸው የአንጨት ጭነቶች ተሸክመው ካምፕ ድረስ መጡ፤ ይህም ካምፑ ውሰጥ ያሉ ሰዎችን

በሙሉ ከልባቸው አንዲደሰቱ አደረጋቸው። መሸት ብሎ ማታውኑ፣ የ4ኛው(የንጉሡ)፣ 33ኛውን ለመተካት ካምፕ ደረሱ።

አራት ሰአት ሲሆን፣ ጦሩ ካምፑን አፍርሶ የመሸገር አምባን ቁልቁለት በመከተል ሲድስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ሙጃ ተጓዘ። መንገዱ በአንድ ቁልቁለት ላይ በመውረድ እያዘገመ ወደ ተከዜ ይወስዳል። በመንገዱ በግራ በኩል የተከዜ ወንዝ ይወርዳል፤ ከመነሻው ትንሽ ወራጅ ውሃ ነው፤ ነገር ግን በምዕራብ በኩል ከአንድ መቶ ማይሎች በኋላ ትልቅ ወንዝ ይሆናል።

የሙጃ ካምፕ፣ በተከዜና በአንድ ትልቅ የገደል ዳርቻ ያለው ሸለቆ መሀከል ነው፤ ገደሉ በቂ የሆነ ውሃ እንዳናገኝ አድርጎናል።

በሚቀጥለው ጠዋት፣ ከሙጃ ተነስተን ወደ ሳንታሪ ተጓዝን፤ ስሙ የመጣው ዋድላ አምባ ላይ ከሚገኝ ሳር የበዛበት ጉብታ ላይ ካለ መንደር ነው።

ከሙጃ ተነስተን የተጓዝን ቀን፣ በአቢሲኒያ ብሩህ ከሆኑ የፀደይ ቀኖች አንዱ ነበር። ለመጀመሪያዎቹ ሰባት ማይሎች መንገዱ ወደ ተከዜ በሚያወርደው በመሸገር አምባ ቁልቁለት ላይ ነበር። በጣም በዝግታ የሚወርድ ቁልቁለት ነው የነበረው፤ ምክንያቱም ዳገትነቱ የአስራ አራት ማይሎች ርቀት ነበረው። መንገዱ በግራና በቀኝ መሰመሮች ማለትም ሸለቆዎች መሀል ነው፤ አንዱ በግራ ሲወርድ፣ ሌላው፣ ተከዜ በመሀሉ የሚወርድበት በቀኖችን በኩል ነበር። ከመሸገር አምባ ተነስቶ አስራ አራት ማይሎች ወይም ከሙጃ ተነስቶ ሰባት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ፣ ተከዜ፣ በድፍረት በድንገት ይታጠፋል።

ተከዜ ሰንደርስ፣ ወደ መጣንበት ወደኋላ ካልተመለሰን በሰተቀር ወይም የሌላውን ሸለቆ ጠመዝማዛ መንገድ ይዘን ካልሄድን በሰተቀር በተከዜ ታጥረናል።

"ወደኋላም ተመልሰን አንሄድም፤ ሸለቆውንም ተከትለን አንሄድም።" ካፒቴን ስፒዲ ነበር የተናገረው፤ "ነገር ግን፣ ከፊት ለፊት የምታዩትን ማቆሚያ የመሰለውን ግድግዳ መውጣት አለብን።"

"ታላቁ ቄሳር!"

አንደውነቱ ከሆነ፣ ወደ ላይ ሰማይ ያቀፍ የሚመስል ያንን የአለት ግድግዳ ሲያዩ፣ አብዛኞቹ ሰዎች ይህንን ቃል በተናገሩ ነበር። ነገር ግን፣ በናፒየርና በሚከተሉት ሰዎች፣ ሁለት ቀናት የሚወስድ ቢሆንም አንኳን፣ መደረግ የሚገባው ነገር ይደረጋል።



የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች በተከዜ ሸለቆ ሲጓጓዙ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

የብረት መንፈስ ያላቸው የ4ኛው ወታደሮች ቀጥ ባለው ግድግዳ ላይ ግማሹ ላይ ደርሰዋል። ግራና ቀኝ፣ ወዲያና ወዲህ፣ ዚግዛግ በሆነ መንገድ አርስ በርስ እየተሰባጠሩ፣ ዙረያውን በዳገቱ እየኮጠማዘዙ ወደላይ ይወጣሉ። ሌሎቹ ሠራተኞችም መንገዱን ለመሞከር ቆርጠዋል፤ ፈረሶቻችን ኮልኩለን ወደላይ ዳገቱ ላይ መግፋት ጀመርን። ከግማሽ ስአት በኋላ አንደኛውን አርከን ወጣን። ቀስ እያለ ከፍ የሚል ዳገት ፊት ለፊታችን ነበር፤ ከሶስት ወይም አራት መቶ ያርዶች በኋላ ሌላ ተመሳሳይ ከፍታ ያለው አርከን ላይ መወጣት ነበረበት፤ ይህንን እንዳሳካን፣ ትንፋሽ ለመያዝ ቆም አልን፤ በዚያም የሚያስገርመውን ተፈጥሮ ገፅታ ለማየትም ነበር።

ወደላይ በወጣን ቁጥር የተፈጥሮ ዕይታ ግርማ አየጨመረ ነበር የሚሄደው። በሚያምር የፀሀይ ብርሃን ስር፣ ኢጣልያ ጉራ የምትነፋበት የሚመስል ለማያዊ ሰማይ ስር፣ ድንግል የሆነው መሬት ተንጣሎ ይታያል። ወደ መቅደላ መንገዳችን በቀጠልን ቁጥር፣ በየቀኑ፣ የቦታው ወጣ ገባነቱ አየጨመረ ነው የሚሄደው። የተራራዎቹ አናቶች ብርቅ ባሉ በፀሀይ ጮራዎች ተውበዋል።

ወደላይ፣ ያለማቋረጥ እየደከምን ነው፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ሰማረፍ እያቆምን ነበር። ፈጣንና ጠንካሮቹ የአረብ ፈረሶችም ቢሆን፣ በትንፋሻቸው አያቃተቱ ነበር፤ ጠንካራ የብረት ሰውነታቸው የተወጠረውን ነርቫቸውን የሚያፍታታው ይመስላል። ጠንካራ ዝርያ ያላቸው ቢሆኑም ተሸንፈዋል፤ እናም ባዶ ጉልበት ነው የቀረው፤ ሆኖም ረዘም ያለ እረፍት እንዲያገግሙ ያደርጋቸዋል።

እያንዳንዱ ከፍታ ማዕዘን ወይም የሚታጠፍ መንገድ ደንበኛ የሆነ መከላከያ ፈጥሯል። ላመል ያከል አንኳን የሚደረግ ጥረት የቶን ያህል የሚከብድን አለት ማንከባለል ይችላል። ከመጠን በላይ የሆኑ ትልልቅ ድንጋዮች ባሉበት ዳገት፣ አስር ጠንካራ ልብ ያላቸው ሰዎች፣ አንድ ሺ የሚሆነውን ሰው መመከት ይችሉ ነበር፤ አናም፣ በታሪክ ሌላ የቴርሞፓይሊ[110] ዝና በጨመሩ ነበር።

የአንግሊዝ ሠራዊት ተጠቃሚ ይሆናል፤ ማለቂያቸው ጥሩ የሆኑ ሁሉም ነገሮች ሂደታቸውም ጥሩ መሆን አለበት። "ፈጣሪ ከኛ ጋር"፣ የሚለውን የናፒየርን መንፈሳዊ ንግግር በማስተጋባት፣ ወደላይ ከፍ አያልን አንወጣለን፤ አናም ከላይ ያለውን የአለም ከፍል እንደገናም አናያለን። ከውቅያኖስ በላይ

---

110 ቴርሞፓይሊ በሚባል ማለፊያ፣ ቁጥራቸው አነስ ባሉ ግሪኮችና የላቀ ቁጥር በነበራቸው ፋርሶች መካከል የተደረገ ጦርነት ነው። በሊኒማ፣ '300' በሚል ርዕስ ለህዝብ ቀርቧል።

የአሰራ አንድ ሺ ጫማዎች ከፍታ አናት ላይ ያለውን አየርም እንተነፍላለን። እንደ ላራሜ ባለ እምባ ቦታ ላይ፣ የሰው አይን ሊያይ እስከሚችለው ርቀት ድረስ ወጣ ገባ እያለ፣ ከተከሎች በተራቆቱ ኮረብታውች ተሞልቶ፣ ልክ እንደሚያንፀባርቅ የባሕር ውሃ ተዘርግቶ የሚታየው፣ ከሌሎቹ ከፍ ብሎ የሚገኘው የዋድላ ከፍታ ይህን ይመሰል ነበር። እንግዳ የሆነ ተፈጥሮ! ሁሉንም አይነት የአየር ጠባይ ያቀፈ እገር!

ጀግኖች ሰዎች፣ የዋድላ እናት ላይ ከወጡ በኋላ፣ ኮሎኔል ካሜሩን የራሱን ሬጅመንት፣ 4ኛው እግረኛን፣ ሶስት ጊዜ ቺርሰ እንዲሉ ጠየቀ፤ በሱ አባባልም ይህንን የ3ሺ ጫማዎች ከፍታ መውጣት ቴዎድሮስን ከማሸነፍ የበለጠ የሚመሰገን ስራ ነው። ሰዎቹ ፈቃደኛም ቢሆኑም፣ በጣም ደከመው ስለነበር ደከም ያለ ሰሜት ከማሳየት በላይ ሌላ ማድረግ አልቻሉም። እናም በነበራቸው ሁኔታ፣ ቦታው ላይ እንደደረሱ ላሩ ላይ ቶሎ መጋደምን የሚከለከላቸው ነገር ቢኖር ጭካኔ ነው የሚሆነው። ሌሊቱኑ በሙሉ፣ በዋድላ አፋፍ ላይ፣ ወደ ማለፊያው መውጫ የሚያስገባው ቦታ በደከሙ ሰዎች ተሸፍኖ ነበር።

ከአፋፉ ሁለት ማይሎች ርቀት ከሳንታሪ መንደር አጠገብ የኛ ካምፕ ተተከለ፤ ቦታው የቲያትር አዳራሽ የመሰለ ነበር፤ ከሙጃ አሰራ ሁለት ማይሎች ርቀን ነበር።

በዚህ ቦታ፣ በጀኔራል ፊልድና በኮሎኔል መርዌዘር የሚመራውን የቃኚዎችን ብርጌድ እገኝን። በጋዜጠኞቹ ሀሜታ፣ እንደዚህ ሰው ዘወትር የሚነሳ አልነበረም፤ በጥሩ ሰምም አልነበረም፤ በመቅደላ ዘመቻ ከተላኩት ዘጋቢዎች በሚያሳዝን ሁኔታ ጨካኝ ሰህተት ነው የተፈፀመው።

በዚህ በላንታሪ ካምፕ፣ ገራም በሆኑ ኮረብታዎች የተከበበ ቲያትር ቦታ ላይ የእንጨት ዘር የሚባል ማግኘት አልተቻለም። ምክንያቱም ዋድላ ራሱ የመዶ ማይሎች ዙሪያ ያለው ሰፋት ቢኖረውም ከሶስት ደርዘን ያልበለጡ ዛፎች ብቻ ነው የሚገኙበት።

ነገር ግን፣ በአቢሲኒያ፣ ዶላር ሁሉንም ማድረግ የሚችል ሀይል አለው። ከአለት ላይ ውሃ ማፍለቅ ይችላል፤ ለ20ሺ ሰዎችና፣ ለ60ሺ እንሰሳት የሚሆን መጣብ ማምጣት ይችላል፤ ሜዳውን በፍየሎችና በሚጮሁ በጎች ማጥለቅለቅ ይችላል፤ ኗሪዎችን የራሳቸውን ቤት እፍርሰው እጣናና ምሰሶዎችን ለሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ እንዲሸጡ ያስደርጋል፤ ለወታደሮች የሚያመጡት ምግብም የተቀቀለ መሆን ነበረበት። በሳንታሪ ይህ ነበር የሆነው።

ቀለል ያለ ጣራ መሸከም የሚችሉ ርዝመታቸው ወደ አሰር ጫማ የሚሆኑ ሁለት ምሰሶዎች ለአንድ ዶላር ይሸጣሉ። ብዙ ዶላር ያላቸው ሰዎች

የሚፈልጉትን ያህል በብዛት ገዙ፤ ለአንድ ሙሉ ቀን የሚሆን ኑዳጅ አንድ ሙሉ ዶላር ነበር የሚያወጣው። ቀለብ በፍጥነት እያነሰ ነበር። እንስሶቻችን ከሚገባቸው ቀለብ በግማሹ አብዛኛውን ጊዜም እሩቡን ያህል ነበር የሚታደላቸው።

እንስሶቻቸውን፣ መልሶ መሸጥ በሚቻልበት ጥሩ ሁኔታ መጠበቅ የፈለጉ ሰዎች፣ ከኗሪዎቹ፣ ማግኘት የሚችሉትን ያህል እህል መግዛት ነበረባቸው። ከለንቅ ከፍሉ በተጨማሪ እንደገና የአንድ ዶላር የሚሆን ዳቦ የሚያሰፈልጋቸው ሠራተኞችም አሉ። ትንሽ ማር ወይም ወተት ሌላ ዶላር ያወጣል፤ ሰለዚህ ባጠቃላይ አንጣሎን ለቀን ከመጣን ወዲህ፣ የኮሚሳሪያቱን ወጭ ጨምሮ የአንድ ቀን ወጭ ሰባት ዶላር ድረስ ይደርሳል። ሁለት መቶ ዶላር የያዘ ከረጢት ብዙ የሚቆይ ቢመስልም በአጭር ጊዜ ያልቃል።

የዋድላ አፋፍ ብዙ መከራ እይቷል። ብዙ ጊዜ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ጉልበታቸው ደከም ባለ ጊዜ ወረውታል። አሁን ደግሞ የዋግሹም ጎበዜና፣ የዋግ ሹሙ እጎትና የጦሩ አዛዥ የደጃዝማች መሸሻ ግዛት ነው። እኛ የደረስን ቀን፣ 1500 ወታደሮች ይዞ በላሰታና በሰሜኑ ጫዥ(መሰፍን) በዋግሹሙ የተጣለባትን ከባድ ግብር አልከፍልም ያለ አመፀኛ መንደር ለመቅጣት እይተንቀሳቀሰ ነበር።

እኛ ሳንታሪ ሰንደርስ፣ ደጃዝማች መሸሻ በምሰራቅ በኩል በሚገኘው መንደር ደርሶ ነበር፤ ወዲያውኑ፣ በሁለቱ የጦር መሪዎች መካከል የወዳጅነት መልከቶች ልውውጥ ተደረገ።

ጠፍቷል ተብሎ ጭምጭምታ የተወራበት መንሲንጀር፣ በዚህ ግዛት እየኖረ፣ የሀበሻ እንጀራ እየበላ፣ በሰላም፣ በወዳጅ ካምፕ ሆኖ የደጃዝማች መሸሻን ጠጅ እየቀመቀመ ነበር። የፈረንሳዩ ቆንስላ፣ የሰላማዊ ዲፕሎማሲ ሥራውን በሚገባ እየሠራ ነበር፤ የጠርጣራውን የሀበሻ ጄኔራል ልብ ማሸነፍ ችሏል። እናም በጄኔራል ናፒየር ጥሪ መሠረት፣ መሸሻ፣ በነጋታው ወደ ካምፕ ለመምጣት ቃል ገብቷል።

በደረቆቹ ኮረብታዎች በታቀፈው ካምፕ፣ ቦማያሰጋ ቦታ ነው ያለነው፤ ሲመዛዘን፣ በማሸ ራሽን እንደሚጠበቀው ከሚሰቃዩ ሰዎች የተሻለ ነበር። ሆኖም መጠጥ አልነበረም፤ ዳበውም መጥፎ ነበረ። የዋድላ ተራራ በጣም ይበርዳል፤ ከታች ከሸለቆው የምጣድ ያክል ካለው ሙቀት ጋር ሲወዳደር፤ እንደ ሪፍሪጂሬተር ማለት ነው። በመጣን በጠዋቱ፣ የተገኘው ከፍ ያለ ቦታና ዳገቱ በሙሉ በረዷማ በሆነ ጤዛ ተሸፍኗል። የነበረን ብርድ ልብስ ወደኋላ ሰለቀረ፤ በደንተኛ የእየር ለውጥ ምክንያት በጣም ነበር የተቸገርነው፤ ምንም አይነት ምቾት አለ ብሎ ከማሰብ በፊት ሰድሰት ብርድ ልብሶች ያስፈልጉን

ነበር። እነዚህን ደግሞ፣ እያንዳንዷቸውን፣ በእንድ ዶላር ሂሳብ ካገሩ ተወላጆች ለመግዛት ተገደደን።

የስንቅና ትጥቅ ከፍሉ፣ መቅደላ ለመድረስ የሰባት ቀን ጉዞ ቀርቶናል ሲል አስታወቀ። ላት እያለን፣ ወደ መቅደላ ስድስት ቀን ነበር ይወስዳል የተባለው። አሁን ግን እምስት ቀናቶች ከተጓዝን በኋላ፣ እንደ ኮሎኔል ፋይሪ ገለፃ፣ ሰባት ቀን እንደሚቀር ተነገረን። ዋና አስተርጓሚው ቻርልስ ስፒዲ ግን በሱ ግምት፣ በፍጥነት ከመጓዝ ይልቅ አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ለማስቀረት መጠባበቂያ ቀኖች ብንጨምር አስራ ሁለት ቀናት እንደሚወስድብን ተናገረ።

የመረጃና የፖለቲካው ከፍል የአቢሲኒያ አለቆችን ገንዘብ በመከፈል ራሱን ወጥሯል፤ ጥሩ ባህሪ እንዲያሳዩ በጉቦ እየደለሉ ነበር። የኮሚሳሪያቱ ክፍልም ቢሆን አቢሲኒያውያን ይዘው የሚመጡትን ሁሉን ነገር በመግዛት ባተሌ ሆኖ ነበር።

ስማይ ያቀፈ በሚመስለው አምባቸው የሚኮሩት የአቢሲኒያ አለቆች እንደ ባህር አለ ሙልጭልጭ የሚሉ ነበሩ። ከዚህ በፊት፣ የሚወዱት፣ እዲስ ብልጭልጭ የሚል ማር ተሬዛ የተከፈላቸው ቢሆንም፣ ጦሩ መካዝኖችን ትቶ እንደሄደ፣ ወዲያውኑ ተጨማሪ ሥጦታዎች በመጠየቅ ማንጎራጎር ጀመሩ። ተጨማሪ ክፍያ ተልኮ የሰዎችን ስግብግብ ባህሪ በሚያረካ መንገድ እንዲከፈልና የነበረው ስህተት እንዲታረመ ተደረገ፤ አለበለዚያ፣ በማግባባት ሰላም መፍጠር ካልተቻለ ደግሞ፣ የጉልበት ወይም የሀይል ሥራም ተሠራ።

ሜጀር ግራንትና ካፒቴን ሙር ወደ ዲልዲ ተላኩ፤ ምክንያቱም የተፈጠረው ችግር በራሱ እልባት ማግኘት የሚችል አልነበርም፤ ጉዳዩን በጊዜ እርምጃ ካልወሰዱበት ወደ ከፋ ደረጃ የሚወስድም ነበር።

የፖለቲካ መኮንኑ ኮሎኔል መርዌዘር፣ በሙል ሥልጣንና ግዴታ፣ የገረኛውን የወልደየሱስን ፍላጎት ለማርካት ሀላፊነት ተሠጥቶት ነበር። ወልደየሱስ፣ ምንም እንኳን ከናፒየር ጋር ዳቦ ተቋርሶ ቃል ቢገባና ቢምልም፣ ቃል ከገባበት ሁኔታ እየራቀ ነበር፤ እኛ ቦታውን ጥለን ከመጣን ወዲህ፣ የሱ ፍላጎት፣ ካደረገው ስምምነት እየጨመረ እየራቀና ልዩነቱም የከፋ ደረጃ ደርሶ ጠብ እስከሚያነሳ ድረስ ነበር።

እንደሚባለው ከሆነ፣ የናፒየር መልከተኞች ተማርከው በደል እየደረሰባቸው ነበር፤ መልከተኞቹ ሳይተባበሩ ድርቅ ካሉ ይለለቡ ነበር። ወልደየሱስና ወንድሙ፣ የራሳቸውን ስዎች ምንም እይነት ነገር ለሽያጭ እንዳያቀርቡ መከልከላቸው የማያጠራጥር ነገር ነበር። የአገሩ ተወላጆች ለእንግሊዝ ሠራዊት ጓዝ እንዳያመላልሱ፣ ወይም የሚሸጥ ነገር ይዘው፣

ከመሸክ እሰከ አፃላ በነሱ ግዛት በዋጀራት በኩል ባለው መንገድ አንዳያልፉ መከልከላቸው የሚያከራከር አልነበረም።።

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ለጦሩ በየቀኑ ያሚያሰፈልገውን ቀለብ ማመላለሱን በሀገሩ ተወላጆች እንዲሆን ወሰኖ ሰለነበር፣ አንደዚህ አይነቱ መሰናከልና መከልከል፣ ቀዳሚው ጦር ላይ ከባድ ችግር አንደሚያሰከትል ግልፅ ነው።። አያንዳንዱን ትንንሽ አለቃ መቅጣቱ ለኛ የሚበጅ ነገር አልነበረም፤ የተገላቢጦሽ ጉዳት ነው የሚያስከትለው።። እያንዳንዱ ገዥ፣ በሰማይ ጠቀሰ አምባው ላይ ተቀምጦ፣ ራሱን ከሌሎች ማለትም ከከፍተኛው ዋሻሙ ወይም ከትግሬው ልዑል የማያንሰ አድርጎ ነው የሚያየው።።

የዚህ አይነቱ ስሞታ፣ ጉዳዩን ሰማረጋጋት ለተላከው ኮሎኔል መርዌዘር በግልፅ ላይነገር የቀረ አልነበረም።።

በሳንታሪ ቆይታችን፣ በሁሉተኛው ቀን፣ ከረፋዱ አምስት ሰአት ላይ፣ በኮረብታዎች ከፍታ ቦታ ላይ፣ በብርድ አየተንቀጠቀጡ አንደ ጥላ የቆሙት ጠባቂዎች፣ በጭጋጋማው ረፋድ ከምዕራብ አቅጣጫ የታጠቁ ሰዎች ሲቃረቡ አይተው የማሰጠንቀቂያ ተኩሰ ጀመሩ።። ወዲያውኑ፣ ቴዎድሮስ ከ50ሺ ሰው ጋር አየመጡ ነው የሚል ወሬ ይሰራጭ ጀመር፤ አንዲህ አይነቱ ጭምጭምታ ሳንታሪ ከመጣን ጀምሮ ጠንከር ያለ ነበር።።

የመጀመሪያው የማሰጠንቀቂያ ተኩሰ አንደተተኮሰ፣ በቀኑ ተረኛ የነበረው መኮንን፣ ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ወደ መጠበቂያ ቦታዎች በመጋስብ የሚመጡትን እንግዶች በቅርብ መመልከት ጀመረ፤ ከዚያ በኋላ፣ አየተቃረቡ ያሉት ሰዎች ወዳጆች ስለነበሩ ጠባቂዎች ተኩሱን አንዲያቆሙ ነገረ።። ዋናው የዕዝ ጽ/ቤት፣ አነዚህ ሰዎች መምጣታቸውን ያውቅ ነበር።። የዋግሹም ጎበዜ ጦር አዛዥ፣ ደጃዝማች መሸሻ፣ ሰር ሮበርት ናፒየርን ለመገናኘት በነጋታው አንደሚመጣ፣ መንዚንጀር፣ የደጃዝማች መሸሻን ውሳኔ በሚመለከት ለሰር ሮበርት ናፒየር ብዙ መልከተኞች ልኮ ነበር።።

የሲንዲ ፊረሰኞችና የአግረኛ ጠባቂዎች ካምፑን ለማሰጠንቀቅ በተኮሱበት ጊዜ፣ በካምፑ ያለው እግረኛ ወደፊት በመገሰገሰ፣ መጣ የተባለውን ጠላት ለመግጠም በውጊያ መሰመር እያመሩ ነበር።። ኮሎኔል ፍሬዝር በወቅቱ ባይደርስ ኖሮ፣ ውጤቱ ወደ ወዳጅ ካምፕ ያለምንም ጥንቃቄ በመዝናናት በሚመጣው የአገሬው ፈረሰኛ ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ፣ የአንግሊዝ ጦርና 40ሺ ሰራዊት ያለው የዋግሹም ጎበዜ ጦር በተፃራሪነት ይሰለፉ ነበር።። በዚህም፣ ዋግሹም ጎበዜ የማታለል ሥራ ተሰራብኝ በማለት ያለምንም ጥርጣሬ ከቴዎድሮስ ጋር ግምባር በመፍጠር የሰዎቹን ደም ይበቀል ነበር።። በዚህ ሁኔታ ደግሞ፣ የአንግሊዝ ሠራዊት፣ ከፊት ለፊቱ ቴዎድሮስ ከ30ሺ

ሰዎቻቸው ጋር፣ ዋግሹም ነበዜ ከ40ሺ ሰዎች ጋር ከኋላና ከጎኑ ይከቡት ነበር።

የአቢሲኒያው ጀኔራል መምጣቱ በጠቅላይ ዕዙ ሲታወቅ፣ በታምቡርና በዋሽንት እማኸኝነት የየሬጂመንቱ ወታደሮች ወደ ዋና ዕዙ ቦታ እንዲመጡ ተደረገ። ወታደሮቹም፣ የፀሀይ ባርኔጣቸውን የሚሸፍን ንፁህ ልብስ አልብሰው፣ ነጭ ጓንት አደረጉ። የ3ኛው ቀላል ፈረሰኞች ቡድን ወደ ሰር ሮበርት ድንኳን እመራና፣ ወደኋላ በመዞር ፊትሰፈቱን በማየት ተሰለፈ። ሁሉም፣ በደንብ የታጠበውን ባለ ብርማ ቀለም ዩኒፎርማቸውን ለብሰዋል። መኮንኖቻቸው ጥሩ ፈረሶቻቸው ላይ ተፈናጠው ከቀረቡ በኋላ፣ ጥቂት ፈረሰኞች እንዲያጅቧቸው አድርገው መሸኛን ለመገናኘት ገሰገሱ። በዚህ መሀል፣ እራት ሬጅመንቶች ከነመሳሪያቸው ወደ ካምፑ ምዕራባዊ ዳርቻ ከተራመዱ በኋላ በመሰመር ተሰለፉ። ሰዎቹ በዛ አቅጣጫ ነው የሚመጡት ሰለተባለ፣ ሁሉም፣ ቦጉት በግራችን በኩል ወደሚገኙት ከፍታ እናቶች አቅጣጫ ነበር የተመለከቱት።

ግማሽ ሰአት የሚሆን ሊገባደድ ሲል፣ የፈረሰኞች ረዥም መስመር ኮረብታው ላይ ብቅ አለ። ትንሽ ቆም አሉ፣ በዚህን ጊዜም፣ ከታች እንግዳ የሆነውን ካምፕ፣ በወሰጡ ያሉትን በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችንና እንስሶችን ከመረመሩ በኋላ፣ ሁሉም ፈረሰኞች ቁልቁለቱ ከበድ ባለው መንገድ በኩል ወደታች መውረድ ጀመሩ፤ በዚህ ገደላማ ኮረብታ፣ ልከ ደልዳላ ቦታ እንደሚጓዝ በርጋታና በዝግታ እየወረዱ ነበር። ምንም እንኳን ቀጥ ያለው ቁለቁለት ወጣ ገባ ያለና በትልልቅ አለቶችና ሸካራ ድንጋዮች የማይመች ቢሆንም፣ ምንም አይነት የማጉረምረም ወይም እርስ በርስ የመጋፋት ምልክት አይታይም። እርስ በርሱ ሳይገፋፋና፣ በቡድን ተጠጋግቶ ሳይደናቀፍና በየቦታው ሳይቢታተን፣ ማንም የአውሮፓዊ ፈረሰኛ እንደዚህ ማድረግ አይችልም ነበር።

የመሸሻ ጦር እሰላለፍ በጣም የሚያስደንቅ ነው፤ ምንም እንኳን የመሬቱ ወጣ ገባነት እንዱን ሰልፍ ከሌላው በሃምሳ ጫማዎች እበላልጦት ቢታይም፣ በሚደነቅ ሁኔታ ሥርአትና ደረጃውን የጠበቀ ነበር። የኮረብታዎቹ ስር እንደደረሱ፣ እቆሙና በሰልፍ መስመር ሰሩ። የእንግሊዝ መኮንኖችና አጃቢ ወታደሮቻቸው የአቢሲኒያውን ጀኔራል ከበቡት፤ ከዚያም፣ ልከ ካምፑንና ከፍታ ቦታውን የሚያለያየውን ትንሽ ወራጅ ውሃ እንደተሻገረ፣ መድፈኛው የከብር ተኩስ መተኮሰ ጀመረ፤ ይህ ደግሞ ያገሩን ፈረሶች እንዲደነብሩና ሰልፉን እንዲያበላሹ አደረጋቸው።

መሳሪያ የያዙት ሪጅመንቶች ለተኮፈሰው ጀኔራል ሰላምታ ከሠጡ በኋላ፣ ከተወላጆቹ ጦር ፊት ለፊት ቀደም በማለት መራመድ ጀመሩ። ወታደራዊ

ባንዱ፣ "ጌሪ አውን" የተባለውን ሙዚቃ መጫወት ጀመረ፤ ይህም ጠየም ያሉትን ወታደሮች፣ ሙዚቃው ከወታደራዊ ሁኔታው ጋር አሰደሰታቸዋል። በዚህ ሁኔታ የናፒየር ድንኳን አሰከተተከለበት ሥፍራ ደረሰ ተጓዙ፤ የእንግሊዝ ወታደሮች በአራት ማዕዘን ቅርፅ ከፍት ቦታ ሲፈጥሩ፣ መሸሻ ወደ ናፒየር መቀበያ ከፍል አንዲሄድ ተደረገ። የእንግሊዙ ጄኔራል ከድንኳኑ ወጣ፤ ወዲያውኑ፣ ሁለቱ ጀኔራሎች ተቃቀፉ።

ጀኔራል መሸሻ መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው ነው፤ ዕድሜው ወደ ሰላሳ አምሰት ይሆናል፤ ፊቱ፣ ደግነት መልካምነት የሚያሳይ ገፅታ አለው፤ የብልህነትም ሁኔታ ያንፀባርቃል። ከሀር የተሠራ ቀሚስ ለብሷል። የለበሰው ሸሚዝና ሱሪው ላዩ ላይ ቅርፃቸው ወጣ ባሉ ቀሰም ባላቸው ምለሎች ያጌጠ ነው፤ አንገቱም ላይ አንደ እንቁ የመሰሉ ብጫማ ቀለም ያላቸው መቁጠሪያ የመሰሉ ህብሎች አድርጓል፤ ጭንቅላቱ ላይ ደግሞ፣ በወርቅ ጥምዝ የተሠራ ብዙ ቀሰማት ያለው የጠርሙስ ጌሮች የተሰኩበት እከሊል የመሰለ ነገር አድርጓል። በምራባዊ ዋድላ ሰፈር ባመፁ ገበሬዎች ላይ የተሳካ ዘመቻ አድርጎ መመለሱ ነበር፤ ይህ ጥምዝ የራስ ጌጥ ከመሀሉ ላይ ቀንድ ተደርጎበታል፤ ያም የአሸናፈነት ምልከት ነው። ይህ ከድል በኋላ ቀንድ ማድረግ ከመፅሐፍ ቅዱስ የፃድቃን ቀንድ ከሚለው የተወሰደ ነበር።[111]

የአቢሲኒያውያኑ ሀይል በግምት ወደ 800 ፈረለኞች ነው የነበረው፤ አነዚህም ከዋሻው ምርጥ ወታደሮች የተውጣጡ ነበሩ። ሁሉም ጠቆር ያሉ ያገሩ ተወላጆች ናቸው፤ አንድ አይነት አለባበስ፣ ከፈቆ ላይ ጥለት ያለው አጀ ጠባብ ለብሰዋል። የሚያንፀባርቅ አምባር ከንዶቻቸው ላይ፣ አንገታቸው ላይ ደግሞ ብጫ ቀለም ያላቸው መቁጠሪያ በመሠሉ ነገሮች የተሰሩ ህብሎች አድርገዋል፤ አግራቸውም ላይ ቢሆን አልቦ አድርገው ነበር። አያንዳንዱ ወታደር ሁለት ጦሮችና ከበሬ ቆዳ የተሠራ ጋሻ ይዟል፤ ግማሽ የሚሆኑት በእሳት የሚለኮሰውን ጠመንጃ ታጥቀዋል። አንዱም ፈረስ የፈረሰ ጫማ አላደረገም።

የአንግሊዙና የአቢሲኒያው ጀኔራል ወድ ድንኳኑ ውስጥ ከገቡ በኋላ የሆነው ነገር አይታወቅም። አለዚያም ማወቁም ጠቃሚ አይሆንም። የንግግራቸው ፍሬ ነገር የሚሆነው፣ ያለጥርጥር፣ ናፒየር ለንበዜ መልካም ምኞቱን መግለፅ፤ በተራው ንበዜ ለናፒየር መልካም ምኞት መግለፅ ነው። በተጨማሪም፣ መሸሻ ቴዎድሮስ የሚዋጋ መሆኑን ያለጥርጥር የሚያምንበት ነገር መሆኑን ገለፀ። ይህ የአንግሊዙን ጀኔራል የሚያረካ መልስ እንዲያገኝ

111 መዝሙረ ዳዊት ቁጥር 75፣ "የክፉዎችን ሁሉ ቀንድ አሰብራለሁ፤ የፃድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል።"

ነው ያደረገው፡፡ መሸሻ ቴዎድሮስን በጣም እንደሚፈራው ገለጠ፤ ይህን ደግሞ፣ አስቀድመን፣ እሱ ለናፒየር ከመንገሩ በፊት የገመትነው ነገር ነበር፡፡ ከዛ በኋላ፣ መንዚንጀር፣ መሸሻ፣ ስፒዲና ተሲገር ከስር ሮበርት ጋር ትንሽ (ራም) አረቄ የመስለ መጠጥ እንዲጠጡ ተጋበዙ፡፡

ንግግሩ ካለቀ በኋላ፣ መሸሻ የፈረሰና ጥንድ አፈሙዝ ያለው ጠመንጃ ስጦታ ተሰጠው፤ ጠመንጃው፣ ወደኋላ፣ የሚኮራበት ነገር የሆነው፡፡ ፈረሱም ቢሆን ያገሩ ተወላጅ ወታደሮችን አድናቆት አግኝቷል፡፡

የደጃች መሸሻ ጋሻ፣ በአንድ ከፍ ያለ ትውልድ ባለው ወጣት ነው የተያዘው፤ ፍፁም ወጣት አዶኒስ[112] ነበር፡፡ በጠይም ፈቱ፣ በጣም መልከ መልካም ሆኖ፣ በአድሜም ሆነ በመልከ የቀድሞ ባሮኖች ጦርና ጋሻ ከሚይዙ ተላላኪዎች አይለይም፡፡ የመሸሻ ጋሻ ከልዑል ካሳ ጋሻ ጋራ ይመሳሰላል፡፡

ከነዚህ ሰዎች ስለ አፄ ቴዎድሮስ ጥንካሬና ሀይል ግንዛቤ ማግኘት ችለናል፡፡ የቴዎድሮስ ወታደሮች ከመሸሻ ወታደሮች በትንሹም ቢሆን በተሻለ ሁኔታ ከታጠቁ፣ መቅደላን ለመያዝ የአንግሊዝ ሠራዊት ከፍተኛ ሀይልና ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የተሻሉ ናቸው ብሎ ለማመን ደግሞ በቂ ምክንያት ነበረ፤ ምክንያቱም፣ ቴዎድሮስ፣ ካገሩ ባላባቶችና መሳፍንቶች ጋር በሚያደርጉት ጦርነት ሁልጊዜ አሸናፊ ነበሩ፡፡ ለማንኛውም፣ ስለቴዎድሮስ ሁሉም ነገር ሚስጥራዊ ነው የነበረው፡፡ ስላዮች ወደ ካምፕ ሲመጡ፣ ስለሳቸው የሚወራው በሙሉ የተጋነነ ስለነበር ትክክለኛውን ሁኔታ ማወቅ አይቻልም ነበር፡፡ ከአስረኞቹ የሚላኩት ደብዳቤዎች ቢሆንም ድፍን ያሉ ስለሆኑ፣ ለጀማሪ ዲፕሎማት ስለመቅደላና አካባቢው በቂ ግንዛቤ አይሰጡም፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ ጄኔራል ናፒየር ወደፊት መግፋት እንጂ ሌላ እማራጭ አልነበረውም፤ በዚህም ተስፋ ያደረገው ሁሉም ችግሮች በሚመጡት ቀናት አልባት እንደሚያገኙ፣ ሁሉም የሚወሩ ወሬዎችና ጥርጣሪዎች ደግሞ ጭራሹን እንደሚያቆሙ ነበር፡፡

በዚህ ቀን ማምሻውኑ፣ ጄኔራል ስታቨሊ ከ33ኛው እግረኛ፣ ፑንጃብ ቃኝዎች ሶስት ኮምፓኒ፣ ከተዊስ ከባድ መሳሪያ ከፍል፣ የ3ኛው የህንድ ተወላጆች ፈረሰኛ ካምፓኒ፣ የሮኬት ከፍሉ የባህር ሀይል ብርጌድ፣ ከእውሮፓ እግረኞች ሌላ ሬጅመንት ማለትም 46ኛው እግረኛ፣ የ3ኛው ድራጎን ጋርድስ (አውሮፓውያን) እና ከቤሉቺዎች ግራ ከንፍ ጋር በመሆን ዋድላ ደረሰ፡፡

---

112 በግሪክ አፈ ታሪክ፣ አዶኒስ በጣም መልከኛ ወጣት ስለነበር፣ በእማልክቷ በአፍሮዳይቲና በገሃነም በምትኖረው ሌላ እማልክት ፐረስፎን የሚወደድ ነበር፡፡ ሲሞት፣ የእማልክቶቹ አለቃ ዙስ፣ ወጣቱን ወደ ምድር እየመጣ ከአፍሮዳይቲ ጋር፣ ከታች ደግሞ ከፐረስፎን ጋር እኩል ጊዜውን እንዲያሳልፍ ፈቀደለት፡፡ አፍሮዳይቲ የፍቅር አምላክ ተብላ ነው የምትታወቀው፡፡



ሜጀር ጄኔራል ቻርለስ ሰታቨሊ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ሳንታሪ በደረሰን በሶስተኛው ቀን፣ ነኖው ብርጌድ ካምፕ ነቅሎ እስራ ስድስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ጋዞ እንቅስቃሴ ጀመረ።።

የዋድላ ከፍታ ከኢሊኒዮስና ከኔብራስካ ሜዳዎች ጋር ይመሳሰላል፤ ነገር ግን፣ በእቢሲኒያው መሬት፣ ድንጋዮች እሁንም እሁንም ከአፈሩና ከሳሩ በላይ ፈጠጥ እያሉ ይወጣሉ።። ብዛት ያላቸው አረንጓዴ የሰንዴ እርሻ ቦታዎች እለፍን፤ በጎናቸው ደግሞ፣ ለእጨዳ የደረሱ የጤፍ እርሻዎች ነበሩ።። በዚህም በዚያም፣ ትንንሽ መንደሮች ይታያሉ፤ መንደሮችም በቁጥቋጦ እጥሮች የተከበቡ ነበሩ።። ሁልጊዜም ቢሆን የሚያስደስት ነፋሻ እየር አለ፤ ይህ ደግሞ ባናታችን ላይ ከሚወርደው የፀሀይ ጨረር ጋር ሊኖር የሚችለውን መቀት ይቀንስዋል።።

የኛ እስተርጓሚ፣ የቀድሞው የቴዎድሮስ ባሻ፣ ቻርለስ ስፒዲ፣ በየመንደሩ እየዞረ እህልና ዶቄት እንዲገዛ በናፒየር ታዘዘ።። ሚሰተር ስፒዲም እኔን እብረን እንድንሄድ ጋበዘኝ፤ በንግግሩም፣ በእንግሊዝ ዶላር ያልተበከሉ ሰዎችን ሁኔታ ማየት እንድችል ነበር።። እኔም ጥሪውን በደስታ ተቀበልኩኝ።።

እኔና ካፒቴን ስፒዲ፣ መጀመሪያ የገባንበት መንደር ዎጣ ይባላል፤ የእንግሊዝ ሠራዊት ባለፈበት መንገድ፣ በግራ በኩል፣ ከሶስት ማይሎች ርቀት ላይ ይገኛል።

የኛን መምጣት ሲያዩ፣ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ ሽማግሌዎች ወደፊት መጥተው እጅ ነሱ። ስፒዲም የተለመደውን ሰላምታ፣ በእማርኛ፣ "እንደምን ዋላችሁ።" በማለት ጀመረ። እነሱም፣ በእጆቻቸው ሶስት ጊዜ ራሶቻቸውን በመንካት ሰላምታ ሲሰጡ፣ ስፒዲም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያዊ ባህል ሰላምታውን መሰሰ።

የሰውነታቸው እንቅስቃሴ፣ እኔ እንደተረዳሁኩት፣ የሚያሳዩት፣ በመፅሐፍ ቅዱስ እንደተፃፈው የመጋበዝ ምልክት ነበር።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አስራ ለምንት እንደተፃፈው፣ "አቤቱ በፊትህ ሞገስን እማኝቼ አንደሆነ ባሪያህን እትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ።"

"ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፣ እግራችሁን ታጠቡ፣ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ፤ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፣ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና።"

ጓደኛዬም በግብጥው ተሰማምቶ ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ነው ብሎ ተናገረ።

እኛም፣ ከሚያምር እርጓዴ የኮሶ ዛፍ ሥር ተቀመጥን፤ ከፊት ለፊታችንም፣ ዳቦ፣ ቅቤ፣ ወተት፣ የበግ የኋላ እግር ሰጋ አቀረቡልን። ከዛፉ ስር፣ በኛ እጠጉበ ቆመው፣ ስንበላ መጥፎ መንፈስ እንዳያየን በጋቢ ጋረዱን። በላን። ወተቱ ጣፋጭ ነበር፤ ዳቦውም ቢሆን በጣም ጥሩ ነበር፤ ሥጋው ደግሞ ለስለስና በርከት ያለ ነበር።

በድንገት የተዘጋጀው ምግብ ከተነሳ በኋላ፣ ሴቶች በቆሎና ዶቄታቸውን ለሽያጭ ይዘው መጡ። እኛም ከብር የተሰሩ ዶላሮችን በሚያጓጓ መልክ ከፊት ለፊታችን ዘርግተናቸው ነበር። መጀመሪያ የገዛነው ዶቄት ስድስት ፓውንዶችም አይሆንም ነበር፤ ግን አንድ ዶላር ከፈልንበት፤ ከዚህ አነስተኛ መጠን በመነሳት፣ ቀስ በቀስ ከብደቱ እየጨመረ በአንድ ዶላር ከፍተኛ መጠኑ አስራ ሶስት ፓውንድ ድረስ መግዛት ቻልን። የአህልና የዶቄቱ ከምር ቀስ እያለ እየጨመረ በመምጣት የግብዖችን ፒራሚድ የሚመስል ቅርፅ መያዝ ጀመረ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ስልቻዎች፣ በቅሎዎችና መጫኛዎችም ገዛን።

ዎጣን ለቀን ከመሄዳችን በፊት፣ ካፒቴን ስፒዲና እኔ 4ሺ ፓውንድ ዶቄትና ሶስት ሺ እምሰት መዶ ፓውንድ አህል ይዘናል። ለቀን ስንሄድ፣ በነዚህ ደግ የመንደሩ ሰዎች ልባዊ ምርቃን ወረደልን።



ካፒቴን ሰፒዲ (ባሻ ፈለቀ)
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ከዎጣ ወደ ማይ አይኒ ሄድን፤ በዚህም የካፒቴን ሰፒዲ የሚታወቅ ታሪክ ያልተለመደ አትኩሮትና ከብር እንዲፈጠር አደረገ። እሱ ሲንቀሳቀስ ሁሉም ባንድ ጊዜ ከፊት ለፊቱ ይርቃሉ፤ በቀልድ መልክም፣ ይህ የእናከ[113] ልጅ፣ ባሻ ፈለቀ ማድረግ የሚችለውን ነገር ለማሳየት በአንድ ጠንካራ እጁ ከወጣቶቹ እንዱን አፈፍ አድርጎ ያነሳ ነበር።

የማይ አይኒ አለቃ ነገር የተለየ ነበር። ለረዥም ጊዜ በሚያከሳ በሽታ ሰለሚሰቃይ አፅም ነበር የሚመስለው። በብዙ ሰላምታዎች፣ እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ ተቀበለን። በዙሪያው፣ ብዛት ያላቸው የሚወዛወዙና የሚስቁ ልጃገረዶች ነበሩ። ወጣት ልጆች የኛን ድምፅ ሲሰሙ፣ ከየመንደራቸው እየተሰባሰቡ መጡ፤ እንደ ብዙ ዳዊትና ዮናታኖች፣ እርስ በርስ ከንዶቻቸው

---

113 በመፅሐፍ ቅዱስ የሚጠቀሱ ግዙፍ ሰዎች (ጂይንቶች)

ላይ ተደጋግፈው ነበር። በአቢሲኒያ፣ ከዚህ ቀን በፊት፣ እንደዚህ የሚያስገርም ፅዮታ አይቼ አላውቅም። እርጎ የተሞላባቸው ምንቸቶችና መያዣዎች ፊት ለፊታችን ቀረቡ፤ እንደ ክሊዎፓትራ ግርማ ያላት አንዲት ሴት፣ እኔን ለማከበር፣ ስፒዲ እንደነገረኝ ከሆነ፣ ግሬራውን ከአፌ አስጠግታ እሷ እንደያዘችልኝ አርጎውን አንድጠጣ ጠየቀችኝ።

ከዚህ መንደር ማግኘት የቻልነው፣ 40 በቅሎዎች፣ 30 ፈረሶች፣ 1700 ፓውንድ ዶቄት፣ 3ሺ ፓውንድ አህል፣ 300 ዳቦ፣ 75 ስልቻ፣ እና 100 ከንድ የሚረዝም የጠፍር ገመድ ነበር። አመሻሽ ላይ የአንግሊዝ ሠራዊት ያለበት ከምፕ፣ ጋዞ ደረስን። *(በዚህ ጊዜ ስፒዲን በማገዝ ለብሪታንያ መንግሥት ያደረግኩት አገልግሎት ታላቅ ነበር። ግን፣ ለመናገር አዘናለሁ፣ ታላቁ የብሪታንያ መንግሥት አመሰግናኝም አያውቅም፤ ቢያንስ ቢያንስ በአቢሲኒያ ዘመቻ የተሰለፉ ጀግኖች ፎተሠጣቸውን ሜዳልያ ሊሰጡኝ በተገባ ነበር። ይህን ጉዳይ፣ እኔ፣ በብሪታንያ መንግሥት በኩል ያልተሰመደ መዘንጋት አደርጊ ነው የወሰድኩት። እናም ለዚህ ታሪክ ፀሀፊ በጣም ከበድ ያለ በደል ነው የደረሰበት።)*

ጠሩ ከጋዞ ተነስቶ አስራ አምስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ አብደቁም ተጓዘ።

የዚህ አካባቢ የአገሩ ሁኔታ በጋዞና በሳንታሪ ካየነው ጋር ይመሳሰላል፤ የሚለየው ነገር ቢኖር ይኼኛው ትንሽ ደልዳላነት አለው።

በአብደቁምና በመቅደላ መሀከል ተራብን የሚሉ ሰዎች ዘገባ ከመጠን በላይ ነበር። አንደሚባለው ከሆነ፣ ቴዎድሮስ አገሩን በሙሉ አቃጥለውታል፤ ያለ የሌለ አህሉን ይዘውት ሄደዋል፤ ሰለዚህ፣ የናፒየር፣ በመላ የተዘጋጀው ፅቅድ፣ መጨረሻው ወደ ድንገተኛ አደጋ የሚያመራ ይመስላል። ነገር ግን፣ ብዙ መሠረት የሌላቸው ወሬዎች ሲሰራጩ ለለነበር፣ ሰዎች በአቢሲኒያ ስለሚወራ ማንኛውም ነገር ሙሉ አምነት አልነበራቸውም።

ያም ሆኖ የምግብ ራሽን ያነስ ነበር፣ የነበረንም ስንቅ ቢሆን መግባደድ ከጀመረ ቆይቷል። ለአንድ ሳምንት፣ ቡና፣ ስኳር፣ ድንች፣ አልኮል፣ ቅጠላ ቅጠልና አይብ አልነበረንም። በጣም ባነሰ ቀለብ ነበር የምንኖረው፤ በቀን፣ አንድ ፓውንድ ሥጋ፣ ስኳር የሌለው ሻይ፣ አስር አውንስ ዶቄት፣ አራት አወንስ ሩዝ፣ አናም ግማሽ አወንስ አሞሌ ጨው ነበር። ሠራተኞቻችን ደግሞ፣ ለወታደሮች ከሚታደለው ራሽን ግማሽ ነበር የሚስጣቸው። ፈረሶቻችንም ቢሆኑ፣ በስምነት ፓውንድ ሳርና በአራት ፓውንድ ገብስ ነበር የሚኖሩት። በቅሎዎች ደግሞ፣ አራት ፓውንድ ሳርና ሶስት ፓውንድ ገብስ ነበር የሚሠጣቸው። የወደፊት ሁኔታው በጣም ጨለም ያለ ነበር። በሁለት ተጨማሪ ቀናት የነበረውን ሁሉንም ቀለብ አንጨርሰዋለን። የስንቅ ክፍሉ በየቀኑ ተጨማሪ ስንቅ ካላገኘ፣ በአርግጠኛነት ረሃብ ይገባል፤ የቀረን ነገር

ቢኖር የነበሩ ከብቶቻችን መማደል ነው። አንደዛ ከሆነ ደግሞ ተጨማሪ ቀስብ ከአንጣሎ አስከሚመጣ ድረስ ለአንድ ወር የሚሆን ቀለብ ይኖረናል። ይህ ሀሳብ ግን ምንም የሚያለደስትም አልነበረም።

በሁለተኛው ቀን፣ ጦሩ ከአብደቁም ወደ ስንዲ ተሻገረ፤ ያም የሶስት ማይሎች ርቀት ብቻ ነው የነበረው። የሰር ቻርለስ ስታቨሊ 2ኛው ብርጌድ ማምሻውኑ አብደቁም ደረሰ። ስለዚህ በሁለቱ ብርጌዶች መሀል የሶስት ማይሎች ልዩነት ብቻ ነው የነበረው።

የነበዜ አንት፣ ጀኔራል መሸሻ፣ ከሰአት በኋላ ወደ ናፒየር መጣ። ሶስት መቶ በሚሆኑ ፈረሰኞች ታጅቦ ነበር። ከደረሰ በኋላም፣ ጀኔራል ናፒየርን፣ 6ሺ ፓውንድ የሚሆን ዶቄትና አህል የገዛ መሆኑንና ያንኑም ወደ ካምፑ በቀጥታ የሚልከ መሆኑን ነገረው። ይህ በጣም የሚያረካ ዜና ነበር።

ቀኑ መሸቶ ስለነበር፣ መሸሻ፣ ከካምፑ ብዙም ሳይርቅ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወዳለ መንደር በመሄድ አብረውት ከነበሩ ሰዎች የተወሰኑትን በመንደሩ አንዲቆዩ መራ። ያንን መንደርም ትቶ ከቀሪው ጦሩ ጋር ለመደባለቅ ሶስት ማይሎች በስሜን አቅጣጫ ሲጓዝ፣ ከጀኔራል ስታቨሊ ጠባቂ ዘቦች ጋር ድንገት ይገናኛል። ጠባቂ ወታደሮቹም፣ አንድ አስር አለቃና የ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ አራት ሰዎች ነበሩ። አነዚህ ወታደሮች መሸሻን አያውቁም፣ ስለሱ ከዚህ በፊት የሰሙ መሆናቸው ያጠራጥራል። ነገር ግን፣ በየቀኑ ድንገት አደጋ ይጥላል ስለሚባሉት ቴዎድሮስ ይሰሙ ስለነበር፣ ይህ በድንገት ወደነሱ የሚገሰግሰው ጦር ወይ ንጉሡ ራሳቸው ናቸው አለዚያም የንጉሡ አሳሽ ጦር ነው ብለው አሰቡ። ፈረሰኞቹ ወደነሱ ሊገሰግሱ ሲያዩ፣ ለማስጠንቀቅ መጮህ ጀመሩ። ነገር ግን፣ ማንም ሰው በድንገት በጠባቂ ዘቦች ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ፈረሰኞቹ በግትርነት ወደፊት ገሰገሱ። ለወታደሮቹም ይህ ሁኔታ ጥርጣሪያቸውን ያረጋገጠ መሰለ። አስር አለቃው ተኩስ አንዲጀመር ትዛዝ ሰጠ። ዘቦቹ ሲተኩሱ ወዲያውኑ ሁለት የመሸሻ ሰዎች አፀፋ ተኮሱ። አስር አለቃው፣ ወታደሮቹ በሰዎቹ ላይ በተከታታይ አንዲተኩሱ ካዘዘ በኋላ፣ "ወደፊት" በሚል ቃል እንዲያጠቁ ተናገረ። አነዚህ አምስት ወታደሮች፣ ሃምሳ የሚሆኑ ጎራዴ የያዙ አቢሲኒያውን ላይ ገሰገሱ። መሸሻ፣ የተፈጠረውን ስህተት በመገንዘብ ሰዎቹ ወደኋላ አንዲያፈገፍጉ ትዛዝ ሰጠ። ነገር ግን አጥቂዎቹ ወደኋላ የዘገዩትን አየቆረጡና አየወጉ ነበር። የቀሩትን ካሳደዱ በኋላ፣ አባረው መያዝ የማይችሉ መሆኑን ሲገነዘቡ፣ አነዚህ ቁጥራቸው አነስ ያለ ጠባቂዎች ሁለት ከገዱሉና ሁለት ካቆሰሉ በኋላ ወደ ምድብ ቦታቸው ተመለሱ።

አንደሚጠበቀው፣ ተኩሱ በሁለቱ ካምፖች፣ በናፒየርና በስታቨሊ መህል ግርግር ፈጠረ። 2ኛው ብርጌድ ትጥቁን አንስቶ ከካምፑ ውጭ መስመር ስራ፣

3ኛው ቀላል ፈረሰኛ ደግሞ በቅርብ ያለውን ጋራ ተቆጣጠረ። 4ኛው የአውሮፓ አግረኛ አና በሎቺዎች ክነኛው ብርጌድ ካምፕ ውጭ ተንቀሳቀሱ፤ በዙሪያው የሚገኝ ሰፊ ቦታ መቆጣጠር የሚያስችል ክፍታ ለመያዝ ነበር። ሁሉም፣ ስለጭር ጊዜ ቢሆን፣ ተኩሱ በጠባቂዎችና በጠላት መህከል ነው ብሎ ያመነው።

አስተርጓሚው ሚስተር መንዚንጀር፣ ከሲንዲ ፈረሰኛ የተወሰነ ክፍል ጋር በመሆን ሁኔታውን ለማጣራት ተንቀሳቀሰ። መሸሻና ሰዎቹ የተጠጉበት መንደር መክላከያ ነበረው፤ አጥሩም በተናደዱ የመሸሻ ሰዎች እየተጠበቀ ነበር። ሰዎቹም፣ ፈረንጆቹ ተንኮለኞች ናቸው፤ ባንድ በኩል ለአለቃቸው የወዳጅነት ፊት ያሳዩት ስመማደል አሰበው ነው በማለት ስላመኑ፣ ወደፊት ወደነሱ ወደሚመጣው የስንዲ ፈረሰኛ ላይ ክመተኮስ የተቆጠቡት በመክራ ነበር።

በመንዚንጀር በኩል በትግሰት ብዙ ውትወታ ከተደረገ በኋላ፣ መሸሻ ወደ መግቢያው በር መጥቶ የሚሰውን ለመስማት ተስማማ። በቂ ገስፃና ምክንያቶች ክተሠጡ በኋላ፣ በአቢሲኒያው አለቃ በኩል ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ ተደረገ። ስሞቱት ሰዎች ቤተሰቦች የደም ካሳ ከፍያ ሶሰት መቶ ዶላሮች ተስጠ፤ ይህም ቤተሰቦቻቸውን የሚያረካ ሆኖ ነው የተገኘው። የሞቱት ሰዎች፣ ክፍ ያሉ አለቆች ሳይሆኑ ተራ ገበሬዎች በመሆናቸው፣ የደም ካሳው በኢትዮጵያ ቀለል ተደርጎ ነው የሚወሰደው። የቆሰሉት ሰዎች ወደ እንግሊዞች ሆስፒታል ተወስደው ህክምና ተደረገላቸው።

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ ከስንዲ ተነስቶ ቁልቁል የጀዳን ሸለቆ አቋርጦ እንደገና ወደላይ፣ በተቃራኒው በኩል፣ ወዳሰው ወደ ዳውንት ደላንታ ክፍታ ተጓዘ፤ የዚህ ቦታ ክፍታም ከባህር ወለል ፲፪ ጫማ ነው።

ከስንዲ እስከ ሸለቆው ድረስ ስድስት ማይሎች ርቀት አለው። ሸለቆ ማለት ረኸም፣ ጥልቀት ያለው ጠበብ ያለ ቦታ ነው። ይህ የሸለቆ ጥሩ ገለፃ ቢሆንም፣ የጀዳን ሸለቆ በሁለት አኩል በሆኑ አምባዎች መካክል የሚገኝ ጥልቀት ያለው ቦታ ነው ብዬ ብገልጥ በጣም ጥቂት ሰዎች ነው የጀዳን ሸለቆ ውነተኛ ሰፋትና ጥልቀት ሊገነዘቡ የሚችሉት። መናገር ካለብኝና ክተናገርኩ፣ ከቆምንበት ክዋድላ ጫፍ ከስራችን አፉን ክፍቶ የሚታየው ይህ ሸለቆ የሰላሳ ማይሎች ርዝምት፣ የሶሰት ሺ ስምንት መቶ ጫማዎች ጥልቀትና፣ በዋድላና በደላንታ መህል የሁስት ማይሎች ስፋት አለው። ሰለዚህ ለአንባቢዎች የጀዳ ሸለቆን የውነተኛ ተፈጥሮ መግለፅ ነበረብኝ። ለብዙዎች ይህ ትክከለኛ ገለፃ እንኳን የሚያሰፈራውን ጥልቀትና ገፅታ በውል ሲያስገነዝባቸው አይችልም። ሰለዚህ ይህንን መግለፅ ደግሞ የኔ ግዴታ ነው ብዬ ስለማምን ስለቦታው በዝርዝር አገልፃለሁ።

ከካምፑ ሁለት ማይል ሳር የበዛበትን አካባቢ ለቀን ሄድን፤ ፊት ለፊታችን ደግሞ በአሳት የተለበለበ የተንጣለለ ቦታ ይጠብቀናል፤ የቴዎድሮስ ወታደሮች የእጅ ሥራ ነበር። ገራገር የሆነ ዳገታማ ኮረብታ ወጥተን ስንጨርስ፣ ጨለማ የሆነ የቋጥኞች ግድግዳ በዋድላ ተቃራኒ በኩል ይታይ ጀመር። ወደ አፋፉ ጠጋ ስንል፣ የቴዎድሮስ ካምፕ የነበር ቦታ አገኘን። ቤት ሆር ነበር፣ ብዙ ጊዜ በጋዜጣዎችም ይጠቀሳል፤ ከታች በጀዳ ሸለቆ መንገድ ሲያለፉ የንጉሥ ካምፕ በዚህ ቦታ ነበር።

በካምፑ ዙሪያ፣ በማያወላውል ሁኔታ የጦርነት ጭካኔ ኮቴ የሆነ የሚያሰፈራ ፅልመት ይታያል። አሁንም ቢሆን መጠጫ ቦታዎች፣ ለወታደሮች ዳስ ሆነው ተሰርተው የነበሩ ከቢጫ ሳር ጋር የተጠላለፉ የዛፍ ቅርንጫፎች ይታያሉ። የተመለመሉ የበግና የበሬ አጥንቶች ሜዳውን ሞልተውታል። ከዚህ ከዚያም ያገሬው ሰዎች የተበጣጠሱ የጥቁር ብልድ ልብስ ብጫቂዎች ይታያሉ፤ ከአንጨት የተሰሩ የጀርባ ማከሚያዎች፣ ከቀንድ የተሠሩ ማንኪያዎች፣ ከቀንድ የተሠሩ ዋንጫዎች፣ የሴቶች ትራሶች እናም ቁጥራቸው በርከት ያለ የቆዳ ሽርጦች ይታያሉ። በዚህ ቦታም ሴቶቹ አህል የሚፈጩባቸው የድንጋይ ወፍጮ ስባሪዎች፤ የተሰባበሩ የመፍተያ አንጨቶች በየቦታው ተብተነው ይታያሉ። በካምፑ መሀል ላይ፣ ለኛ፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን እንዴት በጭካኔ ይገዙ አንደነበር ምልከት የሚሆን፣ የተቆረጠ የለው ከንድና፣ በአግድሞሹ የተተረተረ የራስ ቅል አየን።

የአፋፉ ደንበር ስንደርስ፣ ቴዎድሮስ በጠንካራ አለት ላይ ያለሩት መንገድ ከፊት ለፊታችን ተከፍቶ ጠበቀን። በዚህ መንገድ፣ የተጓዙ የመጀመሪያው ከፍል በአንድ ጊዜ አለፈበት። ለመጀመሪያዎቹ መቶ ያርዶች በጣም ቁልቁለት ነበር፤ ሲለካ፣ ከስር አንድ ጫማ፣ ከፍታው ላይ ደግሞ ሶስት ጫማ ነበር። በዚህ ማለፊያ በሙሉው መንገድ፣ የቴዎድሮስ የመቦርቦሪያ ምልከቶችን ማየት አንችል ነበር። ይህ መንገድ ለንጉሥ በጣም አድካሚ መሆን ነበረበት፤ ምክንያቱም የተጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ጥራት ያልነበራቸው ከመሆኑ በተጨማሪ አንደ ጎበዜ ያለ ጠላት ከላይ አያንጎበበ፣ ሌላው ጠላት፣ የአንግሊዝ ጦር ከኋላቸው እየገለገለ ነበር። ያገሩ ተወላጆች አንዳሉት፣ ንጉሥ ራሳቸው አንደ ተራ ለው በጣም ይሰሩ ነበር። የሥራውን ሁኔታ ለማየት፣ በነጭ በቅሎ ያለማቋረጥ ወዲያና ወዲህ ይመላለሱ ነበር። አንዳንዴ ሲያበረታቱና ሲያመሰግኑ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያሰፈራሩ፤ አልፎ አልፎም ሲያስገርፉ፣ ካልሆነም ደግሞ ለው በሞት አንዲቀጣ ትዛዝ ይለጡ ነበር። አንደገናም ከበቅሏቸው ይወርዱና ራሳቸው በመስራት፣ ስራ አንዴት መለራት እንዳለበት ለሰዎቻቸው በምላሌ ያሳዩ ነበር። ከአምስት ሳምንታት አድካሚ ሥራ በኋላ፣ ከዋድላ ከፍታ ቁልቁል ወደ ጀዳ፣ ከዛም ወደላይ ወደ ደላንታ

እፋፍ የሰላሳ ጫማዎች ስፋት ያለው የስምንት ማይሎች ርዝመት መንገድ ሠርተዋል። በዚህ መንገድ፣ ወደ ታች ቁልቁል፣ ከእንዱ እርከን ወደ አንዱ፣ ወደታች፣ አንዳንዴም ቀጥ ያለ ገደል ሊሆን ትንሽ በሚቀረው ቦታ ተጉዘን፣ ከታች ከሸለቆው ወለል ድረስ ወረድን። ወለሉ ደግሞ በጠጠሮችና ደቦልቦል ባሉ ድንጋዮች ተሸፍኗል። በጣም ጠለቅ ባሉ ጉድጓድ ቦታዎች ውሀ ይገኝባቸው ነበር።

ከቀኑ ስምንት ሰአት ሲሆን፣ የተጓዙ ቀዳሚ ከፍል እንደገና መንቀሳቀስ ጀመረ፤ ወደላይ ለመውጣት የሚታገሉትን ወታደሮች ፊት ማየት በጣም የሚያሳዝን ነበር፤ በፊታቸው ላይ ተስፋ የመቁረጥና የመከፋት ሁኔታ ይነበብ ነበር። አነሱ ደረጃ በደረጃ ሲጓዙ መከተል እያስፈልግም፤ ባጠቃላይ በየሃምሳ እርምጃዎች ቆም እያሉ፣ ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን የደላንታ አፋፍ ላይ ወጡ።

ከዚህ ቦታ ሆነን፣ የጦሩ ጓዝ መስመር ከዋድላ ጀምሮ ቁልቁል ሲወርድና ወደላይ ወደላንታ አቀበቱን ሲወጣ በሙሉ ርዝመቱ ማየት እንችላለን። ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ከስንዲ ተነስተን መንገድ ብንጀምርም፣ የሚያስደንቀው ነገር፣ የጓዝ መስመሩ የመጨረሻው ከፍል፣ ከቀኑ አስር ሰአት ላይ እንኳን ገና ከዋድላ አልተነቃነቀም። ጓዛቸው ወደኋላ የቀረባቸው ሰዎች፣ ሌሊቱን ያለ ድንኳን፣ ብርድልብስ ወይም ያለ አራት እንደሚያሳልፉ በእለምጅቸው መዘጋጀት አለባቸው፤ አዛኝ የሆኑ ሰዎች ተገኝተው ለዚህ ቀን ግታ ምግብ ካላካፈሏቸው በስተቀር።

አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ አሊ በአሸናፊነት፣ የኔን ጓዝ ይዞ ከተፍ አለ። ካርቴን ስዊኒ ሁለት ጊዜ ቢያሰቆመውም፣ በመንገዱ ላይ ብዙ የማይሆኑ ውኔታዎች ስለሚፈጠሩ፣ አረቡ አሊ፣ ሁለቱን ኢጋሰሶች ከሰዎቹ ነጥሎ ለትንፋሽ ካልሆነ በስተቀር ምንም ሳያቆም ይዟቸው መጣ።

በአዲሱ ካምፓችን በደላንታ፣ ማምሻውኑ የጓዙ ግማሹ እንኳን አልደረሰም። ጨለማው ሲመጣ ደግሞ፣ በተጠማዘዘው መንገድ ላይ በመኳተን ላይ ያሉ ሰዎች ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ተዋጡ፤ ስለዚህ አያንዳንዱ ሰው በነበረበት ቦታ የሚቻለውን ማድረግ ነበረበት። ኮርቻዎችን አውርደው፣ ጭነቶችንም አራግፈው፣ በቅሎ ወይም ፈረሶቻቸውን ከጥጋቸው በሚገኝ ቁጥቋጦ አስረው፣ ከዛፍ ወይም ከቁጥቋጦ ሰር በመተኛት በተቻላቸው መጠን ድካማቸውን ለማላለፍ ሞከሩ።

በሚቀጥለው ቀን ማታ ከመሸ በኋላ ነበር የተወጠረው የጓዝ መስመር ደላንታ አፋፍ የደረሰው። በሸለቆው፣ አንስሳቶች በቁጥር ሞተዋል።

ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት ተጨማሪ አንቅስቃሴ ማድረግ የሚሞከር ነገር አልነበረም። በእጃችን ቀሰብ ወይም ራሽን አልነበረም። አንደኮሚሳሪያቱ

ሪፖርት፣ 4ሺ ፓውንድ አህል ብቻ ነው የነበረው። ይህ መጠን በነኛው ብርጌድ ውስጥ ለነበሩ 5ሺ አንስሶች ቢከፋፈል፣ ከሰላሳ ስድስት ስአታት ፆም በኋላ አያንዳንዳቸው ሊደርሳቸው የሚችለው ስድስት ተኩል አውንስ ነበር። በዚያን ቀን ደግሞ የሰር ቻርለስ ስታቨሊ ብርጌድ ከተጨማሪ 5ሺ አንስሶች ጋር ስለሚመጣ ምንም የሚተርፍ አህል አልነበረም። ስለዚህ ካፒቴን ስፒዲ የደላንታውን ገዢ እንዲያናግር በአስቸኳይ ተላከ። የደላንታው ገዥ ሁልጊዜ ለቴዎድሮስ ቀሰብ አልሰጥም በማለት ከሸፍቶች ሁሉ ቀንደኛው ነው የነበረው። ስለዚህ የሚገዛ ቀሰብ ካለ ስፒዲ አንዲጠይቅ ነው።

የስፒዲ ተልኮ በጣም የተሳካ ነበር[114]። መቶ በቅሎዎች ከነሙሉ ጭነታቸው ይዞ ተመለሰ፤ የተጫነው አህል ቢገመት ወደ 10ሺ ፓውንዶች ይሆናል፤ ከዚህ በተጨማሪ፣ በሚቀጥለው ቀን ሌላ መቶ ሺ ፓውንዶች የሚሆን አህል እንደሚያገኝ ቃል ተገብቶለታል።

ይህ በርግጥ በጣም የሚያስደስት ዜና የነበረው፤ በተለይም በቴዎድሮስ ተዘርፏል ከተባለ የአገሩ ከፊል ይህን ያህል መገኘቱ። የደላንታው ገዥ፣ የአንግሊዞችን ጉዳይ ያለማመንታት ተቀብሎታል፤ ስለዚህ ደስታው የጋራ ነበር። በሚቀጥለው ቀን፣ ሚያዝያ 7፣ ከደላንታ የትተረፈረፈ ነገር ሲመጣ ነው ምስከር የሆነው። አህል፣ ዶቄት፣ ዳቦ፣ ማር፣ ዶሮ፣ ሳር፣ ገለባ፣ በሬና ፍየሎች ነበሩ።

ሚያዝያ 7፣ ማምሻውን ለረዥም ጊዜ ሊጠበቁ የነበሩት፣ የ45ኛው ሬጅመንት አና የ3ኛው ድራጎን ጋርድስ ደላንታ ካምፕ ደረሱ።

ጦሩ፣ አሁን አንድ ቦታ ስብሰብ ብሏል አናም የተዋጊዎች ቁጥር ወደ 5500 ደርሷል። የነዚህ ሁለት ከፍሎች ከአንጣሎ እስከ ደላንታ ያደረጉት ፈጣን ጉዞ፣ ሁለት ብርጌዶች በመንገድ ላይ፣ በሪጅመንት ቢከፋፈሉ ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር ነው ያሳየው።

በሚያዝያ 8፣ ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን፣ ጠቅላይ አዛዡ ከረዳቶቹ ጋር ሆኖ በፈረሰኛ ታጅቦ ወደ ደላንታ አፋፍ ደቡብ አቅጣጫ ሄደ፤ ከዚያም ሆኖ በከፍተኛ ቦታ ላይ ሲሆኑ፣ በደንብ የሚታያውን መቅደላን ለመቃኘት ነበር። ሪፓርት ሊያደርግም፣ ከመቅደላ ግርጌ የቴዎድሮስ ሠራዊት ድንኳኖችንና ብዙ መድፎችን በምሽጉ ማየቱን ተናገረ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሊንቀሳቀሱ

---

[114] ከዚህ በፊት በነበረው ትውውቅ፣ ከባላባቶች ጋር ሰላም ለመፍጠር ችሏል። ስፒዲ፣ ከዚህ ቀደም፣ ለዳውንቱ ባላባት ስለ ለማዳ ዝሆን አሜውቶት ነበር፤ ሆኖም ባላባቱ አላመነውም ነበር። ስፒዲም ለዘመቻው ከመጡ ዝሆኖች አንዱን አስፈቅዶ ላዩ ላይ በመሳፈር ወደ ባላባቱ በመሄድ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን በገሃድ አሳይቶ የባላባቱን ስምምነት ማግኘት ችሏል። ለዚህም ነው የተዘረዘረውን ያህል ቀሰብ ይዞ መምጣት የቻለው።



የከባድ መሳሪያ ጉዞ መስመር

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

የታዩ ሲሆን፣ ከካምፑ እሳት የሚነሳው ጭስ ወደላይ እየተጠቀለለ ሲወጣም ይታይ ነበር።

ሰር ሮበርት፣ ቦታውን በጣም ጠንካራ ነው አለ፤ እስካሁን ካየናቸው አምባዎች ሁሉ የበለጠ ነበር፤ ይህ ደግሞ በሁላችንም የነበረውን ሃሳብ አረጋገጠ፤ ማለትም፣ ንጉሡ የበለጠ ጠንካራ ምሽግ ባይኖራቸው ኖሮ በመንገድ ላይ ያየናቸውን ጥሩ አምባዎችን ችላ አይሉም ነበር። ትልቁ ጥያቄ በሚያረካ መንገድ መልስ አገኘ። ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ናቸው!

ሰር ሮበርት ከቅኝቱ ሊመለስ፣ ኢንጂነሮቹ መወጣጫ መሰላሎችን መደርመሻዎችን መስራት ጀመሩ፤ ይህም ብዛት ባላቸው ጠንካራ የምሽጉ ገደሎች ለመውጣትና ለማጥቃት ታስቦ ነው።

አእምሯችን ተረጋጋ። ካምፑም ውስጥ መረጋጋት ሰፍኗል። ቴዎድሮስ በምሽጋቸው አንዳሉ ታውቋል። ነገ ከኛ ካምፕ፣ ከደላንታ በደቡብ ጠርዝ ሆነን መቅደላን ማየት እለብን። ሁሉም የደስታ ስሜት ተሰማው፤ እናም በእቢሲኒያ በአንግሊዝ ካምፕ ውስጥ በደላንታ እንደሆነው እንዲዚህ ሳቅና ጨዋታ ስምተን አናውቅም።

የሚፎካከሩት የወታደር የሙዚቃ ባንዶች የየራሳቸውን የሚያነቃቁ ሙዚቃዎች ተጫወቱ። የባህር ሀይል ብርጌዱ የፑንጃቡን ባንድ ጋብዞ ነበር። የብርጌዱ አባላት በጥንድ መስመር ዙሪያውን ቆርጠጥ በማለት፤ በመሀከሉ መርከበኞቹ የባንዱን የሚያስደስት ሙዚቃ በመከተል ቀለል ያለ እሰደናቂ ውዝዋዜ ያሳዩ ነበር።

ያገሩ ተወላጆቹ ደግሞ የካምፑን ገበያ ትተው እነዚህ መርከበኞች የሚያሳዩትን ያልተለመደና ሊረዱት ያልቻሉትን እንቅስቃሴ አይኖቻቸውን ከፍተው ነበር የሚያዩት። ምናልባትም ለእግልከቶቻቸው ፀሎት እያደረጉ ነው ብለው ያመኑት። ቀስ እያለ ሙዚቃውም አቆመ፤ ሁሉም ወደ ምድብ ቦታው ተመለሰ። የመጨረሻው ድምፅ ተሰማ፤ መብራቹም ጠፉ፤ ነገር ግን በዚህ ብርሃን ባለው የቢጋ ሌሊት ማን መተኛት ይችላል?

ከምድሩ ወደላይ ካሉ ከፍሎች ረጋ ያለ ነፋስ እያፏጨ ይመጣ ነበር። በለማዩ ላይም የደቡብ መስቀል የሚባለው ኮከብ ከበሽሎ ከልል በላይ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፤ የፐለይዲዝ ከዋከብት ጥርት ብለው ያበራሉ። ረጭ ያለ ፀጥታ በካምፑ ውስጥ ሰፍኗል፤ የድካም መልእክ ከንዱን የተኙት እንግዶች ላይ ያሳረፈ ይመስል ነበር።

ምዕራፍ ዘጠኝ



የፖለቲካ መረጃ ሥራ፣ መቅደላ - የድራማው የፍፃሜ ትዕይንት፣ ቴዎድሮስ ተኩስ ከፈቱ፣ የእቢሲኒያኖች ማጥቃት፣ የኮሎኔል ፔን የመጨረሻ ሰላምታ፣ ጅቦች ተኩላዎችና ሥራቸው

ከደላንታ ሰሜን ጫፍ በኩል ተነስቶ እስከ ደቡቡ ዳርቻው ድረስ ያለውን ጉዞ ከመግለፃችን በፊት፣ ከእንጣሎ ከተነሳን ጀምሮ ካምፓችን ድረስ ስለመጣው የፖለቲካ ማዕበል ዕይታ እናድርግ። የመጨረሻው እኔ የጠቀስኩት ዜና፣ ቀኑ መጋቢት 6፣ 1868 ነበር።

መጋቢት 16 - ከራስም የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፤ በውስጡም ቴዎድሮስ የእንግሊዞችን መምጣት ለወታደሮቻቸው መንገራቸውን ይጠቅሰና፣ እንደ ቴዎድሮስ አገላለፅ፣ እንግሊዞች ነጋዴዎች ናቸው፤ ምንም እንኳን ጥሩ ነፍጥ ቢሠሩምና በርቀትም ቢጠቀሙበትም፣ ወኔ የጎደላቸውና በእጅ ለእጅ ጨበጣ ውጊያ ከአቢሲኒያውያን ጋራ አይወዳደሩም። ወታደሮቻቸው እንግሊዞችን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፉና እንደሚጨርሷቸው፣ የተማረከውን ንብረትም ወታደሮቹ መከፋፈል እንደሚችሉ ቃል ገብተውላቸዋል።[115]

መጋቢት 19 - በመንዚንጀር በኩል፣ የዋግሹም ጎበዜ ካምፕ እንደደረሰና በመስፍኑ በዋግሹም መልካም እቀባበል እንደተደረገለት ሰማን። በተጨማሪ ሲገልፅም፣ ጎበዜ ለስር ሮበርት ናፒየር የወዳጅነት እጅ ዘርግቷል፤ ዘመቻውን ለማፋጠን ማድረግ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር በመልካም ፈቃድ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

ቴዎድሮስ በቤት ሆር ይገኛሉ፤ መድፎቻቸውን ከጀዳ ሸለቆ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። በመንገዳቸው አገሩን በሳት ለኩሰውታዋል። የዋድላ[116] ደላንታ ጎሹ ሸፍቶ በንጉሡ ሠራዊትና በደላንታ ሰዎች መሀከል ጥቂት ግጭቶች ተፈጥረዋል።

---

115 በተቃራኒው፣ ቴዎድሮስ ለወታደሮቻቸው ስለንብረቱ ቢያወሩም፣ የእንግሊዝ ወታደሮችን ትክክለኛ ችሎታ ተናግረዋል። ይህን ሁኔታ ራሳም ራሱ በመፅሐፉ ያትታል።

116 የዋድላ ሰዎች የንጉሡን መምጣት ሲሰሙ ቤታቸውን ጥለው ወደ ላስታ ሸሽተዋል።

መጋቢት 20 - ሌላ መልክት ይደርሳል። ቴዎድሮስ የደላንታ አፋፍ ላይ ደርሰዋል፣ ወደ መቅደላ አየተጓዙ ነው።[117]

መጋቢት 29 - የቃኘው ጦር አዛዥ ኮሎኔል ፋይሪ፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር ማስታወሻ ይልካል፤ በማስታወሻውም መንዚንጀር ቡቴዎድሮስ ቃፊር ወታደሮች መያዙን፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው በአምባቸውና በደላንታ መህከል ያለውን የበሽሎን ወንዝ መልሰው አያቋረጡ እንደሆነ፣ ይህም አንግሊዞቸን ለማሰፈራራት ታስቦ መሆኑን ይገልጣል።

መጋቢት 31 - መንዚንጀር ከደጃች መሸሻ ካምፕ ሆኖ በራሱ በአጁ በተፃፈ ማሰታወሻ፣ የጎበዜ ጀኔራል፣ ለር ሮበርት ናፒየር ሳንታሪ አንደደረሰ ሊገናኘው አንደሚመጣ ይጠቁማል። ቴዎድሮስ አዛው መቅደላ ናቸው፤ አምባው ከደረሱ በኋላ ተመልሰው በሽሎን[118] አላቋረጡም።

ሚያዝያ 4 - በመጣው ዜና፣ የደላንታ ሰዎች ለቴዎድሮስ አሜን ብለው ገብረዋል።

ሚያዝያ 8 - ራሳም ለኮሎኔል መርዌዘር ደብዳቤ ይልካል። ኮሎኔሉ ከጦሩ ጋራ፣ ከወልደ የሱሰ ጋር ካደረገው የተሳካ ተልዕኮ አየተመለሰ ነው። የራሳም መልክት፣ "ተጠንቀቁ! ንጉሡ እየተንቀሳቀሱ ነው። በሌሊት ጥቃት ሊያደርጉባችሁ ሰለሚችሉ በጣም ተጠንቀቁ። ለኛ ሰትሉ ከሰውየው ጋር በመልካም ሁኔታ ተደራደሩ። በትንሹም ቢሆን ቁጣቸው ከገነፈለ የህይወታችን መጨረሻ ይሆናል። በካምፓችሁ ጥሩ ሻምፓኝና መጠጦች አላችሁ ወይ? ውድ ኮሎኔል፣ ከአንተ ጋር በምገናኝበት ጊዜ የሚሆን ለኔም ጥቂት አቆይልኝ። ፈጣሪ ይባርከህ።"

ሚያዝያ 9 ጠዋት፣ ሁለት ብርጌዶች ከጀዳ ሸለቆ በላይ ካለው ካምፓችን ተነሰተው ከመቅደላ ትይዩ ወደ ሆነው በደቡብ አቅጣጫ ወዳለው ሜዳ ተንቀሳቀሱ። ሜዳማ ቦታው እንደ ቢሊያርድ መጫወቻ ጠረጴዛ ለለላ የሆነና ስድስት ማይሎች ርቀት ያለው በመሆኑ፣ በሁለት ሰአታት ውሰጥ ደቡብ ጫፍ ላይ ያለው አፋፍ ደረሰንና ካምፓችን መሰረትን፤ ቦታውም ቁልቁል ወደ በሽሎ ከሚወሰደው መንገድ ግማሽ ማይል ርቀት ነበር።

አንባቢዎች ተከተሉኝ፣ በዚህ ደላንታ አፋፍ ጫፍ ላይ ሆኜ በተቻለኝ አቅም ሰመጥሩውን መቅደላና አካባቢውን ላሳያችሁ። አይናችሁን ግለጡና ዕይታውን ተመልከቱ!

---

[117] እንግሊዞች፣ ለዳውንትና ለደላንታ አለቆች፣ ቴዎድሮስ መቅደላ አንዳይደርሱ እንዲቆርጧቸው መልከት ልከው ነበር። ያሰቡት አልሆነም። ቴዎድሮስ የዚህ መረጃ ደርሷቸው እንደሆን ማረጋገጫ የለም።

[118] የበጌምድር ደንበር እሰከ በሽሎ ወንዝ ድረስ ነበር።



ወደ መቅደላ የሚወሰደው መንገድ

ካለሁበት ከደልዳላው ሥፍራ ወደ ጠርዙ በኩል፣ ከቆምኩበት ሆኜ ቁልቁል ስመለከት፣ ቀጥ ያለ የሀምሳ ጫማ ጥልቀት ያለው የአለት ግድግዳ አለ። ከዛም መቶ ጫማ ወይም ከዛ በላይ የሆነ ዳገታማ የሆነ አርከን ወደፊት ይዘረጋና፣ በድንገት በሌላ ቀጥ ባለ ተመሳሳይ ጥልቀት ባለው የአለት ግድግዳ ይቋረጣል። ከስሩ በኩል ወደ መቶ ያርዶች ርዝመት ያለው፣ የተጥመዘመዘ፣



ከደላንታ አፋፍ፣ የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ



ጦንጀቦቹ ሳንጃ ወድረው አቢሲኒያውያንን ሲያጠቁ
William Barnes Wollen - the 1895 British book Illustrated

ለማግኘት በትግስት መጠባበቅ ጀመሩ። ያን ያህል ሳይጠብቁ፣ ጠቆር ያሉት ሰዎች፣ ሰብሰብ ብለው ከጫካው መውጣት ጀመሩ። ጦንጀቦቹም ተኩስ ከፈቱባቸው፤ እየተኮሱም፣ ከዳገቱ ቁልቁል ወደነሱ ይወርዱ ጀመር።



የእንግሊዞች ሮኬት ተኳሾች ብርጌድ (በእጃቸው የያዙት ቱቦ የሚመስል ነገር ሮኬት መተኮሻው ነው።) (From the collections of the Imperial War Museums)



የአሮጌ ሙጊዶ
(ዋቢ መፅሐፍት ኦ.ቁ. 16)



(በዚህ ምስል፣ ሁሉቱ ጋራዎች፣ ፋላና ስላሴ ተለይተው ይታያሉ፤ ከፋላ ጋራ የጣሊያው ጭስ የአፄ ቴዎድሮስ መደፎች ሲተኮሱ ነው።)

የምናርፍበት ቦታ ስንደርስ ድንኳኖቹ አንዳልመጡ አወቅን። አንኳን የሠራተኞች ጓዝ ሊደርስ ምንም ምግብም አልመጣም። ተከታዮች ግን በመቶዎቹ አየመጡ ነበር፤ እናም የተለያዩ ቃላት ለውጦች ሰደቦችና ወቀሳዎች መለዋወጥ ጀመሩ።

የተራቡ በቅሎዎቹ ማናፋት፣ ፈረሶችም ቢሆን የአህል ቀለባቸው ሰላልተሰጣቸው ማሰካካት ጀመሩ፤ ሆኖም፣ ለከብቶችም አህል ሆነ ለሰዎች ምግብም አልነበረም። የደከሙት ወታደሮችም መጡና አንዱ አንዱን ስለ ምግብ ይጠይቁ ጀመር። የተሠጣቸው መልሰ እሉታዊ ነበር። አሰከ አኩለ ሌሊት መቆየት አንዳለባቸው ተነገራቸው፤ ድንኳናቸውም ቢሆን አሰከ ጠዋት ድረሰ አይመጣም። ከዚህ በኃላ ጠንከር ያለ ከፍ ባለ ድምፅ ባይሆንም የመከፋት ጉርምርታ ተጀመረ።

"ለመምጣት ምንም አከል አልነበረም።" አሉ። "ለምንድን ነው ያልመጡት?" ለምን? አይ ሰው፣ ለህተት በየቦታ አየተሠራ ነው ወይ? ለምንድን ነው ሰህተት የሚኖረው? ለምን ሁሉም ነገር ሁልጊዜ ትከክል አይሆንም?

መኮንኖችን በሚመለከት፣ በተፈጥሮ የሚታየው በሁኔታው መንገሸገሽ፣ ሰራተኞቻቸው በየኮረጆቻቸው አንዲመገቡ ባመጡላቸው ቀለብ ምከንያት በረድ ብሏል። የሰዎች ሆድ ሊሞላና የምግብ ፍላጎት ሲረካ፣ በዚህ ቦታ አንደታየው ሁሉ፣ ወደ ጨዋታና መዝናናት ያመራሉ። በየሳቱ ዙሪያ፣ በቡድን ቡድን ተቀምጠው አዲሱ ውጊያና ትዕይንቶቹ ላይ የጋለ ውይይት ተደረገ።

አኩለ ሌሊት ሊሆን አብዛኛው ጓዝ መቷል፤ ነገር ግን ድንኳኖች ሊወጠሩ አልቻሉም፤ ለኛ የቀረው ነገር ወደሳቱና ወደ ጭሱ ጠጋ ብለን ባዶ ሜዳ ላይ መተኛት ነበር።

በካምፑ ዙሪያ፣ ብዛት ያላቸው ዘበኞች እንዲቆሙ ተደረገ፤ ወታደሮቹ ለድንገተኛ ሁኔታ ተዘጋጅተው ሰመጠበቅ መሳሪያቸውን አንደታቀፉ ተኙ።

በምንጣፋችን ላይ ከመጠቅለላችን በፊት፣ የቀኑን ውሎ አያሰብን እያሰን፣ ጆሯችን የዱር አውሬዎች ሰመምጣታቸው መረጃ የሚሆን ድምፅ ያዳምጥ ጀመር። ረሃብ ያንሰፈሰፋቸው የጅብና የተኩላ መንጋ በዚህ ጨካኝ ጦርነት የወደቀላቸውን ድግሰ ለመበጫጨቅ መተዋል። አንግዳ የሆነ፣ በማታ ሰው ሰምቶት የማያውቀው አይነት፣ አንቅልፍ የሚያሰወስድ ዜማ አንቅልፍ እንዲወሰደን አደረገን፤ የደነዘዙት ጆሮቻችን በመጨረሻ የሰሙት ድምፅ ቢኖር፣ የተኩላዎችን የሚሰቀጥጥ ጩኸት፣ የጅቦችን ጉርምርታ፣ ጉጉቶች ከሚያሰሙት የህዘን "ቱ- ዊት-ቱ-ዉ" ጋር ተቀላቅሎ ነበር።

ምዕራፍ አስር

በውጊያው የተጎዱ ሰዎች፣ ጥሩ የለበሰ ምርኮኛ፣ የቴዎድሮስ ተስፋ መቁረጥ፣ ራሳም፣ ያልተጠበቀው እሰረኞችን መቀበል፣ የመጨረሻው የእጅ ስጥ ጥሪ

ከትላንትናው ማዕበላዊ ሜዳ በላይ፣ በዚህ እንግዳ በሆነ የሞቱና የሚሞቱ ሰዎች ባሉበት ሸለቆ በላይ፣ ከአንግሊዞቹ ካምፕ በላይ፣ እና ወደ ሰማይ በተዘረጉት የቋጥኞች ጫፎች በላይ፣ ፀሀይዋ በተለመደው የትሮፒክ መቀትና ብርሃን ማብራት ጀምራለች፤ ይህም፣ ሰው ባለቀበት የሰቅለት አርብ ማግሥት ነበር።

ሰአት አብሳሪ ወፍ ከጫካው ውስጥ ከፍ ባለ ድምፅ ይጮሃል፤ በብሩህ ቀለሙ ሌላው ወፍ በደስታ ያፏጫል፤ ሌላውም ወፍ፣ ወደ ላይ ወደ ሰማይ ከፍ ብሎ በመንሳፈፍ ጣዕም ያለው ዜማ ያሰማል፤ ይህ ግን ወደ ህልም ከሚጎትተን ጉጉቶቹ ከሚያሰሙት የሻከረ ጩኸት ይለያል። የሠላም ከፍታዎች! የደስታ ሸለቆ፣ አይደለም ወይ?

በካምፑ፣ ወታደሮች አንደወትሯቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ፤ ሠላምታና ሀሜታዎችን ይቀያየራሉ።

"ቾከራ ኢደር አአ፣" *(አንተ ልጅ ና)* ጄኒራል ናፒየር ለአንድ ሂንዱስታን ወራቶኛ ሲናገር ሰማሁ። "ለሰርጀን[123] ሳሂብ ምሰጋና ይገባዋል፣ ላየው እንደምፈልገው ሂድና ንገረው።"

"ሰርጀን ሳሂብ መቷል፣" ቾከራው ሪፖርት አደረገ

"አሃ፣ ይሁን። ዶክተር እንደምን አደርክ። የሚያምር ቀን ነው። አይደለም አንዴ? ሪፖርትህን አዘጋጅተሃል?"

"አዎ፣ ሰር ሮበርት፣" ከኪሱ ወረቀት እያወጣ፣ ሰርጀኑ መልሰ ሠጠ። "ይኸውና፣ ሰር! አንድ መኮንን ማለትም ካፒቴን ሮበርት እና ሰላሳ አንድ

---

[123] የቀዶ ህክምና ሀኪሞች መጠሪያ

ወታደሮች ቆሰለዋል፤ ካፒቴን ሮበርትና ሰምንት ወታደሮች በፀና የቆሰሉ ናቸው::"

አዚህ ደረጃ ላይ ለማወቅ የነበረን ጉጉት መልሰ አግኝቶ፣ ሁላችንም አንኳን ደሰ ያለን ሰሜት ተለዋወጥን:: "አሰብ አንግዲህ፤ ወዳጄ፣ አንድ ሰው ሳይሞት ስላሳ ሁለት ሰው ብቻ መቁሰል!" አንግዲህ በሌላው ወገን የደረሰውን ጉዳት እናረጋግጥ::

የአራተኛው አግረኛ ጦር ካፒቴን ሰዊኒ፣ ከእጃቢ ወታደሮች ጋር በጦር ሜዳ ቆሰለው የሚገኙ አቢሲኒያውያንን ወደ ካምፑ ሆስፒታል አንዲያመጣ ታዘዘ:: አኔም አብሬው ሄድኩ:: የሚያሰፈራ ሁኔታ ነበር ለእይታችን የተከሰተው:: የትናንትና ማታ ድምፅና ጩኸት ለዚህ ሰቆቃ ቢያዘጋጀኝም፣ በአውን ያየሁት ግን ካሰብኩት በአሰር እጥፍ ነው የነበረው:: አራዊቶቹ አሰከሬኖቹን ሲርመሰመሱባቸው አድረዋል:: ከመጠን በላይ በተገኘው በዚህ የሰው አካል ፈሰከውበታል:: አንደሚባለው ከሆነ ድርቅ ሆኖም አያውቅም፤ ስለዚህ ብዛት ያላቸው ሥጋ በል አውሬዎች መቅደላ አካባቢ ነግሠውበታል፤ እነዚህ አራዊቶች ሀገሩን ከበሽታ ነው ያዳኑት:: ከአሮጌ ውጊያ በኋላ ማታውኑ፣ ለአነሮች፣ ለተኩላና ለጅቦች፣ አግኝተው የማያውቁት ግብዣ ነው የቀረበላቸው::

የሞቱት ለዎች በጥንቃቄ ከተቆጠሩ በኋላ እዛው በወደቁበት ቦታ ተቀበሩ:: በተጨማሪ ጥንቃቄ፤ የቆሰሉና ሌሊቱን በሙሉ በህመምና በሥቃይ ያደሩት፣ ከአራዊቶች መንጋጋ አንኳን ራሳቸውን በሙሉ ለመከላከል ያልቻሉት፣ በተገኘው መንገድ ወደ ሆስፒታል አንዲወሰዱ ተደረገ:: ከሶሰት ሰኢታት ይህን ከመሰለ አድካሚ ሥራ በኋላ፣ የሚቀጥለው ሪፖርት ለዋናው ዕዝ ተሠጠ::

ሰባ አምሰት የአቢሲኒያ ቁሰለኞች ወደ ሆስፒታል ተወሰደዋል:: 560 የሞቱ የጠላት ወታደሮች በቦታው በሰዎቹ ተቀብረዋል:: በውጊያው ያለማሰለሰ ተከታታይ ጥቃት ያደርሰ የነበረው የጦር መሪ፣ ደጃች ደረሰ፣ ከጉልበቱ በላይ በጥይት ተመትቶ አጥንቱ ሰለተሰበረ በሽክም ወደ ሆስፒታሉ ተወሰደ:: አንደሚባለው ከሆነ በካፒቴን ሰፒዲ (ባሻ ፊለቀ) ጥይት ተመትቶ የወደቀው የፈታውራሪ ንብርዬ አሰከሬን ማታውኑ በጀኔራል ናፒየር ትዛዝ ወደ መቅደላ ምሽግ ተልኳል:: ይህም በዘመዶቹ አንዲቀበርና ቴዎድሮሰ ከዋነኛ የጦር መሪና አማካሪያቸው ምርጡ አንደሞተ አንዲያዩ ነው::

ከቁርሰ በኋላ፣ የቅዱስ ጊዮርጊሰ ሰንደቅ አላማ በኩራት ከሰር ሮበርት ናፒየር ድንኳን በላይ ወደሚውለበለብበት ሥፍራ አመራሁ::

"ምን አዲሰ ነገር አለ፣ ካፒቴን?" ብዬ የሰንቅና ትጥቅ ከፍሉን ረዳት አዛዥ ካፒቴን ሆላንድን ጠየቅሁት።

"ምንም፤ ነገር ግን ጭምጭምታው፣ በካምፑ ወሰጥ የማይታመንና የማይረባ ወሬ ተሠራጭቷል ነው። እኔ ራሴ የማውቀው ነገር የለም፤ የማምነው፣ ሰር ሮበርት ቴዎድሮሰ እጁን እንዲሰጥ ይጠይቃል፤ እና ከዛ በኋላ ጠላት ላይ እንደሚንቀሳቀሰ ደፍሬ መናገር እችላለሁ።" በማለት ካፒቴን ሆላንድ በቀላሉ መልሰ ሠጠ።

ካፒቴን ሆላንድ በትክክል ነው የገመተው። ሰር ሮበርት ያቀደው ቴዎድሮሰ እጃቸውን እንዲሰጡ የሚያሰገድድ ጥያቄ ለመላክና፣ ከመልሳቸው በኋላ የተሻለ ነው የሚለውን ነገር ለማድረግ ለመወሰን ነው። የተሠራው ሥራ ባጠቃላይ ይሆናል ብሎ ካሰበው በጣም የተለየ ነው፤ ሰለዚህ በቸኮላ ምንም ነገር እያደርግም። ትናንትና ባሳየው ችሎታ ቴዎድሮሰ ተደናግጠው ከሆነ፣ የቀረበላቸውን ጥያቄ ለማዳመጥ ዝግጁ ነው የሚሆኑት። "እጅተል አል ሽይጣን"፤ "ችኮላ ሠይጣን ነው!" የአረቦች ጥቅሰ ነው።

የአሰረኞቹ ሁኔታና የዘመቻው የመጨረሻ ውጤት በናፒየር ትግሥት ላይ የተመረኮዘ ነው። በፋላ፣ በሰላሴ ወይም በመቅደላ ላይ የተጣደፈ እንቅሰቃሴ ከተደረገ፣ ተሰፋ የቆረጡት ንጉሥ ሙጥኝ ብለው የያዙትን የመጨረሻ የተሰፋ ፍንጣቂ ሊነሰቸው ስለሚችል ያለምንም ጥርጥር አሰረኞቹ በፍጥነት እንዲገደሉ ትዛዝ ሊሠጡ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ንጉሡ ራሳቸው ከመቅደላ ምዕራባዊ ሰሜን መቶ ማይሎች ርቀት ወደ ሚገኘው ወደቋራ ሊጓዙ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የዚህ የዘመቻውን አላማና ግብ ለዘላለም ያከሸፈዋል።

እነዚህን መጠነኛ እሰተያየቶች ካየን በኋላ፣ በሰር ሮበርት የተላከውን የእጅ ሰጥ ጥያቄ መልከት የያዘውን ሰው ማንነት እንወቅ። የሁሉም ጥርጣሬ ወይም ግምቶች ቁልፍ በዚህ መልከተኛ ላይ የተያዘ መሆን አለበት።

መልከተኛው፣ ወደላይ በፋላና በሥላሴ መህከል በሚገኘው፣ ሸለቆው ወደሚወሰደው መንገድ ግማሽ ላይ ሲደርሰ አሱን ባሰገረመው ሁኔታ ሁለት ሰዎች ቁልቁል ሲመጡ ያያል። ወዲያውኑ እንደታወቀው፣ የወረዱት ሰዎች ሎተናንት ፕሪዶና ሚሲዮናዊው ቄሰ ሚር ፍላድ ነበሩ[124]፤ ከንጉሡ፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር የተላከ መልከት ለማድረሰ በመንገድ ላይ ነበሩ። ከካምፕ የተላከው መልከተኛም የተላከበትን ጉደይ ሳይፈፅም ከአሰረኞቹ ጋር አብሮ ወደ ካምፕ ተመለሰ።

---

124 ፀሀፊው ባይጠቅሰም፣ ደጃዝማች አለሜ ከነዚህ ሁለት ሰዎች ጋር አብረው ተልከዋል።

እንግዶቹ እንደታዩ፣ ወዲያውኑ ካምፑ ውስጥ ግርግር ተፈጠረ፤ ሰዎች ሰብሰብ ብለው ከነበሩበት ሁኔታ ተበተኑ፣ ወታደሮችም ቡበዛት፣ በፍጥነት፣ ሥርአት በሌለው ሁኔታ መሰባሰብ ጀመሩ፤ ነገር ግን፣ ወዲያው ደግሞ ይህ ሁሉ ግርግር ወደ ፀጥታ ተዛወረ። ይህም፣ ቆብ የደፋ፣ አዲስ ቀይ ዩኒፎርም የለበሰና ወርቃማ ማሰሪያ ጠርዝ ያለው መነፅር ያደረገ ሰው በትሩን ይዞ ብቅ ሲል ነበር።

"ይህ ሰው ማነው?" ብሎ እንዱ ጠየቀ።

"ከየትኛው ምድር ነው የመጣው?" ሌላው ደገመ።

"ኢጋድ![125] ይህ ሰው ከሰማይ ነው የወረደው።"

ፕሪዶ በርግጥም አለባበሱ ታላቅ ነበር፤ ዘናጭ ወታደራዊ አለባበስ።

ለትልቁ ጀኔራል እከብሮት ሲል ነበር እንደዚህ የለበሰው። ሰህተት ነበረ ወይ? ሚሰተር ራሰም ወደ እንግሊዝ ካምፕ በመሄድ እዛጉን አንዲገናኝ ሲነግረው፣ ያለ የሌለውን የእንግሊዝ መኮንኖች የወታደራዊ የጀግንነት ምልከቶች ደርድሮ፣ ፂሙን በጥንቃቄ ተላጭቶ፣ ከከንፈሩ በላይ ያለውን ሾጠጥ ያለ ፂሙንና ራሱን ከነበረው የሮውላንድ ሽቶ የመጨረሻዋን ጠብታ ተቀብቶ፣ ጫማዎቹ እሰኪያብለጨልጩ ድርስ በደንብ ወልውሎ፤ ዩኒፎርሙን እንድ የነጥብ ምልክት እሰከማይታይ ድረሰ ቦርሾ፤ ሳጥኑ ውሰጥ ሳይጠቀምበት የከረመውን የእይን መነፀሩን አፅድቶ፤ ከቦት ጫማው ጋር የሚታሠረውን የፈረሰ መኮልኮያ ሳይቀር ወልውሎ፤ ኮፍያውን ካደረገ በኋላ ማንም የእንግሊዝ መኮንን ሳይዝ የማይወጣውን የእጅ በትሩን ይዞ፣ ጀኔራሉን ለማየት ወረደ፤ ህይወቱሰ በዚህ ጀኔራል እጅ እይደለች?

ኮራ ብሎ ሳይጨነቅ የእይን መነፀሩን እሰተካከሎ፣ ወጣቱ ፕሪዶ፣ የያዘውን የእጅ በትር እያሽከረከረ ወደ አዛዡ ጀኔራል ድንኳን አመራ፤ ሰለ እሰረኞቹ መምጣት ሰምቶ የነበረው ጀኔራሉ ራሱ ተቀበለው።

ሉተናንቱ እራሱን ለማስተዋወቅ ጎንበሰ ብሎ እጅ ነሰቶ ሚሰተር ፕሪዶ እንደሚባል ተናገረና ወደ ቴዎድሮሰ ከተላኩት የእንግሊዝ ልውካን እባል መሆኑን ተናግሮ፣ እብሮት የመጣው የእሰር ቤት ጓዱ ደግሞ ሚሰተር ፍላድ እንደሚባል ተናገረ። ታሰሮ የከረመ ቢሆንም ከሰዎች ጋር የሚደረገውን የማንኙነት ሰነሥርአት ህግ አለመርሳቱን ማረጋገጥ ይቻላል።

ከጀኔራሉ ፊት ሰሰሆነም ትንሽ የፍርሀት ምልከት ይታይበታል። ነገር ግን የጀኔራሉ የታወቀ የመልካም አቀባበል ፀባዩ ለእንደዚህ አይነት ወጣት ሰው ፍቱን ነበረና ምልከቱም ወዲያውኑ ጠፋ። ወደ ድንኳኑ እንዲገባ ከተጋበዘ

---

[125] የመገረም አገላለፅ

በኋላ፣ አስፈላጊም ያልነበረ ግን ሰሰ እየር ጠባዩ ጥያቄ ከተጠየቀ በኋላ፣ የመጡበት ጉዳይ ተጠየቀ።።

ሉተናንቱ እንዲህ በማለት ጀመረ፤ "ከንጉሡ ወደእርስዎ ወደ ሰር ሮበርት ተልኬ ነው፤ የመጣሁትም እነዚህን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ነው።። ለምን ወደዚህ ሀገር መጣችሁ? ምንድን ነው የምትፈልጉት? እለረኞቹ ቢለቀቁ ወደ ሀገራችሁ ትመለሳላችሁ ወይ?"

"እመሰግናለሁ" አለ ሰር ሮበርት በርጋታ፤ "የኔን መልከት ስትመለስ ይዘህ ትሄዳለህ፤ ነገር ግን የትናንትናው ውጊያ ቴዎድሮስ ላይ የፈጠረውን ሁኔታ ንገረኝ።።"

ሉተናንት ፕሪዶ ሲናገር፣ ቴዎድሮስ ግዙፎቹን ዝሆኖች ግዙፍ ከሆነ ከጀርባቸው ላይ ካነበረው ጭነት ጋር ከደላንታ በኩል ሲመጡ እንዳዩ፣ ከዚያም በተጨማሪ በሰልፍ የሚመጣውን ነጭ፣ ቀይ፣ የተለያየ ቀለም ያለው ልብስ የለበሱ ሰዎችን፣ እነሱን ተከትሎ የሚመጣውን ማቋረጫ የሌለው የእንስሳቱን መስመር ጨምሮ የወታደራዊውን ትዕይንት ሲያዩ በአድናቆት እንደነበርና፣ በሕይወታቸው የሚመኙት የነበረው ነገር ሊሳካ እንደሆነ እንደተናገሩ ገለፀ።። በውጊያ ላይ ወታደሮች፣ እውነተኛ ወታደሮች እንዴት እንደሚዋጉ ማየት እንደሚችሉ ሲያስቡ በኩራት ነበር የተነቃቁት።።

ጀኔራሉና ኢጋዦቹ ከታች ከደልዳላው ሥፍራ ሲታዩ፣ ወዲያውኑ፣ የራሳቸው እለቆችና ወታደሮች ወደታች ወርደው ፈረንጆቹን እንዲወጉ እንዲፈቅዱላቸው እስጨንቀው ያዟቸው።። ትንሽ ካወላወሉ በኋላ፣ የመድፈኞች ቡድን ወደላይ ሲመጣ ተመልከተው፣ በቅሎዎቹ ላይ የተጫነው የጥይት ሳጥን ገንዘብም ያለው ስለመሰላቸው፣ "ሂዱ፣ ልጆቼ፣ ንብረቱን ማርኩና፣ ፈረንጆቹንም እባሯቸው።።" አሉ።። እራሳቸው ጦሩን ለመምራት አስበው ነበር፣ ግን በታማኝ እዛጉቻቸው ግፊት እንዳይሄዱ ተደረገ።።

ከዚያም በቅጥራቸው ሰር የነበሩትን ጀርመኖችና መድፍ ሰሪዎቹን፣ የመጀመሪያዎችን መድፎች እንዲተኩሱ ትዛዝ ሰጡ።። ከትልልቆቹ እንደኛው[126] መድፍ በመጀመሪያው ተኩስ ፈንድቶ ዙሪያውን ከበው የነበሩ ብዙ ወታደሮቻቸውን ገደለባቸው።። ያለፈቃዳቸው የሚተኩሱት ጀርመኖች መድፎቹን ሳያነጣጥሩ ሲተኩሰ ሲያዩ፣ በጣም ተናደው፣ እራሳቸው መድፎቹን ወደ ኢላማቸው እንዲያነጣጥሩ አደረጉ።። ይህ ሁሉ 200 ፓውንድ እሩሮች በተከታታይ እየተተኮሱ፣ ነገር ግን የእንግሊዝ ወታደሮች ያለማቋረጥ ወደላይ ሲመጡ ሲያዩ ጥርሣቸውን እያፋጩ፣ መሬቱን በግራቸው እየደበደቡ በንዴት

126 (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

በእንባ ተዋጡ። ንዴታቸውን የጨመረው ደግሞ ምርጥ ወታደሮቻቸው በእንግሊዞቹ መድፎች ሲወድቁ ሲያዩ ነው።

ቀጥለውም፣ ለዚህ ውድቀት እሰረኞቹ ዋጋቸውን መከፈል አለባቸው ብለው ዛቱ። ምሽቱ ሲመጣና ጦርነቱ ሲቆም መሪር ሰሜታቸውንና መንፈሳቸውን ጋብ ለማድረግ አረቄ መጠጣት ጀመሩ።

ሕሊናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት እዲሰና ከመጠን በላይ በመሆኑ፣ መርሳት የሚችሉበት ደረጃም አልነበረም። ሰሰት ጊዜ ራሳቸውን ለማጥፋት ሞከረው በረዳቶቻቸው ብርታት በጥበቃ ሊያሰጥሏቸው ችለዋል። በጥልቅ ጭንቀትም የምርጥ ጀኔራሎቻቸውን ሰም ይጠራሉ፤ ፊታውራሪ ጉበርዬ[127]፣ ደጃች ደረሰ፤ ደጃች ወርቁ፤ ረዳቶቻቸው ምንም ቃልም መተንፈሰ አልቻሉም፤ ዝም ብለው ብቻ፣ እንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ገናና የነበሩት ንጉሥ ያሉበትን የሚያሳዝን ሁኔታ በመመልከት ተወሰነዋል።

ከዛም፣ በመበሳጨት ጀግና የወንድ ወታደሮች ነበሩኝ፣ እሁን የቀሩት ሴቶች ብቻ ናቸው ይላሉ። የአልቂቱን ውጊያ ባሰቡ ቁጥር ሰውነታቸውን ያንቀጠቀጣቸዋል። ናፒየር እሰኪገርመው ድረሰ ፍላድና ፕሩዶ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የሆነውን ደጋግመው ነገሩት።

እፍታም ዝም ብለው፣ እይናቸውን አፍጥጠው፣ የሚያሰቅቀውን ባሏቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች የሚያሰሙትን ለቅሶ ይሰማሉ።

በቁጣ፣ "የእነዚህን ሴቶች ለቅሶ እሰቁሙልኝ" ይላሉ።[128]

የደረሰው ሽንፈት፣ ድንጉጮ፣ ከባድና ሰፊ በመሆኑ ጥልቀቱን በልከ ገና ማመዛዘን አልቻሉም።

"ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጡብንን ፈረንጆችን ሄዱና ግደሉ።" ብለው ወታደሮቻቸው ላይ ጮሁባቸው።

"የለም፣" ሽበቶ እማካሪያቸው ነበር፣ "ያቆዩዋቸው፣ ሁለቱን ወደ እንግሊዙ ጄኔራል ይላኩና የሚለውን ይሰሙ"[129]

"እሃ፣ እዎ፣" እሉ በሃሳብ ተውጠው። "ያ ይሻላል። ሱልጣን ራሳምን ወደኔ አምጡልኝ" እሉ።

ይህ የሆነው አሮጌ ላይ በደረሰው አልቂት ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ነበር። የሰቅለት ቀን ነበር። ራሳም፣ ከዚህ በፊት እንደገለጥኩት፣ የንጉሡን ሰሜት ማለስለስ የሚችል ሰው ነበር።

---

127 ፊታውራሪ ጉበርዬ (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

128 (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

129 (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

ራሳም ከቦታው ደረሰና፣ ለንጉሡ በሚገባ መንገድ እጅ ነሳ። ሰላምታው ራሱን ዝቅ ባደረገ ሰሜት ነው የቀረበው። በንፁህ ልብ በተሞላ ተሰፋ ያቀረበው ንግግር፣ "ገናናው ንጉሥ፣" "የአለም ገዥ፣" "የህዝቡ ታዳጊ"፣ "ሀያሉ ጌታ፣ የከርስትና ሀይማኖት ጠባቂ" አድሜዎን ያርዝመው።

ከዚህ ቀደም የተሰማቸውን ሰሜት አንደምንም አፍነው፣ ንጉሳዊነት በተሞላበት ግርማ ሞገሰ ከተቀመጡበት በመነሳት፣ በራሳቸው ሀር የተሸፈነ መቀመጫ ላይ አንዲቀመጥ ጋበዙት። አጠገቡም፣ ጠጅ፣ ጠላና አረቄ ነበር። በተዝናና ሁኔታና በትህትና፣ ለንጉሡ ጤንነት፣ ራሳም የቀረበለትን መጠጥ ጠጣ።

ራሳምን የላከው ሀገር ሰዎች በጀግንነት ለመዋጋታቸው አመስግነው፣ ቴዎድሮስ፣ ራሳምን፣ "ምን ላድርግ?" ብለው ጠየቁት።

ራሳም የተለያዩ ሀሳቦችን ቢደረድርም፣ ንጉሱ፣ አንዳቸውንም ለማድረግ አእምሯቸው አልፈቀደም። ነገር ግን፣ ከአሰረኞች ሁለቱን ልከ፣ የፈረንጆቹ አዛዥ ምን እንዳቀደ ማረጋገጥ ይሻላል ብሰው አሰቡ።

ራሳም በሀሳቡ ተሰማምቶ፣ ሚሰተር ፍላድና ሉተናንት ፕሩዶ የሚታመኑ ሰለሆኑ አነሱ ቢላኩ የሚሻል ነው ብሎ ሃሳብ አቀረበ።

"መልካም፣" አሉ ቴዎድሮስ፣ በከፍተኛ ሀኔታ ተረጋግተው፣ "የኔን ምሰጋናና መልከት ለጀኔራሉ እንዲያደርሱ አንዲዘጋጁ ንገራቸው።" አሉ።

ከዚያም በወንድማማችነት ተቃቀፍው፣ ከመለያየታቸው በፊት ብዙ የመልካም ሰሜት መግለጫ ቃላት ተለዋወጡ።

ይህን ሁሉ የሰማሁት ከሌሎቹ አስረኞች ነበር።

ሉተናንት ፕሩዶና ሚሰተር ፍላድ ከጀኔራሉ ጋር ምሳ በሉ። በዚህ ጊዜም ከላይ የተነገረው ሁኔታ ለጀኔራሉና ለጥቂት ረዳቶቹ ተደጋግሞ ተነገረ። የቀረበው ምግብ፣ አነዚህ ሁለቱ አሰረኞች አንዳደረጉት አይነት አንዲዚህ ሆኖ ተጣጥሞ ተበልቶ አያውቅም።

ሉተናንት ፕሩዶ ከጦሩ መኮንኖች ጋር ከተነጋገረ በኋላ፣ ሁለቱም መልከተኞች ለቴዎድሮስ ሰለሚወስዱት መልከት መመሪያ ተሰጣቸው። "በኔ ሰም፣" አንዲህ ብላችሁ ንገሩ አለ ሰር ሮበርት። "የምጠይቀው፣ አሰረኞቹ ከነንብረታቸው በአሰቸኳይ አንዲፈቱ፤ ራሳቸው አጅ አንዲሰጡና፣ የሰላሴ፣ የፋላና የመቅደላ ምሽጎችን ከውሰጡ ካለው ንብረት ጋር አንዲያሰረክቡ፤ ይህንን ካደረጉ የሚገባቸውን ክብር አንድምንሰጣቸው ላረጋግጥላቸው እንደምችል ነው።"

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ሁለቱ አሰረኞች ከቴዎድሮስ ጋር ከቆዩ በኋላ ተመልሰው መጡ። ቴዎድሮስ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ከናፒየር በተላከው

መልከት ምክንያት በቁጣ ገንፍለው ነበር። በመልከታቸውም፣ ንጉሥ አንደመሆናቸው መጠን፣ የአንግሊዙ ጀኔራል፣ ሌላ የተሻለ መደራደሪያ አንደሚሰጣቸው ፀሎታቸው አንደሆነ ገልፀው፣ ለሴት[130] ለሚያገለግል፣ ለማንም አለቃ አጃቸውን እንደማይለጡ አስታወቁ። "አለዚያ" አሉ ቴዎድሮስ በላኩት መልከት፣ "እጄን ከምሰጥ እስከ ሞቴ ድረስ አዋጋለሁ። የመጣችሁበት ምክንያት የሆኑት ሰዎች ካገኛችሁ አይበቃችሁም ወይ፣ ለምን እኔን በሰላም አተዉኝም?"

ሰዎቹም፣ ወደ አስራ አንድ ሰአት አካባቢ፣ የመጀመሪያውን አይኑት መልስ ያለበትን መልከት አንዲያደርሱ ተላኩ። "ለአንግሊዝ ንግሥት ያሰምንም ቅድሚያ ሁኔታ አጅምን አንዲሠጡ፣ የሚገባዎትን ክብር አንደምንሰጥዎ አይጠራጠሩ።" የሚል ነበር።

መላው የአንግሊዝ ሠራዊት አነዚህን መልከተኞች በጣም በሃዘኔታና በርህራሄ መንፈስ ነው ያያቸው። ቴዎድሮስ፣ በቁጣና በቁም በቀል በአናታቸው ላይ ሊያወርዱባቸው የሚችሉትን አስፈሪ ጥፋት አስቀድሞ በማሰብም ነበር።

ፍላድና ፕሩዶ ሁለተኛውን የተሻለ የድርድር ጥያቄ ይዘው ወደ አንግሊዞች ካምፕ ሲመለሱ፣ የራሳም፣ የአዋቂነት መንፈስ፣ ዙሪያውን ከነበረው አጠራጣሪ የጭጋግ ሽፋን ዘልቆ መታየት ጀመረ።

"ጃንሆይ! ይመኑኝ። ሁሉንም አስረኞች ወደ አንግሊዝ ካምፕ ይላኩ። አኔ ራሴ፣ የአንግሊዙ ጀኔራል ወደ እገሩ አንዲመለስ ዋስትና አለጣለሁ።"

አንደኔ ግል አመለካከት፣ ራሳም በተናገረው ነገር ከልቡ አምኖበት ነው። ምክንያቱም፣ ከሚገባው በላይ፣ ለዘመቻው አሱ ብቻ ዋነኛ ምክንያት አንደሆነ አድርጎ ነው ያሰበው። የሌሎቹ አስረኞች መፈታትና፣ ቴዎድሮስን የመቅጣቱ ሁኔታ በሁለተኛ ደረጃ አንደሆነ አድርጎ ነው የገመተው። አንግዲህ፣ ንጉሠ ነገስቱም ቢሆን፣ በራሳም በመተማመን፣ ከከሩሴደሩ አዛዥ ጀኔራል ጋር ሊያስማማቸው የሚችል ተፅዕኖና ግፊት ማድረግ አንደሚችል አምነው ተቀበሉ[131]። ከዛም፣ ሁሉንም አስረኞች ወዲያውኑ አንዲሰበሰቡ፣ ያላቸውን ማንኛውንም ንብረት ይዘው በምሽጉ ዋና በር በኩል፣ ወደ ቃፊር በር እንዲሄዱ አንዲያደርግ ትዛዝ ሰጡት። ሁሉም ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ስዎቹን ለመሰናበት ወደ በሩ አንደሚመጡ ነገሩት።

---

130 ንግሥት ቪክቶሪያን በመጥቀስ

131 ሌሎች ፀሀፊዎችም በዚህ ጉዳይ፣ ንጉሡ ራሳምን ወሳኝ ሰው አድርገው አንደተመለከቱት ነው የሚገልፁት። የሚነሳው ጥያቄ፣ ራሳም በብልጠቱ ንጉሡን አታሏል ወይ? ነው።

በማይታመን ፍጥነት፣ እሰረኞቹ ባንድ ላይ ተሰብሰበው፣ የራሳቸውን አገልጋዮች፣ የእገልጋዮቻቸውን እገልጋዮችና ባሮቻቸውን ይዘው ቃፊር በር ላይ ተሰበሰቡ።።

ይህ የተሰያዩ ሰዎች ሰብስብ እንግዳ የሆነ ግርግር ሁኔታ ነበረው።። የነጭና የጥቁር ፊት አንድ ላይ ተደባልቋል።። በፍጥነት ለመውጣት በነበራቸው ጉጉት፣ እንደ ባቢሎን ግንብ ሥራ፣ በዚህ ግርግር መህል የተለያየ ቋንቋ ሲነገር ይሰማል።። ምንም አይነት ሥርአትም አልነበረም።። በራሳም የተነገራቸው፣ መቅደላን፣ ከደም መፍሰስ ጋር ከተያያዘው ከነአሰቃቂ ትዝታው ለዘላለም ለቀው ለመሄድ በግማሽ ሰአት ውስጥ እንዲዘጋጁ ነበር።። ወዲያውኑ፣ ሁሉም የትም ይሁን ብቻ ወደየቤታቸው መሄዳቸው ነው የታያቸው።።

ብዙም ሳይጠብቁ፣ ቴዎድሮስ፣ የሚኮሩበትን እልባሳት ለበሰው ከዋና ዋና ሰዎቻቸው ጋር በመሆን ወደ በሩ መጡ።። ከእንድ ሰው በለተቀር ሁሉም እሰረኞች እጅ ነሱ።። ንጉሡም፣ በሩ እንዲከፈት ትዛዝ ሰጡና፣ እሰረኞቹ በፊታቸው ሲያልፉ እጅ እየነሱ በበሩ ወጥተው መሄደ ጀመሩ።።

"ካሜሮን፣ ደህና ሁን።።" ቴዎድሮሰ ቆንሰላውን ነበር ያናገሩት።። "ወዳጆች እንደሆን ነው የተለያየነው፣ ተሰፋ አደርጋለሁ?" እሱ።።

ለተሰጠው የሰንበት ሰላምታ፣ መልሱን በትህትናና በአከብሮት መመለሱ በቆንሰላው እንደበት ላይ ነው ያለው።። በንጉሡ ላይ የሚመጣውን ውድቀት በማወቁ፣ ለግሸው የፀፀት ህዘኔታ እንዲሰማው አድርጎታል።። ነገር ግን ቃላቶቹ በሰርእት ወይም ለስለሰ ባሰ እንደበት መውጣት አልቻሉም።። እንደ ምናብ ፀሬዳም፣ በከንቱ ያሳለፈው የህይወት ጊዜው ፊት ለፊቱ ታየው።። ከዚህ በፊት የነበረበትን ሁኔታም ሲያሰታውሰ፣ ግራጫ መልከ ባለው በቆሸሸ ብርድ ልብሰ ተጠቅሎ ከእሰር ቤት ግድግዳ ጋር መታሰሩ ነበር፤ ጭካኔ የተሞላበት ሰቆቃ፣ ሰንበር የሚያወጡት እለንጋዎች፣ ለረዥም ጊዜ በሱ ላይ ሊደርስ የሚችለው ዕጣ ፈንታው፣ እህ፣ ያሳለፋቸው የረዥም ቀናቶች የእእምሮ ሰቃይና ፍፀም እንግልት፣ ቀኖቹ ተራ በተራ ሲያልፉ የሚታወሱት፣ ማቋረጫ የለሌው ቅጣት፣ በግልፅም፣ ወላዋይ በሆነና ባልተዘጋጀው በራሱ መንግሥት ጥረት አለመደረጉ ሁሉ ነበሩ።። እናም ለዚህ ሳከሰናዊ ሰው ምን እይነት መንፈሰ ቢኖረው ነው ይህንን እምባነን ሰው ይቅር የሚለውሰ።። ነገር ግን የነበረበት ሁኔታ በጣም አደገኛ ሰለሆነ፣ የነበረው ፖሊሲ፣ የቴዎድሮሰን ሰንብት አንዲቀበል አድርጎታል።።

"ደህና ይሁኑ ጃንሆይ።።" በማለት በክብር ሰላምታውን በመመሰሰ ቆንሰላው ካሜሮን አልፎ ሄደ።።

"ደህን ሁን፣ አቶ ኮከቤ(ስተርን)። ለበደልኩህ ሁሉ ይቅርታ አድርግልኝ።"

የከርሰትና እምነቱ ይቅርታ አንዲያደርግ ገፋፍቶት ይሆን፣ ወይም ደግሞ ቴዎድሮሰን ፍራቻ ይሆን፣ ሳይታወቅ፣ አውነታው ግን፣ ሚሰተር ሰተርን፣ አጅ

በመንሳት "ደህና ይሁኑ ጃንሆይ።" አለ።

"አሃ፣ ከረንሰ፣ አንተ ነህ? ደህና ሁን፤ ከዚህ በኋላ አላይህም።"

ወጣቱ ከረንሰ፣ በወጣት ሰሜቱ፣ የተበደለው ሁሉ ሰሜት ገና በአእምሮው ትኩስ አደለ፣ ወደ ቴዎድሮሰ ሄዶ አጃቸውን ይዞ፣ ራሱን ደፍቶ አጅ ነሰቶ፣ "ደህና ይሁኑ ጃንሆይ፣ መልካሙን እመኝልዎታለሁ።" አለ።

"አሃ፣ ሱልጣን ራሳም ደህና ሁን። ከእንግሊዙ እለቃ እንድታሰታርቀኝ በአንተ አተማመናለሁ። ነገ ጥሩ ወሬ ይዘህ ወደኔ እንደምትመጣ አርግጠኛ ሁን።"

"በርግጥ፣ ጃንሆይ። ነገ ጥሩ ወሬ ይገ አንደምመሰስ አርግጠኛ ነኝ። ሰላም ይደሩ፣ የኔ ንጉሥ!" ይህን ብሎ፣ በመግቢያው በር መከላከያ አጥሩን አልፎ የታችኛውን ማማ አልፎ ሄደ። አራሱና ሌሎቹም፣ ነፃና ጤናማ አየር ተነፈሱ። ከመቅደላ፣ በሰላምን በኩል፣ ሰላሴን ዞሮ፣ ፋላን ተጠግቶ በመውረድ፤ ከዛም ረዘም ያለ ወጣ ገባ ወርደው የአንግሊዞች ካምፕን አልም ብልጭ የሚሉ መብራቶች ሲያዩ የጋለ ተሰፋ በውሰጣቸው ተነሳሳ፣ ግልፅ ባለው የሚታ አየር፣ ሁሉም በአንድነት ከጭንቀት በተረፈው ልባቸው ምሰጋና አቀረቡ።

ዜናው በጦሩ መህል ወዲያው በመሠራጨቱ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች አሰረኞቹን ለመቀበል ወደ ዋናው አዛዥ ጽ/ቤት አየተጣደፉ ሄዱ።

ከምሽቱ አንድ ሰአት ሲሆን፣ አየወረደ የሚመጣው የሰዎች ሰልፍ የመጀመሪያው ክፍል ካምፕ ውስጥ ደርሰ፣ የጠቅላይ አዛዡ ድንኳን ፊትለፊት ቆመ።

ሳንጃ የያዙ ጠባቂ ወታደሮች ተመልካቾቹን በመግፋት፣ ለመንገደኞቹ ከፍተት ቦታ ፈጠሩ። ሰዎቹ እንደደረሱም፣ ደከም ያለ የደስታ ሰሜት ድምፅ (ቺርሰ) አንደመጀመር አለና ወዲያውኑ ግልፅ ባልሆነ ጉርምርምታ ተተካ። ቺርሱን የጀመረው ለውም የሚኮተለው ለው አለመኖሩን ሲያውቅ አቆመ።

ሴቶችና ልጆች ነበሩበት፣ የህፃን ልጅ ቀጭን ድምፅ ሲሰማ፣ የተሟሟቀ ቺርሰ አንደማለማት ፈርጠም ያሉት ወታደሮች መሳቅ ጀመሩ። በርግጥ ይሰቁ ጀመር።

በርግጥ፣ አንድ የማይሆን ነገር መኖር አለበት። ይህ፣ አሰረኞቹ ከመለቀቃቸው በፊት የጠበቁት አቀባበል አልነበረም፤ ተሰፋ ያደረጉበት መልካም ሁኔታም አልመሰለም።

እልነበረም፣ አኔ ያየሁትን ልናዘዝ። አኔም የገመትኩት፣ ሁሉም የሠራዊቱ አባላት እንደ አንድ ሰው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሁራ በማለትና በጠራሰና አንድ ላይ በማጋጨት ድምፅ በሚሰጡት ሲምባሎች ጩህት የሚታጀቡ፤ ሁሉም በደሰታ የሚቅነዘነዙ፤ አሰረኞቹም ቢሆን በደሰታ የሚያለቅሱ፤ በምሲጋና ሮጠው የሰር ሮበርት ጉልበት ሰር ወድቀው አግሮቹን አቅፈው እጆቹን የሚሰሙ፤ ሰር ሮበርትም አጋጣሚውን በመጠቀም ሰለ መልካም አመራርና ውጤቱ ንግግር የሚያደርግና፤ ከዛም እጆቹን ወደላይ አድርጎ ፊቱን ቀና አድርጎ ነፃ ለወጡትና ለነፃ አውጭዎቹ የአግዚአብሔርን በረከት የሚጠይቅ ነበር። አንግሊዛውያን ይህን አይነት ነገር ከዚህ በፊት አድርገዋል፤ ነገር ግን፣ እንግዳ በሆነ ሁኔታ አዚህ ቦታ ግን አላደረጉትም።

መኮንኖቹ የአይን መነፀራቸውን ማድረግ ሲጀምረሩ፤ ላንዳፍታ እንኳን ሁኔታውን ለተመለከተ ሰው፣ ዘጠና ዘጠኝ የሚያንፀባርቁ መስታውቶች፣ በዘጠና ዘጠኝ ሰዎች አይን ላይ ተሰከተው፣ ዘጠና ዘጠኝ የሚሆኑ አዋቂ ለዎች፣ ኮለተር ብለው አሰረኞቹን ሊመለከቱ በማየት ምስክርነተ ይሰጥ ነበር። መኮንኖቹ የአሰረኞቹን ሁኔታ አጥብቀው በማየት፣ የለበሱትን ልብሰ ቁልፍ፣ ረጋ ብለው ሰለሚታዩት ህፃናቶቹና ሰለ ሴቶች አሰተያየት ይሰጣሉ፤ በመጨረሻም ያለምንም መግረም የሴቶችን ዕድሜም እሰተዋሉ።

ባጠቃላይ፣ ምርኮኞቹ፣ ለኛ ከተነገረንና ከጠበቅነው በላይ በጣም የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ከሶሰት ሰዎች በሰተቀር፣ ሌሎቹ በሙሉ ደህና ይመስላሉ። ወጣቱ ከረንሰ፣ የካሜሮን አገልጋይ የሆነው የአየርላንደ ተወላጁ መከኤልቪና የቴዎድሮሰ መህንዲሰ የነበረው መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሽራይበር ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ገርጠት ብለው፣ አንደ ሮማውያን ረዘም ያለ አጀ ጠባብ የመሰለ ለብሰው፣ ራሳቸው የሰሩትን የሰሌን ባርኔጣ አድርገዋል። የአየርላንዱ ልጅ፣ ማከኤልቪ፣ ከሚገባው በላይ ደሰተኛና ፍንድቅ ያለ ነበር።

መቅደላን ለመልቀቅ በነበረው ችኮላ፣ ወይዘሮ ፍላድ በራሳም ተረሰታ ወደኋላ ቀርታለች፤ በመጠኑም ቢሆን ህመምተኛ ነበረች።

ሚሰተር ፍላድ፣ ድፍን ባለው ሌሊት ልጆቹና ባለቤቱን ለማምጣት ወደ መቅደላ መመለሰ ነበረበት። ፍላድና ፕሩዶ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ መቅደላ ሲመለሱም፣ እሰረኞቹ፣ በፋላ ቁልቁለቱን ይዘው ሲመጡ ተላልፈዋል።

አሰረኞቹ እንግዲህ አነዚህ ናቸው፤ ጠቅላላ ቁጥራቸው ስልሳ አንድ ነበሩ። ለነዚህ ነው አንግዲህ ዘመቻው የተካሄደው። አነዚህ ነበሩ አንግዲህ

ሲልኩ በነበሩት አሳዛኝ ደብዳቤ የእንግሊዝ ክርስቲያኖችን እንባ ሲያሰፈሰሱ የነበሩት፡፡ እንደ ደብዳቤያቸው አገላለጥ፣ ሁላችንም ሊሞቱ የተቃረቡ ናቸው ብለን እንድናምን አድርገውናል፡፡ ይህም፣ በየቀኑ ይገረፉ እንደነበር፣ ሁልጊዜ በእግር ብረት እንደታሰሩ፣ ርቃናቸውን፣ እካላታቸው ላይ ብዛት ያለው ቁሰልና ጠባሳ ያለበት እንደሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ሲታዩ፣ በደንብ የለበሱ፣ በተለይ እራቱማ የአይን መነፀር ያደረጉ ነበሩ፡፡ አሰገራሚ!

በእሳት የተግለበለበው፣ ለብዙ እቢሲኒያውያን ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነበት የሰቅለት ቀን አልፎ የሚቀጥለው ቀን ነጋ፡፡

ክታመመት ወይዘሮ ፍላድና ባርዴል በስተቀር፣ ሁሉም እስረኞች በኛ ካምፕ ውሰጥ ነበሩ፡፡ የነሱ፣ ጥቁር፣ ነጭና ቀይ ድንኳኖቻቻው ከሠራዊቱ ድንኳኖች በቁጥር ይበልጡ ነበር፡፡ እንደ ዝርዝሩ ከሆነ፣ ሰልሳ አንድ ሰዎች መኖር ነበረባቸው፤ በቦታው እርባ ሰምንት ድንኳኖች ነበሩ፡፡

ከነዚህ እሰረኞች ጋራ፣ 187 እገልጋዮችና 323 እንሰሶች ነበሩ፡፡ ወይዘሮ ፍላድ ክጠዋቱ 3 ሰእት ሲሆን በሰላም ደረሰች፡፡ በመቅደላ የቀረ እንድ ብቸኛ ሰው፣ እርቲሰቱና ፕሮፌሰሩ ባርደል ነበር፤ እሱም ትኩሳት ያለበት በሽታ ይዞት ነበር፡፡ መታወሰ ያለበት፣ ይህ ሰው ነበር እንግዲህ የሚሲዮናውያኑን ደብዳቤ ለቴዎድሮስ በማሰተርነም፣ ንጉሡን የሚሰድብ ፅሁፍ ፅፋችኋል ተብለው እንዲገረፉ እስደረገ ተብሎ የወቀለው፡፡ ሰልሳ አንድ ሰዎች ናቸው ብዬ ነበር፡፡ ሰልሳ ሁለተኛዋ ደግሞ፣ እንግሊዝ ካምፐ ከደረሱ በኋላ በነጋታው ክጠዋቱ እራት ሰእት ላይ የተወለደችው ቴዎዶራ ሞሪተዝ ነበረች፡፡ ሰሚም የወጣላት በንጉሡ በቴዎድሮስ ሰም ነው[132]፡፡

የፖለቲካ ፀሐፊው ቲዊዲ፣ የእሰረኞቹንና የተክታዮቻቸውን ሰም ዝርዝር ሲያነብ ከሚገባው በላይ ነበር የተደነቀው፤ በተለይም ከሰራተኞቹ እንድ ሶስተኛ የሚሆኑት የአቢሲኒያ ሌቶች መሆናቸውን ሲያውቅ የበለጠ ነበር የተገረመው፡፡

ይህን ዝርዝር ውነታ በሰሙ ሰዎች በሙሉ የሚያንሸማሽ ጥላቻ ሰሜት ነው የተፈጠረው፡፡ ከእሰረኞቹ የተፃፉት እሳዛኝ ደብደቤዎች መታመን የማይችሉ ለመሆናቸው መረጃ የሚሆኑ ሌሎች አሰገራሚ ውነታዎች መውጣት ጀመሩ፡፡

---

[132] ልጃቸውን የንጉሡን ሥም ሲሰጡ፣ ንጉሡን ያን ያህል ይጠሉ ነበር ወይ?



የተለቀቁት አስረኞች ከቤተሰብና ሠራተኞቻቸው ጋር
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

አንግዲህ፣ ሥጋ፣ ዳቦ፣ ማር፣ ወተት፣ ቤት፣ አትክልት፣ ወይን ወዘተ ካላቸው፣ ሌላ ምን ተጨማሪ ፈለገው ነው ብለን ተገረምን::[133]

መቅደላን ከተቆጣጠርን ጀምሮ በሁለት ሚይሎች ርቀት ውስጥ ምንም አይነት ውሀ ሊገኝ አልተቻለም:: በሁለተኛው ቀን የሚመጣልን ውሃ ሳይደርስ ቀረ፤ የማመላሻው መንገድ በሚሰርቁ አሮሞዎች ሰለተጥለቀለቀ፣ በቅሎዎቻችን በተደጋጋሚ በነዚህ አጭበርባሪ ሰዎች ይመሰዱብን ነበር:: የሚቀርበው ውሃ ለነበሩን አንሰሳት በሙሉ፣ አሰር ሺ፣ ለሚሆኑት በቂ አለመሆኑ ሲታወቅ፣ ሁሉም አንሰሳት ሰባት ሚይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ በሽሎ ወንዝ አንዲወርዱ ተደረገ:: 500 የሚሆኑት ለሠራዊቱ ከወንዙ ውሃ አንዲያመላልሱ ተመደቡ::

የሚያዝናኑ ነገሮች አንደ አልኮል፣ ሊጃራ፣ ትምባሆ፣ ሰኳር፣ ሻይ፣ ቡና፣ ሩዝ የመሳሰሉት አንዱም አንኳን የለንም፤ ምክንያቱም ሁሉንም ከነበረንበት ካምፕ አጠገብ ጥለን ነው የመጣነው::

አኩለ ቀን ላይ፣ የፋሲካን በአል ምክንያት በማድረግ፣ ቴዎድሮስ፣ አንድ ሺ ሰንጋ ከ500 በጎች ጋር ለናፒየር ሲልኩ፣ የብሪታንያ ወታደሮቹ አሰኪጠግቡ ድረስ መብላት ነበረባቸው፤ እኛስ ብንሆን ከርስቲያን አልነበርንም?

ሰር ሮበርት ግን፣ የዚህን መልከት መምጣት ወዲያውኑ እንደለማ፣ አንድ መኮንን ወደመቅደላ ልኮ፣ ንጉሡ ራሳቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና የመቅደላ ምሽግን ለእንግሊዝ ንግሰት አሰካላሰረከቡ ድረስ ከንጉሡ ምንም አይነት ሥጦታ ለመቀበል የሚያሰበው ነገር እለመሆኑን ይገልፃል:: [134]

ከቀትር በኋላ ከነበሩት አጣናዎች ብዙ የግምብ መውጫ መሰላሎች መሰራት ተጀመረ:: የባሩድ ዱቄቶች፣ ለአጅ ቦምቦች አገልግሎት አንዲውሉ ተዘጋጁ::

አርባ ሁለት የሚሆኑት ዝሆኖች አርምሰትሮንግ የተባሉትን ከባድ መሳሪያዎች ወደ ካምፕ ካመጡ በኋላ፣ ማምሻውኑ መሳሪያዎችን፣ በፋላና የኛን ካምፕ የሚለያየው ጉብታ ላይ አደረሱ:: በቅሎዎችም ቢሆን፣ ከሁለት

---

133 ይህ ሁኔታ ሊተኮርበት የሚገባ ነገር ነው:: ቀደም ባሉ ክፍሎች፣ አስረኞቹ በየቀኑ አንደሚደበደቡ አንደሚሰቃዩ ነበር የሚፅፉት። የነሱ ፅሁፍም ነው፡ በውጫው አለም ለንጉሡ ስም መከፋት ዋነኛ ምክንያት የነበረው:: ሲፈቱ ግን፣ ታዛቢዎች አንዳዩት ሀሰተኞች ነበሩ:: በዚህ ዘገባ የአሜሪካው ጋዜጠኛ ፅሁፍ በመጠኑም ቢሆን ከወገንተኛነት ራቅ ያለ ያደርገዋል::

134 አፄ ቴዎድሮስ ለጄኔራል ናፒየር የላኩት (በምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች)

ቀን መኖ ጋር ከታች ከበሽሎ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ በነጋታው ሲደረግ በታቀደው የመቅደላ ጥቃት ዝግጁ እንዲሆኑም ነው፡፡ ጥቃቱ የታሰበው አኩለ ቀን ላይ ነው፡፡

ስር ሮበርት ናፒየር፣ ከመተኛቱ በፊት፣ ችግሩን በወዳጅነት ለመፍታት በጣም እነሉተኛ ዕድል ባለበት ሁኔታ፣ የከፋ ሰው ላለመሆን ሲል፣ በተወላጆች በኩል እንደገና የመጨረሻ የእጅ ስጥ መልክት አስተላሰፈ፡፡ በደብዳቤው ሲገልጽ፣ መከራከሩ እጉልና ውጤት የሌለው መሆኑን ጠቅሰ፣ ቴዎድሮስ እጃቸውን ቢሰጡ በክበሬታ ሊያዙ እንደሚችሉ ቃል ገብቷል፡፡ በአዋጁ መሰረትም፣ ቴዎድሮስ በነጋታው ጥዋት ሶስት ሰአት ድረስ የፈቃደኝነት መልስ ካልመለሱ መቅደላን ለማጥቃት እንደሚንቀሳቀስ ይገልጣል፡፡

የምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች

ቁጥር 126፣ የፈነዳው መድፍ ቴዎድሮስ የሚባለው ነበር። ትልቁ ግን ሴባስቶፖል ነበር። የሰየሙት ቴዎድሮስ ናቸው። በዚህም፣ በክሬሚያ ጦርነት የነበራቸውን አትኩሮት ያመለክታል። ሩሲያዎች፣ ከሬሚያን ለመከላከል፣ በዋናው ከተማ፣ በሴባስቶፖል መሸገው ተቀምጠው ነበር። እንግሊዞች፣ ቱርኮችና ፈረንሳዮቹ ተባብረው ሩሲያኖቹን መውጋታቸው፣ ከራሳቸው ሁኔታ ጋር የመመሳሰል ባህሪ ሊኖረው ይችላል። በተጨማሪም፣ የጦርነቱ ዋና ምክንያት፣ በቱርክ ግዛት ሰር ለነበሩ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት፣ ሩሲያውያን ህላፊነቱ የኛ መሆን አለበት ስላሉም ነው። ለእፄ ቴዎድሮስ፣ ቱርኮች፣ የቆዩ ጠላቶቻቸው ሊሆኑ፣ እንግሊዞቹ ደግሞ አዲሶቹ ናቸው። ፈረንሳዮችም ቢሆን፣ ደጃች ንጉሴን(እገው ንጉሤ) አያባበሉ፣ ቴዎድሮስ ላይ እንዲሸፍት አድርገው ነበር። እንደተጠቀሰው፣ አሳቸው ፊት የሚጎናተሉት ፈረንሳዮችና እንግሊዞች፣ ግንባር መፍጠራቸው አስገርሚቸዋል።

ቁጥር 127፣ ፈታውራሪ ገብርዬ የቀዳሚው ጦር አዛዥ ነበር፤ በአሮጌው ጦርነት፣ ሙሉ የክብር ልብሱን ለብሶ ሲዋጋ ስለነበር ንጉሡ ይሆናል በሚል ግምት ብዙ ጥይት ነው ያረፈበት። የሱን አስከሬን ለማንሳት የሞከሩ ሌሎች አለቆችም አጠገቡ ወደቀዋል። የገብርዬ አስከሬን ሊላከ፣ ቴዎድሮስ ናፒየርን በጣም ነው ያመሰገኑት። ሆኖም፣ አስከሬኑ የተላከው በደግነት ሳይሆን ተስፋ ለማስቆረጥ የነበረ ይመስላል። ገብርዬን መጀመሪያ በጥይት የመታው ካፒቴን ስፒዲ ነው ይባላል። የኋላ ኋላ፣ ስፒዲ፣ የገብርዬን ለምድ፣ ጋሻና ጦር የግሉ አድርጓል፤ በምሰሶች ላይ ለብሶ የሚታየውም የገብርዬን የጦር ልብስ እንደለበሰ ነው።

ቁጥር 128፣ አፄ ቴዎድሮስ ገና ሥልጣን እንደያዙ ያገዱት ነገር፣ በከምፓቸው ውስጥ በጩኸት ማልቀስን ነው። ስለዚህ ያሁኑ ቁጣ አዲስ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ሊሞት፣ በሀዘን ስም ሰውነትን መጉዳትና ፀጉር መላጨት የአረመኔ ባህል ነው ብለው ስለሚያምኑ በአዋጅ ከልከለው ነበር። በመቅደላ፣ የአቶ ሳሙኤል ሚስት አባቷ ሊሞቱ ፀጉሬን እላጫለሁ ብላ ባልየው ከልከሏት ነበር።

ቁጥር 129፣ እዚህ ላይ ሌሎች መረጃዎች የሚሉት፣ ቴዎድሮስ አለቆቻቸውን ሰብስበው እዝህን አስረኞች ምን እናድርጋቸው ሲሉ፣ አለቆቹ እንግደላቸው ሊሉ፣ አሳቸው በቁጣ፣ ያወም ሃሳብ ያቀረበውን ሰው ሰደብው፣ አስረኞቹ እንዳይገደሉ ተወስኗል። ይህንን የሰማው፣ ቫልድማየር ነበር። ይህ እንግዲህ ከዚህ ቀን በፊት የተደረገ ሊሆን ይችላል። የውጭ ፀሐፊዎች ስዎቹን፣ ምርኮኞች ይሏቸዋል። አንደ አውነቱ ከሆነ ግን አስረኞች ናቸው።

ቁጥር 134፣ አፄ ቴዎድሮስ ለጀኔራል ናፒየር የላኩት የመጨረሻ ደብዳቤ ስለ ንጉሡ ብዙ መግለፅ የሚያስችል በመሆኑ፣ እንደ ሌሎች ሁሉ ደብዳቤውን እንዳለ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ አስፍሬዋለሁ። መስመር በመስመር ላነበበ ሰው፣ ንጉሡ ፈሪህ

አማዚአብሔር እንደነበራቸው፣ ምኞታቸውንና፣ በህገራቸው ሰዎች ተሰፋ የቆረጡ መሆኑን መረዳት ይችላል። በነበራቸው ኩራት ምክንያት ናፒየርን በመናቅ የደብዳቤው አድራሻ ላይ ስሙን እንኳን አላሰገቡትም ነበር። ይህ ደብዳቤ ማህተም እንኳን የለበትም። ነገር ግን በአፄ ቴዎድሮስ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ሁሉ በይዘቱ ይህ በጣም ገላጭ ነው።

የአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በሶስትነት ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሳ፤ መቸም ያገሬ ሰዎች በአማዚአብሔር ሀይል እኔ ካልወረድኩላችሁ ሸሽታችሁን እትተውም። ክርስቲያኑ ሁሉ ጉልበት አሰኝ መሰሎኝ ካረመኔ አገር አግብቸው፣ ወንድ የሌላት ቆንጆ አሰች፤ ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች፤ ትላንትናም የሞተባት ትኖራለች፤ ሸማግሌ፣ ልጅ የሌለው፣ ባልቴት፣ ልጅ የሌላት እኔ የምጠውራቸው ብዙ በከተማየ አሉ። አማዚአብሔር ከሠጣችሁ ፍቀዷቸው ያረመኔ አገር ነውና። ያገሬ ሰው ገብር ሥራት ግባ ብየ ብሰው አምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በሰራት(ሥርአት) በተገዝ ሰው አቸነፋችሁኝ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች እንድ አርሳስ ፈርተው ጥሰውኝ ሸሹ ብትቃጧቸው፤ ክሮጡ ሰዎች ጋራ አልነበርሁም፤ ጌታ ነኝ መሰሎኝ ባልሰላ መድፍ ሥታገል ውየ ነው። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዟል አሰልሚል አያለ አሰሩን ምክንያት ይሠጠኝ ነበረ። እኔ ከከፋሁበት አማዚዘብሔር መልካም ይሥጠው፤ እንደወደደ ይሁን፤ አማዚአብሔር ቢሠጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ። ከተወለድሁ አስታሁን ወንድ አጅን ጨብጦት አያውቅም ነበረ። ሰዎች ሲሸሹ ተነስቼ ማረጋት(ማረጋጋት) ልማድ ነበረኝ፤ ጨለማ ከለከለኝ። ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች አማዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ። እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ሊያሩሴሌም ዘምቼ ቱርክቸን አስለቅቃለሁ መሰሎኝ ነበር። ወንድ ያቀፈ ተመልሶ አይታቀፍም።

(ባህሩ ዘውዴ፣ ስሸን ሩበንስን)

ምዕራፍ አስራ አንድ

ለፍፃሜው ዝግጅት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ 30ሺ ተፋላሚዎች፣ ከባድ መሳሪያ ድብደባ፣ መቅደላ መግቢያ በር ላይ፣ መቅደላ ላይ የንጉሰ ነገሥቱ ራሳቸውን ማጥፋት

ሚያዝያ 13፣ 1868 በፋሲካ ማግስት፣ ሰኞ ጠዋት፣ ኩሩዎቹ የፋላና የሰላሌ ኮረብታዎቸ በፀሀይ ብርሃኑ በድምቀት ወገግ ብለዋል።

በቀጥታ የመቀስቀሻው ጥሪ ተሰማ፣ ጥሩምባ ሲነፋና ከበሮው ሲመታ፣ የሚርመሰመስ ሕይወት መንቃት ጀመረ። ወታደሮቹ ከድንኳኖቻቸው ፊት ለፊት ራሳቸውን ያንቀሳቅሱ ጀመር፤ ብዙዎቹ እያዛጉና እያጉረመረሙ፣ ሳቅና ቀልድም ይቀላቅሉ ነበር። የየኮምፓኒው ወታደሮች በየከፍላቸው ተሰሰፉ፤ ስም ቆጠራ ተጀመረና ሲጠሩ መልስ ከሰጡ በኋላ ሰልፉ ተበትኖ ወደ ቁርስ ገበታቸው አመሩ።

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ በፋላ ቁልቁለት፣ ስምንት የአቢሲኒያ ሰዎች መጡ፤ የተለያዬ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው፣ ከሐር የተሰራ ቀሚስ እንደለበሱ፣ ፀጉራቸው እንደየምርጫቸው ተንጨባርሮም ሆነ ተንጉኖ፣ እንገታቸው ላይ ከበድ ያሉ ጌጦች እንጠልጥለው፣ ደረታቸው ደግሞ በብር ሜዳሲያዎች ተንቆጥቁጧል። ወደ ሰር ሮበርት ድንኳን እንዳመሩ ወዲያውኑ፣ ዙሪያውን በወታደሮች ተከበቡ። ወታደሮቹ የተጠሩት ሥርአት እንዲያስጠበቁና ለውይይት ከፍት ቦታ እንዲፈጥሩ ነበር።

የእንግሲዙ ጦር አዛዥ እንደቀረበ ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ፣ በእስተርጓሚያቸው በአቶ ሳሙኤል (በንጉሥ ተወዳጅ) በኩል ሃሳባቸውን አቀረቡ። ሃሳባቸው፣ ፋላና ስላሴን ለማስረከብ እንደመጡ ነው፤ ያ ግን የሚሆነው ምንም ሳይደረጉ ለቀው መሄድ ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው። ጥያቄያቸው በሰር ሮበርት ተቀባይነት ስላገኘ፣ በጥያቄያቸው መሰረት ወደየቤታቸው ሲሄዱ በሽሎን እሰከሚያቋርጡ ድረስ እሱ ራሱ ሲጠብቃቸው ቃል ገባላቸው።

ስለ ንጉሰ ነገሥቱ ሲጠየቁ፤ አለቆቹ ሲመልሱ፣ ከመጨረሻው የናፒየር ጥሪ በኋላ ቴዎድሮስ ጥለው እንደሄዱ ነው የገለፁት። ይህ እንግዲህ ወደ እኩለ ሌሊት እካባቢ መሆኑ ነው። እንደ እባባላቸው፣ ቴዎድሮስ ወይ ወደጎጃም ሄደዋል፤ አለዛም ወደንግስት መሰታውት የእሮሞ ካምፕ ሄደዋል። ምንም እንኳን ንግስቲቱ የሰውየው ደመኛ ብትሆንም፣ በእስልምና ደንብ

መሰረት በአሷ ካምፕ ውስጥ አስካሉ ድረስ የንጉሡ ህይወት የተጠበቀ ነው የሚሆነው።።

ይህ ነገር፣ ጀኔራል ናፒየር በፍፁም ያሰበው ወይም ያለመው አልበረም።። ቴዎድሮስ፣ በመቅደላ ጀርባ መልካጨሎ በሚባል፣ ከበሽሎ ጋር በትይዩ በሚወርድ ስፍራ ያዘጋጀውን የፈረሰኛ ከበባ አምልጦ መሄድ ይችላሉ ብሎም አሰበ።። ወዲያውኑም፣ ቴዎድሮስን በህይወት ላመጣ ወይም ለገደለ ሰው 50ሺ ዶላር ሽልማት አንደሚሰጥ አወጀ።። ይህን አዋጅ ይዘው፣ መልከተኞች ወደ ዋግሹም ጎበዜ[135] ካምፕ፣ ለሙስሊም አሮሞዎች ንግስት መስታውትና ለአዘቦ ከርሰቲያን አሮሞዎች ንግስት ወደ ወርቂት ተላኩ።።

ሰር ሮበርት፣ ቀጥሎም፣ ፋላና ስላሴ አንደተያዙ ራሱን በነዚህ ምሽጎች ካጠናከረ በኋላ ወደ መቅደላ ለመቀጠል ወሰነ።። ሰር ቻርልስ ስታቨሊም ከፋላ ግርጌ ባለው ሜዳ ላይ ጦሩን እንዲያሰልፍ ታዘዘ።።

በወታደሮቹ አካባቢ የመነቃቃት ሁኔታ ይታይ ነበር፤ በመኮንኖቹ አካባቢ ደግሞ ብዙ ወሬ ይወራል፤ አሽከሮችና የህንድ ፈረሰኞች ፊታቸው ላይ የመደነቅ ስሜት ይታያል።። ይህ የውጊያው የወደፊት ዜና በዚህም በዚያም በጋለ ሁኔታ ሲወራ በሰዎች ላይ የሚነዝር ስሜት ነው የፈጠረው።።

በዘመቻው የታለመው ትልቁ ውጤት ሊከናወን ነው፤ አናም ሁላችንም የተንገላታንበት ይህ ውጤት ወደ ፍፃሜው አየተቃረበ ነው።።

ከዚያም፣ አያንዳንዱ ሬጅመንት ትዛዙን ሲያስተጋባ፣ የጥሩምባዎች ጩኸት በተከታታይ መሰማት ጀመረ፤ የአነዚህን የጥሩምባ ድምፅ ደግሞ፣ ግራጫ መልከ፣ ስፋትና ግርማ ሞገስ ያላቸው ኮረብታዎች በማስተጋባት ራቅ ባሉ የተራራ ሰንሰለቶች ድረስ እንዲሰሙ አደረጓቸው።። ከዚያ ቀጥሎ፣ ከበሮዎች ሲመቱ፤ ትራምፔቶች ሲነፉ፣ ኮሰተርና ቀጥ ያሉ ወታደራዊ ትዛዞች፣ በመጨረሻም ሬጂመንቶቹ በአራት ረድፊ ተሰልፈው በጥቂት ሙዚቀኞች አየተመሩ ወደ ፋላ ሜዳ መንቀሳቀስ ጀመሩ።።

33ኛው የአየርላንድ ሬጅመንት (የዌልንግተኑ መስፍን ጦር)፣ በነበራቸው ጥሩ ባሕሪና፣ የሚያሳፍር ትውስታ ከተፈጠረበት ዲልዲን ከለቀቁ በኋላ ባሳዩት ትዛዝን በፍጥነት የመቀበል ሁኔታ ለግዳጁ ተመረጡ።። ወታደሮቹም በ "ያንኪ ዱድል" ሙዚቃ በሚያነቃቃ ፈጣን ርምጃዎች ሰልፋቸውን ቀጠሉ።። ይህ ሬጅመንት፣ በዚህ በሶስት ምሽቶች በሚደረገው ድራማ በመጨረሻው

---

135 ዋግሹም ጎበዜ ወደ እንግሊዞች ካምፕ ባይመጡም፣ አንታቸውን ደጃዝማች መሸሻን የወከሉ መሆናቸውን ለእንግሊዞቹ ገልጠዋል።። ደጃዝማች መሸሻ፣ ቴዎድሮስ አምልጠው እንዳይሄዱ አምባ ኮሂት የሚባል ቦታ ይዘው እንዲጠብቁ በናፒየር ታዘው ነበር።።

ከፍል ወሳኝ ሚና ለመጫወት የተመደበ ነው። የአጥቂውን ጦር የሚመራው ይህ ከፍል ነው።

በዚህ ቀን፣ ሬጂመንቱ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በአዛዡ ቅርብ ከትትል እንደሚደረግበት ያውቃል። አካሄዳቸውና ሁኔታቸው በሙሉ፣ "አታሰቡ፣ ውጊያና ሰልፍ የተለያዩ መሆናቸውን አናሳያችኋለን፣ በአለም ምርጥ ተዋጊ ሬጅመንት ተብሎ የሚታወቀውን ዝናችን ተግባራዊ ለማድረግ እንጥራለን።" የሚል ይመስላል።

33ኛውን አግረኛ ተከትሎ፣ ባንዱ "ጌሪ አውን" እየተጫወተ፣ እራተኛው የንጉሡ የሚባለው ሄደ። ቀጥሎም 45ኛው (የአውሮፓውያኖቹ)፣ ባንዱ "ቺር ቦይስ ቺር" እየተጫወተ፣ አለፈ። ከነዚህ በጣም በታጠቁ ምርጥ፣ ቁጥራቸው ወደ 1600 የሚሆኑ የአውሮፓውያኖችን ጦር ተከትሎ፣ የሴፖይ ሬጅመንት፣ 800 ሰው ያለበት የቤሉቺዎች፣ 800 ሰው የያዘው የፑንጃቦች፣ ሁለት የ10ኛው የህንዶች አግረኛ ኮምፓኒዎች፣ መሐንዲሶችና ቆፋሪዎች፣ ተከትሎም የኮሎኔል ፔን የተራራ ከባድ መሳሪያ ከሁለት ሞርታሮች ጋር በተጨማሪ የሮኬቶች ከፍል የባህር ሀይሉ ብርጌድ ቀጠለ። የፈረሰኛው ከፍል፣ ከ3ኛው ቀላል የተወላጆቹ(ህንዶች) ሁለት ኮምፓኒዎች ነበሩ። የ3ኛው ድራጎን ዘቦች ደግሞ ቴዎድሮስ እንዳይሸሹ ለማጠር ወደ መቅደላ ጀርባ ተላኩ።

በስላሴና ፋላ መካከል ባለው ሸለቆ የሚወስደው መንገድ በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ነበር። ምናልባትም በየሶስት ጫማዎች ወደላይ ቀና እያለ ነበር የሚሄደው፣ ንጉሡ ራሳቸው አንዳሰሯቸው መንገዶች ሁሉ በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ሰለሆነ በቀላሉ ለመውጣት አይቻልም። ሰር ሮበርት ናፒየርና ረዳቶቹ እንደታዩ እኔም አብሬያቸው ዳገቱን መውጣት ጀመርኩ። አንድ ሺ የሚሆኑ ሰፍራዎች ላይ፣ ወደ ላይ ወደፋላ የሚወስደው መንገድ በቁጥጥር ሥር ውሏል። ሁሉም መኮንኖች እንደሚያምኑበት፣ ከዚህ ግዙፍ አለት ጀርባ፣ የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል፣ ጥቂት አውሮፓውያን ብቻ ማለቀመጥ የዘመቻውን ሁኔታ በእርግጠኝነት ይቀይረው ነበር። ወደላይ ለመውጣት ሰንታገል፣ በአራት ትልልቅ የአለት ድንጋዮች መሀከል አለፍን፣ አንደገና ቁልቁል ትይዩ በሆኑ አለቶች መካከል ወርደን፣ ሰንወጣ፣ ቀጥ ያለ፣ የሚንከባለሉ ድንጋዮች ፈጠጥ ያሉበት ዳገት ማየት ጀመርን። ከጋራው ወጣ ባለ መሄጃ ተጠማዘን ወደላይ ከወጣን በኋላ፣ ትንሽ ደልደል ባለ መንገድ ላይ አርምጃችን ቀጠልን። ይህም ወስዶ ከሌላ ቀጥ ያለ ዳገት ሰር አደረሰን። ከዚያ በኋላ፣ አንደገና ወደላይ፣ ወደላይ፣ ቀጥሎም ወደላይ መውጣት ነበር። ይህም በእኩለቀን ፀሐይ፣ በፋላና በስላሴ አህታማች ምሽጎች መሀከል ባለው ሸለቆ አፋፍ አሰከንደርስ ነበር።

የምሽጎቹ አለቆች እጃቸውን ከለጡ በኋላ፣ በኮሎኔል ሎች የሚመራ የ3ኛው ቀላል ፈረሰኞች ቡድን፣ ምሽጎቹን እንዲይዝና ኗሪዎችን እንዲያስለቅቅ ተልኮ ነበር። የ33ኛው እግረኛ ከፍል ከፍታዎቹ ላይ ሲደርስ፣ ስድስት ኮምፓኒዎች ፈረሰኞቹን ለማገዝ ተመደቡ። ወደ ስላሴ ራቅ ወዳለው ጠርዝ ተጉዘው ወደ ቀኝ ኪታጠፉ በኋላ ከፍታው ላይ በመውጣት ወደምዕራብ እቅጣጫ ገስገሱ። ሳንጃቸውን ወድረው፣ ወደ መንገዱ ሲቀጥሉ፣ የሚያገኟቸውን ያገሬው ተወላጆች ከምሽጉ እያስለቀቁ ነበር። ከዚያም የእንግሊዝ ጦር የቆመበት ቦታ ደረሱ። ከኮሎኔል ሎች ጋር፣ ካፔቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ነበር። እሱም በፈረሱ ላይ ሆኖ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ፣ እለቆችንና ዋና ዋና ሰዎችን ጉዳት እንደማይደርስባቸው እያግባባ ነገር ግን በእስቸኳይ ወደ ፋላ ሜዳ እንዲሄዱ እየመከረ ነበር። ሰዎቹ እልፈው በሚሄዱበት የማለፊያው መውጫ ላይ፣ የወታደሮች ካምፓኒ ግራና ቀኝ በመቆም፣ እልፈው የሚወጡ ሰዎችን ትጥቅ ያስፈታ ነበር። ይሀን ማለፊያ ወርደው ካለፉ በኋላ፣ ያገሬው ሰዎች የእንግሊዝ ወታደሮች ወደቆሙበት እርከን ያለበት ቦታ ብቅ አሉ።

ወታደሮች በረሻም ስልፍ ተስልፈው ሲመጡ ሲያዩ፣ ተወላጆቹ በቅያሜ ቀጥ አሉ። ሆኖም በመረጋጋት፣ መንገዳቸውን ቀጥለው እርከኑ ቦታ ደረሱና ቆሙ። ያም፣ ወደታች ወደሜዳው መውረጃው መንገድ አስኪከፈትላቸው ድረስ ነበር። ፈረንጆቹ የማይጓዷቸው ወዳጆች መሆናቸውን አለቆቹ ሲረዱ፣ በወታደሮቹና በተጠረገው በስላሴ በኩል ባለው ከፍተት ወረዱ። እዛም ሲደርሱ እልልታ ያሰሙ ጀመር፤ የእንኳን ደህና ወጣችሁም ምልከት ሆነና ወደ ስላሳ ሺ የሚሆኑ ሰዎች በደስታ ባንድ ላይ፣ ወደላይ፣ ወደ ስማይ፣ ታላቅ የሆነ የህብረት ዜማ እንደሚሰማ አደረጉት።

ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት፣ አሸናፊዎችን ለመገናኘት ከለላሴ ቁልቁል መውረድ ጀመሩ፤ በሁለቱ ምሽጎች መካከል ባለው ቦታ ላይ ያለውን የሰው ቁጥር በመጨመርም ሜዳውን ሞሉት።

እኩለቀን ስለነበረ፣ እስካሁን ያላየነው ሞቃት ፀሐይ፣ በሰማያዊው ግማሽ ከብ ስፍራ በመሀል አናት ይወርድ ነበር።

የእርምስትሮንግ መድፎችን የጫኑ ዝሆኖች ጋራውን መውጣት ሲጀምሩ፣ ወዲያውኑ፣ ፈረስ ላይ በተቀመጠ መኮንን ትዛዝ መሠረት፣ ወታደሮች ሰዎቹን መንገዳቸውን እንዲቀጥሉ በሰንጃቸው ያስገድዱ ጀመር። መንገዱም በሚጣደፉት ስደተኞች ተሞላ። ቀጥሎም ዳገቶቹ በነዚህ ሰዎች ጢም አሉ። በእልልታው ፋንታ፣ የለቅሶ ጨሁትና የሚያሰን የህዘን እንጉርጉሮ ተተካ፤ በብዛት እየወረዱ ያሉትን ሰዎች ስናይ፣ እኛም ሳይቀር ነፍሳችን እስጨንቆን ነበር።



የአፄ ቴዎድሮስ ቀሪ ሠራዊት ከመቅደላ ሲወጣ
(Roger Acton)



የእንግሊዝ ጦር እንቅስቃሴ ወደ መቅደላ

ካለንበት ኮረብታማ ቦታ ይህ ትዕይንት እያለፈ እያለ፣ ኮሎኔል ሎችና ካፒቴን ሰፒዲ በስላሴ ጠርዝ፣ ምሽጉን ዙሪያውን ባቀፈው መንገድ ላይ እይተጓዙ ነበር። ከዚህ በኋላ፣ መንገዱ ወደ መቅደላ ይወሰዳል። ሰላሴና መቅደላን በሚያገናኘው የሰላምጌ ደልዳላ ቦታ ላይ የተወሰኑ ሰዎች ይታያሉ። እነሱም ፈረሰ ላይ የተቀመጡ የጦር አለቃ ልብሰ የለበሱ አቢሲኒያውያን ነበሩ። ከነሱ መካከል አንዱ፣ በለበሰው የሚያምር ልብሰና በነበረው ግርማ ሳላ ብሎ ይታያል። ይህ ሰው፣ ደማቅ የፈረሰ ልብስ የለበሰ ነጭ ፈረሰ ላይ ነው የተቀመጠው። የእንግሊዞች ፈረሰኛው ከፍል በሰላሴ ጎን መታየት ሲጀምር፣ ሰዎቹ ቀሰ ብለው ወደመቅደላ ተመለሱ። ሲመለሱ ግን እየተኮሱ ነበር።

ሰላምጌ ሜዳው ላይ ከደረሱ በኋላ፣ የጫካ ድመት ዐይን ያለው ሰፒዲ፣ የአቢሲኒያ ፈረሰኞች እዛ ቦታ የታዩበትን ምክንያት ያገኛል። እነሱም፣ ሰላምጌ ሜዳው ላይ ወደቀኝ በኩል ትንሽ ያርዶች ርቀት ላይ የነበሩ መድፎችን ለመውሰድ ነበር። ከፋላ በኩል፣ ወደነሱ አቅጣጫ ሁለት ጋዜጠኞችና ጥቂት የመድፈኛ መኮንኖች ነበሩ። የኮሎኔል ሎች ፈረሰኞችና ከፋላ በኩል የመጡት መኮንኖች የአፄ ቴዎድሮስ መድፎች የተጠመዱበት ቦታ ላይ ተገናኙ። መድፎቹ ወዲያውኑ በቁጥጥር ሰር ውለው የንግሥት ቪክቶሪያ ንብረቶች መሆናቸው ተነገረ። አብዛኞቹ መድፎች የብሪታኒያና የፈረንሳይ ስሪቶች ናቸው። ሌሎቹ ግን ቴዎድሮስ በቀጠሯቸው ሩሲያኖች የተሰሩ ነበሩ።

መቅደላ ከተመለሱ በኋላ ጥቂቶች የአቢሲኒያ ፈረሰኞች ጥቃት ለማድረግ ማሰባቸውን የሚሳይ እንቅስቃሴ አደረጉ። ነገር ግን ሰለ ውጤቱ እርግጠኛ ሰላልነበሩ፣ ወደመሃል መቅደላ መጋለቡን የመረጡ ይመሰላል። በቦታው የቆሙ፣ ቆራጥ የሆኑ፣ ወደመቶ የሚሆኑ የተወላጆቹ ወታደሮች አሉ። በዚህ ባለዝና ምሽግ ዳር ላይ፣ ጠቋቁር ጭንቅላቶች በመሰመር ብቅ ይሉና፣ አልፎ አልፎ ጠመንጃዎች በሚያሰተጋባ ጉልህ ድምፅ ሲተኮሱ ይሰማል።

በድንገት፣ ፈረሰኞቹ፣ ወደ ሰፒዲና መድፎቹን ወደሚቆጣጠሩ ጓደኞቹ ገሰገሱ። ከመህከላቸውም ለየት ብሎ የሚታየው የነጩ ፈረሰ ልዑላዊ ጋላቢ አብሮ ነበር። ሶለት መቶ ያርዶች እንደተጠጉ ሰዎቹ ቆሙ። ሰፒዲም፣ ያ ዘናጭ ነጭ ፈረሰ[136] ጋላቢ የአቢሲኒያው ንጉሥ ቴዎድሮስ ራሳቸው መሆኑን ይገነዘባል።

---

136 መቅደላ የነበረው የቴዎድሮስ ነጭ ፈረስ፣ ሀመር ይባል ነበር። ካፒቴን ስፒዲ፣ ባይከለከል ኖሮ የቴዎድሮስን የፍልሚያ ጥሪ ተቀብሎ ለመሄድ አስቦ ነበር።

ካፒቴን ስፒዲ፣ ነጩ ፈረስ የተቀመጠው ሰው ጮክ ብሎ የተናገረውን ነገር ያረጋግጣል። ፈረሰኛው ፍልሚያ ነው የጠየቀው። "እትመጡም፣ ሴቶች ናችሁ? ጥቂት ፈረሰኞችን ለማጥቃት የምታወላውሉት?"

ይህ በርግጥ፣ ንጉሡ የት እንዳሉ እንዲታወቅ ሰላደረገ፣ የእንግሊዝ ጦርን ከሃሳብ ነው ያዳነው። እንዲያውም፣ ለእንግሊዝ ጦር ያሚየረከ ነገር ነው የሆነው። ሁኔታውን ለመግለፅ ወደ ናፒየር መልከተኛ ተላከ። እብረዋቸው ከነበሩት እግረኛ ጦርና ፈረሰኞች ጋር በመሆን እንግሊዞቹን ለማጥቃት ሙከራ እስከሚያሳዩ ድረስ፣ ንጉሡ ለጠየቁት ፍልሚያ መልስም አልተሠጠም ነበር። ከዚያም፣ የተወሰኑ የ33ኛው እግረኛ ወታደሮች ቦታ እንዲያዙ ምልከት ተሠጣቸው። ወታደሮቹ፣ ከደልዳላው ቦታ ወደ ሸለቆዎች የሚወስዱ በግራ በቀኝም ያሉ መንገዶችን መቆጣጠር በሚያስችላቸው ሁኔታ ቦታ ያዙ። ሰላሴ ላይ ባንዴራቸውን ለመትከል በመዘጋጀት የነበሩ ሌሎች የ33ኛው ወታደሮች፣ የተማረኩ መድፎች ያሉበት ቦታ እገዛ እንዲያደርጉ ታዘዙ። ስድስት መድፎች፣ እርሳስ ተቀባብለው ሰለነበር፣ ጥቂት መድፎች ወደ ተወላጆቹ አቅጣጫ ሲተኮሱ፣ ተወላጆቹ፣ በአፀፋው ያላነጣጠረ ተኩስ ጀመሩ። ይህ የሚፈለገውን ውጤት ነው ያስከተለው። ሰዎቹ ወዲያውኑ በሜዳው ላይ ወደ ነበሩ መጠለያዎች ጀርባ መሄድ ጀመሩ። እነዚህ መጠለያዎች፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን ከደብረታቦር ሲያመጡ ለመቀበያ ብለው ያሠሩት ነበር። ተጨማሪ መድፎች ሲተኮሱ፣ ሰዎቹ ከተደበቁበት ቦታ ወጡ። የእንግሊዝ ጥቂት ወታደሮችና እብረዋቸው የነበሩ ጋዜጠኞች፣ ቴዎድሮስና ተዋጊዎቻቸው በፍጥነት ወደ መቅደላ አምባ ሊያፋገፍጉ ማየታቸው እርከቷቸዋል።

ነገር ግን፣ ቴዎድሮስ ከአለት ጉደባቸው ሆነው፣ ማንኛውም ወደ መቅደላ ጠጋ ለማለት የሚሞክር ሰው፣ ቀረብ ካለ፣ በማለም ጠመንጃ ይተኩሱ ጀመር። የ33ኛው እግረኛ ከፍልም፣ ከመቅደላ በሚመጣው፣ ጉዳይና አሰፈሪ የሆነ ተኩስ መረበሽ ጀመረ። ወዲያውኑ፣ እንድ የካምፐ ረዳት እየጋለበ፣ ከጀኔራል ሰታቨሊ የተላከ የተኩስ እቁም ትዛዝ ይዞ መጣ።

የዚህ ተኩስ ድምፅ ደግሞ፣ ጀኔራል ናፒየርን ወደፊት እንዲመጣና ሁኔታውን እንዲቃኝ አደረገው። የ33ኛው ወታደሮች የእንግሊዚን ባንዴራ ሰላሴ ላይ እንዲተክሉ ታዘዙ። የ45ኛው ደግሞ ፋላ ላይ ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ታዘዙ። የእንግሊዝ ባንዴራ ባንድ ጊዜ በሁለቱም ምሽጎች ላይ እንዲውለበለብ ተደረገ። ምንም ደም መፋሰስ ያልነበረበት ሁኔታ ቢሆንም፣ ከብር የሚገባው ሰለነበር የአድናቆት "ቺርስ" ድምፅ እንዲሰማ አደረገ። እንደገናም፣ ዕይታው የመሥጥ ስሜት እንዲፈጠርም አደረገ። በዚህም፣ ሁለቱ የቴዎድሮስ ጠንካራ ምሽጎች ወደቁ።

በደቡብ በኩል የሚገኘውን፣ መህል ላይ ያለውን ጉብታ እንደተሻገሩ፣ የመቅደላ ውጎተኛው የጥንካሬ ገፅታ ወዲያውኑ መታየት ጀመረ።።

ሙሉ በሙሉ አለት ላይ የተፈጠረ፣ ሞለል ያለ ቅርጽ ያለው፣ ርዝመቱ እንድ ማይል ተኩል የሚሆን፣ ጎኑ ደግሞ፣ ከግማሽ አሰከ ሶስትአራተኛ ማይል የሚሆን ቦታ ነው።። ከሰላሴ በስተሰሜን በኩል ከሚያገናኘው ጠበብ ካለ ደልዳላ ቦታ ወደላይ 500 ጫማዎች ከፍታ አለው።። አለቱ መቅደላ ነው፣ ላዩ ላይ ያለው ደልዳላ ቦታ ደግሞ ሰላምን ነው።። መቅደላ፣ በምዕራብና በደቡብ ጎኑ፣ ከታች ከመልካፈሎ ሸለቆ በ2ሺ ጫማዎች ከፍታ ላይ ይገኛል።። በምስራቅ ጎኑ፣ በተደራራቡ ሶሰት እርከኖች ግድግዳ፣ 600 ጫማዎች ወደላይ ከፍ ይላል።። ከላይ እምባው፣ ሾጠጥ ያለ ቅርፅ ባላቸው ካሳር በተሰሩ የቤት ጣሪያዎች የተሞላ ነው።። የእምባው ዳርቻ፣ በድንጋይ የተገነባ መከላከያ አለው።። ከላዩ ላይ ደግሞ፣ ማሰናከያ የሚሆን መከላከያ ተደርጎበታል።። በሰላምን በፊት ለፊት በኩል ያለው ቦታ ግን፣ እጠር ያለ ግምብና ማሰናከያ አለበት።። ይህም ዳገቱ ኢጋማሽ ላይ ነበር የተገነባው።። በዚህ ቦታ በመህሉ፣ ወደ ምሽጉ መግቢያ ብቸኛ በር የሆነ ግማ ተሰርቶበታል።።

የተወሰኑ ወታደሮች ፋላና ሰላሴን እንዲጠብቁ ከተመደቡ በኃላ፣ ሌሎች ሁሉም ወታደሮች የቴዎድሮስ መድፎች በተማረኩበት ቦታ፣ ወደ ሰላምን መጥተው እንዲሰባሰቡ ተደረገ።።

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የጠላትን ትከከለኛ ሀይልና የምሸጉን ሁኔታ ለማረጋገጥ በጣም ነበር የተጠበበው።። መቅደላን ከእንድ አቅጣጫ ብቻ ማጥቃት ይቻላል ወይ? ይህም፣ ካለንበት ከሰላምን ፊት ለፊት የሚገኘውን ጎን ማለት ነው።። እንደዛ ከሆነ ደግሞ፣ ሠራዊቱ ከያዟቸው በላይ፣ ረዘምና ጠንከር ያሉ መሰላሎች ያስፈልጋሉ።። ምንም እንኳን ከዚህ ከሚታየን የሰሜን ጎን ውጭ ሌላ ጎኖች ላይ ጥቃት ማድረግ ባይቻልም፣ ማንኛውም ወደ መቅደላ የሚወሰዱ መንገዶች እንዲሸፈኑ ማድረጉ ታምኖበታል።። ይህ ግዳጅ፣ 3ኛው ድራጎን ተብለው ለሚጠሩት ለአውሮፓውያኑ ፈረሰኞች ተሰጥቷል።።

የኮሎኔል ፔን የተራራ መድፈኞች ወይም ከባድ መሳሪያ ቡድን፣ ከተማረኩት መድፎች በቀኝ በኩል፣ ከመቅደላ 800 ያርዶች ርቀት ላይ መሳሪያዎቻቸውን እንዲጠምዱ ትዛዝ ተሠጠ።። ከመቅደላ እንድ ሺ ያርዶች ርቀት፣ በሰላሴ ኮረብታ ላይ ደግሞ፣ የቲዊስ የተራራ መድፎች እንዲጠመዱበት ተወሰነ።። የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች፣ በፋላና በሰላሴ መህከል በሚገኘው ኮረብታ፣ ከመቅደላ 2500 ያርዶች ርቀት ላይ እንዲጠመዱ ተደረገ።። ስለዚህ፣ የኮሎኔል ፔን መድፎችና የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች እንደግማሽ ከብ በሆነው ቦታ ላይ ዳርና ዳሩ ላይ ነው የተመደቡት።። በዚህም፣

ከሁለቱ ጎን የሚተኮሰው ተኩሰ መቅደላ ላይ እንደሚገናኝ ተደርጎ ነው። ባለ ሰምንት ኢንች ሞርታሮች ከአርምሰትሮንግ መድፎች ግራ በኩል ተደግነዋል።

ከቀኑ ሰምንት ሰአት ሲሆን፣ የኮሎኔል ፔን መድፈኞች ሰውጊያ ተዘጋጁ፤ ግልፅና ጎላ ባለ ድምፅ ተጀመረ። ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ይህ ሁሉ ተኩሰ ሲወርድ፣ የተከበቡት ሰዎች፣ ለመከላከል ምን አይነት እርምጃ እንደሚወሰዱ ለማየት፣ ስላሴ ኮረብታ ላይ ነበር።

የሀውዜር ከባድ መሳሪያዎችን ተከትሎ፣ ሾል ያሉት የአርምስተሮንግ እርሳሶች፣ የሚንቀጠቀጥ ድምፅ ያሰው የሙዚቃ ቃና እያሰሙ ወደላይ እየተሸከረከሩ በአየሩ ውሰጥ ይሄዱና መቅደላ ላይ ሲደርሱ ይፈነዳሉ። ከዚያ ደግሞ የሞርታር እርሳሶች፣ የታዘዙትን ሰራ ለመፈፀም የጠሉ ይመሰል የሀዘን የመሰሰ ድምፅ እያሰሙ፣ ነገር ግን፣ የሚይቀረውን ዕጣ ለማድረስ ተከትለው ይወነጨፋሉ።

ከዚያም ከባድ መሳሪያዎች ሥራ ጀመሩ፤ ሃያ የሚሆኑ፣ ሁሉም አይነት ካሊበሮች መቅደላ መግቢያውን ያጓሩበት ጀመር። ከነሱ ጋርም የአባብ ቱጨት ድምፅ ያላቸው ሮኬቶች ሲተኮሱ ይሰማል።

በዚህ ሀይለኛ ድብደባ መሀል፣ አንዱ ጋዜጠኛ የቴዎድሮሰን የመጨረሻ የእጅ ሥራ አይቼ እንደሆን ጠየቀኝ። እንዳላየሁት ሰመልሰለት፣ ላሳይህ በማለት ወደ ገደሉ ጫፍ እየመራ ወሰደኝ። በጣቱ እየጠቆም ቁልቁል በሚያመለክትበት እቅጣጫ ሰመለከት፣ ለዕድሜ ልከ መገሰጥ ያለበት ሁኔታ ነው ያየሁት።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አንባቢ ሆይ፣ አሰቃቂና ቀፋፊ ሁኔታ አልወድም። ነገር ግን ማሰብ ከተቻለ ወደ 308 የሚሆኑ ሰዎች እንዱ ባንዱ ላይ ተነባብሮ፣ ራቁት፣ አግርብረት በእግሮቻቸው ላይ እያሉ ተከምሮ ማየት፣ ይህን አሰቃቂ ሁኔታ በመግለፄ ይቅርታ ታደርጉልኛላችሁ።

እንደዚህ ላለ ሰጀምላ ግድያስ በቂ ቅጣት መስጠት ይቻላል ወይ? የበቀል ፍርድ በሚሠጡ በሠለጠኑ ሰዎች ህግ፣ የሌላ ሰውን ህይወት የሚነጥቅ ሰው ሕይወት ራሱ ይሰዋ ነበር። እንግዲህ 300 ሰዎች ሰሚገድል ሰው ምን ሊደረግ ይቻላል?

በቅርብ ጊዜ የተማረኩት ሰዎች እንደገለፁት፣ ቅጣቱ ሲፈፀም በቦታው ነበሩ። እሰረኞቹ እጅና እግራቸው አንደታሰረ፣ በጎራዴና በጥይት እየተመቱ መሪት ላይ ይወድቁ ነበር። ብዙዎቹ እንደምንም ብለው በጉልበታቸው ተንበርከው፣ ምህረት እንዲደረግሳቸው ቢጮሁም ሰሚ አላገኙም። እንድ

ሳይተርፍ ሁሉም ተገደሉ፡፡ ይህ የሆነው እኛ ዳውንትና ደላንታ በደረስንበት ቀን በሚያዝያ 9፣[137] ነበር፡፡

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ከሁለት ሰኣታት ድብደባ በኋላ፣ ተከላካዮቹ ደካማ ስለሚሆኑ፣ የሱ ወታደሮች ጥቃት ቢጀምሩ ከባድ ጉዳት እንደማይደርስባቸው ገመተ፡፡ ሰለዚህ፣ የሮያል ኢንጂነሮችን፣ 33ኛውን፣ 45ኛወን እናም የንጉሡ የሚባለውን ጦር ለመጨረሻው ግዳጅ እንዲዘጋጁ ትዛዝ ሰጠ፡፡

የብሪታኒያ ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ እንደጀመሩ፣ ከምሽጉ የሚተኮሱት ጠመንጃዎች አቁመው ነበር፡፡ በሩን ጥሰው እንዲገቡ የተመረጡት ወታደሮች በባታሊዮን ደረጃ ተሰልፈው በመቅደላና በሰላምጌ መህል እሩብ ርቀት ላይ ተዘጋጅተዋል፡፡ በሜጀር ሳርደን ፕሪቻርድ የሚመሩት መሐንዲሶች ደግሞ፣ እንደ ጠብ አሜሪ ከባታሊዮኑ ፊት ለፊት ሆኑ፡፡ ተከታታይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ሽፋን እንዲሰጥ ከታዘዘ በኋላና ተኩሱም እየቀለጠ እያለ፣ ወታደሮቹ ወደ መቅደላ መራመድ ጀመሩ፡፡ የመቅደላ ግርጌ ሃምሳ ያርዶች ርቅት ሲደርሱ፣ ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ አቆመ፡፡ አሁን ግን የሮያል ኢንጂነር ክፍሎች በያዙት ስናይደር ጠመንጃ ተኩስ ከፈቱ፡፡ ከዛም 33ኛውና 45ኛው በያዙት ከኃላው ጥይት በሚቀባበልበት ጠመንጃ፣ በሚያሰገርም ፍጥነት የጥይት ማዕበል ያወርዱ ጀመር፡፡ ያም ለአስር ደቂቃዎች ነበር፡፡

ቴዎድሮስና ታማኝ ተከታዮቻቸው ከባድ መሳሪያዎች ሲተኮሱ ተደብቀው መሸገው ነበር፡፡ ተኩሱ ሲያቆም፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው እየፎከሩ ተነሱና ከተከታዮቻቸው ጋራ መግቢያ በሮችን ለመከላከል ሮጡ፡፡ ተሰልፎ የሚመጣውን ጦር ለማሸነፍ ወይም ለመሞት ቆርጦ በወሰነ ንጉሥ፣ የሚገባውን የውጊያ አቀባበል ለማድረግም ነበር፡፡

ቴዎድሮስ፣ ለሳቸው ምንም ኣይነት ምህረት አይደረግልኝም የሚለው ሀሳብ በልባቸው እሰካለ ድረስና ለእንግሊዞች ያላቸውን ስር የሰደደ ጥላቻ እንደያዙት ቢቀጥሉ ከበባው ሰኣታት ሳይሆን ወራት ድረስ ቦተራዘመ ነበር፡፡ አሁን ግን ምንም ማምለጫ አለመኖሩን ሲረዱ፣ ለሳቸው ሲሉ ደማቸውን ለማፍሰስ ከቆረጡት ታማኞቻቸው[138] ጋር በመሆን፣ በጥልቅ ድፍረት ወደ መግቢያው ማማና ዝቅ ወዳለው መከላከያ ከመጡ በኋላ ሰዎቻቸውን በየቦታው፣ ክፍተት ባለበት ቦታ መደቡ፡፡ ሲመለከቱ፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በአራት ረድፍ ተሰልፈው፣ እየተኮሱ ወደ መግቢያው በር ሲያመሩ አዩ፣

---

[137] (በምዕራፍ ፲፩ ማስታወሻዎች)

[138] ቴዎድሮስ፣ ወታደሮቻቸውን ሆነ አለቆችን፣ መህላችሁን አነስቻለሁ ሄዱ በማለት ብዙ ወታደሮችን አሰናብተዋል፡፡ እነዚህ ግን ከንጉሡ ጋር ለመሞት ቆርጠው የወሰኑ ነበሩ፡፡

ከዚያም ሰዎቻቸው አንዲተኩሱ ምልክት ሲሰጡ፣ አነጣጥረው የሚተኩሷቸው ጥይቶች ብዙ ሰዎች አቆሰሉ። ነገር ግን ያሉበት ቦታ በአንግሊዞቹ ታወቀ።

ወዲያውኑ፣ የእንግሊዞቹ የአፀፋ ተኩስ መግቢያው ላይ ተጠናከሮ፣ የሚጠረጠሩ መከለያ አጥሮች ላይም ተደረገ። መሸገው የተቀመጡት ሰዎች ከሚተኩሱት ጠመንጃ እንደ ከብ ሆኖ በሚወጣው ጭስ ያሉበት ቦታ ተለየ። በዚህ ጊዜ፣ የሰቅለት ዕለት እንደሆነው ሁሉ፣ መብረቅና ነጎድጓድ ሲታይና ዙሪያውን ሲያነዝረው ለውጊያ አጃቢነት የሚሰማማ መስሎ ነበር። ዝናቡም ደጎስ ባሉ ሞቃታ ጠብታዎች አናታችን ላይ በከብደት ይወርድ ጀመር። በዚህ በሚደባደብ የዝናብ ዶፍ መሀል፣ የማይጠሩ የሚመስሉት ወታደሮች፣ በርግጥም ያለምንም ፍርሀት ግስገሳቸውን ቀጠሉ። የያዙትን የስናይደር ጠመንጃ አየተኮሱ፣ በመቅደላ ዳር ዳር ላይ የሚጠረጠሩ በዚያም በዚህ ቀና ቀና ብለው የቆሙ አለቶችን በደንብ እያማተሩ ነበር።

አሁንም በመሀንዲሶቹ አየተመሩ፣ አነዚያን ነብስ ገዳይ ሚሳይሎች (ሮኬቶች) በዳገቱ ላይ በተገኘው ቦታ ላይ እያረበረቡ ከማማው ስር ደረሱና ቆሙ።

ለደቂቃ የሚሆን ጋብ ብሎ ነበር። ነገር ግን ወዲያውኑ ቀደም እያሉ የሚሄዱት መሐንዲሶች ላይ በደርዘን የሚቆጠሩ ተኩሶች ተከፈቱ። በዚህም ሜጀር ፕሪቻርድና ሶስት አራት የሚሆኑ መሐንዲሶች ቆሰሉ። በአፀፋው ደግሞ በእያንዳንዱ ተኩሰ በታየበት ቦታ ላይ ያነጣጠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ተኩሶች ተተኮሱ። ሜጀር ፕሪቻርድና ወኔ የተሞላበት ሉተናንት ሞርጋን መግቢያውን ለመቆጣጠር እየሮጡ ወደማማው ሄዱ። ሲደርሱም በሩ ተዘግቶ አገኙት፤ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ማማ፣ ውስጡ አስር ጫማ ከፍታ ባለው የድንጋይ ካብ ተደፍኗል። ስለዚህ በውስጡ አልፎ ለመሄድ ቀላል አልነበረም።

"በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" ብሎ ሜጀሩ ጮኸ።

ቀጥሎም፣ በመስመሩ ወደኋላ የተሰተጋገው ድምፅ "በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" "በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" ነበር።

ነገር ግን፣ ማን ነበረ ባሩዱን ማምጣት የነበረበት? ለምን አነዚያ ባሩድ የያዙ ሸሪዎች ማቀጣጠያ ገመድ ላያቸው ላይ የታሰረባቸው ይህንን ቦታ ብትንትኑን ለማውጣት አልነበርም? ከባዶቹ መዶሻዎችስ የታሉ? በሩን ለመፈልቀቅና፣ መቆለፊያና ማጠፊያዎቹን መስበሪያ የሚሆኑት የብረት ሽብልቆችስ የታሉ? ግንቡ ላይ የተደረደሩትን የአንጨት መሰናከሎች መቁረጫ፣ መጥረቢያና መጋዞቹስ የታሉ? ግድግዳውን ለመናድና ለማፍረስ፣ ከበድ ያሉት መቆፈሪያዎችስ የታሉ? ግድግዳው ላይ ለመውጣት፣ ወይም

ከፍታ ያላቸው መሰናከያዎች ላይ መሻገሪያ የሚሆኑት የተደራረቡት መሰላሎችሰ የት ይሆኑ? ያሰተጋባው ድምፅ፣ "የታሉ? አህ የታሉ?" ነበር። ለነዚህ አጣዳፊ ጥያቄዎች መልሰ፣ አንድ ነፍስ አንኳን ትንፍሽ አላለም።

የ33ኘው ወታደር፣ ማጉዋየር፣ የገደል ግድግዳውን መውጣት አችላለሁ ብሎ አሰቧል። ወጣ ወጣ ያሉትን ቦታዎች አየረገጠ፣ ሳያቋርጥ ወደላይ ከወጣ በኋላ፣ ዞር ብሎ፣ መግቢያ አግኝቻለሁ ብሎ ጮኸ። ከሰላምጌ በኩል በተደረገ ደከም ያለ የማበረታቻ ጩኸት በኋላ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዞረ። በዚያን ጊዜ ግን ከኋላው የራሱ ሬጅመንት አባል የሆነው፣ ወታደር በርገን፣ እየተከተለው ነበር።

ጠቅላላው ሬጅመንት፣ በደፋሮቹ ጓደኞቻቸው ምሳሌነት ተገፋፍተው፣ ቀጥ ያለውን ገደል አየተሸቀዳደመ ይወጡ ጀመር። ትንፋሽ ቁርጥ ከሚያደርጉ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አናቱ ላይ ደረሱ፣ ከዚያም መቅደላ አናቱ ላይ የሚንቀሳቀሱ የሚጠረጠሩ ሰዎች ላይ ተኩሰ ከፍተው ከመቅፅበት ፀጥ አደረጓቸው።

በያዟቸው መሳሪያዎች፣ በእንጨት አጥሮቹ መሀል በመግባት፣ ወደላይ በማንሰት፣ ወዲያውኑ፣ ዝቅ ያለውን መከላከያ መሻገር ቻሉ። ከዚያም፣ መሬቱ ላይ ሲደርሱ ተበታትነው፣ በውጊያው ቦታ በብዛት የወደቁትን የሚዘገንኑ አሰከሬኖች አቋርጠው፣ 75 ጫማዎቹ ርቀት ላይ ወዳለው የመከላከያ አጥር ገሰገሱ።

ወዲያውኑ በፍጥነት ሲተኩሱ ሰማን። ጠላት ሲንቀሳቀሰ ሲል ሰላገኙ በጥድፊያ ነበር የሚተኩሱት። ከዚያ ቀጥሎ፣ በሰደፋቸው በሮቹን ሲደበድቡ ሰማን። በሩን ለመሰበር ትልልቅ ድንጋዮች መወርወር ጀመሩ፣ አሁንም አሁንም በተገኘው ቀዳዳ ወይም ከፍተት ላይ ይተኩሳሉ። እነዚህን በሰሜት የተሞሉትን የአየርላንድ ሰዎች፣ አጥር ሆነ በር፣ ግምብ ሆነ ድንጋይ፣ የአንጨት ከምር መሰናከልና ቀጥ ያለ አለት ቢሆን የሚያሰቆማቸው አይነት አይደለም። በአጥሩ ውሰጥ ላንጃቸው አንደዘለቀ፣ አጥሩ ከጥቅም ውጭ ሆነ። አናም፣ የቀረውን መከላከያ ሲዘሉ "ሁዛ!" "ሁራፐ!" እና "ሁራ!"" የሚል ጩኸት እያሰሙ ነበር። ጠመንጆቻቸውን ደግነው ወደፊት አየገሰገሱ አቢሲኒያውያን ላይ በቅርበት ፊት ለፊት ሩምታ ተኩሰ ተከሱባቸው።

ቀደም ብለው ግሰገላውን የጀመሩትን፣ ታምቡር መቺው ማጓየርና ወታደር በርገንን አንርሳ። ሁለቱ ሰዎች፣ አንዱ አንዱን በጥቂት ርምጃዎች አየተከተለ፣ ወደፊት፣ ወደላይኛው መሰናከል አየገሰገሱ ነበር፣ ቦታው ሲደርሱ ሰዎች እያነጣጠሩባቸው አገኙና ወዲያው በፍጥነት ያነጣጠረ ተኩሰ ሲከፍቱ፣

ጥቂቶች አጥቂዎች ብቻ አመለጡ። ቀይ ኮት የለበሱ ሰዎች በቡድን ወደላይ ሲመጡ ሲያዩ፣ አጥቂዎቹ ወዲያውኑ በፍጥነት ነበር የሸሹት[139]።

የላይኛውን መከላከያ ዘለው እንደተሻገሩ፣ ከገለባ ከምር አጠገብ በእጁ ሽጉጥ የጨበጠ አንድ ሰው ቆሞ ያያሉ። ሊተኩሱበት ሲዘጋጁ አይቶ፣ ወደ ገለባው ከምር ጀርባ ዞር ብሎ ሄደ። ከዚያም፣ ሁለቱ ወታደሮች፣ በግልፅ የተኩሰ ድምፅ ሰሙ። የሰናይደር ጠመንጃቸውን እንደያዙ ወደቦታው ሲሄዱ፣ ከገለባው አጠገብ ቆሞ የነበረውና ወደ ኋላ የተመለሰው ሰው መሬቱ ላይ ተዘርሮ ወድቋል፤ በቀኝ እጁ ሽጉጡን ጭምድድ አድርጎ እንደያዘ ህይወቱ እያለፈች ነበር። በአለምሯቸው ሽጉጡ የነሱ ምርኮ ነበር፣ ሰለዚህ ምንም ሳያወላውሉ፣ የኛ ነው ያሉትን ሽጉጥ መንጨቀው ወሰዱ። ነገር ግን ሲመረምሩ፣ እጀታው ላይ ባለ የብር ልጥፍ፣ የሚከተለው ፅሁፍ ተፅፎበት አዩ።

ከንግሥት ቪክቶርያ
የታላቋ ብሪታንያና የአየርላንድ ንግሥት
ለቴዎድሮስ፣ የአቢሲኒያ ንጉሠ ነገሥት
ለአግልጋይዋ ለፕላውደን ላሰየው ደግነት
ምሰጋናዋን ለምግለፅ በመታሰቢያነት የተሠጠ
1854

"ምን ታስባለህ፣ ፓት፣ ይህ ሰው፣ ቴዎድሮስ የሚባለው፣ ንጉሥ የሚሉት ይሆን?" ብሎ ማጓየር ጠየቀ።

"ምናልባት፣ማክ፣ መናገር አልችልም፤ ሃምሳ አለቃው ፊቱን መቅደላ ውስጥ እስከሚያሳይ ድረስ አዚህ አጠገቡ ብንቆም ይሻላል። አች፣ አየመጣ ነው!" በርገን ነበር የተናገረው።

አየገለገለ የሚመጣውን የአየርላንድ ወታደሮች መስመር ሲያዩ፣ እነዚህ ሁለት ጀግኖች፣ ባርኔጣቸውን አውልቀው በራሳቸው ላይ እያውለበለቡ፣ ባልተለመደ ጠንካራ የሳምባ ሀይል፣ በእንግሎ ሳክሰኖችን የጦርነት ጩኸት፣ "ሁራ!" በማለት ጓደኞቻቸውን ተቀበሏቸው።

ሊዋጋ እንደሚዘጋጅ በሬ እንገታቸውን አቀርቅረው፣ "የመስፍኑ ጦር" የሚባሉት ወታደሮች ምንም ሳይጎድልባቸው ወደፊት መጡ። አርማ ያዙ

---

139 የአፄ ቴዎድሮስ ጠመንጃ ያዥ ወልደ ጋብር ለእንግሊዞቹ በሰጠው ቃል፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን፣ መሀላችሁን አንሰቻለሁ ሸሹ፤ እኔ ግን ለጠላት እጄን አልሠጥም ብለው ፈቃድ ስለሰጡ ነበር ሰዎቹ በፍጥነት የለቀቁት።



የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ጥሶ ሲገባ
(Roger Acton)

በመሀል፣ ረጋ ያሉት ወታደራዊ ሥርአት የያዙት መኮንኖች ከየኮምፓኒያቸው ጓላ ነበሩ። ሁሉም በኩራት ወደፊት አየተራመዱ፣ በተጠንቀቅ፣ ለአፍታም ቢሆን የሚያሰጋቸው ካለ፣ አንደሚነድ እንጨት የሞቀ ነጭ ነበልባል በፍጥነት ለማፈንዳት ዝግጁ ነበሩ። አያጣጣረ ያለው ሰው ወደ ወደቀበት ከፍት ቦታ ሲደርሱ፣ የሬጅመንቱ የመሀል ከፍል አቆመ።

በዚህ ጊዜ ዝናቡ አባራ፤ እናም ፀሐይዋ በሙሉ ጉልበቷ፣ በሰውየው፣ ግርማ ሞገሰ ባለው መሰናበቻው ላይ ታንፀባርቅ ጀመር።

ትዛዝ ሲሰጥ፣ አርማ ተሸካሚዎች በጉጉት ወጡ፤ በድል አድራጊነት፣ በከፍታ፣ የሀሩን የተጠላለፈ መስቀል ያለበትን የብሪታንያን ግርማና ሀይል ለንደቅአላማ በአካባቢው ካሉ ተራራዎች በላይ ማውለብለብ ጀመሩ። ምልከትነቱም፣ ለያዙት ሰዎች፣ ጨካኙ ንጉሠ ነገሰት አንደተሸነፈና የሚኮራበት የመቅደላ ምሽጉም በአንግዶቹ እጅ አንደወደቀ ለማሳየት ነው። ሰንደቅ አላማው በአየር ላይ ሲርገበገብና ሲውለበለብ፣ "የመሰፍኑ ጦር" ወታደሮች ባርኔጣቸውን አንዳወለቁ፣ በአንድ ላይ፣ በከፍተኛ የጋለ ሰሜት፣ ድምፃቸውን "ቺርሰ" በማለት አሰተጋቡ። ድምፁም፣ ሰላምን ላሉና፣ ከታች 500 ጫማ ወረድ ብሎ ላሉ ሰዎች፣ አንደውቅያኖሰ ማዕበል ጎላ ያለ ጉርምርምታ ነው ያሰማው። ድምፁም ሰለታወቀ፣ ከመቅደላ ተነሰቶ በቅብብሎሽ፣ ወደ ሰላሴ፣ ከዚያም ወደ ፋላ ሲሰማ፣ ግራጫ መልከ ያለው ቋጥኝ ደግሞ በማንጠር ታች ሸለቆ ድረሰ አደረሰው። በመጨረሻም፣ ሁለት ማይሎች ርቀት ላይ የሚገኘው የአንግሊዞች ካምፕ ድምፁን ተረከበው፣ የሁለ ገቡን "ሁራ"፣ በራሳቸው፣ ጉልበት በተመላበት ድምፅ አጠናከሩት። ከወታደራዊው ባንድ የተለያዩ ሙዚቃዎች ገንፍለው መውጣት ጀመሩ። 'God Save the Queen' የተባሰው የአንግሊዝ ብሔራዊ መዝሙር የሙዚቃ ኖታዎች ከመቅደላ ገደሎች ላይ በጉልህ አየነጠሩ የሚያሰተጋቡት የህብረት ዜማ ሲሰማ፣ ለመቼውም ጊዜ ቢሆን እንደዚህ በሚያሰደንቅ ሁኔታ ተዘምሮ አያውቅም።

ጥቂት ያልታጠቁ አቢሲኒያውያን በሚሰማው ሙዚቃና ጫጫታ ተሰበው፣ በድፍረት፣ ሰንደቅአላማው ቡተራራው ነፋስ ወደሚውለበለብት ቦታ ጠጋ አሉ። መሬት ላይ የወደቀውን ያገራቸውን ሰው ሲያዩ፣ ጎንበሰ ብለው ተመለከቱና ወዲያውኑ የሚያሰፈራ ሀዘኔታ ከሚያሳየው ፊታቸው ጋራ ፈገጠር ብለው፣ በመደነቅ ድምፅ "ቴድሮሰ! ቴድሮሰ!" አሉ።

ቃሉ የአንዳንዱን ሰው ቀልብ ነው የሳበው፤ እና ሁሉም ወደ አሰከሬኑ መሄድ ጀመሩ። የወደቀውን ሰው፣ በተወላጆቹ አጠራር "ቴዎድሮሰ" የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት! አንድ አፍታ አንኳን ለማየት አርሰ በርሰ አየተጋፉ ነበር።



የአፄ ቴዎድሮስ ፍፃሜ

እናስ ምን አዩ? ከሳ ያለው ያገራቸው ሰው ሰውነት፣ ከውስጥ ንፁህ የሰበሰ፣ በላዩ ላይ ግን በመለበስ ምክንያት አደፍ ያለና የተቀዳደደ ልብስ የደረበ ነበር።

በእቢሲኒያ፣ በጣም የሚደነቅ ጠየም ያለው ፊት፣ ብዙ የፈተና ሰአቶች ውስጥ ያለፈ የሚመስል ገፅታ አለው። አይኖቻቸው ምንም እንኳን አሁን የሞት ጥላ ቢጥልባቸውም፣ የሚከበሩና ሰውነት እልፎ የሚሄድ የትኩረት ሀይል የነበራቸው መሆናቸውን ያስመሰክራሉ። የታችኛው ከንፈር ንቀትን ለማሳየት በደንብ የተመቸ ይመስላል፤ አሁንም እንኳን ለእመል ያህል የንቀት ምልክት ይታይበታል። የመጨረሻውን ሰትንፋስ ሲያቃትቱ፣ ሁለት መሰመር የያዙ ነጫጭ ጥርሶች መታየት ጀመሩ። ከአፋቸው ጀምሮ፣ ሁለት ጎላ ያሉ መሰመሮች ከላይ ቀጥ ካለው አፍንጫቸው ጋር ይገናኛሉ። በፍጥነት ጥሏቸው እየሄደ ያለውን ትንፋሻቸውን በሚያጣጥሩበት ጊዜ፣ የአፍንጫ ቀዳዳዎች በጣም ሰፋ ብለው ይታዩ ነበር። ሰፋ ያለው ፊት፣ ፊጠጥ ያሉ የጉንጭ እጥንቶች ይታዩበታል፣ ግንባራቸው ጎላ ያለ ሆኖ፣ ቅንድባቸው ወጣ ያለ ነበር። ፀጉራቸው ከግንባራቸው ይጀምርና በሶስት ጉን ጉኖች ተከፍሎ ወደኋላ በአንገታቸው ጀርባ ይወርዳል። ወደኋላ እንደታየው፣ ፀጉራቸው የጥንካሬያቸው መመኪያ ነበር። ቁመታቸው እምስት ጫማ ከሰምንት ኢንች ሲሆን፣ የፈረጠሙ ጡንቻዎችና ሰፋ ያለ ደረት አላቸው። አነዚህ ገፅታዎች፣ ከፍተኛ የቆራጥነት ባህሪ ከወሳኝነት ወይም ጨካኝነት ጋራ ተቀላቅለው መኖራቸውን ያንፀባርቃሉ። ጨካኝነት የሚለው ሃሳብ እንኳን የተሰነዘረው፣ ብዙ ጭካኔ ያለባቸው ድርጊቶች ፈፅመዋል መባሉን በማስታወስ ነው። እንግዲህ ይኸው ቀሪ ሰውነቱን ያየነው ሰው፣ ሰዎች፣ የኢትዮጵያ አፄ ቴዎድሮስ፣ በምኒልክ ከሰለሞን ሀረግ የሚወለደ፣ ንጉሠ ነገሥት፣ የምድሩ ጌታ፣ የኢትዮጵያ ፓርፎ፣ የእፍረካ መስራች፣ የኢየሩሳሌም ነፃ አውጭ ብለው የሚጠሩት ሕይወቱ እያለፈች ያለ፣ በራሱ እጅ ራሱን ገዳይ ነው።*

(በአስከሬን ምርመራው፣ በቀኝ አግራቸው ከተገኘው ቀለል ያለ ቁስል ውጭ በሌላ ፍንጣሪ እንዳልተጎዱ ሀኪሞቹ መዝግበዋል። ትናጋቸው ተሰብሮ፣ የውስጥ አፋቸው ጣሪያው ተለብልቧል፤ እናም በጭንቅላታቸው፣ በጀርባ በኩል ቀዳዳ ተገኝቷል። ሁሉም የሕክምና ሀላፊዎች ባንድ ላይ የሰጡት ውሳኔ፣ በአፋቸው ውስጥ የተተኮሰ ሽጉጥ ለሕይወታቸው ማለፍ ምክንያት መሆኑን ነው።)*

የስንት ዕደለ ቢስ ሰዎችን ሕይወት የነጠቀው፣ ቀዩ የቀኝ እጅ[140]፣ የራሱን፤ ሽፍታ ባለቤቱን ሕይወት መንጠቁ ተገቢ ቅጣት መሆኑ ነው!

---

140 ያገሬው ሰው "... ወንድ ያለራስዎ ገለውም አያውቁ" ብሎ ተቀኝቷል።





ኮሲት በር በእንግሊዝ ወታደሮች ሲጠበቅ

(ወደ መቅደላ መግቢያ በር፤ በፅሁፉ የተገለፀው የምሽግ መግቢያው የድንጋይ ካፋር [illegible] ያለው የእንጨት መሰናክል በዚህ ፎቶግራፍ ተለይቶ ይታያል።

በወደቀው አስከሬን ላይ፣ ውድቀቱን ለማብሰር በመጀመሪያ ጥላ ያሳረፈበት የቅዱስ ጊዮርጊስ አርማ መሆኑስ?

የአየርላንድ ወታደሮች፣ ሁለት አግሮቻቸውን ይዘው አየንተቱ ወስደው ሸራው ላይ ካደረጓቸው በኋላ፣ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ አቃትተው የመጨረሻ ትንፋሻቸውን ተነፈሱ::

ጥቅጥቅ ብለው ዙሪያውን በቆሙ ሰዎች ያልተለመዱ አስተያየቶች ይሰሙ ጀመር:: አንድ ሰው በላቲን ቋንቋ የሚከትለውን ቃል ሲናገር 'Sic semper tyrannis' ሌሎቹ ተቀብለው "አሜን አሜን!" አሉ:: ትርጉሙም "ሁልጊዜም ለአምባገነኖች ይሁን" አንደማለት ነው:: ሌላ የአየርላንድ ወታደር ደግሞ ከአሁን በኋላ ማንንም አያስቸግርም አለ:: ሌለው ግን፣ የጨዋነት ባህሪ ያለው ሰው፣ የተገለጠው ሆዳቸውን ሸፍኖ፣ አግሮቻቸውን ካሰተካከለ በኃላ፣ ከንዶቻቸውን አጥፎ ደረታቸው ላይ አስቀመጠ::

በአስከሬኑ ዙሪያ የሚሰበሰበው ሰው ቁጥር አየጨመረ ሄደ:: መኮንኖችና ወታደሮች አስከሬኑን ለማየት በችኮላ አየተጣደፉ ይመጡ ነበር:: የተለቀቁት ምርኮኞችም የሞተውን አላሪያቸውን ለመሰናበት ይመጡ ጀመር:: ቴዎድሮስ መሆናቸውን ሲያውቁ፣ ስለለውየው ማንነት የነበረውን ጥርጣሬ አስወገደው:: ቴዎድሮስ፣ የእንግሲዝ አልሞ ተኳሾች ለይተው አንዳይመቷቸው፣ ደማቅ ልብሳቸውን አውልቀው፣ ሌላ የማለመሰያ በመልበስ ነበር ሲዋጉ የነበሩት:: የጦሩ ጠቅላይ አዛዥም ከረዳቶቹ ጋር ሆኖ አስከሬኑን ለማየት መጣ፤ ነገር ግን፣ አንዳችም አይነት ቢሆን የሀዘን ቃል ለሞቱት ንጉሠ ነገሥት አልተነፈሰም:: ሌሎች ላይ ምህረት ያላያሳየ ለራሱ ሀዘኔታ አይገባውም::

የመጨረሻዋ ሰአት፣ መሸነፋቸው አርግጠኛ መሆኑ አስኪታወቅ ድረስ፣ ህይወታቸውን አሳልፈው አልሰጡም:: ወደፊት በቀደሙት፣ ጠመንጃ ባነጣጠሩ ወታደሮች ቅፅበት ያለው ሞት መምጣቱን ሲያዩ ግን፣ ወደ ገለባው ከምር ጀርባ በመሄድ፣ ንግሥት ቪክቶርያ በስጧቸው ስጦታ፣ ሽጉጥ በአፋቸው በመጉረስ፣ ንጉሱ ራሳቸው ተኩሰው ራሳቸውን አጠፉ::

አንቅስቃሴ እንዲጀመር ጥሩምባ ሲነፋ፣ ወታደሮቹ መሳሪያቸውን ትከሻቸው ላይ አጋድመው በሰልፍ በመሆን በጠባቡ የመቅደላ መንገድ መራመድ ጀመሩ:: ከኋላቸው፣ ዋናው ጦር አዛዥና ረዳቶቹ አየተከተሏቸው ነበር:: ረጅም በሆነው መንገድ ሲጓዙ፣ የሳር ከዳን ያላቸው፣ ባለ ጎጆ ጣራ የመካነን ቤቶች በግራና በቀኛቸው በኩል ይገኙ ነበር:: ከዚያም፣ ወደ ደቡብ

አቅጣጫ፣ ሰፋ ያለ ገላጣ ቦታ ደረሱ። ምናልባትም፣ ቦታው ንጉሡ ለሰልፍ ወይም ለልምምድ ይጠቀሙበት የነበረ ቦታ ይሆናል።

ወደ ዳር፣ ከዚህ ቦታ ወደላይ በኩል፣ ከጥቁር ድንኳኖች አጠገብ በርከት ያሉ የታጠቁ ያገሩ ተወላጆች ይታያሉ። አነዚህ ሰዎችም ወታደሮቹን ሲያዩ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ተኩሰ ከፈቱ። የ23ኛው ወታደሮች ደግሞ፣ ሜዳውን የሚሸፍን ያህል መሰመር ሠርተው ሰዎቹ ላይ አየተኮሱ ወደፊት ይራመዱ ነበር። ከነዚህ በቆረጡ ወታደሮችና በማያባራው ጩኻኝ ተኩሶቻቸው ፊት ለፊት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ ወታደሮች፣ በልጃቸው በደጃዝማች መሸሻ[141] አየተመሩ ቁልቁል በገደሉ ሸሹ።

የአየርላንድ ሬጅመንት፣ በምስራቁ ጠርዝ በኩል ሲደርስ፣ የመቅደላ ምሽግ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር መሆኑን ለማሳየት፣ ሌላ ሰንደቅ አላማ ተተከለ። መሰፍኑም[142] ከበራሪ ወታደሮቹ ጋር ሆኖ፣ ይህ ሰንደቅአላማ ሲተከል የተሰማውን የቺርስ ድምፅና 'Rule Britannia' የተባለውን የወታደራዊ ማርሽ ሙዚቃ ሳይሰማ አይቀርም። በተቃራኒ በኩል ባሉ ተራሮች ላይ ያሉት የወሎ አሮሞዎችም ቢሆን ይህንን ድምፅ ሳይሰሙ አይቀሩም።

ሰር ሮበርት ናፒየር አንደደረሰ ግን፣ ሙዚቃው ተቀይሮ 'See the Conquering Hero Comes' "ተመልከቱ፣ አሸናፊው ጀግና መጣ" የሚለውን መጫወት ጀመሩ፤ ተጨማሪ የደስታ ጩኸትና የብሔራዊ መዝሙር፣ የአርሰ በርሰ የአንኳን ደሰ አለን ልውውጥ ጋር፣ መቅደላን ጥሶ የመግባት አንቅሰቃሴ ተደመደመ።

---

141 (በምዕራፍ II ማስታወሻዎች)

142 ደጃዝማች ካሳ ምርጫን ለመጥቀስ ነው

የምዕራፍ 11 ማስታወሻዎች

ቁጥር 137፣ ሰለዚህ የመጨረሻ የቴዎድሮስ ውሳኔ የራሳም ዘገባ ለየት ያለ ነው:: አንደኛ፣ በዛን ቀን የተገደሉ ሰዎች ቁጠር 198 ነው:: በሚያዝያ 8፣ ቴዎድሮስ 570 የአቢሲኒያ እስረኞቹ አንዲመጡ አስደረጉ፤ በመጀመሪያ 37 ታዋቂ የነበሩ ሰዎች እነ ከንቲባ ሀይሉና ባላምባራሰ ተሰማን ጨምሮ ተለቀቁ:: ከነሱ ጋር 186 ሰዎችም ተፈቱ:: በሚቀጥለው ቀን ከጥቂት የፖለቲካ እስረኞች በስተቀር ሁሉም እንዲፈቱ ትዛዝ ሠጡ፣ ያን ቀን 95 ተጨማሪ እስረኞች ተፈቱ:: ነገር ግን የእግር ብረቱን መፍታታ ጊዜ የሚወሰድ ሰለሆነ፣ ገና ያልተፈታላቸው እስረኞች መጮህና ማንጎራጎር ሲጀምሩ፣ ቴዎድሮስ ከቁጥጥር ውጭ ተናደዱና፣ በእግር ብረት የታሰሩትን አንድ ባንድ እያስጠሩ ጥፋታቸው እየተነበበ ቅጣቱ ይሰጥ ጀመር:: ቴዎድሮስ በቃ ሲሉ 198 የሚሆኑ ሰዎች ሀይታቸውን አጥተዋል:: ይህ ግድያ የተፈፀመው ከኛ ካምፕ ሁለት መቶ ያርዶች ርቀት ነበር ይላል ራሳም:: ሰውየው 300 ሰዎች ነው የሚለው ቁጥር ከዚህ በፊት የተገደሉትን ጨምሮ ካልሆነ በስተቀር በሚያዝያ ዘጠኝ በቅርብ ሁኔታውን የተከታተለው ራሳም የሚገልፀው እውነተኛ ይሆናል:: ቁጥሩ ማነሱ የደረሰውን ቅጣት አያቀለውም:: ያን ቀን ሌሊት ግን፣ ቴዎድሮስ ሲፀልዩ ነው ያደሩት:: በፀሎታቸውም ለሠሩት ሥህተት ይቅርታ ሲጠይቁ በጉልህ ይሰማ ነበር::

ቁጥር 141፣ መሸሻ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከመጀመሪያ ሚስታቸው ከወለዷቸው ልጆች አንዱ ነው:: ሌላዋ፣ አልጣሽ ቴዎድሮስ ስትሆን፣ ንጉሡ ለምኒልክ የዳሩላቸው ነበረች:: የነመሸሻ እናት፣ ገሠሠች፣ የእንግዳወርቅ ልጅ ስትሆን፣ እንግዳወርቅ ደግሞ ከቴዎድሮስ ጎን እስከመጨረሻው ድረስ ተዋግተው ከሞቱት የቴዎድሮስ ሰባት አለቆች እንዱ ናቸው:: እንግዳወርቅና ቴዎድሮስ ከሽፍትነት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚተዋወቁት:: ጋብቻው የፈረሰው፣ ቴዎድሮስ፣ እቴጌ ተዋበች አሲን ለፖለቲካ ሲባል እንዲያገቡ በተዋበች እያት በመነን ሲጠየቁ ነው:: ጋብቻው የፖለቲካ ቢሆንም፣ ተዋበች፣ በዘመኑ ቆንጆ ተብላ የምትደነቅ ሴት ከመሆኗ በተጨማሪ፣ በሁለቱ መሀል ፅኑ ፍቅር ነበር:: ካሳ ላይ በተደረገው፣ በተለይም በእቴጌ መነን (የተዋበች አያት) ንቀት ምክንያት፣ ሚስትየዋ ተዋበች ነች፣ አታሰድበኝ፣ ብላ በወላጆቿ ላይ እንዲነሱ ያደረገቸው:: ደጃች ካሳ በሽፍትነት በየቦታው ሲዘዋወሩ፣ ተዋበችን ደብቀው ያስቀመጡት የቴዎድሮስ ወዳጅ አይከል ኮልባ ይባሉ ነበር::

ምዕራፍ አስራ ሁለት



የንጉሰ ነገሥቱ ቤት ዘረፋ፣ ጥቁር ኮት ለባሾች፣ ሚቹ ጎሹ

በመጨረሻው ምዕራፍ በጣም ወሳኝ ሁኔታዎች ከተዘገቡ በኋላ፣ ወታደሮች ከየሬጅመንታቸው ተበትነው ለሁለት ወይም ለሶስት በመሆን፣ የሚዘረፍ ንብረት ለማግኘት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ጀመሩ። ብልጠት በተሞላበት ሁኔታ በነጠላ ወይም በቡድን በመሆን እያንደንዱን ቤት መበርበር፣ የቤት ዕቃዎችን መገለባበጥ እናም በግድየለሽነት የቅዱሳን ምስሎችን ይሰባብሩ ነበር።

ወዲያ ወዲህ ሲሉ፣ ወደ ንጉሰ ነገሥቱ መኖሪያ መጡ። ጠንካራ፣ እንደ በረት የመሰለ ግን ባለ ፎቅ ሆኖ የሳር ከፍከፍ ያለው ነበር። በአጠገቡም፣ የንጉሡ ወጥቤት፣ የከብቶች በረት፣ መካዝኖች፣ የሴቶቹ መኖርያ ቤትና እራት ማዕዘን ያለው ትልቁ አስር ቤት ይገኛሉ።

በግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ሴቶች እንድ ላይ ሰብሰብ ብለው ተገኙ። ሴቶቹ ከንጉሰ ነገሥቱ ቤት የመጡ ናቸው። ልብስ በለበሱና ባለበሱ ደንገጥሮቹ ተከባ፣ የሰሜንና የትግሬ ጎሹ የነበሩት የደጃች ውቤ ልጅ፣ እቴጌዋ ጥሩ ወርቅ ውቤ አለች። ሀያ ስድስት እመት ወይም ወደዛ ገደማ ዕድሜ የሚሆናት፣ ጠየም ያለች ከሁሉም በሳይ የምታምር ነች፣ ነገር ግን ገርጠት ብላ ከሳም ብላለች። በተማረኩ ሰዎች፣ ሰለ ባህሪዋ ወሬ ተዛምቶ ሰለነበር፣ ወታደሮቹ እንዳዩዋት የሚገባትን ክብር እንዲሠጧት ነው ያደረጋቸው። ለረዥም ጊዜ፣ ቴዎድሮስ ካልጠጡ በሰተቀር፣ እቴጌዋ ለቴዎድሮስ እንደጠባቂ መልእክ ነበረች። እንድ ወታደር እጥብቆ እንደ ገለፀው፣ እቴጌዋ እንደ "ደጉ መፅሐፍ" መካሪ ነበረች። ጠባቂና ለሚፈልጉት ነገር በሙሉ የማታሰልስ፣ ግዳጅ ሲመጣ እንደ ባሏ ደፋርና ጀግና ነበረች። ቴዎድሮስ ወደመቅደላ ለመምጣት ደብረታቦር ላይ ሆነው በሚዘጋጁበት ጊዜ እቴጌዋ መቅደላ ትኖር ነበር። ሁለት ጊዜ የሚሆን፣ በዝነኛው[143] የሸዋው ንጉሰ ምኒሊክ ከአርባ ሺ ጦር ጋራ (ምናልባትም የተጋነነ ቁጥር ይሆናል) ቦታው ተከቦ ነበር፣ አለቆችና ሽማግሌዎቹ እጅ እንስጥ ብለው መከረው ነበር፣ ነገር ግን እቴጌዋ በየቦታው

---

143 (ምን ይልክ) ምኒልክ መቅደላ በነበሩበት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

አየተገናኛች[144] ለንጉሰ ነገሥት ባሏ የማትታከት ታማኝና አክባሪ ሰለነበረች፣ የምኒልክ ከበባም ዋጋ ሳያገኝ፣ የከፉ መካሪዎች ሀሳብም ውድቅ ሆነ።

ከደንገጥሮቹ ጋር አየተጫወተ የነበረው፣ የኢትዮጵያ ዙፋን አልጋ ወራሽ፣ ጠንካራና ብልሀ የሆነ የሰምንት አመቱ ልዑል አለማየሁ ነበረ። የሁለቱን መኖር ሰር ሮበርት ናፒየር አንደሰማ፣ ካፒቴን ስፒዲ[145] (ባሻ ፈለቀ) ሀላፊነት ወስዶ የሚያሰፈልጋቸው ነገር እንዲደረግላቸው እንዲያደርግ ትዛዝ ተሠጠው።

ወታደሮች ወዲያና ወዲህ ሲዘዋወሩ፣ የተወሰኑት፣ ብዛት ያላቸው፣ አያንዳንዳቸው ሀያ ጋሎን የሚይዙ መአዛ ባለው ጠጅ የተሞሉ እንስራዎች ያገኛሉ። በደስታ በሚጮሀበት ጊዜ ሌሎች ሃምሳ የሚሆኑት የተገኘውን ጠጅ ለመጠጣት ተቀላቀሏቸው።

በመቅደላ፣ በሁሉም ቦታዎች ላይ፣ የተለያዩ የወታደሮች የግርግር ቡድኖች በሌይነት ተሰማርተውበታል። ግድየሌላቸው፣ ንብረት ፈላጊዎች፣ ስካራሞች፣ ሞራላቸው የወደቀ፣ እዛኞች፣ ስነ ሥርአት የያዙ፣ አላማ የሌላቸውና፣ የእስረኛ ቡድኖች ነበሩ። አነዚህ ሁሉንም በዝርዝር ለመግለፅ አድካሚ ስለሚሆን፣ ከነሱ ውስጥ መግለፅ የሚገባቸውን ነካ ነካ አደርጋለሁ።

የጠፈጁዎቹ ወይም የስካራሞቹ ቡድን በንጉሡ አዳራሽ ተሰብስበዋል፤ ንጉሡ ለራሳቸውም ሆነ ለሴቶቹ ያዘጋጁትን በርክት ያለ መጠጥ ለመቅዳት ነው። ብዛት ያላቸው እንደ ብራንዲ ኮሰተር ያለ ምርጥ አረቄ የያዙ እንስራዎች ተገኙ፤ አናም አረቄ በመቅመስ የሚታወቁ ሰዎች በጉጉት እያነሱ መቅመስ ጀመሩ። አየደጋጋሙ ቀመሱ፣ አናም እንደሚጠበቀው በብዛት የጠጡት አረቄ ውጤት መታየት ሲጀምር ጊዜም አልወሰደም። ነገር ግን ክሚገባው በላይም አልነበረም፤ ምክንያቱም ጥብቅ የሆነ የእንግሊዝ ሠራዊት ህግ አለ፤ ሰክሮ የተገኘ ሰው ከባድ ቅጣት ስለሚያስቀጣም ነበር።

ሌላው የወታደሮቹ ቡድን ደግሞ ወደ ንጉሡ ቤተመንግስት አዳራሽ ዘለው በመግባት በየቦታው ተበተነው የነበሩ ቁጥራቸው የበዛ ዕቃዎችና ንብረቶች ወሰዱ። ያገኙትንም አንድ ባንድ እያነሱ ከተመለከቱ በኋላ፣ ወይ ወደ ኪሳቸው ያስገባሉ አለዚያም ይወረውራሉ። የወረወሩትን ደግሞ ሌላው ተከትሎ አንደነሱ መርምሮ ወይ ወደ ኪስ አለዚያም መልሶ ይወረውረዋል። ከዚያ ሁሉ በጣም ትንሽ ነው ወታደሮቹ መያዝ የሚችሉት፤ ምክንያቱም

---

144 አቴንዋ ለባሏ ስትል (በ9ዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

145 በመቅደላ፣ ቴዎድሮስ፣ የባሻ ፈለቀን ስም ሲሰሙ በጣም እንደተናደዱ ተዘግቧል።

ሊመለሱ ከባድ ሻንጣዎች በጀርባቸው ተሸክመው በሙቶ የሚቆጠሩ ማይሎች መጓዝ ግዴታቸው ነበር።



ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር
ስፒዲ የያዘው የፈታውራሪ ገብርዬን ጋሻ፣ የለበሰውም የገብርዬን ለምድ ነው

ከቤተመንግስቱ ትይዩ የመቅደላ እስር ቤት አለ፤ በጣም ጠንካራ ድርቆ ቤት ሆኖ ከውስጡ ጩኸት ይሰማ ነበር። በጠጡት እረቂ ብርታት የተሰማቸው ወታደሮች በፍጥነት እየዘለሉ ወደ በሮቹ ሄዱና ስባበሯቸው። እየጠለቀ ያለው የፀሀይ ጮራ ወደ ውስጥ መግባት ሲጀመር፣ አለቃቂ የሆነ ከፍል ተጋለጠ።

ለረዥም ጊዜ እገልግሎት ላይ ያልዋለው ከፍል በተወላጆቹ አስረኛ ተጨናንቆ ነበር። አንዳንዶች በየግዛቶቹ ትልቅ ማዕረግ የነበራቸው ናቸው።

ሲመለሱ ከባድ ሻንጣዎች በጀርባቸው ተሸክመው በመቶ የሚቆጠሩ ማይሎች መጓዝ ግዴታቸው ነበር።



ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር
ስፒዲ የያዘው የፈታውራሪ ገብርዬን ጋሻ፣ የለበሰውም የገብርዬን ለምድ ነው

ከቤተመንግስቱ ትይዩ የመቅደላ እስር ቤት አለ፤ በጣም ጠንካራ ድርብ ፎቅ ቤት ሆኖ ከውስጡ ጩኸት ይሰማ ነበር። በጠጡት አረቄ ብርታት የተሰማቸው ወታደሮች በፍጥነት እየዘለሉ ወደ በሮቹ ሄዱና ሰባበሯቸው። እየጠለቀ ያለው የፀሀይ ጮራ ወደ ውስጥ መግባት ሲጀመር፣ አሰቃቂ የሆነ ክፍል ተጋለጠ።

ለረኻቦም ጊዜ አገልግሎት ላይ ያልዋለው ክፍል በተወላጆቹ እስረኞች ተጨናንቆ ነበር። አንዳንዶች በየግዛቶቹ ትልቅ ማዕረግ የነበራቸው ናቸው።

ልዑሎች፣ ደጃዝማቾች፣ ገበሬዎች እንድ ላይ ሆነው በመደናገጥ ቆመዋል፤ በእግር ብረት እንደታሰሩ ናቸው[146]። ለትንሽም ጊዜ ቢሆን በመደናገጥ፣ ከእስረኞቹ ባላነሰ ሁኔታ ግራ በመጋባት ወታደሮቹ ሁኔታውን ተመለከቱ። በእግር ብረት የታሰሩ እግሮችን ሲያዩ፣ በርሀራሄ፣ ድምፅ በሌለው ጥሪ ወደ ግዴታቸው እንዲመለሱ ሆነ። በተቻለ ፍጥነት፣ ወታደሮቹ የእግር ብረቶችን እየሰባበሩ መፍታት ጀመሩ። በሙሉ ልብ ምስጋና፣ የታሰሩት ወደ ውጭ ወደ ፀሀይ መውጣት ጀመሩ፤ እንደገና ነፃነት!

ብዙዎቹ በጣም ደካማ ስለነበሩ መቆም እልቻሉም። ለብዙ ቀናቶች በዚህ ቀፋፊ እስር ቤት በሚያሰፊራ ሁኔታ ተሸማቀው፣ በአጉል ተስፋ ያ ቀን እንዲያልፍ በናፍቆት ይጠባበቁ ነበር፤ ነፃ የሚሆኑበት ትልቅ ቀን ይመጣል ብለው ጠብቀዋል። እስር ቤት ጠባቂዎች እርስ በርስ ሲያወሩ ስለተሰማ ጠቆም ተደርገዋል። የእስር ቤት ዘበኞቹ ስለ እንግሊዘ ሀይል ምንም ዕውቀቱ የላቸውም ስለዚህ ስለውጤቱ እርግጠኛ እልነበሩም፤ ያም ሆነ ይህ የሚይረቡ ሀሜታዎች እንደሚወሩት ሁሉ እነሱም ስለጦርነቱ ያወሩ ነበር። ደረጃ ሳይመርጡ፣ ሁሉም እስረኞች እየቀረቡ የወታደሮቹን እጆች ሳሙ።

ግን፣ ምስጋናን በደንብ መግለፅ ይቻላል ወይ? ከእነዚህ፣ ፀጥ ብሎ፣ ግን እጅ መሳም የመሰለን ነገር ጋር፣ እንዴት ያለ ቃል ነው የሚስተካከለው? ደስተኞቹ ሰዎች በተቻላቸው መጠን በየራሳቸውን መንገድ ሄዱ፤ ንፁህ አየር በተነፈሱም ቁጥር ጉልበታቸው እየበረታ ነበር የሚሄደው። እንደ ባህላቸው፣ ደስታ በሚሆንበት ጊዜ እንደሚደረገው፣ አጨበጨቡ፤ እንኳን ደህና ወጣችሁ በሚል እንደበትም ተናገሩ፤ ከዚያም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነፃ ላወጧቸው ፈረንጆች እልልታ አሰሙ።

በመካዝኑ ተግኝቶ የነበረ ምግብ ለሰዎቹ ከተከፋፈለ በኋላ ከግቢው እንዲወጡ ተደረገ።

ይህ ትዕይንት የተከናወነው በቤተመንግስቱ ነው። በአምባው በሌላ ቦታ ግን፣ ሌሎች ድርጊቶች ታይተዋል። እንደዚህኛው ቀና ባይሆኑም፣ ስሜት የሚቀሰቅሱ ነበሩ። የተለያዩ ማለቂያ የሌላቸው የመኖሪያ ስፍራዎች ይታያሉ፤ ከሀር የተሰሩ፣ ከሸራም የተሰሩ ድንኳኖች፣ የኩርዶች የመሰሉ መኖሪያ ቦታዎች፣ መጠለያዎችና የመሳለሉት ነበሩ። በነዚህ ቦታዎች፣ በያንዳንዳቸው፣ ወንዶች ሰብሰብ ብለው እስተያዬት ይሰጣሉ፤ ሀሜታም፣ ትንተናዎች፣ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ወይም ደግሞ ያለቅሳሉ፤ ብቻ ማንኛውም የታያቸውን ነገር ያደርጋሉ። እየተጠጋሁ ስሄድም፣ ያየሁት ነገር ቁጥር ያጣ መደናገርና

---

146 እንደ ፕላውደን አገላለፅ፣ (በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ ይመልከቱ)

ጩኸት ሳይሆን ያልታሰብ ውካታና ግርግር ነበር፤ ይህም የሆነው የኩርድ ድንኳኖች እካባቢ ነበር፤ በኋላ እንደተረዳሁት እና እንዳሰደነቀኝም እነዚህ ድንኳኖች ለካ የንብረት መጠበቂያ ነበሩ። መሬቱ በሙሉ፣ በየቦታው በወደቁ ውድ በሆኑ ዕቃዎች ተሞልቷል። ከነዚህ ንብረቶች የሚንፀባረቅ የሚብረቀረቅ ብርሃን ይታያል።

በዊንድሶር ቤተ መንግስት ያሉ ውድ ንብረቶች ተሰብስበው፣ ከፋይ ላይ፣ አንድ ላይ ቢደረደሩ እንኳን እዚህ ቦታ የታየውን የውድ ንብረቶች ነፀብራቅ አይበልጡም። እነዚህ ብልጭልጭ ያሉ በቶን የሚቆጠሩ ንብረቶች ወርቅ ከሆኑ፣ የእንግሊዝ መንግስት ለዘመቻው ሰላወጣው ወጭም ያን ያህል ባልተጨነቀ ነበር። ነገር ግን፣ እንድ የሚያብረቀርቅ ከበድ ያለ የሻማ ማብሪያ እንሰቼ በእትኩሮት ሰመለከት፣ ዕቃው ዋጋ የሌለው መሆኑን ተረዳሁ። ምንም እንኳን ብዙዎቹ ውድ ከሆነ ብረት ቢሰሩም፣ አብዛኛዎቹ ወርቅ ቅብ ብቻ ነው የነበሩት።

በነዚህ ዋጋ በሌላቸው ንብረቶች ላይ ሰዎች ይጨቃጨቁና ይጋጩም ነበር። ከነዚህ መካከል ደግሞ፣ ጎላ ብለው፣ እሰከፊ በሆነ ከፍ ባለ ድምፅ የሚጮሁና የለበሱት ኮት እንደጅራት የወረደው ከፍል በነፋሱ የሚግለበለበው ጥቁር ኮት የለበሱ ሰዎች ነበሩ። እነሱም በሀር የተሰሩ ድንኳኖችን ለመጠቅለል እየታገሉ ነበር። እነዚህ ሰዎች፣ ወራዳ የሆነ ባህሪ ባያሳዩና በሚሰቀጥጥ ድምፃቸው የንቢጋባነት ሰሜት ባያንፀባርቁ ኖሮ፣ ለእድሜ ልክ ሰማቸውንም ባልጠቀሰኩ ነበር። እነዚህ ጥቁር ኮት የለበሱ አዋቂ ሰዎች፣ ለሰሙ እሃ፣ ፊላንትሮፒሰት ተብዬዎች፣ ሁሉም ባይሆኑ እብዛኞቹ እሰረኞቹ ነበሩ። ጥቂቶቹ የብሪታኒያ ዜጎች ሲሆኑ፣ ሶስት ሚሲዮናውያን፣ ፕራሻን፣ ጀርመን እና የሩሲያ መካኒኮች ነበሩ። አብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች ወታደሮቹ ከመድረሳቸው በፊት ብዛት ያለውን የተዘረፊ ንብረት በእጃቸው አድርገው ነበር። ከእግራቸው ሰር ተከምሮ ይታይም ነበር፤ ሌላው ሰወር ያለው ደግሞ በጥቆር ኮታቸው ተሸፍኖ ነበር። እንደተባለው ከሆነ፣ ከእነዚህ የተረገሙ ሰዎች አንደኛው፣ ፈሪህ እግዚአብሔር ቀርቶ የዲያብሎስ ሰይጣናዊ እይን እንኳን ፍርሃት የሌለበት፣ የተቀደሱትን የእቡነ ሰላማን የሪሳ ሳጥን በድፍረት በመከፈት፣ የእሰከሬኑ እንገት ላይ የነበረውን ብዙ ሺ ዶላር የሚያወጣ የአልማዝ መስቀል ከአንገታቸው በጥሶ ወሰዷል።

የነዚህ ውድ ንብረቶች ዜና በመቶዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ሰዎችን ወደቦታው እንዲመጡ አድርጓል። ጀኔራል ናፒየር፣ ሰታቪሊ፣ ሰናይደር፣ ዊልቢ ሳይቀር ከረዳቶቻቸው ጋር ለማየት መጡ፤ እነዚህ ሰዎችና የጋዜጠኞች ቡድን አባሎች፣ ለጋዜጠኞች ቡድን ከብርም ሲባል፣ ሌሎቹን ጀግኖች

ካባሊጋቸው ባህሪ ተለይተው፣ አንድ ዕቃ አንኳን እንሰተው ወደ ኪሳቸው አልጨመሩም።

በአሃዝ ለመግለፅ ያህል፣ በየቦታው ተብትነው ከነበሩት ንብረቶች፣ አንድ አሰረኛው አንኳ ለመሰብሰብ ሊደከምባቸው የሚገባ ንብረቶችም አልነበሩም። ከድንኳኖች በአንደኛው፣ በተለያዩ ቀለሞች የነደደ ይሁዳ አንበሳ ምስል የተጠለፈበት የንጉሰ ነገሥቱ አርማ ተገኘ። በሌላው ድንኳን፣ የንጉሰ ነገሥቱ ተመሳሳይ የይሁዳ አንበሳ ምስል የተቀረፀበት ማህተም ተገኘ።



የአፄ ቴዎድሮስ ማህተም

ከንፁህ ወርቅ የተሠራ ጽዋ በሚሰተር ሆልምስ እጅ ገብቷል። ላዩ ላይ በጥንታዊ ኢትዮጲክ ቋንቋ የሚከተለው ፅሁፍ ነበረበት።

የንግስት ብርሃነ ሞገስ ልጅ
የንጉሰ አድያም ሰገድ ኢያሱ ጽዋ
ጎንደር ለቁስቋም ገዳም የተሠጠ
ነብስና ስጋዬ ንፁህ ይሁን
15ኛው ክፍለ ዘመን



በመቅደላ የንጉሥ ቤት ዕይታ

የ300 መቶ አመት እድሜ ያለው የአቡኑ ቆብ፣ ከንፁህ ወርቅ የተሰራ ሲሆን፣ ምናልባትም ክብደቱ ከስድሰት እሰከ ሰባት ፓውንድ ይሆናል፤ ከዚህ በተጨማሪ አራት ዘውዶች፣ ከነዚህ ሁለቱ በዕውቅ በጥራት የተሰሩ ግምታቸው ብዙ ገንዘብ የሚሆን ከፍተኛ ዋጋ ሰላላቸው በብሪታንያ መዚየም



የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ



ከወርቅ የተሠራው የአቡኑ ዘውድ
(ምንጭ ዋቢ መዕሐፍት ተ.ቁ. 16)

መቀመጥ የሚችሉ ናቸው። በዕንቁ ያጌጠ ትንሽ የመፃፊያ ጠረጴዛም ተገኘ፤ በውሰጡም ከአውሮፓውያን መንግሰታትና ሰዎች ምሲጋና ያለባቸው ደብደቤዎች ሞልተውት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ የተለያዩ የሚያማምሩ ጋሻዎች ነበሩ።

ቁጥር የሌላቸው፣ ከወርቅ፣ ከብርና ከኑሓስ የተሰሩ መሰቀሎች፣ በጣም ተውበው የተሠሩ የዕጣን ማጨሻዎች፣ ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ምንቸቶች፣ ጀበናዎች፣ ሰሀኖች፣ የተለያዩ ኩባያዎች፣ ውድ ከሆነ ብረት ተቀርጸው የተሠሩ መጠጫዎች፣ የበሄሚያ ጠርሙሶች (ብርጭቆዎች)፣ ከሰቨረስ የመጡ ሸክላ ሰሀኖች፣ የሰታፈርድሻየር የሸክላ ሰራዎች፣ ሻምፓኝ፣ በርገንዲ ወይን፣ የግሪክ፣ የሰፔይንና የኢየሩሳሌም ወይን፣ የዮርዳኖስ ውሀ የያዙ ጠርሙሶች፣ አረቂና ጠጅ የያዙ ማለሮዎች፣ ጌጣጌጦች የሞሉባቸው ሳጥኖች፣ የወይን ጠጅ፣ ሮዝ፣ ነጭ ሌላም ቀለሞች ያላቸው ከሀር የተሰሩ ድንኳኖች፤ የፔርሺያ፣ የኡሻክ፣ በሩሳ ኪደርሚኒሰተር እና የሊዮን ምንጣፎች፤ ከአንሰሳ ፀጉር የተሰሩ ካባዎች፤ ከአንበሳ፣ ከአነርና ከተኩላ ቆዳ የተሰሩ ቆቦች፤ በሚያሰደንቅ ሁኔታ በወርቅና[147] በብር አጊጠው የተሠሩ ኮርቻዎች፤ ብዛት ያላቸው በብር የተሰሩ ጋሻዎች፤ ውበትና ብሩህ ቀለም ያላቸው በበጌምድርና በጎንደር ባለሙያተኞች ተውበው የተሠሩ ድባቦች፤ ሰይፎችና ጎራዴዎች፣ የተለያዩ ባለሰለት መሣሪያዎች፣ የፐርሽያ፣ የደማስቆ እና የህንድ ጩቤዎች ከወይን ጠጅ ከፋይ ከተሰሩና በላያቸው ላይ የወርቅ ቁልፍ ያለባቸው አፎዶች ጋር፣ የንጉሣዊ የብራና ፅሁፎች ከምር፣ የተደረደሩ በአማርኛ የተፃፉ መፅሐፍ ቅዱሶች፣ የፀሎት መፃህፍቶች፣ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው የፎቶ አልበሞች፣ በጠርሙሰ ላይ የተሳሉ ምሰሎችና የአሜሪካ፣ የአንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የጣልያን የአካባቢ እይታ ፎቶግራፎች፣ በጥበብ የተሠሩ ዴሰኮችና ጠረጴዛዎች ነበሩ። ሰፋቱ አየጨመረ በሚሄደ ቦታ፣ በሺ የሚቆጠሩ አነዚህ ዕቃዎች በየቦታው ግራ በሚያጋባ ሁኔታ፣ በአለታማው አምባ፣ በዳገቱና በኮረብታዎች ወደ ካምፕ በሚወሰደው የሁለት ማይሎች ርቀት ባለው ቦታ ሁሉ ተንጠባጥበው አሰኪፕ ድረስ ተብተነዋል።

ከዚህ ትዕይንት በኋላ፣ የቅርቡ የመቅደላ ጌታ አሰከሬን[148] በሸራ ቃሪዛ ላይ ወደተጋደሙበት ቦታ ወደ ሰሜን በር አመራሁ። በዚህም ደግሞ፣ ሌላ፣ መኮንኖችና ሲቪሊያኖች አርሰ በርሰ እየተጋፉ ያሉበት ግርግር ቡደን ነው

---

147 አፄ ቴዎድሮስ ለራሳም ከሠጡት አንዱ ሥጦታ በወርቅ የተሠራ ኮርቻ ነበር።

148 ምርመራውን ያደረጉት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ያየሁት። እነሱም ደም የነካውን የቴዎድሮስ ቀሚሻ ቁራጭ ለማግኘት ያለማሰለስ እየታገሉ ነበር[149]።

አስከሬኑን የሚጠብቅ ምንም ዘበኛ አልተመደበም። ትንሽ እንኳን ቢሆን ከብር ሳይሰጡ አስከሬኑ እርቃኑን ቀርቶ ነበር። በቃሪዛው ላይ እንደተጋደመ፣ ጨካኝ አአምሮ ላላቸው ሰዎች ሰድብና ሹፈት ተጋልጦ ነበር። ይህን ያዬ መኮንን፣ ለሰር ሮበርት ናፒየር ተናግሮ፣ ጀኔራሉም አስከሬኑ እንዲለብሰና በነጋታው ለቀብር እንዲዘጋጅ ትዛዝ ሰጠ። [150]

ከዚህ ተነሰቼ በተመደቡበት ቦታ ሆነው አስከመጨረሻው ሰአት ድረስ ለእለቃቸው ሲዋጉ የሞቱ የቴዎድሮስ ታማኝ ተከታዮችን አስከሬን ለመርመር ሄድኩኝ። እለቃቸው፣ በደሀናው ጊዜ ዙሪያቸውን ባሉ ሰዎች የመወደድ፣ የመከበር የመፈራትና ገናናት ባህሪ ነበራቸው። የሞቱት እዛጉች፣ በየቦታው በተለያዬ እወዳደቅ ነበር የሚታዩት፤ ነገር ግን የተለየ ረጋ ያለ ገፅታ ይታይባቸው ነበር። ቁስላቸው ብዛት ያለውና አሰቃቂም ነበር። ዋና እዛጉች በቁጥር ሰባት ነበሩ[151]፤ እነሱም አስከመጨረሻው ድረስ በቆራጥነት ከተከላከሉት ከምሽጉ ማማ አጠገብ እንድ ላይ ነበር የወደቁት። የለበሱት የሀር ልብሰና የደረቡት ያጌጠ ለምድ በደማቸው ርሷል፤ ዙሪያውን ያለው ድንጋይ እንኳን ሳይቀር ላደረጉት ግብግብ ምሰከርነት በተመሳሳይ ሁኔታ በደም ተረጭቷል።

ኪታች ማማውን ከበብ እድርጎ በተሠራው የካብ መከላከያ ደርዘን የሚሆኑ ተዋጊዎች ወድቀዋል፤ እንጎላቸው ተከፍቶ፣ እግርና እጃቸው ተገንጥሎ ሌሎችም አሰፈሪ የሆነ ቁስል ይታይባቸዋል። ከፍ ብሎ ባለው መከላከያ፣ አሰራ ሶስት የሚሆኑ የወደቁ ተወላጆች አሉ፣ መቅደላ ውሰጡም፣ ተንጠባጥበው ምናልባትም ቁጥራቸው ወደ ደርዘን የሚሆኑ አሉ።

ወደ ምሽጉ መግቢያ መከላከያ ሆኖ የተሰራው አጥር እንደነገሩ የተገነባ ቢመሰልም፣ በደንብ እንደ አውሮፓና አሜሪካ ወታደራዊ መሀንዲሶች ሊሰሩት በሚችሉት ሁኔታ በደንብ ዕቅድ ያለው ነበር። ያም እንግዲህ ቴዎድሮስ በነበራቸው የግንባታ መሳሪያዎች ነው ሊሰራ የሚችለው። ወደ መከላከያው ቦታ ማለፊያው በሁለት አለቶች ስር ነው የሚያልፈው፤ እነዚህ አለቶች ደግሞ ከመግቢያው በኩል 15 ጫማዎችና ከመከላከያው በላይ 30 ጫማዎች ከፍታ ነበራቸው።

---

149 (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

150 የአፄ ቴዎድሮስ ቀብር ትዛዝ የተሠጠው (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

151 ቴዎድሮስ በመጨረሻዎቹ ሰአታት፣ (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

መግቢያው ሰድሰት ጫማዎች ከፍታ ሲኖረው በሁለት አንጨቶች ነበር የተሠራው፣ በላዩም ላይ፣ ከላይ ወደ ታች የሚወርዱ ሁለት ብረቶች፣ ሁለት በአግድሞሽና ወደ ጎን የሚሄዱ ማጠናከሪያዎች አሉበት። ወደ ውስጥ የሚከፈት ሆኖ፣ ዳር አሰክ ዳር በሚቀመጥ በአግዳሚ ጣውላ ነው የሚዘጋው። ገለጥ ያለው ቦታ ላይ የሰምንት ጫማዎች ሰፋት ነበረው። በማለፈያው በውስጠኛው በኩል፣ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ ከድንጋይ የተሠሩ መሻገሪያዎች አሉ፣ በእያንዳንዱ የአለት ግድግዳ አናት ላይ ደግሞ ምሽጎች ተሠርተውባቸዋል።

በአጠቃላይ ሲታይ፣ በደንብ መከላከል የሚያሰችል ቦታ ነበር፤ አንድ ባለ 12 ፓውንደር መድፍ ብቻ የማይታለፍ ሊያደርገው ይችል ነበር። ነገር ግን ቴዎድሮስ መድፎቻቸውን ፋላና ሰላሴ ላይ ጠምደው አሮጌ ላይ ተሸነፉ። መድፎችን ወደ መቅደላ ለማሰመጣት ዘግይተው ነበር፤ ምክንያቱም ለሁለት ቀናት በውድ ወዳጃቸው በእርመናዊ ራሳም አማካኝነት የሰላም ድርድር አየተካሄደ ነበር። መጨረሻ ሰላም የማይፈጠር መሆኑን ሲገነዘቡ በሶስተኛው ቀን መድፎችን ለማሰወሰድ ጀምረው ነበር፣ ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደጠቀሰኩት፣ ሰፒዲና ሎች 3ኛው ፈረሰኛን አየመሩ ድንገት ሳያስቡ ደርሰውባቸዋል።

የሞቱት ሰዎች ቁጥር ከላይ ቡተለየዬ ሁኔታ አንደተገለፀው ወደ ሰልሳ ይደርሳል፤ የቆሰሉት ቁጥር ግን የዛን እጥፍ ያህል ነበር። የብሪታኒያዎቹ ጉዳት ደግሞ አሰራ ሰባት ቁሰለኛ ሲሆን የሞተ የለም። ምሽጉ ላይ፣ የከባድ መሳሪያ ድበደባው ከሁለት ሰአታት በላይ ነበር የተደረገው። የሚገርመው በሰፍራው ከነበሩ ከ4ሺ ሰዎች መሀከል የንፀህ ሲቪሊያኖች ህይወት በከንቱ አልጠፋም።

በአሮጌ ውጊያ ከቆሰሉት መሀል ወደ መቶ የሚሆኑት በሰላምጌ ጎጆዎች ተጠልለው ነበር። ከእንድ ወይም ከሁለት ቁስለኛ በላይ በማሰጠለል ከሁለት አንዱ ቤት እንደሆሰፒታል ነበር ያገለገሉት።

ወደምስራቅ በኩል፣ ከሰላምጌ ቢታች በነበሩት መንደሮች ሮኬቶች ጠቅላላ ጥፋት ነበር ያደረሱት። አንድ አላማውን የሳተ ሮኬት በአንዱ በቀላሉ በአሳት በሚያያዝ ጎጆ አልፎ አሳት በማስነሳቱ ከዚያም ነፋሱ አያቀባበለ ሌሎቹን ጎጆዎች አንዲቃጠሉ በማድረጉ በአጭር ጊዜ መንደሩ አንዳለ አመድ ነው የሆነው።

የፈረንሳዩ ፕሮፌሰር ባርያል[152]፣ ከሌሎቹ አውሮፓውያን ተነጥሎ ወደ ካምፕ አልወረደም ነበር። በትክሳት ህመም ይሰቃይ ስለነበር አንደ ቅዠትም

---

152 ቴዎድሮስ ራሳምን የተቀበሉት (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ጀምሮታል። ወደ ስላሴ ጠጋ ብሎ በሚገኝ ሰላምን ስፍራ፣ በአንድ ጎጆ ውስጥ በቀፋፊ ሽታና የምግብ ትርፍራፊ ተከቦ፣ በተባይ በተወረረ ምንጣፍ ተሸፍኖ ነው የተገኘው። ወዲያውኑ ወደወታደራዊ ሆስፒታል ተወስዶ ህክምና ከተደረገለት በኋላ ከአንድ ሳምንት የጠና ህመም ሊያገግም ችሏል።

ይህ የገለጥኩት ነገር ሁሉ ሶስት ለአታት ነው የወሰደብኝ። ለሊቪሊያኖቹ አማራጭ ነበረን፤ መቅደላ ቆይቶ በአንድ ጎጆ ማታውን ማሳለፍ፣ አለዚያ ሁለት ማይሎች ርቀት፣ ከፋላ ግርጌ ወዳለው ካምፕ ማምራት ነበር። ብዙ ጎጆዎችን ከተመለከትን በኋላ፣ ወደ ካምፑ ለመሄድ ወሰን።

ስላምኔ ስንደርስ የካምፕ አጃቢዎች ጋረ ተገናኝን። ካምፕ ተከታዮችና የዚህ ገናና ጦርነት ጓዝ በዝግታ ወደ ላይ ወታደሮቹ ወደ ሰፈሩበት የመቅደላ አምባ ይጓዛል። በቅሎዎችና ፈረሶች፣ ቃሬዛና የሰው መሸከሚያውች የሚያባራ በማይመሰል ሁኔታ ይጓዛሉ። ከሰላምኔ በታች ዝሆኖችን ጀርባቸው ላይ ካለው ከከባድ ሸክማቸው ጋር አገኛናቸው፤ በጨለማው፣ ምትህታዊ ምስል ይመስላሉ። በዚህ ሰላም ባለበት ምሽት ደግሞ፣ ሰደተኞቹ ለኢንግላንድና ለህንድ ወታራዊ ማዕበል ደንታ ሳያሳዩ ወደ አሮጌ ሸለቆ ያመራሉ።

ፋላን አንዳለፍን፣ ቁልቁለቱን በምን ግዴ ህይል መንደርደር ጀመርን፤ ያም ፋላና ስላሴን በጥዋቱ ጥለው የወጡ የአቢሲኒያኖችን ካምፕ አስከምናይ ድረስ ነበር። ካምፑ በአሳት ደምቋል። ራቅ ብሎ በምስራቁ አድማስ በኩል ደግሞ ረዥም የአሳት መቀነት ይታያል። ያም ለተወላጆቹ ማስጠንቀቂያ ችቦ ነበር። በዚያ ሆነው አይናቸውን ያፈጠጡ አሮሞዎች በካምፓችን ውስጥ ስለሚታየው ሰፋ ያለ የአሳት ባህር በመገረም ሁኔታ ይመለከታሉ።

የመጀመሪያው ውጊያ በተካሄደበት በአሮጌ ሜዳ ላይ የተተከለውን የአቢሲኒያኖች ካምፕ አልፈን ሄድን። ካምፑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻቸው ከተቀበሩበት ቦታ አጠገብ ነበር። የኛ ካምፕ፣ ከዚህ ግማሽ ማይል ርቀት ላይ ነበር። ካምፑን ስንቃረብ ሙሾና ለሞቱ ሰዎች የሚደረግ ለቅሶ ሰማን። በፈረሶቻችን ኮቴ ስው ረግጠን የምንገድልበት አደጋ ባለበት ሁኔታ በውሰጡ እያለፍን አያለ፣ ድንገት በረዶ የመሰሉ ነጫጭ ድንኳኖች በብዛት አየን። ብዛት ያላቸው ድንኳኖቹ ረጭ ባለ ፀጥታ ምድሩ ላይ ተተከለው ይታያሉ። በዚህ ባገኙት መጠለያ ተሰንራፍተው፣ ድብን ያለ አንቅልፍ ውሰጥ ሆነው፣ በህልማቸው፣ ያለምንም ጥርጥር፣ መቅደላ ሲወድቅ መህሪ አንግሊዘኞቹ ያላዩትን ባህሪ በፀጋ እያመሰገኑ ነበር።

የምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች

ቁጥር 143፤ *(ምን ይልሽ) ምኒልክ መቅደላ በነበሩበት ጊዜ በጣም ተወዳጅ ወጣት ሰው አንደነበሩ ነው የሚታወቀው። ከአቡነ ሰላማ ጋርም የተለየ ወዳጅነት ነበራቸው። ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጃቸውን አልጣሽን ድረውላቸው ነበር። ከአሁኑ ሁኔታ ከሁለት አመት በፊት፣ በኦሮሞዋ ንግስት ወርቂት አርዳታ ከመቅደላ አምልጠው ነው የወጡት፤ አልጣሽንን ግን ይዘው አልሄዱም። የምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ ዋነኛው ምክንያት፣ በቴዎድሮስ፣ ሽዋ ላይ ተሹመው የነበሩት ደጃች በዛብህ፣ ቴዎድሮስን ኪድተው የሸዋ ንጉሥ ሲሆኑ ነው የሚባል ወሬ ሲሰሙ ነው። ምናልባትም ምኒልክ ከመቅደላ ይልቅ አቡኑን የፈሰጉ ይመስላሉ። በመቅደላ ሲያድጉም በአፄ ቴዎድሮስ አንደ ልጅ ነበር የተያዙት፤ ከራሳቸው ልጅ ከመሸሻ ቴዎድሮስ ጋር እኩል ነው ያደጉት። ልጃቸውን ሲድሩላቸውም ወደፊት የምኒልክን ሁኔታ አሰበው ይሆን? ምኒልክ መቅደላን ቢምከሩም፣ የአፄ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ ሀዘን ተቀምጠዋል። አንደ ጳውሎስ ኞኞ መፅሐፍ፣ የምኒልክ የመጨረሻ መሀላ፣ "ቴዎድሮስ ይመት" ነበር።*

ምኒልክ 30ሺ ጦር ይዘው ነበር መቅደላን ለመውሰድ ያሰቡት። ሳይጠቁ ለምን ወደሸዋ አንደተመለሱ ግልፅ አይደለም። የዚህን ዜና፣ ናፒየር በምርጫ ወርቁ በኩል አግኝቶ ነበር። ምኒልክ ወደ መቅደላ ሲዘልቁ፣ ከመቅደላ ባላባት ከወርቂት ጋር ግንባርም ፈጥረው ነበር። መቅደላ የነበሩ ባለሥልጣናት ቴዎድሮስ ቶሎ አንዲደርሱ ሲመኙ ሌሎቹ ደግሞ የምኒልክን መምጣት አንደተመኙ ተዘግቧል። ከምኒልክ ጋር ሲመላለሱ ከነበሩት የቴዎድሮስ ባለሥልጣኖች ቢትወደድ ሀይሉ የሚባል ነበር፤ አቡም ቴዎድሮስ ሲመለሱ፣ መቅደላ ከመድረሳቸው በፊት አምልጦ ለናፒየር ስለመቅደላ መረጃ አቀብሏል። ዋሸሙ ጎበዜም ቢሆኑ ለአቡነ ሰላማ በላኩት ሚስጥራዊ ደብዳቤ፣ አቡኑ መቅደላ ላይ አመፅ ቢያስነሱ ጎበዜ መቅደላን ለማጥቃት ዝግጁ አንደነበሩ ነው።

ቁጥር 144፤ *አቴጌዋ ለባሏ ሰትል ታማኝ ወታደሮቻን ሰብስባ ጥሩ ቁርስ አብልታ፣ ጠጅ አጠጥታ፣ መቅደላ አንዲጠበቅ አድርጋለች። ወጣቷ አቴጌ ጥሩ ወርቅ የለንግሊዞችን መምጣት ሰምታለች። መቅደላ ላይ የነበሩ የተወለኑ የቴዎድሮስ ሰዎች መቅደላን ለማስረከብ መደለያቸው አንደታወቀ፣ ልዑል አለማየሁን የቤተመንግስት አልብሳ፣ ፀጉሩንም በብዙ ፎቶዎች አንዳየነው አስላጭታ። ደንቾቹ ወደተሰበሰቡት ቦታ ወሰዳ፣ የአባትህ ተወካይ መሆንክን አሳያቸው፤ በመሀከላቸው ገብተህ ከተደላደለው ቦታ ላይ ኮርተህ ቁጭ በል በማለት መከራ፣ አሷ ግን፣ ሰብሰባ መግባት ለሴቶች ከልከል ሰለሆነ፣ ከድንኳን ጀርባ አሾልካ ትመለከት ነበር። የልጇን በተደላደለው የአባቱ ቦታ መቀመጥ ያዩ ሽማግሌዎች ተደናገጡ። በጣም የገረማቸው ደግሞ፣ ጎበዙ የሚባለው የቴዎድሮስ አንበሳ ገባ ብሎ ከልጁ አጠገብ መቀመጡና፣ ከዚያም፣ ልዑሉ፣ አንበሳውን፣ ከአባቱ አንዳየው አጁን ጣል ሲያደርግበት ሲያዩ*

ነበር። ከዚህ በኋላ በስብሰባው የነበሩት በሙሉ ለቴዎድሮስ ታማኝነታቸውን አረጋገጡ። ስብሰባው እንዳለቀ ግን፣ ለስብሰባው ያልመጡት ሰዎች፣ የሆነውን ስለሰሙ፣ በፍርሃት እቴጌዋ ያለችበት ድረስ በመሄድ ለቴዎድሮስ ታማኝነታቸውን ሲምሉ ሲገዙ ነበር። እቴጌዋ በዚህ መልከም ይሆናል ሊሉማውን የበተነቸው። ከባሏ ጋር ብዙም ፍቅር አንዳልነበራቸው፣ በተለይም ቴዎድሮስን ትንቅ እንደነበር በተለያዩ ፅሁፎች ተገልጧል። ቴዎድሮስ በወታደራዊ ባህሪያቸው የንጉሳዊ ልብስ መልበስ የማይፈቅዱ ሆነው ሳለ፣ እቴጌዋ ግን ይህንን ትቃወም እንደነበረ ነው። ይባስ ብሎ፣ ቴዎድሮስ፣ ቁባታቸውን ወይዘሮ የተመኙን ከእቴጌዋ ጋር አንድትቆይ መቅደላ መላካቸው ነው።

እቴጌ ጥሩወርቅ፣ የዘውድ ተስፈኛው የደጃዝማች ውቤ ልጅ መሆኗ መዘንጋት የለበትም። ከሌሎች መሳፍንቶች በላይ፣ እቡኑን እባ ሰላማን በእጃቸው አድርገው ስለነበር፣ ለዙፋኑ የበለጠ ዕድል ነበራቸው። በእቡን ካልተቀቡ መንሥም አይቻልም። የሆኖ ሆኖ ለባንልበተኛው ለቴዎድሮስ ማስረከብ ነበረባቸው። ቴዎድሮስ ውቤን ሲያሸንፉ፣ በውቤ ስር የነበረው የትግራይ ግዛት በሳቸው ስር ነው የሆነው። ደጃች ካሳ፣ ውቤን እንዲገበሩ ቢልኩባቸው፣ ውቤ አልገብርም በማለታቸው፣ ራሳቸውን እንደ ንጉሥ ዳዊት የሚቆጥሩት ቴዎድሮስ፣ ውቤን፣ "ነልያድ" ጦርነት ላይ እንገናኛለን ማለታቸውም ይጠቀሳል። አንግዲህ አባቷንና ወንድሞቿን ያሸነፉና ያሰሩ ሰው ነው ያገባችው። ፍቅር ባይኖራትም፣ ለታማኝነታ ጥርጣሬ አልነበረም። አሳዘኝ ሆኖ፣ እቴጌዋ፣ መቅደላ ከመያዙ በፊት የሳለ ሀመም ነበራት።

ቴዎድሮስ ለልዑል አለማየሁ ያላቸው ፍቅር ይህ ነው አይባልም። ለአውሮፓውያኑ፣ መሸሻና አለማየሁን ወደ አውሮፓ ወስዳችሁ አስተምሩልኝ ብለው መናገራቸው ተዘግቧል። ይህም፣ ለፄ ቴዎድሮስ መጨረሻቸውን በደንብ የተገነዘቡ ሰው እንደነበሩ ይጠቁማል።

ቁጥር 146፣ አንደ ፕላውደን እገላለፅ፣ ቴዎድሮስ ባላባቶቹን ለጊዜው አስረው ሥልጣናቸው ሲጠናከር ለመፍታት አስበው ነበር ይላል። ምናልባትም ይህ ሀሳባቸው ሊሆን ይችላል ለነዚህ ሰዎች በእስር ቤት በሕይወት ሊቆዩ ያስቻላቸው። ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ ብዙዎቹ ባላባቶች ሲዋጉ በምርኮ የተያዙ፣ ወይንም ንጉሡን ሲከዱ ወይም አሴራቸው ተብለው ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ገና በፍራቻ ሊከዱ ይችላሉ ተብለው ነው። ቴዎድሮስ፣ እነዚህን ሰዎች መግደልም ይችሉ ነበር። ከታዋቂ አስረኞች መካከል አንዱ ምኒልክ ነበሩ። አሳቸው ግን ከቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጅ፣ ከመሸሻ ካሳ ጋር እኩል ነው ያደጉት። ምኒልክን የሸዋ ባላባቶች ናቸው አሳልፈው የሰጡ፣ ከውጊያ በኋላ ቢሆንም። እንደሚባለው ከሆነ፣ ምኒልክ በተያዙ በማግሥት፣ ቴዎድሮስ፣ ያ ልጅ አንዴት አደረ ብለው ሲጠይቁ፣ በአግር ብረቱ ምክንያት ሲያለቅስ አደረ ተብሎ ሲነገራቸው፣ ከዚያን ቀን ጀምሮ በአግር ብረት አንዳይታሠሩ ሆነ። ቴዎድሮስ፣ አስረኞቻቸው እንዴት አንደሆኑ መጠየቅ ባህሪያቸው መሆኑን በተለይም ከአውሮፓውያን እስረኞች ጋር የተለዋወጧቸው መልክቶችና ደብዳቤዎች ያስረዳሉ።

ንጉሡ ሰዎችን በእሥራት ብቻ ማቆየታቸው ከደግነት ጋር የተያየዘ ይመስላል፤ በርግጥ ለአስረኞቹ ግን የከፋ ነገር ነበር። ሆኖም አስረኛቹ ሌላውን አማራጭ ይዋሙ ያስተዋሉ አይመስልም።

ቁጥር 149፣ *ቀደመው የቴዎድሮስ አስከሬን አጠገብ ከደረሱ ሰዎች አንዱ፣ ካፒቴን ፍራንክ ጀምስ ይባላል። ካፒቴኑ ለናቱ በፃፈው ደብዳቤ፣ "ራሴ የቆረጥኩትን የቴዎድሮስን ፀጉር ሹሩባ ለሴቶቹ ልጆቼና ላንቺ ለውድ እናቴ ልኬያለሁ" ብሏል። የቴዎድሮስ አስከሬን ምሰል ላይ ሙሉ ፀጉራቸው የማይታየው ለዚህ ነው።*

ቁጥር 150፣ *የአስከሬን ምርመራውን ያደረጉት ዶክተር ብላንክና ዶክተር ሉምስዲን ነበሩ። በምርመራውም፣ በሽጉጥ ጥይት ራሳቸውን እንዳጠፉ ተረጋግጧል። ጥይቱ ባፋቸው በኩል ገብቶ በጭንቅላታቸው በጀርባ በኩል ለመውጣቱ ተረጋግጧል። የሚገርመው ነገር፣ ዶክተር ብላንክ ፊታቸውን እያገላበጠ ሲመለከት፣ ፊታቸው ላይ፣ በቅርብ ጊዜ ብዙም ያላሳዩት፣ ደብዘዝ ያለ የደስታ የፈገግታ ምልክት ማየቱን ገልጧል። ሌሎቹ ግን የንቀት ምልክት ነው ብለውታል። ሆኖም ከእዲስ መጫዎች ይልቅ፣ ብላንክ ቴዎድሮስን የበለጠ ያውቃቸዋል።*

ቁጥር 151፣ *የእዬ ቴዎድሮስ አስከሬን እንዲቀብር ትዛዝ የተሠጠው ለመልከተኛው ራሳም ነበር። በሚገርም ሁኔታ፣ ቴዎድሮስ ከሁለት ሳምንታት በፊት ከራሳም ጋር ሲያወሩ፣ ራሳምን፣ "እኔ ሰሞት፣ ሰላደረስኩብህ በደል ሬሳዬ ላይ ቆመህ ትሰደበኝና ታዋርደኛለህ፣ ከፉ ሰው ሰለሆነ እንዳይቀበር ትላለህ።" ብለው ተናገረው ነበር። ይህንንም ሁኔታ አብሮ የሰማው ቫልድማየር፣ ራሳምን፣ ንጉሡ ምን እንዳሉት አስታውሰታል። ራሳም በተቻለው መጠን ንጉሡ በሥርአት እንዲቀበሩ ሞክሯል። ቴዎድሮስ ራሳምን ወዳጄ ብለው ስለሚጠሩት፣ ሰኢትዮጵያውያኑ፣ ወዳጅ የሚለው ቃል ከንቱ እንዳልሆነ ለማሳየትም ነበር።*

ቁጥር 152፣ *ቴዎድሮስ በመጨረሻዎቹ ሰኢታት፣ ወታደሮችን፣ የነቸሁልኝን መህላ አንስቼአለሁ፤ ሂዱ ብለው ሲያሰናብቱ፣ ሰባት አለቆቻቸው ግን አሰመጨረሻው አስከቴዎድሮስ ጋር አንዋጋለን ብለው ወሰነዋል። ከአነዚህም መካከል፣ ራስ አንግዳ (ጠቅላይ ሚኒስትር)፣ አንግዳወርቅ (የቴዎድሮስ የመድፍ ሀላፊ)፣ የቋራው ራስ ባራከ፣ ደጀዝማች አብዬ፣ ኢጋፋሪ መሸሻ፣ የቴዎድሮስ ጠመንጃ ያዥ አማረ፣ የቴዎድሮስ አልፍኝ አስከልካይ ወልደገብረል ነበሩበት። ደጀማች አብዬ፣ ፊረንጆቹን እንገደላቸው የሚል ሀሳብ ሰለሠጡ፣ ቴዎድሮስ ሲድበዋቸው ነበር። ተሰደቡም አልተሰደቡም ቢታማኝነት ከጌታቸው ጋር ወድቀዋል። ሰለ ራስ አንግዳ ታማኝነት፣ ራሳም ሲገልጥ፣ አንግዳ ለቴዎድሮስ ሲል መርዝ ይጠጣል ብሏቸዋል።*

ቁጥር 153፣ *ቴዎድሮስ ራሳምን ሲቀበሉ፣ በጣና ሀይቅ አጠገብ ቆሬጣ በሚባል ቦታ ነበር። እንደ ራሳም ንጉሣዊ አቀባበል የተደረገለት የውጭ ሰው የለም። አስረኞቹን አፈታለሁ ብለው ቃል ገብተው፣ ሁሉም አሰረኞች፣ ችሎት ተከፍቶ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲጠይቁ ተደርገ። ቴዎድሮስ ራሳቸው፣*

አንገታቸውን ደፍተው ስለበደልኳችሁ፣ ይቅር በሉኝ ብለዋል። አስረኞቹም፣ እንደ ባሀሉ ይቅር ብለናል ብለዋል። በኋላ ግን፣ ቴዎድሮስ፣ ሃሳባቸውን ቀይረው፣ አስረኞቹ እንደገና እንዲታሰሩ አስደረጉ። ከውጭ ፀሀፊዎች፣ ሄንሪ ዱፍተን የተለየ መልስ ሲኖረው፣ ሌሎች ግን የቴዎድሮስ ተለዋዋጭ ባህሪ ነው በማለት ስውየውን መውቀስ ይመርጣሉ። ሆኖም፣ እንደ ዱፍተን ገለፃ፣ ለቴዎድሮስ ሃሳብ መቀየር ምክንያት፣ የፈረንሳዩ ባርደልና፣ አስተርጓሚው አቶ ሳሙኤል ናቸው። ሁለቱም፣ ንጉሡን፣ አሁን ቢለቋቸው፣ እንግሊዞቹ ተመልሰው ጦር ይዘው መውጋታቸው አይቀርም የሚል ሃሳብ ስለተናገሩ ነው። ቴዎድሮስ ይህን ሀሳብ ሳያሳዩ ሌላ ስበብ በመፍጠር ስዎቹን ወደ መቅደላ መለሱ። ራሳም ደግሞ ባርደል አላደረገም ባይ ነው። ነገር ግን ባርደልና የቴዎድሮስ አማች እንግዳወርቅ የተለየ ግንኙነት ስለነበራቸው ፈርተው ነበር። የእውሮፓውያኑ ደብዳቤና ወረቀቶች በቴዎድሮስ እጅ ነበሩ፣ አላስነበቧቸውም። እንግሊዞቹ፣ ባርደልን በቅፅል(በሚስጥር) ስም "ሽሪምፕ" ብለው ነበር የሚጠሩት። ንጉሡን ደግሞ "ቦብ" እንላቸው ነበር ይላል ራሳም። ታዲያ ባርደልን አስጠርተን እንዳያጋልጠን ለምነነው ነበርና፣ እሱም፣ ደብደቤው ላይ የሚያስወጅል ቦታ ካየሁ በትከከል አልተረጉመውም ብሎ ቃል ገብቶ ነበር ይላል። እውሮፓውያኑ፣ በእጃቸው የነበሩ ደብደቤዎችና ወረቀቶችን፣ ንጉሡ ሳይደርሱባቸው በተገኘው መንገድ፣ በውሀ፣ በማንከ በኋላም በእሳት ያቃጥሉ ነበር። ካሜሮን ለየሽፍታው ሁሉ እንደማለፊያ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ፓስፖርት ለሁሉም አሠርቶ ነበር፣ ሆኖም ከንጉሡ እጅ ሳይወደቅ ድራሹን አጥፍተውታል።



የአፄ ቴዎድሮስ መስቀል

ምዕራፍ አስራ ሶስት



የቴዎድሮስ ቀብር፣ ባላንጣ ንግሥቶች፣ የመቅደላ ስንብት፣ የጄኔራል ናፒየር ትዛዝ፣ የተዘረፉ ዕቃዎች ጨረታ፣ አፈሻል ሪፖርት

መቅደላንና አካባቢውን ለቀን ከመሄዳችን በፊት መከናወን የሚገባቸው የተለያዩ ነገሮች ነበሩ። የአፄ ቴዎድሮስ አስከሬን መቀበር ነበረበት፤ ንግስቲቱን ማፅናናት ያስፈልጋል፤ የወጣቱ ልዑል ዕጣ መወሰን ነበረበት። ኦሮሞዎቹ፣ አሁን የማይሆኑ ነገሮች አያደረጉና ሰው ለመግደል ጩኸት እያሰሙ ስለሆነ፣ እነሱን የሚያስቆማቸው ነገር መደረግም ነበረበት። የመቅደላ ሰደተኞችም በሽሎን እስኪሻገሩ ድረስ መታጀብ ነበረባቸው። ምሽጎች፣ መከለያ አጥሮች፣ ማማዎች፣ ወህኒቤቱ፣ ቤተመንግሥቱና የገበሬዎቹ ቤቶች ሳይቀሩ መውደም ነበረባቸው፤ በመጨረሻም ሶስቱን የተራራ ምሽጎች ሃላፊነት ላለበት የእቢሲኒያ ባለሥልጣን ማስረከብ ነበር።

የመጀመሪያው ቀን፣ አሸናፊ ወታደሮችን ወደ ካምፕ በመመለስ ነበር ጊዜው የተያዘው። ከነዚህ መሀል ግን አንድ ሬጅመንት ምሽጉን አንዲጠብቅ ወደኋላ ቀረ። በተጨማሪም መቅደላ የወደቁትን የቴዎድሮስ ጦር አለቆችን መቅበር፣ ወደ ሰላሳ ሺ የሚሆኑ ከኛ ካምፕ የጥይት ርቀት የሚሆን ለስፈሩ መጠጊያ ለሌላቸው አቢሲኒያውያን ምግብ ማከፋፈል ነበር።

ናፒየር የቴዎድሮስን ቀብር ትዛዝ ከማስተላለፉ በፊት፣ ቀሪዋ እቴጌ፣ ባልዬው አንዴት አንደሚቀበሩ ፍላጎታቸው ተረጋገጠ። አቴጌዋ ስትመልስ፣ ዋናው የጦር አዛዥ ያሻውን ማድረግ ይችላል፤ ነገር ግን፣ ፍታቱ፣ ንጉሡ በሚወዷቸው ቁስ አንዲደረግ ምኞቷ መሆኑን ገለፀች። ይሆንን አንኳ ጄኔራሉ ምንም አልተቃወመም።

ከዚያም ለተወሰኑ ሰዎች፣ አስከሬኑ በሀር ጨርቅ በከብር ተከፍኖ ለቀበር እንዲዘጋጅ ትዛዝ ሰጠ[153]። ከዚህ በኃላ፣ አስከሬኑ እንደነገሩ በተሰራ ሳጥን ውስጥ ተቀምጦ፣ ናፒየር ይቀበርበት ብሎ ወደጠቆመው ቦታ፣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር ተወሰደ። ጥልቀት የሌለው የመቃብር ጉደጓድ በመህል ቅጥር ግቢው ተቆፍሮ ነበር። በጣም ደከም ያለው መነኩሴ ካህን ተጠርቶ ፀሎት አንዲያደርስ ተጠየቀ። በግልፅ እንደታየው፣ ሁኔታው በጣም አሳዛኝ

---

153 (በምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች)

ሰለነበር፣ ሥርአቱን በጥድፊያ ነበር ያደረገው። በሁለት ጠንካራ ወታደሮች፣ እሰከሬኑ ወደ ጉድጓዱ ወረደ፤ መነኩሴው እፍር ዘግሮ በሳጥኑ ላይ ረጨ፤ ከዚያም በእካፋዎች የሚዘቀው አፈር ሳጥኑ ላይ እየተንኳኳ ወርዶ ለኢይን እስኪሰወር ድረስ ሸፈነው።

በዚያን ቀን፣ ለዋግሹም ጎበዜ መልኩተኛ ተልኮ መቅደላን እንዲረከብ ተጠየቀ። በሶሰተኛው ቀን ጠዋት፣ ለጄኔራሉ መልስ መጣ። ብልጡ መስፍን በመልሱ፣ መቅደላን እንደማይፈልግ ነው። ቴዎድሮስ በሕይወት እያሉ በብልጠት ከመቅደላ ርቆ ነበር፤ አሁን ቴዎድሮስ ሰለሞቱ፣ እንደሱ ሀሳብም፣ የበሽሎ ሽለቆ በአሮሞዎች የተከበበ ሰለሆነ በፈቃዱ እሰረኛ ለመሆን ፍላጎትም የለውም። ይልቁንስ፣ ሰር ሮበርት በደግነት ምሽጉንም ጨምሮ የቴዎድሮስን መድፎች ቢሰጠው የተሸለ ስጦታ አደርጎ በወሰደው ነበር። ለምሽጉም መከላከያ አድርጎ ይጠቀምበት ነበር።

ከእንግሊዙ ጄኔራል ጋር ባደረገው የደብዳቤ ልውውጥ ዋግሹም ምክንያቱን አስረዳ። ጎበዜ የሚታወቅበት ነገር ሌላ ሳይሆን ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ መሸሽ ነው፤ ወይም ከርቀት፣ ለደህነቱ በማያሰጋ ቦታ ሆኖ ጉዳዮችን ማጤን ነው። በሁሰቱ ወራት ውስጥ፣ የቴዎድሮስን ካምፕ የተከታተለው፣ ሊደረስበት ከማይችል ከፍታ ወዲያና ወዲህ እያለ ነበር። የመጨረሻው የአፄ ቴዎድሮስ አንቅስቃሴ፣ ጉረኛውን ዋግሹም በጥድፊያ ወደ ርቀት ቦታ እንዲሸሽ ነው ያደረገው። ናፒየር፣ ለራሱ ሆነ ለሀገሩ፣ አለቃ በመቀየር ለጎበዜ መወገኑ ጥቅሙ አልታየውም። ጎበዜ የቴዎድሮስን ያህል ግብ ያለው ሰው አልነበረም፤ ነገር ግን ብዙም ጨካኝ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ መቅደላም ሆነ መድፎች አልተሠጠውም።

በሚቀጥለው ቀን ሁለቱ ባላንጣ ሻዥዎች (ንግሥቶች)፣ ወርቂትና[154] መለታውት መቅደላን ለመውሰድ ተወዳዳሪ ሆነው ቀረቡ። ይህም፣ ርዳታቸውን ለማግኘት ታስቦ፣ እነሱን እነሳሰቶ ቴዎድሮስን እንዲከቡ ለማድረግ በመጣው ቦሚር እከበር አለ እማካኝነት ነው። ከሁለቱ መህከል፣ ወጣትና ወፈር ብላ መልከመልካም የሆነቸው የእርባ እመቷ መስታውት በናፒየር ተመረጠች። በእንግሊዝ ካምፕ ውስጥ በሰነበተችበት ጊዜ የሚገባው ከብር ተሠጥቷት ከሀር የተሠራ ድንኳን መኖሪያዋ እንዲሆን ተደረገ። እሷና፣ የሰፔይን ተወላጅ የሚመስለው በጣም መልከኛው የስድስት አመት ልጇ፣ በጣም ድንቅ በሆኑ፣ የሀገሩ ጎቦዝ የተባለ ባለሙያ የሠራቸው ልብሶችና ጌጦች አድርገው ነበር የሚታዩት።

---

154 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

የጄኔራሉ ወጥቤቶች፣ ባላቸው ችሎታ ሁሉ ለንጉሣውያን ቤተሰቡ ምርጥና ጣፋጭ ምግቦች አንዲያቀርቡ ታዘዋል። ንግሥቷ፣ በወጥቤቱ የተዘጋጀውን ምግብ አሠራር ችሎታ ማድነቋን ለማሳየት ስትል፣ የቀረበላትን ምግብ ሳታማርጥና ሳታስተውል ትበላ ነበር። በድንጋጤ ለሚመለከታት የፖለቲካ ፀሐፊው ምንም ደንታ ሳታሳይ፣ ገንፎውንም፣ ሥጋውንም፣ ድንቹንም፣ ብቻ በፊቷ የቀረበውን አየበላች፣ ከዛም የቀረበውን ምግብ ሳትጨርስ ቡና ትጠጣና፤ በጣም የጣፈጣት ምግብ ከበላችም፣ የሽጉጥ ድምፅ አሰኪመስል ድረስ ከንፈሯን በማላቀቅ ታጣጥማለች።

ንግሥቷ፣ መርካቷን ለመግለፅ ጮክ ብላ ከልቢ ከት ብላ ትሊቃለች። ከዚያም በሥነ ሠርአት ከለበሰችው ልብስ ወደጫፍ፣ ለዚሁ ብላ ባሰረቸው ጨርቅ ደነስ ያለውን ከንፈሯን ትጠርጋለች። ብርቱካንማ ቀለም ያላት ሔብን[155] የመለሰች ግን ደግሞ የቪነስ ጭንቅላትና ቅርፅ ያላት ሰው፣ ጠጅና አረቄ ተደባልቆ፣ በቀንድ ዋንጫ ይዛላት ቀረበች። የቀረበላትን መጠጥም በደስታ ከተጎነጨች በኋላ፣ ኮራና ኮሰተር ብላ መታየት ጀመረች፤ ይህም ከመጠጣቷ በፊት ከነበረው ሁኔታዋ በለጥ ብሎ ነው። እንደ ኢያን ብልጣ ብልጥ የሆነ መኮንን፣ ዲያብሎስን እንኳን ማባበል በሚችል ምላሱ ንግስቲቷን ለምስል አንደትቀመጥ አግባባት። ተረጋግታ ባለመቀመጧ፣ ከሶስትና ከአራት ሙከራዎች በኋላ ጥሩ ነው የተባለው ስዕል ተወለደ፤ የዚህ ቅጅ ደግሞ ለመላው አውሮፓ መንግሥቶችና ለአሜሪካ መንግሥት ተላከ።

ሶስተኛው ቀን፣ ጠቅላላ ቁጥራቸው 33 የሆኑ የቴዎድሮስ መድፎችን በማውደም ነበር ያለፈው።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ግን በውሃ ጥምና በቀለብ ማነስ ምክንያት ተሰቃይተን ነበር። ሆኖም በአራተኛው ቀን፣ ጦሩ የበሽሎ ሸለቆን ለቆ ወደ ደላንታ አፋፍ ይሄዳል የሚል የጥሩ ወሬ ጭምጭምታ ስለተሰማ በሁሉም ሰው ልብ የደስታ ስሜት ፈጠረ።

መቅደላ በወደቀ በአራተኛው ቀን ጠዋት፣ ቁጥራቸው 30 ሺ የሚሆኑ አቢሲኒያኖች ወደ ደላንታ ጉዟቸውን ጀመሩ። ይህንን ሁኔታ ደግሞ አሮሞዎቹ አውቀው ስለነበር፣ አንደ ጆፌ አሞራ ከጎንና ከኋላ፣ አንዳንዴም በድፍረት መሀል ድረስ እየገቡ ብዙ ሰዎችን እንደ አሰረኛ ወሰዱ።

---

155 ሔብ በግሪኮች ቀደምት ታሪክ የወጣቶቹ አምላክ የሆነች ስትሆን፣ የዙስና የሄራ ልጅ ነች።



ንግሥት መሰታውት ከልጇ ጋር

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ከሌሎች ጋር እንድ ላይ ሆኜ እየጋለብኩ የተረፈውን ምሽግ ለማየት ሄድኩ። ከሁለት ሰአታት በኋላ፣ በሮያል ኢንጂነርስ እማካኝነት ነፍስ ያለው ማንኛውም ሰው እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ፣ ምሽጉን ለመደምሰስ የተመደቡት ሰዎች ለራቸውን ጀመሩ። የደቡብ መግቢያው ወይም የቃፊር በር ነበር መጀመሪያ የተደረመሰው፤ ከዛ ወደ መካዝኖች የሚወስደው የምስራቁ በር ተደገመ፤ ነፋሱ ከምስራቅ እቅጣጫ ይነፍስ ስለነበር፣ በአምባው ላይ፣ በምስራቅ ጠርዙ ላይ ያሉ ቤቶች በእሳት ተለኮሱ።

ከዚያ አየተነሱ፣ መሀንዲሶቹ በቅልጥፍና አያንዳንዱን ቤት በያዙት የአላት ችቦ መለኮስ ጀመሩ። ተመልካቾቹ ተጣድፈው የማያሲጋ ቦታ ሄዱ፤ ከዚያም ሆነው የሚነሳውን የአላት ማዕበል ለማየትም ነበር። ለዚህ ሁኔታ አመቺ ሆኖ የተገኘው የስላሴ ደቡባዊ ጠርዝ ነበር። አንግዲህ ከዚህ ቦታ ሆኖ መቅደላን በአንድ ሺ ያርዶች ርቀት ማየት ያስችላል።

የምሰራቁ ነፋስ አዝግሞ አየጠነከረ እንደ ምላስ ቦግ ቦግ የሚሉት የእላት ነበልባሎቹ በቤቶቹ ጣሪያ ላይ አስኪታዩ ድረስ ካስፋፋ በኋላ፣ እላቱ እየደመቀና አየሰፋ ሄዶ፣ ከነፋሱ ጋር አየተጫወተ፤ ከመሀል ወደላይ አየጎነ መውለብለቡን ቀጠለ። የማያቋርጥ የነፋሱ ትንፋሽ ነበልባሎቹን ወደ ቀይ ማዕበል ቀየራቸው፣ ነበልባሎቹም አንድ ላይ ተነባብረው የአላት ሀይቅ ፈጠሩ።

ሙቀቱም አየጨመረና አየጠነከረ መጣ፤ ያልተተኮሱ ሽጉጦች፣ ጠመንጃዎችና ጥይቶች በብሪታናያ መሀንዲሶች ወደላቱ ሲወረወሩ ሰለነበር ጆሮ በሚያደነቁር ድምፅ ይፈነዱ ነበር[156]፤ ፍንጣሪዎቹም በእስፈሪ ሁኔታ አጠገባችን ድረስ ያፏጩ ነበር። ሶስት ሺ ቤቶችና በሚሲዮን የሚቆጠሩ የሚነዱ ነገሮች አየጋዩ ነበር። በዚህ፣ ግዙፍ፣ በሚውረገረግ አላት አንድ ቤት እንኳን መትረፍ አይችልም።

ጥሩምባዎች የደስታ ድምፅ አሰሙ፤ ከበሮዎችም እንዲሁ፣ የሚነፉት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጎላ ብለው ተሰሙ፤ ወፎችም ቢሆን በደስታ ዘመሩ፤ ብሩህ የሆነ ንጋት የሚያዝያ 18፣ 1868 ቀን መምጣቱን አበሰረ።

ሁላችንም ቢሆን የአቢሲኒያ ዘመቻ ተውኔት ውጤትን አይተናል። በዚህ ቀን፣ ፈታችን ወደ ቤታቻን መመለሻ ጉዞ ወደ ሰሜን አዞርን።

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን ቀዳሚው ጦር የፋላን ቁልቁለት ወርዶ ወደ አሮጌ ሽለቆና ወደ በሽሎ አመራ። የጓዝ መሰመሮችም ተንቀሳቀሱና፣ እራት ሰአት ላይ መንገዱ ለጦሩ ከፍት ሆነ።

ሬጅመንቶቹ ልከ አንደ ሰልፍ፣ ተዘጋጅተው፣ አግረኛው፣ ፈረሰኛው፣ መድፈኛው፣ መሀንዲሶቹ፣ ቆፋሪና ግንበኞች በሥርአት፣ በረድፍ ነበሩ። ዋናው አዛዥ ፈረሱ ላይ አንደወጣ፣ "ወደፊት!" የሚለው ትዛዝ ተሰማ፤

[156] (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

በባንዱ እየተመራ፣ የ45ኛው ሬጅመንት ጠመንጃውን እንግቦ ከሙዚቃው ጋር በተሰማማ ርምጃ በኩራት ቁልቁለቱን መውረድ ጀመረ። የተወላጆቹ የህንዶች ሬጅመንት እግረኛና ፈረሰኛ፣ መድፈኛው፣ የባህር ሀይል ብርጌድ በመጨረሻም "የቄልንግተን መስፍን" የሚባለው ሄደ። የሬጅመንቱ ወደኋላ ያለው የመጨረሻው ከፍል፣ መንገድ ጀምሮ ሲንቀሳቀስ፣ ሰድሰት ሺ ከሚሆኑ ሰዎች የሚወጣ "ቺርስ" የሚል ተደጋጋሚ ድምፅ ሲያሰማ፣ የሚቀባበለው ድምፅ፣ በበረሀውና ባዷቸውን በቀሩት ጉበታዎች ላይ እየነጠረ ነበር። ይህም በእሰር ማይል ርቀቶች በተጠንቀቅ ለሚጠባበቁት አሮሞዎች፣ ወታደሮቹ የሰንብት ድምፅ እያሰሙ መሆኑን እንዲገነዘቡ አደርጓቸዋል።

ግርማ ሞገሰ ያላቸው፣ ጨለም ብለው ግትር ያሉት ሶሰቱ ምሽጎች፣ ከተራሮች በላይ ራሳቸውን ቀና አድርገው የደቡቡን አድማሰ ፈጥረዋል። ከጠዋቱ ሰማይ ጋራ በመደባለቅ፣ በብሩህ የጮራ ቀለሞች ደምቀው ሲታዩ፣ ብርቅዬ ለሆነ፣ የዕይታ የጀርባ ምሰል መጠቀም ያስችሉ ነበር። የሩቅ ባለዝናው መቅደላ፣ እናቱ ጭጋግ በሚመስል ጭስ ተሸፍኗል፣ ከሚቃጠለው ንብረት፣ የእማልከትን ቁጣ ለማርገብ የሚቀርብ ገፀ በረከት እሰኪመስል ድረሰ ጭሱ ወደላይ ይወጣል።

የመጓጓጉ ከብቶቹ ጉልበት እንዲያገኙ፣ መቅደላ በነበርንበት ጊዜ በገፍ ከተሰበሰበው ቀለብ እንዲመገቡ ተወሰኗል። ለዚህም ሲባል፣ ከደልዳለው ቦታ ትንሽ ጎድጎድ ያለ ቦታ ተመርጦ ለካምፕ ሆኗል።

በጣም እሰፈላጊ የሆነ ጉዳይ ደግሞ አትኩሮት መሰጠት ነበረበት። በጦር ግንባሩ ሲጋፈጡ የነበሩ ወታደሮችን ለመጥቀም ሲባል ብዛት ያላቸው ከመቅደላ የተዘረፉ ንብረቶች መሸጥ ነበረባቸው፣ ይህም፣ ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ወይም ጥንታዊ ዕቃዎችን ለሚወዱ ሰዎች ነበር። አዛዥ መኮንኖች ለሬጅመንታቸው ወይም ለወታደሮቻቸው ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ቅርሶች እንዲመርጡ ተጠይቀው ነበር። እነዚህ ንብረቶች ወይም ቅርሶቹ በእስራ እምስት ዝሆኖችና በ200 በቅሎዎች ተጭነዋል።

ከጠዋቱ ሶሰት ሰእት ተኩል ሲሆን፣ ታምቡር ሲመታ፣ የተለያዩ ሬጅመንቶቹ ከየካምፓቸው በመውጣት 200 ያርዶች ርቀት ላይ የሚገኝ ትንሽ ከፍ ያለ ደልዳላ ቦታ ላይ፣ በመሀል፣ እሰረኞች፣ መኮንኖችና ጂኔራሎችን በማድረግ እራት ማዕዘን በሆነ ዙሪያ ቆሙ።

የጦሩ ካህን ሰለ እሰረኞቹ ሁኔታና እና ሰለመጣንበት ድል ሲገልፅ፣ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሀል እንባ ያላረጠበው አይን ማግኘት ይከብዳል። ይህን በሰሙ፣ በሁሉም ሰዎች ላይ ጥልቅ ሰሜት ነው የፈጠረው፣ የሰውየው ድምፅ ቃና፣ የሚያስደስተው የፀሀይ ብርሃን፣ በርቀት የከበቡት የተራራዎቹ ጠቆር ያለ



የመቅደላ ቃጠሎ

ጥላ፣ በላያችንና በዙሪያችን የሚዘምሩት ወፎች፣ የሚንሳፈፉት ደመናዎች፣ ያ አውድ ቀን በካላንደር ላይ ካሉ ቀናት በበለጠ ሁኔታ፣ በቦታው በነበሩ ሰዎች ይታወሳል።

በሚቀጥለው ቀን፣ ወደ አቢሲኒያ በዘመተው ጦር በጣም የሚደነቅና ስልት ያለው ስልፍ ተደረገ።

ዲቪዝኑም ስድስት ረድፍ ያለው የአራት ማዕዘን ቅርፅ በመስራት ተሰለፈ፤ መሀሉ ከፍት ነበር። አሰረኞቹ፣ ሲቪል ሠራተኞች፣ የውጭ ወይም የሌላ ሀገር መኮንኖች ውስጥ እንዲሆኑ ተጋበዙ። የጄኔራሉ ረዳት፣ ኮሎኔል ፍሬድ ቲስገር፣ የጀኔራሉን መግለጫ ከፍ ባለ ድምፅ አነበበ። በዘመቻው ያጋጠሙ ሁኔታዎችንና ግቦችን በሚያዳምቅ አነጋገር ነበር።

"የአቢሲኒያ ጦር ወታደሮች! የኢንግላንድ ንግሥትና ሀዝቡ፣ ያገራችን ሰዎች ከረዥምና አሰቃቂ ከሆነ አሰራት እንድታሰለቅቁ፤ በአቢሲኒያው ንጉሰ፣ በቴዎድሮስ የተደፈረውን የአገራችን ክብር እንድታሰጠብቁ፣ በጣም አስቸጋሪና ፈታኝ የሆነ ዘመቻ ግዳጅ ሰጥተዋችኋል።

የሀገራችን ትዛዝ ክብር በሚነካው ሁኔታ ስለተወጣችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ።

እብዛናውን ጊዜ በትሮፒካል ፀሀይ፣ ወጀብ ባለው ዝናብ መሀልና በሚያዳልጥ መሬት፣ 400 ማይሎች ርቀት ተራራማና አሰቸጋሪ የሆነ አገር አቋርጣችኋል።

ቀጥ ያለ ዳገትና ገደላማ የሆኑ ከ10ሺ ጫማ ከፍታ በላይ ያላቸው ተራራዎችን፣ ሰንቃችሁ ከናንተ ጋር አኩል ባልደረሰበት ሁኔታ ተጉዛችኋል።

ከጠላት አጠገብ ሰትደርሱም፣ ምንም እንኳ በጣም እነሰተኛ ምግብ ብትይዙም፣ እንዳንዶቻችሁ ለብዙ ለእታት ምግብ ሆነ ውሀ ሳትቀምሱ፣ በአራት ቀናት ውስጥ ፈታኝ የሆነውን በሸሎን ተሻግራችሁ፣ ከተመቸው ምሽጋቸው ሆነው እንደሚያሸነፉ በርግጠኛነት ቁልቁል የወረዱትን የቴዎድሮስን ወታደሮች አሸንፋችኋል።

በሺ የሚቆጠሩ መሳሪያዎቻቸውን እግራችሁ ሰር አስቀምጠዋል።

ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ፣ እብዛኞቹ ክብደት የነበራቸውና በቂ አርሳሶች የነበሯቸውን መድፎችን ማርካችሁ ሰባብራችኋል።

በእልምት ባይ ተጋዳይነት፣ ቴዎድሮስ ቀሪ አለቆቹና ተከታዮች ሊከላከሉት የነበረውን የማይደፈር ምሽግ ጥሳችሁ ገብታችኋል።

መግቢያውን ጥሳችሁ እንደገባችሁ፣ ምህረት የማያውቀው ቴዎድሮስ፣ የተሠጠውን ምህረት ሰላላመነ በገዛ እጁ ራሱን አጥፍቷል።

የብሪታንያ አስረኞችን ብቻ ሳይሆን፣ የሌሎች የወዳጅ አገር አስረኞችንም አስለቅቃችኋል። ክዘጠና በላይ የሚሆኑ የአቢሲኒያ ባላባቶችና ገዥዎችን ሰንሰለት ፈታችኋል።

የብዙ ሰዎች ሕይወት የጠፋበት መቅደላ በአሳት ነዶ የተለበለበ አለት ሆኖ ይቀራል።

የኛ፣ ፈጣንን ሙሉ በሙሉ የሆነ ውጤት፣ በመጀመሪያ፣ ለትክክለኛ ምክንያት ሰለመጣን፣ አጅ በኛ ላይ እንደነበረ በሚሰማኝ በፈጣሪ በረከት ነው። ሁለተኛ ደግሞ አናንተ በሳያችሁት ክፍተኛ ስሜት ነው።

የሀንድ ወታደሮች ከአውሮፓዊ ጓዶቻቸው ጋር ለመሰለፍ በዘርና በእምነት የነበረውን ልዩነት ረሰተዋል። ክዚህ በፊት፣ ማንም ሌላ ሠራዊት አንደናንተ በከብር ሰሜት ጦርነት የተቀላቀለ የለም፣ ይህ ደግሞ ብዙ ድካምና ችግር አልፋችሁ አንድትሄዱ አድርጓችኋል፤ ጠላትን ለማጥቃት ሰትቃረቡ ብቻ ነው የችላ መንፈስም ያሳያችሁት።

በየግላችሁ የደረሰው ሁኔታ ማስታወሻ ቶሎ ያልፋል፣ ነገር ግን በድፍረት ያሳያችሁት ወኔ በታሪክ ውስጥ ይኖራል።

ንግሥቷና የኢንግላንድ ህዝብ አገልግሎታችሁን ያመሰግናል።

አንደ ጦር አዛዥነቴ፣ በኔ በኩል ግዳጃችሁን ለመወጣት ላሳያችሁት ሙሉ ስሜት፣ አናም ለጠቢቃችሁት ጥሩ ሥነ ሥርአት አመሰግናችኋለሁ። መንደርተሮቹ ተዘረፉ ወይም ተበደሉ፣ ጉዳት አደረሱ ተብሎ አንድም ወታደር ላይ አቤቱታ አልቀረበም። በሞቃታሙ የዙላ አየር ጠባይና በቁማይሌ ማለፊያ፣ በተጨማሪም በየቦታው ባሉ ጣቢያዎች፣ ለኛ ሲሉ የሚደክሙትና ግንኙነታችን አንዳይቋረጥ ያደረጉ ጓዶቻችንም የሚገበውን ዕውቅና ለመስጠት መረሳት የለብንም። አያንዳንዳቸው አናም ሁሉም፣ ከኛ ጋር ለመሆን ያላቸውን በሙሉ ይሰጡ ነበር። ስለዚህ የኛን ምስጋና ማግኘት ይገበቸዋል።

ተመልሳችሁ አስከትሳፈሩ ድረስ ደህንነታችሁን አጠብቃለሁ፤ አስክ ህይወቴ መጨረሻ የናንተ አዛዥ መሆኔን በኩራት አሰታውሳለሁ።"

ሮ. ናፒየር፣ ሉተናንት ጀኔራል
ጠቅላይ አዛዥ
የደላንታ ካምፕ፣ ሚያዝያ 20፣ 1868

(ካለይ የተጠቀሰው ወታደራዊ መግለጫ እያንዳንዱ ዝርዝር አውነት ነው። ጀኔራሉ ከሚገባው በላይ ራሱን ከፍ አድርጎ በፅሁፉ አላሰቀመጠም። ግልፅና እንደ ራሉ ትሁት ነበር።)

በዳውንትና ደላንታ አፋፍ ጊዜያዊ ካምፕ በቆየንበት በሰሰተኛው ቀን፣ ለሽያጭ የሚቀርቡት ዕቃዎች በሙሉ ለአጫራቹ ተዘጋጁ።

በሥነ ሥርአት በሚተዳደር የወታደር ካምፕ ውስጥ ለአዲስ አይነት አንቅስቃሴ ጥሪ የሚደረግበት ታምቡር መመታት ተጀመረ። ሁሉም መኮንኖች፣ ተመልካቾችም ከመቅደላ የተዘረፈውን ንብረት በተከመረበት የግማሽ ኤከር ዙሪያ ተሰበሰቡ።

ለእጫራችነት የተመረጠው ሰው ሉተናንት ኤሰ ነበር፤ ደከመኝ የማይል ሰው ሆኖ በተፈጥሮው ቀዳማዊ ናፖሊዮንን የመሠለ ገፅታ ያለው ነበር። ከየሀገሩ የተሰበሰቡ ምርጥ ምንጣፎች ተዘረጉ፤ በሺዎች ከሚቆጠሩ አብያተክርስቲያናት የተሰበሰቡ ዕቃዎች በጠዋቱ ፀሀይ ያብረቀርቃሉ። በግርግር፣ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ አርሰ በርሰ የሚጋፉት ሰዎች አቃ ጎሹዎች ነበሩ። (በአለም ውስጥ በጣም ጠብ አጫሪ የግርግር ቡድን ቢኖር፤ የአንግለዞች ነው።) እቃ ጎሹዎቹ ደግሞ፣ በጊዜው ሰለ ጥንታዊ ቁሳቁሶች እውቀት ያላቸው ሰዎች ሆኑ፤ በሚገርም ሁኔታ አውነተኛውን ዕቃ መስሎ ከተሠራው፣ ወርቁን ከበልጭላጩ ለይቶ የማወቅ ችሎታ አላቸው።

የተጫራቾች ቁጥር ትንሽ አልነበረም። እያንዳንዱ መኮንንና የሲቪል ሠራተኛ የመቅደላ ማሰታወሻ መያዝ ይፈልጋል። አንዱ ከብር የተሠራ መሰቀል ወይም ከብሮንዝ የተሠራ ይገዛል፤ ሌላው የዕጣን ማጨሻ፤ ሌላው ደግሞ ጎራዴ። ከብር የተሠሩ ዋንጫዎች፤ መጠጫዎች፤ በብዛት ነበሩ። ከሀር የተሠሩ ጃንጥላዎች፣ በወርቅ ያጌጡና የውድ ቀለም ባላቸው ድንጋዮች የተሸቆጠቆጡ ኮርቻዎች፣ ድንኳኖች፣ ምንጣፎች፣ ብሩህ በሆነ ቀለም የተፃፉ መፅሐፍ ቅዱሶችና ሌሎችም ፅሁፎች፣ ብዙ ዋጋ የሌላቸው ጌጦችና፣ ሀብሎች፣ ቀለበቶች፣ አምባሮችን በሙሉ ጎሹዎች አግኝተዋል።

ሚስተር ሆልምስ፣ እንደ ብሪቲሽ ሙዚየም ተወካይነቱ በጣም ተደሰቷል። ብዙ ገንዘብ ሰለነበረውም ብዙ ነገሮችን በጨረታ አሸንፏል። ነገር ግን ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ሃብታም ለሆነ ሬጅመንት፣ ዘኛው ሁሳር፣ ይገዛ ሰለነበር አየተፎካከረ አሰቸግሮታል። የቴዎድሮስ የግል የሆነ ማንኛውም ነገር ሲቀርብ ግን፣ ሌሎች ሰዎች በግላቸው ሁለቱንም በጨረታ ያሸንፏቸው ነበር።

ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ይይዙት የነበረው ጋሻ ምንም አንኳን በመጠነኛ ብር ቢለበድም፤ ጨረታው በጣም የተጋጋለ ነው የሆነው፤ ከአሰር ዶላር ጀምሮ በፍጥነት ወደ ሁለት መቶ ዶላር ከፍ ብሎ በመጨረሻ በኮሎኔል ፍሬዝር ተገዛ።

ሚስተር ሆልመስ፣ ብዙ የሚያጓጉ ንብረቶችን ማሰቀረት ችሏል።

ጨረታው ሁለት ቀን ፈጀ። ጠቅላላ ገቢው ወደ 5ሺ ፓውንድ ይጠጋል። ይህ ገቢ፣ ለተመለመሉ መኮንኖችና ከበሽሎ ደቡብ ለሚገኙ ሰዎች ተከፋፈለ፤ አያንዳንዱ ሰው ከአራት ዶላሮች በላይ ሊያገኝ ችሏል።

ደላንታ በመጣን በአራተኛው ቀን ጥዋት፣ አሰረኛቹ፣ በዛ "በአለም ምርጥ ሰው" ፣ በኮሚሳሪያቱ በካፒቴን ኤሰ ሀላፊነት ወደ ቤታቸው መንገድ ጀምረዋል።

ከደላንታ ካምፕ፣ ሌፍተናነት ጀኔራል ናፒየር፣ አንፀባራቂ የሆነውን የወታደራዊ መልከቱን ፃፈ። ይህ ሪፖርት፣ በመቅደላ ፊት ለፊት በፍጥነትና በሚገባ የተጠቃለለውን ሁኔታ ለመላው አለም አንዲታወቅ ያደረገበት ነው።

የሰር ሮበርት ናፒየር ወታደራዊ ሪፖርት
የጠቅላይ ዕዝ ጽ/ቤት፣ ዋና ቢሮ፣ የእንጣሎ ካምፕ
ማንቦት 12፣ 1868

ከቡር ፣ ሰር! ሚያዝያ 3፣ ዋድላ አፋፍ ላይ ካምፕ ባደረግሁበት ጊዜ፣ ከደላንታ አለቆች መልክት ደረሰኝ፣ በዚህ መልክትም፣ ቴዎድሮስ ከመቅደላ ተነስተው አሮጌ ሜዳ ላይ ካምፕ እንዳደረጉና ዘመቻ ለማድረግ እንዳሰቡ ነበር። ከእስረኞች የመጣው ደብዳቤም ራሴን እንድጠብቅ የሚያሰጥነቀቅ ነበር። በብሪትሽ ሠራዊትና በደላንታ ሜዳ መሀል የ3400 ጫማ ጥልቀት ያለው የጀዳ ሸለቆ ይገኛል። የዚህ ማለፊያ ደግሞ ምቹ ስለሆነና በቀላሉም መመከት የሚቻል ስለሆነ፣ በጠላት ፊት ቦታውን ለመቆጣጠር፣ ያለ ከፍተኛ ጉዳት መደረግ የሚችል አልነበረም። ፈጣን የሆነ አንቅስቃሴ በማድረግም፣ አስራ ሰምንት ማይሎች በመጓዝ ጀዳን ተሻግሬ ደላንታ ሜዳ ላይ ካምፕ መሰረትኩ። በማይሎች የተጓዝነውን ርቀት መቁጠር፣ ብቻውን፣ በመንገዱ ላይ የተደረገውን ልፋትና ድከመት መግለፅ አይችልም። ከፍተኛ የሆኑ ዳገቶችና ቁልቁለቶች፣ ከመጠን በላይ የነበረው ሙቀት፣ ከባድ ሸክም ለተሸከሙት ወታደሮች ከፍተኛ ፈተና ነው የነበረው። ያም ሆኖ፣ ቴዎድሮስ በሸሎን አልተሻገሩም፤ ነገር ግን በበሸሎ ወንዝና በመቅደላ መሀከል የሚገኙ መንደሮችን ዘርፈውና አቃጥለው ነበር፤ አነዚህ መንደሮች ደግሞ በሌላ ጊዜ ለሳቸው ታማኞች ነበሩ[157]። ከደላንታ ሜዳ ሆኜ፣ ሩቅ ቢሆንም፣ ግልፅ በሆነ መንገድ መቅደላንና ወደመቅደላ የሚያደርሰውን አካባቢውን ማየት ቻልኩኝ። በጥሩ የሩቅ መነፅር (ቴሌስኮፕ)፣ የአካባቢውን አደገኛነት፣ የቦታውን ጠቅላላ አቀማመጥ ስለተረዳሁ፣ ጥቃቱን የተዋጣ ለማድረግ ማማኘት የምችለውን እግረኛ ጦር በሙሉ ማምጣት እንዳለብኝና፣ ጥቃቱ ውጤት እንዲኖረው ሁሉንም የፈረሰኛ ጦር ማስለፍ እንዳለብኝ ተገነዘብኩ። ያም ሆኖ መሰብሰብ የምችለውን ጦር ባገኝም፣ ወደ መቅደላ ደቡብ በኩል ወዳሰው ቃፊር በር ጥግ ድረስ ወታደሮች በረድፍ በመላክ ጥቃቱን መፈፀም እንደማልችል ተስምቶኛል። የመረጃ ክፍል መኮንን የነበረውን ሚር አከባር አሊን፣ ለወሎ

---

157 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

አሮሞዎች ንግሥት፣ ለመሲታውት መልከት እንዲወሰድ አዘዝኩት። በዚህ መንገድ፣ መሲታውት ያለ የሌለ ሰዎቿን አስባስባ፣ ባለ ሀይሏ፣ በዚያ በኩል ያሉትን ማምለጫ ቦታዎች እንድትዘጋ ነበር። የሚር አከበር አሊ ሪፓርት አብሮ ይላካል፤ ሪፓርቱም እንዴት አድርጎ ተልኮውን በደንብ እንደተወጣ ያሳያል። መቅደላ እካባቢ ምንም አይነት መዘግየት እንዲፈጠር ፈቃደኛ ሰላልነበርኩ፣ ምሽጉን ለማጥቃት በሚደረገው ዘመቻ የሚያስፈልገኝን በቂ ቀለብ አስከምይዝ ድረስ ለብዙ ቀናት በሸሎን ሳልሻገር ለመቆየት ወሰንኩ። ያልተረጋጉት የአቢሲኒያን ሰዎች፣ በትንሹ የሚላኩ ወታደሮች ላይና ሰላማዊ ሁኔታ የሚያሳዩትን የኛን ወታደሮች ጥላቻ ሊያሳዩ እንደሚችሉም አልዘነጋሁም። ነገር ግን፣ የማጓጓጉው ከፍል የነበረበትን የተለያዩ ችግሮችና፣ በቂ የሆነ ቀለብም አለመኖሩ በበቂ የወታደሮች ቁጥር ቦታዎችን ለመያዝና በሚፈለገው መጠን ማጠናከር አንደማልችል አድርጎኛል። ያም ሆኖ፣ አያንዳንዱ ቀን ተጨማሪ ጥንካሬ እያመጣ ነበር፤ በመሀሉም፣ በተቻለኝ መጠን ነፃ በሆነ መንገድና በመደለልም ከተከዜ እለከ አንጣሎ ያሉት ትንንሽ ገዥዎች ወዳጅነታቸውን ጠብቀው የሀገሩን ተወላጆቸ ሰርዳታ እንዲልኩ አደርግ ነበር። ሁኔታው የተቃና እንዲሆን ያደረገውና የነበረው እማራጭ ይህ ነበር። ያለዕድል ሆኖ፣ ቢሰካም ሙሉ በሙሉ አልበረም። የኛ ዋናው ጦር በቦታው ስላልነበረና የነበረውም ጫና ስለቀነስላቸው፣ በየቦታው ያሉ አለቆች፣ የኛን ጓዝ የሚጓጓዙ እቢሲኒያውያን ላይ ችግር መፍጠር ጀመሩ። በዚህም የኛ ጓዝና በየቦታው የተመደቡ ወታደሮች ላይ ጥቃት ጀመሩ። ሰለዚህ፣ በሀገሩ ተወላጆች፣ ከአንጣሎ ተነስቶ የሚመጣው ጓዝ በጣም በሚያስፈልግበት ወቅት እንዲቋረጥ ተደረገ። በዚህም የተነሳ፣ በሚያዝያ 4፣ መተማመን የምችልበት የነበረኝ ስንቅ ለጥቂት ቀናት ብቻ የሚሆን ነው የነበረው። ጦሩ ያለውን ጓዝ፣ ላት በሚባል ቦታ፣ ወደ ኋላ 100 ማይሎች ርቀት ላይ ጥሎ፣ ሰዘመቻው የሰበሰውን ብቻ ይዞ ነው የመጣው፤ ብርድልብሶች፣ ከባድ ኮትና ውሀ የማያስገባ አንሶላዎች የያዘው። ሌላ እማራጭም ሰላልነበረ፣ አንድ ድንኳን ለአስራ ሁለት መኮንኖች ወይም ለሀያ ወታደሮች እንዲጋሩ ተደረገ፤ በየቀኑ ያጋጠመን የዝናብ ወጀብ አነዚህን ድንኳኖች በጣም አስፈላጊ ሆነው እንዲገኙ አድርጓቸዋል። የማጓጓጉው ከፍልም፣ የማያስተማምኑ የሀገሩ ተወላጆች ጓዝ በሚይዙባቸው ቦታዎች ተልኮ ቀለብ እንዲያመጣ ታዘዘ። ይህ ደግሞ፣ በስንቅና ትጥቁ ከፍል ለነበረኝ ችግር መፍትሄ ተሰፋ ሰጥቶኛል፤ ሆኖም አጣዳፊው የወቅቱ ሁኔታ ደግሞ ግፊት እየፈጠረ ነበር። በተጨማሪ ሁለተኛ ሁኔታ፣ ብርጋዴር ጀኔራል መርዌዘር፣ ወደ ተከዜ ሄዶ፣ ከአለቆች ጋር በመነጋገር የዶቄት ቀለብ እንዲያቀርቡ እንዲያደርግ ወከልኩት። ሜጀር ግራንት ወደ ላት እንዲመለስ መመሪያ ተሠጠው፤ ካፒቴን ሞር፣ ወደ አሸንጌ ሀይቅ ሄዶ፣ በዚህ ቦታ የተፈጠሩ መሰናክሎችን እንዲያሰወግድ ታዘዘ። ካፒቴን ሰፒዲና ሚስተር መንዚንጀርም፣ ካፒቴን ወደ ዳውንት፣ መንዚንጀር ቴዎድሮስ ወደ ለበለቡት ወደ ደላንታ ደንበር ተላኩ፤ በነዚህ መኮንኖች ሥራ ምክንያት፣ ከብቶቹን መቀለብና፣ ለወታደሮች፣ ለእያንዳንዱ ወታደር 8 አውንስ ዶቄት፣ ሰአስራ አንድ ቀን የሚሆን ቀለብ ማግኘት ቻልኩ። ያገሩ ተወላጅ የሆኑ ተከታዮች ግን በዶቄት ፋንታ ስንዴ እህሉን ተቀበሉ።

የሚደነቅ ስሜት ባላቸው በኔ ሠራዊት በመተማመን፣ ይህን ያለኝን ቀለብ ወይም ሥንቅ በመያዝ መቅደላን ለማጥቃት ተዘጋጀሁ። እኔ ራሴ ካየሁት የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ በተጨማሪ፣ በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ በቅርቡ ከመቅደላ ከድቶ የመጣ ቢትወደድ ሀይሉ[158] ከሚባል ሰው አገኘሁ። ቢትወደድ ሀይሉ፣ ከሸዋው ንጉሥ ከምኒልክ ጋር በመመሳጠሩ፣ ቴዎድሮስ ሲመለሱ ወዲያውኑ የሞት ቅጣት እንደሚያጋጥመው በደንብ አውቋል። ለማጥቃት የምናስበውን ይህን ሀይለኛ ቦታ በቂ ሀሳብ አንዲኖር በፅሁፍ ብቻ ለመግለፅ ይከብዳል።

የመቅደላ ምሽግ፣ ከበሽሎ ወንዝ ዳርቻ በቀኝ በኩል እስራ ሁለት ማይሎች የሚሆን ይርቃል። ነገር ግን ያለው ትልቅ ከፍታና ጥርት ያለው አካባቢው ምሽጉን በደንብ ተለይቶ እንዲታይ አድርጎታል። የቦታው መሀል ቦታ ከባህር ወለል በላይ ፱ሺ ጫማ ከፍታ ያለው የስላሴ አለት ነው። ስላሴ፣ ሰላምጌ የሚባል አምባ ሜዳ ላይ ነው የቆመው። ስላሴ አንደገና፣ ከአለት በተፈጠሩ ቀጥ ያለ ግድግዳ ባላቸው ብዙ እርከኖች ይከፋፈላል። እነዚህ እርከኖች፣ ከፋላ ጋር የሚያገናኛቸው ጎድጎድ ያለ ቦታ አለ። ፋላ ግዙፍ የሆነ የተፈጥሮ መከላከያ ነው፣ እናቱ ጠፍጣፋ ሲሆን፣ ጠቅላላ ከፍት ሆኖ ከሰላምጌ በኩል መቆጣጠር ይቻላል። ወደ ሰላምጌ የሚወስዱ ማናቸውንም መንገዶች በ200 ጫማዎች ከፍታ ያስፈራራል ወይም ይቆጣጠራል። ጎኖቹ ገደላማ ይመስላሉ፤ እናቱ ደግሞ በተፍጥሮ የአለት ስብርባሪዎች ተከቦ ከ8 አሰከ ሀያ ጫማዎች ከፍታ ባላቸው ጥቂት ቦታዎች ብቻ ነበር መደፈር የሚችለው። በፋላና በስላሴ እንደምንም ተሸፍኖ፣ የመቅደላ እናት በአጋማሹ ነበር የሚታየው። ወደ መቅደላ የሚወስደው መንገድ፣ በገደላማው ፋላ ጎን ላይ ነው እየተጠማዘዘ የሚወጣው፤ ከፋላ ለሚተኮስ ተኩስ ከፍት ሆኖ ከዛም ለሚወርድ ድንጋይ ናዳ የተጋለጠ ነበር። የመንገዱ አንዱ በኩል በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ስለሆነ፣ ጥቂት ፈረሶች ያውም የሀገሬው ርቢ የሆኑት ብቻ ናቸው የሚጋልቧቸውን ሰዎች ወደላይ ወደታች ማመላለስ የሚችሉት። ጠቅላላው መንገዱ እንዳለ በጎኑ በስላሴ ጠርዝና ሰፋ ባለው በስላምጌ ከፍል የታቀፈ ነው። በጠቅላላው፣ መቅደላን ላይጨመር፣ ለመከላከያነት ያለው ባህሪ፣ የውጭ ሥራው ካሰበነውና ጠለቅ ያላለ ስለበታው በደረስን ገለፃ ምክንያት ከጠበቅነው በላይ ነበር። የከዳው አለቃ፣ ቢትወደድ ሀይሉ፣ ትግስት አጥሮት፣ ከመቅደላ በደቡብ በኩል፣ በቃፊር በር፣ ላንታ ከሚባል ከፍታ ትይዩ እንድሞከር አንዲህ አለ፤ "ስላሴን መያዝ ከፈለግህ በዚህ በኩል ሂድ፣ ነገር ግን መቅደላ መያዝ ከፈለግህ በላንታ በኩል መሄድ አለብህ።" ነገር ግን፣ ይህ መሆንም የሚችል አልነበረም። ለማከፋፈል በቂ የጦር ሀይልም አልነበረኝም። እንደዚህ ያለውን ሰፊ የተፈጥሮ ምሽጎች ስብስብ፣ በኔና በጦሩ ግንኙነት መስመር መሀል እንዲሆን አልፈለግሁም። ያሰብኩት ደግሞ፣ አውነተኛው አላማ መቅደላን መያዝ ሳይሆን፣ ቴዎድሮስ ሁሉንም መድፎቻቸውን የደረደሩበት ቦታ ስለሆነ ሰላምጌን ነው። ስለዚህ ፋላ ለሁሉም ቁልፍ ነው።

---

158 (በምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች)

በሚያዝያ 7፣ ወደ በሽሎ ወንዝ ወለል ወርጄ መሻገሪያውን ቃኘሁ። ወደ መቅደላ መሄጃ መደበኛው መንገድ በእሮጌ ሸለቆ በኩል ነው፤ ይህ ደግሞ ከሰላምጌ ግርጌ በቀኝ በኩል ባለ ወጣ ያለ ከፍል ጋር ይገናኛና ከሰላምጌ ተነስቶ በሽሎ ድረስ በሚወርድ ጎርባጣ ኮረብታ ይራዘማል። ተመሳሳይ ኮረብታ፣ ከፋላ ተነስቶ እስከ ወንዙ ድረስ ይወረድና ሸለቆውን በግራ በኩል ይዋሰነዋል። የዚህ ኮረብታ ከፍተኛ ቦታው ከእሮጌ ሸለቆ ወለል ወደላይ 2ሺ ጫማ ይሆናል። የቦታው ትልቅነት፣ የሸለቆውን ሁለት ጎን በጥቂት እግረኞች ለመያዝ የማይሆን ነው ያደረገብኝ። የዚህ ሁሉ ቁልፍ ፋላ ነው ብዬ ሰለወሰንኩ ኮረብታውን ለመያዝ ወሰንኩኝ፤ ይህም፣ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች፣ ወደዚህ እሰቸጋሪ ተፈጥሮ በሚመሩ በጊመቦርጊና እፍጆ በሚባሉ በኩል ነበር። እዚህ ኮረብታ ላይ ከሆንኩ፤ በፋላ በሁለቱም በኩል መንቀሳቀስ እችላለሁ፤ ቀረብ ብሎ በማሰተዋል፤ ይህ እስፈላጊ ሆኖ ነው የተገኘው።

በአራተኛውና በዘጠነኛው እንቅስቃሴ መሀከል፣ የኔ ጦር፣ ሌተናነት ኮሎኔል ፓሪሽ ከሚመራው 45ኛው ሬጀመንት በመጡ በስድስት ኮምፓኒዎች ጨምሯል። ይህ ሬጅመንት ለማጓጓዝ ሲባል ወደ ኋላ ተጉትቶ ሰለነበር፣ ከዙላ ተነስቶ የሀያ እምስት ቀን ጉዞ አድርጓል። የ3ኛው የቦምቤይ ከንፍ፤ ቁጥር 1፣ በኮሎኔል ካምቤል የሚመራ ለአጣዳፊው የማጓጓዝ ተግባር ሲባል የሰባት ቀን ጉዞ ያከል መንገድ ወደ ኋላ ቀርቷል፤ ስሰዚህ ጥቃቱን ለመፈፀም ዕቅድ ውስጥ ያሰገባኋቸው የተዋጣለት መኮንንና በጣም ጎበዝ የሆኑ ወታደሮች እገልግሎት እጥቼያለሁ።

በሚያዝያ 9፣ ሁሉም ሠራዊት ከስፋ የሚወርደውን በሽሎ ወንዝን ቁልቁል ማየት ከሚቻልበት፣ በ3900 ጫማዎች ከፍታ ላይ ከሚገኘው ደልዳላ ቦታ ጠርዝ ላይ ሠፈረ። ሜጀር ቻምበርሊን ከ23ኛው የፑንጃብ ቃኝ ጦር ጋር፣ ከበሎቹ ከንፍ ድጋፍ በማግኘት የበሽሎን ወለል በመቆጣጠር የቴዎድሮስን መንገድ ጠገነ። 10ኛው ሮያል ኢንጂነርስ ኮምፓኒ ሬዲዮ ከፍል ደግሞ ግንኙነቱ እንዲቀጥል አደረገ። በካፒቴን ጉድፈሎው የሚመራው የሮያል ኢንጀነርሰና የማይራስና በምቤይ ምሽግ ሠሪዎች፣ የሚያስፈልገውን የእሸዋ ከረጢት፣ መሰላል፣ መማቢያ በሮችን ለመደርመስ በባሩድ የተሞሉ ከረጢቶችንና ሌሎቹንም ነገር አዘጋጀ። በመቅደላና በበሽሎ መሀከል የነበረው ብቸኛ ውሀ ማመላለሻ መሰመር በጠላት ተኩስ ከልል ሰር ሰለሆነ፣ ሁሉም የሠራዊቱ ውሀ ተሸካሚ ከፍሎች በትራንስፖርቱ ከፍል በካፒቴን ቤይንብሪጅ መሪነት ከሁለት ረዳት መኮንኖችና ከትራንሰፖርት ከፍሉ ሉተናንት ራመስቦተም ጋር በመሆን ተደራጅቶ፣ ሥራው፣ ከበሽሎ ወደላይ ውሃ እንዲመላለስ ማድረግ ነበር። ከፑንጃብ ጋማ ከብት መሪዎች የተወሰነ ቡድን በካፒቴን ግሪፍት መሪነት፣ ከትራንሰፖርት ከፍሉ ሉተናንት ጋሰሲ ረዳትነት ተደራጅተው በጦር ሜዳው የቆሰሉ ሰዎችን ማመላለሻ ቃሪዛዎች ተሠጣቸው። ይህ ሁሉ ዝግጅት ከጠናቀቀ በኋላ፣ በኮሎኔል ግሬቭስ የሚመራ ፈረሰኛ በሽሎን እንዲይዝ አደረግሁ፤ ነገር ግን እስፈላጊ ሲሆን ወደፊት ለመንቀሳቀስ እንደሚችል ሆኖ ነው፤ የቀረው ሀይል፣ በሰር ቻርልስ ሰታቭሊ ቀጥታ ትዛዝ በሽሎን እንዲያቋርጥ አደረግሁኝ። ሁለተኛው ብርጌድ፣ በብርጋዴር ጀኔራል ዊልቢይ እዛዥነት፣ ለርዳታ በሽሎ ወንዝ ወለል እንዲቆይ ተደረገ። ኛው ብርጌድ፣ በጀኔራል ስናይደር መሪነት፣ የጊምበርጊን ኮረብታ እንዲይዝና ለካምፕ የሚመች ቦታ

ለመምረጥ ወደፊት እንዲገሰግስ፤ በተጨማሪም በምክትሉ የሰንቅና ትጥቅ ክፍሉ ሀላፊ የሚመራውን የጠላትን ቦታ ለሚቃኘው ክፍል ሽፋን እንዲሠጥ ተደረገ። የሰንቅና ትጥቅ ክፍሉ ምክትል ባቀረበው ሪፖርት፣ ወደጊምቦርጊ መውጫው በጣም ቀጥ ያለ ሰለሆነ አስቸጋሪ ነው፤ ስለዚህ ንጉሡ የሠሩት፣ በአሮጌ ሽሰቆ የሚያልፈው መንገድ ቀለል ያለና፣ የተራራ መድፎችንም ሆነ ጓዝ ለማመላለስ አያሲጋም አለ። በዚህም ምክንያት የንጉሡን መንገድ ተከትለው እንዲሄዱ ታዘዙ።

የተጓዙ ቀዳሚው ረድፍ አፍጆ ሲደርስ፣ አኔም ከፊት ደረስኩ። የንጉሡ መንገድ፣ ከአሮጌ ማለፊያ የሚጀመረው ከአፊጆ 1200 ያርዶች ርቀትና 700 ጫማዎች ዝቅ ብሎ ነው። የሜጀር ቻምበርሌን የጉንጃብ ቃኝ ከፍሎች ወዲያውኑ ተልከው የማለፊያውን አናት እንዲጠብቁ አዘዝኩ፤ ቀሪው የብርጌዱ ክፍል ደግሞ በተቻለ ፍጥነት እንዲሰባሰብ ተደረገ። ሜጀር ቻምበርሌን ቦታውን እንደያዘ ወዲያውኑ፣ በካፒቴን ፌሎውስ የሚመራው የባህር ሀይሉ የሮኬት ብርጌድ፣ ማለፊያውን ተሻግሮ ብቅ አለ። እነሱን ተከትሎ፣ የኮሎኔል ፔን ክባድ መሳሪያ ክፍል በአግረኛ ጦር ታጅቦ መጣ። በዚህ ወቅት፣ ጠላት፣ ክፋላና ከሰላምጌ በኩል ተኩስ ከፈተ፣ ያነጣጠረውም ፑንጃቦችና አፊጆ ላይ ነበር። ያለው ርቀት 3ሺ ያርዶች ቢሆንም፣ የጠላት ተኩስ በትክክለ አላማው ላይ መድረሰ ችሏል። ይህም በትክክል በመተኮሱና ምናልባትም ከመጠን በላይ ባሩድ ስለተጠቀሙ ይሆናል፤ ነገር ግን አሩጉ ዝምብሎ የሚወድቅ አይነት ብቻ ስለሆነ ማንም ሰው አልተጎዳም። ከጠላት መድፍ ተኩስ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ፣ ብዛት ያለው ሠራዊት ከሰላምጌ ተነስቶ በፋላ ጎን ሲወርድ ታየ፤ በቁልቁለቱና በተራራው በፍጥነት ወርደው አርፌን አጥለቀለቁት። ብዙዎቹ የጠላት ወታደሮች ቀይ ለብሰዋል፣ አናም ከሩቅ ሲታይ ከኛ ወታደሮች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ፈጥረዋል። አምሰት መቶ የሚሆኑት አለቆች ፈረስ ላይ ናቸው። የባህር ሀይሉ ብርጌድ ተጣድፎ አፊጆ ላይ ከወጣ በኋላ፣ እያንዳንዱ የሮኬት ቱቦ እንደተዘጋጀ፣ የሚገሰግሰው የጠላት ጦር ላይ ተኮሰ፤ የጠላት ጦርም በመደናገጥ እንደመቆም አለና አንዳንድ ቦታም ወደኋላ አፈገፈገ፤ ነገር ግን፣ በሌላ አቅጣጫ ባሉት ወደሌሎቹ፣ ወደፊት መግስገስ ቀጠለ። ሰር ቻርለስ ስታቨሊን፣ በዚህ ጊዜ፣ ተጠግቶ የነበረውን ቀሪውን እግረኛ ክፍል ወደፊት እንዲያመጣና ጥቃቱን እንዲመክት መመሪያ ሠጠው። 4ኛው ሬጅመንት (የንጉሡ) በኮሎኔል ካሜሩን ስር፣ እነሱን ተከትሎ ደግሞ የበቪሊ ቤሉቺዎችና በሜጀር ፕሪቻርድ የሚመሩት ሮያል ኢንጂነርስ፣ በካፒቴን መዶነል የሚመሩት የቦምቤይ ምሽግ ሠሪዎች፣ በፍጥነት የቁልቁለቱን መንገድ ይዘው ወደ አሮጌ ሜዳ ወረዱ። በመጨረሻም ጠላትን ከፊትለፊታቸው ማየት በመቻላቸው ያልተገደበ የደስታ ስሜት ነው የፊጠረባቸው። ለማጥቃት በዝግጁ ሁኔታ ከአሮጌ የሚለያቸው ትንሽ ዳገት ላይ ወጡ፤ ወዲያውኑም ከጠላት ጋር ተገናኙ፤ የአለቆቻቸው ከፍተኛ ጥረት ቢኖርም፣ የጠላት ወታደሮችን እንዳለ ወደ ኋላ መግፋት ቻሉ። ይህም የሆነው የሰናየደር ጠምንጃዎች ተኩሰ ባሰየው አሰከፊ ውጤት ነው። ጀግንነት የተሞላበት ብዙ ሙከራ በአቢሲኒያውያን ተደርጎ ነበር፣ ነገር ግን ብዙዎቹ አለቆቻቸው ወደቁ፤ አናም ከኛ በግራ በኩል ወደሚገኘው ወደ አሮጌ ሽለቆ ቁልቁለቱን ለመውረድ ተገደዱ። የተወስኑት ደግሞ ወደላይ ወደፋላ ጎን አፈገፈግው

በቁልቋል ቁጥቋጦች ጀርባ ተከለሉ፤ ከዚያም ሆነው፣ በስታቭሊ ቀኝ በኩል በሚተኩሱት ተኩሰ ጉዳት አደረሱ። ካፒቴን ፌሎውሰ ቀድሞ በሚደርሰው እግረኛ እስኪሸፈን ድረስ ሮኬቶቹን ሲተኩሰ ነበር። ከዛም ለሰር ቻርለስ ሰታቭሊ ርዳታ እንዲያደርግ ተላከ። የሮኬቶቹ ተኩሰ፣ የበቪሊ ቤሎቺዎች ከሚተኩሱት ተኩስ ጋራ የሮያል ኢንጂነርስ በሉተናንት ቴይለር ስር ባሉ ሁለት ከባድ መሳሪያዎች እገዛ ተደርጎላቸው፣ በስታቭሊ ጎን የነበረውን ጠላት በማጥራት የተፈጠረውን ችግር እስወገዱት። ከዚህ በኋላ ሮኬቶቹ ፋላ ላይ እንዲያነጣጥሩ ተደረጉ፤ በኋላ እንደተረዳሁት፣ በጣም ጥሩ ውጤት ነበር ያሰገኙት። የጠላት የተወሰኑ ወታደሮች ቡድን በአፈጆ በኩል ለማለፍና፣ በኛ በቀኞችን በኩል ለመዞር ሞከሮ ነበር፤ ነገር ግን በጥቂት ሮኬቶች ተገድቦ፣ በ ኬ ኮምፓኒ፣ በማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች በሜጀር ፐረንደርጋስት መሪነት፣ ሌፍተናንት ኮሎኔል ሎች ከ3ኛው በምቤ ፈረስኛ ከፍል ጋር በመሆን እናም የእግረኛ ርዳታ ተጨምሮበት ሰዎቹ ተበተኑ። ወደ ግራ በኩል፣ ኮሎኔል ሚልዋርድ፣ ከፔን ከባድ መሳሪያ ጋር በመሆን በ4ኛው (የንጉሡ) ሬጅመንት ከፍል በካፒቴን ኪቶ መሪነት ታጅቦ፣ የ23ኛው ቃኝ ጦር በካፒቴን ፒተርሰን መሪነት ተደምሮ፣ መድፎች ከፋላና ከሰላምጌ ተኩስ በጀመሩበት ሰአት፣ ከአሮጌ ማለፊያ ተነስቶ ወደላይ እየወጣ ነበር።

የቴዎድሮሰ ወታደሮች ከሰላምጌ እየወረዱ መምጣታቸውን ሲመለከት፣ ኮሎኔል ሚልዋርድ፣ ጠንካራ ቦታ ላይ በመሆን በፔን ከባድ መሳሪያዎች ተኩሰ ከፈተ። ማለፊያውን ለመሸፈን ቃኝ ጦሩን ይዞ የነበረው ሜጀር ቻምበርሌን ወደግራው በመንቀሳቀሰ ኮሌኔል ሚልዋርድን ተቀላቀለ። ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውያን ሚልዋርድ ወዳለበት ቦታ እየገሰገሱ ነበር። በፔን ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ ይደርስ በነበረው ጉዳት ሳይበገሩ፣ በቆራጥነትና በሥርአት ወደፊት ይገሰግሱ ነበር። ቻምበርሌን ከቃኝ ጦሩ ጋር በመሆን ይህንን ጥቃት በፍጥነትና በወኔ ነበር የተጋፈጠው፤ ብዙ እልቂት በማድረሰም፣ ሰዎቹን በግራ በኩል ፊት ለፊት ወዳለው ሸለቆ ገፋቸው። ያም ሆኖ ግን ከአቢሲኒያኖች በኩል ጀግንነት የተሞላበት መከላከል በማድረግ ያለምንም ፍርሀት ከጉንጀቢዎች ጋር ጨበጣ ውጊያ አደርገው ነው። በጦር መወጋት ምክንያት የታዩት ቁስሎች ምን ያህል ተጢጋማተው እንደተዋጉ ምሰክርነት ይሰጣሉ። ራቅ ባለው በግራ በኩል፣ ጠላት፣ ብዛት ባለው ሀይል ወደ አሮጌ ሸለቆ መግቢያ በኩል እየገፋ ነበር። በዚያ በኩል ደግሞ ጓዝ እየደረሰ ነበር። የጓዙ ኃላፊ፣ የ4ኛው (የንጉሡ) ሬጀመንት ሉተናንት ለዊኒ፣ በከፍተኛ ዝግጅት ጓዙን በማያሰጋ ቦታ ከመረ። ጓዙን ጠባቂዎች፣ ሁለት ኮምፓኒዎች ከ4ኛው፣ አንድ ከ10ኛው ሬጅመንት የተውጣጡ፣ በካፒተን ሮበርት ስር በመጀመሪያ፣ ከዛም ሲጎዳ ከ10ኛው (ሁሳርሰ) ሉተናንት አባዲ መሪነትና ለዊኒ ጋር በመሆን ወደፊት በመምጣት፣ ጠላት ወደ አሮጌ ሸለቆ እንዳይወርድ በሚገባ ተከላከለው ጠበቁ። በአሮጌ ሸለቆ መግቢያ ላይ እንዲቆሙ ተደርገው፣ ከዛም በጓዝ ጠባቂዎች ወደኋላ ተገፍተው፣ በቻምበርሌን ቃኝ ጦርና ከ4ኛው ከመጡት ሲታቭሲ በጎናቸው በኩል ባዞረባቸው በሁለቱ ካምፓኒዎች ተከበው፣ የጠላት ተዋጊዎች ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባቸው። ቁጥራቸው በርከት ያሉት፣ በቀጥታ በሚተኮሰባቸው የተራራ መድፎች ተመተው ሲወድቁ ይታያሉ። የቴዎድሮሰ

ወታደሮች ማሸነፍ የለመዱ ስለሆነ በሙሉ ልብ ነበር ወደፊት የገሰገሱት። ከነበሩበት ጥሩ መከላከያ ቦታቸው፣ ራሳቸውን አውርደው መመለሻ ወደሌለበት ቦታ ገብተዋል። በቴዎድሮስ ቃል የተገባላቸው፣ ከእንግሊዞቹ የማረኩት ነገር የራሳቸው እንደሚሆን ነበር፤ በመጨረሻም ከሜዳው ተገፍተው ቢሄዱም ጠንካራ ፍትጊያ ሳያደርጉ ቀርተው አልነበረም።

በዚህ ውጊያ፣ በአብዛኛው ወቅት ከባድ ዝናብ እየወረደ ነበር። ወታደሮቹ በዝናብ ርሰውና ደክመው ነበር፤ ሆኖም ባገኙት ድል ሰሜታቸው በጣም ከፍ ብሎ ስለነበር ለአዳሩ ካምፕ መፈለግ ጀመሩ። ወደ አሮጌ ማለፊያ የሚወስደውን መንገድ ተቆጣጥረው፣ ሳይመሽ፣ የአቢሲኒያን ወታደሮች ለመግጠም ወርደው የመጡበትን የአፍጆ ከፍታን መልሰው ያዙ። የቆሰሉት፣ በሆስፒታሉ ሀላፊ በዶክተር ቸሪ መሪነት እርዳታ ተሰጣቸው። ብዙ የቆሰሉ አቢሲኒያውያንም ቢሆን፣ በኛ ወታደሮች ከጦር ሜዳው ወደ ሆስፒታሉ ተወሰደው እርዳታ እንዲሠጣቸው ተደረገ። ማምሻውን የደረሰው 2ኛው ብርጌድ፣ በገኘው ብርጌድ በውጊያ የተያዘውን ቦታ ተረከበ። በነበረን የተቻለ መረጃ፣ የአቢሲኒያ ተዋጊዎች ቁጥር ግምት ከአምስት ሺ ያላነሰ ነበር፤ ሶስት ሺ የሚሆኑት ጠመንጃ የያዙ ሲሆን፣ ሌሎቹ ግን ከዛ ባነሰ ሁኔታ ነው የታጠቁት። ከውጊያው አንድ ቀን ቀደም ብሎ፣ ቴዎድሮስ አዲስ ጠመንጃዎችን ለወታደሮቹ አድለው ነበር። በጠላት በኩል የደረሰው ጉዳት በትክክል ሊገመት አይችልም፤ 349 የሞቱ ሰዎች ከፊት ለፊታችን በግራ በኩል ባለው ቦታ ተቀበሩ። እነዚህ፤ ሁሉም የወደቁት በስታቭሊ የመጀመሪያው ጥቃት ነበር። በጣም የቆሰሉ ሰላሳ አቢሲኒያውያን ወደ ሆስፒታሉ ተወስደዋል። የቴዎድሮስ የጦር አበጋዝ፣ ፊታውራሪ ገብርዬና ሌሎችም የሚታወቁ አለቆች ከወደቁት መሀል ነበሩ። ሌሊቱን፣ የወደቁ ጓደኞቻቸውን የሚጠሩ የአቢሲኒያውያን ጩኸት ይሰማ ነበር፤ ብዛት ያላቸው የቆሰሉ ሰዎችም ከውጊያ ሜዳው ተወስደዋል። የቴዎድሮስ ወታደሮች አጃቸውን በሠጡበት ወቅት ብዛት ያላቸው የቆሰሉ ሰዎች አይተናል። የብሪታንያ ጉዳት ደግሞ ሀያ ብቻ የቆሰሉ ሲሆን ሁለቱ ሞተዋል። የዚህ የጉዳት ልዩነት የመጣው፣ አቢሲኒያኖቹ ባደረጉት ቆራጥ የሆነ ያልተቋረጠ፣ በደንብ በሰነ ሥርአት ከተደራጀና በበለጠ ሁኔታ ከታጠቀ ወታደር ላይ ባደረጉት ጥቃት ነው። የ23ኛው ቃኘ ወታደሮች ከታጠቁት መሳሪያ ጋር ሲወዳደር አንኳን የበለጠ ታጠቁ ማለት አይቻልም። 23ኛው የታጠቀው ጠመንጃ አቢሲኒያኖች ከያዙት ባለሁለት አፈሙዝ ጠምንጃ ጋር አይወዳደርም ነበር። ያልተጣደፈ ውጊያ ነበር፤ የጠላት ወታደሮች በየትኛው ባገኙት የተመቸ ቦታ ለማጥቃት ይመለሱ ነበር። እኔም የጠላት ወታደሮችን ወደላይ ወደከፍታው ማሳደድ እንዲቆም ትዛዝ ሠጠሁ፤ ምክንያቱም የመጨረሻው ውጤት የኛ ወታደሮች ወደ ቦታቸው መመለስ ስለሆነ፣ ይህ ደግሞ አዲስ የጉልበት ስሜት በጠላት ወታደሮች እንዳይፈጥር ነበር።

በ11፣ በጠዋት፣ ሉተናንት ፕሪዶና ሚስተር ፍላድ በደጃች አለሜ ታጅበው ወደኔ ካምፕ መጡ። ደጃች አለሜ የአፄ ቴዎድሮስ ታማኝና አማችም ናቸው፤ ሁሉም የመጡት የሰላም ጥያቄ ይዘው ነው። እኔ ስመልስም፣ ቴዎድሮስ፣ ሁሉንም እስረኞች የሚለቁ ከሆነና፣ ራሳቸውም ለእንግሊዝ ንግሥት እጃቸውን የሚሠጡ ከሆነ፣

ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚገባውን ክብር ለመሥጠት ቃል እንደምገባ ነው። ሉተናንት ፕሩዶ፣ የዚህን ቃል የያዘውን ደብዳቤ ይዞ ወደ መቅደላ ተመለሰ። እኩለ ቀን ሲሆን ግን፣ ደጃች አለሜ ቀርተው፣ ከሚሰተር ፍላድ ጋር በመሆን ወደ እንግሊዝ ካምፕ ተመለሰ። ያመጣው ደብዳቤ፣ የቴዎድሮስ ፊርማ ወይም ማህተም የሌለበት ሲሆን እኔ ያቀረብኩትን ጥያቄ የማይቀበል ነው። እኔም ደብዳቤዬን መልሼ ላኩኝ። ሉተናንት ፕሪዶና ሚሰትር ፍላድን፣ ከዚህ ውጭ ሌላ ድርድር እንደሌለ አንዲያስታውቁ መልሼ ላኳቸው። እኔ የወሰንኩት፣ እስረኞችን መረከብ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ ቅጣት፣ በተለይም እስረኞች ከቁጥጥር ነፃ ከሆኑ በኋላ፣ በፍፁም አስፈላጊና መፈፀምም ያለበት ነገር ነው። ቴዎድሮስ ተበሳጭተው በእስረኞች ላይ ሊፈፅሙ የሚችሉትን ማሰብ በጣም የሚያም ነገር ነው፤ የነሱን ደህንነት ለማስጠበቅ የተማመንኩበት ነገር፣ የቴዎድሮስ ወታደሮች ድል የተመቱበትንና ሞራላቸውን የገደለውን ግጭት ሁኔታ እንደ አዲስ መቀሰቀስ ነው፤ በዚህም ቴዎድሮስ ራሳቸው ነፃ አይሆኑም፤ ያሰፍላጎታቸው ደጃች አለሜ ቴዎድሮስን መከዳታቸውን ማስታወስ ነበረብኝ። በሌላ ወገን፣ ደጃች አለሜን ማሰመን በቻልኩበት በማስፈራራዬ ተማመንኩኝ፤ በዚህም፣ ማንም እውሮፓውያኑ ላይ የሚጎዳ ነገር ያደረገው ሰው ላይ የማይታክት ማሳደድ እንደማደርግና እንደምቀጣ ገልጫለሁ። የእንግሊዘ ሀይል መቅደላ መድረሱንም በመጠቆም፣ ልንቀጣው የፈለግነው ሰው የቱንም ያህል ሩቅ ቢሆንም በማንኛውም የአቢሲኒያ ማዕዘን ተደብቆ ሊያመልጥ እንደማይችል ገለጥኩ።

ሉተናንት ፕሪዶ ወደ መቅደላ ሲመለስ፣ በመንገድ ላይ፣ ከራሳምና ከቀሪዎቹ የእንግሊዝ እስረኞችና ከሌሎች ከተሰያዩ ሀገራት አስረኞች ጋር ተገናኘ። ማምሻውኑ ሁሉም እስረኞች የኔ ካምፑ ደረሱ። በደጃች አለሜ ጥያቄ መሠረትና በገባሁት ቃል ለሀያ አራት ሰአታት ምንም አይነት የማጥቃት እንቅስቃሴ ከማድረግ ተቆጠብኩ። አርባ ስምንት ሰአታት እንዳለፉ፣ ቴዎድሮስ እጃቸውን አልሠጡም። በደረሰኝ አስተማማኝ መረጃ፣ የቴዎድሮስ ወታደሮች ከደረሰባቸው ሽንፈት እያገገሙ ነው። በ10፤ በማታ፣ መቅደላ መድረስ ያልቻሉ ወታደሮች ተመልሰው ከጦሩ ጋር ተቀላቅለዋል፤ አዲስ የመከላከያ እደረጃጀቶች እየተደረጉ ነው። ከዚያም ጋር፣ ቴዎድሮስና የጦር አለቆቻቸው፣ ከታች ከደልዳለው ቦታ በሰፈረው በ2ኛው ብርጌድ ላይ ሌሊት ጥቃት ለማድረስ እያሰቡ እንደሆነ ነው። ስለዚህ እኔም የጠላትን ቦታ ለማጥቃት መዘጋጀት ጀመርኩኝ። መጀመሪያ ያሰብኩት፣ በካምፓችን ፊት ሰፊት ያለውን ፋላን ከሰላምጌና ከሰላሴ የሚመጣውን ተኩሰ በሚከልል ሁኔታ ከጎን በኩል ለማጥቃት ነበር። ሆኖም ጠላት ላይ በደረሰው ለውጥ ምክንያት፣ ቴዎድሮስ፣ በመቋሰል፣ በሞትና በመከዳት ከነበራቸው ጦርና ጀግኖች አለቆቻቸውን ማማሹን ሰላጡ፣ ሰላምጌን በንጉሥ መንገድ በኩል ለማጥቃት ወሰንኩ። ለዚህ የሚያስፈልገው ዝግጅትም ተጠናቆ፣ ለከባድ መሳሪያዎችም ቦታ ተቀይሮና ከተጠመዱ በኋላ፣ የመጣልኝ ዜና፣ ቴዎድሮስ መቅደላን ለቀው ሄደዋል እናም ብዙ አለቆቻቸው

ከነተከታዮቻቸው እጃቸውን መስጠት ይፈልጋሉ ነበር[159]። እጅ መስጠቱን ተስማምቼበት፣ ሰር ቻርለስ ስታቨሊን ጥንቃቄ ሳይጎድል ከዚህ ቀደም የታቀደው ዕቅድ እንዳለ ወደ ሰላምጌ አንዲገፉ አዘዝኩ።

የነበረው የውሀ እጥረት፣ መቅደላ ፊት ለፊት የሚበቃ የፈረሰኛ ሀይል ሊያስቆም አልቻለም። በሀንድ መኮንን ስር የነበረው የራሴ የግል እጃቢ ቡድን ብቻ ነው የቀረው። የተወሰኑ የሌላ ከፍሎች በሉተናንት ስኮት እየተመሩ የመቅደላን የምዕራብ ጎን እንዲጠብቁ ተላኩ፤ አነሱም፣ የቃፊር በር ግዳጁን ፊፅሞ የሚመለሰውን በኮሎኔል ግሪቨስ የሚመራው ፈረሰኛ አስኪመለስ ድረስ ጥሩ ቦታ ሆነው ነበር። ቃፊር በር በኦሮሞዎቹ እየተጠበቀ ነበር። ከጠቅላይ ጽ/ቤቱ ፈረሰኛ ስንዲ ሆርስ በሜጀር ብሪግስ፣ ከ3ኛው ድራጎን ዘቦች አንድ ከፍል፣ ከ3ኛውና 12ኛው ፈረሰኛ በሜጀር ሚለር ስር በሽሎ ላይ ቁልፍ ቦታ ይዞ ይጠበቅ ነበር፤ በምንጀራ ሸለቆ በኩል ጠላት እንዳይሸሽ ለመዝጋት ነው። በሉተናንት ቡቨሊ የሚመራ የበሉችዎች አንድ ከፍል፣ በፋላ ኮረብታ በኩል፣ ወደላይ ወጥቶ በጣም ወሳኝ የሆነ ቦታ ያዘ፤ በኮሎኔል ፊልድ ስር ከዕዝ ጽ/ቤቱ የነዐኛው ከንፍ ተጨማሪ ማጠናከሪያ ድጋፍ ተጨመረላቸው። መድፎቹ በቦታ ከተጠመዱ በኋላ፣ እግረኛው ወደፊት ቀጠለ፤ ይህም ከፍል፣ በመረጃ ከፍሉ በካፒቴን ስፒዲ፣ ከ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ በኮሎኔል ሎች መሪነት ታጅቦ ቀደም ብሎ እየመራ ነበር። እነዚህ የተላኩት፣ እጃችን እንሰጣለን ካሉት አለቆች ጋር ግራ መጋባት እንዳይፈጠር ለመነጋገር ነበር። ምንም አይነት የመከላከል ሁኔታ አልታየም። ሰር ቻርልስ ስታቨሊ፣ በአስቸጋሪ የአለት ከፍተት በኩል ወደ ሰላሴና ሰላምጌ መግቢያ መድረስ ችሏል። በስላምጌ ፣ መሳሪያቸውን አውርደው እጃቸውን የሠጡ የታጠቁ ተዋጊዎችን ቁጥርና በስፍራው የተገኘውን ህዝብ፣ ማለትም፣ ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት ቁጥር በትክክል መገመት ያስቸግራል። የተማረኩ ጠመንጃዎችን መሰብሰብና መጠበቅ አስፈላጊ ነበር። ወደ መቅደላ እንቅስቃሴ ከመጀመሬ በፊት፣ እጃቸውን የሠጡትን ወታደሮችና የተከተሏቸውን ሰዎች ወደታች ወደሜዳው መውሰድ አስፈላጊ ነበር። ቴዎድሮስ ራሳቸው፣ ለማምለጥ ምንም ሙከራ ሳያደርጉ፣ ለመከላከል በመዘጋጀት በመቅደላ ፊት ለፊት በአልበገር ባይነት እየተፈታተኑን ነበር። ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን፣ ሁሉም ሰው ሰላምጌን ከለቀቀ በኋላ፣ መቅደላ ላይ ወዲያውኑ ጥቃት እንዲጀመር ትዛዝ ሰጠሁ። ወደ መቅደላ መግቢያው፣ ከሰላምጌ ወለል በ300 ጨማዎች ከፍ ይላል። ዳገቱም በጣም ቀጥ ያለና መንገዱም የማይመች ነበር። የመግቢያውን አስቸጋሪነት ካየሁ በኋላ ጥቃቱ በተቻለ መጠን ከፍተኛና ጠንካራ እንዲሆን አደረግሁ። ያለኝን ከባድ መሳሪያ በሙሉ ቦታው ላይ እንዲያነጣጥርና እንዲሸፍን በማድረግ የጠላትን የመከላከል ችሎታ ለማዳከም ነበር፤ በዚህም ሊደረስ ይችል የነበረውን የሰው ጉዳት ለመቀነስ ነበር። የአጥቂው ሀይል የተውጣጣው፣ 2ኛው ብርጌድ በ33ኛው (የመስፍኑ) ሬጅመንት በመመራት፣ ከሮያል ኢንጂነርስ፣ ከማዳራስና ቦምቤይ ግንበኛና ምሽግ ቆፋሪዎች ጋር ነበር። የኃለኞቹ፣

---

159 ቴዎድሮስ ለጦር አለቆቻቸውንና ተከታዮቻቸውን መሀላችሁን እንስቻለሁና ሂዱ በማለት ለቀዋቸዋል።

የነበረውን መለናከል እንዲያስወግዱ ነበር፤ የነኛው ብርጌድ ደግሞ በቅርብ ርዳታ እንዲያደርግ ሆኖ ነው። የመድፍ ወይም ከባድ መሳሪያው ተኩስ በመግቢያውና በምሽጉ በለሜን በኩል እንዲያተኩር እደረግኩኝ፤ የለሜኑ ከፍል በወታደሮች ጎጆዎች የተጣበበ ስለነበር ነው፤ በተቻለ መጠን የአቢሲኒያ አስረኞችና ሲቪሎች ያሉበትን መህል ላይ ከፍ ያለውን ቦታ እንዳይነካ ለማድረግ ምክርኩ። ጠላት በጥንቃቄ ራሱን ደብቆ ስለነበር፤ ቦታው ጭር ያለ ሰው የሌለበት ይመስል ነበር። ነገር ግን ወታደሮቻችን መግባት ሲጀምሩ፣ ቦታው፣ ጠመንጃቸውን በወረወሩ ወታደሮች፣ የተፈቱ አስረኞች፣ ብዛት ያላቸው ቴዎድሮስን ወደው ወይም ሳይወዱ ይከተሉ በነበሩ ሰዎች ተሞልቷል። በለው እጅ የተሠራው መከላከያ ደግሞ፣ የካብ እጥር ሲኖረው፣ በላዩ ላይ፣ ሾህ ባለው የእንጨት መስናከል ተሸፍኗል፤ በመሀሉም ጠባብ በደንጋይ የታቀፉ መግቢያዎች አሉት። ዝቅ ያለው መከላከያ ከውስጥ በኩል ነው የተሠራው፤ ከፍያለው ደግሞ ዝቅ ብሎ ከተሠራው መከላከያ በሰባ ጫማ ከፍ ይላል። ከወታደሮቹ ጎጆዎች፣ ጠባብ፣ ቀጥ ያለ ዳገት ያለበት የተጠማዘዘ መንገድ ወደዚህ መከላከያ ይወስዳል። የዚህ መከላከያ ጥቃት የተካሄደው በለር ቻርለስ ስታቨሰ ሲሆን፣ ወታደሮቹ በጀግንነት የፈፀሙት ተግባር ነበር። የዚህ ሪፓርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዟል። እንደ ዕድል ሆኖ መከላከያዎቹ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አልተሠሩም፤ ምንም እንኳን ጥቃቱ ከጠላት በኩል ጀግንነት በተሞላበት ሁኔታ በተኩስ ቢፋጠጥም፣ ተኳሾቹ ወደነሱ እየገሰገሰ የሚሄደው ጥሶ የሚገባው ወታደር ላይ ማነጣጠር አልቻሉም፤ እንደሱ ካደረጉ ደግሞ ራሳቸውን ከሰናይደር ጠመንጃዎች ከሚተኮሰው ፈጣንና ገዳይ ለሆነ ጥይት ያጋልጣሉ። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ከኛ በኩል የሚደርሰው አደጋ ቀለል ያለና ብዙም ውጤት የማይኖረው ይሆናል። የሮያል ኢንጂነርስና መንገድ ሠሪዎቹ ከ33ኛው ሬጅመንት ቀዳሚ ከፍል ጋር ሆነው መግቢያውን ከመጣሳቸው በፊት ቀደም ብለው ሄደው ስለነበር፣ ዘጠኝ መኮንንኖችና ወታደሮች የመቁሰልና ቀላል የስውነት አደጋ ደርሷባቸዋል።

ከረጅም ጊዜ በኋላ መግቢያ መንገድ ሲከፈት ተቻለ። ይህም በመግቢያው አካባቢ ተዘጋጅቶ በነበረው መሰላል አማካኝነት የ33ኛው ቀዳሚ ግንባር ስዎች በአለቱ በኩል ወጥተው የመከላከያ ቦታ ማለፊያዎችን ስለከፈቱ ነበር። ጠላትም ወደ ሁለተኛው መከላከያ እንዲያፈግፍግ ተገደደ፤ ከዚያ በኋላ ግን መከላከሉ ቆመ። በውጭ በኩል በነበረው መግቢያው በር አካባቢ፣ ቁጥር ያላቸው የቴዎድሮስ ታማኝ አለቆች ሞተው ተገኙ፤ ከነዚህ መህል እንዱ ደጃች እንግዳ ነበር። ደጃዝማቹ ሁሉንም አስረኞች እንግደላቸው ብሎ ቴዎድሮስን ተማጥኖ ነበር፤ ነገር ግን ጉዳዩ በሌሎቹም ግፊት ሳይደረግ ቀርቷል። በሁለተኛው ማለፊያ በር አጠገብ ቴዎድሮስ ወድቀዋል። የ33ኛው ሰዎች ማሰፊያውን ጥሰው ሲገቡ፣ ቴዎድሮስ ወደቁ፤ በኋላ እንደለማሁት ከሆነ በራሳቸው እጅ ነው። ወታደሮችም ወዲያውኑ ሸሽት ጀመሩ፤ እንዳንዶቹ በቃፊር በር በኩል ነበር፤ በሩም ወታደሮቹ ሲሸሹ በወረወሯቸው ጠመንጃዎች ተጨናንቆ ነበር። ከነዚህ ከሸሹት ወታደሮች አብዛኞቹ በአሮሞዎች እጅ ወደቁ፤ የቀሩት ደግሞ፣ በጓደኞቻቸው ላይ የደረሰውን ዕጣ ካዩ በኋላና ከአሮሞዎች በኩል የሚመጣውን የዛቻ ጥሪ ሲሰሙ ወደ መቅደላ ተመልሰው እጃቸውን ሠጡ።

የመቅደላ ሀላፊነት ለብርጋዴር ጄኔራል ዊልቢ ነው የተሠጠው፤ እሱም ከ33ኛውና ከ45ኛው ሬጅመንት ከንፍ ጦር ጋር ቦታውን ተቆጣጠረ። በጣም ብዛት ያላቸው ሰዎች ስለሚኖሩበትና የሰዎቹ ቁጥርም ከመጠን በላይ ስለነበር፣ ሥርአት ማስያዝ ቀላል አልነበረም። በየመግቢያው ላይ ዘቦች ተመደቡ፤ ይህም ለደህንነት ወይም ጥቢቃ አስፈላጊ ስለነበር ነው። የቴዎድሮስ ቤተሰቦች በሚስተር ራሳም ሃላፊነት ስር ተመድበው፣ በተቻለው መጠን የሚያስፈልጋቸው ጥቢቃና እንክብካቤ እንዲያደርግላቸው ተጠየቀ። እቢሲኒያውያን እሰረኞች ከእግር ብረትና ሰንሰለታቸው ተፈቱ። ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውን፣ በዚያን ጊዜ ጉዳያቸውን ለመመርመር ጌዜም ስላልነበር፣ ለመጠበቅ እንዲቻል ወደመሀል ቦታ እንዲሰበሰቡ ተደረጉ። እነሱም ወዲያውኑ ጎጆዎችን ቀልሰው መጨረሻ መቅደላ ለቀን እስከንወጣ ድረስ በቦታው ቆዩ። በ15፣ 4ኛው(የንጉሡ) ሬጀመንት፣ መቅደላን ከ33ኛው ተረከበ፤ 45ኛው ደግሞ ወደ ሰላምጌ ተዛውሮ፣ በኮሎኔል ፊልድ የሚመራውን 10ኛውን ድጋፍ እንዲሠጥ ተደረገ። ይህም የተማረኩትን መሳሪያዎችና መድፎቸን ለመጠበቅና፣ እነዚህን መሣሪያዎች ለማውደም ለሚዘጋጁ ሰዎች ተጨማሪ የሰው ሀይል ለመስጠት ነበር። የመቅደላ ነዋሪዎች ደግሞ እሮጌ ላይ እንዲሰበሰቡ ተደረገ፤ ይህም የሆነው ቀንና ሌሊት ሰዎቹን ለመዝረፍና ለመግደል አድፍጠው ከሚጠብቋቸው ኦሮሞዎች ለመጠበቅ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ስለነበረ ነው።

ምንም እንኳን ከኦሮሞዎቹ ንግሥቶች ጋራ መልካም ወዳጅነት ቢኖረንም፣ ሰዎቻቸው ግን በመጠኑ እንኳን ራሳቸውን ስለማይቆጣጠሩ የመጥጥ ውሃችን እንዳይወስዱና የጋማ ከበቶቻችን እንዳይነዱብን፣ በመተኮስ፣ በተደጋጋሚ ማባረር ነበረብን። የተወሰኑት የነሱ ሰዎች ለዘረፋ መቅደላ ድረስ ይፍረው ገብተው በ33ኛው ዘብ ወታደሮች ተያዙ። በ15ና በ16፣ ጥትቃቸውን የፈቱ ወታደሮችና ህዝቡ ከእሮጌ መውጣት ጀመሩ። ሁሉም አይነት አሰተያየት ተደርጎላቸው፣ የነበራቸውን ንብረት ይዘው እንዲሄዱ ተፈቀደላቸው። ከእሮጌ ሲወርዱ በእግረኛ ወታደሮች እንዲጠበቁ ሲደረግ፣ በሽሎን ተሸግረው ዋድላ እሰኪደረሱ ድረስ ደግሞ መንገደኞቹ በፈረሰኞች እንዲጠበቁ ተደረገ። አብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች፣ በቴዎድሮስ ብዙ መከራ በደረሰባቸው በደላንታ ገበሬዎች ያሰምንም ጥርጣሬ ትንሽም ምህረት አይሠጣቸውም ነበር፤ ሆኖም ለእንግሊዝ ሠራዊት እጃቸውን ሰለሠጡ፣ ደህና ቦታ ደርሰው ወደ የቤታቸው እስኪሄዱ ድረስ የነሱን ደህንነት መጠበቅ የኛ ሀላፊነት ነበር።

በ17ኛው ጠዋት፣ እሰክ ቀኑ አስር ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ ማንም ሰው ከመቅደላ እንዲወጣ ትዛዝ ተላለፈ። በዚያ ሰአት፣ ሁሉም መቅደላ መግቢያ ላይ የተማረከ መሳሪያ እንዲወድም ተደርጎ፣ መግቢያ ማለፊያዎችም እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ በመቅደላ የሚገኙ ሁሉም ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደረገ። ሊረዷቸው የሚችሉ ጓደኞች የሌላቸው የቆሰሉ አቢሲኒያውያን ወደኛ ሆስፒታል ተወሰዱ። ዝሆኖቹና ከባድ መሳሪያውች በ15 አስቀድሞ ሰለተላኩ፣ በሚያዝያ 18፣ ሠራዊቱ ወደ ባህር ዳርቻ ጉዞው በሽሎን መልሶ ተሻገረ። የዘመቻውን ፕላንና ፎቶግራፎች በአከብሮት አያይዣለሁ። የህንን መልክት አሰቀድሜ መጨረስ ባለመቻሌ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ነገር ግን በዚህ አሰቸጋሪ ህገር ጉዞ ማድረግ፣ ቀናቱንና አብዛኛውን ጊዜ

ስለሚወሰድና እና ባለኝ ጊዜም ላይ ጫና ስለሚፈጥር፣ ከአቅሜ በላይ ነው የሆነብኝ። በሚቀጥለው መልክቴ፣ የሪፖርቱን ማጠቃለያ እንደምጨርስ ተስፋ አለኝ፤ ይህም የአብዛኘውን ጦር መመለስ ስለሚጨመር፣ እናም ከዛ በኋላ ለንግስታችን መንግሥት ለእውቅና መቅረብ የሚገቡቸውን ሁኔታዎች ማቅረብ ስለምችል ርካታ ይኖረኛል። ይህም፣ በሥሬ ለማዘዝ ከብሩ ያጋጠምኝን የመኮንኖችና የወታደሮችን አገልግሎት በከፍተኛ ሁኔታ ለመፃፍ ስለማልቸል እሁን ብፅፍም ደግሞ በበቂ ሁኔታ የሚገባውን ያህል ስለማይሆን ነው።

ታዛዥ አገልጋይዎ በመሆኔ ከብር ይለማኛል
አር ናፒየር፣ ሉተናንት ጀኔራል
የጦር ጠቅላይ አዛዥ

በሚያዝያ 13፣ በመቅደላ ምሽግ የተማረኩ ከባድ መሳሪያዎች መመለስ

ከብራስ የተሠሩ 3 ባለ አምስት ኢንች አፈሙዝ 56 ፓውንደሮች
አንደ ባለ 18 ፓውንድ ዲቶ
አራት ብራስ 6 ፓውንደር ዲቶ (የቱርክ)
ሁለት ባለ 6 ፓውንደር ዲቶ (የአንግሊዝ፣በካስፒሮ የተሰራ)
አንድ ባለ 6 ፓውንደር (የፈረንሳይ)
አምስት ባላ 24 ፓውንደር ሀውዜር (የፈረንሳይና በህገሩ የተሰሩ)
ሶስት ባለ 12 ፓውንደሮች ዲቶ
አንደ ባለ 3 ፓወንዩር፣ አራት ከብረት የተሰሩ ፣ ፓወንደር ሀውዜር

ከለር ሮበርት ናፒየር መልክት ጋር፣ የሰር ቻርልስ ስታቨሊ ስለ መቅደላ መማረክ የሚገልፅ ለጦር አዛዡ የተፃፈ ሪፖርት ተያይዟል። ሰር ሮበርት በራሱ ደብዳቤ የገለጣቸውን ሁኔታዎች ያትትና በመደምደሚያው ላይ ለአዛዡ የቀረቡ የመኮንኖች ሥም ይዝርዝራል።

የሚከተሉትን የመኮንኖች ሰም ዝርዝር ለአዛዡ ለማቅረብ ምኞቴን አገልጣለሁ፡ ብርጋዴር ጀኔራል ዊልቢ የ2ኛው ብርጌድ አዘዥና ጥቃቱን የመራ። አሱም ውጤታማ የሆነ አገልግሎት ያበረከቱትን መኮንኖች ይጠቅሳል፣ ካፒቴን ሂከስ፣ የብርጌዱ ሜጀር፣ ካፒቴን ጀምስ፣ ምክትል ረዳቱ ሜጀር ጀኔራል፣ አና የ12ኛው የቤንጋል ፈረሰኞቹ ካፒቴን ካፐል፣ ሜጀር ፕሪቻረድ (የቆሰለ) ፣ ከሮያል ኢንጂነሮችና ምሽግ ሠሪዎች ከፍተኛ መኮንን ከሚከተሉት መኮንኖች ውጤታማ ርዳታ እንዳገኘ ይጠቅሳል፣ ካፒቴን ኤልየት ከኬ ኮምፓኒ፣ የማዳራስ ምሽግ ሠሪዎችን በመምራት። ካፒቴን ፎርድ፣ ሉተናንት በርድ፣ ከሎኔል ዳልሪምፕል፣ እና ከማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች ሰርጀንት ፐርል፣ ሰርጀንት ሃርልድ አን ዲን፣ ኮርፖራል መደናግና መንገድ ሰሪ ቢይሊ፣ የ33ኛው ሪጂመንት አዛዥና ረጅመንቱን ወደ መግቢያውና ከመግቢያው አልፎ የመራ። አዚህ ላይ የተለየ ማለታወሻ ለማቅረብ በልመና አጠይቃለሁ፤ ለቁጥር

3691 ታምቡር መችው ሚካኤል መትዋየር እና ለቁጥር 949 ወታደር ጀምስ በርገን ከ33ኛው ሬጅመንት፤ ሁለቱም ሰዎች ለመጀመሪያ ወደማለፊያ ጥሰው የገቡና መግቢያውን የከፈቱ ናቸው። ካፒቴን ኤልየት የማዳራስ ምሽግ ሠሪዎች አዛዥ፣ ካፒቴን መዶነል የቦምቢይ ምሽግ ሠሪዎች አዛዥ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ፓሪሽ የ45ኛው አዛዥ፣ የ10ኛው ረጅመንት አዛዥ ኮሎኔል ፊልድ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ካሜሮን የ4ኛው(የንጉሥ) አዛዥ፣ ሜጀር በሽሊ የበሉቺ ሬጅመንት ከንፍ አዛዥ፣ ሜጀር ቻምበርሊን የ23ኛው ፑንጃብ ቃኝ ከፍል አዛዥ፣ ብርጋዴር ጀኔራል ፐተሪ የሮያል ከቢድ መሳሪያ አዛዥ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ዋላስ የሮያል መድፈኛ ዲቪዝን አዛዥ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ሚልዋርድ የሮያል መድፈኛ ዲቪዝን አዛዥ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ፔን የሮያል ከቢድ መሣሪያ (ኤ-21) አዛዥ፣ የባህር ሀይሉ ሮኬት ብርጌድ አዛዥ ኮማንደር ፌሎውስ፣ ካፒቴን ተዊስ የሮያል ከባድ መሣሪያ(ቢ-21) አዛዥ፣ ከ3ኛው ብርጌድ ቀላል ፈረሰኛ ኮሎኔል ግራቭስ የፈረሰኛው ብርጌድ አዛዥ፣ የ3ኛው ይራጎን አዛዥ ሉተናንት ኮሎኔል ታወር፣ የ12ኛው ቤንጋል ፈረሰኛ አዛዥ ሜጀር ንህ፣ ሜጀር ብሪግስ የ ሰንዲ ፈረሰኞች አዛዥ፣ ሉተናንት ኮሎኔል ሎች የፈረሰኛ አዛዥ፣ የ3ኛው ብርጌድ ቀላል ፈረሰኛ ከፍል አዛዥ ካፒቴን ሙር፣ የጠቅላይ አዛዡ አጃቢ አዛዥ ሉተናንት ለስት፣ የሮያል ኢንጂነርስ ሉተናንት ኤ ል መሰረር፣ ካፒቲን ለስሊ እና ሉተናንት ሊኮክ ከቦምቢይ ምሽግ ሠሪዎች፤ ካፒቴን ቤይንብሪጅ የመንገድ ትራንስፖርት ኮር አዛዥ፣ ጦሩ በሸሎን ከለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ለወታደሮቹ ውሀ ለማቅረብ ከፍተኛ ግዳጅ የነበረበት፣ ካፒቴን ሮስ፣ ግሪፍት እና ትወንቲማን ከ20ኛው ሁሳር የመንገድ ትራንስፖር ዲቪዚዮን ኮር አዛዥ፣ ሜጀር ሚኖን የነኖው ብርጌድ ረዳት ኮሚሳር ጀኔራል፣ ሜጀር ጎልድስዎርተ ከ2ኛው ብርጌድ የፈረሰኛ ብርጌድ ሜጀር ተጠባባቂ ኮሚሳር ጀኔራል፤ የነኖው ዲቪዚዮን ዋና ህክምና መኮንን፣ ዶክተር ማሬ ለፊልድ ሆስፒታል ያደረገው ዝግጅት የሚፈለገውን አይነት የነበረ፤ ሰርጀን ሜጀር ዋይሊ ከ2ኛው ብርጌድ የፊልድ ሆስፒታሉ ሀላፊ።

ከኔ ረዳቶች ደግሞ የሚከተሉትን መኮንኖች ሥም ለማቅረብ እፈልጋለሁ። ሉተናንት ኮሎኔል ዉድ ረዳት፣ ሜጀር ቤይሪ ረዳት ሰንቅና ትጥቅ፣ ሉተናንተ ላውንደርስ ከ20ኛው ሁሳር የከምፕ ረዳት፣ ካፒቴን ጅርጅ አርቡትኖት ተጨማሪ የከምፕ ረዳት።

እነዚህ መኮንኖች፣ ከተከበሩት የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ የተሠጡኝን ትዛዞች እንድወጣ፣ ዙሳ ከደረሰከብትና የመጀመሪያው ብርጌድ ከመጣ ጀምሮ ትልቅ እርዳታ ያደረጉ ናቸው።

ሉተናንት ጀኔራል ሰር አር፣ ናፒየር፣ G.C.B.C.S.I., ለህንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

የጠቅላይ ዕዙ ጽ/ቤት፣ ቁማይሌ ካምፕ

ሰኔ 1፣ 1868

ከቡር ሆይ፣ ሰር፣ በግንቦት 20 በተላከው ቁጥር 40 መልከቴ በመቀጠል፣ በዚህ ቀን እኔ ራሴ ወደ አቢሲኒያ ከዘመተው የመጨረሻው ጦር ከፍል፣ የ25ኛው ቦምቤይ

የተወላጆች ቀላል እግረኛ እና የቤሎቹ 27ኛው ባታሊዮን ጋር በመሆን የሶሮ ማለፊያን እንዳለፍኩ በእከብሮት ሪፖርት አደርጋለሁ።።

ከደላንታ እሰከ አንጣሎ የነበረው ጉዞ ፈታኝ ነበር፤ ይህም አብሮን ይጓዝ ከነበረው በተዳጋጋሚ ከወረደው የዝናብ ማዕበል የተነሳ ነው፣ በከፊልም ቢሆን ወታደሮች እና በተሲይም ካምፕ ተከታዮችና የመጓጓጥ ከብቶች ከችግሩ ነፃ ሲሆኑ አልቻሉም።።

የምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች

ቁጥር 153፣ *ራሳም፣ አሰከሬኑ የቴዎድሮስ መሆኑን እንዳረጋግጥ የተጠየቅሁ አኔ ነኝ፤ ቀብራቸውንም እንዳስፈፀም የታዘዘኩ አኔ ነኝ በማለት ዘግቢል።። አሰከሬኑ ሲከፈን፣ ከፋሮች ያሳዩትን ሰሜት በማየት፣ ራሳም ሲያትት፣ ምንም ቢሆን፣ በዚህ ሰአትም ለቴዎድሮስ ፍቅርና እከብሮት ያላቸው ሰዎች ነበሩ ይላል።። ቀብሩ ሲፈፀም ግን፣ በሌላ ሥራ ምክንያት በቦታው አልነበረም።።*

ቁጥር 154፣ *ከንግሥት መስታውት በፊት መቅደላ የደረሱቸው ወርቂት ነበረች።። ቴዎድሮስን ባለ እቅማችን ሰንታገል ኖረናል፤ ሀይሉን ሰላልቻልነው፣ ልጇ አምኖ ገብቶ ነበር፣ አሁን ግን ተገድሲል፤ መቃብሩን ማየት እፈልጋለሁ፤ መቅደላም ይገባኛል ብላ ነበር።። ይህንን ሰትል፣ መስታውት እየመጣች ነው ሲባል፣ በችኮላ መቅደላን ሊቃ ወረዩች።። መስታውት ወንድ ልጅ ሰለነበራት ከወርቂት የተሻለች ነበረች።። ሁለቱም አንዲ ሌላዋን የምትታመን አይደለችም በማለት ለእንግሲዞቹ ነግረዋል።። አንደኛዋ ሌላዋን፣ ቃሏን አትጠብቅም በማለት የተናገሩት፣ ሁለቱም አንድ ላይ እንዲሰማሙ በተጠየቁበት ጊዜ ነበር።።*

ቁጥር 156፣ *ይህ ፍንዳታ ሲሰማ፣ ከታች የነበሩት እቴጌ ጥሩ ወርቅና፣ የቴዎድሮስ ዕቁበት ወይዘሮ የተመኙ፣ እንድ ላይ ወደ መቅደላ ዞር ብለው ተመለከቱ።። ከዚህ በፊት ከፉ ነገር እምበዛም የሚይውጣት፣ በወታደሮቹም ተወዳጅ የነበረችው ወይዘሮ የተመኙ (እንግሲዞቹ እቴጌ ይሏታል)፣ "እንግዲህ ጌታችን ሞተ፤ ከዚህ በኃላ ግን የአቢሲኒያን ሰው እሳት ይፍጀው።።" በማለት ተራግማለች።። በቁንጅናዋ የታወቀች የየጁ አሮሞ ነበረች፤ ከእንግሲዞቹ ጋር አልሄድም በማለት ወደ ትውልዶ ቦታዋ ወደ የጁ ሄዳለች።። አፄ ቴዎድሮስ፣ ለወይዘሮ የተመኙ ያደሉ አንደነበር ግልፅ ነበር።። ሌሎች የሚጠቅሱት፣ እቴጌ ጥሩ ወርቅ፣ የደጀች ውቤ ልጅ አንደመሆኗ ቴዎድሮስን ትንቅ ነበረ።። አንድ ጊዜ፣ ቴዎድሮስ ወደ ክፍል ሲገቡ እቴጌዋ ከመቀመጫዋ ሳትነሳ ባይኗ ብቻ ገርመም አድርጋ ማንበቧን ቀጠሉች።። ባልየው፣ ራሳቸው ንጉሡ እንደገቡ አውቃለች።። የተናደዱት ቴዎድሮስ፣ "እንቺ ሴት ተመልከቺኝ" በቁጣም "ተነሽ! እኔ አሽከር አመሰልሻለሁ?" አሉ።። እቴጌዋ ቀሰ ብላ ከመቀመጫዋ ተነሺታ የታጠፈውን ልብሷን በመዘርጋት፣ ቀዝቀዝ ባለ አንደበት፣ "ሲገቡ አልሰማሁም፤ ከሰም የበለጠ*

ጌታን፣ ፈጣሪን እያናገርኩ ነበር።" በማለት ሰትመልስ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለባቸው ቴዎድሮለ ንዴታቸው በርዶ፣ ምንም ቃል ሳይተነፍሱ ወጥተው ሄደዋል። እቴጌዋ የቴዎድሮስን ባህሪ በደንብ ታውቅ ነበር።

ቁጥር 157፣ *የደላንታ ሰዎች ከዋግሹም ጎበዜና ከወሎ ኦሮሞዎች ጋር ሸፍተው ነበር። ሆኖም ዋግሹሙ፣ የቴዎድሮስን ምመጣት ሲሰማ የ30ማይሎች ርቀት ሸሽቶ በመሄዱ፣ የደላንታ ሰዎች የግድ ለቴዎድሮስ እጅ መስጠት ነበረባቸውና ምህረት ጠይቀው ገቡ። ቴዎድሮስም፣ እኔ ልጠብቃችሁ ካልቻልኩ እንዴት እድርጌ አማችኋለሁ በማለት ምህረቱ ሰጥተው ነበር። አልፈው ሲሻገሩ ግን፣ የደላንታን ሰዎች፣ ለምን ከዚህ ቀደም ወደኔ አልገባችሁም ብለው ሲጠይቁ፣ ሰዎቹም ዋግሹም ጎበዜና ኦሮሞዎቹ ከልከለውን ነው በማለት ሲመልሱ፣ ቴዎድሮስ ተናደው፣ አናንተም እንደነሱ መጥፎዎች ናችሁ በማለት መንደሮቻቸው እንዲበረበሩ አዘዋል። በርግጥ፣ የደላንታ ሰዎች ከዋግ ሹም ጎበዜ ጋር ከማበራቸው በፊት፣ ለመቅደላ ምሽግ ቀለብ ይሰፍሩ ነበር።*

ቁጥር 158፣ *ከምኒልክ ጋር ተላልከዋል ከተባሉት አንዱ የመቅደላው አዛዥ የበጌምድሩ ራስ ኪዳነ ማርያም ነበሩ። በቴዎድሮስ ትዛዝ ታስረው ወደ ደብረ ታቦር ስለተወሰዱ የበጌምድር ሰው አኩርፎ ነበር። በኋላ፣ ራስ ኪዳነ ማርያም፣ ቴዎድሮስን ቀድመው መቅደላ እንዲመለሱ ሆኗል። በመቅደላ አምባ የነበሩ ሁለት ቢትወደድ ሀይሉ የሚባሉ ነበሩ፣ አንደኛው የጭልጋው ሲሆን ይህ ሌላው መሆኑ ነው። ከመቅደላ በሌሊት በመለላል ነው ያመለጠው፤ ለማምለጡ ምክንያት፣ የስውየው የቅርብ ዘመድ የሆነ ባለምባራስ ገብሬ መድሀኔአለም የሚባል የወንደጂ ገዥ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍቶ ሰለነበር አሱንም ያስጠይቀዋል በሚል ፍራቻ ነበር።*

ምዕራፍ አስራ አራት

ወደ መጣንበት - ወደ ተከዜ ጉዞ፣ የሉተናንት ሞርጋን ሞትና ቀብር፣ ታቦት፣ የቄሶች የምስጋና ቅዳሴ፣ ከመቅደላ ስደተኞች ጋር መለያየት፣ የንግሥት ቪክቶርያ ለክሩሴዱ ጦር እንኳን ደስ ያላችሁ መልክት፣ የእቴጌዋ ሞትና ቀብር፣ ልዑል አለማየሁ፣ የካሳ ሽልማትና ከናፒየር ጋር ስንብት፣ በስሮ ማለፊያ ትልቅ ጎርፍ

በሚያዝያ 24፣ ሠራዊቱ፣ እምባው ላይ የነበረውን ካምፕ አፍርሶ ወደመጣበት ለመመለስ መንገድ ጀመረ።

የእንግሊዝ ሠራዊት፣ በአራቱ ቀናቶች ውስጥ በነበረው የተትረፈረፈ ሁኔታ፣ ጥሩ ዕረፍት አድርጎ ስለነበር በጣም በተዝናና እና ደስተኛ ሁኔታ ወደ ባህር በሩ ለፍጥነት ጉዞ የተዘጋጀ ነበር።

ሁሉም አደጋዎችና የነበሩ ፍራቻዎች በመወገዳቸው፣ ወደቤት በሚደረገው ጉዞና ከሱም ጋር ተያይዞ በሚታየው አስደሳች ለሜት

ለማንም ጠላት፣ ለምንም አደገኛ ማለፊያ እንበገረም፣
ዳተኛነትን አንቀበልም፣ ወደፊት ያለምንም ልዓም
በፍጥነት ወደፊት መሄድን ነው እንጂ።

እናም የሚያነቃቃው "የጌሪ አውን" ጣዕመ ዜማ በጆሯቸው እየተንቆረቆረ፣ እነዚህ ደፋር የእየርላንድ ወታደሮችና "የቄልንግተኑ መስፍን" ፈጥኖ ከመንቀሳቀስ ውጭ ምን ያደርጉ ነበር።

በጋራዎች ላይ፣ እንደ ጀግና ተዋጊ
እንበታትናለን ሁሉንም

እነሱንም ተከትሎ የጦር ጓደኞቻቸው፣ "የንጉሡ"፣ 45ኛው፣ የ3ኛው ድራጎን ጋርድ፣ በሺ የሚቆጠሩት የህንድ ሠራዊት አባላት፣ ከነሱም ጋር በሺ የሚቆጠሩ የካምፕ ተከታዮች ነበሩ።

ጦሩ ከደላንታ ሲነሳ በጣም ጥሩ ጤንነት ላይ ነበር። ነገር ግን ከመሀከላቸው ለማንያ የሚሆኑ፣ በመቅደላና በአሮጌ የቆሰሉትን ጨምሮ፣ የተጎዱ ሰዎች ነበሩ። የሆነ ሆኖ በየብርጌዱ ሆኖ በብዛት የሚደረገው ጉዞ፣ ሳይውል ሳያድር በበሽሎ ሸለቆ የደረሰባቸውን የእንሰሶቹን ጉዳት ማሳየት ጀመረ። የጀዳን ሸለቆ እንዳለፍን፣ የሚቀጥለው ቀን አስቃቂ ሁኔታ ነው

የፈጠረው። መኮንኖቹና ወታደሮች ተዝናንቶ በነበረው የሰውነታቸው ሁኔታ መቸገር ጀመሩ፤ ይህም ለዘመቻው ሲባል ጓዝ እንዳይሸከሙ ተደርጎ ስለነበር ነው።

ምንም ሳናቆም ከሰንዲ ተነስተን እብደቁምን አለፍን፤ ከዛም ጋዞና ሳንታሪ፣ ቁልቁል ወደ ተከዜ ወርደን፣ በሚያዝያ 28 በወንዙ ዳርቻ ካምፕ አደረግን።

በዚህ ቦታ፣ የእንግሊዝ ሠራዊት አንደ ምስጉን መኮንን፣ የ10ኛውን የሮያል ኢንጂነርስ ኮምፓኒ ሉተናንት ሞርጋንን አጣ። ወጣት፣ ደፋር፣ ታታሪ፣ ከዛም በተጨማሪ እውነተኛ ክርስቲያን ሰው ነበር። በተከዜ ዳርቻ፣ በቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ዙሪያ ካሉ ዛፎች በአንዱ ጥላ ሥር ተቀበረ። የነኛ ብርጌድ ሲቪልና ወታደሮች በሙሉ አስከሬኑን ተከትለው ወደቀበር ቦታው በመሄድ የሚገባውን ክብር ለመስጠትና የሚያውቁት ሰዎች በሙሉ ሀዘናቸውን ለመግለጥ ነበር። በቀበሩ ሥነ ሥርአት ላይ የተነበበው በጣም ስሜት የሚነካ ሰለነበር፣ በመቃብሩ ዙሪያ የቆሙ ሁሉም፣ በርግጥ ብሩህ ተሰፋ የነበረው ወታደር ከዚህ አለም መለየቱን እንዲሰማቸው አድርጎታል። በሚወዛወዙት ዛፎች ሥር ነበር መቃብሩ የተቆፈረው፤ እንግዲህ ወደፊት ትውልድ በትውልድ ሊተካ፣ ይህ ወደ መቅደላ የዘመተ፣ ታዋቂ ከሩሴደር ያረፈበት ቦታ፣ በእውሮፓውያን መንገደኞች የሚከበር ሥፍራ ይሆናል።

የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ፣ ሉተናንቱ ሰለነበረው የላቀ አገልግሎት፤ ለማያወላውል ጉልበቱና ጥረቱ፣ በማለፉ ምክንያት የሚሰማውን ሀዘንና የእንግሊዝ ሠራዊት የደረሰበትን ጉዳት የሚገልፅ የምስጋና መግለጫ አስተላለፈ። ሉተናንት ሞርጋን በሙሉ ወታደራዊ ሥርአት ተቀበረ።

ማምሻውኑ፣ የሀገሩ ተወላጆች ለአሸናፊዎች የሚያሳዩት ስሜቶች መረጃ የሚሆኑ ምልከቶች ማየት ጀመርን።

ወደ ደቡብ ስንጓዝ፣ ጆሮቻቸውን በጣቶቻቸው ደፍነው ወታደሮቹ ሊያደርጉ ያሰቡትን ነገር ሲነግሯቸው ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር። አሁን ግን ወታደሮቹ ምሽጉን የተለበለበ አለት አስኪሆን ድረስ እቃጥለው የማይበገረውን የቴዎድሮስ ሠራዊት በአራት እቅጣጫ ለነፋስ በትነው መምጣታቸውን ሲያውቁ፣ ለማዳመቅ መምጣት ጀመሩ።

የነበራቸው ትቢትና ኩራት የ "ቴዎድሮስ አሸናፊዎች" ላይ ባደረባቸው አሰደናቂ ስሜት መተካት ጀመረ። በብዛት እየሆኑ ለምስጋና ይመጡ ጀመር። ከመዝሙረ ዳዊት የምስጋና መዝሙር፣ "በሀይሉ ማዳንና ከበረከቱ ብዛት"፣ የሚጀምረውም፣ "እግዚአብሔር አለቴ አምባዬ ነው መድሀኒቴ ነው፣ እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፣ በእርሱም እታመናለሁ፤ ጋሻዬና የረድኤቴ ቀንድ፣

መጠጊያዬና መሸሸጊያዬ፣ መድኃኒቴ ሆይ፥ ከግፍ ሥራ ታድነኛለህ" (2ኛ ሳሙኤል፣ 22)

በተመሠጠ ዳዊታዊ በሆነ ስሜት ነበር የተደገመው። "ዳዊት በጌታ ፊት በተገኘው የሙዚቃ መሳሪያ ነበር የተጫወተው።" የሳውል ልጅ ሚካስ እንዳየችው የአይሁዳውያንን ሽርጥ አሸርጦ ሲዘልና ሲወዛወዝ ነበር። ጥሩምባ እየተነፋና በከፍተኛ ድምፅ እየጮሁ የእቢሲኒያ ቄሶች፣ ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎችና የቤተከርስቲያኗ ልጆች የፅላቱን እምሳያ ታቦቱን ይዘው መጡ።

የኢትዮጲክ የታቦቱ እምሳያ ርዝመቱ አምስት ያርድ፣ ጎኑ እንድ ያርድ ሲሆን ከፍታው እንድ ጫማ ይሆናል። ዳር ዳሩ በወርቅ ባጌጠ ቀይ ልብስ ተሸፍኗል፤ በላዩ የምህረት ወንበር እምሳያ አለው፤ ግን ከወርቅ የተሠራ እይደለም። ከእንጨት የተሠራ ሆኖ ሀር ለብሷል። ላዩ ላይ ከፍፉ ያጌጠ ሀር እንደ ዘውድ ሸፍኖታል፤ የሰንዝር ርዝመት ያለው የተንጠለጠለ ነገር በሁለቱ ጎኖች አሉ።

ፅላቱ ላይ ኪሩቤሉም ሆነ የስርየት መከደኛው እይታዩም። እነዚህ ሁለት ነገሮች ስለሚጎድለው፣ እንደ ዋናው የሙሴ ፅላት አይሆንም። ከሚያሸበሽቡት ሰዎች እናት ላይ ከፍ ብሎ የተለያዩ ቅዱስ የተባሉ የቤተክርስቲያን ዕቃዎችን ጨምሮ፣ ሻማዎች፣ ከብርና ከብሮንዝ የተሠሩ መስቀሎች ወዘተርፈ ተይዘዋል።

ዋናው ቁስ፣ ረዥም እጅጌ የሌለው ቀሚስ ለብሷል፤ አናቱም ላይ ጥምጣም አድርጓል። ደረቱም ላይ በደንብ ያጌጠ የበሬ ቆዳ ይታያል።

ተክታዮችም ከጥጥ የተሠራ እጀ ጠባብ ለብሰው፣ ቀበቶዎችን ይዘው ከቁሱ ጋር ይጓዛሉ። ይህ በተራው የልጆቹን ከፍተኛ አድናቆትን በመፍጠሩ፣ ጆሮ የሚያደነቁር ዜማ እያሰሙ የያዟቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች እየተጫወቱ ወደ ጠቅላይ ዕዙ ቢሮ ይጓዛሉ።

ከነሱ መሀከልም በከፍተኛ ድምፅ የሚያዜሙ ብዛት ያላቸው ቅጥ ያጡ ባለጌዎች ነበሩ፤ ሀፍረት በሌለው ድፍረት ከፊረንጆቹ ገንዘብ ይለምኑ ነበር።

ከነዚህ ብዛት ካላቸው የተደበላለቁ ጠያይሞች ወንድ፣ ሴትና ህፃናት ባሉበት ቦታ፣ በሚያስገርም ሁኔታ ንፁህ ልቦና ያለው የሰዎች ፊት በጣም ጥቂት ነበር። ለአመል ያህል አንኳን አጋጣሚዊን ሲያገኝ የማይገባውን ንብረት ከማንሳት የሚቆጠብ እንድ ነብስ እለ ብል እንኳን የማጋንን ይመሰለኛል።

የራሱ ያልሆነውን ንብረት በከፍተኛ ብልጠት ለመውሰድ ያለው የሰው መሠረታዊ ባህሪ በነዚህ ሰዎች በያንዳንዳቸው ላይ የታተመ ይመስላል።



ቄሶች ለሮበርት ናፒየር ሲያሸበሽቡ
(Roger Acton)

የነበረው ወዳጅነት በሚታየው ተመሳሳይ ባህሪ ከቀዘቀዘ ወዲያ፣ ከሠራዊቱ ውስጥ፣ ማንም ሰው ቢሆን፣ እኔ እንደማምነው ከሆነ፣ አንድም አቢሲኒያዊ ድንኳኑ አጠገብ እንዲገኝ የሚፈቅድ አልነበረም።

ነገር ግን ለፈረንጆቹ ከብር ሲባል ለመዘመር ሲመጡ ማንም ቢሆን ለመቃወም ልቡ የከጀለ አልነበርም። ያም ግን ሰዎቹ ከድንኳኖቻቸው በር በቂ ርቀት አስከቆዩ ድረስ ነበር። ለር ሮበርት ናፒየር በነሱ ላይ በተቀዳጀው እሽናፊነትና በነበረው ትልቅ ልቦና፣ ለጦርነቱ እህልና ሌሎቹንም እስፈላጊ ነገሮች በማቅረብ የጦሩ ረዳቶች ነበሩ ብሎ ሰላመነ፣ ወታደሮቹና መኮንኖቹ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚችሉትን ያህል ጥሩ ፊት ለማሳየት ሞክሩ፤ እንዲያውም በልቦናቸው የሚበቃ የመዝናናት ስሜት ስለተሰማቸው ዘፈንና ዜማውን ለመውደድም በቅተው ለታየው ዘፈንና ሽብሸባ ሲያጨበጭቡ ነበር።

በተወላጆቹ መህል ቄሶቹ ከፍተኛ ክብር ስለነበራቸው ከተለብላቢዎቹ ፊት ለፊት የነበሩት እነሱ ነበሩ። ሁሉም፣ ከጠቅላይ ዕዙ ቢሮ ሃምሳ ርምጃዎች ርቀት በሚገቡቸው ቦታ ከቆሙና ከተሰበሰቡ በኋላ፤ ከመሃከላቸው ጠንካራ ድምፅ ያለው ቄስ ንጉሡን ላሸነፉ ፈረንጆች ክብር ሲባል የሚቀደሰውን ዜማ ከፈተ።

ዜማውን እያዜመ መሚሚቅ ሲጀመር ድመፁ እየጎላና እየደመቀ ሄደ፤ የተሰበሰቡትም፣ መሰቀል በሚወዛወዝበት ጊዜ፣ ዜማውን ተቀላቀሉ፤ በከፍተኛ ድምፅ ሲዘምሩም የሚያስደነቅ ውጤት ነው የፈጠረው።

ከዚህ ዜማ በኋላ፣ ሰድስት ቄሶች በዋናው ቄስ እየተመሩ ማኑበነብ ጀመሩ። ወዲያውኑ ድምፃቸው ከፍ ብሎ ሳንባቸው የሚቀደድ እስከሚመስል ድረስ ከዚህ ቀደም እንደሆነው አይነት እንደገና በዜማ ተጨረሰ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ዙሪያ ፈጥረው፣ ባፏጩ ሲገለፅ፣ ወረብና ሽብሸባ ጀመሩ፤ ዜማው እየደመቀ ሲሄድ፣ ለምልከት ጭብጨባ ሲጀመር፣ በዙሪያው የነበሩ ሴቶችና ህፃናትም "እልል እልልልል!" በማለት እነሱም ወደ ላይ መዝለል ጀመሩ።

ከዚያም በሶስት ረድፍ ተከፍለው እንደቀደመው ሁሉ በከፍተኛ ድምፅ በማዜምና እንቅስቃሴም በመጨመር ሽብሸባውን ቀጠሉ። ከመህከላቸው ሰድስት የቄሱ ረዳቶች ነበሩ በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት፤ ከነዚህ መህል፣ በጣም ልጅ በነበሩት በሶስቱ የተለየ የሽብሸባ እንቅስቃሴ ተደረገ።

ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ፅላቱ ከቄሶቹ አጠገብ ነበር። ሁሉም ከተደረገ በኋላ በከፍተኛ ድምፅና ዜማ እንቅስቃሴውና ዜማው ተጠናቀቀ።

ላዳረጉት ውለታ ተብሎ በአገልግሎት ምክንያት የተጎዱ አንድ መቶ ሀያ ሶስት በቅሎዎች ለእነዚህ ሰዎች ተሠጣቸው። በተጨማሪም በርከት ያለ

የበቆሎና የሳር ከምር፣ እኛ በሌለንበት ጊዜ በማጓጓጉው መሰመሩ ተሰብሰቦ ነበር፤ የጦር ማጓጓጉው በምንም አይነት ሲወሰደውም አይችልም ነበር።

በዚህ ካምፕ ከመቅደላ ከተለቀቁ ሰዎች ከመጨረሻዎቹ ጋር ተለያዬን። እነሱም መንገዳቸውን በላሊበላ በኩል አድርገው ወደ ጣና ሀይቅ አቅጣጫ ሄዱ። እኛም ጉዟችን ወደ ሰሜን ቀጠልን። ከጦሩ ጋር እያሉ በአያንዳንዱ ጣቢያ በበቂ ሁኔታ ተመግበው ነበር።

ሰንመለሰ የምግብ እጥረት አልነበረም። እኛ በሌለንበት ጊዜ የወታደር ካምፖቹ ከየምግቡ አይነት ከምር በሚሆን ደረጃ ሰብስበው ነበር። የብር ዶላሩ፣ የሀገሩ ተወላጆች እጅ ላይ ካረፈ ምንም አይነት ያላቸው ነገር በሙሉ ለሽያጭ ይቀርባል። መሬቱ በበቂ ሁኔታ ያልታረሰ እንደ መሆኑ፣ በተፈጥሯቸው ድንጉጥና አንግዶችን ተጠራጣሪ እንደመሆናቸው መጠን፣ በተጨማሪም ቀለቡ የተሰበሰበበት አካባቢ ጠበብ ካለ የሀገሩ ከፍል እንደመሆኑ፣ ለምግብ የሚሆነው ቀለብ አሰባሰቡ በጣም የሚያሰገርም ነው።

ጦሩ ወደፊት በደሰታ ይገሰግሳል፤ ጉዞውም ከተከዜ ወደ ሙጃ፣ ከሙጃ ወደ ወንደች፣ በደመና በታጠረው መሸገር አምባ ላይ የተከዜን ሸሰቆ ተሰናብቶ ነው። ከዛም ቁልቁል ወደ ዲልዲ ወርደን ልብሳችንና የነበረን ንብረት ሰበሰብን። አንደገናም፣ ዕይታው፣ የተጠማ ከንፈር ላይ እንደሚያርፍ ውሃ በሚያረካው በቦሄያ ተደሰተን። ከዲልዲ ወደ ማርዋ የሚያቆሰል ጉዞ ነበር፤ በመቶዎች የሚሆኑ በቅሎዎች ሞቱ። ከማርዋ፣ ወደ መቅደላ ለጥቃት ሲሄድ የነኛው ዲቪዚዮን ያረፈበት ቦታ፣ ወደ ላት፣ ከዚያም መሰጊታ ቀጥሎም የሚያምረው አሸንጌ ሀይቅ ነበር። ከሀይቁ ባሻገር ያለው የሚያምረው ረግረግ በአረንጓዴ ገፅታው ፈገግ ብሎ ይታያል።

አሸንጌ እያለን፣ በሶሮ ማለፊያና በሰናፌ ቁልቁለት የሚወርደው ጎርፍ መጀመሩን ዜና ሰማን። በማለፊያው ውሰጥ የተሠራው የወታደሮች መንገድ መፍረሱን፣ በተጨማሪም ዝናቡ በሀይል ለመጀመሩ ምልከቶች መኖራቸውን፣ ሰለዚህ፣ መንገዱ ወታደሮችን ወደ ባህር ዳርቻው ሰማሳለፍ የሚሆን አለመሆኑን ነው።

የብዙ ማይሎች ርዝመት የነበራቸው የቴሌግራፍ መስመሮች በጎርፉ ተወሰደዋል። ብዙ የድርቆሽ ከምርም ከጥቅም ውጭ ሆኗል። በርግጥ፣ ለዚህ የከፋ ሁኔታ መሻሻል የሚበጁ የተለያዩ ሀሳቦች መሰንዘር ተጀምሯል።

በሰናፌ፣ የዝናቡ ወራት እስከሚያልፍ ወታደሮቹ የሚሰነብቱባቸው ጎጆዎች እንዲሠሩ ሀሳብ ተሰጠ። እንደገናም ካምፑ አንዳለ በሰናፌ ቁልቁለት ላይ እንደነበረው እንዲቆይና እያንዳንዱ ጣቢያ ለሚመጡት ወታደሮች ምግብ አዘጋጅቶ እንዲጠብቅ፤ ቴሌግራፎችም ወታደሮቹ የሚደርሱበትን ሰአት

አንዲያስታውቁ ተባሉ። ነገር ግን አነዚህ ሀሳቦች በሙሉ ውድቅ ሆኑ። ያም ውሳኔ ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሆነ በጎርፋ ምከንያት የደረለው ጉዳት በሙሉ ለሰር ሮበርት ናፒየር በዝርዝር አስኪቀርብ ድረስ ነበር።

ያን ቀን ማታ በአሸንጌ ከባድ ዝናብ ጥሎ ድንኳኖችን ስላበሰበሰ ላያያዝ አሰቸጋሪ ሆኗል፤ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን ጥዋት አራት ሰአት ላይ ድንኳኖቹ በደንብ ደረቁ፤ አናም ጦሩ ጎዞውን ቀጠለ። ብዛት ያለው የተረፈ ጓዝ በአሳት አንዲቃጠል ሆነ፤ ጀኔራሉ ለነዚህ ለተረገሙ ሰዎች መስጠት አልፈለገም። ደግነት ባደረገላቸው፣ ሰዎቹ ምስጋና ቢስ ነው የሆኑት፤ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ፣ ጓዙ ከዚህ ጣቢያ ጀምሮ ወደ ፊት ከመሄድ አንዲጓተት አደርገዋል። ያም ኮሎኔል ሚልዋርድ ከቀናት በፊት በሀይቁ አጠገብና በውሀው ላይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ ነበር።

አሸንጌን ከለቀቅን በሁዋላ፣ በምሰባ ተራራ ደቡብ በኩል ባለ ዳገት ላይ የሚገኘው የሀያ ጫካ ከሶስት ወይም አራት ሰአት በኋላ ደረስን።

ስንመለስ፣ በመንገዳችን ላይ፣ የሮያል ኢንጂነርስ ትሪጎኖሜትሪካል ሰርቬይ (አሳሽ) መኮንኖች የሆኑትን ሉተናንት ካርተር፤ ደምለር እና ሆልዲችን አገኘናቸው። በብዙ ድካምና ጥረት ከባህሩ ዳር ተነስቶ እስከ ደላንታ ድረስ ወደ 6ሺ ሰኩዌር ማይል የሆነ ቦታ በማሰስ ተሳክቶላቸዋል።

ሀያ በሚባለው ቦታ ምንም በአርጥበት፣ በጉምና በጭጋግ ብንከበብም፣ ሆዳችን በፖርት ዋይን፣ ብራንዲ አና ንፁህ ጃማይካ ረክቷል። ይህም አስፈላጊ የሆስፒታል ዕቃዎችን ማከፋፈል የግድ አስፈላጊ ስለነበረ ነው። ዕቃዎቹን ለማጓጓዝ ብዛት ያላቸው የጭነት አንስሳት ሰለሚያስፈልጉና ጉበረቶችን በቦታው አንዲጠበቅ ከማድረግም ሰለሚሻል ነበር።

ከሀያ ወደ ፒላጎ፣ በዝናቡና በጭቃው ምከንያት አጭር ጉዞ ነው የተደረገው። አምስት የጭነት ዝሆኖች በጥይት ተመቱ። በጣም ደከመው ስለነበረ ይህን አማራጭ መውሰድ የግድ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ ፒላጎን ለቆ ወደ ሙካን ሄደ ከዛም ወደ አፃላ። በዚህ ቦታ ስንደርስ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር አምባ አላጌ ላይ ትንሽ የመድፍ ተኩስ ወርወር ለማድረግ አስቦ ነበር። ምከንያቱም፣ የአምባው ጌታ በተቻለው መጠን በጭነት ተሸከርካሪ የሚሄደው ቀሰብና ጓዝ እንዲጓተት አድርጎ ስለነበረ ነው። ደግነቱ፣ ወልደየሱስ ከቦታው ተሰውሮ ስለነበር፣ አምባው ላይ መተኮሱ የሚፈለገውን ውጤት አያመጣም ነበር።

ከአፃላ፣ ጀኔራል ናፒየር፣ የተሰባጠረውን ጦር ምንም ሳያቆም ወደ ሰሜን፣ ወደ ቤት፣ ጉዞ አንዲቀጥል አደረገ። የሚያሰደስቱት የመሸከ ሜዳዎችንና የሚንበሰበሱትን ውሀዎችን አልፈን ሄድን። የሚያስፈራውና ለየት

ያለው፣ ከመስኒ በፊት የሚገኘውን ቦታ የአላጌን ሸለቆ አንዳለፍን አየነው። በሚቀጥለው ቀን ለኛ እፎይታ፣ አንጣሎ የሚገኘው የተመሸገውን ካምፕ ማየት ቻልን። ወደ ባህር በሩ በምናደርገው ጉዞ ማማሹ ላይ ነን። የመጨረሻው የኋላ ብርጌድ በግንቦት 12 አንጣሎ ደረሰ።

ከመቅደላ አለከ አንጣሎ የነበረው ጉዞ፣ ለብዙ የትራንስፖርት መስመሩ የጭነት ከብቶች መሞት ምክንያት ሆኗል። መንገዱም በነሱ ጪም ብሎ ነበር። በማወዳደር፣ ከሞስኮው ሽሽት የነበረው ሁኔታ ለእንስሶቹ የከፋ በመሆን ከዚህኛው የበለጠም አልነበረም። በሙቶዎች የሚቆጠሩ የጋማ ከብቶች በየቀኑ ይሞቱ ነበር። ግመሎቹ በቀላሉ ነበር የሚሞቱት፣ ዝሆኖችም ቢሆን በጣም ተስቃይተዋል። የፈረሰኛው ከፍል ፈረሶች በደርዘን ነበር የሞቱት።

የጀዳን ሸለቆ ማቋረጥና የዲልዲ ተራራ፣ የ700 አንስሳት ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። የመንገዱን ካርታ ላንዳፍታ ማየት፣ አነዚህ የተያያዙ ኮረብታዎች፣ ጓዝ ለተጫኑ አንስሶች አንዴት አድካሚ አንደነበሩ መረዳት ይቻላል።

ከአንጣሎ ተነስቶ ወደ ባህሩ ዳርቻ በሚደረገው ጉዞ ግን፣ ከዚህ ቀደም ሥርአት ያልነበረው የተደበላለቅ ጉዞ ሳይደረግ ተከፋፍሎ እንዲሄድ ተደረገ፣ እያንዳንዱ የእግረኛ ወይም የፈረሰኛ ሬጅመንት የተለያዩ የጉዞ ቀናት ተሠጠው።

ጦሩ አንጣሎ አንደ ደረሰ፣ የሚከተለው አጠቃላይ ትዛዝና ቴሌግራም ከኢንግላንድ ንግሥትና ከካምብሪጁ መስፍን ተልኮ ሰለነበር በጠቅላይ አዛዙ አማካኝነት ለየሬጅመንቱ መኮንኖች ተነበበ።

የአንጣሎ ካምፕ ግንቦት 12፣ 1868

በዚህ ቀን በቴሌግራፍ የደረሰውን መልክት ጠቅላይ አዛዙ ለእቢሲኒያው ጦር ሲያስተላልፍ በከፍተኛ ርካታ ነው። ስር ሮበርት ናፒየር፣ በዕዙ ስር ያሉትን ሁሉም ስዎች፣ ሁላችሁም ላደረጋችሁት አገልግሎት ለጋስ የሆነችው ንግሥት ቪክቶርያ ዕወቅና በመሥጠቷ አንኳን ደስ ያላችሁ ይላል። "ንግስታችን ለሰር ሮበርት ናፒየርና ለጀግና ተዋጊዎች፣ ለተቃና ውጤታችሁ ከልብ የመነጨ የአንኳን ደስ ያላችሁ መልክት ልካለች።"

የአንጣሎ ካምፕ፣ ግንቦት 12፣ 1868

የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ፣ በርሱ ትዛዝ ሥር ላሉ ወታደሮች የሚከተለውን፣ ከግርማዊ ፊልድ ማርሻሉ፣ ጠቅላይ አዛዙና ከተከበሩት የህንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በቴሌግራም የተላከውን መልክት ሲያነብ በታላቅ አርካታ ነው።

"በተጎናፀፋችሁት ታላቅ ስኬትና ቻይና ጀግና በሆኑት ወታደሮች ሁላችንም ተደስተናል።"

"ከቡርነትዎን በሙል ልቤ እንኳን ደስ ያለህ እላለሁ። እንደገናም፣ የትም ቦታ መሄድ የሚችልና ሁሉንም ማድረግ የሚችል ጦር ምን ማለት እንደሆነ አስተምረኸናል። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ፣ ሁሉም ነገር በሚገባ ነው የተከናወነው።"

ድፍን ኢንግላድን ያስደሰተው፣ ወደ አቢሲኒያ ውስጥ የዘለቀው የደስታ መልከት የመጀመሪያው ይህ ነበር። ግርማዊነቷ፣ ንግስት ቪክቶርያ በመደሰት ሰር ሮበርት ናፒየርንና ከሩሴደሮቹን እንኳን ደስ ያለህ መልከት መላኳ፤ የካምብሪጁ መስፍን፣ ለአቢሲኒያ ዘማች ጦር ቡቴሌግራም ሰላምታ መላከን ጨምሮ ነው። ትንሽ ጦርነት ቢሆንም፣ ትልቅ ዘመቻ ነበር። በተራራ የተቆለፈች አቢሲኒያ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ምንም አይነት የጥላቻ ስሜት አልተንፀባረቀም፤ ዝናው ደግሞ በጉልህ ሁኔታ፣ በመላው ኤሰያ እንዲሰማ አድርጎታል። ተራርቀው የሚኖሩ ልዑሎችና፣ ሌሎች ገዥዎች ዝናውን ሰምተው መንቀጥቀጥ ጀመሩ። የሰላም ዘመን ቢሆንም የኢንግላድን ጉልበት እንዳላደከመው ተመለከቱ። ስለዚህ፣ ይህ የመጨረሻው፣ በጣም ጥሩውና፣ ከድሎች ሁሉ ታላቅ የሆነው፣ ምንም እንኳን ትንሽ ቢመስልም የኢንግላንድን ክብር ከዚህ ቀደም ከሆነው በላይ ጠንካራ መሠረት ላይ አስቀመጠው።

ሠራዊቱ ያለምንም ማቋረጥና ያለምንም ድካም ከአንጣሎ ወደ ስናፈ መንገዱን ቀጠለ። የነበረ አንድ ሞት የእቴጌ ጥሩነሽ ነበር፤ የሞተችውም በሳንባ በሽታ ነበር። ቀብሯ ላይ በእቴጌዋ ዘመዶች ጥልቅ የሆነ ሀዘን ነበር የታየው። በግንቦት 15 ሞታ፣ አይኩለት የሚባል ቦታ ተቀበረች[160]። "የንጉሡ ጦር" የወታደር ባንድ፣ እስከሬኑ ወደ መቃብሩ ሲሄድ ፊት ለፊት እየተራመደ፣ 'Dead March in Saul'፣ የሚባለውን ሙዚቃ ተጫወተ። ከእለከሬኑ ሳጥን አጠገብ፣ የማይተካ ሰው ሕይወት በማለፉ ደንገጡሮችዋ ለቅሶና ከባድ የሀዘን ስሜት ነው ያሳዩት። ከኋላ ከእቴጌዋ ቤተከርስቲያን ወጣ የሆነው የቀብሩን ስርአት የሚመራው ቄስ ይከተላል፤ ወጣቱ ልዑል ከሚስተር ራሳም ጋር ሆኖ፣ የጠቅላይ እዛዥ ጽ/ቤት ረዳት፣ ብዛት ያላቸው ረዳቶቹ፣ ብዛት ያላቸው አቢሲኒያውያን ይከተላሉ።

---

160 ኢጋጣሚ ሆኖ የእቴጌዋ አያትም እዚህ ቦታ ነበር የተቀበሩት።



የእቴጌ ጥሩ ወርቅ የቀብር ሥነ ሥርአት
(Roger Acton)

አቴንዋ ከትንሹ ልጇ[161] ጋር ሆና ወደ ቦምቤይ ለመሄድ ነበር ያሰበችው፤ ሰር ሮበርት የመከራትም ይህንኑ ሰለነበር፣ የተሻለ አማራጭ ነው ያለችው መንገድ ነበር።

ወጣቱ ልውል አሰማየሁ አሁን ወላጅ አልባ ሆነ[162]። ነገር ግን እሱን በሚመለከት ተወሰኖ የነበረው የጦር አዛዡ ሃሳብ አልተቀየረም አንዲያውም ተጠናከረ።[163]

ወደ አቢሲኒያ የዘመተው ሠራዊት የመጨረሻው ከፍል በግንቦት 24 ሰናፈ ደረሰ። ከአንጣሎ ጀምሮ ወደዚህ ከፍተኛ ቦታ ላይ ወደነበረ ካምፕ መጓዝ ምንም አሰልቺ ቢሆንም፣ በየቀኑ፣ የዘመቻው መጠቃለያ ለመቃረቡ ምልከት ነበር። ባህሩን እየተቃረብን እንደሆነ፣ አናም አንዴ ባህሩ ላይ ከሆን፣ ወደ ቤት፣ ከፊት ለፊታችን ወደ ውድ ቤት የምናደርገው ጉዞ ሩቅም አይሆንም።

ከስድሰት ወራቶች በፊት፣ ወታደሮቹ በልባቸው የብረት ያህል ጥንካሬ ይዘው፣ ለሚደረገውም ነገር አአምሯቸውን አዘጋጅተው ነበር ሰናፈን ለቀው የሄዱት። የመጀመሪያው ጣቢያችን ሰናፈን ከለቀቀን በኋላ ሁለት ዙር ሰብል ታጭዷል። አሁን ደግሞ ምርት የደረሰበት ወቅት ሰለሆነ የበቆሎ ቅጠልና ፍሬ ለሶስተኛ ጊዜ ደርሷል።

የትግሬውን መሰፍን ካሳን፣ ሆን ብዬ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ሳላነሳው በፀጥታ ያቆየሁት ሰው፣ የኔን ትውሰታ እንደገና ማግኘት ይገባዋል። ታማኝ አጋዥና ታማኝ ሰው ነበር። በመጀመሪያ ጊዜ በሀውዜን፣ ከወራጅ ውሃ አጠገብ ቃል ከገባ ወዲህ ቃሉን ሳያጥፍ ነው የቆየው። በልዑሉ በኩል የተደረገ ማናቸውም ነገር በራሱ በልዑሉ ነው የተደረገው። ያለማሰለስ፣ የአንግሊዙን ጄኔራል አላማ ለማሳካት ይጥር ነበር። በብልሃት፣ ጥንካሬ በተሞላበት ሁኔታ የሚያስፈልገውን ርዳታና ለሰውም ለእንሰሳም የሚሆነውን ቀለብ ሰበሰበ። ቅንጣት ያህል ሥራውን የማጓደል ሁኔታ አልታየበትም። የሚያስፈልገው የምሲጋና ቃል የሚገባውም ነበር። ዋግሹም ጎበዜም ቢሆን አንደ መሰፍኑ ሙሉ ቃል ነበር የገባው። ነገር ግን፣ የገባው ቃል ለእንግሊዙ ጄኔራል ፍሬ አልባ ቃላቶች ብቻ ነበሩ። በግዛቱ፣ በላስታና በሰሜን በነበረበት ጊዜ፣ ጀኔራሉ፣ የነበዜን የውሸት ጓደኝነትና የማይታመን አለመሆኑን ሙሉ በሙሉ ያወቀ መሆኑን መናገር አይችልም ነበር። ነገር ግን፣ ግልፅ የሆነው፣

---

161 ስለ ልውል አለማየሁ (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)

162 አያቱ ለልውል አለማየሁ የሞቱለት ደብዳቤ (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)

163 (በምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች)



ወላጅ አልባ የቀረው ልዑል አለማየሁ
(Roger Acton)

የወንዱና ቃል ጠባቂው የትግሬው ልዑልና ያደረገው ትብብር በእዝዙ እእምሮ ብልጭ ይላል። ሰሰዚህ፣ በርግጥ፣ ልዑል ካሳ ውለታና ወዳጅነቱ የኔ ይሁን ብሎ መጠየቅም አያሰፈልገውም።

የእንግሊዝ ሠራዊት ሰናፈ እንደ ደረሰ በሁለተኛው ቀን፣ ልዑል ካሳ ከሶሰት መቶ ምርጥ ፈረሰኞች ጋር በመሆን የእንግሊዝን ሠራዊት ለመሰናበት መጣ። በናፒየር የተሳካ ውጤት በጣም ደሰተኛ ነበር፤ አናም ጀኔራሉን ባለ የእቢሲኒያ መዝገበ ቃላት መያዝ በሚችለው ቃላቶች በሙሉ ምሥጋናውን ደረደረለት። ለናፒየር ያለውን ምኞት ለመግለፅ እንዲህ አለ፣ "የመንግሥተ ሰማይ ሁሉ ደሰታ ይሰጥህ፣ ያገርህን ሰዎች አድናቆት፣ ከፍ ያለ ማዕረግ፣ ብዙ ሚሰቶችና ልጆች ይሰጥህ፤ ዕድሜ ይሰጥህ፤ በፓትርያርኩ፣ በእብርሃም፣ በይሰሐቅና ያዕቆብ በቀኝ ጎን ያሰቀምጥህ።" ፀሐፊውም አሜን! አለ።

ያለምንም ጥርጥር፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ምንም እንኳን የእንግሊዝ ጀኔራል ቢሆንም፣ ቀዝቀዛ የሆነውን ሥነ ሥርአት እርግፍ አድርጎ ትቶ፣ ለደማቅ ምሰጋናው መልስ በመሰጠት ላሳየው ታማኝነትም በፍቅር አቀፈው።

የንግሥቷን ልደት ለማክብር በሰናፈ ሌላ የተካሄደ ሥርአት ነበር። የወታደሮቹ የሚደነቅ ሰልት የተመላበት ትርኢት የልዑሉን የጋለ አድናቆት ነው የቀሰቀሰው። እሱም ቢሆን በጀኔራል ናፒየር ፊትና በረዳቶቹ እንዲሁም የሌላ ሀገር መኮንኖች ባሉበት ጥሩ ሰሜት ለማሳየት ባለው ፍላጎት፣ የራሱን ሰዎች በሁለት መሰመር ካሰለፈ በኋላ የውጊያ ትርኢት ማሳየት ጀመረ።

ልዑሉ የራሱን ድርሻ በደንብ ነው የተወጣው፤ በተለይም የፈረስ ግልቢያ ቸሎታው ከምንም በላይ በጣም ጥሩ ነበር። እንዴ ምልከት ከተሠጠ በኋላ የውጊያ ትርኢቱ ተጀመረ። በዚህ ትርኢትም አያንዳንዱ ሰው ለነበረው አሰላለፍ ደንታ ሳይለዋ ወደ ተቃራኒው ገሰግሰ ይሄድና በጦሩ በድልድሙ በኩል ከፊት ለፊቱ የመጣውን ማንኛውንም ሰው ያጠቃል። የሚሸሹት ወገኖች ደግሞ ወዲያው እንደታወቁ፣ እየሸሹም ቢሆን አደገኞች መሆናቸውን ለማሳየት ገና መሸሸት ሲጀምሩ፣ እንደ ፓርቲያን፣ ጥይት የሚተኩሱ እየመሰሉ በሜዳው ይሮጣሉ።

ላሳየው ጥሩ እምነት፣ ሰር ሮበርት ናፒየር ለካሳ በጣም ዋጋ ያለው ሽልማት ስመስጠት ደሰተኛ ነበር፤ በተለይም እንደሱ በጣም ጠቃሚ ለሆነ ሰው፤ ሰለዚህ 1500 በእፈሙዝ በኩል ባሩድ የሚገባበት ጠመንጃ፣ Brown Besses[164]፣ 400 ሺ ጥይቶች በካርታ፣ ሰድሰት መድፎች ከነአርሳሳቸው ነበሩ።

---

[164] የእንግሊዝ ወታደሮች ነፍጥ



የንግሥቷን ልደት በማክበር በሰናፊ የተደረገ ሠልፍ
(Roger Acton)

በዚህ በሚደነቅ ሥጦታ፣ ወራሪ ግብፆች ላይ ብድሩን መመለስ እንደሚችል ምንም ጥራጣሬ አይኖርም።እነዚህ ግብፆች ሲረዝም ጊዜ ይህ ነው የማይባል ወንጀል ያለምንም ገደብ አቢሲኒያውያን ላይ ሲያደርሱ ነበር። ካሳ፣ ከሱ ጋር መመለስ ከፈለጉ በርከት ያሉ አውሮፓውያን ጋር በመሆን እንግዲህ ዋግ ሹም ጎበዜና ግብፆች ላይ፣ ራሱ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችላል።

ጦሩ ለመመለስ ከመነሳቱ ሶስት ወይም እራ ቀናት ቀድሜ፣ እምስት፣ ጓዝና የተወሰዱ ንብረቶች ከተጫኑ ከብቶች ጋር በሰናፈ ቁልቁለት መውረድ ጀመርኩ። እብረውም ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ነበሩ። ማለፊያው፣ ያን ጊዜ ወደ ዘመቻው ስመጣ የነበረውን ይመስላል፤ ነገር ግን በሃሳቤ፣ ወፎቹ የእንኳን ደኅና መጣችሁ የሚል የደስታ ፉጨት የሚያስሙ መስለኝ። በጣም ቀጥ ያሉት ቁልቁለቶችም ብዛት ባላቸው ቁጥቋጦዎች ተሸፍነው በጣም እረንጓዴ መስለው ይታያሉ፤ ከብርሀኑም ጋር ተጨማሪ የደስታ ስሜት ይፈጥራሉ። እኩለ ቀን ሲሆን ራያ ጉደ የሚባል ቦታ ደረስን፤ ለእንድ ስለት የሚሆን ካረፍን በኋላ የቁልቁለት መንገዳችን ቀጥለን ጠመዝማዛ መንገዶችንና መታጠፊያዎችን በትግስት ካቆራረጥን በኋላ እንደል ዌልስ ደረስን።

በሚቀጥለው ቀን፣ ገና ሳይነጋ፣ የተሠራ ቁርስ ከበላን በኋላ መንገዳችን ቀጥለን እኩለ ቀን ሲሆን የላይኛው ሶሮ የሚገኝ ጣቢያ ደረስን። በዚህ ቦታ፣ ከብቶቻችን ሲመገቡና የኛም ምሳ ሲሰራ ለሁለት ሰኣታት አረፍን።

ከቀኑ ሰምንት ስኣት ሲሆን፣ የኔ ትንሹ መንገደኛ ቡድን እንደገና መንገዱን ቀጠለ። ከኋላችን ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ መኮንኖች ከነጭነት ከብቶቻቸው ይከተሉናል፤ እነሱም እንደኔ ዙላ ለመድረስ በጉጉት ላይ ነበሩ።

ሙቀቱ በዚህ ስኣት በጣም የተጠናከረ ነበር፤ ይህም፣ በተለያዩ ነጭ የአለት ግድግዳዎች ላይ የሚንፀባረቀው ብርሃን ሰለተጨመረበት ነው። በነዚህ ግድግዳዎች መሀል ነው ጠመዝማዘው የሶሮ ማለፊያ የሚሄደው። ለሁለት ማይሎች ርቀት፣ የሶሮ የመንገዱ ስፋት ሰላሳ ጫማዎች ቢሆን ነው፤ ከዚያ በኋላ፣ ለእምስት ማይሎች ርቅት፣ የማለፊያው ጎን ስፋት በየሥፍራው ወደ ሃያ ጫማዎች ይጠባል፤ ቀጥ ያለው የአለት ግድግዳ ወይም ቋጥኝ ወደ ላይ ስምንት መቶ ጫማዎች ከፍታ አለው። መንገድ እየገፋን በሄድን ቁጥር ሙቀቱ እየጨመረ ይሄዳል፤ ፀሀይዋ ደግሞ በሚሸሽ ደመና ስትጋረድ አስተዋልኩኝ። የሚጋረፍ ነፋስ አልፎ አልፎ እኛን እያለበስን ያልፋል።

ከሶሮ መግቢያ ሶስት ማይሎች፣ የእውሎ ነፋስ መምጣትን የሚጠቁሙ እነዚህ ምልከቶች ከኋላችን በሚከተሉን ቡድኖች በጭንቀት ነበር የተስተዋሉት። ድንገት፣ የሚታጠፈውን፣ በሸለቆው ውስጥ ያለውን መንገድ

እንደዞርን፣ ብዛት ያላቸው ወደ ሺ የሚሆኑ መኮንኖችና ሲቪሊያኖች በነፍስ አውጭኝ አይነት ሩጫ ወደኛ ሲመጡ እገነናቸው።።

እርስ በርሳችን እየተቀራርብን ስንመጣ፣ መኮንኖቹ ወደ ሶሮ ማለፊያ እንድንመለስ ወደኛ ይጮሃሉ፤ የሚሉትም፣ ከዚህ በፊት ውሃ ያልነበራቸው ጉድጓዶችና ሥንጥቆች በውሀ ስለተሞሉ ወደፊት መሄድ እይቻልም።።

እንደሚሉት ከሆነ፣ ከመንገድ ሠራተኞች ጋር በመሆን ጦሩ ከስናፌ ሲመጣ ማለፍ የሚችልበትን መንገድ እየሠሩ ነበር፤ ነገር ግን ወደላይ ወደ ጣቢያ እንዲመለሱ ተገደዋል።። ምክንያቱም በዝናቡ ጊዜ ማንም ህይወት ያለው ፍጥረት በማለፊያው ውስጥ መቆየት አይችልም፤ ዝናብ ከጣለ፣ በሶስት ሰአታት ውስጥ የእስር ጫማዎች ጥልቀት ድረስ ጎርፍ ስለሚሞላውና በተጨማሪም መቶ ፓውንድ ድረስ የሚከብዱ ትልልቅ ድንጋዮችን ውሀው በድንገተኛው ጎርፍ እያንከባለለ ስለሚወስድ ነው።።

ጎላ ያሉት ደመናዎች፣ የተሸፋፈነው እየር፣ ባጠቃላይ የሚታየው ጨለማ ሁኔታ፣ ያለ ምንም ጥርጥር በቀን የሚከሰተው የዝናብ ማዕበል መምጣቱን ይጠቁማሉ።። እናም አሉ፤ አሁንም ቢሆን ሶሮ ለመድረስ እዳጋች ነው ምክንያቱም በማለፊያው የውሃው ጥልቀት ሁለት ጫማዎች ይደርሳል።። ከልባቸው የተቃወሙበት ሁኔታና የሚከሰተው ችግር በኔ ኮምፓኒ ውስጥ በነበሩ መኮንኖች ላይ ተገቢ ውጤት ነው ያሳየው፤ እናም ወደኋላ ወደ ዲፓው ተመለሱ።። እኔ ግን ወደፊት ለመግፋት ወሰንኩኝ፤ የነበረው ምክንያት ደግሞ፣ ደብዳቤ የምታመላልሰው መርከብ በሚቀጥለው ቀን ማታውኑ ከዙላ ወደ ሱዊዝ ስለምትሄድ ነው።። ስለዚህ የግማሽ ቀን መዝግየት ደግሞ በጊዜ ዙላ ለመድረስና ለመጓዝ የማድርገውን ዝግጅት ስለሚያስተጓጉልብኝ ነው።። የመንገዱ ርቀት ደግሞ ባልለሰለሰው መንገድ ላይ ስላሳ ማይሎች ነበር።። እንግዲህ እኔን ወደጥፋት የሚሄድ ሰው ነው ብለው በማመን መኮንኖቹ ወደ መንገዳቸው በፍጥነት ሄዱ።።

የአየርላንድ ወታደሮች ሁልጊዜም ቢሆን በነገር ለመሳሸም ዝግጁ ስለሆኑ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው የሹፈት ስላምታ ስጡኝ፤ ለሁሉም፣ መልሴ በደግ ሁኔታ በቀልድ መልክ ነበር።። በእለምሯቸውም፣ ከእስር ሰአታት በኋላ እኔ ራሴን "በደቪ ጆንስ ሎከር" (Davy Jonese Locker)[165] ውስጥ ነው የማገኘው ብለው እምነዋል።። እንዳንዶቹ ከሰተር ብለው ከኔ ጋራ በሀይል ተከራከሩ።። ምናልባትም፣ "የወደደ ሰው በራሱ መንገድ ይሂድ"፤ የሚለውን አባባል አስታውሰው ይሆናል ትተውኝ ሄዱ።። የጉልበት ሠራተኞቹም ቢሆኑ

---

165 የባህር ወለልን ለመጥቀስ የአነጋገር ዘይቤ፤ ማለትም በባህር ውስጥ የሰመጡ መርከበኞች አሟሟትን ሁኔታ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት አባባል ነው።።

ባንድ ደምፅ፣ ራሀ ናሂን፣ ሳሂብ ሳሂብ፣ (ጌታው፣ መንገድ የለም) ብለው ጮሁ፤ ነገር ግን ጩኸታቸው በተደፈነ ጆሮ ማረፉን ሲያዩ፣ እነሱም ቢሆን የያንኪውን ጌታ ለመጨረሻ ጊዜ ነው የምናየው በማለጥ ሰላረጋገጡ፣ ኩሀዳ ሃፊዝ፣ ሳሂብ፤ (ፈጣሪ ይጠብቅህ!) በማለት መንገዳቸውን ቀጠሉ። ሰለፀሎታቸው እመለሣኘ፣ በፍጥነት እንዲጋልብ ፈረሴን መግረፍ ጀመርኩ።

በሁለቱ የማለፊያው ግድግዳዎች ላይ ያለው የሰማይ ጥለት ጥቁር በሆነ የከፋይ መጋረጃ የተከተረ መሰለ፤ እናም የመንገድ ሠራተኞቹ የመጨረሻው ቡድን በማለፊያው ውስጥ ለእይታ ከመሰወሩ በፊት ዝናብ መጣል ጀመረ።

ዝናቡ ቀስ እያለ መውረድ ጀመረ፤ በጠጠሮችና በድንጋዮች ላይ የሚያርፉት የዝናቡ ጠብታዎች የማር ተፈዛ ዶላር ያካክሉ ነበር። ቀጥሎ ግን ዝናቡ እየፈጠነና እየገዘፈ መሄድ ጀመረ። የሚያጉረመርመው ነጎድጓድ፣ መጀመሪያ፣ የእንጨት ደልድይ ላይ መድፍ ሲተኮስ እንደሚሰማው መርገብገብ ዝቅ ያለ ድምፅ ነበረው፤ ነገር ግን ድንገት ተለውጦ ከፍ ያለ ድምፅ ማሰማት ጀመረ። መንትያ ብልጭታዎች ገሃድና እስፊሪ መሆን ጀመሩ። ደመናዎቹ ራሳቸውን ሲገላለጡ የመንግሥተ ሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ፤ ዝናቡም ያለማቋርጥ እንደ ጎርፍ ወረደ።

ለህይወታችን ሰንል፣ ውሀ በሞላባቸው ጉደጓዶች እየተንቦራጨቅን፣ ውሀ ገና ያለሞላባቸውን ጉድጓዶችን በላያቸው ላይ እየዘለልን፣ በትልቅ ድንጋዮች ዙሪያ፣ በሚያዳልጥ እለት በግልቢያ ወደፊት ገሰገስን። ማዕበሉ እሰከሚያልፍ መቆየት የምንችልበት ወጣ ያለ መጠለያ የሚሆን እለት ለማግኘት ሳናሰልስ ዙሪያውን እየተመለከትን ነበር።

በቅፅበት ቆዳችን ድረስ ብስብስ ብለናል፤ የባህር እሳ ይመሰል ውሀው ከላይችን ላይ ይወርድ ነበር። ጓዙም በዝናቡ በጣም ሰለራሰ እንሰሶቹ መሸከም የማይችሉት ጭነት እየሆነ መምጣቱ ግልፅ ሆነ፤ ድንኳን የተሸከመው በቅሎ በከብደቱ ምክንያት መንገዳገድ ጀመረ። የቴዎድሮስን ምንጣፍ የተሸከመውም ድንገት ጀርባው የተሰበረ መሰለ። መንገዱ በወራጅ ውሀዎች ተሞላ፤ የውሀው ፈሰስ ፍጥነት ጨምሮ እየገዘፈ በመምጣት በጥልቀት እየጠረገ መውረድ ጀመረ። እሰካሁን ድረስ፣ እይጥ እንኳን መጠለል የሚችልበት ቦታ የሚሆን ምልክቱም የለም፤ በጎንና በጎናችን ያለው ግድግዳ ልክ በመሰመር ወደላይ የተገነባ ይመሰል ቀጥ ያለ ነበር።

ከእያንዳንዱ ግድግዳ እናት ላይ፣ ውሀው ቀጭን መስመር በመስራት የቀለጠ መሰታውት መስሎ ወደታች ይወርድ ነበር። ነገር ግን ገና ሀሳባችን ሳንቀይር፣ እነዚህ ቀጠን ብለው የሚወርዱት ውሃዎች ወደፏፏቴ በመቀየር በሁለቱም ግድግዳዎች ሳይ ሙሉ በሙሉ ይወርዱ ጀመር፤ በሚወርደው ውሀ

የተፈጠረው ነጎድጓድ የመስለ ድምፅ ራሱ ጆሮ የሚያደነቁር ነው የሆነው። ይህ አዲስ የተፈጠረው አደጋ በቀጥታ አስኒ መሆኑን ግልፅ አደረገ፤ ዛሀሩካ የሚባለው አንደኛው የሂንዱሲታን ሠራተኛዬ በግድየለሽነት ግድግዳውን ተጠግቶ ወደሚወርደው ወደ አንዱ ፏፏቴ ስር ሄደ፤ አናም አንደኛው ወራጅ ውሀ በቅፅበት ከመሬቱ ጋር አላተመው፤ የተፈጠረው ወራጅ ውሀ ጉልበት እያገኘ ሰለነበር ልክ በቀስት እንተወረወረ ፍላጻ በትልልቅ አለቶች ላይ እየገፋ ወስዶ ከኛ ትንሽ ርቀት ላይ በሚገኝ የውሀ ኩሬ ውስጥ ወረወረው።

በፍጥነት በተደረገለት ርዳታ ሀይውቱ ተረፈች፤ ነገር ግን ጭንቅላቱ ላይ ቆስሎ ሰውነቱ ደግሞ ተላልጦ ነበር። የኩሬው ውሀ የኔን ቡድን አስቆመው፤ ወደፊት መሄድ አልቻልንም። ኩሬው ሲመረመር፣ የ8 ጫማዎች ጥልቀትና የ50 ጫማዎች ርዝመት ነበረው፤ ርዝመቱ ደግሞ ማለፊያውን ዳር አሰከዳር ይሸፍናል። ዳሩና ጎኖች ለዘመናት በሚወርደው ጎርፍ ውሀ ምክንያት የለሰለሰ፣ አንደ ሀውልት የቆመ አለት ለአስር ጫማዎች የሚሆን ርዝመት ወደ ኩሬው ገባ ብሎ ይታያል። በዚህ አለትና በማለፊያው ግድግዳ መሀከል የአምስት ጫማዎች ስፋት ያለው ክፍት ቦታ ይገኛል። በቦታው ከፍ ባለው አካባቢ፤ መሬቱ በሚሸረሸር አሸዋማ አፈር ነው የተሞላው፤ የዚህ አሸዋማ አፈር ልል ስለሆነ በሀይለኛ ጎርፍ እየታጠበ በመሸርሸር ወደ ባህር ከመሄድ የሚያስጥለው መከላከያ የለውም።

በዚህ አለት ላይ ቡድኔን ሰበሰብኩበት። ለኛ፤ የእውነትም የመዳኛ አለት ነው የነበረው፤ ነገር ግን የእንግሊዝ መኮንኖች እንዳሉት፤ ውሀው ማለፊያውን አጥለቅልቆ የአስር ጫማዎች ጥልቀት ያለው ጎርፍ ከፈጠረ፤ የነበረን አማራጭ ሴላ ሳይሆን ፈረሶቻችንን ከስር ሆነው በሰአት ሀያ ኖት[166] ፍጥነት መዋኘት ነበር፤ አለዚያ ደግሞ መስመጥ ነው።

አእምሯችን ባጋጠመን አደጋ ተውጥሮ እያለ፣ አሁን መጠጊያ ሰላገኘን የአደጋዎቹ ተፈጥሮና መጠን ግልፅ አልነበረም። ስለዚህ የነበረን አማራጭ በዚህ መጠጊያ ሥፍራ ያለምንም አንቅስቃሴ መቆየት ነበር። ሰለ አደጋዎቹ የነበረን ዕውቀት፣ አደጋ የተጋረጠ እንስሳ ጎርፉን እንዴት ማምለጥ እንደሚችል በሀሳብ የተወጠረ አንጎል ማሰብ የሚችለውን ያህል፣ ምንም በቅጡ የሚታወቅ ሁኔታ ሆኖ አልነበረም የቀረበልን። አሁን ግን መጠለያ ሰላገኘንና ከድንገተኛ ሞት ስለተረፍን፣ አአምሮዬ ወዲያውኑ ስለዚህ የጎርፍ አደጋ ሁኔታ አመጣጥ ማንሰላሰል ጀመረ። ስለ ሁኔታው በጥልቅ ለመዘርዘር ቦታው አይደለም፤ ነገር ግን ለአንባቢ በሚበቃ ዝርዝር፣ ይህ ድንገተኛና ሀይለኛና የሚጠራርግ ጎርፍ፣

---

166 ኖት(knot) በውሃ ላይ የፍጥነት መለኪያ ነው። 1 knot 1.8 ኪሎሜትር በሰአት ነው። ሰለዚህ በሰአት 38 ኪሎ ሜትር ፍጥነት መዋኘት ነበረባቸው።

የ800 ጫማውች ጥልቀት ሲፈጥር ማረጋገጥ እንደቻልነው፣ እመጣጡ ከመቶ ማይሎች ርቀት ባሉ ቦታዎች የተጠራቀመ ዝናብ ነበር፤ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው ፈፋዎችና ትንንሽ ሸለቆዎች የነበራቸውን ውሀ በሙሉ ወደዚህ ውሃ ወደ ባህሩ ለመውረድ ዋና መንገድ ወደሆነው ወደ ማለፊያው ሰለተፉም ነበር።

በተፈጥሮው ሰው በአደገኛ ሁኔታ ሲከበብና በዚህም ምክንያት ሰውነትና እእምሮ መነዳት ሲጀምሩ፣ ለረዥም ጊዜ መፈላሰፍ አይችልም። የሚወርደው ውሃ የሚፈጥረው ጎርፍ ሀይል በፍጥነት ወደሚያጥለቀልቅ ትልቅ ውሀ ከፍ እያሰ ሲሄድ ተመሰከትን፤ ዝናቡ ካልቆመ በሰተቀር በዚህ ሁኔታና ዕይታ የኛ ዕጣ እየተወሰነ ነው የሚሄደው። ምርር ባለ ሁኔታ፣ የሠራተኞቹ ቡድን የሠጡኝን ማሰጠንቀቂያ ባለመሰማቴ ያደረብኝን ፀፀት እኔ ራሴ ነው የማውቀው። ቦታውና ጊዜው በጣም መጥፎ ሰለነበር፣ ትርጉም የሌለው ፀፀትን ለማስተናገድ የሚሆንም እልነበረም። ለኛ ማድረግ የምንችለው የቀረ ነገር ቢኖር በታቻለ መጠን ትግስተኛ መሆነ ነበር፤ በሚቆረቁር አይን እየጨመረ የሚሄደውን ጎርፍ ማየት፤ የሚያሰማውን የሚያጓራ ድምፅ በሽብር መስማት፤ እናም የሁኔታውን ትልቅነት ሁላችንም እያደነቅን ነበር።

ዝናቡ ቁልቁል ያለማቋረጥ ይወርዳል፤ በላያችን ላይ ደግሞ ጆሮ የሚያደነቁረው የነጎድጓድ ድምፅ ይሰማል፤ ከግድግዳ ግድግዳ እየነጠረ ሲቀባበል ደግሞ በሺ ዕጥፍ ሆኖ ነበር የሚሰማው፤ ከዚህም ጋር ብልጭታው በአረንጓዴ ነበልባሎች በእያንዳንዱን የጋራ አናትና የገደል ጠርዝ ላይ ብርሃን ያበራ ነበር።

የውሀ ንጣፎች እሁንም ወደታች ይወርዳሉ፤ እሁን ግን ብርማ ቀለም ካለው አረፋ ጋር ነው። ወደፊትና ወደታች፣ ማለፊያው፣ የሚገነፍለውን ጎርፍ ያሸከረከረዋል። ከአሁን እሁን ወደላይ ከፍ ከፍ እያለ እኛ ከቆመንበት የአለት ንጣፍ በሰተቀር በፊት ለፊቱ የሚየገኘውን ሁሉንም ነገር ተሸከሟል፤ አሸዋማውን መሬት በቶን በሚሆን መጠን እየሸረሸረ፤ በመታጠፊያ ቦታዎች እየተንበጫረቀና እየተወረወረ ሰብሰብ ይልና የሚገደብው ነገር ካለ ደግሞ አረፉ ይፈጥርና በላዩ ላይ ፈጣን ፏፏቴ በመፍጠር ነጫጭ ቁልቁል የሚረወሩ የውሃ ወራጆች እየሰራ እንደገናም ኩሬዎች ይፈጥራል፤ ይህ ሁሉ ሲሆን፣ እሰር ሺ የሚሆኑ ለጦርነት የሚቀሰቅሱ ታምቡሮች ያከል የሚያጓራ ድምፅ ያሰማ ነበር።

እነዚህ የማያቋርጡ ድምፆችና በተራቸው በብዛት የሚነጥሩት ገደል ማሚቶዎች ጠንካራ የሚባለውን ሰው እንኳን የፍራቻ ሰሜት ይፈጥሩበታል፡ የኔ፣ የእረብና የሂንዱ ሠራተኞች ከዚህ በምንም ርቀናል ማለት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ነው ያሉት። የነበረባቸውን ፍርሃትና መጠን እልባ የነበረውን ሰጋት በማያቋርጥ ጩኸት ነበር የገለፁት።

አሁንም ቢሆን ዝናቡ ያለማቋረጥ እይወረደ ፊታቸን ይገርፋል፤ በውሃ ፍንጣሪም አይናችን አውሮናል። የውሃው ማዕበል ከፍ እና ወደላይ ከፍ እያለ፣ በእያንዳንዱ ቅፅበት እየጨመረ፣ በእያንዳንዱ ጠብታ ደግሞ ጉልበቱንና እሸባሪነቱ እየጨመረ ነበር። በማለፊያው፣ ሶስት ጫማ ጥልቀት ያለው ወራጅ ውሀ ነበር።

የጎርፉ ወራጅ ማዕበል ወደ ሀይለኛና ግዙፍ ወንዝ ተቀይሮ መገደብ በማይቻል ፈሰስ ወደኛ እየወረደ ነው። ፀጥ ብሎ የሚወርደው ውሀ፣ እኛ አጠገብ ሲደርስና ከቆምነበት አለት ጋር ሲጋጭ መንቦራጨቅ ይጀምራል። ከዚህ በፊት እንደሆነው ሁሉ፣ ወደ አለቱ ለመምጣት የተራመድንበት አሸዋማ መሬት ጎርፉ ጉልበት ሲያገኝ ተሸርሽሮ ሄዷል። እኛም እንግዲህ በምንም መንገድ ቢሆን ከአደጋ ነፃ ነን ማለት አንችልም። ውሃው በፍጥነት ከፍ እያለ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ከአለቱ የሰምንት ኢንች ርቀት ነው ያለው፤ ግን በተደረገው ሰሌት ለግማሽ ሰአት ተጨማሪ ዝናብ ቢወርድ አለቱን በሶስት ኢንች ጥልቀት ያለብሰው ነበር።

በነዚህ ከፍታዎች ተከበን፣ የአለም መጨረሻ በመሰለ ሁኔታ ሀይለኛ የሆኑ የፏፏቴ ወራጆች ጋርደውን፣ ወደላይ በግርማ ሞገሰ በሚተኑት ውሃዎችና በሚፈነጠቀው ውሀ ፅልመት ተውጠን፣ የኛ ሁኔታ በእውነት የሚያላዝን ነበረ።

በሚታየው አሰቃቂ ሁኔታ ላይ ለመጨመር፣ ከሚገነፍለው ውሃ በላይ፣ እጃቸው የተዘረጋ የሰዎች አሰከሬኖች እየተንሳፈፉ እያለፉን ይሄዱ ጀመር። የበሬ፣ የፈረስና የበቅሎ ሬሳም ቢሆን እርሰ በርሰ እየተላተመና እንደመሰናከል ከተቀመጡ አለቶች ጋር በሀይል እየተጋጨ እብሮ ይወርዳል። የቴሌግራፍ ምሰሶዎችም ከኋላቸው የቴሌግራፍ ሽቦዎችን እየጎተቱ በብርሃን ፍጥነት አልፈውን ይሄዳሉ። ጋሪዎችና የጋሪዎች ጎማ እኛ ከተጠለልነበት አለት ጋር ይላተማሉ። ድርቆሽ፣ የገለባ ክምር፣ ቁጥቋጦዎች፣ እንደገናም የሰዎች አሰከሬኖች በሚገነፍለው ወራጅ ውሰጥ ተደበላልቀው ይመጣሉ።

በዚህ አውሬ በሆነ ተፈጥሮ የሚታየው ጥፋትና ሞት አሰፈሪ ምሰከርነት የኔን ሠራተኞች ሽብር ጨምሮታል፤ እናም በሚያሰቀቅ ጩኸት ለእላህ የሚያሰሙት ፀሎት ከማዕበሉም ሆነ ከጎርፉ በላይ ይሰማ ነበር።

ለእንድ ለእት ከአርባ እምስት ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ከዘነበ በኋላ ለአፍታ ያህል ጋብ አለ። እንደገና ሲጀምር ግን ከመጀመሪያው በበለጠ ሀይለኛ ሆኖ ነበር የተመለሰው። ውሀው ከቆምንበት አለት ክፍተኛው ቦታ ጋር እኩል ሆነ፤ እንደገናም እየጨመረ ነበር። በውሀው የተፈጠረው ጭጋግ እየለቀቀ ሰለነበር ወደላይ አንጋጠን ተመለከተን። የፀሀይ ብርሃን ፍንጣቂዎች

ጨለም ባለው ጭጋግ በሰርቆሽ አየገቡ ያልፉ ነበር፤ አንደዛም ሲሆን የዝናቡን ጠብታዎች የተለየ የሚያንፀባርቅ ገፅታ አየፈጠሩባቸው ነበር። ከእናቱ ላይ የተወሰነ ቁጥቋጦዎች መኖራቸው ለኛ መታየት ጀመረ፤ ልክ በዘላለም ሞት አፋፍ ላይ አንደንተንጠለጠለ ነፍሰ፤ በወጀቡ ምከንያት አየተርገፈገፉና አየተወዛወዙ ነበር። በዚህ በጨለማው ሁኔታ ድንገት ብልጭ ያለው ብርሃን መገለፅ የማይቻል ትልቅ ሁኔታ ነበረው።

ውሀው አግራችን መንካት ጀመረ፤ አለቱ ላይ አሰቀምጠን የነበረውን ጓዛችንም ይዞት ሄደ። እንሰሶቹ ደግሞ መቁነጥነጥና በሚያሳዝን ሁኔታ ድምፅ ማሰማት ጀመሩ፤ ከብት ጠባቂዎቹም ቢሆን ባልተለመድ ከፍ ባለ ድምፅ ፀሎት ጀመሩ፤ አኔም ተሰፋ ቆረጥኩ። በርግጠኛነት የተሰማኝ ሰሜት ቢኖር በጥቂት ሰከንዶች ውሰጥ በዚህ አየጨመረ በሄደው ውሀ ውሰጥ ለሕይወታችን ሰንታገል ነው። ግን፣ ድንገት ዝናቡ ቆመ። የነበረው ጭጋግ ደግሞ ተመልሶ ለመጣው ፀሀይ ብርሃን ቦታውን በመልቀቅ ሚሸሸ። የቃል ኪዳን ቀሰተ ደመና አንድ ጎን በኢድማሱ በከል መታየት ጀመረ። ተርፈናል!

በጥቂት ደቂቃዎች ውሰጥ ሲወርድ የነበረው ፏፏቴ ሀይሉ ቀንሶ ወደ ደካማ ወራጅ ውሃ ተቀይሮ ትንሽ ቆይቶ ጭራሹን አቆመ። በአሰር ደቂቃዎች ውሰጥ ደግሞ የውሀው ጥልቀት በሁለት ኢንቾች ቀነሰ።

ከቀኑ አሰራ እንድ ለአት ሲሆን፣ ከዚህ በፊት ወንዝ ይወርድባቸው የነበሩ ቦታዎች ትንንሽ ጨረቅረቅ የሚሉ ውሀዎች ሆነው ነው የሚታዩት።

ነገር ግን ከዚህ ካለንበት የአለት ከፍታችን አንዴት ብለን ነው የምንወርደው? ቦታው ከውሃው በላይ አራት ጫማ ከፍ ይላል። አኔም፣ አምሰት የጭነት ከብቶችና የምጋልበው ፈረስ፣ ከሁሉም ጓዜ ጋር ዙሪያውን የሰምንት ጫማዎች ጥልቀት ባለው ውሀ በተከበበ ደሴት መሀሉ ላይ ነው ያለሁት። የረጠበው ልብሳችን አንደለበለን በብርድ አየተንቀጠንቀጥን በዚህ ቦታ ማደሩ በጣም እሰቸጋሪ ነገር ነው፤ ነገሮች በፍጥነት ካልተንቀሳቀሱ በሶሰት ማይሎች ርቀት መንገድ ከሚገኘው የታችኛው የሰሮ ጣቢያ ከመድረሳችን በፊት ጨለማ ይሆናል። አብዛኛውን ጓዜን ጥዬ መሄድ እንዳለብኝ ግልፅ ሰለሆነ ወዲያውኑ መጣል የምችላቸውን ለመምረጥ ሥራ ጀመርኩ። ሰለዚህ ከጨረታው በሀምሳ ሩፒዎች የገዛሁት የቴዎድሮስ ምንጣፍ አሁን 800 ፓውንድ መመዘን ሰለጀመረ፤ ተንከባሎ አጠገብ ወዳለ ኩሬ ተጣለ፤ ያም ሲሆን ላጠፋሁት ገንዘብና አዚህ ድረስ አሰከምደርሰ የተጓዝኩት የ350 ማይሎች መንገድ አየቆጨኝ ነበር። ከዛም የሠራተኞቹ ድንኳኖች፣ ግማሽ የሚሆነው የአልጋ ልብሳቸው ተጣለ። ከዚህም ጋር፣ ሣጥን ሙሉ ልብሰ፣ አንዳንድ ብርቅ ነገሮች፣ የአንበሳ ቆዳዎች፣ የካምፕ ጀበናዎች አብረው ተጣሉ። ለሁለት ቀን የሚሆን ምግብና ሁለት ሣጥኖች ከነዕቃቸው ቀለል እያደረግኩ

ለነበሩት የጋማ ከብቶች ለጭነት እከፋፈልኩ። ቀጥሎም የኔ የራሴ ድንኳን ነበር፤ ከሁለት ተቀዶ ምሰሰዎቹ ከተወረወሩ በኋላ ሽራውን ብቻ ማጓጓዝ ቀላል ነበር።

ለኔ እሁን የቀረኝ ሥራ፣ እንስሶችን ከእለቱ ማውረድ ነበር። የእለቱ ጎኖች ቀጥ ያሉና እንደጠርሙስ ለስላሳ ስለነበሩ፣ እንስሶቹ በራሳቸው መሄድ አልቻሉም፤ እንዲሄዱ ማስገደዱም እልሰራም። ተሞከሮ ነበር፤ ነገር ግን ውጤት አልባ ነው የሆነው።

ሰለዚህ የነበረኝ አማራጭ ተገፍተው እየዋኙ ወደ መንገዱ እንዲሄዱ ነበር፤ መንገዱም ከኛ 15 ያርዶች ርቀት ላይ ነው፤ የመጀመሪያ ሙከራ የተደረገባት የእቢሲኒያ ፈረስ ነበረች። ውሃ ውስጥ በትልቅ መንቦጫረቅ ዘፍ አለች፤ ሆኖም በድፍረት እየዋኘች ወደ ታች ካለው ወደ ውሀው ዳርቻ በጥሩ ሁኔታ ደረሰች። የሚቀጥለው ደግሞ በቅሎ ነበር፤ የጠጠረ ጭንቅላት ነው የነበረው፤ እናም በሚያደርገው ነገር ሁሉ የበቅሎ ባህሪ ነው የሚያሳየው። አሱን ከአለቱ ገፍቶ ለማውረድ ሁሉም ሠራተኞቼ መተባበር ነበረባቸው። ሲወድቅ እግሮቹን ወደላይ ገልብጦ በከባድ ድምፅ ነበር ውሀው ውስጥ የወደቀው፤ ከዛ በኋላ ተመልሶም እልታየም። ሁሌም፣ ድርቅ ያለ ደደብነት ይኸው ነው ውጤቱ። የቀሩት ሶስት ከብቶች በደህና ሁኔታ የውሃው ዳርቻ ደረሱ። ቀጥሎ ጓዙ ላይ የመጎተቻ ገመድ ከታሠረ በኋላ ውሀው ውስጥ ተወርውሮ በሰላም ወደ ዳር ተጎተተ።

መተኪያ የሌለው የኔ ረዳት እሊ፣ የእረቡ ፈረሴ ሰይድና እኔ ነበርን እለቱ ላይ የቀረነው። ስለዚህ ሰይድን ከእለቱ ማውረዱ የኔና የእሊ ሥራ ሆኖ ተገኘ። ኮርቻውን ካወረድን በኋላ፣ ልጓሙን አንገቱ ላይ አስረን ወደ እለቱ ጠርዝ ከመራነው በኋላ ለመግፋት ሞከርን፤ ነገር ግን፣ ይህ ሥራ በሰይድ የኩራት መንፈስ የሚያዋርድ ነገር ሆኖ የተገኘው፤ ስለዚህ በኮቴውና በጥርሱ መሄድ የማይችልና የማይፈልግ መሆኑን በመግለፅ የሚደረገውን ነገር የሚቀበለው እለመሆኑን ማሳየት ጀመረ።

ስለ ፈረሶች፣ በተለይም ስለ አረቢያ ፈረሶች ዕውቀት ያለው አሊ ጋር ከተሟገትን በኋላ፣ ውሳኔው "የያንኪው ሳሂብ"[167] ፈረሱን እንዲጋልብ ተወሰነ። እኔ እንኳን፣ በደልዳላ ሜዳዎችና በእቢሲኒያ መንገዶች ታላቅ ፈረስ ጋላቢ ብሆንም፤ ከፈረስ ጋር ዘሎ ጥልቀት ወዳለው ውሀ መግባት ሌላ ነገር ነበረ፤ ሰለዚህ በትልቅ ቅሬታ ነበር ፈረሱ ላይ የወጣሁት። መጀመሪያ ግን፣ አሊ በአረብኛ ፈረሱን ሲያሞካክሽ ኮርቻው ትከከል መሆኑን ማየት ነበረብኝ።

---

[167] የአሜሪካው ጌታ ለማለት ነው

እሊ ዘለሎ ውህ ውሰጥ አንዲገባና እንዲዋኝ ከጠየቅሁ በኋላ፣ በጥንቃቄ ልጓሙን በመያዝ፣ ለይድን ወደ አለቱ ዳርቻ መራሁትና ውህውን አንዲያሸት፣ አፍንጫውን አንዲያናፋና አንደፈለገው እንዲሆን ሰሶሰት አራት ደቂቃዎች የሚሆን ፈቀድኩለት። ከዛም ሁለት አርምጃዎች ወደኋላ ከሳብኩት በኋላ ራሴንም በኮርቻው ላይ ካሉተካከልኩ በኋላ፣ ባንድ ጊዜ በሁለት ጎኖቹ በመኮልኮያዎች ኮረኮርኩት፤ ያን ጊዜም ልጓሙን በመጎተት ወደላይ ሳብኩት። በዚህ ጠንካራ ፈረሰ፣ የመኮልኮያዎቹ ውጤት ፈጣን ነበር፤ ልክ እንደ ግሥላ፣ ለሰከንድ የሚሆን ካደባ በኋላ ከአለቱ ተነሰቶ ወደላይ ወደአየር ዘሎ ውህው ውሰጥ ገባ። ሰይድ፣ ጆሮዎችን ካራገፈ በኋላ በከፊል አየዋኘ ወደ ውህው ዳርቻ አመራ።

ዳርቻው ሲደርሰ፣ የተደሰተው አሊ፣ ምርጡ የአረብ ፈረሰ በአሸናፊነት ለመወጣቱ ከብር ሲል ሰይድን አቀፈው፤ በፈረሱ ድፍረትም ያልተጠበቀ አድናቆቱን ቢዘህም በዚያም አያለ ገለፀ።

ጓዛችን አንደገና ጠፍረን ጉዟችን ቀጠልን፤ በዚህ ጊዜ ማለፈያው አየደረቀ ነበር። ለሁለት ማይሎች፣ በትልልቅ ድንጋዮች፣ ጉድጓዶችና፣ ንጣፍ እሰቶች ላይ ከታገልን በኋላ፣ ከፍተቱ ሰፍቶ ወደ ሸለቆ ተቀየረ። በጎንና በጎኑም ዳገታማ ኮረብታዎች፣ ርጥብ ገደሎች፣ ውሃ የሚያንጠባጥቡ ደኖች፣ ተለይቶ በማይታወቅና ሚለጥራዊ ሁኔታ ወደፊት ተዘርግተዋል።

በግምት፣ ከምሽቱ አንድ ሰአት ሊሆን የታችኛው ሶሮ ጣቢያ ደረሰን፤ ምሽቱ ወደ ጨለማ አየተቀየረ ነበር። የጣቢያው ሀላፊ የሆነ መኮንን በማለፈያው ከነበረው አደጋ ተርፈን በመምጣታችን በጣም ተደነቀ። ጎርፉ ሀይለኛ በነበረበት ሰአት፣ የአምሰት ሰዎቹ አሰከሬን ሲንሳፈፍ አግኝተው ሰለነበር፣ የጣቢያው ሰዎች የበለጠ ጥፋት ይደርሳል ብለው ገምተው ነበር። ሁኔታውን አውርቼ ሰጨርሰ፣ መኮንኑ፣ "ከሚገባው በላይ ተጨንቄ ነበር።" አለ፤ "ሰውነትህን ለማሞቅ፣ መጠጥ ወይም አንድ ነገር፣ ታውቃለህ፣ ወይም አንድ ብርጭቆ ብራንዲ ዋይን አና ሶዳ ላንተ ጥሩ ነው፣ ታውቃለህ" በማለት ጋበዘ።

የአንግዳ ተቀባዩን መኮንን የመጠጥ ግብዣ ከብዙ ምስጋና ጋር ነው የተቀበልኩት፤ ነገር ግን መጀመሪያ ድንኳናችን መወጠር ነበርብን፤ ከዛም የደመቀ እሳት አንድደን ጥሩ ራት በመብላት ሰውነታችን መልሰን፣ ትኩሰ ቡና ጠጥተን፣ የጋያ ትምባሆ ለኩሰን፣ በግድግዳ ሰለታጠረው ማለፈያ፣ ሰለ አደገኛው ጎርፍ፣ እና ሰለ አሰቃቂ የታላቁ ሶሮ አደጋዎች በመዝናናት ካወራንና ከሳቅን በኋላ ነበር።

በሚንቦገቦገው አሳት ሙቀት ካገኘን በኋላ፤ ትኩስ መጠጥ በመጠጣት ከሚመጣው ቁርጥማት ራሳችን ከተከላከልን በኋላ፤ አንድ ላይ ቁጭ ብለን በተስበበረ አንግሊዝኛ ማውራት ጀመርን። ምከንያቱም ሠራተኞቼ ጥሩ ነገር በሠሩ ቁጥር ወዳጅነት ስለማበዛም ነበር። በደበዘዘው የአለቶቹ ጥላ ስር ሆነን ለስአታት አወራን፤ ያም ሳናውቀው ወደ አንቅልፍ አለም ተሻግረን፣ መንገድ የለሽ በሆነው የአንቅልፍ በረሀ ድብን ብለን አስከንተኛ ድረስ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን፣ ከንጋቱ አስር ሰአት ሲሆን ወደ ቁማይሌ መንገድ ጀምረናል፤ ከአንድ ሰአት በኋላ ከሶሮ ማለፊያ መውጫ ካምፕ ደረስን።

ቁርስ በልተን፣ ቁማይሌን አልፈን ሄድን። ሙሉ ቀን ሲሆን፣ በግራና በቀኛችን በተንጣለለውና ፊት ለፊታችን ለአስራ ሁለት ማይሎች በተዘረጋው ግለታም የዙላ ሜዳ ብቅ አልን። እንደ በረዶ ከሚነጣው ጊዜያዊ የወታደሮች ካምፕ ባሻገር የቀይ ባህር ስማያዊ ውሃ ያብረቀርቃል፤ በላዩም በሚያለገርም አስላለፍ የባህር ጥልቅ አንስሳዎች ሲጋልቡ ይታያል።

እኩለ ቀን ሲሆን ሁላችንም ዙላ ደረስን፤ ወደፊት የምናገኘውን ዕረፌት በማሰብ ከልባችን ደስተኛ ነበርን።

ዙላ፣ በመጀመሪያ ሳርፍ ከነበረው የተወሳሰበ፣ ግርግርና ጩኸት ስፍናበት ከነበረበት ሁኔታ ይለያል። ትልልቅ መካዝኖች ተሠርተዋል፣ በወስጣቸውም በቶኖች የሚቆጠሩ በጥንቃቄ የታቀደ ዘመቻ የሚያሰፈልገው ነገሮች በሙሉ ተደርደረዋል። የገበያ ቦታዎች በብዛት ነበሩ፤ ግማሽ ምግብ ቤትና በግማሽ መጠጥ ቤት የሆኑ፣ በቅጽል ስም "የአነስሊ አዳራሽ" ተብለው የሚጠሩ ቦታዎች አስከ 120 ዲግሪ ፋራናይት በሚደርስው ሙቀት ለሚስቃዩ መኮንኖች ማስተናገጃዎች ተሠርተዋል። በውስጣቸውም መጠጠ የያዙ የአንጨት በርሜሎች፣ ሶዳ ውሀ፣ ብራንዲ ዋይን አናም ከፈንግታ ጋር ሰውነት የሚያዝናኑ መጠጦች ነበሩ። ሁሉም ሆስፒታሎች ወደ ቁማይሌ ተወስደዋል፤ ቦታውም በደጋው በሰናፈና በባሀሩ መካከል ስለሆነ ለህክምና ጥሩ ቦታ ነበር።

ከምሽቱ 12 ሰአት ሲሆን፣ የጭነት ከብቶቼን በቅናሽ ዋጋ ሸጥኩኝ፤ ሠረተኞቼንም አስናበትኩ፤ ኤሊንና ሰይድ የሚባለው የአረብ ፈረሴ ኢንዶር በተባለች መርከብ ውሥጥ መሳፈራቸውን አረጋገጥኩ። *(ሰይድ የአረብ ፈረሴ ወደ ኒው ዮርክ በመርከብ ተልኮ፣ ከአቢሲኒያው ችግር ተርፎ የክብር ኗሪ በመሆን በሚመች ጋጣ በምቾት ይኖራል)* መርከቧ፣ በጠዋቱ፣ ኮሎኔል ሚልዋርድንና የሮያል መድፈኛውን ቡድን በመያዝ ወደ ሱዊዝ ካናል ልትሄድ ነው። አነዚህ ሰዎች፣ የዘገየውን የጄኔራል ናፒየር ሪፖርትና የአፄ ቴዎድሮስን አራት ዘውዶች ለእንግሊዝ ንግሥት አንዲያደርሱ የተመረጡ ነበሩ።

የኮሚሳሪያቱ የጋራ ጓደኞቻችንና ካፒቴን ደውስ፣ ለሚመለሱት የከሩሴድ ተዋጊዎች ያልተጠበቀ ድግስ አዘጋጅተዋል። ከመሳፈሬ በፊት፣ በመሀከላችን በጓደኝነት መንፈስ እንድንቀጥል ርስ በራሳችን ቃል ገብተናል፤ ቃለ መሀላውን የገባነው የመጨረሻውን የመጠጥ በርሜል እውርደን እየጠጣን ነበር፤ በህይወት እስካለን ድረስ ደብደቤ እንድንፃፃፍ ነበር። ከዛ በኋላ ደግሞ ለሜት የሚነካ መለያየት ነበር፤ ታምናላችሁ? ከበሩ አሰር ያርዶች ርቀት ከመሄዴ በፊት፣ እንደገና ተመልሼ ለመልካም መንገድ እንድ መጠጣት ነበረብኝ፤ እናም ሆነና፣ ሁላችንም የመጨረሻ ደህና ሁኑ ስንብት ተነፈስን።

በሚቀጥለው ቀን ሲነጋ፣ ኢንዶር የተባለችዋ መርከብ ጉዞ ጀመረች። ፀሀይዋም በምስራቁ አድማስ በኩል በመነሳት፣ በላያችንና በዙሪያችን ያለውን ደመና፣ ደመቅ ያለ ቀይ ቀለም እየቀባች በመንገዳችን ላይ ታጅበን ነበር። ዝቅተኛው የእነስሲ ወሽመጥ እሸዋማ ቦታ፣ ሰፈው የዙላ ካምፕ እና ኩሩዎቹ የእንግሊዘ መርከቦች ወደኃላ እየራቁን ሄደው በመጨረሻም ከዕይታ ተሠወሩ። ነገር ግን፣ የሰናፈና የሶሮ ሸለቆዎች በውሰጣቸው የሚሄዱባቸው ትልልቆቹ ወይም ከፍታ ያላቸው የሃዳስ እና የእዞርታ ተራራ ሰንሰለቶች፣ ከዕይታችን የተሠወሩት ከሶሰት ሰእታት በኋላ ነበር። ሲሰወሩም ተለይተው በማይታዩበት ሁኔታ ከኑቢያ ተራራ ሰንሰለቶች ጋር በመደባለቅ ነበር።

ጦሩ በሰላም ቁማይሌ ደረሰ፣ በሰኔ ፲፣ በባቡር ወደ ዙላ መጣ። በጎርፉ ባጠቃላይ ፲0 ሰዎች አጥቷል። ከሰምንት ቀን በኋላ የተለያዩት ሬጅመንቶች ወደየ መድረሻ ቦታቸው ወደ ሱዌዝና ወደ ቦምቤይ መንገድ ጀመሩ።

ከእንድ ወር በኋላ፣ በእቢሲኒያ የነበረው ያ ትልቅ ካምፕ እከተመ። የማጓጓዣ መርከቦችም ከእቢሲኒያ ባህር ለዘላለም ለመለየት ከንፋቸው ዘረጉ። ስለዚህ ይህ ዘመናዊ የከሩሴድ ዘመቻ፣ ከሌሎች ካለፉ ሁኔታዎች፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር ለመታወስ፣ በሁሉም ስፍራ እናም በተሳካ ሁኔታ ከተጨረሱ ዘመቻዎች ጋር በቁጥር የሚጨመር ሆነ።

ፍፃሜ

የምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች

ቁጥር 161፣ አቴጌ ጥሩ ወርቅ ሰለ ልዑል አለማየሁ ስትጠየቅ፣ የሰጠችው ቃል፣ አባቱ እንደተመኙለት ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሄድ ነበር። ሌላ የጨመረቸው ነገር ቢኖር፣ ልዑሉ የአማርኛ ቋንቋ እንዳይረሳ፣ አለቃ ዘነብ በአስተማሪነት አብረው እንዲሄዱ ጠይቃ ነበር። ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ አለቃ ዘነብ ከመንገድ ተሰናብተዋል፤ ምክንያቱ ግን አልታወቀም። እኝህ አለቃ ዘነብ፣ የቴዎድሮስ ታሪክ በሚል ፅሁፍ የተውልን ሰው ሳይሆኑ አይቀርም። አፄ ቴዎድሮስ፣ አለማየሁ ብቻ ሳይሆን ትልቁ ልጃቸው መሸሻም እንግሊዝ አገር እንዲሄድ ምኞታቸው ነበር። መሸሻ ግን መቅደላን እንደለቀቀ ወደ አብሮ አደጉ ወደ ምኒልክ ወደ ሸዋ ነው የሄደው። ቴዎድሮስ፣ በመቅደላ፣ አለማየሁን አሰጠርተው ከራሳም ጋር በደንብ እንዲተዋወቅ ማድረጋቸው ተዘግቧል። ለራሳም አደራ መስጠታቸው ነበር። ራሳም ሲገልፅ፣ ትንሹ ልጅ የተደገፍኩትን ትራሰ ሳመ ይላል። ቴዎድሮስ ከነበሯቸው ሰድስት ልጆች፣ ሁለቱ ወደ በጌምድር ሲሄዱ፣ ከሌላ ኦሮሞ ሴት የተወለደው ሀይሉ የሚባለው ከእናቱ ጋር ወደ የጁ ሄደል። የምኒልክ ሚስት የነበረቸው አልጣሽ ደግሞ ለትግሬው ባላባት ለደጃች ባርያው ጳውሎስ ተድራ ነበር።

ቁጥር 162፣ ልዑል አለማየሁ በእንግሊዝ አገር ሲኖር፣ የእናቱ እናት፣ የደጃች ውቤ ሚስት፣ አያቱ የፃፉለትን ደብዳቤ መመልከት በዚያን ጊዜ፣ አፄ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም በህዝቡ ላይ የነበራቸውን አመለካከት ያስረዳል። በዚህ ደብዳቤ ላይ፣ እናትየዋ አቴጌዋን ጥሩነሽ ሲሉ ይታያል። ፀሐፊዎችም ሁለቱን ስም፣ ጥሩነሽንና ጥሩ ወርቅን ሲጠቀሙ ይታያል። አቴጌዋ ሰሚ ጥሩነሽ ሲሆን፣ አፄ ቴዎድሮስ ናቸው ጥሩ ወርቅ የሚለውን መጠሪያ የሰጧት።

ደብዳቤው እንደሚከተለው ነው።

ይህ፡ ቃል፡ ይድረስ፡ ከደጃዝማች አለማየሁ።።
የተላከ፡ ከወይዘሮ፡ ላቃየ፡ ከቴየ፤ ጥሩነሽ እናት፡
እኔም፡ ያለሁ፡ ከናትህ፡ አገር፡ ከዳጃዝማች፡ ውቤ፡ ደብር፡ ነው።።
ልጄ፡ ወዳጄ፡ እጅጉን፡ እንዴት፡ አለህ፡
ከተለየየን፡ ጀምሮ፡ አሰከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡
ምነው፡ ወረቀት፡ አትሰደልኝ፡ በኃዘን፡ በልቅሶ፡ ስሞት፡
ካላንተ፡ በቀር፡ ሊላ፡ ልጅ፡ ሊላ፡ ተሰፋ፡ የለኝም።።

አሁንም፡ ተሎ፡ ወረቀት፡ ሰደድልኝ
መልክህን፡ በሥዕል፡ አድርገህ፡ ዘወትር እንዳየው።፡
ከርስቶስ፡ ሰመናኛት፡ ያብቃን፡ አሜን።፡

ከንግሊዚቱ፡ ንግሥት፡ ከመስኮብ፡ ንጉሥ፡ ከፈረንሳዊ፡ ንጉሥ፡
ከነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ ወዳጅ፡ ሁን፡ ወረቀት፡ ላከ፡
የሀበሻ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እንተን፡ ይጠብቃል፡ ይመኛል፡ ብልህ፡ ሁን፡
ለሀበሻ፡ ሰው፡ ዓይን፡ አውጣለት፡ ዕውር፡ ሁኗል፡
ጥበብ፡ አውጣለት፡ እንዲህ፡ ዕውር፡ እንደሆነ፡ ኢይቅር።፡

በዘመነ፡ ዮሐንስ፡ በጥር...ቀን፡ ተጻፈ

ቁጥር 163፤ የአቴጌ ጥሩ ወርቅ ሁለት ወንድሞች በመቅደላ በእስራት ይኖሩ ነበር፤ ከተለቀቁ በኋላ ራሳቸው ወደ አገራቸው መመለስ ሲፈልጉ አቴጌዋን ማስተዳደር እንደማይችሉ፣ ልዑሉን ደግሞ፣ ለመንገስ ያስበ ሰው ይገለዋል በማለት አናትና ልጁ ከእንግሊዞቹ ጋር እንዲሄዱ ተስማምተው ነው የተለያዩት።፡

ዋቢ መፃሕፍት

(ለግርጌ ማስታወሻዎች)

1. Record of the Expedition to Abyssinia
2. Narrative of A Journey Through Abyssinia In 1862-3 (Henry Dufton)
3. Narrative of 8ritish Mission to Theodor, King of Abyssinia, Hormuzd Rassam
4. የቴዎድሮስ ታሪክ፣ በደብተራ ዘነብ፣ በዶክተር ኢኖ ሊትማን አሳታሚነት፣ በርሊን፣ 1902 ዓም
5. The 8arefoot Emperor (Philip Marsden)
6. The Prince Who Walked with Lions (Eliabeth Liard)
7. አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት በተከለፃድቅ መኩሪያ
8. አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት በተከለፃድቅ መኩሪያ
9. አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት በተከለፃድቅ መኩሪያ
10. አጤ ቴዎድሮስ ከጳውሎስ ኞኞ
11. የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 አስከ 1983፣ ባህሩ ዘውዴ
12. Dairy of a Journey to Abyssinia, 1868, With the expedition under Sir Robert Napier
13. A History of of The Abyssinian Expedition Clements R. Markham
14. http://www.royalark.net/Ethiopia/tewodros.htm Christopher buyers
15. The 8ritish expedition to Abyssinia Henry Montague Hozier, January 1, 1869
16. The Abyssinian Expedition (Roger Acton) with engravings from illustrated London News

መቅደላ!

መቅደላ
አንቺ ለው በላ
ደግሞ እንደ ገደልሽ
እንደ አቀበቱ፣ እንደ ዳገትሽ
ወደላይ እንደሚወጣው
የበላሽው ሽቅብ ቢልሽ ምነው?

አንቺን አምኖ፣ እንቺን ብሎ
መንገዱን ጠርጎ ቢመጣልሽ
ምነው በንዴት መቃጠልሽ::

የተበተነውን በየሥፍራው
ሰፍቶ ላለበለ ለው
ምን ብትሰለቺ ነው
መከለያ የነሳሽው::

አንቺን ያመኑማ፣ አንቺን የወደዱ
አንለይም ብለው፣ በሮኬት ነጎዱ::
አልቆርጥለት ያለው፣ ካንቺ መለየቱ
አንድ ወዳጅ ቢኖርሽ፣ የነበረ ብርቱ
ካንቺው ጋር አደረ በገዛ ብረቱ::

ደግሞ እንደ ለውየው ከፍ ብለሽ
እትታይም ብለው በሳት አደመቁሽ::

መቅደላ! አንቺ ንፉግ፣ አንቺ ስስታም
ለብቻሽ ለትወስጅ፣ ሀፍረት የለሽም
መሬትም እንደለው፣ ለካስ ይቀናል
የወደደውን ለው፣ ይዞ ያሰቀራል::

በዚህ እንኳን ላመስግንሽ
አሳልፈሽ ባለመስጠትሽ::

ገበየሁ ተፈሪ

መዝጊያ

ይኸው እንግዲህ ባንድ ሰው እድሜ፣ ለዘመናት የነበረች ሀገር፣ ብዙ ፈተና የተመላበት ታሪክ አስመዘገበች። ታሪኩ፣ የንጉሡ የቴዎድሮስ፣ አነሳስና ፍፃሜ ቢሆንም፤ በጥሞና ለመረመረው ሰው፣ ታሪኩ በርግጥ የህዝቡ ነው። ህዝቡ በተለያዬ ገፅታው፣ በተለያየ ጊዜ፣ የሚጠበቅና የማይጠበቅ ሥራዎችን ሠራ። እንደ ንጉሡ አርቆ አለማሰቡም ግልፅ ነበር። ባላባቶችና መሳፍንቶችን፣ ልጓም ያልነበረው ሥልጣን ሠጥቶ በላዩ ላይ እንዳልተፈጠረ አድርገው ኖሩበት። ካሳን አስነስቶ፣ ቴዎድሮስ ብሎ አሰይሞ ታሪክ ሠራ። ተመልሶም ለቴዎድሮስ ያላቢቃው ይመስልና፣ በየጎጡና በየግዛቱ የነበረው የባላባት ኑሮ የናፈቀው ይመስል፤ አገር ማለት፣ እሱን በቅርቡ የሚመስሉ ዘመዶቹና ያደገበት ቀዬ ብቻ የመሰለው የሚመስለው ህዝብ፣ በጠባብ ጎዳና በመጨናነቅ ለሰውዬው ፍፃሜ ምክንያት ሆነ። ሊቀይሩት ያሰቡትን ንጉሥ በተገላቢጦሽ የቀየረ ህዝብ ነው።

እዬ ቴዎድሮስ ህዝቡን ያዩበትን አይን የበለጠ በመረዳት፣ ዋናው ጥያቄ መቅረብ ያለበት ለህዝቡ ነው። ለደግም ሆነ ለክፉ የሚንቀሳቀስ ሀይል ሁልጊዜም ቢሆን ጭፍራ አለው። ጭፍራ ደግሞ ከህዝብ ነው። ህዝብ ያነሳል፣ ህዝብ ይጥላል። አንደ ቴዎድሮስ ጊዜ ሁሉ፣ አርቆ ማሰብ ካልተቻለ ድካሙ ብዙ ነው። ሌላው ጥያቄ፣ በህዝብ ደረጃ፣ እኛ ለለኛ ከሚገባው በላይ ራሳችን ክፍ አድርገን እያየን ይሆን? ከሆነ ደግሞ፣ አደጋው ይጨምራል እንጂ አያንሰም።

የማይነቃነቅ ሀይል የነበራቸው የሚመስሉ ብዙ ሀያላን ስርወ መንግስታት፣ ጠንካራ የነበሩ ህዝቦች፣ ታላቅ የሚባሉ ሀገሮች መጥተው ሄደዋል። አሁን ያለንበት አለም፣ ለጊዜው ዘመናዊና ሰላማዊ ቢመስልም፣ ሰው በመሠረታዊ የተፈጥሮ ባህሪው ለራሱ ብቻ ማሰቡ እንግዳ አይሆንም። ስለዚህ በረቀቀ መንገድ ቀለብና ንብረት ለራሱና ለወገኖቹ ለመሰብሰብ በየክፍለ አለሙ የተበተነው ሀይል፣ የጎደለ ሰት፣ ያከማቸውን ነፍጥ ይዞ ደክም ያለውን ላለማጥቃቱ ዋስትና የለም። ይህ እንኳ ለኢትዮጵያ እንግዳ አይሆንም። በአጭሩ፣ ደክመን ከተገኘን በራሳችን ውሀም እናልቃለን። አሁን ከንፈር የሚመጥልን ከሌለ፣ ከዚህ በፊትም ካልነበረ፣ ወደፊትም አይኖርም። እንደ ሀገር ለመኖር አማራጩ ግልፅ ነው። ሰብስብና ጠንክር ማለት ነው። ሰብስብ ማለትና መጠንከር ደግሞ የቴዎድሮስ ነበር።

አሜን

ገበየሁ ተፈሪ



ከዙላ እስከ መቅደላ ከእንግሊዝ ጦር ጋር የተጓዘ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ የዘገበው ታሪክ።
በአፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዋ ሰአት በቦታው የነበረ የአይን ምስክር።
አንድ ጊዜ ተወዳጅ ሀይለኛና ገናና የነበሩትን ንጉሥ የመጨረሻ ምዕራፍ ግልፅና ጥልቅ
በሆነ ሁኔታ ያቀርባል።
ከመቅደላ በፊት የነበሩ ሁኔታዎችን ያስገነዝባል።
መቅደላ እንደዚህ በዝርዝር ቀርቦ አያውቅም።
ስለ አፄ ቴዎድሮስ መነበብ የሚገባው ፅሁፍ።



ISBN 978-0-692-92203-3 $20.00
52000>
9 780692 922033